

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

**“**Ethiopian literary interest in the patriots-and condemnation of – the fascist invasion and occupation- continued after the Ethiopian Revolution of 1974. This later period witnessed the publication of at least four important novels on the subject as well as the production of several significant plays…..The first of these novels Tilahun Tassew’s (Adabai) …. appeared in 1982-3.**”**

Richard Pankhurst: The Ethiopian Patriots, As Depicted in Amharic Literature: Some Introductory Remarks, Part 4, Addis Tribune, Friday April 19, 2002

“In June, 1983, …Seyoum Wolde, Lecturer at the Addis Ababa School of Fine

Arts, asked his junior students to collect some money and every student contributed 50 cents. With that money, Seyoum bought ..two novels (Maebel and Adabai) .

Since the end of the academic year approached, the books were distributed by lot. Melaknesh Atnafu, a 17-year-old, got Maebel and Hailemariam Feleke, aged 22, obtained Adabai.

“After two months, the students produced 60 sketches. Melaknesh read the novel three times and created 25 impressive sketches, while Haile Mariam on his part made 35 sketches after reading the novel four times.

The director of the school is so moved by the sketches that he had decided to exhibit the works in the gallery of the school.”

The Ethiopian Herald, Promising Illustrators, Wednesday 16 November 1983

*“…የጥላሁን ጣሰው ታሪክ ቀመስ ልቦለድ ድርሰት፣ አዳባይ፣ በአምስቱ ዓመት የነፃነት ትግል ወቅት ለተከናወኑ ድርጊቶችና በወቅቱም ለነበሩ ጭብጥ ሁኔታዎች ሳይንሳዊ ትርጓሜ ለመስጠት ጥረት የተደረገበት በመሆኑ ድንቅና መልካም ጅምር የሚያሰኝ ነው። በእኔ አመለካከት ለሌሎችም የታሪክ ጸሐፊዎች የአጻጻፍና የድርጊቶች አተረጓጐም አርአያነት ያለው ነው።”*

*መሠረት ይጥና (መጽሐፍ ግምገማ) ሠርቶ አደር ጋዜጣ ሐሙስ የካቲት* 10ቀን 1975

"የጥላሁን ጣሰው አዲስ መጽሐፍ "አዳባይ" የወረራው ዘመን አካታች አንድ ብርቅዬ መዘከር ይመስለኛል።"

**ልሣነ ዮሐንስ፣ የእናት ኢትዮጵያ "እርመኛ" ባለቅኔዎች፣ አዲስ ዘመን መጋቢት 30 ቀን 1975**

አዳባይ በእውቁ ደራሲ በዳኛቸው ወርቁ "የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ" ላይ አራት ጊዜ ለመጠቀስ የቻለ ድርሰት ነው።

**የሕትመት ታሪክ**
ከፒ ራይት ጥላሁን ጣሰው 1975(1982 እኤአ)
የመጀመሪያ እትም በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት 1975 (1982 እኤአ)

የሽፋን ስዕል ጥበበ ተርፋ።
ድጋሚ በክሬት ስፔስ የአማዞን ኩባንያ በ2007 (2015 እኤአ) በዩናይትድ ስቴትስ ታተመ።

**ISBN 13: 978-1512072808**
**ISBN 10: 151207280x**

ይህን መጽሐፍ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራን፣ ጋዜጠኞችና በአጠቃላይ ማንኛውም ቤተሰብ ለትምህርት ጉዳይ በአንድ ጊዜ እስከ ሃያ ገጽ ድረስ በማንኛዉም ዘዴ በማተም ለመጠቀም ይችላሉ። ለትርፍ ለሆነ ጉዳይ ግን የዚህን መጽሐፍ ከፊልም ሆነ ሙሉ አካል ካለደራሲው ስምምነት መልሶ ማሳተምና ማሰራጨት ክልክል ነዉ።

ደራሲውን በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል፣
tilahuntassew@yahoo.com
ጥላሁን ጣሰው
ፖሳቁ 1110/1033 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ለደራሲው አስተያየታችሁን ብትጽፉለትምስጋናው ከፍ ያለ ነው።

መጽሐፉን ከኢትዮጵያ ውጪ ያላችሁ በኢንተርኔት ከአማዞን ዶት ኮምና ሌሎች አከፋፋዮች ክፍያ በመፈጸም ማዘዝ ትችላላችሁ።

# ማውጫ

ለሁለተኛው እትም መግቢያ ........ 8
መንገድ ........ 10
ክፍል አንድ ........ 16
አዳባይ ሲፈስ ........ 16
ዳኘው ዘለልክ ........ 19
አስካለ ........ 28
ማንም ሰው ከሕሊናውና ከባሕሉ ሸሽቶ አያመልጥም ........ 36
ሩህሩህ እናትም እጇዋን የምታነሣበት ጊዜ አለ ........ 43
አዋቂዎች እንደ አፍላ ወጣቶች ያለሙበት ወቅት ........ 49
ክፍል ሁለት ........ 58
ይደርስ እንደሆነ እስቲ እጃችሁን ወደ ሰማይ ዘርጉት ........ 58
ክብ ሲሰበር ........ 64
ለራሴና ለቤተሰቤ የማደርገውን ለአገሬ እንዳደረኩትአልቆጥረውም ........ 72
ንጉሥ አንጋሽ ........ 78
ሁለት ባቄላዎች ........ 84
የምትፈራውን ነገር እንዳያነሱብህ ከፈለግህ ሲመሻሽ ሄደህ ነገ እመጣለሁ ብለህ ተመለስ ........ 91
ይህንንስ ጠላት አይስማው ........ 96
እንዴ! ........ 101
ጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች ማኅበር ........ 106
ችግርና ጦር ጠብቁኝ ብሎ አይመጣም ........ 111
የጀግና ቀብሩ በፉካሮ በቀረርቶ በሆታ ነው ........ 116
ችግር ብቻውን አይመጣም ........ 125
ክፍል ሦስት ........ 131

ዝንጀሮና አርበኛ ገደሉን አይለቅም ........ 131

አስካለ መጣች ........ 137

የጠላት ዕርቅ ........ 141

ጌታዬ ሰው ውሃ ይጠጣ እኛ በዚህ በኩል እንለፍ ........ 152

የዱር ፍሬ የሚበላው ጦር ........ 158

አንድ ሌሊት በሁለት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ........ 161

ጋብቻ ........ 166

ጣሊያንና ሥልጣኔ ........ 170

እንቁላል የምትወደው ጣሊያን ........ 178

ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ ........ 182

የዳኘው ማኅበር ........ 187

ክፍል አራት ........ 193

ውሃ ዋናም ቸር ወሬ ያሰማል ........ 193

ደህና ሰንብች ዳኘው ........ 196

ጀግና ፀጉሩን ሲላጭ ........ 200

አይጣልን ነው ማውራት ........ 205

የመጀመሪያው መጨረሻ ........ 210

የሁለተኛው መጀመሪያ ነው ........ 210

ሁለት ያጣ ........ 215

የመጀመሪያው እትም መቅድም ........ 221

አባሪዎች፣ የአርበኞች ደብዳቤዎችና ካርቱኖች ........ 224

# ምስጋናና ውዳሴ

1. የሽፋን ስዕል በታላቁ ሰዓሊና ኢሉስትሬተር ጥበበ ተርፉ ነው። ለመጀመሪያው እትም የሠራውን የሽፋን ስዕል ለዚህ እትም እንድጠቀምበት ስጠይቀው ይበልጥ አሻሽሎ ስለፈቀደልኝ ምሥጋናዬ ከፍ ያለ ነው። ፈጣሪ ይበልጥ ያግዝፍልኝ።
2. ለጌታቸው ወንድማገኘሁና ባለቤቱ ምሥራቅ አላክሳንደር እንዲሁም ለመስፍን ተመስገን። የዘወትር አለኝታዬ ናችሁና ፈጣሪ ረዥም ዕድሜና ጤና ይስጣችሁ።
3. አሁንም የመጽሐፉ ማስታወሻነት ለውድ ወንድሞቼ ለገዛኸኝ ደጀኔና ለተስፋዬ ኃይለ ሚካኤል ነው። እንኳን ከረዥም ዘመን በኋላ በዓይነ ሥጋ ለመተያየት ያበቃን።

# ለሁለተኛው እትም መግቢያ

በዚህ ሁለተኛ እትም ትረካውን ለማዋዛትና በመጀመሪያ እትም መግቢያ እንደተጠቀሰው ትረካው ከምርምርና ጥናት ጋር የተዛመደ ነው የተባለውን ለማርገጥ ታስቦ የግርጌ ማስታወሻዎች፣ አርበኞች የተጻጻፉዋቸው አንዳንድ ደብዳቤ ቅጅዎችና በዘመኑ ጋዜጦች ላይ የወጡ ካርቱኖች በአባሪነት ተካተዋል። ለታሪክ ተመራማሪዎች ይረዳሉ። ከዚህ በተረፈ ማውጫውና የመጀመሪያው እትም መግቢያዎች ወደ መጨረሻ ከመወሰዳቸው በቀር ትረካው በ1975 እንደተጻፈው ሳይለውጥ የቀረበ ነው።

ውድ አንባቢዎቼ፣ የዛሬ 79 ዓመት እንዲህ ሆነ።

በ1928 በተንቤን ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ተኩሱን፣ ፈንጅውን፣ የመስተርድና ፎሰጂን ጋዝ የኬሚካል ጦርነትን ተቋቁሞ የጣሊያንን ጦር ድል አደረገ። ብዙ ሺ የኤርትራ ተወላጅ የኢጣሊያ ወታደሮች፣ ጣሊያንን ከድተው፣ ወንድሞቻቸውን ተደባለቁ። ድል አድራጊው የኢትዮጵያ ጦር መቀሌን አስለቅቆ ኤርትራን ነጻ ለማውጣት ተንቀሳቀሰ። በዚያን ጊዜ ከመስታርድና ፎስጅን ጋዝ የተለየና እስካሁን እንኳን የመርዙ ምንነት ያልታወቀ የመርዝ ፈሳሽ በመጠቀም ኢጣሊያ አሸነፈች።

ትንሽ ቆይቶ የማይጨው ጦርነት እንደ ማግስቱ ሊደረግ በተደረገ ስብሰባ፣ የተወሰኑ ራሶችና ደጃዝማቾች የጦር ሰፈራቸውን ገጠር አድርገው የአርበኝነት ወጊያ እንዲቀጥሉ፣ የተወሰኑ መኳንንት ለጣሊያን እንደገቡ ሆነው አርበኞቹን እንዲረዱ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ መንግሥታቱ ድርጅት ለአቤቱታ እንዲሄዱ ተወስኖ የማይጨው ጦርነት ተካሄደ። የአርበኝነት ዉጊያው አዋጅ ሚያዚያ 5 ቀን 1928 ላስታ ጥላሰፈሬ እንዲህ ተብሎ

ቀኃሥ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ገጽ 255 ላይ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ባደረጉት ንግግር እንዲህ ይላሉ፣''የኢጣሊያ የጦር ጠቅላይ ሹም መቀሌን የኢትዮጵያ ወታደሮች በከበቡ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት መፈታቱን ስለ ተረዳውና ስለ ሥጋ ሌላ ዓይነት የኤፐሪት አጣጣል አደረገ።''

ታወጀ፣ ጠላት “ባገርህ ሲገባ የምትችል ባለ አቅምህ በሰፈረበትና በሚጓዝበት ላይ አደጋ እየጣልህ ባገርህ ላይ እየተዘዋወርህ አገር ምድርህ እንዳይደፈር ተዋጋ።”[1] ይህ ውሳኔ ንጉሠ ነገሥቱ ከማይጨው አዲስ አበባ ሲገቡም ተመክሮበታል።

[1] *ቀኃሥ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ገጽ 241*

ከላይ በተደረገው ውሳኔ መሠረት የሸዋን አርበኝነት ውጊያን እንዲያስተባብሩ የተመደቡት ሽማግሌው ራስ ከበደ ነበሩ። እሳቸው ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ሰላድንጋይ ከተማ በጣሊያኖች እስክትይዝ ጦርነቱን ሲመሩ ቆይተው ትግሉ ወደ ሽምቅ ውጊያ ሲለወጥ እጃቸውን ሰጥተው ወደ ውስጥ አርበኝነት ሲገቡ የዘመኑ ወጣቶች የአርበኝነት ጦርነቱን ቀጠሉ።[2] በ1975 ደግሞ እኔ ያንን ዘመንና የወጣቶቹን ውሎ በዚህ መጽሐፍ ተረኩት። በታሪክ ላይ የተመሠረቱ የትረካ መጽሐፎች ስለ አንድ ያለፈ ዘመን ቢሆኑም ያለፈውም፣ ያሁኑም፣ የመጭውም ዘመን ይታይባቸዋል፣ ይዳሰስባቸዋል። ይህንን መጽሐፍ አንብባችሁ ስትጨርሱ ይህንን በደንብ እንደምትረዱት አምናለሁ።

መልካም ንባብ።

[2] በራስ ከበደ አስተባባሪነት የተደረገውን ሰላድንጋይ ከተማን ያለማስያዝ የአርበኝነት ተጋድሎ ደራሲው ለእንግሊዘኛ ተናጋሪ ትውልደ ኢትዮጵያውያን Trying Times በሚል ርዕስ መጽሐፉ ተረኮታል።

# መንገድ

ከነጻነት በኋላ በአሥራ ስድስተኛው ዓመት አስካለ አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ እስከነቅጠሉ በቤቱዋ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ጣለችና የአለፈ ሕይወቱዋን መለስ ብላ ተመለተከችው።

ማርሻል ቲቶ በኢትዮጵያ የይፋ ጉብኝት ያደርጋሉ ተብሎ ከተወራ በኋላ በከተማው ውስጥ ያሉ ደሳሳ ጎጆዎች ለዓይን እንዳይቀፉ፣ አካባቢው ጫካ እንዲመስል፣እርጥብ የዛፍ ቅጠል እንዲለብሱ፣ ሻል ያሉ የቆርቆሮ ቤቶችም ቀለም እየተቀቡ እንዲታደሱ ታዞ ስለነበር፣ የአስካለ መኖሪያም ሳር ቤት ስለሆነ፣ የዛፍ መልበስ ተፈርዶበት፣ አስካለም ይህንኑ ሥራ እያከናወነች ነበር። የዚያን ሰሞን ይህ ዓይነቱ ትዕዛዝ ሲመጣ ያስደነቃት ቢሆንም አላናደዳትም ነበር። ዛሬ ግን ይህ የማያስፈልግ ችግር ከጎተተቻቸው የዛፍ ቅርንጫፎች ይበልጥ ከበዳት።

"ከከተማው ይልቅ ጫካ ይሻላል ማለት ነው?" ስትል በቁጭት አሰበች። "ጣሊያን ከወጣ አሥራ ስድስት ዓመቱ ነው። ፈረንጅ እንደሆነ ውስጣችንን ሁሉ ያውቀዋል። ስንት ፈረንጅ በአገራችን ይኖር የለም? ምን ምስጢር አለንና ነው ዛሬ ዛፍ እየቆረጥን በራሳችን አገር ራሳችንን የምንደብቀው?" አለች ከቤቱዋ ገብታ መደቡ ላይ እየተቀመጠች። ከዚያም ትንፋሹዋ መለስ ሲል እጆቹዋን ወደ ላይ ዘርግታ ተንጠራርታ ተመቻችታ ቁጭ አለችና "አይ ልክ ናቸው፣" አለች ምሬቱዋን አዲስ በአእምሮዋ የተፈጠረው ሃሣብ ሥራዋን ጨርሳ ከማረፉዋ ጋር ተደባልቆ አቀዝቅዞዋት። "እኛም ድሃዎቹ ከቤታችን እንግዳ ሲመጣ ገበናችንን ለመሸፈን የሌለንን ያለን መስለን እንቀርባለን። ንጉሦቹም እንደዚህ ማድረጋቸው ነው ።" ስትል አሰበች። ቸኩላ ቅር በመሰኘቱዋ ራሱዋን ታዘበችው። በሕይወቱዋ ውስጥ ካለማጤን ሰውን ካለ ሥራው የሚሰጡ ብዙ ሰዎች ታውቃለች። "ሰውን ሥራውን ካልተረዱለት፣ ነገሩን በቅንነት ካልተመለከቱለት መልካም ሃሳቡን የሰይጣን፣ መልካም ምግባሩን መጥፎ አድርጎ ማየቱና ማሳየቱ አይቸግርም።" አለች። አንድ ጊዜ ስለሱዋና ስለ ባለቤትዋ፣ ስለ ዳኘው፣ የልጅነት ባሉዋ በጋሻው፣ ጣሊያን እንደወጣ አሥራት ሊከፍል ከቤታቸው መጥቶ ያላትን ታስታውሳለች። በጋሻው ዳኘውን በስም እንጂ በዓይነ ሥጋ አያውቀውም ነበር። ከሰው ስለ ዳኘው በሰማው ወሬ ግን የሰይጣን ቁራጭ አድርጎ ይገምተው ነበር።

ጣሊያን እንደወጣ ዳኘው የመንግሥት አሥራት ሰብሳቢ ሆኖ በጋሻው አሥራቱን ለመክፈል እህሉን በአህያ ጭኖ ይመጣል። (የዚያን ጊዜ አሥራት በዓይነት እንጂ በገንዘብ አይሰበሰብም ነበር ።) በጋሻው አስካለን ከውጭ ያገኛትና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እንደ መሸሽ ይላታል። አስካለ ጠባዩ ሁሉ አልገባትም። የልጅነት ዘመኑዋ ትዝ ብሏት ባደረገው ነገር ሳትከፋ ቆይታ ወደ ቤት ሲገባ ለዳኘው ከብዙ ሰዎች መሃል በጣቱዋ አመልክታ "ልጄ በጋሻው የምልህ ያ ነው ።" ብላ አስተዋወቀችው። በጋሻው መልኩ አመድ ሲመስል ተመለከተች። ነገሩ ስላልገባት ተወት አደረገችው። የበጋሻው ተራ ደርሶ አሥራቱ ሲሰፈር፣

ዳኘው ወጣ ብሎ ነበርና፣ በጋሻው ከአሥራቱ ሁለት ቁና ስንዴ ስለተረፈው ሳቅ ብሎ "አስካለ ይህ ለልጅሽ ክርስትና ይሁንሽ፣" ብሎ ስልቻውን አመለከታት።

የከሱ ክንዶቹን ዓይታ ቀና ብላ ፊቱን ተመለከተች። የአምስቱ ዓመት ጦርነት በባላገሩ ሕዝብ ላይ በኢኮኖሚው በኩል ያደረሰበት ችግር፣ በመንፈሱ ላይ ያስከተለው ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ጥርጣሬ ሁሉ በዓይኑ ላይ፣ በግንባሩ ላይ ታያት። ስጦታህን አልቀበልም ችግረኛ ነህ፣ እኛ እንሻላለን ማለቱ ደግሞ ይበልጥ እንደሚያስከፋው ተረዳችው። ሌላ ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ልትረዳው እንደምትችል አስባ በደስታ፣ በፈገግታ ተቀበለችው። ከዳኘው የመጀመሪያ ልጁዋን በመውለዱዋ ደስ በመሰኘቱ፣ በሌላም አንፃር ቀደም ሲል ባሳየው ጠባዩ የተከፋ መስሎዋት ነበርና፣ ከልቡ የተቀየመበት ነገር እንደሌለ በማየቱዋ ደስ አላት።

ዳኘው ከውጭ ወደ ቤት ሲመለስ አስካለ የበጋሻውን ውለታ ላለማስቀረት ለዳኘው ስለ ሁለቱ ቁና ስንዴ ነገረችው። በጋሻው እንደገና ደነገጠ። ዳኘው ግን በጣም አመሰገነው።

በጋሻው ወደ ሰፈር ለመመለስ ሲነሳ አስካለ ልትሸኘው እንደወጣች፣ በአካባቢው ሰው አለመኖሩን ተመልክቶ፣ "አስካለ ምን ማለትሽ ነው? እኔና አንቺ በወንድምነት ብንተያይም ሰው ሊጠረጥር ይችላል።" አላት። ዳኘው በማለት ፋንታ ሰው ብሎ።

"ሰው የማያስበውን ማሰብ፣ ወይም እንዲህ ይባል ይሆናል ማለት፣ የጀግና፣ የጎበዝ ጠባይ አይደለም።" አለችው።

ትንሽ ዝም ብለው እንደ ቆዩ "ለመሆኑ ዳኘውን ምን አርገህ ትገምተዋለህ?" አለችው። ዳኘው እንዳልበደለው ስለምታውቅ የዳኘው ጠላቶች በውሸት የሚያስወሩበትን አምኑዋል ብላ ጠርጥራለች።

"አውሬ ነው የሚመስለኝ።" አለ። ንገረኝ ካልሺኝ እውነቱን ልንገርሽ ለማለት ትከሻውን ወደ ላይ ገፋ አድርጎ።

"ለምንድነው አውሬ አድርገህ የምትገምተው?" አለችው አስካለ በመገረምም በቅሬታም።

"አርበኞች መልካቸው አውሬ ከመምሰሉም ሌላ ጨካኞች ናቸው።" አለ በጋሻው ከአስከለ ፊት ላይ ቅሬታ በማየቱ በግል ዳኘውን መጥላቱ እንዳልሆነ ለማሳየት አስተያየቱን ስለ አጠቃላይ አርበኞች አድርጎ።

"ጠላትን ጠላት አድርገህ ካልወሰድከው እንዴት ትዋጋዋለህ? ጭካኔ ይህ ነው?" አለችው። ከጥያቄም ይልቅ ትዝብት ነበር።

"እኔ ምን አውቄ ተዋጊ አይደለሁም።" አለ። ይህን ነገር ተከራክሮ የሚረታበት እንዳልሆነ ያውቀዋል።

"እኔም አርበኛ ነኝ። አውሬ አድርገህ ትቆጥረኛለህ?" አለችው በመገረም።

“አልገምትሽም። ሕፃን ሆነሽ እንኳን ከአጠገቤ ካለሽ ችግር ቢደርስብኝ ከእናቴም ቀድመሽ የምትደርሽልኝ አድርጌ እገምት ነበር።” አላት የቃሉ ቅላጽና መላ ሰውነቱ ከልቡ እንደሚናገር በግልጽ እያመለከተ።

“ዳኘውን ትፈራዋለህ?” አለች አስካለ አሁንም ተከዛ። ዳኘው በሱ ላይ ክፋት ሳያስብ እሱ የጠላው ከፍራቻ ይሆናል ብላ በመጠርጠር።

“አዎን።” አለ አሁንም የምሩን መሆኑን ለማሳየት ፈገግ ሳይል። አስካለ የልቡን ብታውቅ በአሁኑ ጊዜ አይጨነቅበትም።

አሁንም መልሳ “ለምን?” አለችው። ከንብዋሻ መንደር አፋፍ ወደ ታች ቁልቁል አዳባይ ወንዝን ተመልክቶ ከዚያም እንደገና ዐይኑን አቅንቶ ከአፋፉ ላይ ተከሎ “ባልሽ አንቺን ከማግባቱ በፊት ከዚያ ከአፋፉ ጦርነት ገጥሞ፣ እልህ ይዞት፣ ከንዴቱ ብዛት ከተኛበት መትረየሱን ይዞ ቆሞ ጠላትን ረፍርፎት ወደ ኋላው ያስፈገፈገበት ነው አሉ። ጥይት አይነካውም የተባለው ከዚያ ወዲያ ነው ይላሉ።” አላት።

“በዚህ ዓይነት ወሬ ነው አራዊት የሚመስልህ?” አለች እሱዋ ጀግንነት የምትለውን እሱ አውሬነት ሲያስመስለው አስተሳሰቡ ግራ አጋብቱዋት።

“እንኳን መሣሪያ የታቀፈ ቀርቶ ድንጋይስ ይዞ በነፍሱ የቆረጠ ሰው አያስፈራም?” አለ ቢጋሻው ያለችውን ነገር በደንብ ሳያጤነው።

አስካለ ከት ብላ ሳቀች።

“ምን ያስቅሻል?” አላት የሆዱን ሲያጫውታት በመሳቁዋ ያሾፈችበት መስሎት በመከፋት።

“ድንጋይ የያዘ እብድ ሰው ሰዎች ሲያዩ የሚሸሹትና የሚረበሹት ትዝ ብሎኝ ነው።” አለች አስካለ ፈገግ ብላ።

“ያለበደም ሰው በነፍሱ ከቆረጠ ያው ነው።” አለ ቢጋሻው አሰካለ እንዳለፌዘችበት ገብቶት ቅጭም ያለ ፊቱ ፈካ ብሎ።

“ለመሆኑ እኔን ትፈራኛለህ?” አለችው የቀልድ ያለመሆኑን ግልጽ ለማድረግ አትኩራ እየተመለከተችው። የዳኘውና የሱዋ ሕይወት ተቆራኝቱዋል።

“አልፈራሽም። ስትቆጭ ግን እንኳን እኔ ወታደሮችሽም ይደነግጣሉ አሉ። አንቺን መፍራትና ዳኘውን መፍራት ግን ሌላ ነው።” አለ ስትቀልጂ ካልሆነ መች አጣሽው ለማለት ፈገግ ብሎ እየተመለከታት።

“ከምኑ ላይ ይለያያል?” አለችው ዛሬ የልቡን አውጥቶ በመናገሩና ያስለፍልፍ የበላ ይመስል በመቀባጠሩ ተደንቃ። አብረው በነበሩበት ዘመን እንዲህ ተናግሮ አያውቅም።

“ዳኘውና ነበር አንድ ናቸው። ነብር ከተቆጣ ሳያጠፋሽ አይመለስም። እረኞች ዋሽንት ሲጫወቱ ነብር ከመጣባቸው እንዳይቆጣ ለማድረግ ዋሽንቱን ሲነፉ ልባቸው ትፈነዳለች ይላሉ። አንቺ ግን እንደ እናት ነሽ። እናትሽ ተቆጥታሽ ቁጣዋ ያስፈራሽ ከመሰላት ወዲያው እንድትረሺው፣ በድንጋጤ ከበሽታ ላይ እንዳትወድቂ፣ የማባባያ ዘዴ ስለምትፈጥር፣ ዓላማዋ ውሱን መሆኑን ታውቂያለሽ።” አለ አሁንም መች አጣሽው ለማለት አንገቱን ወደ ጎን ሰበር አድርጎ ፈገግ እንዳለ።

“ዳኘው አንተ እንደምታስበው አይደለም። ቅድም ከሱ ፊት ስትጨነቅ፣ ሲከፋህ የነበረው ራስህ በፈጠርከው ሃሣብ እንጂ በሱ ጠባይ አይደለም።” አለችው። መልስ እንዲሰጣት የተናገረችው አልነበረም።

በጋሻው ግን ዳኘውን እሱ ከሚያስበው ውጭ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ጊዜ ፈጀበት። አዋቂም ሰው እንደ ትንሽ ልጅ አንድን ነገር ለመማር ብዙ ጊዜ ሰምቶት፣ ተነግሮት፣ ተመልክቶት አንድ ባልተጠበቀ ቀን ከሕይወቱ ጋር ተገናዝቦ ማግኘት አለበት።

አስካለ በትዝታ ተውጣ ሳታስበው ብዙ ጊዜ አለፈ። ሕይወት ተግባርና ግዴታ ስለሆነ እንደፈለጉ ለማሰብ፣ ለመመራመር በቂ ጊዜ አይሰጥም። አስካለም ለምሣ የሚሆን ክክ መግዛት እንዳለባት ትዝ ብሏት ልጁዋን አዘለችና ፈጥና ከቤት ወጣች። የጎረቤቱዋን ሰዎች እንኳን “ቤቱን እያያችሁልኝ፣” ብላ ከተናገረች በኋላ መስማታቸውን ለማረጋገጥ ዘወር አላለችም።

አስካለ ከቤትዋ ተመልሳ ከምድጃው ዳር ቁጭ ብላ እሳቱን እየቆሰቆሰች ዘወር ብላ ልጁዋን ማጫወት ቀጠለች። ልጁዋ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ይገርማታል። የትኛውስ ወላጅ እራሱ በልጅነቱ ሳለ እንደ አሁን ልጅ ወሬ ያወራ፣ ከእድሜው በላይ የሠራ፣ እንደ አዋቂ ያሰበ ይመስለዋል?

አስካለ ልጁዋ አንድ ጊዜ የሠራው ትዝ ብሏት ፈገግ አለች። ያለፈው ዓመት አያቱዋን ልትቀበል አውቶቡስ ተራ ሄዳ አያትዋን ስትስም ልጁዋንም ታቅፋው ስለነበር “ጎረምሳ ትታቀፊያለሽ በእግሩ አይሄድም።” ሲሉ ተቆጡ ። ሕፃኑም ቂም ይዞ ስለነበር ልሳምህ ቢሉት እንቢ ብሎ በግድ ከተሳመም በኋላ ጉንጮቹን በጥብቆው መጥረግ ያዘ።

ወደ ቤት ደርሰው ለአስካለ አያት ለእመት ድንቅነሽ ሳሩ ተጎዝጉዞ ከዚያ በላይ ፍራሽ፣ ከጎን መደገፊያ ተመቻችቶላቸው ቁጭ እንዳሉ የጎረቤት ሰዎች እየመጡ እጅ ይነሱአቸው ጀመር። የዚያን ጊዜ በሠፈሩ የአስካለ ቤተ ዘመዶች ይበዙ ስለነበር አዋቂውም ልጁም እመት ድንቅነሽን ለማየት ይመጣ ነበር። ልጆች እየመጡ እግራቸውን ሲስሙ ያስተውሉና የጠፉዋቸውን የማን ልጆች እንደሆኑ ጠይቀው ይስሙዋቸዋል ወይም ጉልበታቸውን ሊስሙ ሲሉ ቀና አድርገው የሚስሙዋቸው፣ ሌሎችም ጫማቸውን ከሳሙ በኋላ ስመው ወይም ሳይስሙ የሚተዋቸው አሉ።

ከፊት ለፊታቸው የነበረው ቢሳምም አንዳንዶቹ ጫማ ወይም ጉልበት ከሳሙ በኋላ የጉንጫቸውን መሳም ሳይጠብቁ ወደ ኋላ አፈግፍገው የሚርቁ አሉ። ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹን እንደገና በመጥራት የሚስሙዋቸው አሉ። ልጆች ግን ይህን ትህትና አያውቁም። ጫማ ሳም! ጫማ ሳም! ተብለው ጫማ ከሳሙ በኋላ ቀድሞዋቸው ከፊት የነበረው ከተሳመ ሁሉም ለመሳም ይጠጋሉ። የዚህን ጊዜ በአካባቢያቸው ያሉት ሰዎች መሳም ሳይገባው ተጠግቶ የቆመውን "እላያቸው ላይ ሊወጣ ነው? አትሄድም፣" ብለው ይመልሱታል።

የአሰካለ አያት የአጎታቸውን ልጅ ስመው የወተቴን ልጅ ሲተውት የወተቴ ልጅ የአስካለ ጓደኛው ስለነበር "አንተን ይስጠኝን ሳሚው፣" አላቸው።

"ባለጌ፣ ከዚህ ዘወር አትልም፣" ሲሉ በክፉ ዓይን ተመለከቱት። ዙሪያውን የነበሩት ሰዎችም "ዘወር አትልም፣ ከትልቅ ሰው ጨዋታ መሃል ይገባል።" ሲሉ አዋከቡት። እሱም እናቱን ጭምድድ አድረጎ ይዞ ከጉልበትዋ ላይ ተደፍቶ ማልቀስ ቀጠለ።

"አስካለ ልጅሽን ከሰው መሃል ይዘሽ አትግቢ። ልጅ ሰው በክፉ ዓይን ካየው መጥፎ ነው። ውቃቢ ያርፍበታል።" የሚል ምክር ከጎኑዋ ሲሰነዘርላት ልጁዋ ቀና ብሎ "እማማ ሸንኮራ አገዳ ትስመው የለ። ይች ካካ ናት።" አለ።

እማማ ሸንኮራ አገዳ የሚላቸው በአባቱ በኩል ሴት ቅድመአያቱን ነው። ከአገር ቤት ሲመጡ ሸንኮራ ይዘው ስለሚመጡ ይህን በማየት ይህን ቅጽል ሥም ሰጥቶአቸዋል። እኝህኛዋ ቅድመአያቱ አለባበሳቸው አዳፋ ሲሆን እጅና እግሮቻቸውም የሻከሩ ነበሩ። ከቤት መጥተው ብዙም ሳይቆዩ ማድ ቤት ይገቡና ሴቶቹን ሥራ ያግዛሉ። የቤቱ ሥርዓት አይለወጥም። እግራቸውን የሚስም፣ አጀብ አጀብ የሚያደርጋቸው አይኖርም።

"ምናለ እምዬ ቢስሙት ኑሮ፣" ብላ አስካለ ከትዝታ ባሕር ስትወጣ የሱዋን አያትና የዳኘውን አያት አወዳድራ ታዘበችና ልጁዋን ተመልክታ፣ የዚያን ጊዜ ያለቀሰው ትዝ ብሏት፣ እንደገና አቅፋ ሳመችው። "ካካ! ካ.ካ" አለችው እየሳቀች፣ አተኩራ እየተመለከተችው። ቅድመአያቱን ካካ! ካካ! የሚላቸውን ያስታውስ እንደሆነ ለማየት። ከዚያም አለማስታወሱን አይታ ሥራዋን ለመቀጠል "አንተን ይስጠኝ ዘንድ ሄደህ ተጫወት የኔ ጎበዝ፣ ጎሽ፣" አለችው።

አስካለ ብቻዋን ስትቀር ትዝታ ይዞዋት አዳባይ ወንዝ ወረደ። በልጅነትዋ ለቁጥር ለበዛ ጊዜ ከንብዋሻ መንደር አፋፍ ቁልቁል ከሦስት ኪሎ ሜትር በታች እየተመለከተችው ልቡዋን የሚያሞቀውን አዳባይን ዛሬ በዓይነ ህሊናዋ ብዙ መቶ ኪሎሜትር ከቦታው እርቃ፣ ዓይኑዋ ከምድጃው ላይ ተተክሎ፣ ተመለከተችው። ይኸኛው ግን ናፍቆት ነው። የቀድሞው ግን የወጣትነት ነፀብራቅ ነበር።

ሰው እነደ ዘመኑ እነደ ልበ ሙሉነቱ በአንድ ነገር ላይ የተለያየ ነገር ያያል። የተለያየ ስሜት ይሰማዋል። አስካለ በልጅነቱዋ አዳባይን ስትመለከተው፣ በአርበኝነት ዘመን

ወታደሮቹዋን አስከትላ ስትመለከተው፣ አሁን ነጠላዋን በአቅመቢስነት፣ በዓይነ ሕሊና ስትመለከተው የተለያየ ሆነባት።

ፍዝዝ ብላ ተቀምጣ እንዲህ ስታሰላስል ዳኘው ከቤት ሲገባ

እንኳን ልብ አላለችም። ልብ ካላየ፣ ልብ ካልሰማ ዓይን አያይም፣ ጆሮ አይሰማም።

"ምን ታስቢያለሽ?" አላት። ቀደም ባለው ጊዜ ልጄ እያለች

ስለምትጠራው እሱም እናቴ ብሎ ይጠራታል። ዛሬ ግን የሚናገረውንም በደንብ አያስተውለው። ዝም ስትለው እነደመናደድ ብሎ "ወየው ጉድ ምን ሆነሻል!" አለ

ሆድ እንደ ባሰው ልጅ ቆጣ ብሎ።

"ምን?" አለች ደንግጣ። "መቼ መጣህ ልጄ?"

"ምን ታስቢ ነበር?" አለ ቀድማው መርዶውን ሰምታለች ብሎ በመጠርጠር።

"እስከ ዛሬ ያሳለፍኩትን ሕይወት።" አለች አስካለ ሊነገር የሚገባው መሆን አለመሆኑን በደንብ ስላላወቀች በቅሬታ ፈገግ ብላ።

"አረጀሽ ማለት ነው። ሰው ሲያረጅ ወደ ፊት መመልከቱን፣ መመኘቱን ትቶ ወደ ኋላ ይመለከታል። ለወደፊቱ ለነፍሱ እንኳን ሲያስብ ያለፈውን እያስታወሰ በመፀፀት ንስሃ እየገባ ነው።" አለና እሱም ተከዘ።

"ምነው ተከዝክ?" አለችው። ከሁኔታው ልብ የሚሰብር ነገር እንዳጋጠመው ጠርጥራ። ቀደም ሲል ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰው ሃሳብ አደንዝዞዋት በደንብ አላስተዋለችውም ነበር።

"ከሥራየ መሰናበቴ ሲገርመኝ ባሮ ሁዳድን ተነቀልኩ።" አላትና ዓይኖቹ ወደ መሬት አቀረቀሩ።

አስካለም መሸነፉን አውቃ፣ ወኔውን መቀስቀስም ጥቅም እነደሌለው አውቃ፣ እሱዋም እንባዋ መጥቶ አቀረቀረች። ዳኘውም አስካለን ስላለፈ ሕይወት ስለማሰብ የመከራትን ረስቶ፣ ወደፊት ማለሙን ትቶ፣ ወደ ኋላ ሄዶ ሕይወቱን እንደ ሸማግሌ መመርመር ጀመረ።

⅄ ⅄ ⅄

# ክፍል አንድ

## አዳባይ ሲፈስ

እያንዳንዱ ወንዝ የራሱ የሆነ እጽዋት፣ እንስሳት፣ የሰው ልጅ ማህበረሰብና ታሪክ አለው። እያንዳንዱም ቤተሰብ የራሱ ወንዝ አለው።

የሞፈር ውሀ ወንዝ ወደ ምዕራብ ሰሜን እየተጠማዘዘ፣ በመጨረሻ ከሌሎች አምስት ዥረቶች ጋር የዳኘው የትውልድ መንደር አቅራቢያ ይደባለቅና ስሙን ቀይሮ አዳባይ ተብሎ ይጠራል። አዳባይ ደግሞ እየራቀ ሲሄድ ዠማ ይባላል። ከዚያም ከአባይ ወንዝ ይደባለቃል።

የዳኘውን የትውልድ መንደር አገረ መርፌያንና፣ አስካለ ያደገችበትን ንብዋሻ መንደርን፣ የተወለደችበት ገረገራ መንዝን፣ ከንብዋሻ መንደር አፋፍ ላይ ቆሞ፣ ተጉለትና መንዝን እያነፃፀሩ፣ ቁልቁልና አግድም መመልከት ይቻላል። መንዝና ተጉለትን ለሁለት ከፍሎ ከትልቅ ሸለቆ ስር አዳባይ ለጥ ብሎ ይታያል።

ከአንድ ኪሎሜትር በላይ ቁልቁል እንደ ደረጃ እየሆኑ ከሚወርዱ መንደሮች በታች፣ በሁለት አፍ ሸለቆዎች ሥር፣ በግርማ ሞገሱ አዳባይ ተኝቷል። ወዴት እንደሚፈስ እንኳን አያስታውቅም። አይተውት የማያውቁት የሚመጣበትን አቅጣጫ የሚፈስበት አቅጣጫ አድርገው ይገምቱታል። ከግራ ከቀኙ የቆሙት ጥርብ ገደሎች ቅርጽ ይህን ማሳሳት ይፈጥራሉ። ሁለት እኩል የሆኑ መስመሮች ዳርና ዳርቻቸው አንደኛው ወደ ውስጥ በታጠፉ ጦሮች ሁለተኛው ወደ ውጭ በታጠፉ ጦሮች ሲታጠሩ አንደኛው ረጅም ሌላው አጭር እንደሚመስሉት ሁሉ አቃፊዎቹ ገደሎችም የወንዙን አፈሳሰስ አቅጣጫ ያሳስታሉ።

በጡዋቱ ቀዝቃዛ አየር ደርበብ ያለው ሰማይ፣ ቀን ላይ ሩቅና ጥልቅ መስሎ ጭር ይላል። ወደ ማታው ላይ ስስ ጉም ዙሪያውን በሸፈነው ሰማይ፣ ፀሐይ በምዕራብ በኩል ውሀ አዘሉ አየር እንደ መስተዋት አሳድጓት ትልቅና ቀይ ሆና ቅርብ ካለው ተራራ ባሻገር፣ ከአድማስ፣ ታቆለቁላለች። እንደ ችግኝ እድገት ተመንደጋ እንጂ ስትፋፋ የማትታየው ጨረቃ ዙሪያዋን በቀስተ ደመና ብርሃን ተከባ ከምሥራቅ ካለው ተራራ በላይ ብቅ ትላለች። መሬት ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ስትዞር ፀሐይ እየጠፋች ጨረቃ ደግሞ ከምሥራቅ አድማስ እየተጓዘች ፀሐይን ተከትላ ከምዕራብ ካለው ተራራ በውድቀት ሌሊት ለመጥፋት ጉዞዋን ትቀጥላለች።

እንደ ደረጃ እየሆኑ፣ የመኖሪያና የርሻ መስኮች እየሠሩ፣ ለብዙ ኪሎሜትር ወደ ታች በግራና በቀኝ ከሚሽቆለቆሉት ተራራዎች መሃል፣ በወርዱ ከኪሎሜትር በላይ በሚሆን ለጥ ያለ ሜዳ መሬት ላይ፣ አምስት ጅረቶች ተደባልው ያስገኙት የአዳባይ ወንዝ፣ የረጋ በሚመስል ዝግተኛነት ወደ ደቡብ ይጓዛል። ቁልቁለቶቹ ላይ ሲደርስ ኃየለኛ ፏፏቴ

እየሠራ፣ እየተጠማዘዘ፣ ከአባይ ወንዝ ይገባል። አባይም ከሜዲትራኒያን ባሕር ይገባል። እያንዳንዱዋ ጠብታ ባትሆንም፣ ውሀዎች ሁሉ፣ ወደ ውቅያኖስ እናታቸው ይመለሳሉ።

አዳባይ ለመንዝና አካባቢዋ ሕዝቦች ብዙ ትዝታ ያመጣባቸዋል። አዳባይ ለጠላቶቻቸው የማይመች ተገናቸው፣ የከፋው የሚሰደድበት በረሃ ነው። በዘመናት ውስጥ ለእርሻ አካባቢው በተመነጠረ ቁጥር፣

አቃጠሉት አሉ አዳባይ ጫካውን፣ አቃጠሉት አሉ ዝማ ጫካውን፣ ከማይረባ ወንድም የሚሻለውን። እየተባለ እንደሚወዱት ዘመድ ሙሾ ተወርዶለታል።

ብዙ ከአዳባይ የሚበልጡ ወንዞች ይኖራሉ። ለአገሬው ሕዝብ ግን አዳባይን የሚያክል ወንዝ ማን ያለ ይመስለዋል! ። ሁሉም ሰው በመንደሩ ለሚያልፈው ወንዝ ልዩ ግምት አለው። በልጅነት ዘመን ያዩት ኩሬ ባሕር ነው። በመንዝና አካባቢዋ ከሚፈሱት ብዙ መቶ ወንዞች ግን አዳባይ ትልቁ ነው። ከሌሎች ወንዞች ሸለቆዎች ሁሉ፣ የአዳባይ ሸለቆ ባለግርማና ትልቅ ነው።

አዳባይ ሲፈስ ወቅትም ታሪክም ይፈሳል። ምድርም፣ እጽዋቷም ብቻ ሳይሆን፣ መልኩዋ ይቀየራል። አዳባይ በሺ ዘመናት ውስጥ መሬቱን ሲንድና ሲሸረሽር፣ ተራራዎችንና ሸለቆዎችን ሲፈጥር፣ ሲሞላ ሲጎድል፣ ዝንተ ዓለም ሲፈስ፣ ለቁጥር የሚያታክት ትውልድም ያልፋል፣ ይደባለቃል፣ ይታመሳል፣ ይወጣል፣ ይወርዳል።

ሴማውያን ከአረብ የባሕር ሰላጤ በቀይ ባሕር በኩል ገብተው ከሃማይቶች ጋር ተጋብተው ሲኖሩ፣ በየጊዜው ሌሎች ሕዝቦች እየመጡ ይደባለቁዋቸው ነበር። ከክርስቶስ ልደት 2,000 ዓመት በፊት ጢምና ሪዛቸውን አገጫቸው ላይ ካለው በቀር ሙልጭ አድርገው የሚላጩ፣ የራሳቸውንም ፀጉር ላጭተው የውሸት ፀጉር (ዊግ) የሚያደርጉ፣ እርቃናቸውን ለመሸፈን ከወገባቸው በታች እራፊ ጨርቅ የሚያስሩ ግብጻውያን ጋር ተገናኙ። ብዙ ዘመናት ካለፉ በኋላ በቀይ ባሕር ጥገት ላይ ከግብጽ አገር የመጡ፣ አለባበሳቸው ገላቸውንም የሚሸፍን፣ ረዣዥም ጦር ለአስር አሥራ አምስት ይዘው በብዙ ረድፍ ሆነው ወደፊት የሚገፉ፣ ግራ ቀኝ በማለት እንደ ዳንኪረኛ ውዝዋዜ የሚራመዱ ጦረኛ ግሪኮች መጡ። ከነዋሪዎቹ ጋር ተጋቡ። እነዚህ የብዙ ዘር ውጤት የሆኑት አክሱማውያንና ሌሎች በቁጥራቸው ሲበዙ ወደ ደቡብ ሲፈልሱ አዳባይ ዙሪያ ደረሱ። መንዞች ሴማዊ ቋንቋና ደም ተዳቀለባቸው።

አዳባይ በሜዳዎች ላይ ወይም በትላልቅ ሸለቆዎች መሃል ሳይሆን፣ በትላልቅ የተፈጥሮ ቦዮች ውስጥ ይፈስ ነበር።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአክሱማውያን ሥርዎ መንግሥት ወደ ሌላ ሲዛወር የአክሱም ንጉሥ ሸሽቶ እንደገና አዳባይ አካባቢ ለመደበቅ ሲመጣ ዮዲት አገሩን ወሰደችው።

የአዳባይ ዙሪያ እንደየትኛውም የዚች ዓለም መንደር ብዙ ዘርና ነገድ ማስተናገድ አለበትና ከደቡብም መጥተው ሰፍረውበታል። አዳሎች የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትን

በራሳቸው ሥርዎ መንግሥት ሥር እንደገና ለማዋቀር ሲነሱ በግራኝ አህመድ[3] መሪነት በአዳባይ ዙሪያ አለፉ።

የግራኝ አህመድ ትዝታ ዛሬም ቢሆን በየጎዳናው ላይ በየአድባራቱ በጨዋታ ላይ ይከሰታል። በመንዝና አካባቢዋ ትላልቅ ቋጢኞች የግራኝ ፈረስ ማሰሪያ ሲባሉ፣ ብዙ ጎድጓዳ ድንጋዮች የግራኝ ፈረስ የረገጣቸው እየተባሉ ተሰይመዋል። ኩሩ ሕዝቦች ስለሆኑ የሰው ቁመና፣ የሰው ቁመት፣ የሰው ጉልበት ብቻ የያዘ አሸንፎን ነበር ብለው ለማመን አይፈልጉም። ለእነሱ ግራኝ ልዩ ፍጡር፣ ሥራው የሰይጣን፣ ያደረሰወ ጥፋት በእግዜር ቁጣ የመጣ ነው። ለመንዞች ከሰው በታች ከመሆን ይልቅ፣ የሰው በታች ነኝ ብሎ ማሰቡ ሽንፈትን መቀበል ነው።

የኦሮሞዎች መፍለስ ግን አዳባይ ዙሪያን ስላጥለቀለቀው ብዙ ለውጥን አስከተለ። የላላው የቤተዘመድ ወጋቸው በኦሮሞዎች የነገድ ሥርዓት ግፊት ወይም ማዕከላዊ መንግሥት ስለተዳከመ፣ ወረራን ለመከላከል የቤተዘመድ ወግ ተጠናከረ። ጋብቻ በሩቅ ዘመዳሞች መሃከል ተከለከለ። መንዞች ወደ ተራራዎች ጫፍ አፈገፈጉ። ቆይቶ ግን መንዞች ከኦሮሞዎች ጋር በመጋባት ተዳቀሉ።

ከአንድ ምዕተ ዓመት ተኩል በፊት ደግሞ ከመንዝ ደጋ አገር ወደ ቆላው አዳባይ፣ ሦስት የወንድማማች ልጆች ወርደው ሰፈሩ። ያቀኑትንም መሬት አስካል፣ ባሮ፣ ጆር ብለው ሰየሙት። ለምን እንዲህ ብለው እንደሰየሙት፣ ኑሮዋቸውስ እንዴት እንደነበር በደንብ የሚየስታውስ የለም። የመሬቱ አሰያየም ግን የዚያን ጊዜ ሰዎች የሥር ልባቸው ስሜቶች ነፀብራቅ ነው። ልጁን፣ ከብቱን፣ መሬቱን፣ ለመሰየም ማንም ሳያስብ አፉ እንደመጣ አያደርገውም። አስካል ማለት መልካም፣ ባሮ ማለት ሰጥቶ የማይጠግብ፣ ጆር ማለት ውሀ ስለሆነ፣ አዲሱ ድንግል መሬት ምርታማና በጣም ተስማሚ ሆኖላቸው እነደነበር ይጠቁማል። ያ ሁኔታ ዳኘው በዚያ ቦታ በተወለደ ጊዜ ላይታይ ይችላል። ጎርፉ፣ ንፋሱ፣ ዝናቡ፣ የመሬቱን ገጽና ሽፋን ይንድዋል፣ ይከበዋል፣ ይለውጠዋል። የትኛውም ትውልድ አባቱ በረገጠው አፈር ላይ አይራመድም።

በዚሁ ዘመን ከመንዝ የተጉለት አዋሳኝ መንደሮች አንደ ብቸኛ ሰው፣ ሞፈር ውህን ተሻግሮ፣ ከንብዋሻ አፋፍ ላይ ካለው መንድር ከሚኖረው አሮሞ ቤት ገብቶ፣ የኦሮሞውን ሴት ልጅ አግብቶ መኖር ጀመረ። አሮሞዎች መንዞችን ወደ ተራራማው መንዝ ሲያስፈገፍጓቸው የተነጠቀ መሬት ነው ተብሎ ንብዋሻ ለመንግሥት ተመልሶ ስለነበር፣ ይህ የአስካለ ቅድመ አያቱዋ የሆነ ግለሰብ የተጋባው ከጭሰኞች ጋር ነበር። በደረቅ መሬት ጭሰኛ ከመሆን በለም መሬት ጭሰኛ መሆን የሚሻል ብቻ ሳይሆን ከደርቅ መሬት ርስት ይመረጣል።

---

[3] በመጀመሪያው እትም በስህተት ግራኝ ሙሃመድ የሚለው ተስተካከሎ።

በዚህ ሁኔታ የዳኘው ቤተ ዘመዶች በአዳባይ መልካ አስካል፣ ጆርና ባሮ በሚሉዋቸው መሬቶች ላይ፣ የአስካለ የእናቱዋ በኩል ቤተ ዘመዶች ተጉለት ንብዋሻ ተራቡ። ከመንዝ ወደ ንብዋሻ ብዙ ሰዎች እንደሚሄዱ፣ ከንብዋሻም ወደ መንዝም እየመጡ ይጋባሉ። አዳባይን ማቋረጥ ተለምዶ ነበር።

የአስካለና የዳኘውን ቤተ ዘመዶች በመሃከላቸው የሚያለያያቸው ወንዝ ብቻ ሳይሆን ጊዜም አንደኛውን እያነሳ ሌላውን እየጣለ ነበር። ዳኘው ከአዳባይ መልካ፣ አስካለ በንብዋሻ መንደር በተወለዱ ጊዜ፣ የአስካለ ቤተ ዘመዶች ከጭሰኝነት ወጥተው ባለርስት፣ የዳኘው ቤተ ዘመዶች ከመሃላቸው ቀደም ሲል በተነሳ አስነቃይ መሬት አልበቃ ብሏቸው እየተጋዙ የሚያርሱ ድሃዎች ሆነው ነበር።

አስካለ ቤተ ዘመዶቿዋ ዘለዓለም ሃብታም የነበሩ እንጂ ከጊዜ በኋላ ያገኙት ነው ብላ መጠርጠር ቀርቶ፣ አስባበት አታውቅም። ዳኘው ግን ነፍስ ከአወቀ ጀምሮ በተጋዥነት የሚታረሱት ቦታዎች፣ የቤተ መንግሥት እርስት የሆኑት በአንድ ቅድመአባቱ ስሕተት እነደሆነና፣ መሬቱ ሊመለስ እነደሚገባ አባቱን ተከቶ የሚከራከርና በድህነቱም የሚቆጭ፣ ዘሮቹ ባላባትም እንደነበሩ የሚናገር ነበር።

አዳባይ በክረምት ይደፈርሳል፣ ቀይ አፈር ይመስላል። ጥቅር፣ ትልቅ፣ ሰፊ፣ ሆኖ ፍጥነቱ እየጨመረ፣ እንደ ገደል ናዳ እየተወረወረ፣ የበጋውን ቀጭን ጅረት ኩል መሳይ ውሀውን እያለበሰ፣ ደረቅ በነበሩት ቦታዎች ሁሉ እየተሹለከለከና ድንጋዮችን እየናደ፣ ዛፍ እየነቀለ፣ እያጓራ፣ ገስግሶ ደረቅ የነበረውን ቦታ ሁሉ ያለብሰዋል። ክረምቱ ሲያልፍ ወተት ይመስላል። ቆይቶ ኩል መስሎ ይጠራል። በአንድ ወቅት አይተውት በሌላ ወቅት የነበረውን ለማስታወስ እድል አይሰጥም። በየትኛውም መልኩ ውብ ስለሆነ ያለፈውን የመናፈቅ ትዝታ አያመጣም።

⅄ ⅄ ⅄

# ዳኘው ዘለልከ

እያንዳነዱ አባት ልጁ ለአቅመ አዳም የደረሰበትን ቀን በአጋጣሚ ያውቀዋል። ልጁ ከፍርሐት፣ ከወላዋይነት፣ ከአምልኮኛነት ወጥቶ የአባቱን ዓይን ትኩር ብሎ መመልከት መጀመሩን፣ ሳያመነታ መከራከር መያዙን፣ ያልመሰለውን ነገር ቸል ማለቱን ያስተዋለ አባት፣ ልጁ በመንፈሱ ለአቅመ አዳም መብቃቱን ያውቅና ከሞግዚትነት ወደ ጓደኛነት ይተላለፋል። አባትና ልጅ በእኩልነት ይጫወታሉ። ዘለልከ ልጃቸው ዳኘው አንድ ቀን ሽንጡን ገትሮ፣ ትኩር ብሎ እያየ፣ ሲከራከራቸው ገረማቸው። የሕፃንነት ዘመን ካለፈ በኋላ በነፍስ ማወቁ ዘመን ያፍራቸው፣ ይፈራቸው ነበር። ይሀ ባሕሪ ቀደም ብሎ ይጀምር አይጀምር እርግጠኛ አልሆኑም።

ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ዘለልከ ልጃቸውን ዳኘውን፣ ከጎናቸው አስቀምጠው፣ በቁም ነገር፣ አሁን ባሉበት ቦታ ላይ እንዴት ገባር እንደሆኑ፣ አስጠኑት።

“አየኸው ይህን ሁሉ መሬት። በጣም ለም ነው። አባቶቻችን ሦስት ሆነው መጥተው ያቀኑት ነው።” ሲሉ ጀመሩ። እንደ ማንኛውም አስተማሪ ከሥር መሠረቱ ለመጀመር ብለው። ዳኘውም ለሱም ባይሆን ለሌሎች ሰዎች ሲያወሩት ደጋግሞ የሰማው ስለሆነ ዝም አለ። “ለማያውቀው ከቆላ እንዲህ ዓይነት ለም መሬት ያለ የሚመስለው የለም....” አሉ። ዘለልከ ፈገግ ብለው ከፊታቸው ላይ ዝንብ እነዳረፈባቸው ያህል እጃቸውን ግራና ቀኝ ሽው አድርገው። ቁም ነገር በሚናገሩበት ጊዜ እንዲህ ያደርጋሉ። “የኔ ቅድምአያት እስክንድር፣ እኔ አለቃ ልሁን እኔ አለቃ ልሁን በማለት ከወንድሙ ልጅ ጋር ተጣልተው፣ በአገር ሽማግሌ የሚረታ መሆኑን ሲያውቅ፣ የብቻ አክስቱ ለነበሩት ለአጼ ሚኒልክ እናት፣ ለልዕልት ዘነበወርቅ፣ መሬቱን የግሉ አስመሰሎ አወረሰው....” ብለው አሁንም ከፊታቸው ላይ ቀኝ እጃቸውን አራገቡና “ቢሆንም እስክንድር ትልቅ ሰው ነው። እልህ ይዞት ነው። ከኛ ቤት እልህ አለች......” ብለው ቅድም አያታቸውን፣ የራሱን ደም እንዳይጠላ ለማግባባት ያደረጉት ሙከራ ምን ያህል የተሣካ እንደሆነ ለማየት ፈገግ ብለው አተኩረው ተመለከቱት። ዳኘውም ምንም ባይጥመውም ሊቃወማቸው አልፈለገም። ፈገግታቸው ሃሳባቸውን እንዲቀበላቸው ልመና መስሎታል።

“ይኸውልህ ከዚህ ከበረሃ ለም መሬት ያለ የሚመስለው የለም ነበርና እስክንድር መሬቱን እንዲወርሱለት ሲጠይቅ፣ መቸም ቢሆን ውለታ ተቀባይ ባለ ዕዳ ነውና፣ እምቢ ስላሉት፣ ለም መሆኑን ለማረጋገጥ ከባሮ ሁዳድ እሸቱን ይዞ ሲሄድ ፍሬው ጡጫ ጡጫ ያክል ነበርና ደስ ብሏቸው ወረሱት።” አሉ ቁጭታቸው ከሽማግሌ ፊታቸው ላይ እየተነበበ።

“ቀድሞስ ሳያውቁ የግሉ ነው ብለው ወረሱ፣ በኋላ ግን ያደረገው እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ብሎ መሆኑን ሲያውቁ ለዘመዶቹ አይመልሱም?” ሲል ዳኘው እልህ ተናንቆት ተናገረ። ዘለልከም እንደዚህ ሲሉ የኖሩ ስለሆነ አዲስ ነገር ባይሆንባቸውም፣ ዳኘው እልህ ሲተናነቀው ግን ደስ አላቸው።

የዚያን ሰሞን ቀስ ብለው፣ ጊዜ ፈጅተው፣ በጨዋታ መሃል እያነሱ፣ ጉዳዩን አጫወቱት። የሳቸው አባቶች ያልጨረሱትን ክርክር እሳቸው ቀጥለውበታል። እሳቸው አንድ ነገር ቢሆኑ እሱም ክርክር እንዲቀጥልበት አደራ አሉት።

ዳኘው እንደሚሳካለት በወጣትነት ስሜቱ ባለሙሉ ተስፋ ሆኖ ደስ አለው። ዘለልከም ተተኪ በማግኘታቸው አንድ ነገር ከትከሻቸው የወረደላቸው ያህል ቀለላቸው።

ገባርነት ዱብ እዳ እንጂ ብዙ ትውልዶች ሲሽረሽር ኑሮ አይመጣም። ዘመነ መሳፍንት ይከሰትና፣ እርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እራሱን መጠበቅ ያቃተው ቤተዘመድ፣ የአንዱን ኃይለኛ መከታ ለማግኘት ከሞተ በኋላ መሬቱን ሊለቅ ያወርሳል። ካለዚያም ዘማች ይመጣና ገባሪ ካደረገው በመሬቱ ላይ ይመራበታል። ይህ ካልሆነም ከመሃከሉ አንድ

አስነቃይ ይወጣና ቤተ ዘመዱ ባዶ እጁን ይቀራል። ከዚያ ጌትነት እንደሚለመድ ድህነትም ይለመዳል። ጌትነት እንደሚወረስ ድህነትም ይወረሳል።

የዳኘው አባት ዘለልከ ከሦስት ሴቶች የወለዱአቸው ከዳኘው ጋር ወልደ ሰማዕት፣ ካብታሙዋ፣ አስኳል፣ ንጋቷ፣ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አይሌ የሚባሉ ስድስት ልጆች ነበሩዋቸው።

ሁሉም ቤተሰብ የራሱ ቃየልና አቤል ይኖረዋል። ብዙ ልጆች ያለው ቤተሰብ ብዙ አቤልና ቃየል ባይሆንም የሌሎች ምስሌታውያን ባሕሪ ቅጅዎች ይኖሩታል። ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው ልጆች ግን የሚወልድ የተለመደ አይደለም። የናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው። ዳኘውና ወልደ ሰማዕት የአንድ እናት ልጆች ሲሆኑ የተለያየ ባሕሪ ነበራቸው። እንደ ሁለቱ ግን የሚዋደድ የለም ነበር።

ዳኘው ወታደር መሆንን የሚወድ ሲሆን ወልደ ሰማዕት ግን እርሻን ይወዳል። ዳኘው ከአገሩ ወጥቶ በሌላ አገር እድሉን ለመሞከር የሚደፍር ሲሆን ወልደ ሰማዕት ግን ከትውልድ ቦታው መውጣትን እንደ ሞት የሚቆጥር ነው። ዳኘው ያልታወቀውን አዲሱን ነገር ሲመኝ ወልደ ሰማዕት የያዘውን የሚያውቀውን ይወዳል። ስለ ጥብቆቻቸው ባላቸው አስተያየት እንኳን ይለያያሉ። ዳኘው አዲስ ልብስ ከተገዛለት አሮጌውን ለመልበስ ፍላጎት የሌለው ሲሆን ወልደ ሰማዕት ግን ከአሮጌው ጋር በጣም በመተሳሰሩ የሚዝናናው በአሮጌው ልብሱ ውስጥ ሲሆን ነው።

ካብታሙዋ ከትውልድ መንደሩዋ እርቃ የምትሄድ፣ ዘመድ ያልሆኑ ጓደኞች የምታፈራ፣ ለጓደኞቿዋ ሙት የሆነች፣ የምታምንበት ሰው ካገኘች የምታመልክበት የመግደላዊቱ ማርያም ልብ አላት።

ንጋቱዋ ከትውልድ መንደሩዋ ረግታ የምትቀመጥ የቤት እመቤት፣ ስትሆን የዘመድ ማረፊያ የሆነች፣ ኤልያስን በዚያ ከፉ ቀን እንደመገበችው እመበለት ነበረች።

አስኳል ዘመዶቹዋም ሆኑ ሌላ ሰው ስሜትዋን በቀላሉ የሚያደፈርስባት፣ የእለት በእለት ኑሮዋን እንጂ ስለ ወደፊቱ ለመጠንቀቅም ሆነ ለማቀድ ፈቃድ የሌላት፣ በቀላሉ የምትደሰት፣ ከሙቶ በጎች መሃል ጠፍቶ የተገኘው በግ ተብሎ በምሳሌ እንደሚነገርለት ሰው መንፈስ ያላት ነበረች።

አይሌ የመጨረሻው ልጅ ሲሆን የዳኘውን ፈለግ የሚከተል ነበር። ዳኘው ግን ሁልጊዜም ባለፈው የሚፀፀት ስለሆነ አይሌን በዚህ መስከ አያደፋፍረውም።

ዘለልከ ወልደ ጊዮርጊስን አብልጠው ይወዳሉ። ከወልደ ጊዮርጊስ በፊት ወልደ ሰማዕትን ከሁሉም የሚበልጥባቸው ልጅ ነበር። የዓይኔ አበባ የዳኘውና የወልደ ሰማዕት እናት፣ ለወልደ ሰማዕት ታዝናለች። እናት በፉክክር ዓለም ውስጥ ደከም ብሎ ለሚገኘው ልጁዋ ልቡዋን ትሰጣለች። የነዘለልከ ግቢ ከመንደሩ በስተምዕራብ በኩል ነው። የቦታው አቀማመጥ ግን ቅድም አባቶቹ የመረጡት እንጂ የሱ ፈቃድ አልነበረም። የመኖሪያ

ቤታቸውን፣ ከግቢው ውስጥ ግን፣ ዘለልከ በራሳቸው እጅ፣ እንደራሳቸው ፍላጎት የሠሩት ነበር።

የዚያን ጊዜ ወጣቱ ዘለልከ አሁን ያለበትን ቤት የሠራው የመጀመሪያ ልጁን ዳኘውን ወልዶ ዳኘው አራት ዓመት ሲሞላው ነበር። ከዚያ በፊት በአንዲት አነስተኛ ጎጆ ውስጥ ይኖር ነበር። እንደማገኛውም ጎጆ ወጭ፣ ከእርሻ ቦታው ሲመለስ፣ ሁልጊዜም አንድ ድንጋይ ይዞ እያመጣ ከግቢው ይጥላል። እርሻ በሌለበት ጊዜ ደግሞ ብዙ ድንጋዮችን ያመላልሳል። ዳኘውም እንደ አቅሙ ያግዘዋል። ዘለልከ በግቢው ውስጥ አንድ ቤት መሥራት እንጂ ስለ አጥሩ መጨነቅ እንደሌለበት ያውቃል። በአካባቢው፣ መንደሮች ከአንደ ሰፊ ሜዳ ዙሪያ በቤተ ዘመድ፣ በቤተ ዘመዱ ግቢዎች የተሠሩባቸው ናቸው። አንድ ቤተ ዘመድ አንድ ሰፊ ግቢ ይኖረዋል። ግቢው ዙሪያውን በድንጋይ ካብ ታጥሮ በስተ ሜዳው በኩል እድሞ ይኖረዋል። የዘለልከ ቤተሰብ ግቢና አሠራርም ከመንደሩ ቤቶችና ግቢዎች ተመሣሣይ ነው። የነዘለልከ እድሞም ከግራና ከቀኙ በድንጋይ ታንጾ አሞራ ክንፍ ጣሪያ ተሠርቶለታል። ከመሃሉ መግቢያና መውጫ በር ሲሆን፣ በተጨማሪም ከአናቱ ያለው ጣሪያ በክረምቱ ወራት ለበሬዎች መጠለያ ያገለግላል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁልጊዜም የቤቱ ሰዎች ማታ ማታ ፀሐይ ልትጠልቅ ስትል፣ ከዚህ እድሞ ሥር እንደ መደብ በተሠሩት የድንጋይ ክምሮች ላይ ቁጭ ብለው፣ ሰፊውን አገር እያስተዋሉ ይጫወታሉ። የቤተዘመድ ጉባዔዎችም ብዙውን ጊዜ እዚሁ ይካሄዳሉ። ዘለልከም ከእርሻ መልስ ልጁን ታቅፎ ከዚሁ እድሞ ተቀምጦ ቤቱን እንዴት እንደሚሠራ እቅድ አወጣ። ሁልጊዜም ቢሆን ፀሐይ ከአድማሱ ስታቆለቁል ቀዩ ቀለም ወደ ላይ ይነሣል። የጉሙ ቅርጽ በጥቁር ቀለም በላያቸው ላይ ይሠፍራል። የአካባቢው ሰማይ ከቀረው ሁሉ ይበልጥ ብርሃን ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች ከእድሞው እየተነሱ ወደ ቤት ይገባሉ። በከብት መብያው ገንዳ ላይ ከብቶችን እያስተካከሉ ያበሉ የነበሩትም ሳሩን መስጠት አቁመው በገንዳው ላይ ገለባ ነስንሰው ከብቶቹ እንደፈለጉት እንዲበሉ እየተው ወደ ቤት ያመራሉ። የዚያን ዕለት ግን ዘለልከ የቤቱን እቅድ ሲያወጣ ጊዜው ስላልታወቀው ከመሸም በኋላ ከዚያው ተቀምጦ ነበር።

በማግስቱ በባሕሉ እንደተለመደው ጠላና ዳቦ እንዲዘጋጅ አዘዘ። በሳምንቱ ወዳጅ ዘመዱን ደቦ ጠርቶ ከመንደሩ ሰዎች ጋር እንደ ቤተክርስቲያን ሕንፃ በክቡ በድንጋይ ቤቱን መገንባት ያዘ። ግንቡ በትንሽ ቀናት አራት ክንድ ያህል አደገ። ከዚያም በእንጨት የኮን ቅርጽ ያለው ጣሪያ ከተሠራ በኋላ በስተውስጡ በኩል በመቃ ክብ ችምችም ብሎ እንደ ኮርኒስ ከተሠራ በኋላ ከውጭው በኩል ሳር ለበሰ። ቤቱ መሠራት ከጀመረበት ቀን አንስቶ ጠይም፣ ፀጉረ ሉጫ፣ ፈርጣማ የአራት ዓመት ልጅ ከአካባቢው አልተለየም። በመጨረሻም ዘለልከ ልጁን ዳኘውን ከጎኑ አቁሞ ራሱን እያሻሸ አዲሱን ቤቱን ተመለከተው። በደስታ ፈገግ አለ።

በግቢው ውስጥ አራት አዳራሽ ቤቶች አሉ። አንደኛው የቅድም አያቱ፣ ሌላው የአባቱ፣ ሁለቱ ደግሞ የአጎቱ ናቸው። ከነዚህ አዳራሽ ቤቶች ሌላ ደግሞ በክብ ቅርጽ ፎቅ ሆነው የተሠሩ መኝታ ቤቶች አሉ። ሁሉም ቤቶች በራፋቸው በስተምሥራቅ በኩል ስለሆነ

የጢት ፀሐይ ከቤት ትገባለች። የአዳራሽ ቤቶች ወለል ዙሪያውን በመደብ የተከበበ ስለሆነ በድግስ ጊዜ ለማስተናገጃ፣ በሌላ ጊዜ ለመዝናኛ ያገለግላሉ። ዘለልከም አዲሱ ቤቱን በዚህ መንገድ ካዘጋጀው በኋላ ገባበት። የዚያን ጊዜ ግን ከዳኘው ሌላ ብዙ ልጆች ተወልደውለት ነበር።

የዘለልከ ቤት ውስጥ አራት ሴቶች ተፈራርቀው ገብተዋል። አንዱዋ ለአንዳቸው ወይም ለሁለቱ ልጆች እናት ስትሆን ለሌሎች እንጀራ እናት ናት። ልጆች ሁሉ ነፍስ እስኪያውቁ ድረስ የአንድ እናት የአንድ አባት የሚል መለያያ አልነበራቸውም። ከጊዜ በኋላ ግን በአካባቢያቸው አስተምህሮ ልጆቹ በቡድን በቡድን ይቀራረቡ ጀመር። ሁሉም ልጆች ለማንኛውም ነገር በአንድነት የሚቆሙ ሳይሆን፣ ሕይወት ራሱዋ ታቧአድናቸው ነበር። ዳኘውና ወልደ ሰማዕት የተቀራረቡት ለዚህ ነበር።

እንደ እንጀራ እናት የሚጠላ የለም። እንጀራ ጋግራ ያበላች ናት እናት፣ እያሉ አባቶች ሊያሳማምሩት ቢሞክሩም፣ ልጆች ሁልጊዜ ከእናታቸው ተነጥለው መኖርን በመጥላታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ልጆች የሚጠላቸውን ሰው በደመ ነፍስ በማወቃቸውም ጭምር፣ እንጀራ እናት ይጠላሉ። ሌላው ቀርቶ ሁለት ጠበኞች አንድ ልጅ እያንዳንዳቸውን ይበልጥ እንዲወዳቸው በሚጠብቁበትም አኳኋን ማደግ የመንፈስ መከፈልን፣ መጨነቅንና ማዘንን ያስከትላል። ሁለት ጣውንቶች በከፋት እርስ በርሳቸው በሚተያዩበትና በሚተሳሰቡበት ሁኔታ ከሚወዳት እናቱ ተነጥሎ ከማያውቃትና እናቱን ከምትጠላ ሴት ጋር የሚኖር ልጅም አስተዳደጉ የሃዘን ይሆናል። የጥንቱ የቤተዘመድ ሥርዓተ ማህበር ሕግ በፈረሰበት ሕብረተሰብ፣ ሰውን ሰው አያለምድም። ጉድፌቻ ሆኖ ማደግና የእንጀራ ልጅ ሆኖ ማደግ ልዩ ናቸው።

ዘለልከ የዳኘውና የወልደ ሰማዕትን እናት አባሮ ብቻቸውን ይዙዋቸው ትንሽ ጊዜ በቆየበት ወቅት፣ ልጆቹ የናታቸውን ሚናም እነዲጫወት ስለሚጠብቁበት፣ ሁልጊዜም ከእርሻ መልስ አድርጎት የማያውቀውን ልጆቹን እራሳቸውን እያሻሸ ሊያጫውታቸው ይሞክራል። እናታቸውን እንዳይናፍቁ የማያደርገው የለም። ሁልጊዜም ግን ጥረቱ ደስታን አያስገኝለትም። ዳኘውን ያቀፈው ጊዜ ወልደ ሰማዕት አኩርፎ ቁጭ ይላል። ወልደ ሰማዕትን ሲያቅፍ ዳኘው መበጥበጥ ይጀምራል። እነርሱም ከእናታቸው ጋር አድመው ሊያበሳጩት የተሰለፉ ይመስለውና በቁጣ ሊያርማቸው ይሞክራል። ምርር ብለው ሲያለቅሱ ደግሞ ሆዱ ይባባበትና ይፀፀታል።

አንድም ቀን ግን ከባለቤቱ ጋር በሚኖርበት ዘመን እሱ ዳኘውን ካቀፈው ወልደ ሰማዕት እናቱ እቅፍ ላይ ዘሎ እንደሚቀመጥ ወይም ወልደ ሰማዕት ከአባቱ ጋር ሲጫወት ዳኘው ከእናቱ ጋር ይሆን እንደነበር ትዝ ብሎት አያውቅም ። ብቻ አንዲት ሴት ቢያመጣ ልጆቹንም የምታሳድግለት መሆኑንና የሱን ሸክም እንደምታቀልለት አስቦ ሚስት ፈልጎ ወደ ቤት ይዞ መጣ።

ከእድሞው እንደገባ ልጆቹን ከአዲሲቱ እናታቸው ጋር ለማስተዋወቅ “እናት ይዠላችሁ መጣሁ፣” ሲላቸው ጥለውት ሸሽተው ሲሮጡ ተመልክቶ የፈካው ፊቱ አመድ

መስሎ፣ "እናንተ ጭራቆች!" ብሎ ጮኸ። ሴትዮዋም ብትጠራቸው "ጭራቆቹ" ሽሽታቸውን ቀጠሉ።

ልጆች ግን ወደ ቤት ተመልሰው መምጣታቸው አይቀርም። ማታውን በስንት መከራ ከአዲሲቱዋ እናታቸው ጋር ትንሽ ትንሽ ለመነጋገር በቁ። እሱዋም ፍቅራቸውን ለማግኘት ታባብላቸው ጀመር። ዘለልክም ደስ አለው።

ጊዜ እያለፍ ሲሄድ ግን እንጀራ እናታቸው በሁሉም ነገር ስታመናጭቃቸው ይመለከት ጀመር። ልቡ በሴትዮዋና በልጆቹ መሃከል መከፈል ጀመረ።

አንድ ቀን ዳኘው እንደራሱ ቁመት አጭር የሆነችውን ዱላውን ከቤቱ በራፍ አጋድሞ ሲጫወት፣ እንጀራ እናቱ ከውጭ በሁለት እጆቹዋ ይዛው የመጣችውን ሌማት ወደ ቀኙዋ አዞራ፣ በግራ እጁዋ ዱላውን መንጭቃ፣ "ምን ይገትርሀል! ድንባዣም!" ስትለው ተመልክቶ፣ ሰምቶ፣ ግልፍ አለበት።

"ልጅን መያዝ በብልሃት ነው። ልጅ ጎሽ ጎሽ ሲሉት ያዘዙትን ይሠራል። ልጅ እንደ አዋቂ ክፉንና ደጉን ስለማያውቅ በሆነ ባልሆነው ማመናጨቅ አይገባም።" ሲል ተናገረ። የዛሬው እለት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ሌላም ቀን ያያቸው ነገሮች በአእምሮው ስዕል እየተፈራረቁ እየታዩት።

"እንዲህ እያልክ ነው ያባለግካቸው።" አለችው። ልፋቴ ሁሉ ከንቱ ሆነ በሚል ዘይቤ።

እልሁን ጨርሶ በቁጣ ሲነሣ እሱዋም እሮጣ ከቤት ወጣች። አልተመለሰችም። ዘለልክ የዚያን ዕለት ልጆቼን በእንጀራ እናት ጠበስኳቸው ሲል አሰበ። በዚህ ግን አልፀናም። ሁለተኛም ያመጣት ሚስቱ ከዚህ የተሻለች አልነበረችም። እራሱዋ ልጅ እስክትወልድ ድረስ ጠባዩዋን ብታሳምርም፣ ልጅ ከወለደችለት በኋላ ግን የእንጀራ ልጆችዋን በሆዳቸውም፣ በመንፈሳቸውም መበደል ቀጠለች።

በዚህን ጊዜ ዳኘውና ወልደ ሰማዕት ይበልጥ እየተቀራረቡ ሄዱ። ምስጢራቸውን እርስ በርሳቸው መካፈልና መደበቅ ብቻ ሳይሆን ከሌላ ቦታ ያጡትን ፍቅር ከርስ በርሳቸው አገኙት። አንደኛው ከሌላው ተነጥሎ አይበላም። አንዱ ያገኘውን ለሌላው ያካፍላል። አንዱ መንገድ ከሄደ እስኪመለስ ድረስ ሌላው ይጨነቃል። ከመሸ ሊፈልገው ይወጣል። በዚያውም ልክ ደግሞ ከከባቻው ውጭ ሌሎች ሰዎች ጋር ሲገናኙ ዓይናፋርና ገለልተኛ ሆኑ። የወልደ ሰማዕት ዓይናፋርነት የበዛ ስለነበር ትህትና ይመስላል። የዳኘው ወደ ቁጣ ያዘነብላል።

ጡዋት በማለዳ ተነስተው ከብቶቹን ከበረት ካስወጧቸው በኋላ "ለልጆቹ አፋቸው የሚያደርጉት ስጡአቸው!" ብሎ ዘለልክ ይናገራል። ቆሎም ይሁን ቂጣ ወይም ጭብጦ ይሰጣቸዋል። ሁልጊዜም ቢሆን አላፊ አግዳሚ መስሎ የሚሰጣቸውን ያያል። ከብቶቻቸውን እየነዱ ወደ ቆላው ይወርዱና ገር የሆነችውን ላም ይጠቡአታል። ገር

ያልሆነችውን ላም ያልቡዋታል። ይህም የተለመደ በመሆኑ አባታቸው ላም ሙልጭ ተደርጋ ስትታለብ አይወድም።

ልጆቹ ወደ ቤት ሲመለሱ ጠዋት በተደረገላቸው መስተንግዶ ዓይነት እንጨት ሰብረው ይመለሳሉ። እንደ ሁኔታው ይበዛል ያንሳል። ወይም ይቀራል። ዳኘው ጎሽ ጎሽ ያሉት ጊዜ ምንም ነገር ይሠራል። ድካም አይሰማውም። ተቆጥተውት ደግሞ ምንም ነገር አያደርግም። ወልደ ሰማዕት ይህን ያህል ግድ ባይኖረውም፣ ወንድሙን ላለማጋለጥ ከወንድሙ በላይ ሠርቶ አያውቅም።

ሰፈሩ የራሱ ታቦት ሲነግሥ መላው አገር ደጋሽ ቢሆንም፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ ግን የራሱ ማህበር ስላለው፣ በዚህ ዓይነት ጊዜ ልጆች እየተወናፈሉ እንጨት ከዱር ያመጣሉ። የእንጨት ሠባሪነታቸውንም በድግሱ ጊዜ በሰፊው ይስተናገዳሉ። ለፍተው መስተንግዶአቸውን ያሳነሰባቸውንም መበቀያ ዘዴ አላቸው።

ከመንደሩ አፋፍ ላይ ቁጭ ይሉና በጣቶቻቸው ጉሮሮአቸውን ለቀቅ አፈን እያደረጉ የስድብ ናዳ ያወርዳሉ። “እረኞች አፍ ገባሁ” ብሎ ተሰዳቢው ከአፍ የሚድንበትን ዘዴ ይሻል። ውሪ ልምታህ ቢሉት ጥብቆውን ነፋስ ሲያርገበግበው ቂጡን ገልቦ እየሮጠ፣ ጨዋታ ይመስል እየሳቀ፣ እንደገና እየቆመ፣ እያበሸቀ፣ አንጀት ያሳርራል። ዝም እንዳይሉት ምሱን እስኪያገኝ አያርፍም። ስለዚህ መታረቂያ ሌላ ግብዣ ይጠራሉ።

ወልደ ሰማዕት ለዚህ ጠንሳሹ ነው። ግጥም ማውጣት ብቻ ሳይሆን ተሰዳቢውን ከሚስቱና ከጎረቤቱ ለማጣላት የሚባለውን ነገር ያውቃል። እሱ ጮሆ ባይናገረውም ለዳኘውና ጓደኞቹ ሲነግራቸው ጮኸው ያስተጋቡታል።

አያ እከሌ ጦር አትገዛም ወይ ጋሻ አትገዛም ወይ

ቤትህ ሲደፈር በወዳኝ ነኝ ባይ። ለዳኘው ዱሩ፣ ተራራው፣ ድፍረት ይሰጠዋል። ቤትና መንደር ግን የሰደባቸው ወይም ክፉ የሚላቸውን ሰዎች የሚያገኝበት ስለሆነ፣ ደስ አይለውም። ወልደ ሰማዕት ጮሆ ተናጋሪ ስላልሆነ ትሁትም ስለሚባል በመንደር ውስጥ መዝናናትን ያውቃል።

ወልደ ሰማዕት ሌላው ቀርቶ እናቱ ልትጠይቀው ስትመጣ ስሙዋት እንጀራ እናቱም በዚህ ሳትከፋበት አስደስቶ ለመኖር ይችላል። ዳኘው ወልደ ሰማዕት ይህን እንዴት ሊያደርገው እንደሚችል ይገርመዋል። ወልደ ሰማዕትን እድለኛ፣ እራሱን ግን ደመ መራራ፣ አድርጎ ይገምታል።

ዳኘው ከዱር ሲመለስ ከቤት የሚጠብቀው ሳቅ ይሁን ቁጣ ስለማያውቅ ሁልጊዜም ተቆጥቶ ይገባል። የማይወደው ቁጣን ስለሆነ እሱ ቀድሞ ፊቱን አጥቁሮ በመግባት፣ ከሌላ አቅጣጫ እንዳይመጣ ይከላከላል። ከዚያ በኋላ አሽሙርንም ሆነ የማይመስለውን ነገር እንዳልሰማ ያልፈዋል። ወታደርን የሚያዝ አለቃ ኮምጨጭ ማለቱ ተሰሚነት እንደሚያስገኝለት፣ አስተማሪም ኮምጨጭ ካለ ተማሪዎች እንደሚያዳምጡት፣ እሱም ኮስተር ማለቱ በቤተሰቡ ዘንድ የዚህ ዓይነት ውጤት አስገኝቶለታል።

በቡሔ በዓል ጊዜ እናታቸው የቡሔያቸውን ዳቦ ይዛ ስትመጣ፣ እንጀራ እናቱ እናትህን ሳም ሳትለው፣ ስሞ መቀበል የጀመረው ካደገና ይህ ዓይነቱ የመከላከያ ዘዴውን ካዘጋጀ በኋላ ነበር። ከዚያ በፊት ግን እንጀራ እናቶቹ እንዳይጮሁበት፣ እንዳይበድሉት፣ በመፍራት እናቱን የሚስመው እነሱ ጠርተው ሳም ሲሉት ሲሆን አብሮ ከሱዋ ጋር መቆየትንም ይፈራ ነበር።

ያ ትዝታ አይጠፋበትም። የምትናፍቀው እናቱ የቡሔውን ይዛ ስትመጣ እንጀራ እናቱን በመፍራት ይሸሻታል። እናቱም እንባዋ ይመጣል። ጠልታው እንዳልሆነ ይገባዋል። እንጀራ እናቱ ለትህትናው ያህል ስትጠራውና ሲገባ “ናፍቆ ነው የሚያፍረው ሳማቸው።” ትለዋለች። ይስማታል። በእናቱ እቅፍ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይፈልጋል ። ፍራቻ ግን ቶሎ ያወጣዋል። እናቱ ስትሰናበተው ሰው እንዳያያት ፊትዋን አዙራ አይኑዋን ስትጠርግ እንዳለቀሰች ያውቃል።

አንድ ቀን ግን እናቱን በደንብ አጫወታት። እናቱ ከቤት እነደነበረች ያውቅ ነበርና ፊቱን ኮምጨጭ አድርጎ የውጭውን እድሞ ሲገባ፣ እንጀራ እናቱን አግኝቷት፣ አፉዋን የሚዘጋውን የተኮሳተረ ግንባሩን ሳይፈታ “እነደምን ዋላችሁ!” ብሏት፣ አልፎ ከቤት ገባ። እናቱን በደንብ ስሙዋት ከዚያም ብዙ ጊዜ እያጫወታት ቆየ። ወደ አገሩዋም ስትመለስ ሩቅ መንገድ ድረስ ሸኛት። ወልደ ሰማዕት እንኳን ሸኝቱዋት አያውቅም። ዳኘው የልጅነት ጊዜውን ጨረሰ። ነፃነት።

“እንዴት ነው ኑሮህ?” አለችው እናቱ የዓይኔ አበባ። ጠይቃው የማታውቀውን፣ እድል አግኝታለት የማታውቀውን ጥያቄ፣ ሁልጊዜ በራሱዋ ሐሳብ በመጥፎ የምትተረጉመውን ጥያቄ ስታነሳው ሐዘን ድምጽዋን እያርገደገደው። ቀጥላም “ወንድምህስ እንዴት ነው?” አለች።

“ኑሮ አሁን ጥሩ ነው። አንዲት ላም ለመግዛት አስቤአለሁ።” አለ ዳኘው ትልቅ ሰው ስለመሆኑ ለመናገር አጋጣሚ በማግኘቱ ደስ ብሎት።

“ገንዘቡን ከየት ታገኛለህ። አባትህ እሰጥሃለሁ ብሎሃል?” አለች የዓይኔ አበባ ግራ ገብቱዋት፣ ሃሳቡን ለመስማት ግን ፈልጋ።

“ሸማኔ ሥራ ተምሬአለሁ። ላንቺም ቀሚስ እሠራልሻለሁ። ፊትሉን ቶሎ ቶሎ በይ። ” አለ ዳኘው ሥራውን የሚያሞግስለት ሰው እንደሚያገኝ አምኖ ብቻ ሳይሆን እናቱንም ሊረዳ በመቻሉ ደስ ብሎት።

የግብርናን ሥራ የጨዋ ሥራ፣ የሸማኔ ሥራን ግን የጠይብ ሥራ አድርጋ የምትገምተው እናቱ ቅር አላት። ሆኖም ግን ራሱን መቻሉ አስደሰታት።

“ይሁን፣” አለችው። “ቀሚሱን ሌላ ቀን ተሠራልኛለህ። እንዲህ ካደረግህ አይጠራቀምልህም።” አለችና አሁንም የልጅነቱ መንፈሱ ሙሉ በሙሉ አለማከተሙን አስተውላ ፈገግ አለች። ዳኘው ቁመቱ መሀከለኛ፣ አመለካከቱ ኮስተር ያለ፣ ሉጫ ፀጉር ያስዋበው፣ ጠይም፣ ለግላጋ ወጣት ሆኑዋል።

ለዳኘው በሕይወቱ ውስጥ አዲስ ብርሃን የፈነጠቀበት ጊዜ ነበር። በትውልድ መንደሩ ለመቆየት ግን ሃሳብ አጣ። እራብ ሲጠገብ ይረሳል። ችግር ካለፉት በኋላ እምብዛም ትዝታ የለው። ነገር ግን በሚጠሉት አካባቢ ዙሪያ ብዙ መቆየት ለሕሊናም እረፍት አይሰጥ።

አንድ ቀን ዳኘው ለወልደ ሰማዕት ስለ አዲስ አበባ አጫወተው። “እኔ ልሄድና ወታደርነት ልቀጠር አስቤአለሁ።” አለ ዳኘው አንተም ትሄድ እንደሆነ ሳታማክረኝ እንዳተለኝ ነው የሚል ዘይቤ ባዘለ አነጋገር።

“ለምን ከመንደራችን፣ ከቀያችን፣ ከአገራችን እንወጣለን?” አለ ወልደ ሰማዕት የሚያስተሳስራቸው ገመድ ስላልተበጠሰ እንሂድ ተብሎ በግልጽ የተጠየቀ ያህል እኛ ብሎ።

“እኔ ከዚህ አልኖርም፣ ሰልቸቶኛል።” አለ ዳኘው ወልደ ሰማዕትን ከማግባባት አፈግፍጎ።

“እኔ መቸም ቢሆን ከአገሬ ወጥቼ መኖር አልችልም......” አለ ወልደ ሰማዕት ተከዞ። ዳኘውን የተወው መስሎት፣ በዳይነት ተሰምቶትና ዳኘው ከዚህ አስቸጋሪ አማራጭ ሳይቸግረው ስለከተተው ተናዶ፣ የሚይዝ የሚጥለውን አጥቶ። ለማንም የተናገረው ሳይሆን እራሱን በራሱ ከመረመረ በኋላ የደረሰበት ውሳኔ ገንፍሎ በቃል ተገልጾ ነበር።

“እንግዲህ ለማንም እንዳትናገር።” አለ ዳኘው ሳይቸግረው ምሥጢሩን አውጥቶ እንዳይባክንበት እንደተጨነቀ ሰውና ውለታ ጠይቆ እንቢ እንደተባለ ሰው ድምጹ ጎርንኖ።

“እሱን ግዴለም፣ ግን ከማን ጋር ነው የምትሄደው?” አለ እንደከፋው።

“ከተክለሃይማኖት ጋር ተነጋግረንበታል። ግን የቁርጥ አይደለም።” አለ ዳኘው ተክለሃይማኖት ሊሄድ ቆርጧል ብሎ የገመተ ቢሆንም ጥያቄው እንዲህ ሲቀርብለት ቁርጥ ብሎ ያልሰማው ነገር እርግጠኛነቱ ምን ያህል እነደሆነ ተደናግሮት።

“ብትተወውና አገራችን ብንኖር.......... ባንለያይ ጥሩ ነበር።”

ዳኘው ጨዋታውን ወደ ሌላ በመቀየር ቁርጠኝነቱን አሳመነ።

እንዴት እንደሆነ ሁለቱም ሳያውቁት መተፋፈር ያዙ። ዳኘው ከወልደ ሰማዕት እየራቀ ከተክለሃይማኖት ተጠጋ። የወንድሙን ቦታ ጓደኛው እየወሰደው ሄደ። ከገጠር ወደ ከተማ፣ ከቤተ ዘመድ ኑሮ ወደ ባልደረብነት ኑሮ እየተጓዘ ነው። “የወንድም ፍቅር በጓደኛ የሚተካው በመራራቅ ነው። አንዱ ለአንዱ መጨነቅ፣ አንዱ ሌላው ምን ላይ እንዳለ ከለማወቅ የተነሣ ሲቀር ፍቅርም ይቀንሳል።” ሲሉ አባቱ የጫወቱት ትዝ አለው። ዳኘው ወታደርነት ተቀጥሮ እድሉን ለመሞከር አዲስ አበባ ለመሄድ ከተክለሃይማኖት ጋር ሲነሳ ከወልደ ሰማዕት ጋር የሚገናኙት ከዘመናት በኋላ መሆኑን ወይም ተለያይተው እንደሚቀሩ ለማሰብ እንኳ የባልደረቦች ጨዋታና የመንገዱ ሃሳብ አሳስቻለውም። የማያውቁት ነገር ፍራቻ ልቡን ሰልቦታል።

⅄ ⅄ ⅄

# አስካለ

አስካለ የብዙዎቸቹ እናት የተወለደችው በፀደይ ወቅት ነበር። ምድር በአበባና በለምለም ቅጠል ተሸፍና የደስደስ በሚታይበት ወቅት ነበር። የአደይ አበባ ወርቅማ ምንጣፍ ምድርን ያለብሳታል። የጎርጎው፣ የእንቧጨው አበባ ቀይ ፈርጥ ይጥልባታል። ሰማያዊ አበባዎች የጠፈርን መልክ እንደ መስተዋት ያንፀባርቁባታል። የሰዎችም ልብ በተስፋ ይሞላል። ኢዮሐ አበባየ መስከረም ጠባየ።

በፀደይ መጀመሪያ ሰዎች እሸቱን እየበሉ መኸራቸው እርግጠኛ መሆኑን በማወቅ ልበ ሙሉ ይሆናሉ። እንደ ልበ ሙሉነት ምን የሚያረካ አለ? አስካለ የተወለደችው በተስፋ ወቅት ነበር። የሰዎች ገጽታና መሬት የደስ ደስ በለበሰበት ወቅት የተወለደችውን ልጃቸውን ወልደ ዮሐንስና ፀዳለ አስካለ ብለው ሰየሙዋት። አስካለ በሚለው ስም ሁለቱም ከስምምነት ላይ የደረሱት ለስድስት ወራት ስሙዋ እከሌ መሆን አለበት የለበትም በማለት ሲጨቃጨቁበት፣ አንዳንዴም ሁለት ስም ሲሰጡዋት ከከረሙ በኋላ ነበር። ለመስቀል በዓል ቤታቸውን ቄጤማና አደይ አበባ በጎዘጎዙ ጊዜ ትንሽዋንም ልጃቸውን እየተፈራረቁ እየታቀፉ በአደይ አበባ ቀንበጥ አጫወቷት። በትናንሽ እጆቹዋ አበባዎቹን ጨፍልቃ ወደ አፍዋ ልትወስዳቸው ስትል "ካካ! ካካ!" እያሉ እየሳቁ ይነጥቁዋታል። መልሰው ግን ሌሎች አበቦች ይሰጡዋታል። ትንንሽ እጆችዋና ጣቶቹዋ ሲጨብጡ ሲያዩ ደስ ይላቸዋል። ወልደ ዮሐንስ ትንሹዋ ልጁ ፈገግ እንድትልለት የማያደርገው ነገር የለም ነበር። የሳቀችለት ጊዜ ደስታው ፈንቅሎት "አይ ሳቅና ሰው!" ሲል ሳያስበው ጮሆ ተናግሮ አትኩሮ ተመልከቱዋት፣ የሱም ዓይን ይበላት ይመስል፣ ዓይኑን ሰበር ያደርጋል። እንግዶች ግን ካዩዋት በኋላ ከመጥፎ መንፈስም ይሁን ከመጥፎ ዓይን እንዲጠብቃት እንትፍ እንትፍ ይላሉ።

እስከ አምስት ዓመት እድሜዋ በወላጆቹዋ ዘንድ ብርቅዬ ሆና ቆየች። በአምስተኛው ዓመት ግን ፀዳለና ወልደ ዮሐንስ ቁርጥ ያለ ጠብ ሲጣሉ አስካለም ከአባትና እናትዋ ተለየች። ፀዳለ ልጁዋን ከወልደ ዮሐንስ ቤት ይዛ ጠፍታ ለእናቷ ለድንቅነሽ ሰጥታ፣ እሱዋ አዲስ አበባ ገባች። ወልደ ዮሐንስ ለልጁ ሲል ሊታረቅ የሞከረው ሁሉ ከሸፈ። ፀዳለ አዲስ አበባ ገብታለች። አዲስ አበባ የገባ ደግሞ አይወጣም። በአዲስ አበባ ውስጥ ሁሉም ከተሜነትን ተከትቦ፣ ከከተማው ቀልጦ፣ ተዋህዶ፣ ከገጠሩ እርሙን ቆርጦ፣ ይቀራል። አስካለም በአያቱዋ ቤት ከአክስቶቹዋና ከአጎቶቹዋ ልጆች ጋር ለመደች።

ሁሉም ልጆች ዘጠኝ ዓመት እስኪሆናቸው የቤተሰብ ቁጥጥር ስለማይበዛባቸ አስካለም ደስተኛ ነበረች። ልጅ ኲቲው ኲቲው ካሉት ይደነዝዛል ስለሚባል፣ አልፎ አልፎ ካልሆነ ሲያጠፉም ቢያዩ እንዳለየ ማለፍ የተለመደ ሲሆን፣ እንደ አስካለ አያት ደግሞ ሃብታቸው በተደላደለ ዘንድ፣ ልጅ የሚያደርገውን እንዳለየ ከማለፍ፣ ወደ ማዕድ ቤት፣ ወደ

ጉዋሮ አብዛኛውን ጊዜ እንዲያጠፉ ይደረጋል። ልጆችም ይህን ሁኔታ ይወዱታል። አስካለ በጣም ትወደዋለች። አዋቂዎች የሚሠሩትን ሁሉ በራሳቸው ጠባብ ዓለም መልካሙንና አፀያፊውን በመሞከር ከትልልቅ ሰው ሕብረተሰብ የመደባለቂያውን ወግ ያጠናሉ። አስካለም ከአጎትዋና አክስቶቹዋ ልጆችና ከመንደር ልጆች ብዙ ተማረች።

አንድ ቀን ወላጆቻቸው ለቁርባን ወስደዋቸው ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ የዚያን ዕለት መነጋገር፣ ውጭ መውጣት፣ ክልክል መሆኑ ቢነገራቸውም፣ አስካለና የአክስቶቹዋ ልጆች ነጋና ፋናዬ፣ ከቤታቸው ካለ ትልቅ ዋርካ ሥር ከሰሩት ጎጆ ሄደው ጨዋታ ያዙ። አስካለ የነፍስ አባት ቄስ ሆና፣ ጠብል ስትረጭ፣ ከመንደራቸው ልጆች አንዱ መጥቶ ሴት ቄስ አይሆንም፣ እኔ ልርጭባችሁ ብሎ ከአስካለ ውሀውን ተቀበለ። አስካለ ደስ ባይላትም ሁሉም ይርጭ፣ ይርጭ ሰላሉ ዝም አለች። ወንዱም ልጅ እንደ ቄሱ የሆነ ነገር ተንተባትቦ ጠበሉን ሲረጭ ፋናዬን በሃይል ስላፈሰሰባት ከሱዋ ጋር ተጣላና አባረሩት። ልጁ እንደሄደ "አቦ ደግ ናቸው።" አለች ነጋ ሁልጊዜ እናቱዋ ሲሉ የምትሰማውን ።

"ሲቆጡ ደግሞ ክፉ ናቸው።" አለች አስካለ። አቡየ መንፈስ ቅዱስ ቀሰፋዋቸው የሚባሉ ብዙ ሰዎች ታውቃለች።

"የለመኑዋቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። እጅሽን እንደዚህ ታደርጊና፣" አለች ነጋ እጅዋን ከደረቱዋ ላይ ዓይኑዋን ወደ ሰማይ አቅንታ። "ስትለመኛቸው ያዝኑልሽና የጠየቅሽውን ሁሉ ያደርጋሉ።" አለች ጡዋት የጎረቤታቸው ሴት እንደዚያ ሲፀልዩ አይታ ያዘነችላቸውን እያስታወሰች።

"እስቲ እንለምናቸው።" አለች ፋናዬ።

"ምን?" አለች ነጋ። በዚች ቅጽበት የሚያስፈልጋት ነገር አልታይ ብሎዋት።

"አቦ አባታችንን እንዲገድሉዋቸውና እኛ ነገ ጭፋሮ እንድንሄድ። ብንፈልግ አዳባይ ወንዝ እንድንወርድ።" አለች ፋናዬ፣ ይኸን ሁሉ እንዳታደርግ የሚከለክሏትን አባትዋን በዓይነ ህሊናዋ አይታ።

ሕፃናቱም ወላጆቻቸው እንደሚያደርጉት የአቦ ቤተ ክርስቲያን ከግቢያቸው ሆኖ ስለሚታይ፣ ጣሪያውን እየተመለከቱ፣ ከንፈራቸውን እየመጠጡ፣ ነጋ እንዳለችው ትንንሽ እጆቻቸውን ከደረታቸው ለጥፈው፣ እነ ፋና አባታቸውን እንዲገድልላቸው፣ አስካለ አጎቱዋን እንዲገድልላት ለመኑ።

በነገታው ጡዋት ከመኝታቸው ሲነሱ አቦ የተለመኑትን እንደሚያደርጉ አልተጠራጠሩም። ፋናዬ የሞቱትን አባቱዋን ለመመልከት ቸኩላ፣ በዚያው የክት ልብሱዋን ልታወጣ፣ ወደ አዳራሹ ተዝናንታ እየሮጠች ስትገባ፣ በብልግናዋ የተናደዱት አባት፣ ከሚደግሙት ዳዊት ቀና ብለው ምን ያስሮጥሻል፣ በሚል ዘይቤ ዐይናቸውን በማጉረጥረጥ ተቀበሏት። እጢዋ ዱብ ብሎ እንደሰረቀች ውሻ ሹልክ ብላ ከአዳራሹ ወደ እህቶችዋ ተመልሳ በትልቅ ተስፋ መቁረጥ "እኝህን አባባ አቦ አልገደሉአቸውም።" ስትል መርዶውን

ነገረች። የቀልድ የመሰላቸው አስካለና ነጋም፣ ወደ አዳራሹ ብቅ ብለው ሲመለከቱ፣ የሚደግሙትን ዳዊታቸውን አጣጥፈው ሲነሱ ደርሰው ደንግጠው ተመለሱ።

ሦስቱም ሕፃናት በትልቅ ተስፋ መቁረጥ በትልቅ ንቀት አቦን "ድሮስ የዚያ የፈሪ ወንድም አይደሉም?" አሉ። በአለፈው ጥምቀት በዓል የአቦን ታቦት ተሸክመው የነበሩት ቄስ፣ ጠብ ተነስቶ፣ ሲሸሹ፣ አንድ ቀን አይተዋቸው፣ ፈሪ የሚሉዋቸው ሲሆን፣ በነሱ አእምሮ ደግሞ ቄሱ፣ የአቦ ወንድም ናቸው።

አስካለ የልጅነት ልምዱዋ ምንም ይሁን ምን፣ ስታድግ ግን ሃይማኖተኛ ሆነች። ከአደገች በኋላ ከፋናዬና ከነጋ ጋር ስትገናኝ የልጅነታቸውን ድፍረት አንስታ የምትስቀውም፣ በነፍስ ማወቅ ሃይማኖት አጥባቂነቱዋ ስለምትመካ ነበር።

አስካለ ከአደገች በኋላ ብዙ ጊዜ ከአጎቶቹዋ ልጆች ጋር ብትውልም እናቱዋ ፀዳለ አዲስ አበባ ከሄደች በኋላ በሞግዚትነት ያሳደጉዋት ከጀሌ የሚባሉ፣ ከወላይታ የመጡ ሴት ነበሩ። አያቱዋን ድንቅነሽን የምታያቸው አንዳንድ ቀን ነበር። ከጀሌም አስካለን እንደ ልጃቸው እንደ ሳቆቴ ያህል ይወዱዋታል። አስካለም እናት ብላ የምትቆጥራቸው ስለነበር በጣም ተቀራረቡ። አስካለ የእናቱዋን ቋንቋ ያህል ወላይትኛ ቋንቋ ያወቀችው ለዚህ ነበር።

ከጀሌ አረፍ ብለው ሲቀመጡ አስካለን ይጠሩዋትና በጉያቸው ደብቀው ይዘው ካመጡላት ጠላ ይሰጡዋትና፣ "ይችን ዝም ብለሽ ጠጪ።" ይሉዋታል። እመት ከጀሌ ጠላ ቤት ስለሆኑ ጠላ ያገኛሉ። በተለይ ማታ ማታ መብራት ስለማይኖር፣ ሰው ሁሉ ዙሪያውን ቁጭ ብሎ እርስ በርሱ ሳይተያይ በሚያወራበት ሰዓት፣ ከጀሌም ለአስካለ ስለ አያቶቹዋ ስለሚያወሩዋት፣ ብዙ ለማወቅ ቻለች። ከጀሌ ከአያትዋ ከእርገጤ ጋር ከጋሞ ጀምረው እስከ መንዝ ብዙ የተመላለሱ ስለሆነ በወሬም የሰሙት፣ በዓይንም ያዩት፣ ብዙ ታሪክ ነበራቸው።

ከጀሌ ሁልጊዜም ጨዋታ ሲጀምሩ "አይ ደጉ ጊዜ፣" ብለው ሲሆን፣ በጨዋታቸውም መሃል ስለ አለፈው ደጉ ጊዜ ተፀፅተው ከንፈራቸውን ብዙ ጊዜ መጥጠው፣ ሲደመድሙም ስለ ደጉ ጊዜ አውስተው ነው።

"ደጃዝማች ኃይሉ ዘንድ ጌቶች እርገጤ በወታደርነት ለማደር አስር ሆነው ሌሊቱን ሲጓዙ አድረው ሲነጋጋ ደከሙዋቸው ቁጭ ካሉበት ሁለት ሴቶች ሲያልፉ ተመለከቱ፣ አሉ። አይ ደጉ ጊዜ፣ ሰው እንደ አሁኑ ሸረኛ አልነበረም።" ይሉና እርገጤ አንድ ጊዜ አጋጠመችው ስለምትባለው ሴት ለአስካለና ለሳቆቴ ያወሩዋቸዋል።

እርገጤ ንብዋሻ ገባር ከነበሩት ኦሮሞና አማራ ድብልቅ ቤተሰቦቹ፣ ድህነት አስመርሮት፣ ደጃዝማች ኃይሉ ዘንድ ወታደርነት ለማደር ከአገሩ ጠፍቶ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ፣ ከዚያም እሳቸው ይገኛሉ ወደተባለበት ወደ ጋሞ ከሌሎች አስር ሰዎች ጋር ሌሊቱን ሲጓዝ አድሮ፣ ሲነጋጋ፣ ከጓደኞቹ ጋር ደክሞት ቁጭ ካለበት ሁለት ሴቶች ሲያልፉ ተመለከተ።

እውነቱን ተጠራጠረ። የነፍስ አባቱ ሰይጣን፣ ክፉ ሃሣብ፣ በሴት፣ በእንቅፋት፣ በአውሬ እየተመሰለ እንደሚገለጽ ነግረውት ነበር። ያሁኑ ክስተት ግን የሚያስደንቀው ብቻ ሳይሆን፣ ልቦናውንም የሰወረው ነው። ልብ ከተሰወረ ባሕል፣ ወግ፣ ሐጢዓት፣ መች ከስሜት ያደናል? አንደኛዋ ላይ ዓይኑ አተኮረ።

ትከሻዋ ጉርብጥብጥ ሳይኖረው እንደተወለወለ መስተዋት እያንፀባረቀ ከቀጭን ወገቡዋ ተገናኝቱዋል። ቀጭን ወገቡዋ ከዳሌዋ ሲደርስ፣ ዳሌዋ ብቻውን የቆመ ይመስል፣ ከሕብለ ሰረሰሩ መጋጠሚያ ሰርጎድ ብሎ ወደ ጎንና ወደ ጎን ሰፍቶ፣ ኮርቶ፣ ከወፍራም ባቶቹዋ የሚወርድና የሚወጣ ይመስል በእንቅስቃሴዋ ልዩ ጨዋታ ይጫወታል። ልብስ ለካስ ስንት ውበትን ይሸፍናል? የሚያምረው ክፍል በልብስ ይሸፈናል ብሎ አስቦ ትኩር ብሎ እየተመለከታት ምራቁን ዋጠ። ከመንገዱ መጠምዘዣ ስትደርስ ፊቱዋን ወደ እሱ አዙራ ትንሽ ተራምዳ ቆመች። አጎጥጎጤ ጡቶቹዋን፣ ስርጉድ ያለ አንጀቱዋን ተመለከተና እንደ ሕፃንነቱ በደረቱዋ ላይ ሊለጠፍ ተመኘ። እግሮቹ ሲደዝዙ፣ መላው ሰውነቱ እንደ መንቀጥቀጥ ሲል ተሰማው። አትነቃነቅም እንዴ ሲል አሰበ። እስካሁን ቀና ብሎ ፊቱዋን አልተመለከተም። ወደ ሰዶም ዘወር ብላችሁ ከተመለከታችሁ ጨው ትሆናላችሁ ብለው እንዳስፈራሩት ሰው፣ ፊቱዋን ለማየት አልደፈረም። ንቅናቄዋ መቆሙ ግን…ሌላም አንዳች ነገር ስቦት ቀና ብሎ ተመለከተ። ዓይኖቹዋ ላይ ንዴትና ጥላቻ አነበበና መጥፎ ቅዠት መስሎት አማተበ። ወዲያው ግን እየጮኸች፣ እየተወራጨች ተጠግታ፣ ጆሮ ግንዱን በጥፊ አጮለችው። ደንግጦ፣ ፈዝዞ ጉንጮቹን ይዞ አካባቢውን ተመለከተ።

ጓደኞቹ ሠረቅ እያደረጉ እየተመለከቱት በሳቅ ይንፈራፈራሉ። ቀድሞም ይስቁ ነበር እንዴ? ብሎ አሰበ። መጥፎ ሕልም ነው አለ። አማትቦ ተመለከተ። ወንድ አፈረው የሚባለው ጓደኛው ከአጠገቡዋ ቆሞ ሴትዮዋን በቋንቋዋ ሲያነጋግራት አስተዋለ።

የዚያን ሰሞን ጨዋታው፣ ቀልዱ ሁሉ በሱ ነበር። እሱም ከዚያ ወዲህ እራቁታቸውን የሚያያቸውን የአካባቢውን ሰዎች አፍጥጦ መመልከቱን ተወ። እንዳንድ ጊዜ ብቻ ሰው መጀመሪያ እንደተፈጠረ የሚኖርባት ገነት ምን ትመስል እንደነበር ትንሽ ያስባል።

"ራቁታቸውን መሆናቸውን አወቁ……." ሲሉ ነፍስ አባቱ አንደ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያነበቡለት ትዝ ይለዋል። አዳምና ሔዋን እፀ በለስን፣ የእውቀትን ዛፍ ከበሉ በኋላ የተገለጸላቸውን ግንዛቤ እያሰላሰለ "እሱዋም እራቁቱዋን መሆኑዋን አንድ ቀን ታውቃለች። ….ውብቱዋን ትሸፍነዋለች … ትሰለጥናለች…. እንደ እኛ ትሆናለች፣" እያለ ቁና ቁና ይተነፍስ ነበር። እድሜውን ሙሉ ያን አጋጣሚ ረስቶት አያውቅም።

ከጀሌ ግን ስለዚህ ታሪክ ለነአስካለ ያወሩአቸው፣ እንዴት ሴት ኩሩ እንደ ነበረች፣ ወንዱም ጨዋ እንደነበረ፣ አይ ደጉ ጊዜ አለፈ፤ ጌቶች ሲያስታውሱት ይስቃሉ። አይ ደጉ ጊዜ። እያሉ ነበር።

ሌላ ጊዜ ደግሞ ከጀሌ ስለ ሁለቱ አያቶቹዋ ያጫውቱዋታል። የዚያን ጊዜ አባትሽ (ወንድ አያቱዋን አባትሽ ሴት አያቱዋን እናትሽ ይላሉ) እሜቴን ጠልፈው ነው የወሰዱዋቸው አሉ። አይ ደጉ ዘመን አለፈ። ይሉና የሰሙትን ሁሉ ደግመው ያወሩዋታል።

እርገጤ በነፍጠኝነት ዘመን፣ ማለትም፣ ከፊውዳሊዝም ወደ ኢንደስትሪያዊ ሕብረተሰብ የመሸጋገሪያ ዘመን፣ በወታደርነት ብዙ ሃብት ሊያገኝ ቻለ። በኢተዮጵያ ፊውዳሊዝም እንደ ምሥራቃውያን ፊውዳሊዝም ሁሉ፣ የቤት ባሪያዎች በብዛት የታዩበት ስለሆነ፣ ባርነት በአዋጅ በተከለከለበት ዘመን እንኳን ቅሪቱ አልጠፋም ነበር። እርገጤ በደቡብ ባሳየው አገልግሎት ምሥጋና ለመቀበል አጼ ሚኒልክ ዘንድ ሲቀርብና ምን ሊደረግለት እንደሚፈልግ ሲጠየቅ፣ ጥንት ከኦሮሞ አያቱ ተወስዶ የቤተርስት የሆነው፣ አንቀላፊኝ የሚባለው የንብዋሻ መንደር አካባቢ፣ እንዲሰጠው ለምኖ፣ ተፈቅዶለት አገሩ ተመለሰ። ሻለቃነትም ተሰጥቶት ስለነበር እሱ የዳኘው ባሪያ፣ እያለ እንደሚፎክረው፣ የእርገጤ ባሪያ እያሉ የሚፎክሩ፣ ባሪያ አከል፣ የአማራ፣ የወላይታ፣ የጋሞ ወታደሮች ነበሩት። በቤትም ውስጥ በጦርነት ላይ የማረካቸው፣ በሕግ ሳይሆን በድብቅ ባሪያ ያደረጋቸው፣ የቤት ሠራተኞች ነበሩት። ከጀሌ ለነአስካለ ስለዚህ ሲያወሩላቸውና አይ ደጉ ዘመን አለፈ ሲሉ፣ አስካለ ከእርገጤ በፊት የነበረው ወይም ከእርገጤ ጋር ከጀሌ ያሳለፉትን ጊዜ እንደሆነ ይደናገራት ነበር። ስለ አያቶቹዋ እመት ድንቅነሽና እርገጤ ጋብቻ ያወሩት ግን የተቆራረጠ ቢሆንም ደስ ይላት ነበር።

እርገጤ ከንብዋሻ እንደተመለሰ አንድ ጊዜ ዘመድ ሊጠይቅ ባሻገሩ መንደር ወግዳ ሄዶ ድንቅነሽን አገኛት። ድንቅነሽ የሩቅ ዘመዱ ናት። ቀደም ሲል የኦሮሞዎችን ግፊት ለመቋቋም እያንዳንዱ ቤተ ዘመድ እራሱን ለማጠናከር በሩቅ ዘመዳሞች መሃልም ጋብቻን ከልክሎ ስለነበር፣ እነዳያት ቢወዳትም፣ ችግር ገጠመው። የዚያን ዕለት ግን ድንቅነሽን ሲያሽኮረምም እንደነበር ሰዎች ያወሩበታል። በግብዣው ላይ ሞቅታ እንደሰፈነ ጭፋሮ ሲጀመር እርገጤም በየስንኞቹ መሀል እየሠረቀ እየተመለከታት፣

ከባቄላው ሜዳ እንውረድ ግርግራ

ከአውላላው ሜዳ እድንግል ተራራ

ወይ እንደ ነፍጠኛ እንውረድ አዳባይ

ወይም እንደ አሞራ ይዤሽ ወደ ሰማይ

እያለ ሲዘፍን እሱዋም አፍራ ነበር።

ከዕለታት አንደ ቀን ኃይለኛ ዝናብ ሲዘንብ፣ ስለ ደቡብ ዘመቻ እያወራት ከቀየ በኋላ፣ በቤተሰቦቹዋ አለመኖር፣ ኑዋሪነቱ አዲስ አበባ በመሆኑና በኃይለኛው ዝናብ የተደፋፈረው እርገጤ፣ መብረቅ ሲጮህ፣ እሱዋ ፈርታ ስታቀረቅር፣ እሱ ለችግር የደረሰ መስሎ አቀፋት። እንዲያሻሻት የፈለገች ይመስል ዝም አለችው። ጀርባዋን አንድ ጊዜ ወደ ታች ዳሶት ሊደርስበት የማይችል ልዩ አስደናቂ ውበት በእጁ መዳሰሱ ተሰማው። ደጋግሞ አሻሽቶ ይበልጥ ድንቅ፣ የማትመረመር፣ ሊደርሱባት የማይቻል የእግዜር ጥበብ ሆና ተሰማችው።

የሱዋም እጆች በአንገቱ ላይ ተጠመጠሙ። እሺ አትለኝም ብሎ ስንት የፈራው ልቡ ሰገደላት። እሱዋም ሁለመናዋን ሰጠችው። ሁለት ዘመዳሞች ከቤተ ዘመድ ወግ ወጡ።

በዚያው ወር ስንዴውና ገብሱ ማሸት ጀምሮ፣ ንፋስ ሲነካው እንደ ወራጅ ውሀ ማዕበል እየሠራ ዘንፈል ቀና በሚልበት፣ ባቄላውና አተሩ ግማሹ አካሉ አፍርቶ፣ ጫፉ አበባ ሆኖ፣ በንፋስ ሲወዛወዝ፣ በድንጋያማ ቦታ እንደሚፈስ ውሀ ሲርገደገድ፣ ጨረቃ በውድቅት ሌሊት ወጥታ ከፀሐይ ጋር ሳትገናኝ በማትጠፋበት ሰሞን፣ ሁለቱ ፍቅረኞች ከቤተሰቦቻቸው ኮብልለው አዲስ አበባ ገቡ። የሩቅ ዘመዳሞችን ጋብቻ የሚከለክለው ወግ ፈረሰ።

እርገጤና ድንቅነሽ ይህን ደንብ ያፈረሱት ደንቡ ከወጣ ከሙቶ ዓመታት በኋላ ነበር። የኦሮሞዎችን ግፊት እያንዳንዱ ቤተዘመድ ለመቋቋም እራሱን ለማጠናከር ያወጣው ደንብ ነበር። እነሱ ባፈረሱበት ዘመን ግን አጼ ሚኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ሆነው ወሰኑ ሩዶልፍ ሃይቅ በደረሰበት ዘመን፣ እያንዳንዱ የመንዝ ሰው የኦሮሞ ደም ከተደባለቀበት በኋላ ነበር። ስለሆነም ባሕሉ መነሾው ካበቃም በኋላ ቢቀጥልም፣ ጠቃሚነቱ ስላለቀ፣ የባሕል ደፋሪዎች ቅጣት ላልቶ ነበር። ግዝቱን ጥሰው ግን ትውልድ ቦታቸው በዓይን ዓውጣነት ሊኖሩ ስለማይችሉ፣ ጉዳዩ እንዲበርድ አዲስ አበባ እርገጤ ቤት ገቡ።

እርገጤና ድንቅነሽ ከዚህ ግኑኝነት መጀመሪያ የወለዱት ልጅ ሁለት እጆቹ አጫጭር ነበሩ። በጭንቀቱዋ የተፈጠረ ሊሆን ቢችልም፣ ቤተ ዘመዱ ግን ግዝቱ ስለተሻረ ነው በማለት ሲያምን፣ ለሌላው ሰው መመፃደቂያ ሆኑ። የሆነው ቢሆንም ከትንሽ ዓመታት በኋላ እናትና አባትዋ ዘንድ ባይሆንም፣ድንቅነሽ ንብዋሻ መጥታ ለመኖር ቻለች። አዳባይን ተሻግሮ መሄድ፣ መኮብለል፣ ጥንት የማይታሰብ፣ የማይታለም፣ ሲሆን በአዲሱ ዘመን ለአስካለ አያቶች እንደ ቀለለ ሁሉ፣ ከቤተ ዘመድ ግዝት መውጣቱ በኋላም የቤተ ዘመዱን ይቅርታ ለማገኘት እምብዛም አልከበዳቸውም። ይቅርታ ጥየቃቸውን ሁሉም ዘመኑ ነው በማለት በምፀት ምህረቱን ሰጣቸው። ነፍስ አባቶችም፣ ጥንትም ቢሆን በመጽሐፍ ከሰባት ቤት በኋላ መጋባት አይከለከልም ሲሉ አሳረጉ።

የተቋቋመበት ወቅት የተወገደበት ወግ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሠረቱ ያለፈበት ሥርዓት፣ ሥር ስለሌለው እነሱም ሊያፈርሱትና ሊጥሱት የደፈሩት ወቅቱ መርቶአቸው ሲሆን፣ ይቅርታ ለማድረግም ይቅርታ አድራጊዎቹን ወቅቱ ስለመራቸው አላስቸገራቸውም። ዘመኑ ያልደረሰ ነገርን ቢያደርጉት መዓት ያስከትላል። ዘመኑ ካለፈበት ግን ጥፋትም ቢሆን ጥሩ ይቅርታ ሰጭ አያሳጣም። የሰው ልብ ይህን ዘመን ያውቀዋል።

ከጀሌም ስለ እርገጤና ድንቅነሽ የሰሙትን ወሬ ቀነጣጥበው አውርተው፣ “ከዚያም ሽማግሌ ተልኮ ታረቁ። እግዜር ሳይደግስ አይጣላም ይባል የለ። የዚያን ጊዜ ሰውም ደግ ነበር። ይቅርታ አደረገላቸው። አይ ደጉ ዘመን አለፈ።” ብለው ያሳርጋሉ።

በዚህ ማድቤትና በከጀሌ ዙሪያ ሳቆቴና አስካለ ዘላቂ ጓደኝነት መሠረቱ። አስካለና ሳቆቴ አንደኛቸው በሞት እስኪቀድሙ ድረስ ለረጅም ጊዜ የተለያዩት አስካለ በአስር ዓመቱዋ በጋሻው ለሚባል ሰው የታጨች ጊዜ ነበር።

ለአስካለ በጋሻው ጥሩ ወንድሙዋ ነበር። መጀመሪያም ያስተዋወቋት ወንድምሽ ነው ብለው ነበር። እሱም በቅርብ ከምታውቃቸው ወንድሞቹዋ በላይ ደግ ሆነላት። አብረው መኖር ጀምረው እንኳን ከወንድምነት ሌላ ሃሣብ እንዳለው አታውቅም ነበር። ጥሩ ጥሩ ያበላታል፣ ትንሽ የከፋት ጊዜ ቤተሰቦቼ ዘንድ ውሰደኝ ብላ ታለቅሳለች። መንገድ እንደጀመሩ ደከመኝ ስትል እንኮኮ ብሎአት ዘመዶቹዋን አሳይቶ ይመልሳታል።

ጠይቃው ያልፈጸመላት ነገር ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ነበር። አስካለ በሜዳ ላይ ስትጫወት ተምልክታው፣ ልትደርስበትና ክሥሩ ልትቆም የምትሻው ነገር ነበር። በተራራዎች በተከበበች የትውልድ መንደሩዋ ውስጥ ደመና አለፍ አለፍ ብሎ ሰማዩን ባስጌጠበት ወቅት በጉም በሩቅ በተሸፈነው ሰማይ፣ ፀሐይ ስትጠልቅ፣ በደመናው መሃል የጠራ ሰማይ ካለ ሰንጥቆ የሚያልፈው የፀሐይ ብርሃን፣ በጨለማ ውስጥ እንደተበራ ባትሪ ፋዋ ብሎ፣የግንድ ቅርጽ ይዞ፣ ወደ ታች ይወርድና አንድን አካባቢ በብርሃን ያለብሳል። ነገር ግን በጉም በተሸፈነ ሰማይ ቀዳዳ አግኝታ ሠርቃ የምታልፍ የፀሐይ ብርሃን ከሩቅ ሆነው ካልተመለከቱዋት ከሥሩዋ ሆነው ሊያዩዋት ስለማይችሉ፣ ለአስካለ አብርታላት አታውቅም። ከዚህ ዓይነት ቦታ ወስዶ እንዲያቆማት ለበጋሻው ላቀረበችለት ጥያቄም፣ በጋሻው ሊሳካለት አልቻለም ነበር። መጀመሪያም ጥያቄዋን ያቀረበችለት ዕለት አይ የልጅ ነገር ብሎ ሳቀ። አስካለም በንጭንጭ ልታስገድደው ስትሞክር በደንብ ሲቸገር አይታው ተወችው።

አስካለ ካደገች በኋላ እንደ የእየሱስ ጥምቀት ስዕል ደስ የሚላት አልነበረም። በጥምቀቱ ስዕል ላይ እየሱስ በወንዝ ውስጥ ሆኖ፣ በጉም ውስጥ የሰረቀች ፀሐይ የሚመስል በላዩ ላይ ሲያበራ፣ በውበት ላይ ውበት ተጨምሮለት፣ በእራሱ ላይ እርግብ አርፋበታለች። እግዚአብሔር ከደመናዎቹ በታች በጣቱ ሲያመለክት በስዕሉ ላይ ይታያል። አስካለ እርግቡና እግዚአብሔርን ሳይሆን በደመና ውስጥ የሰረቀችውን ፀሐይ ታተኩራለች። ከአዳባይ መልካ ፀሐይ ስታበራ ትዝታ ያመጣባታል።

ከንብዋሻ መንደር ቁልቁል አዳባይን መመልከት ከሁሉም ይበልጥ ሲያስደስታት፣ ከተራራዎች ላይ ተንደርድሮ ወርዶ አዳባይ ውስጥ ተንቦጫርቆ መመለስ ደግሞ ሌላ ደስታ ነው። የአባቱዋ አገር ገረገራ ደግሞ ጡዋት ጡዋት ፀሐይ ስለሚወጣባት ደስ ይላታል። ንብዋሻ መንደር ከአፋፍ ስር በመሆኑ እስከ አራት ሰዓት ድረስ ፀሐይ በመሬት ላይ የምትፈሰው ባሻገሩ ተራራ ላይ ካልሆነ ንብዋሻ ከመንጋቱ በቀር ፀሐይ አይገኝም። ጡዋት ጡዋት ሁልጊዜም ልጆች ቤታችን ባሻገሩ አፋፍ ላይ ቢሆን ኑሮ ፀሐይ ትሞቀን ነበር ብለው ይጓጓሉ። ንብዋሻ ተወልዶ አባቱን ከዚያ ማዶ ከፀሐይዋ እንሂድ ብሎ ሳይጠይቅ ያደገ የለም። ከገረገራ መንዝ ግን አዳባይን በጣም በርቀት፣ ቁልቁል እየተመለከቱ፣ ግርማ ሞገሱ

በልብ ውስጥ የሚፈጥረው ሞቅታ፣ አይገኝም። ሁሉም ቦታዎች የየራሳቸው ውበት አላቸው።

የልጅነት ዘመን ግን አንድ ደረጃ ላይ ያልፋል። ያንን ቀን በቅድሚያ የሚያውቀው የለም። ብቻ በስጋም በመንፈስም መለወጥ ይመጣል። አስካለ አስራ ሁለት ዓመት ሲሆናት እንደ ድሮዎ ከበጋሻው ጋር ስትጫወት እስከዚያ ያላስተዋለችውን አስተዋለች። ከዓይኑም ከፊቱም ትልቅ ፍራቻ የሚፈጥርባት ነገር አነበበች። እሱም ለመጀመሪያ ጊዜ ስታፍር ተመልክቱዋት፣ ልቡን ደስ አለው። እሱዋ በልጅነት ስሜቱን ለማስተዋል አለመቻሉዋ ገደቡ ሲሆን፣ መመልከት መጀመሩዋ ግን እሱዋም የልጅነት ዘመኑዋን እንደጨረሰች ማረጋገጫ ነበር። ከድምጹ ቅላጼ ሁሉ ከወንድምነት ሌላ ፍላጎት እንዳለው አነበበች። ሆኖም ሁልጊዜም እንደዚህ ነው የሚናገረው ብላ አሰበች። ጥርጣሬውን ለማስወገድ ደግሞ የመንደሩ፣ የቤቱ ሰው አለ። እሱም እራሱ ጥርጣሬዋን አስወገደው። ወንድሙዋ አለመሆኑን ተገነዘበች። ይህ የሽግግር ወቅት ግን የሁለቱንም ሕይወት ለወጠው። እስከ አሥራ አምስተኛው ዓመቱዋ እንደ ድሮው አለተቀራረቡም። በአሥራ አምስተኛው ዓመቱዋ ግን የመጀመሪያ ልጁዋን ከበጋሻው ወለደች። የበጋሻውም ቤተሰቦችም ትንሹዋን ልጅ ኩሪባቸው ብለው ሰየሙዋት። አስካለ ግን በጋሻውን በወንድምነት ብትወደውም፣ ያ ወንድምነት፣ ያ እህትነት፣ በአሁኑ ባልና ሚስትነት ሊተካ አልቻለም። በጋሻው ለዘላለሙ ወንድሙዋ ቢሆን ሁልጊዜም ከማንም ታስቀድመዋለች። ባሉዋ ግን ለዘላለም አይሆንም። ይህን የልቡዋን ሃሳብ ይፋ ያወጣው አጎቱዋ ኃይለማርያም እርገጤ፣ አባቱን ተክቶ ንብዋሻ ተሹሞ የመጣ ጊዜ ነበር። ኃይለማርያም የበጋሻውን ባልነት ማጥላላት ያዘ። አስካለም እስከ ዘላለሙ በጋሻውን ውድ ወንድሙዋ ብታደርገውም፣ በባልነት ግን ፈታው፣ ንብዋሻ ተመለሰች።

ንብዋሻ ከሳቆቴ ጋር አብሮ ሆኖ ሕይወት አስደሳች ሆነላት። 1928 ዓ.ም መጀመሪያ ነበር። ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር እንደሚያስብ በሰፊው ይወራል። ብዙም ሳይቆይ ሃይማኖት ለማፍረስ፣ እርስት ለመንቀል፣ ሚስቶችንና ልጆችን ለመድፈር፣ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መውረሩ ተሰማ። ይህንንም የግፍ ወረራ ለመቋቋም ሕዝቡ ለጦርነት እንዲነሳ ትዕዛዝ ተላለፈ። የሚሞቱላት አጥታ የማታውቀው አገርም ነፍጠኛው፣ ጭሰኛው፣ ባሪያው ከንዱን አስተባብሮ ተነሣላት።

በጥቅምት ወር 1928 ኃይለማርያም የራሱን ወታደሮችና ሃምሣ ዘመዶቹን አስከትሎ፣ ከንብዋሻ አፋፍ ጥሻ ወጥቶ ሜዳው አገር ወጣ። ዘማቾቹ ከንብዋሻ ጎራውን ወጥተው ጭልጥ ባለው ሜዳ የዘመዶቻቸውና የሸኝዎቻቸው ዓይን እየተከተላቸው እርቀው ሄዱ። እየራቁ ሲሄዱ እያነሱ እያነሱ ከዚያም ለዓይን ጠፉ። ሸኝዎቻቸውም ምርር ብለው አለቀሱ። ጎራውን ወርደው ወደየቤታቸው እንደ ለቅሶኛ በትካዜ ተመለሱ።

አስካለም ከአደማስ የሚጠልቁትን ዘመዶቹዋን እያስተዋለች አለቀሰች። እርቀው የሚሄዱት ዘመዶቹዋ የሚያልፉትን መከራ እንጂ፣ የሱዋ እድል ምን እንደሚሆን እንኳን አላሰላሰለችም። ብቻ ያ ዘመን፣ በሕይወቱዋ ላይ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ገባት። ችግር

ሊመጣ ሲል፣ ከመድረሱ በፊት፣ በሰዎች ላይ እንደሚነበበው የግዴለሽነትና ለራስ መጨነቅ መተው መንፈስ ሰፈነባት። ለመስዋዕትነት መድረኩ ይህ ነው። ለብዙዎቹ ይህ ስሜት ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከሰመላቸው። አስካለ ግን ለቀጣዮቹም ዓመታት በበሽታው ላይ ግርሻው እየጨመረባት ሄደ።

⅄ ⅄ ⅄

# ማንም ሰው ከሕሊናውና ከባሕሉ ሸሽቶ አያመልጥም

በየዓመቱ እንደ ወቅቱ የመሬት ገጽና የአየሩ ጠባይ ይለዋወጣል። ገበሬዎች ወቅቱን በመከተል ከተፈጥሮ ጋር በመታገል የተፈጥሮን መልክ ይቀይራሉ። በዚህም ያመርታሉ። በጥንት ጊዜ በተፈጥሮ በመስከረም አደይ አበባ ይለብስ የነበረው መሬት እያደር ገበሬዎች በዘሩአቸው እህሎች አበባ ይዥጎረጎራል። በአጠቃላይ ግን በወቅቶች መለዋወጥ፣ በክረምቱ መጀመሪያ መሬቱ አረንጓዴ ቀለም ሲለብስ፣ በነሐሴና በመስከረም በአበባዎች ይሸፈናል። በህዳርና በታህሣሥ መኸር ተሰብስቦ አፈሩ ለፀሐይ ይጋለጣል። በጥር በየመንደሩ በብዛት ችምችም ብለው ያሉት ባለወተት ቁልቋሎች ያፈሩና በቀይ ቀለም መንደሩን ያለብሱታል። ደኖችና ጢሻዎች በጎርጎ ዛፍና በእንቧጮ አበባ፣ ቀይ ይሆናሉ።

ተፈጥሮ መልኳን በዚህ ዓይነት ስትለዋውጥ፣ የሰዎችም መንፈስና ሕይወት ተከትሏት ይለወጣል። በክረምት ወቅት ወንዶች እርሻ ላይ ከጡዋት እስከ ማታ ሲጠመዱ፣ ሴቶች አረም ለማረም ከጡዋት ጀምረው እየተወናፈሉ በአረንጓዴዎቹ ሰብሎች መሃል አለፍ አለፍ ብለው ሲያርሙ ይታያሉ። ዝንጀሮዎች በሚያጠቁዋቸው አካባቢዎች ግማሾቹ ልጆች ጦጣና ዝንጀሮ ሲጠብቁ፣ ግማሾቹ ልጆች በእረኝነት ይሠማራሉ። በዚህ ጊዜ በክረምቱ ድሃ ጭሰኞች ከሥራው ከባድነት ጎን፣ እስከ ቤተሰቦቻቸው የሚበሉት እያጡ፣ በበዶ ሆድ እርሻም ስለማይሆን፣ በከፍተኛ ወለድ ከሃብታሞች እህል ይበደራሉ። ክረምቱ አልፎ የመኸር ወቅት ሲደርስ፣ በእሸቱ ተስፋ በማድረግ የሰዎች ልብ ይታደሳል። የደስታ ፊት ይታያል። የአደይ አበቦች ይፈካሉ። ፀደይ የደስ ደሱን ይዞ ይመጣል። የመኸር ጊዜ ያልፍና ከየካቲት ጀምሮ ሰብሉ ጎተራ ከገባ በኋላ፣ በልግ ካልበለገ፣ እስከ ግንቦት ድርስ፣ በመስክ ላይ መሥራቱ ይቆማል። እንጨት መሸከም፣ አጥር ማጠር፣ ቤት መሥራት፣ ይቀጥላል። በእህል ዘር ተሸፍኖ የነበረው መሬት ቡና ዓይነት ቀለም ይለብሳል። መረሬው አፈር ይሰነጣጠቃል። የሰዎችም ልብ በፀሐይ ሐሩር ይደከማል።

ዳኘው ከትውልድ መንደሩ ኮብልሎ አዲስ አበባ ለመግባትና ወታደርነት ለመቀጠር ያሰበው፣ ወታደርነት ከግብርና ይልቅ የሚያስከብርና ሃብት የሚያስገኝ ነው ብሎ በማመኑ ብቻ ሳይሆን፣ የገጠር ኑሮ በየዓመቱ የማይለዋወጥ፣ አሰልችም፣ በመሆኑ ነው። በአሥራ ሁለቱም ወራት ሰውን የሚጠብቁት ሥራዎች የታወቁ ናቸው።

ከዚህም በቀር ከከተማ ሰዎች ሲመጡ ስለ ወታደርነት ጥቅም ብዙ ያወራሉ። በተለይ ከከተማ ወደ ትውልድ መንደሮቻቸው ሲመጡ፣ ለማስቀናት እንደሚያደርጉት ያህል፣ ከተማውን ሲያሞካሹትና ጨርቅና ገንዘባቸውን ሲያሳዩ ሌላ ነው። ዳኘውና ተክለሃይማኖት ለረጅም ጊዜ ሲያወጡ፣ ሲያወርዱ ቆይተው፣ ለምን እንደዚያ እንደተቀየሩ እንኳ ሰው ግራ እስኪገባው፣ በሆነ ባልሆነው ነገር አልለያይ ብለው ከርመው፣ የመሄጃቸውን ቀን ቆርጠው፣ ተክለሃይማኖት ሌሊት መጥቶ ዳኘውን እንዲቀሰቅሰው ተስማሙ።

ዳኘውና ተክለሃይማኖት ምንም ያህል ቢያወላውሉም በመጨረሻ ተገናኝተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ጎበዝ ፍራቱ ከዓላማው እንዳያግደው ለማድረግ ቢችልም፣ መፍራቱ ስለማይቀር፣ ጉዞአቸውን ቢጀምሩም፣ በሃሳብ ተውጠው፣ ጨዋታ አይጫወቱም ነበር። አዳባይን ሲሻገሩ እንኳን አልተነጋገሩም። ከወንዙ እንደወጡ ተክለሃይማኖት "ያ ጠንቋይ ለአዝብጤ የተናገረው ትንቢት ደረሰለት።" አለ።

"ምን ትንቢት ነበር የተናገረው?" አለ ዳኘው በሃሰብ ቢዋጥም መልስ ሰጥቶ።

"ወንድ ልጅ ትወልዳለህ ብሎት አልነበር?" አለ ተክለሃይማኖት ጨዋታውን ለመቀጠል።

"ሲመኘው የነበረው ደረሰለት።" አለ ዳኘው ያልቾገረውን ወሬ በመስማቱ እያዛጋ።

"አንተም ከሸዋንግዢው ወንድ ልጅ ትወልዳለህ።" አለ ተክለሃይማኖት አሁንም ጨዋታውን በመቀጠል።

"አንተም ጠንቋይ ትባላለህ።" አለ ዳኘው ወደ ሃሣቡ ለመመለስ ቸኩሎ።

ሸዋንግዢው ለዳኘው አባቱ የመረጡላት እጮኛው ናት። ሸዋንግዢው እቤታቸው እንኳ ተልካ ስትመጣ ተዝናንታ ትጫወታለች። ዓይን አፋር በመሆኑም ይሁን ወይም ሰው ናቂ፣ ዳኘው ሁልጊዜም ሴቶች ባሉበት እምብዛም አይዝናናም። አባቱ ካጩለትም በኋላ በየትኛውም ቦታ ሲገናኙ በደንብ አድርጋ ትመለከተዋለች። ግዴለሽነቱዋ፣ ቁርጥ ያለ ነገርዋ፣ ተጫኝነቱዋ፣ ሁሉ ለሱ ግድ እንደሌላትና እንደማትወደው ማረጋገጫ ይመስለዋል። እሱ እንደምትወደው በግልጽ የምታሳየውን፣ በዓይን አፋርነቱዋ፣ በቅልስልስነቱዋ፣ ውብ የምትሆንበትን ሴት የሚፈልግ ነው።

"አዲስ አበባ ሴት ጠፍቶ እሱዋን ተመልሼ እወስዳለሁ?" አለ ዳኘው ለተክለሃይማኖት መልስ።

"ለምን ያንን ጠንቋይ አትጠይቀውም ነበር።" አለ ተክለሃይማኖት በሆዱ የሚብላላውን ሃሳብ ለመግለጽ አፍሮ ዳር ዳር እያለ።

"አንተ ጠይቀኸዋል?" አለ ዳኘው። የተክለሃይማኖት ነገር ግራ አጋብቶት።

"አልጠየኩትም፣ ግን እጠይቀዋለሁ።"

"ከአዲስ አበባ ወታደር ሆነህ ስትመለስ?" አለ ዳኘው በማሽሙዋጠጥ፣ በቀልድ።

"ለምን ተመልሰን ሰለ እጣችን ጠይቀነው፣ ነገ ወደ አዲስ አበባ አንሄድም?" አለ ተክለሃይማኖት እንደማፈርም፣ እንደ ቀልድም እያደረገ።

ዳኘውም ብዙ አላቅማማም። የማያውቁት አገር፣ የማያውቁት መንገድ፣ የማያውቁት እድል፣ ሆዳቸውን ስላባባው ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ተመልሰው አገራቸውን ለማየት ስለፈለጉ፣ በቂ ሰበብ ያገኙ መስሎአቸው፣ መልሰው አዳባይን ተሻግረው፣ ከአገራቸው፣ ከቀያቸው ካለው ጠንቋይ ቤት ለመሄድ ፊታቸውን መለሱ።

"የዛሬ ሌሊት መኝታ፣ እንቅልፍ፣ አይበለው።" አለ ተክለሃይማኖት ከወንዙ እንደገና ተመልሰው እንደገቡ። "እንቅልፍ ጥሎኝ ቀጠሮየን አፈረስኩ ለማለት ዳድቶኝ ነበር።"

ዳኘው የኮረኮሩት ያህል ከት ብሎ ስቆ "እኔም አፍሬ እንጂ ተኝቼ አላደርኩም። አስር ጊዜ እየተነሳሁ መንገዱን ስመለከት ምነው ቀጠሮውን ረስተኸው በቀረህ እያልኩ ስመኝ ነበር።" አለ።

ሁለቱም ተያይዘው ሳቁ። ጥብቅ ጓደኝነት ያለው መልካም ነገር መተፋፈር ሳይኖር የልብ ጥልቅ ምስጢርን፣ ጭንቀትን፣ እየተገላለጡ መሳቁ ነው።

ፀሐይ ልትጠልቅ ስትል ከጠንቋዩ ቤት ደረሱ። ዙሪያውን በመደብ ከተከበበው ክብ ቤት በስተበራፉ በኩል፣ ጠንቋዩ ጋቢውን ተከናንቦ፣ እሳቱን ይሞቃል። የሚጠነቁለው በትርፍ ጊዜው ስለሆነ አንጃ ግራንጃ የበዛበት አካባቢ የለውም። ተክለሃይማኖትና ዳኘው እንደገቡ በመደቡ ላይ ተቀምጠው ስለቤተሰቦቻቸው ደህንነት እንግዶቹና ባልተቤቶች ከተጠያየቁ በኋላ፣ የመጡበትን ጉዳይ ተነጋገሩ።

"ወታደርነት ልንገባ ፈልገን ነበር። እርሰዎ ይታየዎታልና እባክዎ ይንገሩን።" አለ ተክለሃይማኖት ስለ ሁለቱም ሆኖ በመናገር።

"ዳኘው ወታደርነት አይሆንህም።" ሲል ጀመረ ጋቢውን እስከ አፍንጫው የተከናነበው ጠንቋይ። አፉን ነፋስ እንዳይነካው የፈራ ይመስላል። "ሸውንግዥሮውን አሁን አላገባትም ብለህ ታስባለህ። ግን ታገባታለህ። ከሱዋ ወንድ ልጅ ትወልዳለህ። በመጀመሪያ ግን ወንድ ሳይሆን ሴት ከወለደች ትሞታለህ።"

"ከበፊተኛው ባሉዋ ወንድ ነው የወለደችው።" አለ ተክለሃይማኖት። ጠንቋዩ ሁለቱንም ትንሽ አስተዋላቸውና "ከዚያም ሸዋንግዥሮውን ፈተህ ከኦሮሞ [4] ባላባት ደም ያላት ሴት ታገባለህ። ከሱዋም ወንድ ልጆች ትወልዳለህ፤ በእርሻም ሃብታም ትሆናለህ። ወታደርነት ከገባህ ግን አገርህ ባዶ እጅህን ትመለሳለህ።" አሁንም ንግግሩን አቁዋርጦ

[4] ቀድሞ በተጀመረው ለመጨረስ የተቀየረ

መዓት የተመለከተ ይመስል ድንጋጤ በሚነበብበት ፊት ወደ ተክለሃይማኖት ዞወር ብሎ "ወታደርነት እጣህ አይደለም። ወታደር ከሆንክ ትሞታለህ፤" አለና ራሱን ጉልበቱ ላይ ደፋ።

ሁለቱም ብዙ ጥያቄዎች ነበሩአቸው። ዳኘው የኦሮሞ[5] ደም ያላት ሚስቱ የምትሆነው ሴት መልኩዋ፣ ስሙዋ፣ አገሩዋ ሁሉ እንዲነገረው ለመጠየቅ ተክለሃይማኖትም ማ እንደሚገድለው ለማወቅ ቸኩሏል። ጠንቋይ ግን ይህን አይናገርም። ጠንቋይ የሚናገረው በአጠቃላይ መድረሱ የማይቀረውን እምብዛም የማያጠራጥረውን ወይም ተቃራኒዎችን በመናገር ከሁለቱ አንዱ እንዲይዝ በማድረግ ነው። ሰው የወደፊቱን ለማወቅ ሃይለኛ ጉጉት ስላለው ስለዚህ ጉዳይ አውቃለሁ፣ የሚል ሰው፣ ሲያገኝ ግን ለማዳመጥ የፈጠነ ነው።

"እውነቱን ሊናገር ሲጀምር ይፈዛል።" አለ ተክለሃይማኖት ጠንቋዩ የማይሆን ነገር ከተናገረ በኋላ የሚመስል ነገር የተናገረው ትዝ ብሎት።

"እንደፈለገ።" አለ ዳኘው ጉዞ የመጀመራቸው፣ የመመለሳቸው ቀጥሎ ሊደረግ የሚገባው ነገር ሁሉ፣ ግራ ገብቶት።

ሆኖም ዳኘውና ተክለሃይማኖት በ1916 ላይ አዲስ አበባ በቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ ወልደ አብ[6] ባልደረብነት የጥይት ቤት ዘበኛ ሆኑ። በክብር ዘበኝነት ደንብ ብዙም ሳይቆይ የግቢ ጠባቂ ሆኑ።

የተክለሃይማኖት አባት ወደ ከተማ ስለማይመጡ ተክለሃይማኖት ሄዶ ይቅርታቸውን ለመጠየቅ ያስባል። የተክለሃይማኖት አባት ቄስ ስለሆኑ የውትድርና አገልግሎት ግዴታ የለባቸውም። የዳኘው አባት ግን ከአባት በወረደ ደንብ፣ በመንግሥት ደንብ መሠረት፣ በዓመት ለአንድ ወር አዲስ አበባ እየመጡ ዘብ ይቆሙ ነበርና፣ ይህም ሥራ በግብር መልክ የሚፈጽሙት ግዴታ ስለነበር ብቻ ሳይሆን፣ ስንቃቸውን ይዘው በእግር ሩቅ አገር ሄደው የሚያከናውኑት ስለነበር፣ ስለሚሰለቻቸው፣ ዳኘው አዲስ አበባ ከገባ በኋላ የሳቸውንም ወር ተራ ስለሚቆምላቸው፣ ደስ ስላላቸው፣ ይቅርታቸውን በቀላሉ እንደሚያገኝ እርግጠኛ ነበር።

ዳኘው አዲስ አበባ ጉለሌ ሲኖር ጎረቤቱ ከምትኖር ጥሩወርቅ ከመትባል ልጅ ጋር ተዋወቀ። መጀመሪያ ያስተዋወቃቸው ተክለሃይማኖት ነበር። ተክለሃይማኖት ከወላጅ እናቱና አባቱ ጋር ያደገ ከመሆኑም ሌላ ሴቶችን በሚመለከትም ሆነ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት፣ ዓይናፋርነት የሌለበት፣ አመሉ ከዳኘው ለየት ያለ ነበር። ተክለሃይማኖት ከሁለቱም ጾታዎች ጋር ካለምንም መጨነቅ የሚደባለቅ ነበር። ዓይናፋርነት የከፉውን ዓይን

[5] እንደላይኛው

[6] ቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ ወልደ አብ የጥይት ቤት ዘበኞች ኃላፊ የነበሩ ሲሆን በኋላ ምን እንደሆኑ አላወቅሁም።

መሸሻ ከሆነ ተክለሃይማኖት ምንም ዓይነት የበታችነትና የበላይነት ስሜት ስለሌለው የሚጨነቅ አልነበረም። ተክለሃይማኖት ከጎረቤት ሰዎች ጋር እንደሚቀርብ ሁሉ፣ ጥሩወርቅንም የተቀራረባት እንደዚሁ ነበር። ለዳኘው እንዲሁ ሲያስተዋውቀው ለወጉ ያህል ብቻ ነው።

ከዚህ በኋላ የጥሩወርቅ እናት ሁለቱንም ለቡና ሁልጊዜም ስለሚጠሩዋቸው ዳኘውና ተክለሃይማኖት ቤተኛ ሆኑ። ዳኘውም ቤተኛ በመሆኑ ከጥሩወርቅ ጋር በጣም ተቀራረበ። በሰበብ ባስባቡ ከጥሩወርቅ ለመለየት አይፈልግም።

ከዕለታት አንድ ቀን ዳኘው የእረፍት ቀኑ ስለሆነ ከቤት እንደዋለ፣ ጥሩወርቅ ጠርታው ከጎተራ እህል እንዲያዋጣት ለመነችው። እሱም ደስ ብሎት እሺ አላት።

እሱዋ ከጎተራው ውስጥ ሆና በቁና ስንዴውን እያፈሰች ታቀብለዋለች። እሱ ተቀብሎ ከቁርበቱ ላይ አፍስሶ ይመልስላታል። የወንድ ልጅ ፍቅር የሚወዱዋትን ሴት አትኩሮ ማየት፣ የራስ ማድረግ፣ እንደ ብርቱካን ለመግመጥ መጓጓት፣ ስለሆነ ዓይን ጨፍኖ እንኳን ስለሚሰማ ጥሩወርቅ ተጠራጥራ ከጎተራው እንዳለች በድንገት ቀና ብላ ወደ ላይ ስታየው ዓይኖቹ ገለጥ ካሉት ጡቶቹዋ ላይ አርፈው ተመለከተች። ትክ ብላ አይታው ሳቀችና ቁናውን ስትቀበለው ጣቶቹንም አብራ ያዘቻቸው። ወዲያው እንዳጋጣሚ እንደሆነ ያህል ቶሎ ብላ ለቀቀችው። እሱም ያጋጣሚ እንጂ ሌላ አይሆንም ሲል ደመደመ። ልቡ መምታትን ጨምሮ እንደመፍራት ብሎ አቀረቀረ። ከዚያም ለብዙ የቁና መመላለሶች ፀጥታ ሰፈነ።

እህሉን አውጥተው ሲጨርሱ ከጎተራው ለመውጣት ሲያቅታት ቢያይም፣ ዳኘው አፍሮ ሊያግዛት አልሞከረም። እጅህን ስጠኝ፣ ብላ ትክ ብላ ተመለከተችው። የድፍረት፣ የፍቅር፣ የስሜት መቃጠል ሁሉ የሚታይበት አመለካከት ነበር። "እህሉን ለመቋጠሪያ ስልቻ ላምጣ ጠብቀኝ። ጎተራውን ታካድነኛለህ።" ብላው ወደ ቤት ገባች።

ጎተራዎች ከቤት ውጭ ዙሪያቸውን አጥር ታጥሮላቸው፣ ዝናብ እንዳይገባባቸው የኮን ቅርጽ ያለው በሳር የተከፈከፈ ተከፋች ጣሪያ ያላቸው፣ በመቃ እንደ ቤት በክብ የተሠሩ፣ ተነቃናቂ የእህል መያዣ ናቸው።

ጥሩወርቅ ወደ ቤት ስትገባ የቀድሞ አመለካከቱዋ ድንግዝግዝ ብሎ ታየው። የፍቅረኛ ሁሉ ነገር እንዲህ እንደ ጉም ጥላ የተሸፈነና ግን ልዩ የሚመስል ነው። ሁለመናዋ ጥንት ከሚያውቀው ጭራሽኑ አይቶት እንዳላወቀ፣ ልዩ፣ ውብ፣ የሚያስጎመኝ፣ ሆኖ ታየው። ቅድም የራሱ ሊያረጋት ሲችል ፈርቶ እድሉን ስለዘጋ ተበሳጨ። ከእንግዲህ ይህ እድል ተመልሶ አይመጣም ብሎ አሰበ።

ስልቻዎቹን ይዛ እንደመጣች፣ እሱዋ ስልቻዎቹን በየተራ እየያዘችለት፣ እሱ ከቁርበቱ ላይ እህሉን በቁና እያፈሰ መከተት ያዘ። እጇዋን እንዳይነካ ጭራሽኑ ይጠነቀቅ ጀመር። የፈለጋት መሆኑን ለማሳወቅ፣ እምቢ ብትለው ሽንፈትን ላለመቀበል ይሁን ወይም በኩራት ወይም የመጀመሪያውና የሁለተኛው አንድ ዓይነት ነገሮች ሆነው፤ አልፈለገም።

“እንዳታፈስው፤ ስልቻውን እያስጠጋህ ጨምር።” ብላ ትክ ብላ በፈገግታ ተመለከተችው። እሱም ሃፍረት ባስዋበው ፊት ፈገግ አለ።

እህል የያዙትን ስልቻዎች አንዱን ዳኘው፣ ሌላውን ጥሩወርቅ፣ ይዘው ወደ ቤት ለማስገባት ሲያመሩ፣ ከበራፍ ላይ የጥሩወርቅን እናት አግኝተው፣ ጥሩወርቅ ዝም ብላ ወደ አዳራሹ ስትገባ፣ ዳኘው ቆም ብሎ ሰላምታ ተለዋወጠ። “እቃ ተሸክመህ አትቁም ግባ።” ብለውት እሳቸው ወደ ጎተራው አመሩ።

ዳኘው ወደ አዳራሹ ሲገባ ጨለማ ነበር። ፀሐይ ከውጭ እየጠለቀች ሲሆን ከቤት ግን መስኮቶች ስለሌሉ ጨልሙዋል። ብዙ ሃሣብ በራሱ ውስጥ መተረማመስ ያዘ። ጥሩወርቅንም አልጠራት። የያዘውን ስልቻ ከአንዱ ጥግ አቁሞ ቀና ብሎ ሲቆም፣ ነፍሰ ገዳዩን ሰው በጨለማ ውስጥ አገኛለሁ ብሎ እንደሚደነግጥ ሰው ራመድ ሲል፣ ከአንድ ነገር ጋር ተጋጨ። ፀጥ ብሎ ቆመ።

“ተጋጨን።” አላት ቀስ ብሎ፣ ጥያቄ አይሉት ገለፃ በሆነ ቅላጼ።

“አዎን።” አለችው እጁን ጨበጥ አድርጋ።

“እንግዲህ ደህና እደሪ።” አላት ቀስ ብሎ። ወዲያው ለምን ደህና እደሪ አልኩዋት ብሎ አሰበ። እንደፈራው ግን የተጀመረው ሂደት አላቋረጠም።

“ዛሬ አብረን ነው የምናድረው። አይደለም?” አለችው መጀመሪያ ተነጋግረው እንደጨረሱት ጉዳይ። “እመጣለሁ፣ እማዬ ስትተኛ፣ ጠብቀኝ።” አለችው መልስ ሳይሰጣት።

“እሺ። እንዳትቀሪ፣” አላት ውለታዋን ለመክፈል ቃል ምሥጋና እንዳጠረው ሰው። ወገቡዋን በእጆቹ ያዝ አደረገ። አንድ ኃይል፣ ጨለማውም ይሁን የሱዋ ደፋርነት፣ ለሱም ድፍረት ሰጠው።

ኮሽ ባለ ቁጥር ሲነሳ፣ ከቤቱ በራፍ ብቅ ብሎ ሌላ ሰው ምሥጢሩን ያወቀበት ይመስል እያጮለገ ሲመለከት፣ ብዙ ዓመታት ያለፉ መሰለው። አንድን ነገር በጉጉት መጠበቅ እንዴት ያስጨንቃል።

መጣች፣ ተገናኙ፣ ራሱዋን በሙሉ ሰጠችው፤ ራሱን በሙሉ ሰጣት፤

ተዋደዱ፤ ተጋቡ። አወቀችው፣ አወቃት።

ሌላ ሰው ጥሩወርቅ እሱን የሠራችውን ሥራችኝ ብሎ ቢያጫውተው ዓይን አውጣ፣ ዘማዊ ይላት ነበር። እሱ ግን የራሱን ከሁሉ የምትበልጥ ሆና አገኛት። የሰሜቱዋ ሃይለኛነት ከሁሉ ይበልጥ የሚያረካው መሆኑን አወቀ። ሕይወቱ ሙሉ ሆነ፣ ረካ፣ ሰከነ።

በአዲስ አበባ በሙሉ ጦርነት በቅርቡ ይመጣል እየተባለ ይወራል። ሁሉም ሰው ይጨነቃል። ዳኘው ከፍቅሩ ዓለም ውጭ ያለው ሁሉ እምብዛም እውነታው ጠልቆት አይገባም። የሰማም አይመስለው።

ዳኘው አንድ ቀን ከሥራው ሲመለስ ከቤቱ በራፍ ላይ አባቱ ተቀምጠው አያቸው። እንደ መቆም አለ። መሬት ተሰንጥቃ ብትውጠው ደስ ይለው ነበር። አሁን ግን ተመልሶም ሊሄድ፣ መሬትም ልትውጠው አትችልም። አባቱ የዳኑለትን ሽዋነግዥውን ትቶ፣ አባቱን ሳያስፈቅድ፣ ጥሩወርቅን አግብቱዋል።

አባቱን ስሞ በሃፍረት ከፊት ለፊታቸው ቆመ። ምንም አልተናገረም። ጥሩወርቅ ግን ከጭንቁ አወጣችው። "ቡና ፈልቷል። ግቡ።" አለች። እሱ ግን ይበልጥ ሃፍረት ዋጠው።

"ቆንጆ ሚስት አግብተሃል። ጥሩ ልጅ ናት።" አሉት አባቱ እንዲደፋፈርና ከድንጋጤው እንዲነቃ በታሰበ አባባል። ጭንቁ

ገብቱዋቸዋል። ማን በዚህ ጎዳና ያላለፈ አለ? አብሶ በነፍጠኝነት ዘመን።

"እንዴት መጣህ?" አለ ሳያስበው። በመጥፎ እንዳይተረጎምበት በመፍራት "ትመጣለህ ብዬ አላስብኩም ነበር።" ብሎ ጨመረ።

"ጦርነት ሊመጣ ነው ይባላል። አባቶቻችን ድል ያደረጉት ጣሊያን እየተዘጋጀልን ነው አሉ። እንዳይህ ብየ ነው የመጣሁት።" አሉ ደንገር ብሎዋቸው።

እራት ከተበላ በኋላ አባቱ "እስቲ ወገባችንን እንሞክር፣ ወደ ጉዋሮ ዘወር እንበል።" አሉ። ዳኘው ውቃቢው ይሁን ጥፋቱ አስጠርጥሮት፣ ወደ ሞቱ እንደሚሄድ እስረኛ በጸጥታ ተነስቶ ተከተለ። ጥንካሬው፣ ቆራጥነቱ ሁሉ በአባቱ ፊት በኖ ጠፍቱዋል። የአባቱ ገጽታ እንደ አፍዝ አደንግዝ ምታት ቀልቡን ገፎታል። በተረት ውስጥ፣ የጀግናው ጥይት ስንቱን ሲቆላ የነበረውን፣ ምታት የጀግናውን እጅ አስተሳስሮ፣ ጥይቱን አከሽፎ፣ ጠበንጃውን አስነክሶ፣ ሕሊናውን አደንዝዞ፣ በጠላቱ እጅ የሚጥለው ሁኔታ ምሳሌ ነው።

"ዳኘው፤" አሉ ዘለልክ ከትንሽ ፀጥታ በኋላ።። "የሽዋንግዥው ቤተሰቦች ውለታ አፈረስክ ብለው እንደከሰሱኝ ሰምተሃል።" ዳኘው ልቡ እየመታበት ጸጥ ብሎ ማዳመጡን ቀጠለ። ዘለልክም የሚፈልጉት መልስ ተሰጥቶአቸው አፀፋውን እንደሚሰጥ ሰው ለየት ባለ አባባል ቀጠሉ። "ሽዋነግዥውን ላንተ ሳጭልህ ቀደም ሲል ወንድ ልጅ ስለወለደች፣ ላንተም ትወልድልሃለች ብየ ነው። አባትህን ቃል አፍራሽ አታድርገኝ፣ ደግሞም።" አሉት። "ሰው ከሕሊናውና ከባሕሉ ሸሽቶ አያመልጥም።"

"አባባ ቅጣቱን እኔ እከፍላለሁ።" አለ ዳኘው የሚናገረው ጠፍቶት።"

"የለም ይህችኛዋ ሚስትህ መካን ናት። እኔንም ለአገር መሣቂያ ታደርጋለህ። ይችኛዋን አትጥላትም። ትረዳታለህ። ግን ሽዋንግዥውን ማግባት አለብህ። ካለዚያ እረግምሃለሁ።"

"ማሪኝ!" አላት ዳኘው ከሚስቱ ጋር ሊለያዩ አንድ ቀን ሲቀረው። "አባቴ ያጨልኝን እጮኛ ካላገባሁ ይረግመኛል። ከአባቴ ቃል ልወጣ አልችልም። ማንኛችንስ እንችላለን።" ፀጥ ብላ ማዳመጡዋ አስደንግጦት ቀጠለ። "በቻልኩት ሁሉ እረዳሻለሁ።"

“እርዳታህን አልፈልግም!” አለችው ሳያስበው። ከዚያም ጡዋ ብላ አለቀሰች፡ በአንገቱ ላይ እየላሉና እየላሉ ይሄዱ የነበሩት የአቀፉት እጆቹዋ ተሰብስበው ከአንገቱ ወለቁ። ከአልጋው ወርዳ ከመደቡ ተኛች።

ሊያባብላት ያደረገው ሙከራ ሁሉ ከሸፈበት። አባቱን ለመጀመሪያ ጊዜ

ጠላቸው።

ጡዋት ሲነጋ ጥሩወርቅ ከቤት አልነበረችም። ከብዙ ዓመታት በኋላም ግን ትዝታዋ አዲስ ነው። ፍቅሩን ሳይጨርስ ለአጉል ባሕል የፈታትን ሚስቱን ዛሬም ልክ እንደዚያን ጊዜው ሆና በዓይነ ሕሊና ያያታል። አታረጅም፤ ጠባዩዋ አይለወጥም፤ አትሞትም፤ አትነቅዝም። እሱ ያለፈበትን ጎዳና አትራመድም። ያላለቀ ፍቅር ይህ ነው።

ትዝታ አያረጅም።

# ሩህሩህ እናትም እጇዋን የምታነሣበት ጊዜ አለ

ለጥቂት ወራት ያህል በማይጨው ጦርነት ማን ድል እንዳደረገ ግራ የሚያጋባ ወሬ ይነፍስ ነበር።[7] ጠላት አሸነፈ ሲባል ሁሉም ሰው ሲተክዝ፣ ወገን አሸነፈ ሲባል ቀደም ሲል መጥፎ ወሬ አምጥቶ የነበረው ሲወቀስ ከርሞ፣ ሳቀቴ ከአዲስ አበባ የመጣ ሰው መጥፎ ወሬ ሲያወራ እንደሰማች ለአስካለ ነገረቻት።

ሳቀቴ ቸኩላ ገብታ፣ የአስካለን ነፍስ አባት እንኳን አሳልሙኝ ሳትል “አስካልዬ ጣሊያኖች እንደ አሞራ እየበረሩ መርዝ ሲረጩ፣ መርዙ ከነካሽ አመድ ትሆኛለሽ አሉ።”[8] አለች በትልቅ ፍርሃት።

[7] በአገራችን የታሪክ አጻጻፍ ስልት ንጉሡ የተሳተፈበት ጦርነት ተጠቃሽ ስለሚሆን የማይጨው ጦርነት የሚባለው በሰሜንና በደቡብ ምሥራቅ ኦጋዴን የተደረጉትን ብዛት ያላቸው ጦርነቶች አጠቃሎ የሚያሳይ ነው፡፡

[8] ይህ ዓይነቱ መርዝ ከመስታርድና ፎሰጂን የተለየ ሲሆን የሰሜኑ ጦር አዝማች ከነበሩት በልዑል ራስ ካሣ እንደሚከተለው ተገልጿል። “ጥቅጥቅ ያለ የዝናብ ዓይነት ፍንጣቂ ሲዘንብብን አገሩ በሙሉ እሳት የተያያዘ ይመስል ነበር።…ቡናማ ቀለም ያለው፣ የማይጨበጥ ቆዳን አቃጥሎ የሚበላ እንፋሎት ዓይነት የመርዝ ጋዝ ነበር በወታደሮቻችን ላይ የሚዘንብባቸው። በዚች ቀን ብቻ ቁጥሩን መናገር የሚያስቅቅ ወታደሮቻችን አለቁ። ከሁለት ሺ ከብቶች በላይም በመርዙ አለቁ። በቅሎዎች፣ ላሞች፣ በጎችና የጫካው ዱር አራዊት ሁሉ እየሸሹ ወደ ሸለቆው እየሮጡ ገደል ገቡ። ለ ማርሴል ግሪዮል በወቅቱ ከሰጡት ቃለ መጠይቅ (ላቀች አክሊሉ ተርጉመው “የንጉሠ ነገሥቱ ትዝታዎች” በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ ገጽ 66/68) ። ንጉሠ ነገሥቱ “ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ” ላይ የመርዙ ዓይነት ቀደም ብሎ በየትኛውም ጦርነት ሥራ ላይ ያልዋለ እንደሆነ ገልጸዋል።

“ምን? ምን አለች?” አሉ የአስካለ ነፍስ አባት የሰሙትን ማመን ተጠራጥረው፣ ግን ከቀደምት ልምዳቸው የሚመሳሰል ነገር የሰሙ መስሎአቸው፣ በዚህ ላይ አስካለ ሳቆቴን እንደ እኩያዋ እያረገቻች በማባለጉዋ ተናደው።

“ጣሊያኖች የሚረጩት መርዝ ሰውን ከነካ አመድ ያደርጋል አሉ።” አለች ሳቆቴ አባ በቀጥታ ባይጠይቁዋትም ፍላጎታቸውን ለማርካት መልስ ሰጥታ።

“ወይ ዘመን። በመጽሐፍም ተብሏል ጥንት። ሰዶም የተቃጠለች ጊዜ….”

ንግግራቸውን ከመጨረሳቸው በፊት አስካለ አላስችል ብሏት አቋርጣቸው ሳቆቴን መጠየቅ ያዘች። እንዲህ ዓይነት ወቅት መጽሐፍ የሚጠቀስበት አይደለም።

ሳቆቴ የሰማችውን ሁሉ ዘርዝራ ጀግናው ሁሉ ምንም ሊያደርግ

እንዳልቻለ የእግዜር ቁጣ መሆኑን ነገረቻት።

“እግዜር ምን ብሎ ይቆጣናል።” አለች አስካለ በሳቆቴ ሳይሆን በሁሉም ነገር ተናዳ። “እግዜር ያለው ከኛ ጋር ነው። ለካቶሊኮች አይደለም።” አለችና ምን ብላ እንደምትቀጥል ጠፍቷት ዝም አለች። “እግዚአብሔር ፊቱን ከኢትዮጵያ አያዞርባትም።” አሉ ቄሱ። ብዙ ቀናት ሳይቆይ ከአዲስ አበባ ወደ አዳባይ ዙሪያ አገር ብዙ ሰዎች መጉረፍ ጀመሩ። ደጃዝማች አውራሪስ ከልጃቸው ጋር መጥተው ላሎ ምድር መንዝ ተቀምጠዋል አሉ ይላል አንዱ[9]። ሌላው ልጅ ግዛቸው ኃይሌ[10] ከማይጨው ተመልሶ መንዝ ገብቱዋል። ከቀያችን ሆነን እንዋጋለን ብሎ ሰው ያሰባስባል አሉ። የመንግሥት ጎተራም እየከፈተ ጣሊያን ከሚበላው ብሉት እያለ ለሕዝቡ ያድላል አሉ ይላል ሌላው። ሰው ንቅል ብሎ ከአዲስ አበባ እየመጣ ነው የሚል ወሬም ይነፍሳል። ከአዲስ አበባ ወደ ገጠር ተመላሹ ቁጥር ግን እየበዛ ሲሄድ ሁሉም መንደር የአዲስ አበባ ሰው ኖረው። የአስካለ አጎቱዋ ግራዝማች ኃይለማርያም በጦርነቱ ላይ ስለሞተ ይሁን ስለጠፋ ወደ አገሩ አልተመለሰም። የት ቦታ እንደወደቀ፣ እንደቀረ ያየው የለም። ተመልሰው የመጡት ወታደሮች እንኳን የሚያወሩት የተምታታ ነበር።

ነፍሳቸውን አትርፈው ከማይጨው ከተመለሱት ዘማቾች የግራዝማች ኃይለማርያም የት መድረስ አለመታወቅ እንደተሰማ በቤተሰቡ ላይ ፍራት አይሉት ጭንቅ አንድ መርግ ወደቀበት። በእንደዚህ ዓይነት ቀውጢ ቀን ከሌሎች ተቀናቃኞች እራሱን ለመከላከል አንድ

---

9 ደጃዝማች አውራሪስና ልጃቸው ቀኛዝማች አበበ አውራሪስ (በኋላ ደጃዝማች) ።

10 ልጅ ግዛቸው ኃይሌ መጀመሪያ በራስ ከበደ ስር በኋላም ራሱን ችሎ የመንዝ፣ ተጉለትና ይፋት አርበኞች አስተባባሪ የነበረ። ከተምቤን ጦርነት ቆስሎ የተመለሰ።ከነፃነት በፊት መስዋዕት የሆነ።

መሪ የሚፈልግ ቤተሰብና ንግስቲቱ የሞተችበት ንብ አንድ ነው። ንግሥቲቱ ንብ፣[11] በሥራ፣ በውጊያ ባታግዝም በሠራተኞቹ፣ በተዋጊዎቹ ንቦች መሃል ግን የተግባር አንድነትና ልማዳዊ አሠራራቸው እንዲቀጥል የሚያስችላቸውን መንፈስ ትሰጣቸዋለች። ዘሩ እየተራባ እንዲሄድ ንግሥቲቱ መኖሩዋ ግድ ነው። ንግሥቲቱ ከሌለች ዘሩ ተቋርጡዋል። ዘሩ ከተቋረጠ የስብስቡ እድሜም አጭር ነው። የቤተሰቡ አለቃም ሲሞት ቤተሰቡ ተረበሸ። በተለይ ወደ ዘመቻ ያልሄዱት የቤተዘመድ አውራዎች ቤተዘመዳቸውን ሲንከባከቡ ሲያዩ አገር ፈርሶ መንግሥት ጠፍቶ በሚደረገው ብጥብጥ ውስጥ ስጋቱ ኃይለኛ ሆነ።

አስካለ አንድ ቀን ወንድሙዋ የሆነ (የቅርብና የሩቅ የአጎትና የአክስት ለጆች ውንድምና እህት ይባላሉ) በሻህ ኃይሌ [12] ከማይጨው ተጉለት ተመልሶ ጦር እያዘጋጀ መሆኑን ሰማች። ድንቅነሽም መልዕክተኛ ልካ ስለ ልጁዋ ኃይለማርያም አስጠየቀች። የሚያውቅ ግን አልተገኘም።

ከእርገጤ በኋላ ለቤተሰቡ ትልቅ ሃብት ያስገኘው ኃይለማርያም ነበር። ነግዶ ከሚገኝ ጌትነት ሌላ ጌታ የመሆኛ ሌሎች ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። በጥንት ዘመን ከሆነ ዘምቶ፣ መሬት ተመርቶ፣ ሃብታም የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። መሬቱ ማዕድን ይኖረውና አንድ ዘመን ማዕድን ማውጣትን ሲያስችል ሃብት ይገኛል። በአጋጣሚ በርስት ላይ ከተማ ከተመሠረተ፣ መሬቱ በውድ ዋጋ ተሸጦ ይከበራል። ለፍቶ ጌትነት ግን እምብዛም የሚታወቅ አይደል። በየትኛውም ዘዴ ሃብታም የሆነ ግን ለልጆቹ ሃብትንና አዲስ የኑሮ ዘይቤን ያወርሳል።

ኃይለማርያምን አስካለ በግል ትፍራውም ትውደደውም ለቤተሰቡ አዲስ መንገድ ከፋች የሆነው በነፍጠኝነቱ ነው። ኃይለማርያም በነፍጠኝነቱ ከብሮ ወደ ትውልድ መንደሩ ሲመጣ ካጀቡት ወታደሮች ሌላ በሁኔታውና በሰውነቱ ላይ የሚነበበው ቁጣ እንኳን በደንብ የማያውቁትን፣ እየቀጡ ያሳደጉትን ሰዎች ሁሉ አስደንበሮአቸው ነበር። አስካለም የዚህ ዓይነት ሰዎች ክፉ ስለሚመስሏት አትወደውም ነበር። ነፍጠኛ የሚለውን ስም ከዚህ ዓይነት ገጽታ ጋር ታገናኘው ነበር።

አስካለ በዚህ በኩል ያለባትን ቅሬታ ያቃለለላት እንደ አጋጣሚ አንድ ጊዜ አጎትዋ በሻህ ኃይሌና እንደ ፈረንጅ ናቸው፣ ከፈረንጅ ጋር ነው የሚውሉት እየተባለ የሚወራላቸው የእናትዋ እህት ባል፣ መርን ጣዩ[13] ሲጫወቱ በአጋጣሚ የሰማችው ነገር ነበር። መርን ጣዩ ብዙ ጊዜ አዲስ አበባ ስለሚኖሩ፣ ብዙ ጊዜ አይታቸው አታውቅም። ከአዲስ አበባ የመጡ

[11] በዚህ እትም አውራ ንብ የሚለው ንግሥቲቱ ንብ በሚል ተተክቷል። በባህል አውራ ንብ በመባል ይታወቅ ነበር። በሳይንስ አንጻር መስተካከሉ ለተማሪዎች ስለሚረዳ።

[12] ባላምባራስ በሻህ ኃይሌ የተጉለት አርበኞች አስተባባሪ የነበረ። ከነፃነት በፊት መስዋዕት የሆነ።

[13] መርን ጣዩ የጎንደር ሰው ሲሆኑ በሹመት ሸዋ ነበሩ። ከነፃነት በፊት መስዋዕት ሆኑ።

ጊዜ ግን ከበሻህ ኃይሌ ጋር ሠንጠረዥ እየተጫወቱ፣ ስለ ፈረንጅ አገር ማውራት ይወዳሉ። ይህንን የሠንጠረዥ ጨዋታም ከሁለቱ በቀር የሚያውቀው ሰው ስለሌለ ሰው ሁሉ በአድናቆት ይመለከታቸዋል።

“ነፍጠኛውን እንጥራውና ይህን ጨዋታ እናለማምደው፣” አሉ አቶ መርን። ኃይለማርያምን ነፍጠኛው እያሉ ይጠሩታል።

“ግራዝማች ኃይለማርያም ለምን አትልም፣” አለ በሻህ ኃይሌ። ብዙ ጊዜ ቀልዶች ወደ ጠብ እንዳያመሩ ይጠነቀቃል።

“ነፍጠኛ ማለት እኮ ትልቅ ክብር ነው። በእንግሊዝ አገር የነበረው ንጉሥ አርሰር ክብሩን ከፍ በሚያደርጉለት ነፍጠኞች ነበር ተከቦ የሚውለው። ቅዱስ ጊዮርጊስም ሰማዕትነቱን ያገኘው በነፍጠኝነት ሙያው ነው። ነፍጠኛ ማለት እኮ ዘመነ መሣፍንትን አውድሞ የአንድ ንጉሥ ነገሥት አገረ ለመመሥረት ግንባር ቀደም ሆኖ የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን የሚያስፋፋ ተጋዳይ ነው።” አሉ አቶ መርን ጣዩ። ኃይለማርያም ዘመድህን የሰደብኩብህ ውይም ያቃለልኩብህ መሰለህ እንዴ? በሚል ስሜት ፊታቸውን ከሠንጠረዡ ላይ ሳያነሱ በጎሪጥ እየተመለከቱት።

“የፈረንጁ አገርና የኛ አገር ምን ተመሳሳይነት አለው?” አለ በሻህ ኃይሌ ማወዳደሩ አልገባ ብሎት።

“ምኑ ላይ ይለያያል። ቅዱስ ጊዮርጊስም በዘንዶ የሚያመልኩ ሕዝቦች ዘንድ ያደረገው ታምር ቀኛዝማች እርገጤ እራቁታቸውን ከሚኖሩ ሰዎች ዘንድ ሄደው የአጼ ሚኒሊክን ግዛት ያስፋፉበት ሁኔታ ምን ልዩነት አለው። ዋናው ነገር ግን አውሮፓ በሙሉ ሰልጥና ስለነበር ጎጃም ሸዋ ላይ ሸዋ ወሎ መሣፍንት ላይ እንደሚዘምተው ወይም አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሐንስ ያደረጉት ዓይነት ዘመቻ ነበር። የአውሮፓ ነፍጠኛ በእንጨት፣ በዘንዶ የሚያመልኩ ሰዎች ጋር የሚገናኘው አገር አቋርጦ፣ ባሕር ተሻግሮ ነበር።” አሉ መርን ጣዩ የኢትዮጵያ ነፍጠኛ በኢትዮጵያም ውስጥ የቤተዘመድ ሥርዓተ ማህበሮችን እያፈራረሰ፣ የቤተዘመድ አለቃና አዝማቾችን ወደ ባላባትና የመሬት ባለቤትነት እያሸጋገረ፣ ለራሱም መሬት በርስትነት መያዙ እየታያቸው። ከዚያም ወሬውን ለመቀየር ፈልገው “እስካለ ግራዝማች ኃይለማርያምን ጥሪው!” አሉ በሻህ ኃይሌን “የልብህ ደረሰልህ?” ለማለት ፈገግ ብለው በማሾፍ እየተመለከቱት።

ኃይለማርያም ወደ እነ መርን ዘንድ ሲመጣ “ፈረንጁ ምን እናድርግ ትላለህ?” አለ መርን ጣዩን በማሽሟጠጥ እየተመለከተ።

“በሻህ ዘመዴ ተነካብኝ ብሎ ይቆጣኛል። ለምን ነፍጠኛው ትለዋለህ ይለኛል። ትስማማበታለህ?” አሉ መርን ጣዩ ከአጠገባቸው ያለውን ጠጅ ፉት እያሉ።

ኃይለማርያም አስካለ የቀዳችለትን ጠጅ ፉት ብሎ "ይስማማኛል። እንኳን ነፍጠኛ ጋኔልም ልትለኝ ትችላለህ፣" አለ ፈገግ ብሎ።

"የፈረንጅ ነፍጠኛ፣ የአበሻ ነፍጠኛ እያለ ልቤን ያወልቀዋል፣" አለ በሻህ ኃይለማርያምን እየተመለከተ።

"ግዴለህም አትጨነቅ ። መርን አንድ ሰማዕት ኢትዮጵያዊ ነፍጠኛ በቅርብ ቀን ይፈጥርልናል።ለኔም ሁልጊዜም ስለዚሁ ጉዳይ ያወራኛል።" አለ ኃይለማርያም ጠጁን ፉት እያለ፣ በሻህን ፈገግ ብሎ በመመልከት ቅኔውን እንዲያውቅ እየጠቀሰው።

"ዘመነ መሣፍንት ከኢትዮጵያ ማክተም አለበት ከተባለ ይህንን ለማድረግ ካለ ነፍጠኛ አይሆንም። ነገር ግን ነፍጠኛው፣ ፈረንጁ ማለት ምን ይጠቅማል።" አለ በሻህ ኃይሌ አንዳንድ ሰዎች ለክርክር ያህል ብቻ ለምን እንደሚከራከሩ አይገባውም።

አስካለ ያንን ጨዋታቸውን ግን ሁልጊዜም እያሰበችበት ትኖራለች። የኃይለማርያም ጠባይና ገጽታም ለሷ ደስ ባይላትም ለሀገሩ ግን ከፍተኛ ነገር እያከናወነ እንደሆነ ገመተች። የዘመነ መሣፍንት መጥፎነት በተነሳ ቁጥር የነፍጠኝነት ሙያ ታላቅነት ተያይዞ ይታያት ጀመር። ቀስ በቀስም ኃይለማርያም ለቤተሰቡ ሴቶች ባልነት ወታደርን እንጂ ለምን ገበሬን እንደማይመርጥ እየገባት ሄደ። በሷ በኩል ገበሬን ባትንቅም ይህ ሃሳቡ ግን ገና ከሕፃንነቷ ጀምሮ እንደተዋሃዳት በጋሻውን በባልነት አለመፍቀዱዋ ስላረጋገጠላት ይገርማታል።

ኃይለማርያም ምንም ቢሆን ምን ለቤተዘመዱ ታዳጊ ነበር። ኃይለማርያም ሲሞት ኃይለማርያምን ተክቶ ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ሰው ከነአስካለ ቤት አልተገኘም። የኃይለማርያም ሃብቱ እንጂ ልምዱና ግርማ ሞገሱ በውርስ የሚተላለፍ አይደለም። ከዚህ በላይ መንግሥት ፈርሷል፤ አገር ተናግቷል፤ ነፃነት፣ የኑሮ ዘይቤ አደጋ ላይ ነው።

አስካለ ጡት ያልጣለች ልጅዋን አቅፋ ብዙ ጊዜ አቀርቅራ መተከዝ ያዘች። በሃሳቡዋ ስታወጣ፣ ስታወርድ፣ ስታለቅስ ብዙ ጊዜ ቆየች። አንድ ነገር መወሰን ካለዚያም ሕይወቱዋ መራራነቱ እየተባባሰ መሄዱ አልቀረም። አንዳንድ ጊዜ ፈሩን ያልያዘ ሃሣብ ይዙዋት ጥርግ ይላል። ከሃሣቡዋ ስትነቃ ችግሩ ምን እንደሆነ፣ መፍትሔውስ ምን እንደሆነ፣ ሃሣቡዋን አቅጣጫ አሲይዛ እንዲመራመርበት ለማድረግ ትሞክርና ሁሉም ነገር ዝብርቅርቅ ይላል።

የሌሊት ሕልሙዋም ከዚህ የተለየ አልነበረም። አንድ ቀን ቀኑን ሙሉ ከይፋት ከመጣ ሰው ጋር እነ ባሻ ተሰማ እርገጤ[14] ጣሊያን አዲስ አበባን ለመያዝ ሲገሰግስ፣ ከአውራው ጎዳና ላይ ያደረሱበትን ጥቃት፣ ዘመዱዋ በሻህ ኃይሌም በበኩሉ ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ ላይ በሽምቅ ውጊያ ስለሚያደርገው ተጋድሎ፣ ስታወራ ቆይታ፣ ሲመሻሽ ከልጁዋ ጋር ጋደም

[14] ባሻ ተሰማ ዕርገጤ በኋላ ደጃዝማች የታወቁ የይፋት አርበኛ።

አለች። ውጥንቅጡ የወጣ ሃሳብ ስታደራ፣ ስትገለባበጥ ቆየች። ሳታውቀው ከአንድ ተራራ ጫፍ ላይ ቆማለች።

ከኋላዋ አያቱዋ ድንቅነሽ የአስካለን ትንሽ ልጁዋን ኩሪን አዝለው ራቅ ብለው ቆመዋል። "ወዴት ነው የምትሄጅው?" ይሏታል ድንቅነሽ። "ሴት ልጅ በረሃውን አቋርጣ ከወዲያ ማዶ ትደርሳለች ማለት ዘበት ነው። ምክሬን ካልሰማሽ ግን ሞክሪው።"

"መሄድ አለብኝ እምዬ። ከዚህ አይስማማኝም። እስክመጣ ኩሪን ያዙልኝ።"

"ድሮውንስ አንቺንም እናትሽ ጥላሽ ሄዳ ያሳደግኩሽ እኔ ነኝ። ግን ይቅርብሽ። ሴት ልጅ የመከራ ጊዜን የምታልፈው በብልሃት እንጂ በእልህ አይደለም።"

አስካለ ግን ቁልቁለቱን መውረድ ትይዛለች። ወዲያው ግን የሕፃን የጣዕር ለቅሶ ሰማችና ዘወር ስትል ልጁዋን አንድ ፈረንጅ ከድንቅነሽ ነጥቆ ቁልቁል ወደ እሱዋ ሲወረውራት በድንጋጤ ከእንቅልፍዋ ነቃች።

ሰውነቱዋ በላብ ተዘፍቁዋል። ትንቀጠቀጣለች። ሳምባዋ ጉሮሮዋ ውስጥ እንደተወተፈ ትንፋሽ አጥሩዋታል። ልቡዋ በርራ ከደረቱዋ ልትወጣ እንደፈለገች ትንደፋደፋለች። ከአጠገቡዋ ያለችውን ኩሪ እንኳ ሦስት አራት ጊዜ ደባብሳ አቅፋ ስማትም ያ ቅዠቱዋ አሁንም እውን መስሎዋታል። በጨለማው ውስጥ ልጁዋን ደጋግማ እየሳመች ጡዋ ብላ አለቀሰች። ከልቅሱዋ በኋላ ግን መንፈሱዋ ትንሽ በረደ። ሰበብ ፈልጋ ሳቆቴን ቀስቅሳ ጨዋታ በመጫወት ፍራቱዋን ለማስታገስ አለመሞከሩዋ አሁን ደስ አላት።

በበነገታው እንደ ቀልድ እያደረገች ጣሊያኖች የአርበኞችን ልጆች ምን እንደሚያደርጉ ከብዙ ሰዎች ወሬ ጠየቀች። የተለያየ ወሬ ሰማች። አንዱ ከሌላው መቃረኑ ብቻ ሳይሆን ወሬውንም አውሪው እሱ አርበኛ ለመሆን ባለው ፍላጎትና ፍላጎት ባለመኖሩ የሚመራ ነበር። ስለዚህ ቀስ በቀስ አርበኞችን የሚደግፉ ሰዎች የሚሉትን ተቀብላ፣ የሌሎቹን አንቀርቅባ ጥላ፣ ውሳኔ ላይ ደረሰች።

ክረምት አግቢ በየመስኩ ውር ውር በሚልበት በሰኔው ወር፣ አስካለ ኩሪን ለድንቅነሽ ሰጥታ፣ ወንድሙዋን በሻህ ኃይሌን እጠይቃለሁ በሚል ሰበብ ተጉለት ሳሲት ወረደች።

በሻህ ኃይሌ የተጉለትን ሕዝብ አስተባብሮ የተነሣ ታላቅ አርበኛ ሲሆን ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ባቀረበለት ሃሣብ መሠረትም በግዛቸው ኃይሌ አስተባባሪነት ከመንዝና ከይፋት አርበኞች ጋር ክንዱን አስተባብሯል።

በሻህ ኃይሌም አስካለን ባያት ጊዜ ደስ ብሎት አቅፎ ስሙዋት "እቴ ልትጠይቅኝ መጣሽ? ነይ ቁጭ በይ።" ብሎ ዓይን ዐይኑዋን መመልከት ቀጠለ። እቴ የሚለው አጠራሩ አስካለን በልጅነቱዋም ደስ ይላታል። በአገር ባሕል ሁሉም ዘመዳሞች ወንድሜ እህቴ ስለሚባባል ከልብ የመነጨ ስሜት አለው። በሻህ አትኩሮ በተመለከታት ቁጥር ከገጽታዋም፣ ከአቋሙዋም ከድሮው ለየት ያለ ጠባይ አየባት። ይህ ጠባይ ደግሞ

አርበኝነት[15] በቅርቡ ከጀመረ ጀምሮ የምን ጠባይ እንደሆነ አውቆታል። ሕይወት የሥነ ልቡና ተመራማሪይ ሊቅም አድርጎታል። አዲስ የተፈጠረው ጥርጣሬ በፈጠረበት ስሜት ድምጹ ጎርነን ብሎ፤

"ቤተሰብ ደህና ነው?" አላት።

"ሁሉም ደህና ናቸው።" አለችው አጠቃላ።

"መች ልትመለሺ ታስቢያለሽ?" አለ ይህ በግድ መጠየቅ ያለበት ጉዳይ ይመስል።

"መቼም አልመለስ።" አለችው ቁርጥ ባለ መንፈስ። ይህንን መልስ ሲሰማ ተነጋግረው እነደጨረሱት ጉዳይ እሱም ምንም መልስ አልሰጠም። ቁርጠኛ መሆኑዋን ሳለወቀ ስለ ልጁዋ አንስቶ ሊያባባት አልፈለገም። ብቻ ሳያስበው "ሩህሩህ እናትም እጁዋን የምታነሳበት ወቅት አለ።...." ሲል ተናገረና ወዲያው አፉን እንዳዳጠው አውቆ ለማረሳሳት ፈጠን በሎ "መቼም አልመለስ።" ላለችው መልስ ተስማሚ ይሆናል ያለውን መልስ "ካልሽማ እኔንም ደስ ይለኛል፣" ሲል ተናገረ። በልጅነቱዋ እነደሚያደርገው ፀጉሩዋን እያሻሸ ተመለከታት። "ደረሽልኝ የኔ እህት።" አላት እየሳቀ።

አስካለም በአክብሮት አይኑዋን ሰበር አድርጋ መሬት መሬት ተመለከተች።

ከሦስት ወር በኋላ አስካለ ከአርበኞች ወንድሞቿ ጋር በንብዋሻ በኩል ስታልፍ ዘመዶቿ የጫካ ኑሮ መጀመሯን ብቻ ሳይሆን አርበኛ ባልም እንዳገባች አውቀው ተገረሙ።

⅄ ⅄ ⅄

# አዋቂዎች እንደ አፍላ ወጣቶች ያለሙበት ወቅት

ዳኘው ከአገሩ ሲወጣ ወታደርነት ተቀጥሮ፣ ከአዲስ አበባ ሴት አግብቶ፣ ትዳር መስርቶ፣ ወደ አገሩ ሳይመለስ ለመኖር እቅድ ነበረው። ይህንን እቅዱን በበኩሉ መቸም ሊተወው ሃሣብ አልነበረውም። የኢጣሊያ ፋሺስት ወረራ ግን እቅዱን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን የኑሮ አቅጣጫውንም፣ የወደፊት እድሉንም ቀየሰው።

[15] ሽፍትነት የሚለው ቃል በአርበኝነት ተተክቷል።

እንደዚህ ዓይነት ወሳኝ ወቅቶች ሲመጡ ጫና ይሰማል። ሰዎችም እነዚህን ወቅቶች እንዴት እንደሚያልፉዋቸው ያቅዳሉ። የኢጣሊያኖች ወረራ እንደተሰማ ብዙ ሰዎች ያንን አስቸጋሪ ወቅት እንዴት በጀግንነት እንደሚወጡ አለሙ። በጦርነቱ ወቅት ሺ ገድለው፣ ሺ ማርከው፣ ከጦርነቱም በኋላ ለዚህ አገልግሎታቸው ካባ ለብሰው፣ ተሹመው፣ ተሸልመው እራሳቸውን አዩ። ሽማግሌዎችም፣ አዋቂዎች እንደ አፍላ ወጣት ያለሙበት ወቅት ነበር። ተሸልመው እራሳቸውን አዩ። ሽማግሌዎችም፣ አዋቂዎች እንደ አፍላ ወጣት ያለሙበት ወቅት ነበር።

በተረት መጽሐፍ ውስጥ ገፀ ባሕሪው እልፍ ገድሎ፣ እልፍ ማርኮ፣ ለዚህ ውለታው ንጉሡ ሴት ልጁን ዳረለት የሚለውን፣ ልጆች ሲያነቡ፣ እነሱም አንድ ቀን ይህንን እንደሚያደርጉ ያልማሉ። ልጆች ጦርነትን የሚወዱት ይህን የመሰለ ጀብዱ ሊሠሩበት ነው። በዚያች የሰውን መንፈስና አቅጣጫ በምትወስን ቀን ዋዜማም፣ አዋቂዎችም እንደ ልጆቻቸው አለሙ። ዳኘውም ከእንደዚህ ዓይነት ሃሣብ ተብጠልጣዮች ውስጥ አንደኛው ነበር። ወደ ማይጨው ሲዘምት እሱ ቤተ መንግሥቱን እንዲጠብቅ አዲስ አበባ እንዲቆይ ሲደረግ፣ ዓላማውን እንዳያሳካ ትልቅ በደል የደረሰበት የመሰለውም ለዚህ ነበር። ወደ ማይጨው እንዲዘምት ብዙ ሞክሮ ሲያቅተው ምርር ብሎ አለቀሰ። ዘማቾቹን በቅናት ዓይን ሸኛቸው። አብዛኞቹ አልተመለሱም።

የኢጣሊያ ኢትዮጵያን የመውረር ጉዳይ በሹክሹክታ ከጆሮ ጆሮ ሲተላለፍ ቆይቶ፣ መንግሥት በይፋ አውጆት ስላልነበር፣ ግማሹ ምሥጢር አዋቂ ለመባል፣ ሌላውም በነገሩ ከባድነት በመደናገጥ፣ በጦርነት ውስጥ ገብቶ ያላለፈው ለጦር ወዳድነት፣ ሲያልጎመጉመው ኑሮ፣ የጦርነት ክተት አዋጅ በሥራ ላይ ዋለ። የተወራ ነገር ሳይደርስ አይቀርም የሚባለው እንደዚህ ላለው ጉዳይ ነው።

ዳኘው ልጅ ሳለ ከአባቱ ጋር አንድ ጊዜ ሲጫወት የነበረውን ያስታውሳል። ሊያስታውሰው የቻለው ሰዎች በየጊዜው በልጅነቱ እንዲህ ብሎ ነበር እያሉ ሁልጊዜም ስለሚያወሩ ወይም አዲስ ሕይወት ሲጀምር የጥንቱን ለመከለስ ይሆናል።

"አባዬ፣ ሸረሪቶቹን ቤታቸውን አፈረስኩባቸው።" አለ የአምስት ዓመቱ ልጅ እየተኮላተፈና የሸረሪት ድር የተተበተበበት ልምጭ ይዞ።

"ጎበዝ ጥሩ ነው። ግድግዳውንም ወዲያው ጠረግከው ማለት ነው።" አለ አባቱ በፈገግታ እየተመለከተው።

ዳኘው ዱንቸር ዱንቸር እያለ እየሮጠ ሄዶ፣ ትንሽ የሸረሪት ቤቶች ካፈረሰ በኋላ፣ እየሮጠ ወደ አባቱ ተመልሶ፣ "አባዬ፣ አንተን ሳክል ግን የሸሪቶችን ቤት አልጠርግም? አዎን? እሺ?......." አለ።

"ለምን?" አለ ዘለልክ። አሁንም ልጁን ፈገግ ብሎ እየተመለከተ።

"ትልቅ ሰው አይጠርግማ።"

"አንተ ዶለዝ የማታመጣው የለም።" ብሎ እራሱን አሻሸው።

አንድ ጊዜ ደግሞ አባቱና አጎቱ ጠበኛ ስለነበሩ አባቱ ስለዚህ ጉዳይ ለሰዎች ስሞታ ሲነግሩ ብዙ ጊዜ ይሰማ ነበርና አንድ ቀን "አባዬ!" ብሎ ተጣራ።

"ወይ።"

"እኔም ሳድግ ከወልደ ሰማዕት ጋር እጣላለሁ፣ እንኮራረፋለን፣

አላነጋግረውም።"

አባቱ በድንጋጤ "ለምን" አሉ።

"እናንተን ስናከል እንዳንተና እንዳጎቴ እንጣላለና።"

ዳኘው ቀስ በቀስ የቤተሰቡን፣ የአካባቢውንና የባልንገሮቹን ጠባይ እየለቀመ፣ የነሱን የኑሮ ዘዴና ምኞት እየተቀበለ፣ አደገ። አባቱ ገበሬ ስለነበሩ ግብርናን መተዳደሪያው አደረገ። አባቱ አዲስ አበባ ለወር ተራ ዘብ ሲቆሙ እየሰማ፣ ሌሎች ወታደሮችን እያየ፣ እሱም ወታደርነትን ወደደ። ከጓደኞቹ የሸማ ጥበብን ቀሰመ።

ከግብርና ኑሮው ወደ ወታደርነት ኑሮ ሽግግር ከሕፃንነቱ ጀምረው የነበሩት ፍላጎቶች አንዱ ከሌላው ማየል ስለነበር እምብዛም በሥነ ልቦናው ውስጥ ችግር አልፈጠረበትም። ከሕብረተሰቡ ወግና ፈሊጥ አልወጣም።

ልጅና ነብይ የመሰለውን ያደርጋል የሚባል ፈሊጥ እንዳለ ሁሉ ልጅና የተትረፈረፈ ሃብት ያለው ብቻ እንዳሻው ይኖራል። ልጅ፣ ያየውን ሁሉ ልብላው፣ ልጠጣው፣ ልውሰደው ይላል። እሱን እስካስደሰተ ድረስ የትኛውንም ዕቃ፣ የማንም ይሁን የማንም፣ አንስቶ ከመውሰድ አይመለስም። የግል ሃብት ይዞታዎችና የዕቃዎች እጥረትና ውድነት ለእሱ አእምሮ ትርጉም የላቸውም። የዚህን ጊዜ ወላጆች ልጃቸው ሌባ የሆነ እየመሰላቸው ይቀጡታል። እሱም ቀስ በቀስ ሳያውቀው የሕብረተሰቡን ወግና ፈሊጥ ይማራል።

ከዚህ ወግና ፈሊጥ ከእንግዲህ ለማምለጥ ቀላል አይደለም። ርስት የሚነቀልበት ወይም ነፍስ በዋጋነት የሚከፈልበት ሰንሰለት ነው። ዳኘው ካደገ በኋላ የሚወዳት ሚስቱን ጥሩወርቅን በአባቱ ተፅዕኖ ፈታት። እንደ ገመምተኛ በጥንት ጎዳናዎች እያዘገመ፣ የጥንቱን ሕይወት እንደ አዲስ ለመጀመር፣ ተጋተረው። ጥሩወርቅ ጋር እነደተለያየ ዳኘው ሸዋንግዥውንና ትንሽ እህቱን ካብታሙዋን ከአገሩ ወደ አዲስ አበባ አመጣቸው።

ካብታሙዋ አዳባይን አብራው እንድትዋኝ ዋና ያስተማራት፣ የሚመካባት፣ አለችኝ የሚላት እህቱ ናት። እሱዋ ለሱ የሚያደናግረውን ነገር ሁሉ መክፈቻ ቁልፍ ትመስለዋለች። የሴት ልጅ ጥበብ የሚለውን፣ ፈጥኖ መልስ ማግኘት፣ የሰው ልብ ገልጦ ማየት መቻል፣ የምታመለክተው ይመስለዋል። አዲስ አበባ መጥቶ የፈረንጅ ዓይን አይቶ እንደ ባሕር ጠልቆ የሚታይ መሆኑን ሲያይና የአገሩ ሴቶች ልጆች ዓይን ወደሚመለከቱት ውስጥ የሚጠልቅና የሚያይ ጦር መሆኑን ሲያይ በሀገሩ ሴቶች አስተዋይነት ይደነቃል። ዘመናችን አንድን ውስብስብ ነገር ፍቺ ለመስጠት የሚያግዙ የሂሳብ ማስሊያ መኪናዎች፣ ወረቀትና እርሳስ፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ቡና ቤቶች ወዘተ አሉት። 17 የዳኘውም ዘመን፣ ዘመድ ወይም

ጓደኛ የዚህ ዓይነቱ ቁልፍ ነው። ለአንድ ነገር ፍች ለመስጠት፣ መፍትሔ ለማግኘት፣ መፍትሔው ከራሱ ከሰውየው ቢፈልቅም ሃሳቡን የሚያዳምጠው፣ የሚያከራክረው፣ የሚያካፍለው፣ ከዚያም መፍትሔውን ለማፍለቅ ወረቀትና እርሳስ የሚሆንለት፣ ሰው ያስፈልገዋል። ካብታሙዋ ግን ለዳኘው ከዚህ በላይ ናት።

በንቃት ይገንዘበውም አይገንዘበው ጥሩወርቅን በሙተው የደረሰበትን የልብ ስብራት ሽዋንግዥረው ለማስተካከል ብትፈልግና ብትቆርጥ እንኳን ተጨማሪ አጽናኝ፣ ካብታሙዋ፣ እንደምታስፈልገው እውቅ ነበር። ሽዋንግዥረው በቁስሉ እንጨት ከሰደደችበት ግን፣ ካብታሙዋ ነፍስ አዳኝ ትሆናለች። ሽዋንግዥረው ብትሆንም እሱዋን ትቶ አዲስ አበባ ሌላ ሴት ማግባቱን ከሰማች በኋላ ለሱ ግዴለሽ ከመሆን አልፋ ጠልታዋለች። የቤተሰብ ግዴታ ሆኖባት እንጂ ልታገባው ፍላጎት የላትም ነበር። ራሱዋን ለሱ ሙሉ በሙሉ ሰጥታ አታውቅም። እሱም ጥሩወርቅን አልረሳም። ካብታሙዋም ደስ ይበላትም አይበላት በሁለቱ መሃከል ሚዛን ፈጣሪና አጽናኝ ሆና ቆየች።

ዳኘው በዚህ ዘመን የመጀመሪያ ልጁ አምሳሉ ተወለደለት። ወንድ ልጅ በመወለዱም ተደሰተ። ሽዋንግዥረውን ማግባቱና ወንድ ልጅ የመውለዱ ጉዳይ ለጠንቋዩም ያዘለት። የሕብረተሰቡ ወግና ባሕል ላይ ተመስርቶ የሚተነብይ ይይዝለታል። ወላጆቹ ያጩለትን ሳያገባ ማን ይቀራል? ሁለተኛው ትንቢት ግን የአጋጣሚ ሲሆን መነባበሩ ክብሩን ከፍ አደረገለት።

አምሳሉን እንደወለደች በ1928 መጀመሪያ ላይ ሽዋንግዥረው አገር ቤት ተመለሰች። ዳኘውም የሱዋ አገር ቤት መቀመጥ ለሁለቱም እንደሚበጅ ያህል ተስማማበት። ሽዋንግዥረውም አባትና እናቱዋ ዘንድ መኖሩ ከዳኘው ጋር ከመኖሩ ተሻላት።

ብዙም ሳይቆይ ወደ ማይጨው ተዘመተ። 18 ኢትዮጵያ ጦርነቱን እንዴት ማካሄድ እንደሚገባት የተለያዩ ሃሣቦች ነበሩ። እነታከለ ወልሀዋርያት የሽምቅ ዉጊያ ዘዴን ገና ከመጀመሪያው መጠቀምን ይደግፉ ነበር። ሌሎችም እንደ አድዋው ፊትለፊት ተጋጥሞ ዝምበር የምትለየው ጦርነት ይፈልጉ ነበር። ሁሉም ቀውጢ ወቅቶች አማራጭ መፍትሔዎችን ይፈጥራሉ። ታሪክ ግን በሰዎች መልካም ፈቃድ ስለማትሄድ፣ በተለመደው፣ በሚታወቀው ዓይነት የጦርነት ዘዴ፣ ክብር አለው ተብሎ በተገመተው መንገድ፣ ከኢጣሊያን ጋር ግጥሚያው ተካሄደ።

የማይጨው ጦርነት ላይ ተካፍሎ ጀብዱ ባለማሳየቱ ሲቆረቆር ጦርነቱ በጣሊያን አሸናፊነት ተፈጽሞ ንጉሡ ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ደብረብርሃን ላይ መሽጎ ከጓደኞቹ ጋር እንዲቀበል ትዕዛዝ ሲደርሰው ተስፋው ጭላንጭል አበራ። ጀብዱ የሚያስቆጥርበት እለት እንደገና የመጣ መሰለው።

በታላቅ ናፍቆት፣ አክብሮት ንጉሡን ለመቀበል እሱ በተራ ወታደርነት ያለበት በሻምበል መንገሻ አሊ የሚመራ የሻምበል ጦር ደብረብርሃን ሲጠብቅ ንጉሡ በሌላ መንገድ ማለፋቸውንና እነሱ በናዝሬት በኩል የባቡር ሃዲዱን እንዲጠብቁ ትዕዛዝ ተላልፎላቸው ካለምንም ፋታ ከባቡር ሃዲዱ ጋ ሲደርሱ ንጉሡ ለዓለም መንግሥታት ለማመልከት

መሄዳቸውን ሰማ። ከዚያ ጀምሮ ለስደተኞችና ለአቤት ባዮች አክብሮቱን አጣ። የጀብዱ መሥራት ፍላጎቱ የተቀጨበት ወጣት ቁጭት ያዘው። ብቻ አንዳንድ ጊዜ በወታደራዊ ሚዛኑ አንፃር ይኸኛው ጎዳና መልካም ይሆናል የሚሉት ጥርጣሬ ነበረው።

ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ ከጓደኞቹ ጋር ሲመለስ አዲስ አበባ በኢጣሊያኖቸ ተይዛ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ ደረሰ። እህቱ ከመሃል አዲስ አበባ እሱ ከአዲስ አበባ ዳር ተለያይተው መገኘታቸው አሁን እስከ ሙሉ ክብደቱ ተሰማው።

ከተበተነው ጦር ውስጥ ሻምበል መንገሻ አሊ ብዙ ወታደሮች ይዞ ወደ ባላንባራስ አበበ አረጋይ ዘንድ ሲያመራ ዳኘው ወደ አገራቸው አብረው ለመግባት ከተስማሙት አምስት ጓደኞቹ ጋር ሆኖ እህቱን ከአዲስ አበባ ይዞ ለመውጣት አቀደ። እሱ ብቻውን የባላገር ልብስ ለብሶ፣ ባላገር መስሎ እህቱን ይዞ እስኪመጣ ከከተማው ዳር እንዲጠብቁት አማከራቸው። ግማሾቹ ለእሱ በመፍራት ይቅርብህ አሉት። በጣም የፈሩት፣ በመሸነፍ የተርበተበቱት ደግሞ፣ ከአዲስ አበባ ቶሎ ቶሎ ለመራቅ የነዚህኑ ሃሣብ ደገፉ። አንዳንዶቹም አብረውት አዲስ አበባ ለመግባት ሃሣብ ሰጡ። እሱ ግን የሁሉንም ሃሣብ ሳይቀበል፣ የባለገር ልብሱን ለብሶ፣ ብቻውን ወደ ጉለሌ አመራ።

ንጉሡ ጥለውት የሄዱት ከተማ ተዘርፎአል። ተቃጥሏል። ጣሊያኖች ይህን የተቃጠለ ከተማ በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጀው፣ በየመንገዱ ፍተሻና ጥየቃ ያደርጋሉ።

ወደ አደጋው በተጠጋ ቁጥር እየጨመረ የሄደበትን ማወላወል እንደተወጣውና ከማይመለሱበት ጎዳና እንደደረሰ "ከእንግዲህ ልመለስ አልችልም፣" ሲል አስቦ፣ ከየአቅጣጫው ከመጡት መንገደኞች ጋር ተደባለቀ። የመጀመሪያው ኬላ ላይ ልቡ በሃይል ቢመታም ስሜቱ እንዳይነበብበት፣ ልዩ ትኩረት እንዳይደረግበት እየተጠነቀቀ በድብልቅልቁ ውስጥ ተፈትሾ ሲያልፍ ከአንድ የፈረንጅ ዓይን ጋር ግጥም አለ። የማያዩ የሚመስሉት ዓይኖቹ ዋሻ መስለው ስለታዩት ፍራቻ አልተሰማውም። ዘወር ብሎ ከአገር ልጅ ባንዳ ጋር ተያየ። ተጠራጠረ። ኬላውንም አልፎ እርቆ ከሄደ በኋላ መልሰው የሚጠሩት መስሎት ተጠራጥሮ ነበር። የጠራው ሰው ግን አልነበረም። ከዚህ በኋላ የፍተሻው ረቂቅ አለመሆን ልቡን አደነደነው። ሌሎችን ኬላዎች ተዝናንቶ አለፋቸው። እንዲያው ሽብር ለመፍጠር፣ ለማስፈራራት የሚደረጉ ነገሮች ናቸው፣ ሌላውን የሚያስፈራ የሚያደርገው የራስ ልብ ፍራት ነው ሲል አሰበ። ይህንን እያወጣ እያወረደ ወደ ቤቱ ተጉዋዘ። በሰበብ ባስባቡ ሰዓቱን እየጎተተ "ካብታሙዋ" አላት ድንግዝግዝ ባለው ጨለማ ውስጥ ቀስ ብሎ። "እኔ ዳኘው ነኝ፣" አላት ለምናልባት ደንግጣ ስሙን ጮሀ ጠርታ በጎረቤት ዘንድ እንዳይሰማ በመፍራት።...... ማን ያውቃል ጎረቤት በዚህ ወቅት አይታመንም።

"ዳኘው፣" ብላ አቅፋ ደግማ ደጋግማ ሳመችው። የታናሹ ታናሽ ብትሆንም ጋሼ አትለውም። የልጅ ልጁዋ በስሙዋ አንቺ ብላ ስትጠራት ደስ እንደሚላት አያት፣ ዳኘውም

ካብታሙዋ በስሙ ስትጠራው ደስ ይለዋል። ልዩ ደስታን ትሰጠዋለች። በእቅፉዋ ውስጥ ሆኖ ቤቱን ተመለከተ።

የዳኘው ቤት ተዘርፎአል። ካብታሙዋ በፈንታዋ አንድ ሺ የሚሆኑ ቤሳዎች ዘርፋለች። አዲስ አበባ ካለ አስተዳደር በቀረችበት ጊዜ አንዱ የሌላውን፣ ሁሉም ከየመሥሪያ ቤቱ፣ እንደገና ደግሞ ዘራፊውን ዘራፊ ሲዘርፈው፣ ካብታሙዋ የራሱዋን አዘርፋ፣ የንጉሡን ቤሣዎች ዘርፋለች። ትንሽ ከተጠያየቁ በኋላ "ጋሼ ተክለሃይማኖት መጥቷል፣" አለችው።

ዳኘው ደስታ ፈነቀለው። ተክለሃይማኖት ከማይጨው ዘመቻ ተመልሶ መምጣቱ ተአምር ሆነበት። ሰው ወዳጁ ወደ ጦርነት ሲሄድ ክፉ ይደርስበታል ብሎ ስለሚጨነቅ ተርፎ መጣም ሲሉት ተአምር ሆኖ ይታየዋል። "መቼ መጣ?" ብሎ ጠየቀ ይኽ ቃል ሁሉንም በስሜቱ የተትረመሰመሰውን ሃሣብ ያሚያጠቃልል ያህል።

"ትላንት ነው የገባው። በጣም ከስቷል። ብቻ ነፍሱ እንኳን የተረፈች፣" አለችና ወጥታ ሄደች። ስትመለስ ተክለሃይማኖት አብሩዋት ነበር።

ተክለሃይማኖትና ዳኘው ከተሳሳሙ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ስለ ወደፊቱ እቅዳቸው መነጋገር ያዙ። ተክለሃይማኖት ዳኘው ማይጨው ባለመዝመቱ እንደሚናደድ ስለሚያውቅ የማይጨው ወሬ ሲነሣ ወሬውን ይቀይራል። ዳኘውም ለትህትናው ካልሆነ ስለ ማይጨው ባይነሣ ደስ ይለዋል።

"ልትሄድ ነው?" አለ ተክለሃይማኖት ዳኘው አገራችን እንግባ ብሎ ተከራክሮ ሁለቱም ስላልተረታቱ።

"አዎን፣" አለ ዳኘው። ምክንያቱ፣ ሰበቡ በቃል የሚነገር ሳይሆን ዝም ብሎ ካለቃል የሚሰማ ስለሆነ።

"ንጉሡ ሄዱ አሉ…. ከእንግዲህ ምን ይደረጋል?" አለ ተክለሃይማኖት ነገሩ ሁሉ እንደገና ሲያስበው እየገረመው ለዳኘው ሳይሆን ለራሱ እራሱ የተናገረውን ጮሆ አስተጋብቶት።

"ምን እንደሚደረግ እኔም አልገባኝም። ነገር ግን አገሬ ገብቼ አየዋለሁ። በክፉ ቀን የትውልድ ቦታን የመሰለ የለም፣" አለ ዳኘው ተክለሃይማኖት ይህን ማወቅ እንዴት እንዳቃተው ገርሞት።

"እነ ባላምባራስ አበበ21 ከቃጠሎው በኋላ ወደ ጅሩ ሄደዋል። እኔም እዚህ ስቆይ ክብር ዘበኛ ስለነበርኩ ጣሊያኖች ሊተናኮሉኝ ይችላሉ። ሆኖም ግን ንግዱን እየነጋገድሁ ከዚሁ ሆኜ የሚመጣውን አያለሁ። ዳኘው መገናኘታችን አይቀርም። እግዜር በሰላም ያገናኘን ደህና ግባ።" አለ ተክለሃይማኖት ሆዱ እንደባባበት።

"አሜን ደህና ሰንብት። ደህና ያገናኘን።" አለ ዳኘው ያ ዘመን ተመልሶ ለመገናኘት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ በማወቁ በተሰማው ስሜት። አብረው ወደ አዲስ አበባ መጥተው አብረው ባለመመለሳቸው ቅር ብሎት።

የዚያች እለት ወደፊት ዳኘው አርበኛ እንደሚሆን፣ ተክለሃይማኖት ከመንዝ ከታወቁ ሰላይ የውስጥ አርበኞች ታዋቂው እንደሚሆን፣ ወይም ሁለቱም ሕይወታቸው በሦስት ቀን የተቆረጠች መሆኑዋን ወይም ሌላ አጋጣሚ እንደሚደርስ፣ በሁለቱም ልቦና ጥርጣሬ እንኳ አልነበረም።

የአጋጣሚ ነገር ቀላል አይደለም። አጋጣሚ ሕይወት የሚቀይስበትም ሁኔታ ቀላል አይደለም። በዚያች ወቅት ዳኘውና ተክለሃይማኖት ሲያወሩ የሰማቸው፣ ከፊታቸው ላይ የልባቸውን ስሜት ያነበበ፣ የሚሄዱበት ጎዳና የጠፉቸውና ያንን ጎዳናም ፈልገው ለማግኘት ተስፋ የሌላቸው ይመስሉ ነበር።

ዳኘው ከዝርፊያው በተፈችው አህያው የተረፉትን እቃዎቹን ሲጭን፣ ካብታሙዋ የዘረፈቻቸውን ቤሳዎች ከእንግዲህ በጣሊያን ቤሳ ስለሚተኩ ጥቅም የላቸውም ብሎ ሲበትናቸው፣ ካብታሙዋ በዝርፊያው ወቅት ማትረፍ ሳይሆን መክሰር እንደደረሰባት አውቃ አዘነች። ዳኘው ግን አጽናናት። "አሁን እኛ የመንዝን ጎዳና ተከትለን ለመሄድና ቢቻል አገራችን ለመድረስ ስንነሣ፣ ሌላውን ግን ለእድላችን ትተን ነው። የምንፈልገውና የማንፈልገውን አናውቅም። ተክለሃይማኖት እዚህ አዲስ አበባ በንግድ ለመተዳደር ሲቀር፣ ሌላውን ግን ለዕድሉ ትቶ ነው።" አለ። ዳኘው ይህንሲናገር በአካባቢው ያሉትን ብዙ ሰዎች ሁኔታ እየተመለከተ ነበር።

ዳኘው አህያውን ሲጭን፣ የጎረቤቱ ሰዎች አንዳንዶቹ እየተገላመጡ ለወጉ ያህል ሰላም ሲሉት፣ ሌሎችም እንዳለየ ሆነው ሲያልፉ አያቸው። እነሱ ሲቪሎች፣ እሱ የንጉሥ ወታደር ነው። አዲሱ የኢጣሊያ አዋጅ በሰዎች መሃከል አለመተማመንን ብቻ ሳይሆን፣ ሁሉም ሰው እራሱን ብቻ ለማዳን እንዲራወጥ አድርጎታል። በራፉን ዘግተው እሳት የለኮሱባቸው ሰዎች፣ በአንዲት ቀዳዳ ለመውጣት፣ አንዱ ከሌላው ለመቅደም ወደ ኋላ የሚጎትተው ዓይነት ለመጀመር፣ የመጀመሪያው የሽብር ደረጃ ነበር። ዳኘው፣ በአስቸኳይ አህያውን እየነዳ፣ እህቱን አስከትሎ ጓደኞቹ ዘንድ ለመድረስ ሲጣደፍ፣ በጫካዎቹ ውስጥ በሚያልፈው መንገድ፣ ጠበንጃ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን በጣሊያኖች በመታወጁ፣ በፍራት የተወረወሩ ጠበንጃና ጥይቶች፣ መትረየሶች፣ በጨረቃ ብርሃን ተመለከተ። ሁኔታው ይበልጥ ፍርሃት ፈጠረበት። የአንዱ ፍራት ለሌላው መጋባቱ አይቀርም። አለፍ ሲል ይኸው ነገር ገጠመው። አነዱንም ጠበንጃ ግን አላነሳም። መንገዱን ግን በደህና ጨርሶ ከከተማው ውጭ ከሚጠብቁት ጓደኞቹ ጋር ተገናኘ።

ጓደኞቹ ጋር እንደተገናኘ በየመንገዱ ላይ ወድቀው ስለሚገኙት ጥይቶችና የጦር መሳሪያዎች አጫወታቸው። ስለ አዲስ አበባ ነገራቸው። ብዙ ከተጫወቱ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ዘልቀው ጥይቶቹን በየጋቢያቸው አስረው የቻሉትን በትከሻቸው፣ የዳኘው አህያም የቻለችውን ያህል ጭነው ወደ አገራቸው አቀኑ።

በባዶ እጃቸው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ቅር ብሏቸው ስለነበር የጥይቱ ነገር ትንሽ ሃሣባቸውን መለስ አደረገው። "ለወልደ ሰማዕት ጥቂት፣ ለተክለጊዮርጊስ ሰላሳ….. ለነአከሌ…. እሰጣቸዋለሁ…. ደስ አይላቸው ይሆን……ልብስ ምን ያደርጋል……በአሁኑ ጊዜ ለወንድ ልጅ ጥይት ነው የሚያስፈልገው…. አይደለም። ማንደፍሮ በዚህ ዘመን የጥይት ስጦታ ይቀበላል …..ይሁን። ከምንም ምንም ይሻላል።" እያለ ዳኘው ከሃሳቡ እየታገለ መንገዱን ተያያዘው። የሌሎቹም ሃሣብ ከዚህ እምብዛም የተለየ አልነበረም።

ከአውራ ጎዳናዎቹ እየራቁ ወደ ገጠሩ ሲሄዱ እየተዝናኑ መጡ። በአሁኑ ጊዜ ዳኘው ከጓደኞቹ ገብሬ ሰንበታና ጋሼ ዲንግዴ ሌላ ወደ ጅሩ የሚያመሩ ሌሎች ሰዎችም ስለተደባለቋቸው ቁጥራቸው በዝቱዋል። ወታደሮችና ሌሎች አገራቸው ገቢ ሰዎች ናቸው። ሁሉም መጥፎውን ጊዜ በአገራቸው፣ በቀያቸው ለማሳለፍ የሚመለሱ ነበሩ። ሁሉም በቅርቡ ከመንደራቸው የወጡ እንጂ በነፍጠኝነት ዘመን አባቶቻቸው ወጥተው ከተማ ተወልደው ያደጉ አልነበሩም። አዲሱ የከተማ ኑሮ የቤተ ዘመድ መተሳሰርን አላልቶት ነበር። ይህ ቀውጢ ቀን ደግሞ እንደገና የቤተ ዘመድ አባሎች እንዲሰባሰቡ አስቻለ። ከቤተ ዘመድ እቅፍ በቅርብ ወደ ከተማ የወጣው አብዛኛው ከእትብቱ ቦታ ተመለሰ። ከተማዎችን ለማስፋፋት፣ አዲስ ከተማዎችንም በመቆርቆር፣ የምዝበራው ማዕከሎች ለማድረግ የመጣው ካፒታሊዝም፣ በመጀመሪያ ግፊቱ ከተማዎችን በማራቆት ተቃራኒውን አደረገ። አዲስ ነገር ሲመጣ ሁልጊዜም አሳሳች የሚሆነው በመጀመሪያ ደረጃ የሚያፈርሰውን ነገር፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለሚያጠናክር ነው።

"አገራችን ደህና ልንገባ ነው።" አለ ዳኘው ለማንም ሳይሆን እንዲሁ አፉ ላይ መጥቶለት። ለምን እንደተናገረው እንኳን አያውቅም። ይህን ተናግሮ ቀና ሲል ከፊለፊቱ ካለው ኮረብታ ብዙ ሰዎች አይቶ ደነገጠ። ለተናገረው ነገር መልስ ብሎት ጋሼ ዲንግዴ እንኳን "እግዚአብሔር ካለ፣" ያለውን አልሰማም። ከመቅጽበት ብዙ ሃሳቦች በአእምሮው ውስጥ ተርመስምሰው የጠላት ጦር መሆኑን ውሳኔ ላይ ደረሰ። ከዚህ ቦታ ጠላት ያጋጥመኛል ብሎ አላመነም ነበር።

በዚህ ሁኔታ ከአዲስ አበባ ጉዞ በጀመሩ በሰባተኛው ቀን ከጠላት ጋር ተያዩ። የኢጣሊያ ጦር ወደ ጅሩ እየዘመተ እንጂ ወደነዳኘው መምጣቱ አልነበረም።

ደንግላይ፣ የጅሩ መንደር ስትሆን፣ ዙሪያዋን በተቀራረቡ ኮረብታዎች የታጠረች፣ አንድ መተላለፊያ ያላት ናት። እነዳኘውና የጣሊያን ጦር እንደተያዩ ሁለቱም አንዱ አንዱን ያላየ ለመምሰል፣ አለመደናገጥን ለማሳየት ቢሞክሩም፣ በመጨረሻ እነዳኘው ሁኔታውን አገናዝበው፣ አመች ቦታ ሲደርሱ፣ ቀጥ ብለው ቆሙ። የጠላትም ጦር የነዚህን መቆም አይቶ፣ ነገሩ እንዳልገባው ለመምሰል ትንሽ ሄዶ፣ አመችነት ካለው ቦታ ሲደርስ ቆመ። ሁለቱም ንቅናቄያቸውን በማቆማቸው ለደም መፋሰስ የሚያስፈልገው እልህ ሰረፀባቸው።

"ምንድን ናችሁ? አትቁሙ። እለፉ። ካለዚያ ተኩስ እንከፍታለን።" አለ ከፈረንጁ አጠገብ የቆመ ሀበሻ ጮክ ብሎ።

ዳኘው ጠበንጃችሁን ቀስ ብላችሁ አዘገጃጁ ብሎ በሹክሹክታ ተናገረና ወደ ጠላት ፊቱን አቅንቶ "ወደ አገራችን ለመግባት የምንሄድ ነጋዴዎች ነን፣ ሰላማዊ ሰዎች ነን፣" ብሎ ተናገረ። ጋሼ ዲንጊዳም ተኙ ብሎ ከመቅጽበት አዞ ተኩስ ከፈተ። በሁለቱም ወገን ቆሞ የሚታይ ሰው ጠፋ። ተኩሱ ቀጠለ።

የመጀመሪያው ተኩስ ሊከፈት ሲል ሆዳቸውን ባር ባር ያላቸው ሰዎች፣ ተኩሱ ሲሟሟቅ፣ ጥይት እነሱን እንደማይነካ ያህል ተሰማቸው። ይህ ሁኔታ ግን እምብዛም አልቆየ። የጠላት ጦር እያየለ መጣ። የመማረክ፣ የመሞት፣ አፋጣጭነት ይታያቸው ጀመር። በዚህ ወቅት ላይ በሌላ አቅጣጫ ተኩስ ተሰማ። ባላምባራስ አበበ አረጋይና ደጃዝማች ያረጋል [16] በተኩሱ ድምጽ ተሰባስበው ለርዳታ ደረሱላቸው። እነሱን ለማደን የመጣው ጋር የሚዋጉት፣ እነዚህ ሰዎች፣ እነማን እንደሆኑ አላወቁም። ባላምባራስ አበበ አረጋይ ጠላት ከሚደሰትበት አዲስ አበባን አቃጥለው ጅሩ መግባታቸውን ጠላት እንደሰማ ወዲያው አዳኝ ጦር መላኩ ነበር። እነ ዳኘውም ቢሆኑ ለእርዳታ የደረሱላቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ አላወቁም። ብቻ የኢትዮጵያን ባንዲራ ከፍ አድርገው ይዘው ስላዩዋቸው ወገን መሆናቸው ተሰማቸው። ዳኘውና ጓደኞቹ ባንዲራዋን በየቀኑ ሲያዩዋት ከነበረውም በላይ ዛሬ ውብ ሆና ታየቻቸው። በወታደርነት ሕይወታቸው የተማሩት ሁሉ ትዝ አላቸው። እንደነሱ ያህል የተሰማው ማንም አልነበረም።

ጠላት እንዳፈገፈገ፣ ዳኘው ፋታ ሲያገኝ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የሽምቅ ተዋጊ ምንነት፣ እስከሙሉ ክብደቱ ተሰማው። ንጉሥ ሳይኖር፣ አገር በሌላ ንጉሥ ተይዞ፣ አርበኛው በአካባቢው እስከደፈረ ድረስ፣ ነፃነት ሊኖረው መቻሉን አወቀ። ይህ እውቀት ግን የዚያኑ ዕለት አገሩ መግባትን አስትቶ ከነባላምባራስ አበበ ጋር አላሰለፈውም። በደንብ ዘልቆ አንጀቱን እስኪያርሰው እራሱ ብቻውን ሊፈትነው ይገባል። የባላገር አስተዳደጉ እንደ ቶማስ ካልዳሰሰ የማያምን አድርጎታል። ከሽምቅ ተዋጊዎቹም ጥያቄ እንደሚቀርብለት አውቋል። በዚያው በተለመደው የባለገር አገላለጹ ስሜቱን ሳይገልጽ ሁኔታውን በደንብ ለማጤን ጊዜ የሚሰጠውን መልስ ሰጠ። ከባላምባራስ አበበ ጋር ተገናኝቶ ከነሱ ጋር እንዲሆን ሲጠይቁት፣ እህቱን አገሩዋ ማድረስና ወላጆቹን ማግኘት፣ ማደላደል እንዳለበት፣ በተረፈ ግን ምንም ጊዜ ቢሆን በተቻለው ሁሉ በተጋደሎው የሚረዳ መሆኑን ተናግሮ ተሰናበተ።

[16] ባላምባራስ አበበ በኋላ ራስ አበበ አረጋይ። ደጃዝማች ያረጋል የታወቁ የሸዋ አርበኛ።

ዳኘው በሰባተኛው ቀን በሰኔ ወር ላይ አገሩ መንዝ ገባ። ከምርኮም፣ ከአዲስ አበባም በአህያውና በትከሻው ተሸክሞ ያመጣውን ጥይት፣ ለወንድሞቹና ለቅርብ ዘመዶቹ አከፋፍሎ፣ በትውልድ መንደሩ ሰው አጀብ አጀብ የሚያደርገው፣ ለመሆን በቃ።

1928 ከማለፉ በፊት የመንዝ፣ የይፋትና የተጉለት አርበኞች በግዛቸው ኃይሌ አስተባባሪነት ወደ ሰላድንጋይ ለመዝለቅ የሞከረውን የጠላት ጦር ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ መገንጠያ ላይ ድል ማድረጋቸውን ሲሰማ ልቡ በደስታ ፈነደቀ።በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ላይ ባላምባራስ አበበ ወደ መንዝ ሲያመሩ ዳኘው እስከባልደረቦቹ በደስታ የተቀበላቸው በሙሉ ልብ ነበር።

የአርበኝነት ዘመን ለአርበኞች ያለው ትዝታ አርበኛ ማለት እርመኛ መሆኑ ነው። እርሙን፣ ተዝካሩን በቁሙ አውጥቶ ለኢትዮጵያ ጉልበት ሊሆናት የሚቀጣጠል መስዋዕት ነው። ነጻነት እስካልተመለሰ ራሱን ምላጭ አይነካውም። ቤቴ ንብረቴ አይልም። ዳኘው የአገሩ ሰዎች ቃሉን ሲያሳምሩት በፊታቸው ላይ እርካታ እየታየ እንደሚሉት “እርመኛ” ሆነ። እርሙን ማን ይበላል?

⅄ ⅄ ⅄

# ክፍል ሁለት

# ይደርስ እንደሆነ እስቲ እጃችሁን ወደ ሰማይ ዘርጉት

የበልግ ዝናም ጀመረ። ኩል መሳዩ ሰማይ በልቃቂት ደመናዎች ሲዥጎረጎር ከርሞ፣ በጥቁር ደመናዎች ተሸፈነ። የሙብረቅ ነጎድጎድ አስተጋባ። በፀሐይ ሙቀት አርሮ የነበረው አፈር የበልግ ዝናም ሲነካው፣ ሽታው አገሩን አጥለቀለቀው። የመሬት ጠረኑዋ እንዴት ደስ ይላል! ።

አሰካለ ዙሪያ ገባውን ያወደውን ሽታ በኃይል ስባ፣ “የአገራችን ሽታ ደስ ይላል።” አለች ነፍስ አባቱዋን እየተመለከተች። እሳቸውም የመንገዱን ግራና ቀኝ አስተዋሉና “አስካለ ማርያም ምን አልሽ?” አሉ። የነፍስ አባቱዋ በክርስትና ስሙዋ ለመጥራት አስካለ ማርያም ይሏታል።

“የመሬት ጠረኑዋ ደስ ይላል ነው ያልኩት አባቴ፣” አለች በትህትና።

“ጥንት በአገራችን ክርስትና ከመምጣቱ በፊት በብዙ አምልኮዎች ብዙ አማልክት ነበሩ።” አሉና ትንሽ እንደማሰብ ብለው ነገራቸውን ቆረጥ አደረጉና “በአገራችን ጥንትም

የመሬት አምላክ የሁሉ የበላይ ነበር። በክርስትናም መምጣት ታላቁ አምላክ እግዚአ-አምላክ-ብሔር-ምድር- እግዚአብሔር ማለት የምድር አምላክ ተብሎ መሰየም ለመሬት ላለን ፍቅር ምስክር ነው፤" አሉ።

አስካለ ይህ ዓይነቱ ነገር ስለማይገባት በትህትና አዳምጣ ዝም አለች። እዳሪው መሬት እየተተረመሰ ባቄላና ዘንጋዳ ሲዘራ መሬትም አፍና ይዛው የነበረው ጠረኑዋ ሲበተን የበልግ ሽታ አገሩን አወደው። የመሬት ጠረኑዋ ደስ ይላል።

አስካለ በእርሻዎች መሃል ካለው አውራ ጎዳና ከሁለት ሌሎች ሴቶች ጋር ወጣ ብላ በአቋራጭዋ ቀጭን መንገድ ውስጥ ገብታ አለፈችና ቀጭኑዋ መንገድ ከዋናው መንገድ ከምትገጥምበት ቦታ ላይ በሻህ ኃይሌ ዘንድ ስትደርስ "አብዬ እኛ ሴቶቹ እንቅደም።" አለችው።

"እንደፈለጋችሁ፣" አለ በሻህ ኃይሌ ፈገግ ብሎ። ከማረፊያቸው ቤት ቀድመው ሄደው ሥራ ለማገዝ እንደሆነ ገብቶታል። አስካለ እንደገና በሌላ አቋራጭ መንገድ ከብዙ ሴቶች ጋር አልፋ ሄደች። ሴቶቹ እየፈጠኑ ሄደው ከተራራው ጫፍ እንደወጡ፣ ወንዶች ገና ከወገቡ ላይ ነበሩ። ሴቶቹም ትንፋሽ ለማግኘት ትንሽ አረፍ ብለው ቁልቁል ሲመለከቱ፣ ወንዶቹ ወደ ላይ ሲያመሩ አስተዋሉአቸውና ተራ በተራ ቃኙዋቸው።

የመንዝ፣ የይፋት፣ የተጉለት፣ አርበኞች መጋቢት 1 ቀን 1929፣ ትላንት፣ ሰላድንጋይ ከተማ በጠላት እጅ እንዳትወድቅ ለአንድ ዓመት ያህል ሲከላከሉ ኑረው፣ ከለቀቁ በኋላ፣ ወደ መንዝ እያፈገፈጉ ነበር።[17]አስተባባሪያቸው ግዛቸው ኃይሌ ቁምጣ ሱሪው ተጨማዶ፣ ነጠላው አደፍ ብሎ እንደነጠላ ጫማው እግሩ አቡዋራ ለብሶ ከተሰማ እርገጤና[18] ከበሻህ ኃይሌ[19] ጋር እየተጫወት ቀና ብሎ ወደ ተራራው ጫፍ ተመለከተ።

ግዛቸው ኃይሌ ተምቤን[20] ጦርነት ላይ ከተሳተፈ በኋላ አስከትሏቸው የሄዳቸውን የመንዝ ሰዎች ቆስሎ ከተኛበት ቃሬዛ ላይ ሆኖ የማይረሱትን ንግግር ያደረገላቸው ነው። "…. እናንት የመንዝ ልጆች ይደርስ እንደሆነ እስቲ እጃችሁን ወደ ሰማይ ዘርጉት፣" አላቸው።

"እንዴት ይደርሳል?" አሉ ወታደሮቹ በመገረም በአንድነት። አንድ የምር ነገር ሊናገር እንደሆነ አውቀዋል።

[17] ንጉሠ ነገሥቱ በመደቧቸው በራስ ከበደ አስተባባሪነት ሰላድንጋይ ከተማ እንዳይያዝ ለአንድ ዓመት መከላከል ተደርጓል። ሰላድንጋይ ከተማ በጣሊያን እጅ ከወደቀች በኋላ አብዛኛው ውጊያ ለተወሰኑ ጊዜያት የማሸመቅ በመሆኑ፣ ራስ ከበደ ሽማግሌ ስለሆኑ፣ እጅ ሰጥተው ወደ ውስጥ አርበኛነት ተዛወሩ። ግዛቸው የመንዝ፣ ይፋትና ተጉለት አስተባባሪ ሆነ።

[18] ልጅ ተሰማ እርገጤ ዝነኛ የይፋት አርበኛ የነበሩ በኋላም ደጃዝማች።

[19] ባላምባራስ በሻህ ኃይሌ የተጉለት አርበኛ ከነጻነት በፊት መስዋዕት ሆነ።

[20] ማይጨው ተብሎ የነበረው ተተንትኖ።

“እንግዲያውስ መንዝም የዚያን ያህል ሩቅ ነው። መንዝ ተመልሰን እንገባለን ብለን ከማሰብ፣ ከዚሁ በጀግንነት እስከ መጨረሻው መዋጋት አለብን።”

ጦርነቱ እንዳበቃ ግን ወታደሮቹ በቃሬዛ ይዘውት ከትግራይ[21] መንዝ ገቡ። ግዛቸው ከቁስሉ እንዳገገመ ከይፋት፣ ከተጉለትና ከመንዝ አርበኞች ተጻጽፎ አስተባበራቸው። መጀመሪያ አብረውት ለመሥራት ከተስማሙት ሰዎች የተጉለት አርበኛው በሻህ ኃይሌ ነበር። ቀስ በቀስ ከይፋት የጦር መሪ ባሻ ተሰማ እርገጤ፣ ከመንዝ ከፈለው ወልደ ጻዲቅና ሌሎች አስተባባሪነቱን ሲቀበሉ ደጃዝማች አውራሪስና ቀኛዝማች አበበ አውራሪስ[22] የጦር እቅድ ለማስተባበር ተስማሙ። ከዚያም የመንግሥት የነበረውን እህል በጠላት እጅ ሳይገባ ጎተራውን ከፍቶ ለሕዝቡ አከፋፍሎ አርበኝነቱን ጀመረ። ጣሊያኖችንም ከጣርማ በር ወደ ሰላድንጋይ አላነቃንቅ ብሎ ለአንድ ዓመት በመገተሩ ዝናው ታዋቂ ሆነ።

በተለይ የመጀመሪያው ጦርነት በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ የሞራል ተሃድሶ የፈጠረ ስለነበር ትዝታው ገናና ነው። ጳጉሜ 3 ቀን 1928 የጣሊያን ጦር ወደ ሰላድንጋይ ሊያመራ ሲል ጣርማበር ላይ የይፋትና የተጉለት አርበኞች ገጥመውት ሲዋጉ፣ ግዛቸው ኃይሌ የመንዝን አርበኞች አስከትሎ መጥቶ ባደረጉት ውጊያ ጣሊያን ተሸንፎ ተመለሰ። ተጉለትን እንዲጠብቁ በሻህ ኃይሌና ተሰማ እርገጤ ተጉለት ሲቀሩ ግዛቸው ኃይሌ መንዝ ሲመለስ አገሩ በሙሉ አዲስ ልብ ዘራበት። በማይጨው ሽንፈት፣ በንጉሡ መሄድ ልቡ የተሠበረው ሕዝብ ተስፋ ልቡን አሞቀው። ከዚያም ጣሊያኖች በተደጋጋሚ ያደረጉት ሙከራ ከሸፈ። በተለይ በየካቲት ወር ላይ አርበኞች ጣሊያንን ቢያርበተብቱትም፣ በመጨረሻ ግን ኃይሉን አጠናክሮ አርበኞችን ጥሶ፣ ከአንድ ዓመት ውጊያ በኋላ ሰላድንጋይን ያዘ። በዚህም የተነሳ የይፋት፣ የተጉለት፣ የመንዝ አርበኞች ወደ መንዝ እያመሩ ነበሩ።

ከሰላድንጋይ ከተማ ተራራውን ወርደው፣ ትንሿን ጅረት ተሻግረው፣ ሌላውን አቀበትና ተራራ ወጥተው፣ እንደገና ወርደው፣ ሌላ የምንጭ ውሀ ተሻግረው፣ እንደገና ወጥተው ወርደው፣ ሌላ አቀበት ሲጀምሩ ግዛቸው ከተራራው ጫፍ የተቀመጡትን ሴቶች አይቶ “ጎበዝ እኛም አረፍ እንበል። ካለዚያ ሴቶቹ ከኛ ብዙ ለማራቅ ሲሉ ልባቸው ይፈነዳል፣” አለ ፈገግ ብሎ።

ሁሉም በየድንጋዩና ሳሩ ላይ እንደተቀመጠ፣ አንደኛው አርበኛ ትላንት የተገጠመውን ግጥም በሽለላ ደገመው።

እሪ በሉ ለመሬ ንገሩ፣

እሪ በሉ ለአዳባይ ንገሩ፣

---

[21] እንደላይኛው ማይጨው የሚለው ተለውጧል።

[22] ደጃዝማች አውራሪስ ቀኛዝማች አበበ አውራሪስ (በኋላ ደጃዝማች) አባትና ልጅ ሲሆኑ የታወቁ የመንዝ አርበኞች ናቸው። ደጃዝማች አውራሪስ ሽማግሌ በመሆናቸው ምክራቸው ጥልቀት ያለው ነው። የአርበኝነት ደብዳቤዎቻቸው ይህን ይመሰክራሉ።

እሪ በሉ ለደብብ ንገሩ፣

ልቦናዬ ያውቃል ሰምተው እንዳይቀሩ፣

መሳቁ ለቀቀ ተከፈተ በሩ።

“ይፋት ያንን ሁሉ ጣሊያን ተሰማ እረፍርፎት፣ ያንን ሁሉ መኪናውን አቃጥሎት፣ አፈግፍጎ ተጉለት ቢቀመጥም፣ ተሰማ በጉልበቱ አላነሰም፣ ጣሊያንም አላረፈም።” አለ ግዛቸው ኃይሌ። “ዛሬ ደግሞ ተጉለትን ለቀን ወደ መንዝ ስንሻገር፣ እኛ ተዳከምን፣ ጣሊያን ጠነከረ ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ፊቱን ይመልስልናል።”

“ለኛ ላዩም ፊለፊት ገጥመን አናሳልፍም ብለን ለመያዝ ስንሞክር በጥይትም ማለቅ፣ በሰውም መጎዳት፣ ይደርስብናል።” አለ ተሰማ በይፋት ጦርነት ያጋጠመው ትዝ ብሎት። “ለኛ የሚሻለን ጣሊያንን የቻልነውን ያህል እያጠቃን መዘዋወሩ ነው። ከተቻለም ገድቦ መያዝ ነው።”

በሻህ ኃይሌ አቅራሪውን በቀለን ጠቀስ አደረገው። “ያችን የትላንቱዋን በላት፣” አለው ቀስ ብሎ። ሽፈራው እርገጤ[23] ፉከራውን መጀመሪያ ያላት ተምቤን[24] ጦር ሜዳ ሲሆን በቀለ በቃሉ ይዟታል። ዛሬም ቦታው መሆኑን አውቆ ቀጠለ።

እኒያ ብዙ ናቸው፣ እኛ ጥቂቶች ነን ብሎ ይላል ፈሪ፣

አንድ አንበሳ እንጂ ነው ሺ ላም አስደንባሪ።

ሴቶቹም ከአፋፉ ላይ ሆነው የፉካሬውን ድምጽ ሰምተው ፊታቸውን ዘወር አድርገው መንዝን ተመለከቱ። “ማነው እሱ?” አለች አስካለ።

“የከፈለው ወልደ ፃዲቅ አሽከር ነው።”

“ድምጹ እንደ ቁመቱ አይደለም።” አለች ሳቆቴ እየሳቀች።

“ቁመቱ ባይረዝም ምን አለ።እሱ የጣሊያን ንጉሥ አሽከር አይደል።” አለች አስካለ የጣሊያኖችና ይዘዋቸው የመጡት የሱማሌና የሊቢያ ወታደሮች ቁመት እየታያት። በአገራቸው እንደነዚህ ዓይነት ረጃጅም ሰዎች የተለመዱ አይደሉም። “እረፍቱ ይብቃን እንጓዝ፣” አለች አስካለ።

ሴቶቹ ተነስተው ጉዞአቸውን ከቀጠሉ በኋላ ቆይተው ወንዶቹ ጉዞ ቀጠሉ። ማፈግፈግን መሸነፍ አድርጎ ያልወሰደ ልበ ሙሉ ጦር ነው። ያርበኛው ጦር ከተራራው ጥገት

[23] ሽፈራው እርገጤ በኋላ ደጃዝማች። የጣሊያን ፋሽስቶች ከነጻነት በኋላ የሚሠሩትን በመመልከት፣ ትጥቃቸውን ሳይፈቱ፣ ከጦሳ ተራራ ጥግ እንደ መሸጉ፣ አርጅተው ሞቱ።

[24] እንደበፊቱ

ወደ ጫፉ ሲጉዋዝ ይዟት የነበረችው ትንሽ ባንዲራ በሃይል ተውለበለበች፡፡ አስካላም መለስ ብላ ባጋጣሚ አይታት "ውይ ደስ ስትል፣" ብላ አሰበች፡፡ እንዳትቀደድ ግን ሳስታ ቅሬታ ተሰማት፡፡ ማለቅ፣ መቀደድ፣ ማርጀት ባይኖር ኑሮ አንዳንድ ነገር ሁልጊዜም ቢያዩት፣ ቢለብሱት ደስ ይል ነበር አለች፡፡ ብዙ ሴቶች የቀሚሳቸውንና የነጠላቸውን ጥለት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ያደርጋሉ፡፡ አስካለ ሰላድንጋይ አንድ የመንደር ልጅ ጋር ስትጫወት "ይች ደስ የምትለዋ ምንድናት?" ብሎ ባንዲራዋን ሲጠቁማት ስቃ የምትመልሰው አጥታ "የአገራችን ምስል ናት፣" ብትለውም ሳይገባው የቀረው ግን ደስ የምትል ያለው ትዝ ብሏት ብቻዋን ፈገግ አለች፡፡

አርበኞች ከማረፊያቸው ቤት ሲገቡ እነ አስካለ ከቤቱና ከመንደሩ ሴቶች ጋር ተደባልቀው የሚበላውን የሚጠጣውን እያዘጋጁ ነበር፡፡ አርበኛውም እህሉን እየቀማመሰ ስለ ጦርነቱ ብዙ አወራ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስለሚደረገው ቁርጥ ያለ ነገር ባለመታወቁ ነገሩ ይዘለል ነበር፡፡

በበነገታው አስካለ ከምታውቃቸው ብዙ ሰዎች ጋር ተሰነባብታ ከበሻህ ኃይሌና እሱ ከዳረላት ከባልደረባው ከአዲሱ ባሉዋ ለገሥ ጋር ወደ ደንገዜ አመራች፡፡ ከፈለው ወልደ ፃዲቅ ገዘት ወዳለው ቤቱ፣ ግዛቸው ኃይሌ መንዝ ሞላሌ አቅራቢያ ካለው ቤቱ እስከነሰዎቻቸው ሲያመሩ አስካለ ያለችበት የበሻህ ኃይሌ፣ የአየለ ኃይሌ፣ የደስታ ሽዋርካብህ፣[25] የተሰማ እርገጤ ጦር ወደ ደንገዜ እያመራ ነበር፡፡

ጦሩ እንደገና ተመልሶ እንዴት እንደሚሰባሰብ፣ እንደሚረዳዳ በውል መመሪያ አልተሰጠም፡፡ አስፈላጊም ሆኖ አያውቅ፡፡ ሁሉም በተራራማው አገር ከአንድ ጫፍ እንደ ሠንሠለት ባሉት ተራሮች ጫፎች ሆነው በጥሪና በኡኡታ ድምጽ በሚያስተላልፉ ሰዎች መገናኘት ይችላሉ፡፡ የወንድሙን ኡኡታ ሰምቶ ደግሞ የሚቀር የለም፡፡ እንኳንስ በጦር ሜዳ ብዙ ቀን አብረው የዋሉ ሰዎች ቀርተው ሁለት የማይተዋወቁ ሰዎች ተገናኝተው ሁለቱም አርበኞች ከሆኑ ከናት ልጅ በላይ ይቀራረባሉ፣ ይተማመናሉ፡፡ የኢጣሊያ ጦር ሰላድንጋይን ለአንድ ወር ከሃያ ስድስት ቀን ከያዘ በኋላ ምንም ችግር ስላልገጠመው መንዝን ለመያዝ ፕላኑን በማገባደድ ላይ ሲሆን አርበኞቹም ኃይል ለማሰባሰብ በሚያደርጉት ጥረት ወቅቱ የበልግ እርሻ ጊዜ በመሆኑ ጭምር አስቸግሮአቸው ነበር፡፡

የሰማዩ ደመና እንደሚያመጣው መከበድ የክረምቱ ወራት ሁሉንም ቀን እንደ ከበደ አይደለም፡፡ የበልግ ሰማይ ደግሞ ወዲያው ጭልም ወዲያው ቦግ ይላል እንጂ በጉም ተሸፍኖ አይውልም፡፡ ስለዚህ ሰማዩ ኩልል ብሎ የደመና ቁራጭ እንኳን ከማይታይበት ባዶ መስሎ ከሚያስፈራው የበጋ ሰማይም የተሻለ ነው፡፡ ሚያዚያ 26 ቀን የበልግ ደመና አሸግሽጎ ኩል

---

[25] አየለ ኃይሌ፣ ደስታ ሽዋርካብህ በኋላ ደጃዝማች፡፡ የታወቁ የሸዋ አርበኞች ናቸው፡፡

ሰማይ በነበረበት ወቅት ኡኡታው ከአገር አገር አስተጋባ። አርበኞች ከያለበት ቦታ ወደ ገዘት የተጉለትና የመንዝ አዋሳኝ መሩዋሩዋጥ ጀመሩ።

አርበኞች ተበታትነዋል ብሎ የተዘናጋው የፋሺስት ጦር ወደ መንዝ ዘልቆ ሲዳከር በፕላንና በዕቅድ በተመራ ክብ ውስጥ ሳይሆን ከየአቅጣጫው በገነፈለ አርበኛ ተከቦ ብትንትኑ ሲወጣ ወንዱም ሴቱም የሚሸሸውን የጠላት ጦር በዱላና በድንጋይ እየደበደበ ጠበንጃውን እየማረከ ዘፈነ። የመንዝ ሕዝብ ባልታሰበ ሁኔታ ታጠቀ። አምልጦ ሳሲት የገባው አዝማች ኢጣሊያዊ ከጎኑ የተሰለፉት ባንዳዎች አውቀው ተማርከው ያስጠቁት ይሁን ወይም በጥንት ዘመን አባቶቹ ሮማውያንን የጀርመን ዘላን ጦር ባልታሰበ በሁሉም አቅጣጫ በመግፋት እንዳሸነፋቸው ዓይነት ይሁን ለመወሰን አስቸግሮት ሲያስብ ቆይቶ ባንዳዎቹን ጨፍጭፎ ማሳበቢያ አደረጋቸው።

የመንዝ ሕዝብ ያልታሰበ ደስታ ብዙ ሳይቆይ ሚያዚያ 29 ቀን ፀሐይዋ ፈገግ እንዳለች ሰማዩ በጉርምርምታ፣ አየሩ በማዕበል ተሰነጠቀ። ብዙ አውሮፕላኖች የመንዝ መንደሮችን መደብደብ ያዙ። የፋሺስት ሠራዊት በየአቅጣጫው ወደ መንዝ ገባ። መንዝ በአራቱም ማዕዘን ተከባ የሽብር፣ የእሳት፣ የዋይታ መንደር ሆነች። በአሥረኛው ቀን አንድም ሰው አይተርፍም የተባለው ቢቀርም አንድም የሳር ክዳኑ ላይቃጠል የቀረ ቤት ግን አልነበረም።

የመጀመሪያው ሌሊት ያልታሰበ ነበር። ሌሊቱ እንደ ችቦ በሚንቀለቀሉት ቤቶችና ጢሻዎች ብርሃን ሆነ። አገር በጢስ ታፈነ። ሽማግሌ፣ አዋቂ፣ ሕፃናት የሞቱባቸውን አፈር አልብሰው ሌሊቱን ሰማዩን ጣሪያቸው፣ ተራራዎችን ግድግዳቸው አድርገው ጋደም አሉ።

ሁሉም ጸጥ ብሏል። ግዛቸው ኃይሌ እንኳን የተለመደውን ፉከራውን፣

ግዛቸው ኃይሌ፣ ኃይሌ ዋጫራ፣

ነፍስ አሰናባች በጀርመን ሥራ።

እያለ አልተንጎራደደም። አንዳንድ ነገር ከጨኸትም ያግዳል። አርበኞች ቆመው የሚቃጠሉትን መንደሮች በትካዜ ያያሉ።

አስካለ ብዙ ቆይታ አጎቱዋን በሻህ ኃይሌን ቀና ብላ አስተዋለችው። የሚቃጠሉትን መንደሮች በትካዜ አይኑዋን ተክላ ስትመለከት ነበርና አሁንም ዞር ስትል የመጎርበጥ ስሜት ብቻ ሳይሆን አጎቱዋም በደንብ አልታይ አላት። ዓይኑዋን በመዳፉዋ ጠራርጋው እንደገና ተመለከተች። ተክዞዋል።

“አብዬ የዚያን ጊዜ አንተም የጣሊያንን ካሚዎኖች ስታቃጥላቸው የተንቦገቦጉት እንደዚህ ይሆናል፣” ስትል ፈገግ ብላ ነገሩዋን በክፉ እነዳይተረጉምባት ተጨንቃ ተመለከተችው። ቀና ብሎ ተመለከታትና ፈገግ አለ። አስካለም ደስ አላት። በሻህ ኃይሌ ተስፋ እንዳልቆረጠ አወቀች።

ዝምታ ግን ወሰን ስላለው አርበኞች ወደ ጦርነቱ ቦታ በየአቅጣጫው ወረዱ። ተሰብስበው ስለ ሁኔታው የተወያዩትም ከአሥራ አምስት ቀናት ያላቋረጠ ውጊያ በኋላ ነበር።

⅄ ⅄ ⅄

# ክብ ሲሰበር

"ጣሊያን ባሻገራችን እንደምናየው ሰላድንጋይና ሞላሌ ላይ መመሸጉ ብቻ ሳይሆን ዙሪያችንን እየከበበንና የሕዝቡን ልብ ለመስበር ካለማቋረጥ በአውሮፕላን እያቃጠለው ነው። [26] ይህንን ቀውጢ ቀን አፈግፍገን ብናሳልፈው እንደገና ተጠናክረን ተሰባስበን ለማጥቃት እንችላለን።" አለ በሻህ ኃይሌ[27] ሁሉም የጦር መሪዎች ከበቅሎዎቻቸው ወርደው መቀመጫ እስቲዘጋጅላቸው ከአፋፉ ላይ ቁልቁልና አግድም ያለውን አገር በሚቃኙበት ጊዜ።

አሽከሮችና ጋሻጃግሬዎች የየበቅሎዎቹን ድልድልና ግላስ እያነባበሩ የሚደሉ መቀመጫዎች እያዘጋጁ ነበር።

"ሌሎቻችሁስ ምን ታስባላችሁ?" ሲል የተንጨበረረውን ጒፈሬውን ቁጥርጥሩን ፈትቶ ይጨርሰው ይመስል ሥራቸው በተግተረተረ ቅጫጭን ግን በጣም ጠንካራ እጆቹ እያድበሰበሰ ጠየቀ። ግዛቸው ኃይሌ[28] ነበር።

ተሰማ እርገጤ[29] መቀመጫዎች እንደተዘጋጁ ተመልክቶ "ቦታችን ተዘጋጅቶልናል አለና ግዛቸው ኃይሌ ከተቀመጠ በኋላ ተቀምጠው የሱን ሃሳብ መስጠት ቀጠለ። "የኔም ሃሳብ እንደ ልጅ በሻህ ነው። ባላምባራስ አበበ አረጋይ በጅሩ በኩል ከፍተኛ ጦር አሰባስበው ተጠናክረው ይገኛሉ ይባላልና ወደዚያ ሄደን የጣሊያን ጦር እንደ ደራሽ ውሀ እንደመጣ

[26] አርበኞች የቦንብ ድብደባውን በቃጠሎ የሚገልጹበት ምክንያት ከላይ እንደተገለጸው የኬሚካል ጥቃቱ በዓለም ላይ እስከዚያ ጊዜ (በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጭምር) ታይቶ የማይታወቅና አገሩን በሳት የሚሸፍን ስለሆነ ነው። "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" በሚለው መጽሐፍ ጃንሆይ ለዓለም መንግሥታት ጉባዔ ያደረጉትን ንግግር ተመልከት። ይህ መርዝ እስካሁን ከሚታወቁት ውስጥ በቬትናም ሥራ ላይ የዋለውን ኦሬንጅ ኤጀንትን ይመስላል።

[27] ባላምባራስ በሻህ ኃይሌ የተጉለት አርበኞች መሪ። ከነፃነት በፊት መስዋዕት የሆነ።

[28] ልጅ ግዛቸው ኃይሌ መጀመሪያ በራስ ከበደ ስር በኋላም ራሱን ችሎ የመንዝ፣
ተጉለትና ይፋት አርበኞች አስተባባሪ የነበረ። ከነፃነት በፊት መስዋዕት የሆነ።

[29] በኋላ ደጃዝማች ተሰማ ዕርገጤ የይፋት አርበኞች መሪ።

እስኪጎድል ድረስ ከዚያ ሆነን እናጥቃው፣" አለ ተሰማ እርገጤ ይፋት ላይ ሰባ የጣሊያን ካሚዮን ያቃጠለው ተጉለት ላይ ብዙ ጀብዱ የሠራው፣ ቦታዎችን መዘዋዊያና ማጥቂያ እንጂ ሌላ አድርጎ የማይወስደው።

"ወንድሞቼ ሌሎቻችሁስ?" አለ ግዛቸው ቀና ብሎ ወደ እነ ልጅ ከፈለው ወልደፃዲቅ[30] እየተመለከተ።

በአንድ ድምጽ ሁሉም መልካም ነው፣ መልካም ነው፣ ሲሉ አጉተመተሙ።

"እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ብዙ ታምራት አድርጎልናል፤" ሲል ጀመረ ግዛቸው ኃይሌ። "ይኸው ለአንድ ዓመት ጣሊያንን ሰላድንጋይን ሳናስነካ ገትረን ይዘነው ቆይተን የነበረ ከጣሊያን የበለጠ ሰውና መሣሪያ ኖሮን አይደለም። በቅርቡ የንጉሥ ኢሬ አሸከር የሙሶሎኒ ጅል ሁሉ ወደ መንዝ ሊሻገር ሲል ገዘት ላይ ድል አድርገን ሴቶች እንኳን በዱላና በድንጋይ ጠበንጃ ለመማረክ የበቁት በኢትዮጵያ አምላክ ድጋፍ ነው። ዛሬ ደግሞ ጣሊያን ከአውራ ጎዳናዎች ወጥቶ ከመሃከላችን መሽጓል።

ይህ ዘላቂ አይሆንም። ወንድሜ ተሰማ እንዳለው ጎርፍ ሲመጣ ሃይለኛ ቢሆንም ቆይቶ መጉደሉና ማሻገሩ አይቀርም። ሁሉም በእግዚአብሔር እጅ ያለ ነው።" አለና እንደ መተከዝ ብሎ ሃሳቡን እንዴት እንደሚያስቀምጠው አሰላስሎ፣ "የወንድሞቼን ሃሳብ ማቃለሌ ሳይሆን ከዚህ መቆየት እወዳለሁ። እናንተ እንደ ሃሳባችሁ ወደዚያ ሄዳችሁ፣ አምላክ ካለ ተመልሰን እንገናኛለን። ወልደ መስቀል ተሸበሩ [31] መንገዱን ስለሚያውቀው እየመራችሁ ይሂድ። እግዚአብሔር አምላካችን የሚሠራውን ተአምር እስቲገልጽ ድረስ፣ መንዝን፣ ተጉለትን፣ ይፋትን ለቅቄ አልሄድም። የሕይወቴ ፍጻሜ እዚሁ ቢሆን እወዳለሁ።"

"አይሆንም ጌታዬ!" አለ ተሰማ እርገጤ ያቀረበው ሃሳብ ባላሰበው መንገድ በመሄዱ ተበሳጭቶ። "አብረን እንጂ አንተን ጥለን እንሂድ አላልንም፤" አለ በሻህ ኃይሌም ቅር ብሎት።

"በእርግጥ! በእርግጥ!" አሉ ብዙ ድምጾች።

"አይደለም ወንደሞቼ የናንተ ሃሳብ ጥሩ ነው። መሄድ አለባችሁ። ሁላችንም ከዚህ መቆየት የለብንም። ምክንያቶች አንደርድር፣ መሄድ አለባችሁ.........." ሃሳቡን

[30] በኋላ ደጃዝማች ከፈለው ወልደፃዲቅ ። ታላቁ ሰው ከፈለው፣ ደጋፊዎቹ በነጻ ክልሉ ካለ ሥጋት እያረሱ እንዲኖሩ በማስቻል፣ ባንዳዎችን ካለምህረት በመቅጣት፣ ነጻ ክልሉን አስፋፍቶ፣ በተራውም ሰው፣ በቀድሞ ሹሞችም ተፈርቶ፣ ተከብሮ ያስተዳደረ ጀግና።

[31] በግዛቸው ሥር የነበሩ። በአርበኝነቱ ዘመን ይሙቱ ወይም ከነጻነት በኋላ ያልተረጋገጠ።

ለመሰብሰብና እንዴትም ሊያሳምናቸው እንደሚችል በመጨነቅ፣ ጭንቅላቱን ቀና አድርጎ ሰማዩን ተመለከተ። ከወደ ዋሲያ ተራራ በኩል ጥቁር ጉም ሰማዩን እያለበሰው ይጠጋል።

“ዝናብ ሊመጣ ነው።” አለ የግዛቸውን ዓይን ተከትሎ ሰማዩን የተመለከተ አንድ አርበኛ።

“አይዘንብም፣” አለ ግዛቸው ኃይሌ “ዋሲያ ተራራ በከበደ ጊዜ ከዚህ አይዘንብም። ከዚህ የሚዘንበው በደንገዜ በኩል ሲጨልም ነው።” ይህንንም ብሎ ወደ ደንገዜ ተመለከተ። የሁሉም ዓይን ወደዚያ አተኮረ። “አያችሁ ደንገዜመ ጠቁሩዋል፣ መዝነሙ አይቀርም። ቶሎ ብለን ስብሰባችንን ጨርሰን መበታተን አለብን። እኔ ወደ ደንገዜ እወርዳለሁ። ከዚያ ምንም ጉዳት አይደርስብኝም። እናንተም ወደ ባላምባራስ አበበ [32] መሄድ አለባችሁ። ይህ እንግዲህ ቁርጥ ነው። ዝናቡ ደረሰብን፣ የግዜር ያለህ፣ ጎርፍ እኮ ነው......ጎበዝ በሉ በዚህ ይብቃ ተነሱ።” ብሎ ወደ መጠለያው አመራ። ሁሉም በሁካታ ተከተሉት። ሁሉም በየመንደሩ ቤቶች ተበተኑ። ለገሠ፣ የአስካለ ባል፣ የአስካለ ዘመድዋ ከሚሆን አይፎክሩ ከሚባል ሰው ቤት ከስብሰባው መልስ ሲገባ፣ አስካለ በሩቅ አይታው ስለነበር፣ “እርሰህ የለም እንዴ? ጋቢህን አውልቅና ዘርረው፤ እስከዚያ እንካ የኔን ልበስ፣” አለችው። ጋቢዋን አውልቃ ከአይፎክሩ ሰቀላ ቤት አስቀምጣ እሱዋ አዳራሹ ከብዙ ሰዎች ጋር ስለነበረች ለገሠን በሩቅ ስታየው ሮጣ ከሰቀላው ቤት ገብታ፣ እድሞውን ሲገባ፣ ጠርታው ነበር የመጣው።

“ልበሰው፣” አለችው። ጋቢውን ተቀብሏት እቅፍ አድርጎት እሷን ሲመለከት፣ የታጠቀውን ዝናርና አፈሙዙን ወደ ሰማይ አድርጎ ያነገተውን ጠበንጃውን እያየች። ጋቢውን ሲለብሰው ዝናሩም ጠበንጃውም ተሸፈኑ።

“አስካለ ምን ታስቢያለሽ? አጎትሽና ሌሎቹ ወደ ባላምባራስ አበበ ጋ ለመሄድና ይህን ጊዜ ለማሳለፍ ይፈልጋሉ......። ልጅ ግዛቸው ግን ከዚህ አልሄድም ብለዋል፣” አለ በሻህ ኃይሌን አጎትሽ ብሎ። የሩቅ ዘመዳሞች ወንድም እህት ቢባሉም ታላላቆች አክስት፣ አጎት ስለሚባሉ።

“አብዬ በሻህስ?” አለችው እሱ ከበሻህ ጋር መቆየት ተግባሩ እንደሆነ ለማስታወስ። አጎትሽ ብሎ የተናገረውን ሳታጤነው።

“እሳቸውማ የመሄዱ ሃሳብ አመንጭዎች ውስጥ ናቸው፣” አለ ለገሠ አስካለ በማያስፈልግ ነገር በመቆጣቱዋ ከፋ ብሎት።

---

[32] ባላምባራስ አበበ በኋላ ራስ አበበ አረጋይ ። የአርበኞች መሪና እውቅ ስትራቴጂስት።

"እንሄዳለና ምን ጥያቄ አለ። ልጅ ግዛቸው አይሄዱም። ልጅ ግዛቸው ከሁላችንም ለየት ያሉ ናቸው።" አለች አሁንም እንደከፋት።

ለገሠ በሃሳብ ተዋጠ። አስካለም ከራሱ ጋር ተሟግቶ ውሳኔ እንዲደርስ ዝም አለችው። ማንም ሰው መልካሙንና መጥፎውን መንገድ ለመለየት የሚያዳግተው የለም። ዋናው መቁረጥ ነው ስትል አሰበች።

ከበራፉ ላይ ቆም ብላ የሚወርደውን ዶፍ ተመለከተች። ወደ መስክ ባልተሰማሩት በሬዎች ላይ የሚወርደው ዝናብ እያጠባቸው፣ ፍዝዝ ብለው ቆመዋል። ብዙ ጊዜ በተመለከተቻቸው ቁጥር የነሱ መደበት ወደ እሱዋም ተሸጋገረ። ድሮ በሚያዚያ ዝናብ አይጥልም ነበር ስትል አሰበች። ወዲያው መብረቅ ሰማይና መሬቱን አናጋው። አስካለም ከሰመመን ወጥታ "ውይ!" ብላ ጮሃ ወደ ውስጥ ገባች። መብረቅ ሲጮህ በኃይል ትፈራለች። "ለገሠ እንዴት ደነገጥኩ!" አለችው።

"አይዞሽ፣" ብሏት እሱም ከሃሰቡ ነቅቶ ሳቀ። "አሁን እንግዲህ ያባራል፣" ብሎ ከመደቡ ተነስቶ ጋቢውን እንደማራገፍ አድርጎ፣ ራሱን ሽፍኖ፣ ዝቅ አድርጎ ለብሶ፣ ወደ በራፉ ተጠጋና ተመለከተ። "ቀኑም መሽቷልና፣" አለ በመገረም። ለማንም የተናገረው አልነበረም። መልስ የሰጠውም የለም።

"ራት ቀርቡዋል ከአዳራሹ፣" አሉ የመንዝ ወርቅ[33] በአውሮፕላን ቦምብ ከተቃጠለ በኋላ ለይድረስ ይድረስ እንዳኳኋኑ ጣሪያ የተበጀለትን ቤት እያመለከቱ። በሃይል ከመጨለሙ በፊት ካልተበላ በኋላ በምን መብራት ይበላል። አንትሽ አስካለ ዪት ሄደች ብሎ ሲጠይቅ ነበር፣" አሉና "ሁለታችሁም ተነሱ፣" ብለው ወደ አዳራሹ ገቡ። አስካለ ወደ ማዕድ ቤት ሴቶቹን ሥራ ልታግዝ ስትሄድ፣ ለገሠም ከአዳራሹ ገባ።

"ነወር! ነወር!" አሉት ብዙ ሰዎች ከመቀመጫቸው እንደመነሳት ብለው አንዳንዶቹም ቆመው።

"ኧረ በእግዜር፣" ብሎ ግራና ቀኙን ሳያይ ሮጥ ብሎ ተቀመጠ። ከየአቅጣጫው የተለያዩ ሀሳቦች እየቀረቡ ይነፍሳሉ። አንዱ ያለውን

ሌላው ይደግመዋል። ጨለም ባለው ቤት ውስጥ ክርክሩ ደርቱዋል።

"ለመሆኑ የመሄዱ ሃሳብ ጥሩ ነወይ? ከዚያስ ጣሊያን አለ አይደለሞይ?" አለ ከመሃከላቸው አንዱ። የልጅ ግዛቸው ሃሳብ ስለተስማማው ከዚሁ ለመቅረት ወስኑዋል።

[33] የመንዝ ወርቅ የበሻህ ኃይሌ ባለቤት የነበሩ ናቸው።

“ከዚያም ጣሊያን ቢኖር በተዳከመ ኃይል ነው። ሃሳቡ መጀመሪያ ይህን አካባቢ አጥፍቶ ወደ ሌላ አካባቢ ሃይሉን ማዞር ስለሆነ አሁን ለጊዜው የተጫነን እኛን ነው፣” አለ ሌላ አርበኛ በስሜት ለምን እንገፋፋለን በሚል ዘይቤ።

“በምን ይታወቃል?” አለ የመጀመሪያው ተናጋሪ። ተከራክሮ ለመርታት ወይም ለመረታት ሃሳብ ስለሌለው፣ በግዴለሽነት ሃሳቡን ጣል አድርጎት።

“ሁልጊዜም ስናየው የኖርነው ነው። እኛ እራሳችን ጠላት ባንድ በኩል ብቅ አለ ሲሉን እንደምንሰባሰበው፣ ጠላትም አንድ አካባቢን ለማስለቀቅ ሞክሮ ሲያቅተው ከሌላ ቦታ ያለውን ጦሩን ወደዚያ ያዞራል።” አለ ሁለተኛው ተናጋሪ፣ ምኑ አልገባህ ብሎ ነው ለማለት ትከሻውን ንቅንቅ አድርጎ።

“ባላምባራስ አበበ አረጋይ ደግሞ ኃይላቸውን አጠናክረዋል፣” አለ ለገሠ ከጨዋታው መሃል ሳይታሰብ ጣልቃ ገብቶ።

“እኛም ጠንካሮች ነበርን፣” አለ የመጀመሪያው ተናጋሪ። “ሃሳቡ መጥፎ ነው ብዬ ሳይሆን የልጅ ግዛቸው መቅረት አባብቶኝ ነው።”

አንድ ፎካሪ ተነስቶ፣

ጣሊያን ተሰብስቦ ሲጫወት ገበጣ የአባ ተግብ አሽከር ጅም አፍራሹ መጣ።

አለ። አባ ተግብ የግዛቸው ኃይሌ የፈረስ ስም ነው።

“አሁን የመፎከሪያ ጊዜ አይደለም። ወደ ጨዋታችን እንመለስ። ጣሊያን አሁን ያተኮረው በመንዝ ላይ ነው። የጎንደሩን፣ የወሎውን፣ ጦር፣ ከደብረብርሃኑ ጦር ጋር አዳብሎ፣ ሲከብ እንደነበር ቀደም ሲል ከውስጥ አርበኞች ደርሶን ነበር። ምን ያከራክራል። የኛ መሄድ ደግሞ ልጅ ግዛቸው ያዘዙት ነው፣” አለች አስካለ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን በሻህ ኃይሌ መሬቱን በጠበንጃው ሰደፍ እየቆረቆረ ዝም ብሎ ተቀምጦ ነበር። አስካለ አጎትዋን ይህን ሁሉ ንትርክ ማዳመጡን አልፈለገችም። “አብዬ እግርህን ልጠብህ?” አለችው።

“ተይው፣” አለ በመገረም። “ልጆቹ ያጥቡኛል፣” አለ።

“ምናለ አጥብሃለሁ። ደግሞ ዛሬ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው?” አለች አስካለ ጥሩ ሰራሁ ብሎ ሲቆጡት እንደሚከፋው ልጅ ቅር ብሎዋት።

“ድሮ ልጅ ነበርሽ። ዛሬ አግብተሻል፣ ወልደሻል።” አለ። ድሮ ወጣት ሳለ አያቱዋ ቤት ሲመጣ ትልቅ ውለታ የሠራችለት መስሎዋት ሳይሆን ፍቅሩዋን ለመግለጽ ለእግሩ ውሀ

የምታሞቅለት፣ የምታጥበው ትዝ ብሎት፣ ነገር ግን አሁን እሱ ብዙ አሽከሮች[34] እንዳሉት ማስታወሱን ባለመፈለግ።

“አትቀልድብኝ።” አለችው እግሩን እየጎተተች።

“ይሁን እሺ። እግዜር ይባርክሽ።” ብሎ እግሩን ከጣባው ከተተ። ቀስ ብላ በሞቀው ውሀ እግሩን ስታሽለት፣ ስለጥንት አያቱዋ ጋር ኑሮ ስታጫውተው፣ እሱም በሱዋ ወሬ ተስቦ፣ እንደዚሁ እራሱ ያጋጠመውን ታሪክ ሲያወራት፣ በአካባቢው ስላለው ነገር አላዳመጠም። ከዚያም እግሩን ታጥቦ ሊጨርስ ሲል፣ “አስካልዬ እቴ፣ አንቺን ባላገኝ እንዴት ይቆጨኝ ነበር፣” በማለት ራሱዋን እያሻሸ በአጎት ፍቅር ተመለከታት። እሱዋም ደስ ብሏት እንደ ልጅነቱዋ እራሱዋን አወዛወዘች። “ባልሽን አጫውችው።” ብሎ አሰናበታት፣ በወታደሮቹ ፊት መለሳለስን በማሳየቱ፣ እንደማፈር ብሎ።

“ጎበዝ እንግዲህ ጉዞአችንን መቀጠያችን ጊዜ ደርሱዋል። ፈጠን ብላችሁ ተነሱ።” ብሎ ከመቀመጫው ተፍ ብሎ ተነስቶ፣ ጠበንጃውን ጠበቅ አድርጎ ይዞ፣ አካባቢውን ተመለከተና ወደ ውጭ ለመውጣት ራመድ ሲል፣ ጋሻጃግሬው ተወርውሮ ተነስቶ፣ ፉከራውን ደቀደቀው።

ለትንሽ ጊዜ ሽለላውና ፉከራው እየተደጋገመ ከየአቅጣጫው ተሰማ። “ጎበዝ በሉ መንገድ እንቀጥል።” ብሎ በሻህ ኃይሌ ከቤት ወጣ። ሌሎቹም የጦር መሪዎች በዚሁ ሰዓት ከያረፉበት ተነስተው አማካይ ቦታ ለመገናኘት ተቃጥረዋል።

አድካሚ ጉዞ ነበር። የጨረቃ ብርሃን ባለበትም ሌሊት መጓዝ ያደክማል። አስካለ እንቅፋት እየመታ ሲያስቸግራት ጊዜ ለገሠ ደገፍ አድርጎ ያዛትና “አስካለ ከመንገዱ አትውጭ። የእግሩ መንገድ በጨለማ ከሌላው ቦታ ይልቅ ነጭ መስመር መስሎ ይታያል። የሰዎችን እግር እያዩ ከመሄድ ነጣ ያለውን ቦታ መርገጥ ነው። አይዞሽ።” አላት። አሰካለ በጨለማ ጉዞ ያወቀችው ከአርበኝነት በኋላ ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ ለገሠ የነገራትን ሌላ ሰው ነግሩዋት አያውቅም። ለገሠ የመከራት ምክር በመንገዱዋ ረዳት። ለአንድ ኪሎሜትር ያህል፣ በቀጭኑ የእግር መንገድ፣ ከፊትና ኋላ ሆነው የሚጉዋዙት ሰዎች፣ ፊታቸውን ሳይተያዩ፣ ማጅራታቸውን እየተያዩ፣ ይጫወታሉ። ለጥ ያለ ሜዳ ሲደርሱ፣ በቀጥታ መስመር የተሰለፉ ይመስላሉ። በተራራዎችና ኮረብታዎች ላይ ደግሞ፣ እንደ እግር መንገዱ እየተጠማዘዙ፣ የተጣጠፈ ገመድ ይመስላሉ። ሙልጭ በሆነው ዳገት ላይ ደግሞ መንገዱ ቶሎ ቶሎ ስለሚጠማዘዝ፣ ከመጨረሻ ያለው ሰው ከፊት የቀደመውን ከበላዩ እያየ ሲቀልድበት፣ የመጀመሪያውም የመጨረሻውን ያሾፍበታል።

---

[34] በአርበኝነት ዘመንና ከዚያ በቀደመው አሽከሮች የሚባሉት በአርበኛው መሪ ስር ያሉት፣ በዘመናዊ አጠራር ወታደሮች የምንላቸው ናቸው። በኋላ ዘመን አሽከር የሚለው አጠራር የተሰጠውን ተዋራጅነት አያሳይም። በአርበኞች ደብዳቤዎች ስለ አሽከር የሚወራውን በዘመኑ ቋንቋ ለመረዳት ወታደር በሚለው ተረዱት።

ለዓይን ሲገልጥ ሲል፣ ከየአቅጣጫው የመጡት አርበኞች ከተቃጠሩበት ቦታ ደርሰው፣ ለምክክር ጊዜ ስለሌላቸው፣ ለትንሽ ደቂቃ ከአዳባይ መልካ የሠፈረውን የከበባ ጦር ቃኙት።

ከዚህኛው መንዝ ወደ ጅሩ መሻገሪያው መልካ በጠላት ተይዟል። ሌላ መሻገሪያ ለመፈለግ መንከራተቱ ደግሞ፣ ጠላት ከባድ ኃይል አከማችቶ እንዲያፍናቸው ማስቻል ነው። ፍጥነትና ሳይታሰቡ ማጥቃት አማራጭ የሌለው ዘዴ ነው። በፍጥነት አንጻር ሲታይ፣ በዚያች ደቂቃ የጠላት መከላከል ከዚያ ዝቅ ብሎ ለመገኘት አይቻልም። ከዚህ ወዲያ ጠላት ያይላል። ጊዜ፣ ጦሩን ለማሰባሰብና ያንን መተላለፊያ ይበልጥ ለማጠናከር ያስችለዋል። ጠላት አመች ቦታ ይዞ መታኮስ ከያዘ፣ እስኪመሽ ጦርነቱ ሊቀጥልና በዚህን ጊዜ ውስጥ ጠላት ከሌላ ቦታ ኃይሉን አሰባስቦ፣ ወደዚህ ሊያዞር ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በመደበኛው መንገድ ሳይሆን አዳባይን ባልተለመደ ቦታ ለማቋረጥ ዋነተኞች ያስፈልጋሉ። በተለይ ሴት ልጆችና ሕፃናት ይህ እንክብካቤ ያሻቸዋል። ከብቶችን በሚመለከት ግን ችግር የለም። የትኛውም ከብት በውሀ ዋና ለመሻገር ይችላል። ውሀ ዋና የሚችሉ ሰዎችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል።

ጠላት፣ ጉዋዝ በወንዝ ውስጥ እንዳለ፣ ጦርነት ከፍቶ ጉዳት እንዳያደርስ፣ በካምፑ ውስጥ ትርምስ የሚፈጥሩና፣ ጉዋዝ በደህና ከተሻገረ በኋላ አፈግፍገው ከጉዋዙ የሚደባለቁ፣ ጠንካራ ተዋጊዎች መምረጥ ያሻል። ብዙ አጣዳፊ ችግሮች በአንድ ላይ ተረባረቡ።

ጉዋዝና ደካሞች በውሀ ዋና ለመሻገር ወንዙ ውስጥ መግባታቸው እንደታየ፣ ሃያ የሚሆኑ ምርጥ ጦረኞች አውራ ጎዳናውን ሳይታሰብ አልፈው፣ በጠላት ካምፕ ላይ በቦንብና በጥይት አደጋ ጣሉ። የጠላት ጦር በትልቅ ትርምስምስ ውስጥ ወደቀ።

ለገሠ፣ አስካለ በጦርነቱ መሃከል ቆማ፣ ጉዋዝ ወደሚሻገርበት ቦታ ስታስተውል ተመልክቶ፣ ወደዚያ ዘወር ቢል ሳቆቴን ሂጂ እያለች እንደሆነ ተመለከተ። ወዲያው የጠላት ጦር ከድንጋጤውና ከትርምስምሱ ወጥቶ የአጸፋ ተኩስ ጀመረ። ለገሠም "በሆድሽ ተኚ፣" ብሎ አስካለን ጎትቶ ጣላት። "ለትንሽ ነው የተረፍሽው፣" አላትና መትረየሱን ወደ ጠላት አነጣጥሮ መተኮሱን ያዘ።

"ጉዋዝ ተሻግሩዋል አፈግፍጉ!" የሚል ትዕዛዝ ተሰጠ። ተዋጊው ጦር ማፈግፈግ ያዘ። የጠላት ጦር ለማጥቃት ወደፊት መነቃነው ለመጀመር ሲሰናዳ፣ በሩጫ ከአዳባይ ወደ ትንሹዋ ኸረት መታጠፊያ የአርበኛው ኃይል ታጥፎ፣ ሌላ አመች ቦታ ለመያዝ ተሰናዳ።

"ሳቆቴን ወሰዱዋት!" አለች አስካለ ከመቅጽበት ወደ መጣችበት እየሮጠች። ለገሠ ተከትሎዋት እሮጠና ይዞ እንደገና በጉልበት ስቦ መለሳት። "እኔን ስትፈልግ ነው ይህ ችግር የደረሰባት። እኔ ልሙትልሽ! እኔ ልደፋልሽ!" እያለች አስካለ፣ ሳቆቴ የሞተች ያህል ማልቀስ ቀጠለች። ሰው ሁሉ ተደንቆ አስካለን ተመለከታት። አስካለ ጠንካራ እና ማንም አርበኛ ጉዋደኛውን መበቀል እንጂ ማልቀስ እንደማይገባው ሰባኪ ነበረች! ።

ሳቆቴ ከወንዙ ገባ ብላ ቆማ አስካለን ስትመለከት ቆይታ፣ አስካለም አይታት ሂጂ ስትላት ቆይታ፣ ድንገት ዘፍ ብላ በመውደቋዋ፣ በጥይት የተመታች መስሎዋት፣ ደንግጣ፣ ነፍሱዋን ስታ፣ ወደዚያ ስትበር፣ የአርበኛው ጦር ያንን ቦታ ሲለቅ፣ ያ ቦታ በጠላት በመያዙ፣ ሳታስበው ከጠላት ሰፈር ገብታ ተማረከች። አስካለ ያየችው አንድ ጠረንገሎ የሱማሌ ወታደር፣ በጥፊ እየመታ፣እየገፈተረ፣ እየረገጠ፣ እያዳፋ ሲወስዳት ነበር።

የአርበኛው ጦር ይህንን እገዳ ካለፈ በኋላ፣ ጠላት ምንም ሊያደርግ እንደማይችል በመገመት ሲገታለት፣ ወደ ጅሩ አቀና። ባለፈው ወር ጀምሮ በጦርነት ላይ የከረመ ስለሆነ በአጠቃላይ ሁሉም ተዳክመዋል።

ለገሥ በጣም የደከመው ሲሆን፣ የአስካለ ሃዘን ተጨማሪ ሸክም ሆኖበት ይበልጥ ደክሙዋል። ሊያጽናናት የሚያደርገውን ሙከራ ሁሉ ታከሽፍበታለች። ከዚህም በቀር ደግሞ ከሩጫዋ መልሶ ይዞ ስላመጣት፣ ሳቆቴን እንዳታገኝ ሰበብ የሆነባት እሱ የሆነ ያህል፣ ተቀይማዋለች። የሚያረገው ጠፍቶት ሲጨነቅ ቆይቶ፣ በስንት ማባበል አነጋግራዋለች። አሁንም ቢሆን ግን ብዙ አትነጋገርም። አስካለ የሳቆቴ ነገር አንጀቱዋን እየበላው፣ መንገዱ አልተሰማትም። አርበኞች ግን ጅሩ እንደደረሱ ሁሉም ጆሮአቸውን እንዲያቀኑ የሚያደርግ ድምጽ ሰሙ። ሁሉም መጠያየቅ ያዘ።

- ምንድነው የሚሰማኝ
- ናዳ ይመስላል እንጃ
- ተኩሰ ነው
- የምን ተኩስ

አንዱ የጦር አለቃ መነጽሩን አውጥቶ አካባቢውን በደንብ ቃኘው። “ጣሊያን ባላምባራስ አበበን እየወጋ ነው፣” አለ በመገረም። እነሱ እዚህ የመጡት የተሻለ ሁኔታ ለመፈለግ ነበር። ከዚህም ግን ችግር አለ።

አርበኞቹ ሳያስበው የጣሊያንን ጦር ከክብ ውስጥ ከተው ሲቆሉት፣ ተበተነ።

“ይገርማል ጌቶቼ፣” አሉ ባላምባራስ አበበ አረጋይ። የአርበኞች ሁሉ በላይ ተደርገው ቢገመቱም ሲናገሩ ጌታዬ ማለት ይወዳሉ። “እኛ ሳናስበው ስለደረሳችሁልን እንዲህ የደነቀን ጠላት በጥበብ ያደረግነው መስሎት እንዴት ይድነቀው።” አሉ ፈገግ ብለው። የአጋጣሚ ተአምር የሚያስደንቅ ውጤት ይሰጣል።

አርበኞች ግን ከዚህ ብዙ ሊቆዩ አይችሉም። ጠላት መሰባሰባቸውን እንዳየ ኃይሉን አዞሮባቸዋል። አርበኞች ወደ ግንደ በረት ሰላሌ ለመሄድ ተስማሙ።

⅄ ⅄ ⅄

# ለራሴና ለቤተሰቤ የማደርገውን ለአገሬ እንዳደረኩት አልቆጥረውም

ከባላምባራስ አበበ [35] ጋር ወደ ግንደበረት ለመውረድ የመንዝ፣ የተጉለትና የይፋት አርበኞች እንደወሰኑ፣ ከፈለው ወልደ ጻዲቅ[36] የግዛቸው ኃይሌ ንግግር እየደጋገመ እራሱን ይመታው ጀመር። "…እግዚአብሔር ታምሩን እስኪሠራ ድረስ… እግዚአብሔር ታምሩን እስኪሠራ …." ። ዛሬ እግዚአብሔር ታምሩን መሥራት የጀመረ መሰለው። ከዚህም ሌላ እሱ ወደ ሰላሌ ሲሄድ በቤተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ፣ ቤተሰቡ ተገን ጠለላ ማጣቱ ታየው።

ሰሞኑን ከደንገዜ መልዕክት ይዞ የመጣ ሰው፣ ግዛቸው ኃይሌ በክቡ ውስጥ ጠላትን ለመቋቋም እንደቻለም አጫውቶታል። "ከደንገዜ በረሀ ውስጥ ሺ ዓመትም መመከት ይቻላል።" ሲል አሰበና ጠላትም አቅጣጫ ሊቀይር መቻሉ ገባው። የደንገዜ በረሀ ቁልጭ ብሎ ታየው።

የአባት አገር ዱሬ፣

የናት አገር ዱሬ፣

እገባብሻለሁ የትም የትም ዙሬ።

ብሎ ፎካሪው ያቅራራውን በልቡ እያዜመው፣ እንደ ደረጃ እየሠሩ ከሚወርዱት ብዙ ጥርብ ገደሎች በታች፣ የደንገዜ በርሀ፣ እስከ ጫካውና በውስጡ እየተጠማዘዘ፣ ፏፏቴ እየሠራ፣ በደን እየታጠረ የሚሽቆለቆለው ወንዙ፣ ታየው። እራሱንም ከዚያ ቦታ ወስዶ በዓይነ ሕሊናው ብዙ ጦርነቶች ገጠመ። "ቦታዬ ከዚያ ነው።" ሲል ደመደመ።

ከአማራው፣ ከኦሮሞው፣ ከአዳሉ፣ ከመላ ሸዋ የተውጣጣው አርበኛ ከመላው ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ የተከማቸውና ወደ ዱር የፈለሰው አርበኛ፣ በሙሉ ከመረሃቤቴ ወደ ግንደበረት ጉዞውን ለመቀጠል ሲነሳ፣ ከፈለው ወደ መንዝ እመለሳለሁ በማለት ለመሰናበት ከባላምባራስ አበበ አረጋይ ዘንድ ቀረበ።

"ጌታዬ ለምን ትመለሳለህ?" አሉ ባላምባራስ አበበ ጉዳዩን ካዳመጡ በኋላ በተለመደ የትህትና አነጋገር ጌታዬን ጨምረው።

"ጌታዬ ዘመዶቼን ጥዬ አልሆነልህ ብሎኝ ነው፣" አለ ከፈለው በአክብሮት።

---

[35] ባላምባራስ አበበ በኋላ ራስ አበበ አረጋይ። የአርበኞች መሪና ዕውቅ ስትራቴጂስት።

[36] ከፈለው ወልደ ፃዲቅ በኋላ ደጃዝማች። ግዛቸው ኃይሌ ከሞተ በኋላ የመንዝ፣ ተጉለትና ይፋት አርበኞች አስተባባሪ የሆኑና፣ ሰፊ ነጻ ክልል ያስተዳደሩ፣ ዝናቸው የገነነ አርበኛ ነበሩ።

ብዙ ከተነጋገሩ በኋላ ባላምባራስ አበበ ፈቃዳቸውን ሰጡት። ከፈለው ከውጭ ሲወጣ ግን ጓደኞቹ እየተቀባበሉ እንዳይመለስ ይወተውቱት ጀመር።

– አብደሀል? ዛሬ ነፍሱን ያዳነ ነገ ይዋጋል። የሞተ ግን ነገን አያይም።
– እንዴት ብለህ ትመለሳለህ? መንገዱ ሁሉ ታጥሯል። ሕዝቡ ተሸብሯል። ሽብር ወንድም ወንድሙን እንዲከዳ ያደርጋል። ይህንን ላንተ ነጋሪ መች ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ ያየኸው ነው።
– እኛም ውሎ አድሮ መመለሳችን አይቀርም። አብረን እንመለሳለን። አሁን አታስቸግረን።

ብዙ ሀሳቦች ፈሰሱለት። አንደኛቸውም አርሰውት ከውስጡ አልዘለቁም። ገጽታው በራሱ ውሳኔ ብቻ ረግቶ፣ ሌላውን ሀሣብ ሁሉ እያነጠረ ይመልሰዋል። በመጨሻም፣ ጓደኞቹ እንዳሻህ ሁን ብለውት፣ ብቻውን ከራሱ አርበኞች ጋር ወደ መንዝ እንዲመለስ በትዝብት ዓይን ሸኙት። ከፈለውምሬቱን ሳይመልስ፣ ቁልቁል ወደ በረሀው ወረደ። አዳባይን ግን በጤና ተሻግሮ መንዝ አልገባም። አንደ የኢጣሊያ ጦር እንቅስቃሴውን እየተከታተለው ነበር።

ከፈለው እስከ አርበኞቹ ሌሊቱን ለማሳለፍ፣ አንድ ዋሻ ውስጥ ገብተው፣ ጡዋት ሲነሱ፣ ዙሪያውን መከበባቸውን ያወቁት ሳያስቡት ነበር። ከባቢው ጠላት አርበኞቹ በዋሻው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት እንደማይችሉ ያውቃል። አርበኞቹም ጠላት ዋሻው ውስጥ ገብቶ እጃቸውን ለመያዝ እንደማይሞክር ፤ ግን በራብና በውሀ ጥም ሊያልቁ እንደሚችሉ ያውቃሉ። አልፎ አልፎ የተኩስ ልውውጥ እየተደረገ ቀኑ እየጨለመ ሄዶ፣ ሌላው ቀን ተተካ። አማራጭ ሃሳቦች ሁሉ ሲደረደሩ፣ ክርክር ሲደረግባቸው መቋዋጫ ታጥቶ ሲዋለል ተቆየ። ሁሉም ግራ ገብቶት ካቀረቀረበት ላይ የተነሣው አቅራሪው የኮረኮረው ጊዜ ነበር።

ወይ እነሱ አይመጡ፣ ወይ እኛ አንሻገር፣

መልካሙ ጦም አደር፣ የሁለት ፈሪ አገር።

አለና እንድ ጊዜ ሰላሌ ላይ እንደነሱ የተከበቡ ወንድሞቻቸው እንዴት እንዳመለጡ፣ ይህንንም የገጠመው ሰው በዚህ ሁኔታ እንደነበር አጫወታቸው። ሁሉም ሃሣብ ገብቱዋቸው አቀረቀሩ። ከብዙ ዝምታ በኋላ ሁሉም በአንድነት፣ ተመሣሣይ ውሳኔ ላይ የደረሱ ይመስል፣ ከፈለው እንውጣ ሲል በደሰታ ተቀበሉት። ሴቱም፣ ወንዱም፣ እያንዳንዱ ስለሚከተለው አቅጣጫ፣ የቦንብ አጣጣል መመሪያ ከተሰጠ በኋላ፣ ከፈለው ፍጥነት ከሁሉ በላይ አስፈላጊ በመሆኑ አንድ ጊዜ መንደርደር ከተጀመረ ወደ ኋላ ማፈግፈግ፣ መቆም፣ እንዳይኖር አደራ አለ።

ከዚያ ቀኑ ለዓይን እንደመያዝ ሲል፣ በጠላትም ሰፈር ስጋት ቀነስ ሲል፣ አርበኞቹ በድንገት ከዋሻው ወጥተው እየተንደረደሩ በመውረድ፣ ቦንብ በመወርወር ጠላትን

ሲጠጉት፣ የሚይዘውና የሚጨብጠው አጥቶ ሲተራመስ አርበኞች አልፈው ከባሻገሩ አመች ቦታ ይዘው ተኩስ ከፈቱ።

ጀምበር ከአድማስ ስትጠልቅ፣ ሁለቱም ወገኖች ገላጋይ የገባባቸው ይመስል፣ ተኩስ እየቀነሰ ሄዶ ቆመ። አርበኞችም እርስ በርሳቸው የተቀኛኙት በዚህ ጊዜ ነበር። ከፈለው "አሰገደች!" ብሎ ሳያውቀው ተጣራና ልቡ ስንጥቅ አለ። በዚህ ዓይነት ወቅት፣ መቸም ይሁን መቸ፣ ከጎኑ ወይም ከፊለፊቱ ያያታል። አሁን አጠገቡ ያልኖረችው....... ሊሆን ይችላል!" አለ ምርኮን ቃሉን እንኳን መጥራት ጠልቶ ይሁን ወይም ሞትን። አርበኞቹም ስሙዋን ሲሰሙ እርስ በርሳቸው መንሾካሾክ ያዙ።

"ሸዋፈራስ?" አለ አንዱ አርበኛ ደንግጦ።

"እሱስ ደህና ነው። ሰልዬ ልምጣ ብሎ፣ ስለ እሜቴ[37] እንደተሰማ፣ ወደ መጣንበት ተመልሱዋል።" አለ ሌላው። ሸዋፈራ በእንዲህ ዓይነት ሥራ ትዕዛዝ እስኪሰጠው የማይጠብቅ ጎበዝ ጋሜ ነው። ከሁሉም አርበኞች ወጣት ሲሆን በሥራውና በድፍረቱ ግን ከማንም አይተናነስም።

ከፈለው ባለቤቱ ተማርካ ይሁን ሞታ ሳያውቅ በጉዳዩ ሲብጠለጠል፣ በመጨረሻ ሞታ ነው የሚለው ውሳኔ ላይ ደረሰ። የሚወዱት ሰው ላይ የደረሰ አደጋ በዝቶና የመጨረሻ ከፋቱ ነው የሚታይ። ደግሞስ በዚያ ሁሉ ተኩስ መሃል አልሞተችም ተብሎ በምን ይገመታል። ተራ በተራ ጥርጣሬውን የሚያጠናክሩ ትዕይንቶች በዓይነ ሕሊናው ሲያልፉ ቆዩና፣ በመጨረሻ፣ አሰገደች የእግሩዋን ኮቴ እየተከተለ የሚነጉደው የመትረየስ ተኩስ ሲከተላት፣ እሱዋ ስትሮጥ፣ ሲከተላት፣ በመጨረሻ ስትመታ ታየችውና የፊትዋ ገጽታ በዓይነ ሕሊናው እንደ አዙሪት ሲሽከረከር ታይቶት፣ ልቡ ታፍኖ "እህቴ እኔ ልደፋልሽ፣" ብሎ ከወገቡ እንደተሠበረ አጎንብሶ እንባው ይጎርፍ ጀመር። ቀስ በቀስ እየቀዘቀዘ ሲሄድ፣ አቅመ ቢስነት ተሰማው። ምን ሊያደርግ እንደሚችል ጠፋው። ቀጥሎ ደግሞ እልህ ተናነቀው። ገዳዮቹዋን ዛሬውኑ አጥፍቼ እኔም እጠፋለሁ ከሚል ውሳኔ ደረሰ።

ከፈለው በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለ፣ ሸዋፈራ ደርሶ ሲመለከት፣ ነገሩ ሁሉ ግራ ገባው። ሸዋፈራ በአሰገደች ላይ የደረሰውን እንዴት ብሎ እንደሚናገር ሲጨነቅ፣ ከዚህ በልቅሶ ላይ ሰለደረሰና የሃዘኑም ምክንያት አሰገደች ሞታለች የሚል መሆኑን ሲሰማ፣ አንዳች ነገር ከትከሻው የተነሣለት ያህል ቀለለው። ሁኔታው አይፈቅድም ብሎ እንጂ፣ ፈገግ ቢል እንኳ ወዶ ነበር። ውጦ ነው ያስቀረው።

---

[37] የልጅ ከፈለው ባለቤት በመሆናቸው እሜቴ ይባላሉ። ይህ አጠራር በከተሞች እየቀረ ሄዷል።

ሸዋፈራ ወደ ከፈለው ሲጠጋ ሁሉም ሰው ሸዋፈራ ይዞ የመጣው ወሬ ለመስማት ቸኩሎ አቆብቁቦ ነበር። “ጌታዬ እሜይቴ ደህና ናቸው። አበስ ገበርኩ ሞትን ምን አመጣው፣” አለ ከሽማግሌ ባላነሰ ገጽታ። “ብቻ ተማርከው ከጠላት ካምፖ ናቸው አሉ።”

“ቸር ወሬ ያሰማህ፣” አሉ አካባቢው ያሉት ሰዎች በረጅሙ ተንፍሰው። ከዚያ ሸዋፈራ የሚጎርፍለትን እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ማ፣ እንዴት ወዘተ በማለት እየተደጋገሙ የሚቀርቡለትን፣ መልሳቸውን ሁሉ በደንብ የማያውቃቸውን ጥያቄዎች፣ መመልስ ያዘ።

የከፈለው ተከታዮች ሞት ካልደረሰ መማረክን፣ ቀላል አድርገው ይመለከቱት እንጂ፣ ከፈለው ግን ምርኮውን ከሞት ያነሰ አድርጎ ካለመመልከቱም በላይ፣ ከካምፑ ውስጥ ወዲያውኑ ሄዶ ሊያስፈታት ቆረጠ።

ይህ ውሳኔው ትክክል እንዳልሆነ፣ ሌሎች የተሻሉ አማራጭ ብልሃቶች እንዳሉ ለማሳመን ጓደኞቹ የቻሉት፣ ከብዙ ልመናና፣ ማግባባት በኋላ ነበር።

ይህ በሆነ ሰሞን ከፈለው በላሎ ምድር ውስጥ እየተዘዋወረ፣ የተማረከችውን ባለቤቱን የሚያስፈታበትን ዘዴ፣ በረጋ አእምሮ ከማዘጋጀቱም በላይ፣ ለዚህ ዓይነት ተልዕኮ ብቁ የሆነ ድርጅት አዋቀረ። በዚህም ጉዞው ከዳኘው ጋር ተዋወቀ።[38]

ለከፈለው፣ ስለ ዳኘው የነገረው፣ ከዚህ አገር ለከፈለው አድሮ የነበረ አርርበኛ ነው። አርበኛው ዳኘው በዚያ አካባቢ ተደማጭነትን እያገኘ የሄደ ሰው መሆኑን፣ ለባላምባራስ አበበም ተባባሪ የሆነ፣ በጠላት ካምፕ ውስጥ ብዙ የሚያውቃቸው ሰዎች ያሉት እንደሆነ ሁሉ ነግሮታል። ከፈለውም ዳኘውን ሊያገኘው የፈለገው ለዚሁ ነበር።

ዳኘው ከፈለው ሊያነጋግረው እንደሚፈልግ ሲነግረው በሕይወቱ ውስጥ ትልቅ ለውጥ የሚያስከትል ነገር እንደሚያጋጥመው በማወቁ ልቡ ተረበሸ። ያንን ቀን በጉጉት ተጠባበቀው። ከፈለውም ዳኘውን ያየው ዕለት ጥሩ አጋር ማግኘቱን እርግጠኛ ሆነ። ከፈለው ዳኘው ክብር ዘበኛ የነበረ መሆኑን ሰምቶ ስለነበር፣ ምስጢሩን ሳያካፍለው በፊት፣ ስለ ቤልጅግ መትረየስ አፈታትና አገጣጠም እንዲያሳየው ጠየቀው። ዳኘውም መትረየሱን ፈታትቶ እንደገና ገጣጠመና ለተኩስ አዘጋጅቶ ሲያነጣጥርበት፣ ከፈለው ፈገግ ብሎ ተመልከቶት፣ በደንብ ይስማማሃል አለ።

ዳኘው ከፈለው አብረን እንሥራ ብሎ የሚጠይቀው ያህል ተሰማው። ልቡ ተሸበረ። ደስታም ልብ ያሸብራል። ከፈለው እንደገና መናገር ሲጀምር ዳኘው ከፈለው አብሮ ስለመሥራት ይናገራል ሲል ጠበቀው። ከፈለው ግን “አዲስ አበባ የት ነበር የምትኖረው?” ሲል ጠየቀ።

---

[38] ከፈለው ወልደፃዲቅ በዚህ ወቅት ጥርሱን ነክሶ ወደ መንዝ መመለሱ በኋላ ጊዜ ተጠናከሮ ለመውጣቱና የሰፊ ነፃ ክልል አስተዳዳሪ ለመሆን አስችሎታል። የአርበኛነት ውጊያ ተመራማሪዎች ይህንን ሁኔታ በሰፊው ሊያጠኑት ይችላሉ።

“ጉለሌ ነበር። እርሰዎስ?” አለ ዳኘው ከፈለውን በእድሜው ብቻ ሳይሆን በሙያውም በማክበር።

“ዳግማዊ ሚኒሊክ ትምህርት ቤት ሳለሁ አዳሪ ስለነበርኩ፣ እዚያው እኖር ነበር። በትምህርት ብዙም አልገፋሁም። አባቴ የመሬት ክርክር ስለነበረባቸው፣ ትምህርቴን አቋዋርጬ አገሬ ተመለስሁ። በትምህርት ቤት በነበርኩ ጊዜ ከሁሉም ይበልጥ የተማረኩት ለኢትዮጵያ ፍቅርን፣ ለባንዲራ መሞትን፣ ንጉሠ ነገሥትን ማክበርን፣ ነው። አለ ንጉሠ ነገሥት ሲል ንጉሡ አሁን ስለሌሉ ፈገግ ብሎ። ፈገግታው ሁልጊዜም የማሽሟጠጥ ይመስላል። ፈገግ ሲል ከንፈሩን ጠመም ያደርገዋል። “ጠዋትና ማታ ባንዲራ ስናወጣና ስናወርድ፣ ለዚች ለባንዲራችን ፍቅር ያዘኝ።” አለ ጋሻጃግሬው የያዛትን ትንሽ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራ ትምህርት ቤት ስትውለበለብ እንደነበረችው ያህል አስመስሎ።

“እርግጥ ነው።” አለ ዳኘው፣ ባንዲራዋን ሲመለከት፣ ሳያውቀው እንደወታደርነቱ በተጠንቀቅ ለመቆም ነሸጥ አድርጎት። “እኔም በወታደርነቴ ነው ያገር ፍቅር ጥልቀቱን ያወኩት።”

“ለምን አንተም ባልደረቦችህንና ወንድሞችህን ይዘህ አብረን አንሠራም?” አለ ከፈለው በድንገት። “ባንድነት ብንሠራ ነፃነታችን እንደገና ተመልሶ፣ ኢትዮጵያ ከወደቀችበት የምትነሣበት ሁኔታ፣ ይፈጠራል።”

“እኔም ይህንኑ ሳስብ ነበር።” አለ ዳኘው ሳያስበው ስሜቱ ፈንቅሎት።

ከፈለውም ብዙ ለማግባባት ያዘጋጃቸው ንግግሮች ቦታ አጥተውበት ዝም አለ። ሁለቱም ዝም ብለው ቆዩ። በልቦናቸው ዘመናት እንደ ጎርፍ ውሀ እየተንከባለሉ አለበሱአቸው። ቤተሰባቸው፣ የነሱ ሁኔታ፣ መጪው ብሩህ ሁኔታ፣ ጨለማው ሁኔታ፣ እየተፈራረቁ ታያቸው።

“ጣሊያን በቅርብ ድል ይሆናል፣” ሲል ከፈለው መናገር ጀመረ። በእርግጥ ጣሊያን በቅርቡ ድል ስለመመታቱ የሚያውቀው ነገር የለም። ይልቁንስ የአሁኑ የአርበኞች ሁኔታ አሳሳቢ ችግር ላይ መውደቁ ይታየዋል። ነገር ግን እድል በጨለመች ጊዜ፣ የሰዎች ልብ ሊፈስ የደረሰ እየመሰለው፣ ስለ ድል መቃረብ መናገር ይወዳል። በደህና ቀን የተካበው በቀውጢ ቀን ስለሚናድ፣ እንዳይናድ መጠንቀቁ ግዴታው እንደሆነ ያምናል። ዳኘውም ስለ ሃገሩ ስላለው ፍቅር ከፈለው የሚጠራጠር መስሎት ቅር አለው። ወዲያው ግን ተወው።

ከአድማሱ የምታቆለቁለው ፀሐይ በተራራዎች ጀርባ ከመጥለቋዋ በፊት በሰማዩ ላይ ቀይ ቀለም ጥላ ሁለቱም ተመለከቱ። የገዳይ ልብ የምታስረቀርቀው የምትጠልቀው ጀምበር ልበ ሙሉነታቸውን ይበልጥ አፀናችው። ይሸምቅ ተዋጊ መዝናኛው በረሃ፣ ጫካ፣ ጨለማ ነው።

“ከጣሊያን ምሽግ ውስጥ ባንዶች ታውቃለህ?” አለ ከፈለው።

"አዎን። ከኛም አገር ሄደው የተቀጠሩ ሞልተዋል። አብዛኞቹ ጊዜውን ለማሳለፍ ብለው እንጂ ከልባቸው የሚያምኑበት ሆነው አይደለም፣" አለ ዳኘው እውነቱን ሃቁን መናገሩ ሁልጊዜም ጠቀሜታ እንዳለው ያውቃል።

"የጣሊያን ፉርኖ እየበሉ ለማሳለፍ!" አለ ከፈለው ከንፈሩን ጠመም አርጎ እየሳቀ።

"አዎን እንደዚያ ነው። ሁሉም ሰው ዳቦውን ለመብላት እምነቱን መስጠት የለበትም፣ " አለ ዳኘው ከፈለውን አትኩሮ እየተመለከተ።

"በቅርብ የምታውቃቸው ካሉህ ተላልከህባቸው፣ ባለቤቴን አሰገደችን ለማስፈታት እንዲተባበሩኝ አታደርግልኝም? ውለታ ሠራህልኝ ማለት ነበር።" አለ ከፈለው እሱ ለሌሎች ውለታ ሲሠራ ደስ የሚለው ቢሆንም፣ ሌላ ሰው ሲያደርግለት ግን ይከብደዋል።

"ለአገራችን ነፃነት የምናደርገው ነገር ውለታ መሥራት ተብሎ አይቆጠርም። በጦር ሜዳ ጓደኞቻችንን ላለማስማረክና እሬሳቸውን በክብር ለማስነሣት የምናደርገው ጥረት ሁሉ፣ የግል አፍቅሮት ሳይሆን፣ የኢትዮጵያዊነታችን ስሜት እንዳልጠፋ ለጠላት የምናስመሰክርበት ነው።" አለ ዳኘው ውለታ የሚለው ቃል ደስ ስላለው።

"ይህስ ልክ ነው። እኔ ግን ለራሴና ለቤተሰቤ የማደርገውን፣ ለአገሬ እንዳደረኩት አልቆጥረውም ።" አለ ከፈለው የሆዱን ስሜት በመግለጽ።

"ይሁን፣" አለ ዳኘው በከፈለው ትህትና ተደሰቶ።

ከፈለው እየተዘዋወረ ባዘጋጀው በዚህ እቅድ፣ አንድ ቀን ሌሊት፣ በኢጣሊያ ምሽግ ውስጥ ተኩስ ሲንጣጣ፣ ከምሽጉ ዙሪያ የነበሩት አርበኞች ልብ በደስታ ፈነደቀ። የጠላት ወታደሮችም እየተደናበሩ ከእንቅልፋቸው ተነስተው የሚይዙት ጠፋባቸው። ግማሹ ተኩሱን ሲያንጣጣ፣ አሰገደችን ይጠብቁ የነበሩት የአገር ተወላጅ ዘቦች፣ አሰገደችን ይዘው መጥተው ለአርበኞች አስረክበው፣ ወዲያው ተመልሰው በከንቱ ትርምስምስ ውስጥ መርመስመስ ቀጠሉ። አርበኞችም ተኩሱ ጋብ እንዳለ ከሩቅ ሌላ ቦታ የያዙ መስለው ትንሽ ተኩሰው ፣ እየሳቁ፣ ወደ አዳባይ በረሃ ወረዱ።

በካምፑ ውስጥ አሰገደችን ይጠብቁ የነበሩት ዘበኞች፣ ተነጠቅን እያሉ ሲያጉዋሩ፣ የማስመሰያ ተኩስ የከፈቱት የአገር ተወላጅ የጣሊያን ሠራዊት ግን አርበኞቹ ከየት እንደመጡ፣ እንዴት እንደተኮሱባቸው፣ አፀፋውን እንዴት እንደመለሱ፣ ሽፍቶቹ ግን አይለው አሰገደችን እንደነጠቋቸው፣ የፈጠራ ታሪካቸውን እየተዘዋወሩ አወሩ። ጣሊያንም የደረሰበትን ውርደት ለመበቀል አርበኞችን ለማሳደድ ሲነጋጋ ከካምፑ ሲወጣ አርበኞቹ እርቀው ሄደው ከማያሰጋቸው ቦታ አርፈው ነበር።

ከፈለው አሰገደችን እቅፍ አድርጎ፣ ሁለት ጉንጮቹዋን አገላብጦ ስሙዋት፣ ሁለመናዋን በአዘኔታና በናፍቆት ይመለከታት ነበር። አሰገደችም እየተዘዋወረች ከደስታዋ ብዛት አርበኞቹን ስማ በሲቃ አለቀሰች። ፀጉራቸው ጎፍሮ ሚዶ ሳይነካው የተንጨባረረውና

የተቆጣጠረው፣ ከፊታቸው ላይ ሞት የሚነበብባቸው፣ ሻካራዎቹና ጎስቋላዎቹ፣ አርበኞች እንኳ ልባቸው በሃዘን ተነክቶ፣ ከፊታቸው ላይ የመለሳለስ ሁኔታ ታየባቸው። የፋኖ ቅጭም ያለ ፊት ተለሳልሶ የሚታየው እንደ ብርቅ ነው።

ከፈለው ዳኘውን ለአሰገደች ያስተዋወቃት የዚህን ጊዜ ነበር። "አብረን ለመሥራት የተስማማነው ዳኘው ይኸውልሽ፣" አላት። ሁሉም ቀና ብለው ዳኘውን በፈገግታ ተመለከቱት። ጥሩ መትረየስ ተኳሽ ባልደረባ ብቻ ሳይሆን፣ አብሮ ይዞዋቸው የመጡት አርበኞች ቁጥራቸውን አበርክቶታል። አሰገደችም ሳቅ ብላ ሰላምታ ሰጠችው።

"እንኳን እግዚአብሔር ያወጣዎት፣" አለ።

"ባምላክዎ።"

⅄ ⅄ ⅄

# ንጉሥ አንጋሽ

ከባላምባራስ አበበ ጦር ጋር አስካለ ቡልጋ እንደደረሰች አካባቢውን ተመስጣ አየችና በጣም ደስ አላት። እንዴት ቆንጆ አገር ነው፤ በጣም ያምራል። እሸቱ፣ ዛፉ፣ ተራራው ያምራል ስትል ብቻዋን ተናገረች። ከጎኑዋ ከነበሩት ቁጥቋጦዎች ተመለከተችና "የአገሬ ከሴ እዚህም አለ፣" አለችና አንድ ዘንበለል ቆርጣ አሸተተች። አንድ ዓይነት ደስታ ተሰማት። በሎጋ ቁመናዋ እየተንጠራራች አካባቢውን አገር እያየች፣ ደስታ ልቡዋን ቀስፎት፣ ቀይ መልኩዋ ይበልጥ ፈክቶ፣ አጠር ብሎ ወደ ላይ ቀና ያለው አፍንጫዋና ተነስ ያሉም ቢሆኑ ብሩህ ዓይኖቹዋ ከጥቁር አጭር ጐፈሬዋ ጋር የልብ እርካታ ተጨምሮበት ይበልጥ ፈክቶ፣ ለገሠ አያትና የሱዋ ደስታ እሱም ተጋብቶበት ፈገግ አለ። ባለ ቀይ ጥለት ቀሚሱዋን ንፋስ ወደ ሁዋላ ስቦት፣ የታጠቀችው አረንጓዴ እጀጠባብ ሱሪ ቁርጭምጭሚቱዋ ጋ አጥብቆ ይዞዋት፣ ትናንሽ ሆነው ውብ ጣት ያለቸው እግሮቹዋ መሬቱን አጥብቀው ይዘው፣ ከመሬት የበቀለች የደስ ደስ ያላት እጽዋት መስላለች። ለገሠ አስካለን ተጠግቶ ከጐኑዋ ቆመና በግራ ትከሻዋ በኩል ያነገተውን ሁለተኛ ጠበንጃ አውርዶ ቀኝ ትከሻዋ ላይ በማንገቻው አስያዘላትና ሳቀ።

"ምንድነው የምትሠራው?" አለችው ወደሱ ዘወር ብላ። ጠበንጃውን በእጁ በኩል አጥልቆ ከትከሻዋ ላይ ማንገቻውን አድርጎ ሲያስተካክልላት ሁሉ በደስታ ተውጣ ስለነበር አልሰማችውም፣ አልተነቃነቀችም ነበር።

"ዝም ብለሽ ቁሚ። ጠበንጃውን አንግተሽ ብትቆሚ ምን እንደምትመስይ ለማየት ነው።" አለ አሁንም ፈገግታ አስውቦት። "አስካልዬ ምን የሚያስደስት ነገር አግኝቶሽ ነው

እንደዚህ የምትፍነከነኪው?” አለ ነገሩ ደስ የሚል እንጂ የሚያስከፋ ነው ማለቱ እንዳልሆነ ከፊቱ እየተነበበ።

“ቡልጋ ቆንጆ አይደለም?” አለችው እሱም ቡልጋን እንደሱዋ አይቶት እንዲደሰት ከልቡዋ እየጋበዘችው።

“ላንቺ ምን የማያስደስት ነገር አለ።” አለ እንደሱዋ ባለመሆኑ ቀንቶባት፣ ትዝታ ወደ ኋላ ዘመኑ ይዞት እየሄደ። አስካለም ወደ ትዝታ ዓለም ሲገባ አይታው ጨዋታውን ለመቀየር ፈለገች። እንደሱዋ ሊያይ አይችልም። “ለገሡ፣ ከዚህ በኋላ የት እንሄዳለን?” አለችው። ቡልጋ ተስማምቷታል፡ ጠላትም እነሱን መከታተሉ ተስፋ ቆርጦ ብዙ ጉዳት ደርሶበት ወደ ደብረብርሃን ተመልሱዋል።

“የትም እንሄድ፤ ቡልጋ ላይ የአምላክ ፈቃድ ከሆነ ብዙ እንቆያለን። ባላምባራስ አበበ፣ በፈረንጅ አገርና በአዲስ አበባ አስኮላ ተምረው የነበሩት ሰዎች ጥሩ ሃሳብ አቅርበውላቸው ፣ተቀብለውታል ይባላል።” አለ እንዴት ብሎ እንደሚገልጸው እየተቸገረና ጨዋታውን ሳያስበው ቀይሮ። ነገሩን አንድ ጊዜ ከጀመረው ግን አስካለን በሚገባት መንገድ ማስረዳት አለበት። ሌላው ቢቀር እሱ ከገጠር ወደ ከተማ ወጥቶ ሰለቆየ፣ እሱዋ የማታውቃቸውን ብዙ ነገሮችን ያውቃል። “ሰው ካቶሊክ ይላቸዋል እንጂ እንዴት ጥሩ ሰዎች መሰሉሽ። ትህትናቸው ደግሞ ደስ ይላል።” አለ ስለነዚህ ሰዎች አስካለ በጥሩም በመጥፎም አንስታ ባታውቅም፣ ብዙ ሰው የሚያስበውን ማሰቡዋ አይቀርም ብሎ።

“ምን ጥሩ ሃሳብ አመጡ?” አለችው። ሃሳቡን እንዲገልጽላት ፈቃደኛ መሆኑዋን ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን ጥሩውን ነገር ለመስማት ቸኩላ።

“አውራ የሌለው ንብ[39] ተበታትኖ ይቀራል። ይህንን ታውቂያለሽ። እኛም ይኸው ከያለበት ተሰብስበን ስንሠራ አንድ አውራ ከሌለን በያለበት እንበተናለን። አንድ መሪ ያስፈልገናል።” አለ። አጠቃላዩን አርበኛ እኛ ብሎ።

“ንጉሳችን አሉ አይደለም?” አለችው ስለ ንብ አውራ ያወራው ነገር ወደ ውጭ አገር ቤተሰባቸውን በሙሉ ይዘው ስለሄዱትና አርበኞች በየጊዜው ስለመምጣታቸው የሚያወሩላቸውን ንጉሥ አስታውሱዋት። ገና በ1928 እንኳን ጣሊያን አዲስ አበባን ለመያዝ ሲገሰግስ፣ የይፋት አርበኞች መሪ ሕዝቡን አስተባብሮ ለማስነሳት፣ ጃንሆይ እየመጡ ነው በማለት ነጋሪት እየመታ፣ ብዙ የጣሊያን ካሚዮኖችና የጣሊያን ወታደሮችን መንገዱ ላይ መሽጎ ፈጅቱዋል። የዚያን ጊዜ ንጉሡ ገና አውሮፓ አልደረሱም። ከዚያም በኋላ

[39] በሳይንስ ንግሥቲቱ ንብ የምንላት በባሕል አውራ ንብ ይባል ነበር። በዚህ እትም፣ ወጣት አንባቢዎችን ላለማስቸገር “አውራ ንብ” የሚለው “ንግሥቲቱ ንብ” በሚል ተተክቷል።

ይኸው ወሬ በየጊዜው በአርበኞች ይናፈሳል። ሕዝቡም ተደጋግሞ እየተነገረ ውጤት ባለማሳየቱ ጥርጣሬ አድሮበታል።

“ንግሥቲቱ ንብ በቀፎው ውስጥ እስከሌለ የሞተ ያህል ነው።” አለ ለገሠ አስካለ ለጠየቀችው ጥያቄ በምሳሌ መልሱን ሲሰጥ። ዝም አለችው። ሀሳቡ ትልቅ ነገር ያዘለ መሆኑ ተሰምቱዋታል። ሰሞኑን ብዙውን ጊዜውን የሚያጠፋው፣ አብሮ የሚጉዋዘው፣ ከነዚሁ የተማሩ ከሚባሉ የጦር አዘገኖች ጋር ነው። እሱም እንዴት ንግግሩን እንደሚቀጥል አሰበና ያሰበውን ነገር ሁሉ ይደመድምለት ይመስል “ባላምባራስ አበበ አሁን ያሉት ከመልአከ ፀሐይ እያሱ ጋር ነው።” አለ።

“ማናቸው መልአከ ፀሐይ እያሱ?” አለች በደመ ነፍስ መልአከ እያሱ እጅግ አስፈላጊ ሰው መሆናቸው ተሰምቱዋት።

“የልጅ እያሱ ምኒሊክ ልጅ ናቸው። ጣሊያን ለሱ እንዲገቡለት ቢያባብላቸውም አገሬን አልክድም ብለው እስካሁን ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ነበር።” አለ እምብዛም ስለሳቸው የሚያቀው ስለሌለ ብዙ ማውራት አቅቶት።

በቀጣዮች ቀናት ውስጥ ብዙ ስብሰባዎች ምክክሮች ከተደረጉ በኋላ ለአንድ ትልቅ በዓል ዝግጅቱ ይጣደፍ ጀመር። አስካለም በምግብ ዝግጅቱ በኩል ቀን ከሌት መሥራት ያዘች። አንዳንድ ቀን ከሥራ በኋላ ስብሰባ ተደርጎ የተማሩት ሰዎች ስለ አንድ መሪ አስፈላጊነት፣ በመላው ኢትዮጵያ ያለው አርበኛ ኃይል በአንድ መሪ ስር መሰባሰቡ ለነፃነት ተጋድሎው፣ ለአርበኝነቱ ሥራ ፍሬያማነት፣ አስፈላጊ ስለመሆኑ ንግግር ያደርጋሉ። ባላምባራስ አበበን ከፍ ከፍ አድርገው ያቀርባሉ። ግጥሞች እየተገጠሙ በውርድ ንባብ ይሰማሉ ወይም አዝማሪዎች በየቦታው ያዜሙዋቸዋል። እንደ ህልም እንደ ቅዠት የሆነ ወቅት ነበር። የመልአከ ፀሐይ ንግሥ እየተዘጋጀ ነው። አርበኛው ሁሉ በአንድ መሪ ሥር፣ በአንድ የዕዝ ሠንሠለት ሊተሣሠር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የልጅ ኃይለማርያም ማሞ[47] ጦር በነገሩ ባለመስማማት ራሱን ከባላምባራስ አበበ ጦር ሊገነጥል ነው ይባላል። ጥሩ ነገር አልሞ ከእንቅልፍ ነቅቶ እንደገና አሸልቦ ተቃራኒውን የሚቃዥበት እረጅም የሚመስል አጭር ሌሊት ይመስል ግራ ያጋባል። ከለአንድ መሪና ካለአንድ ወጥ የትዕዛዝ ሰንሰለት አርበኝነቱ አይሳካም የሚለው ነገር አሁን ያሳመነው ሰው ወዲያው ደግሞ ባላምባራስ አበበ ራሳቸውን ለመሾም ያደረጉትና ራስ ወዳድነት ነው የሚለው ክርክር ልቡን ለሁለት ይከፍለዋል።

የድሮ ክብር ዘበኞች በያለበት የገበሬውን ጦር የወታደራዊ ሰልፍ ሥነ

ሥርዓት ያስተምራሉ። ብዙ የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ይውለበለባሉ።

“እሺ?” አለችው አስካለ በረጅሙ ተንፍሳ ለገሠን በዚሁ ሰሞን አንዱን ቀን የወታደራዊ ሰልፍ የማስተማር ግዳጁን ፈጽሞ ወደ ቤት ሲመለስ። ብዙ ዘመን ተለያይተው

ኑሮው አንዳቸው በአንደኛው ሕይወት ውስጥ ምን እንዳለፈ የማያውቁ ሰዎች አባባል ነበር። ምን ሆነ? ነገሩ ምንድነው? የሚል የመሰልቸት አባባል ነበር።

ለገሠ ወደ መደቡ አመራና ጠበንጃውን አውርዶ በእግሮቹ መሃል አሳለፈና አፈሙዙን በሁለት እጆቹ ይዞ እንደምርኩዝ ተመርኩዞት ተቀመጠ። ከዚያም ግንባሩን አፈሙዙ ላይ ደፋና "የቸገረ ጉዳይ ነው።" አላት።

"ምኑ ነው የቸገረ ጉዳይ?" አለችው። የዚህ ሰሞን ጉዳይ ችግሩና ጥሩነቱ ምኑ ከምኑ ላይና የቱ የትኛው መሆኑ ጠፍቱዋታል። ችግሩ ይህ ነው ብሎ የሚያውቅ ቁርጠኛ ሰው ብታገኝ፣ ችግሩን መፍትሔ ያገኘለት ያህል አድርጋ ትቆጥራዋለች።

"ሁሉም ነገር።" አላት እንዴት ላውቀው እችላለሁ የሚል ስሜት እየተነበበበት። እንኳን እሱ ቀርቶ ተማሩ የተባሉት ሰዎች ስለ ሁኔታው ግልጽ ያለ ሃሳብና የሚከተለውም ነገር ውጤቱ እንዴት እንደሚሆን በግልጽ እንደሚያውቁት፣ እንደተከሰተላቸው፣ ያህል ያወራሉ እንጂ ከፊታቸው፣ ከመንፈሰቸው፣ የሚታየው ግን ምን እንደሚከተልና ምን እንደሚሆን በግልጽ አለማወቅና እንደ ተራ ሰው ሆድ መባባት ነው።

"የተማሩት ሰዎች ምን ይላሉ?" አለችው። ጥያቄዋን አለሳልሳ። ሌላው ቢቀር ሃሳቡ እንዲከፈልና የሚይዘው እንዳጣ በባህር ላይ እንደተወረወረ ኩበት እንዲዋልል አትፈልግም። የሰው ልጅ በአንድ ነገር በቁርጥ ማመን አለበት። ሰው የሚሠራው፣ የሚኖረው፣ የሚያልመው በእምነት ነው። ሃሳቡ የተከፈለ ሰው የሞተ ያህል ነው። አስካለም የለገሠ ሃሳብ ሲዋልል ስታይ በአንድ ነገር እንዲያምን ፈለገች። ለዚህም መፍትሄው ቀደም ሲል ቃላቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል አግንኖ የሚናገርላቸው የተማሩ ሰዎች ናቸው ስትል አሰበች።

"እነሱማ የሚሉት ተከፋፍለን፣ ተበታትነን፣ ከቆምን ዓላማችን ግቡን ስለማይማታ፣ የሞቱት ወንድሞቻችን ደምም ደመከልብ ስለሚሆን፣ ለመተባበር የምንከፍለውን መስዋዕትነት፣ መሪ ለማግኘት የምንከፍለውን መስዋዕትነት፣ ከጣሊያን ነፃነታችንን ለማግኘት የምንከፍለው መስዋዕትነት ዓይነት አድርገን እንቁጠረው ነው።" አለ አስካለን በተስፋ ዓይን በፍቅር ዓይን እያስተዋለ።

"ጥሩ ሳይሆን አይቀርም። መሪ የመፍጠሩና የመተባበሩ ጉዳይ የሚያስከፍለው መስዋዕትነት ምንድነው?" አለችው። የሚያስፈልግ መስዋዕትነት ሊከፈል ይገባል በሚል ዘይቤ። ጥያቄዋን አሁን በገለልተኝነት ወይም እንዳልገባው ሰው ሁና ማቅረብ አልፈለገችም ።

"ደም ነው፣ አስካለ።" አለ ተከዞ። "ይህን ሃሳብ የማይቀበሉትን እንዲቀበሉት ማግባባት፣ የማይቀበሉትን ማስገደድ። ጃንሆይ አልጋወራሽ ሲሆኑ ያልተቀበሉዋቸውን መሳፍንት እንዳስገደዱት ማለት ነው። አጼ ቴዎድሮስ እንዳደረጉት ማለት ነው። ይህ ሲሆን ግን

ጣሊያኖች ከባሕር ማዶ ሆነው ሳይሆን ከአጠገባችን ሆነው እያናፈሱት ነው።” አለ በምሬት።

“ቀስ በቀስ በማግባባት ሊሆን ይችላል። አሁን ጦርነት አይከፈትም። ለረጅሙ ጊዜ ደግሞ በእንዲህ ዓይነት ወቅት ማን ሊተነብይ ይችላል።” አለችው።

“አዎን።…አዎን። እነሱም እንደዚሁ ነው የሚሉት፤” አለ። የተማሩት ሰዎች የሚሉት ትዝ ብሎት። ለወደፊቱ እርስ በርስ መዋጋት ሊኖር ቢችልም ለጊዜው ግን እንደማይኖር ትዝ ብሎት በመደሰት። ይህንን ጉዳይ ደጋግሞ የሰማው ቢሆንም፣ በቡድኖች የእልህና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ውስጥ የሚወረወሩት ቃላት፣ ጦርነት ነገ ተነገወዲያ የሚከፈት ያህል አሳምነውት ነበር። አስካለ ይህንን ባትል ኑሮ ይህ ከዕለት በዕለት ጩኸትና ሁካታ ሥር የተደበቀ እውነት ተገልጾ አይታየውም ነበር።

“ይህ አሁን የምንሠራው ሥራ ምን ይባላል?” አለችው ለምን መጨቃጨቅ ትተን ጥሩ ጥሩ ነገር አናወራም የሚል ስሜት የሚፈጥርበትን ራሱን እያሻሸችው። የለገሠ ሃሳብ መዋለሉን መተው ገብቱዋት ፈገግ ብላ።

“ንጉሥ ማንገሥ ይባላል አስካልዬ፤ ንጉሥ አንጋሽ!” አለ አዲስ በልቡ የሰረፀው ሃሳብ ጭንቀቱን ከፍሎለት፣ ብጤ ጓደኞቹም ጋር ያስጨነቃቸው ለነበረው ችግር መፍትሔ ስላገኘ ሊያጫውታቸው ቸኩሎ። በእንዲህ ዓይነት ወቅት ከፊት ለፊት ላለው ችግር መፍትሔ ከተገኘለት የበኋላው አያስጨንቅም።

በማግስቱ መልአከ ፀሐይ እያሱ ታላቅ ወታደራዊ ሰልፍ ተደርጎ፣ ንጉሥ ሲባሉ፣ ባላምባራስ አበበን ደግሞ መልአከ ፀሐይ እያሱ ራስ ብለው ሾሙዋቸው። በፈንጠዝያው፣ በደስታው፣ በሰልፉ፣ በባንዲራው ብዛትና ድምቀት ውስጥ ስለወደፊቱ ችግር ትዝ ያለውም የለ። ጃንሆይ በአጋዴን በኩል እርዳታ ይዘው እየመጡ ነው አይዞዋችሁ ብለዋል! እያሉ ሕዝቡን ለማጽናናት ነጋሪት እየመቱ አዋጅ ከወር በፊት ይናገሩ የነበሩ የጦር አዛዦች ስደተኛውን ንጉሥ አላስታወሱም። ሁሉም ወደ ሰማይ ከፍ ብለው እንደሚውለበለቡት ባንዲራዎች በተስፋና በደስታ መጠቀ።

እያንዳንዱ የደስታ ወቅት ግን የሃዘን ወቅት የሚያረግዝ ይመስል አሳዛኝ ወሬ ያስከትላል። ራስ አበበ ለልጅ ኃይለማርያም ማሞ የክብር ስምና የግዛት ክልል ቢሰጡዋቸው፣ “እኛ ሰባኪዎች እንጂ ተሰባኪዎች አይደለንም፣” ብለው አልቀበልም ማለታቸው ተሰማ። እንዲያውም ጦራቸውን ከራስ አበበ ስር ማውጣታቸው የሚያስደንቅ ወሬ ሆነ። ሁለቱ የጦር መሪዎች ግን ለጦርነት ስላልተፈላለጉ እፎይታ ሰፈነ።

እፎይታው ብዙም ሳይቆይ ግን የኢጣሊያ መንግሥት በሁኔታው በመደናገጥ ከወሎ፣ ከኤርትራ፣ ከሊቢያ፣ ከሱማሊያ፣ ያመጣውን ጦር

አሰባስቦ ከፈተኛ ጦር ሊያዘምት መሆኑ፣ መልአከ ፀሐይ እያሱም በጠና ታመው መተኛታቸው አብሮ ገጥሞ ታወቀ።

አስካለ፣ ለገሠና አንድ ጓደኛቸው የሆነ አስታጥቄ የሚባል ሰው ስለሁኔታው በዚያ ሰሞን ሲወያዩ አስታጥቄ "ነገሩ አሳሳቢ ነው። ያስፈራል። ግን ያልፋል፤" አለ እንደዋዛ አድርጎ። ሌላም የሚጨምረው ነገር እንዳለ ከሁኔታው እየታየ።

"እንዴት?" አሉት ሁለቱም በአንድ ላይ። ጨዋታውን እንዳያቋርጥ ለማደፋፈር የተናገሩት ነበር።

"የካቲት 12 ቀን አዲስ አበባ ላይ ጣሊያን በአካፋና በዶማ፣ በሳንጃና በጥይት፣ በእሳትና በግፍ ኢትዮጵያን የለበለባት እለት እኔ ያሳለፍኩዋትን ፍራት አስታውሳለሁ።" አለ አስታጥቄ ከየካቲት 12 ፍጅት በኋላ ከአዲስ አበባ ጠፍቶ አርበኞችን የተደባለቀ ሰው ነው። የዚያን እለቱን ግርግር ያስነሱት አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በአሁኑ ጊዜ ከራስ አበበ ጋር ይገኛሉ። [40] "የዚያን እለት ቤቴን ዘግቼ በበራፉ ቀዳዳ አሾልኬ እየተመለከትኩ ወፍ ዝር ሲል ወይም የጣሊያኖች ካሚዎኖች በመንገዱ ሲያልፉ ድምጻቸውን ስሰማ እጣየ የደረሰች እየመሰለኝ እርበተበት ነበር። በእንብርክኬ ነው……እንደ……ሴት የሸናሁት። ከእናንተ ምን እደብቃችኋለሁ። እያንዳንዱዋ ቅጽበት ዓመት ነበር የሆነችብኝ…… ሰው ሕይወቱን እንዴት እንደሚወዳት የተረዳሁት የዚያን ዕለት ነው። ከዚያ በፊትማ ጀግና እንደሆንኩ፣ ከሞት ፊት እንደማልርበተበት ይሰማኝ ነበር።" አለና በሃዘን ፈገግታ ተመለከታቸው። እነሱም አቀርቅረው ዝም ማለታቸውን አይቶ ቀጠለ። "እንደዚያ እየፈራሁ ስርበተበት የጣሊያን ወታደሮች ወደ ቤቴ ሲያመሩ ሳይ ግን ልቤ ከዳኝ። ብቻ በደመነፍስ በበራፉ መካፈቻ በኩል ግድግዳውን ተጠግቼ ቁጭ አልኩ። በራፉን እንኳን አልቀረቀርኩትም። መጨረሻዋ የመከላከል አቅሜ እንኳ በና ጠፋች። የጣሊያኖቹ አዛዥ ወታደሮቹን ወደ ኋላ ትቶ በራፉዋን በእርግጫ ሲመታት በራፉዋ ከመሬት የምትታከክ ሰለነበረ ትንሽ ተከፍታ ቆመች። ይገርማል እኮ። ሕዝቡን መሣሪያውን ባይገፋት ኑሮ፣ አለቃው ኋላ ሆኖ፣ ተከታዩን ወደፊት ይልክ ነበር።" አለ በመገረም። "በራፉዋ ከፊት ስትልለት፣" ሲል ቀጠለ። "አንገቱን አስገብቶ ያችን ጎጆ ቃኛትና ከቤት ውስጥ ምንም እንደሌለ ገምቶ ደም አስክሮት ኑሮ ሌላ ሰው ለመፈለግ ወጣ። ወታደሮቹም ተከትለውት ሄዱ። እኔ ግን ከዚያች ከተቀመጥኩበት ቦታ የተንቀሳቀስኩት ብዙ ሰዓት ቆይቼ ከጨለመ በኋላ ነበር። ለመነሳትም፣ ለመነቃነቅም ድፍረት አልነበረኝም። እያደር ግን ነፍሴ ስትመለስ በራፉን ከፍቼ፣ ጨለማን ተገን አድርጌ ከከተማው ወጣሁ። ለሚሸሽ ሰው ጨለማ እንዴት ዘመዱ መሰላችሁ። … መቸ አጣችሁት……..ሌላ ቀን የሚያስፈራንና የሚያደናቅፈን የዚያን ዕለት ጋሻ መከታና አጋር ይሆነናል።" አለና ትንሽ እንደመተከዝ ብሎ ከዚያም ከከተማው ውጭ አብርሃም ደቦጭንና ሞገስ አስገዶምን አግኝቱዋቸው ያላቸውን ነገር

[40] የየካቲተ 12 በማርሻል ግራዚያኒ ላይ የተጣለው አደጋ በስደት የነበሩት ንጉሠ ነገሥቱ በበላይነት ያቀነባበሩትና የመሩት እንደነበር የታሪክ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ።

አስታወሰና ፈገግ አለ። ሁለቱን ሰዎች እንዳገኛቸው እነሱ መሆናቸውን ሳያውቅ መጥፎ ሰዎች አስጨረሱን እያለ አውርቶአቸው ነበር። "አሁንም ጦርነት ሊመጣ ሲል በሃይል እረበሻለሁ። ወደ ጦርነት ቦታ ስንሄድ ጩኸም፣ እሩጥም ያሰኘኛል። አንድ ጊዜ ተኩስ ከተከፈተ ግን ፍራቻ ከልቤ ይጠፋል። መግደል እንጂ መሞት አይታየኝም። ዛሬም እንዲሁ ነው፣" አለ አሁን አዲስ የተፈጠረው ሁኔታ የተለየ ስሜት እንደማይፈጥር እርግጠኛ ሆኖ።

"መች አጣነው ብለህ ነው?" አለ ለገሠ የሱም የፍራት ወቅቶች ትዝ ብለውት። የወንድ ልጅ ፍራት አለ። ከጦርነት የማያግድ። ለገሠ ግን የጀመረውን ወሬ አልጨረሰውም። ሌላ ጓደኛው እየተጣደፈ ወደሱ ማረፊያ እየመጣ ነው። "ምነው ወንድሜ?" አለው ከሰላምታ በፊት ጥያቄ አሰቀድሞ።

"መልአከ ፀሐይ እያሱ ሞተዋል። ጣሊያን ጦርነቱን ከቃፊሮች ጋር ከፍቱዋል።" አለ እሱም ከሰላምታ በፊት መርዶውን አስቀድሞ። አንዳንዱ ዘመን፣ አንዳንዱ ነገር፣ ለሰላምታና ለትህትና፣ ለወግና ለባህል፣ ለፈሊጥ ጊዜ አይሰጥም።

አስካለም፣ ለገሠም፣ ጓደኛቸውም ልባቸው እየመታ ደንግጠው ተነሱ። በዚያው ወቅት አካባቢው ተተረማመሰ። የኢጣሊያ አውሮፕላኖች አምስት ሆነው በቦንብ አካባቢውን ደበደቡት።

⅄ ⅄ ⅄

# ሁለት ባቄላዎች

እያንዳንዱ ጦርነት የራሱ ታሪክ አለው። እያንዳንዱን ጦርነት ግን ማንም ግለሰብ በራሱ ዓይን ብቻ ውጣ ውረዱን፣ ሂደቱን፣ ሊቆጣጠረውና ሊያየው አይችልም። ዛሬም አርበኞች በከበባ ውስጥ በወደቁበት ጊዜ በርትቶ መዋጋትንና በአመች ሁኔታ ማፈግፈግን መረጡ። ይህኛው ጦርነትና ከበባ ግን ከአለፉት ጊዜያትም የከፋ ነበር። በመጀመሪያው ከበባ ጊዜ ሃምሳ ሺ ጦር አሰልፎ የመጣው ጠላት፣ ዛሬ በብዛት መጥቱዋል። በሌላ በኩል በአርበኛው መሃከል የእህል ችግር ብቻ ሳይሆን የወረርሽኝ በሽታ ገብቶ ረፍርፎታል።[41] አርበኞቹ አመች ወቅት ለማግኘት አስከማታ ድረስ ተዋግተው ቢያፈገፍጉም ጠላት አየለባቸው። በመጨረሻም ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ ገቡ።

አርበኞች እያፈገፈጉ በሄዱ ቁጥር ኃይላቸው እየተዳከመ ሄደ። የዚህን ጊዜ ግን አርበኞች የእግዜር ታምር የሚሉት፣ ሌላው አጋጣሚና የሽምቅ ውጊያ አሳችነት ብሎ

[41] ፋሺስት ጣሊያን የኬሚካል ውጊያ ብቻ ሳይሆን ወረርሽኝ የሚያስከትሉ በሽታዎችን በተዋጊው ነጻ ክልሎች እንደሚያሰራጩ እንደነበር አንዳንድ ተመራማሪዎች ይጠቁማሉ።

የሚጠራው ሁኔታ ተፈጠረ። ልጅ አየለ ኃይሌና ደስታ ሸዋርካብህ ባልታሰበ ሁኔታ ራስ አበበ ላይ የተጫነውን ኃይል ገቱት።[42] ሰሞኑን አስካለ አሙዋታል። ህመሙዋን ግን ለማንም አልተናገረች። የአልጋ ቁራኛ የሆነ ሰው ከጤነኛው ሊበልጥ በደረሰበት ሁኔታ ውስጥ አስካለ አቅም አጥታ እስክትወድቅ ድረስ አመመኝ ብሎ መናገሩ ይሉኝታ ቢስነት አድርጋ ወስዳዋለች። ስለ አስካለ መታመም የጠረጠረና አሞሻል ወይ እያለ የሚጨቀጭቃት ለገሥ ባሉዋ ነው። እሱዋ ግን "ምን ሆነሃል፣ ማን አመመኝ አለህ?" እያለች አፉን ስለምታሲዘው ዝም ብሎ በመተከዝ ከመመልከት በቀር መናገሩን አቁሙዋል።

አርበኛው ሦስት አራት ቀን ካለምንም ምግብ በባዶ ሆዱ ወንዝ ለወንዝ ይወርዳል፣ ይወጣል፣ ይጓዛል። ወፍ ዘራሽ አታክልትና የዱር ፍሬ ሲያገኝ ይበላል። ችግሩ በሃይል ሲጠና አሳሽ ክፍል እየተላከ የተቻለውን ያህል እህል እየያዘ ይመጣል። የሚመጣው እህል ግን አንድም ቀን አጥግቦ አብልቶ አያውቅም።

"ዛሬስ አስካልዬ ሻል ያለሽ መሰለኝ።" አለ ለገሥ አስካለን በዓይኑ እያባበላት።

"ተሽሎኛል፣ ዛሬስ ይመስገን።" አለች አስካለ ያለፈውን ሰሞን ስቃይዋን ስታስታውሰው እያንገሸገሻት።

"ለምን ታዲያ አላመመኝም ትይኝ ነበር?" አለና ለገሥ ተናደደ። ዛሬ መዳኑዋን ሲያውቅ የዚያን ጊዜ የቻለው ብስጭቱ ገንፍሎበት። "ለኔ ሕመምሽን፣ ችግርሽን ካላማከርሽ ለማን ታማክሪዋለሽ?" አለ ቁና ቁና እየተነፈሰ።

"የአርበኝነት ዘመን ነው። አትርሳ፤" አለችው ቁጣውን ለማብረድ ሳቅ እያለች። ፀሐይ ከአድማሱ ብቅ ብላ ትልቅ ሆና ትታያለች። በየድንጋዩ ላይ ሰዎች ተቀምጠው ግማሾቹ ሲጫወቱ ጠና ያሉት ፀሎት ያደርሳሉ።

"ትንሽ ትንሽ ባቄላ ከአፋችሁ አድርጉ።" ብሎ አንድ ወጣት አርበኛ ለአስካለና ለገሥ ሥጥቶአቸው አለፈ። አስካለ ባቄላዋን በፍኙዋ ይዛ ወደ አጎቱዋ ወደ በሻህ ኃይሌ ሄደች።

በሻህ ኃይሌ ዳዊቱን ደግሞ እንዳበቃ በቃሉ የሚማፀነውን እያለ ምራቁን እጁ ላይ እንቱፍቱፍ በማለት ፊቱን እየጠራረገ ተለማምኖ ሲጨርስ ቀና ብሎ አትኩራ የምትመለከተውን አስካለን አይቶ ፈገግ አለ።

"ምን ፈለግሽ አስካለ?"

"ፈንታህን ይዤ መጥቼ ነው አብዬ።"

---

[42] ልጅ አየለ ኃይሌና ደስታ ሸዋርካብህ በኋላ ደጃዝማች። እጅግ የታወቁ የሸዋ አርበኞች።

"ምኑን።" አለ በመገረም። ፋንታህን የሚባለው ቃል ከንብረት፣ ከምግብ መጥፋት ጋር አብሮ የጠፋ አድርጎ ቆጥሮታል።

"አፍህ የምታደርገው።"

"ከየት ተገኘ?" ብሎ በመገረምና በመደነቅ ተመለከታት። እሱም ሆነ ሌሎች አርበኞች እህል ከቀመሱ ሦስት ቀን አልፏቸዋል። ጥሬውን ሙዝ በጉጉት ከበሉ ሦስት ቀን አልፏቸዋል። ከበሻህ ኃይሌ ዓይን ላይ ግን የመጓጓት ነገር አይታይበትም። የመጀመሪያው አሥራ ሁለት ሰዓት ካለፈ በኋላ ሆዱን ይበላው የነበረው ስሜት ቆሟል። የገረመው ግን በእጇዋ ምግብ ይዛ አይታየውም።

"እፍኝ ባቄላ፣" ብላ ጥቂት ባቄላዎች የያዘ እጅዋን ዘረጋች።

"ለሎቻችሁስ?" ብሎ ጠየቀ ብቻውን ተለይቶ መብላት ደስ አይለውም። አይዋጥልኝም ይላል። ሰው መተሳሰቡ የሚታወቀው ደግሞ በዚህ ዓይነት ቀን ነው። እህል በተትረፈረፈበት ቦታ የሚያጎርስና በሰላሙ ጊዜ ጦርነት እወዳለሁ ብሎ ከሚያወራው፣ በችግር ወቅት እጅግ ከሚፈለገው ለሰው የሚያካፍልና በጦርነት ውስጥ ቆሞ መራመድ የሚችል ልዩ ነው።

"ሁላችንም ፈንታችንን በልተናል። አንተ ፀሎት ስለያዝከ አስቀምጬልህ ነው።" አለችው።

"እህት ጥሩ ነው።" አለ ጉርሜሳ፣ በሻህ ኃይሌ የያዘውን እፍኝ ባቄላ እየተመለከተ ፈገግ ብሎ። "እንደ ዛሬው ባቄላ ጣፍጦኝ በልቼው የማውቅ ምግብ የለም። ወደፊት የአገራችን ነፃነት ቢመለስ የምበላው ምግብና የምጠለልበት ጎጆ ካገኘሁ ሌላ አልመኝም።" አለ ተከዝ ብሎ። ጉርሜሳ ከሰላሌ አርበኞች አንዱ ነው። በመስኩ አገር ኦሮሞዎች አዲስ የፈረስ ላይ የሽምቅ ውጊያ ጥበብ መስርተው ጣሊያንን ያርበተብቱ እንደነበር በሻህ ኃይሌ ሲሰማ ቆይቶ ጊዜ አጋጥሞት እነሱ አገር ከርሞ ደግሞ ጣሊያን በዚያ በኩል ስለበረታ ከዚህ ተገናኝተው፣ አሁን ወደ መንዝ ሌላ ከበባ ጥሰው እየመጡ ነበር ።

በሻህ ኃይሌ ለጉርሜሳ ከባቄላው ሊያካፈለው ቢፈልግም ጉርሜሳ ለቅልውጥ የመጣሁ መሰልህ ወይ ብሎ ቅር እንዳይለው ፈርቶ ብቻውን እያንዳንዱዋን ጥሬ ባቄላ መቆርጠም ጀመረ።

"ይህ ጅብ በላብኝ እኮ፣" አሉ መምሬ ነውጡ ንዴት በሌለበት ዓይናቸው ሰውን ሁሉ እየቃኙ። "አንድም አላስተረፈልኝ እኮ።" አሉ የመጨረሻዋን ባቄላ ሲጎረድም አዝብጤን እየተመለከቱ። "ግሩም ነው እኮ።" አሉ። እያንዳንዱን አረፍተ ነገራቸውን በእኮ መጨረስ ይወዳሉ።

"መብላቱንስ ሁሉንም በልቸዋለሁ።" አለና ጓደኞቹ ሁሉ ጉድ የሚሉት ስለመሰለው የሠራው ሥራ መርሮ እንዳይተረጎምበት እራሱን ለመከላከል ሲል፣ "አንተ ጠግበህ

አስቀምጠሃቸው ምን ላድርግ። አትበላቸውም ኑሮዋል?" አለ። አብሮ አደግ ስለሆነ ቄስ ቢሆኑም አንተ ይላቸዋል።

"ዳዊቴን እስከጨርስ ነበርኮ፣ ደግሞስ አንድ ፍሬ ባቄላ እፍኝ የማይሞላ ምን ሊያረግልኝ ነውኮ……ብላው።"

"እኔ እንዴት ነው እፍኝ ሙሉ ባቄላ የደረሰኝ?" አለ በሻህ ኃይሌ በመገረም።

"አስካለ የራሱዋን ጨምራልህ ነው ማለት ነው።" አሉ የበሻህ ኃይሌ ሚስት እንደመተከዝ ብለው።

"እኔስ እህት ያለው እድለኛ ነው ያልኩት መብዛቱን ተመልክቼ አልነበር?" አለ ጉርሜሳ እየሳቀ።

"አስካለ ጉደ ሠራሽኝ፣" ብሎ ስላሰበችለት ተከፍቶ ሳይሆን ራሱዋን መስዋዕት በማድረጉዋ ተናዶ ገላመጣት። "ደግነቱ ጨርሼ አልበላሁትም። እንዲህ አታድርጊ እቴ።" ብሎ በመቆጣቱ ተጸጽቶ ፈገግ እያለ መለሰላት። ከፍቱዋት ተቀበለችው። ጥሩ ሰጭ መሆን አይበቃም። ጥሩ ተቀባይም ያስፈልጋል።

መምሬ ነውጡ ወደ ፀሎታቸው ተመልሰው ተመስጠው ፈጣሪያቸውን መለመን ቀጥለዋል። በአካባቢያቸው የሚሆነውን ሁሉ የሚሰሙ አይደሉም። ቆይተው ፀሎታቸውን ጨርሰው ዳዊታቸውን አጣጥፈው ጋቢያቸውን ሰብሰብ አድርገው ሲነሱ ከላያቸው ጥቂት ነገሮች ተንጠባጠቡ። የሚወድቁትን ነገሮች ዓይናቸው ተከትሉዋቸው ከመሬት አረፉ። ባቄላዎች። "ይህ ጅብ ሁሉንም አልበላቸውምኮ። አስተርፎልኛል፣" ሲሉ ጮኸው ተናግረው ወዲያው ሌላ ነጣቂ የመጣባቸው ይመስል እየተገላመጡ ከአፋቸው ከተው ጉርድምድም አደረጉት። በድል አድራጊነት ፈገግ አሉ። "የታለ ያ ጅብ? ወላዲት አምላከን ባያስተርፍልኝ በዚህ ምንሽሬ በስመአብ ብዬ እባርከው ነበርኮ።" አሉ ጠበንጃቸውን እንደማስተካከል አድርገው በቀልድ።

በሻህ ኃይሌም ንዴቱም፣ እልሁም ሁሉም ተነባብሮ ተደናግሮት "አይ አስካለ!" አለና ቀና ብሎ ሰማዩን ተመለከተ። እንደገና አግድሙን ሲያማትር የሚወዛወዝ ነገር ያየ መሰለው።

ጆሮው፣ ዓይኑ፣ መላ መንፈሱ ወደዚያ አተኮረ። የሽምቅ ተዋጊ ውቃቢው ቀፈፈው። መነፅሩን አውጥቶ በልቦናው የጠረጠረውን ለማየት እየመዘዘ አርዝሞ ወደዚያ አነጣጠረው። "ወደ ገጦ ነው የሚያመራው፣" ሲል መንጽሩን ከዓይኑ ሳያወርድ ተናገረ። "ለራስ አበበ ቶሎ አስታውቁ፣" ሲል አሁንም ከመነጽሩ ዓይኑን ሳይነቅል ተናገረ።

መንዝ ከሚያዚያ 27 ቀን 1929 ጀምሮ በተቃጠለችና በተከበበች ጊዜ ወደ ባላምባራስ አበበ ጅሩ ከበባውን ሰብረው ከሄዱት አርበኞች መሃል ከፈለው ወልደ ፃዲቅ በሰኔ ወር ወደ መንዝ ተመልሶ ከልጅ ግዛቸው ኃይሌ ጋር ሲገናኝ ሌሎቹ ግን ከራስ አበበ

ጋር ወደ ግንደበረት ሰላሌ ሄደው አሁን እንደገና ጥቂቶቹ ወደ ጎጃም ሲሻገሩ አብዛኞቹ ወደ መንዝ ተመልሰዋል። ከዚህ የተሰበሰቡት አርበኞች ከኦሮሞው፣ ከአዳሉና ከአማራው የመንዝ አካባቢ የተውጣጡ አርበኞች ብቻ አይደሉም። ከኤርትራ እነ አብርሃም ደቦጭ፣ እን እምአእላፍ ከጎንደር፣ ከጎጃም የመጡ የጥንት ክብር ዘበኞች አሉ።

ገጦ ለአርበኞቹ ቅርብ ስለሆነ ትንሽ እረፍት አድርገው፣ ከዚያም እስከዚያው ሄደው፣ አመች ቦታ ይዘው፣ ሊወጉት ተቆረጡ። አስካለም ወዲያው ጋደም ካለችበት እንቅልፍ ይዞዋት ሄደ። አስካለ ምን ያህል እንደተኛች አታስታውስም። ትንሽ ሸለብ ሲያደርጋት የተሟሟቀ ጦርነት ውስጥ ገብታ ለገሥን በዚህ ውጣ፣ በዚህ ውጣ ስትል ብንን ትልና መጥፎ ቅዠት ብላ ጥሩ እንቅልፍ እንዲወስዳት እንደገና ታሸልባለች። ተመልሶ ግን ያው ነው። በመጨረሻ የነቃችው ለገሥ ከጎኑዋ ቁጭ ብሎ ሲኮረኩራት ነው። ዓይኑዋን ገለጥ አድርጋ እንደመደናገር ሲላት አይቶ ሰው እንዳይሰማው ቀስ ብሎ በሚስቁ አይኖቹ እየተመለከታት፣ “የጥሪኝ ባቄላዎች ቻሪዋ እመቤቲቱ ተነሺ፣” አለ።

“ጥሪኝ ባቄላ ቆርጣሚው፣” አለችው እየሳቀች ዓይኑዋን እያሻሸች።

“አንቺ ይህንን ጭብጦ ገማጭ፣” ብሎ በኋላ በኩል የደበቀውን ጭብጦ አውጥቶ ሰጣት።

“ከየት አመጣኸው? ይኸ ሁሉ አህያ ምንድነው?” አለች የጭብጦው ጉዳይ አካባቢዋን እንድትቃኝ አድርጉዋት። ሌሎቹም ብዙ እንግዶች ይታያሉ።

“አንቺ ስታንቀላፊ አገሬው መስተንግዶ አምጥቶ ስንተራመስ ነበር።”

“እንካ!” አለችው ግማሹን ቆርሳ ቀምሳለት።

“እስከጠግብ በልቻለሁ። ላንቺ ነው ይዤ የመጣሁት። ማን ይመስልሻል መስተንግዶውን ያመጣልን?” አላት በፈገግታ እየተመለከታት።

“እንዴት አውቃለሁ። ያገሬው ሕዝብ ነው አላልከም?” አለችው ምን ሊናገር እንደፈለገ ለማወቅ ሞከራ ስላቃታት ሰልችታ።

“ልጅ ከፈለው ወልደ ፃዲቅና ዳኘው።” አለ ስሙ የሚፈጥርባትን ሁኔታ ለማስተዋል አትኩሮ እየተመለከተ።

“ራስ ምን አሉ?” አለች አስካለ በመገረም።

“ራስ አስተዋይ ሰው ናቸው። ምንም ጉዳይ አላነሱም።” አለ ለገሥ ፍፃሜውን አርቆ ለማስተዋል እየሞከረ።

በአለፈው ዓመት ከፈለው ጦር ልኮ ተገኘ ቡሴይራ[43] የሚባለውን ሰው መትረየሱን አስነጥቆ እሱን አስሮት ነበር። ከፈለው መትረየሱን ከተገኘ ቡሴይራ እንደተረከበ ዳኘውን “ዳኜ እንግዲህ መትረየሴን ለኔው መልስ። አንተ ይህንን ለራስህ አድርግ፣” ብሎ እንደሰጠውና ከፈለውና ዳኘውም አንዳንድ መትረየስ ከያዙ በኋላ ከፊታቸው ጠላት የማይቆም የጦር አዝማቾች እንደሆኑ ሰምተዋል። “ለመሆኑ ዳኘው መትረየሱን ይዞት መጥቶአል?” አለች አስካለ ።

ተገኘ ቡይሴራ የደረሰበትን በደል ባይሾሙም እንደ አርበኞች ሁሉ መሪ ይቆጠሩ ለነበሩት ለራስ አበበ አረጋይ አመልክቶ ራስ ከፈለውን መጥቶ መልስ እንዲሰጥ ቢጠይቁት እንቢ በማለቱ ራስ በጣም ተቀይመው ከፈለውን ልክ ለማግባት ቆርጠዋል። ዛሬ ደግሞ ከፈለው ምንም እንዳልተፈጠረ ራስን ለማስተናገድ እህል ውሀ ይዞ መጥቷል። “መትረየሱንስ ይዘው አልመጡም፣” አለ ለገሥ አስካለ ለጠየቀችው ጥያቄ። “አስካለ ዳኘውና አንድ ሰው ወደዚህ እየመጡ ነው፣” አላት ቀጥሎ። አስካለ ቀና ብላ ተመለከተች።

“ታደሰ የምልህ የዚያች የአክስቴ ልጅ የፋና ባል እሱ ነው፣” አለችና አስካለ ተነስታ ወደነሱ አመራች።

አስካለ ታደሰን አገላብጣ ስማው ዳኘውን ሰላምታ ሰጥታ ስለጤንነታቸው ብዙ ጠየቀች። “ፋና እንዴት ነው?” አለች የቤተሰቡዋ ሰው ወንዱ አንቺ፣ ሴቱ አንተ ይባባላል።

“ደህና ናት። ሰላምታም አቅርባለች። አገላብጠህ ሳምልኝ ብለኛለች።” አለ ታደሰ አስካለን በናፍቆትና በፍቅር እየተመለከታት።

“ታስቸግርሃለች?” አለችው በመሃከላቸው ስለ ፋና ሁለቱ የሚያውቁት ምስጢር እንዳለ ሰው ፈገግ ብላ እየተመለከተችው።

“አታስቸግርም። አይ አስካለ!” አለና ሳቀ። “በኋላ ስንመለስ እንገናኛለን።” አለ ታደሰ።

“ወዴት ልትሄዱ ነው?” አለችና ወዲያው ጉዳዩ ገብቷዋት ለገሥን ከሁለቱ ሰዎች ጋር አስተዋወቀችው።

አስካለ በእጇዋ ይዛ ከነበረው ዳቦ እየቆረሰች ስትሰጣቸው ዳኘውና ታደሰ እንቢ አሉ።

“የነሱ ድግስ ነው ተያቸው።” አለ ለገሥ ፈገግ ብሎ። ዳኘውና ታደሰ ተሰናብተው ሲሄዱ ለለገሥ አሁንም የቆረሰችውን ዳቦ ሰጠችው።

“ጠግቤአለሁ አስካለ፣” አለ የሚያደርገው ጠፍቶት።

[43] ቀኛዝማች ተገኘ ቡሴይራ በኋላ የተሰጣቸውን ማዕረግ አላወኩም። በሸዋ በተለይ በይፋት የታወቁ አርበኛ ነበሩ።

“እኮ እንካ።” አለችው ቅር ብሎዋት።

“ወደ ጦርነት መውረዳችን ነው። ልቅመስልሽ እሺ! ብዙ ግን አልበላም። ዛሬ ማርያም ናት። እናሸንፋለን።” አለ በሙሉ ልብ።

“ጠንቀቅ በል ታዲያ።”

“በደንብ እንጂ፣ ከተጠነቀቁ ጥይት አይመታም። ወንድሞቼ ሲታኮሱ እኔ ጉድጓድ ቆፍሬ ከዚያ እደበቃለሁ። አታስቢ።” አለ እየሳቀ።

“በርታ ጎሽ።” አለችው በስስት ዓይን እየተመለከተችው። “እነዚህ ስንቅ ይዘውልን የመጡት ያግዙአችሁ የለም?” አለች በተስፋ በመጨነቅ።

በሻህ ኃይሌ አሁንም መነጽሩን አውጥቶ ተመለከተ። ከሳሲት ምሽግ ተነስቶ የመጣው ጦር ሞፈር ውሀ አዳባይ ከሚሆንበት ከሦስት ኪሎሜትር በፊት ካለው ቦታ ከመስኩ አገር ወደ ተራራማው አገር ማቆልቆል ጀምሩዋል። አሁን አንዱን ረባዳ ጨርሶ ሌላው ረባዳ ገብቷል። ደጀኑ የኢጣሊያ ጦር ከመስኩ ጫፍ ቆመ።

“ራስ አበበ አደራዎን ብለዋል።” አለ መልዕክተኛ። “የተነጋገርንበት አይታጠፍም።” አለ በሻህ ኃይሌ። አሁን የጠላት ጦር ሞፈር ውሀ ወንዝ ገብቷል። ራስ አበበ ተኩሱን ከፈቱ። መላው አርበኛ ከወንዙ ያለውን የጠላት ጦር ቁልቁል ይፈጀው ጀመር። ባሻገሩ ያለው የደጀን ጦር በመድፍ አርበኞቹ ያሉበትን ቦታ መደብደብ ያዘ።

“ዛሬ ፊታውራሪ ደጃዝማች ሆነ!” አለ ለገሠ በማሾፍ። ጣሊያን ጦርነት ሲከፍት መድፍ ያስቀድማል። የመድፍ ድምጽ መጀመሪያ ያስደነግጥ ነበር። አውሮፕላንም እንዲሁ። በኋላ ግን የመድፍ ጥይትና የአውሮፕላን ቦንብ ሰብሰብ ብለው ካልተከማቹለት የማይመታ መሆኑን አርበኞች ስላወቁ ማሾፊያ አድርገውታል።

ከግንባር ቀደሙ የጠላት ጦር ለወሬ ነጋሪ እንኳን አንድም ሳይተርፍ አለቀ። ደጀኑም ጦር ወደ ካምፑ ሳሲት ተመለሰ። በጭንቅና በስደት የቆየው የአርበኞች ልብ ታደሰ።

አርበኞች ጠላት ለቆት ወደ ሄደው ቦታ ሄደው ጠላት ጥሎት የሞተውን መሣሪያና እቃ መሰብሰብ ቀጠሉ።

ለገሠም ጥቂት ቦንቦች በሻንጣው ይዞ ወደ ሠፈሩ ሲመለስ አንዲት ፍሬ ከመሬት አየ። ጎንበስ ሲል የተቆጣጠረው ጐፈሬው ከወደፊቱ ስለወደቀ ያንን ደገፍ አድርጎ ይዞ ባቄላውን አነሳና ተመልሶ ቀና ሊል ሲል ዳግመኛ ሌላ ባቄላ አይቶ እሱዋንም አንስቶ ሳቁ መጣበት። ወደ ሰማይ እያየ ሳቁን ለማፈን ሞከረና ሲያቅተው ጊዜ ሰው ብቻውን ይስቃል እንዳይለው በጋቢው አፉን ሸፍኖ ዓይኑ እንዳይታይ አቀርቅሮ ትንሽ ተራመደና ሲለቀው ቀና አለ። በሻህ ኃይሌ ይህ ሳቅህ ወታደሮችህን ያስንቅሃል እያለ ሁልጊዜም ይቆጣዋል። ለገሠ በበሻህ ኃይሌ በሚመራው የአርበኛ ክፍል ውስጥ የአንዱ አዛዥ ነው።

ለገሥ ከሰፈሩ ሲደርስ “ምን አገኘህ?” አለችው አስካለ ከፊቱ ላይ ደስታ አንብባበት። እስካሁን የታፈነው ሳቁ ገንፍሎበት ተነከተከተ።

“እስቲ ምን አግኝተህ ይሆን የፈነደቅከው?” አለችው ሁልጊዜም ደስ ሲለው ሳቁ ይቀድማል።

“ይኸውልሽ፣” አላት እጁን ጨብጦ። ወዲያው “ምንድነው?” ብላ እንደተቀበለችው የማያቋርጥ ሳቅ ያዘው።

“ባቄላ ምን ያስቃል?” አለች አስካለ በሁኔታው የሱዋም ሳቅ መጥቶ።

“የምትቸሪያቸው ሁለት ባቄላዎች ከጦርነት አውድማ ሰብስቤ አመጣሁልሽ።” አለና እንባው እየተንጠባጠበ ሳቀ። በመጨረሻም መቆም አቅቶት ተቀመጠ።

አስካለም ፀጉሩን እያሻሸችው፣ ፊቱዋ ፈክቶ፣ ሁለቱን ባቄላዎች ቆረጠመቻቸው። ስለባቄላው ሳይሆን የሰዎች ደስታ እንደ ሃዘናቸው ሁሉ በቀላሉ ይነካታል።

⅄ ⅄ ⅄

# የምትፈራውን ነገር እንዳያነሱብህ ከፈለግህ ሲመሻሽ ሄደህ ነገ እመጣለሁ ብለህ ተመለስ

ጦርነቱ ያበቃው ከመሸ በኋላ ስለነበር ለገሥ ወደ አስካለ ሲሄድ፣ ከፈለው ወደ ራስ ዘንድ ለመቅረብ ከዳኘው ጋር ከራስ አበበ ድንኳን ራቅ ብሎ ትንሽ ቆመና፣ የሚያበረታታውን ዳኘውን ተመለከተና፣ ከዚህ ከማይወደው ሁኔታ ያደረሰው ዳኘው ራሱ መሆኑን አስቦ፣ ዳኘውን በክፉ ዓይን አይቶት፣ ነቀል ነቀል እያለ ወደ ራስ ዘንድ አመራ።

የራስ አበበ ጦር ሳይታሰብ በድንገት የከፈለው ጦር ካለበት አካባቢ መድረሱን ከፈለው እንደሰማ የመጣለት ሃሣብ ቢቻል አፈግፍጎ ቦታ መቀየር ካልተቻለም ተዋግቶም ቢሆን ማፈግፈግ እንጂ ራስ አበበን ማስተናገድ አልነበረም። ዳኘው ግን በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ራስ አበበ ቂም ስለማይዙና ነገሩን ከማክበድ ማብረድ ስለሚሻል፣ እንኳን ደህና መጡ ብሎ ማስተናገድና፣ ጉዳዩንም ካነሱት የዚያን ጊዜ ባለመመቸት ለመገናኘት እንዳልተቻለ ገልጾ ጉዳዩን ግን በማግስቱ ለመወያየት በዘዴ አስተላልፎ በዚያኑ ጊዜ የራስን ሃሳብ ማሰለል እንደሚሻል አማክሮ፣ ከፈለውን ሃሳቡን አስቀየረው። ከፈለውም እያመነታ ተቀበለው።

ዛሬና ትላንት አንድ አይደሉም። ባላምባራስ የነበሩት ሰው ራስ ተብለዋል። የአርበኛውም ኃይል ከመሃከሉ ያሉ ራስ እሳቸው ብቻ ስለሆኑ አበበን ሳይጨምር ራስ ይላቸዋል። ስልጣናቸውም በሁሉም አካባቢ ተቀባይነት እያገኘ ሄዷል። ከፈለው በበኩሉ የአርበኛው መተባበርና መሪ ማግኘት ያስደስተዋል። ቢሆንም ራስ አበበ ጋር ከሹመታቸው በፊት ባጋጠመው ግጭት ቂም ያጠቁኛል ብሎ ስለፈራ ስልጣናቸውን ፊት ለፊት ሳይጋፋ በሩቅ ለመኖር ፈልጎ ነበር። ዳኘው ግን ሃሣቡን አስቀየረው። ራስ የዚያን ጊዜ በወቅቱ ከፈለው ወልደጻዲቅን ለመቅጣት ቢያስቡም ለጊዜው ግን ሌሎች አጣዳፊ ጉዳዮች ስለነበሩባቸው ከፈለውን ልክ ሳያሳዩ ቆይተው አሁን በአጋጣሚ ከፈለው ካለበት ቦታ ድረስ መጡ። ከፈለውም ትልቅ ድግስ አዘጋጅቶ ስላመጣላቸው ያለፈውን ነገር ቸል ብለው እንዳሉ ጦርነት እንደገና ተከፍቶ በድል አድራጊነት ተመለሱ። ከፈለው አሁን ነገ እንመለሳለን ብሎ ለመሰናበት ወደ ራስ አበበ ዘንድ ሲቀርብ ጉዳዩን ቢያነሱበት ካልፈለገው ሁኔታ ውስጥ መውደቁ ታሰበውና ዳኘውን በቁጣ ዓይን ተመልክቶት ወደ ራስ ዘንድ አመራ።

"ጌታዬ አረፍ በል!" አሉ ራስ አበበ በተለመደው ትህትናቸው የከፈለውን ጠባይ ለመገምገም ዓይናቸውን ከሱ ላይ ሳያነሱ።

"ነገ ተመልሰን እንመጣለን። አሁን ስለመሸ ሠፈራችን ለመሄድ ለመሰናበት ነው የመጣሁት ጌታዬ፣" አለ ከፈለው ለራስ በሚገባ አክብሮት። ይህን ዓረፍተ ነገር ለመናገር ብዙ የተጨነቀበትን ያህል አሁን ተናግሮ ከጨረሰው በኋላ እርካታ ተሰምቶት ፈገግ ብሎ።

"የሚነጋገሩት ጉዳይ አለ እኮ ጌታዬ፣" አለ የራስ ጋሻጃግሬ ወደ ጆሩዋቸው ጠጋ ብሎ። ከፈለው ለራስ አበበ ምን እንደሚላቸው ሰውየውን ስለሚጠላው ስለጠረጠረ በክፉ ዓይን አየው።

ራስ አበበም ጉዳዩን ስላልረሱት ማስታወስ አያስፈልጋቸውም ነበር። ለጊዜው በቀኑ ጦርነት ደክሞአቸው ስለነበር፣ ነገሩንም ከማክረር ይልቅ ቀስ ብሎ መያዝ እንደሚገባ አሰበው፣ ከፈለው ነገ የሚመለስ ከሆነ ችኮላ እንደማያስፈልግ አመዛዝነው፣ ወደ ከፈለው ዘወር አሉና "ይሁን እንግዲያው ሂድ። ልጅ ግዛቸው ኃይሌን ልኬበታለሁ። እናንተም ላኩበት። ነገ እንዳትቀሩ።" አሉ።

ከፈለው ራስን ተሰናብቶ በአስቸኳይ ከነሰዎቹ ወደ ቋቸ ሰፈሩ ወረደ። "ዳኘው ያ ዘመድህ ሌሊቱን እንዲልክብን አደራ ብለኸዋል?" አለ በመንገድ ላይ የጉዳዩ አሳሳቢነት ትዝ ብሎት።

"ይልክብናል። ልጨኛ ሰው ነው።" አለ ዳኘው የሰውዬው ቁምነገራምነት ትዝታ ልቡን አርክቶት ፀዳሉን እያበራው።

ልጨኛው ቁምነገረኛ ሰው ሲመጣ ግን ጥሩ ወሬ ይዞ አልመጣም። እንዲያውም ሌላ ተጨማሪ ከሳሽ በነከፈለው ላይ ተነስቷል።[44] ደጃዝማች ይፍሩ[45] የሚባሉ ሰው ከፈለው አገራቸው የባንዳ ሰፈር ነው በሚል ሰበብ እንደዘረፉቸውና አገሩ ግን ራስን ቀደም ሲልም በጥሩ ያስተናገደ መሆኑን አስታውሰው ከፈለው በእልህ እንጂ አመዛዝኖ እንዳለሠራ አሳምነው ራስም ነገ እነከፈለው ሲመጡ ስለ ተገኘ ቡሴራም፣ ስለ ደጃዝማችም ለመጠየቅ ወስነዋል። ከፈለው ይህን ሁኔታ ሲሰማ ከንፈሩን ጠመም አድርጎ "ሃ!ሃ!ሃሃ" ብሎ ሳቀ።

ዳኘው ከከፈለው አሳሳቅ አደገኛ አዝማሚያ ተመለከተና የላይኛውን ከንፈሩን እስከሪዙ በታችኛው ከንፈሩ ሸፍኖ ትንፋሹን ወደ ውስጥ ስቦ ከፈለውን አትኩሮ እየተመለከተ ትንሽ አስቦ "እርስ በርስ ጦርነት ብንከፍት ጥሩ አይሆንም። ጠብን ማብረድ ነው፣" አለ ለጠቡ ማብረጃ መንገድ አሁንም እየፈለገ።

"አንጣላም። ምን ቆርጦን፣ ምን ገዶን። እኛ ቦታውን ለቀንላቸው እንሄዳለን። ቢፈልጉ እንሱ ተከትለው ይውጉን፣" አለ ከፈለው እንደመሳቅ ብሎ ምሬቱ ግን ከፊቱ መጥቆር፣ ከግንባሩ መጨማደድ እየታየ። "ይልቁንስ ለጉዞ እንዘጋጅ። ወፍ ሳይንጫጫ በፊት ወደ ታች እንድንወርድ እንዘጋጅ፣" አለ ዳኘው እንቢ ካለ ሊቀር ስለሚችል ዳኘው ሃሳቡን እንዲሰጥ ዝም ብሎ እየጠበቀው። ዳኘው ሃሳቡን ሳይሰጥ ዝም አለ።

ለጡዋት ጉዞ ዝግጅት ተደርጎ ትንሽ እረፍት ለማድረግ ሁሉም ጋደም እንዳሉ ፋናዬ፣ ዳኘውና ታደሰን መጠየቅ ያዘች። "አስካለ እንዴት ነው?" አለች ወንዱ አንቺ ሴቱ አንተ ስለሚባል፣ ቀደም ሲል የጠየቀቻቸውን ጥያቄ አሁን ለሦስተኛ ጊዜ አንስታ። የሚወዱትን ሰው ወሬ አስር ጊዜ ቢሰሙት አይሰለችም።

"ደህና ናት አልኩሽ! ስንት ጊዜ ልንገርሽ?" አለ ታደሰ በማባበል ቁጣ ጀርባዋን፣ ዳሌዋን እያሻሸ ቀጭን ወገቡዋን ጨመቅ እያደረገ። "ደህና ናት ብየሻለሁ፣" አለ ግንባሩዋን እየሳመ ሰውነቱዋን ብቻ ሳይሆን መንፈሱዋ ከሱ ላይ እንዲያርፍ እየጓጓ። መልክ፣ ቁመና፣ ማን እንደ ፋና የሰጠው አለ። በዚህ ጨለማ ውስጥ ከእቅፉ ውስጥ ናት።

"ወደ ላይ ከፍ ብለህ እከከኝ፣" አለችው። እሱም ከወገቡዋ ወደ ትከሻዋ ሲወጣ የሱን የብራኩዋና ብራኩዋ መሃል ያለውን ጎድጓዳውን ቦታ እያሻሸች "እዚህ ጋ እከክልኝ፣" አለችው። "በጥፍርህ እንዳታደማኝ ዝም ብለህ አሻሽልኝ፣" አለችው "…… አዎ ቀስ

---

[44] በመጀመሪያው እትም መግቢያ እንደተጠቀሰው፣ የዚህ መጽሐፍ ትረካ የተመሠረተው በዘመኑ አርበኞች በሚለዋወጡዋቸው ደብዳቤዎችና ከባለታሪኮቹ ደራሲው በሰማውና ጠይቆ በተረዳው ላይ ነው። ለዚህ መጽሐፍ መሠረት የነበሩትን አንዳንድ ደብዳቤዎችን አቶ ገበየሁ ጣሰው "የአርበኝነት ዘመን ደብዳቤዎች" በሚል ርዕስ ለ62ኛው ዓመት የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር መታሰቢያ በተዘጋጀው መጽሔት ገጽ 14 እስከ 21 ጠቅሷቸዋል። ከነዚህ ደብዳቤዎች በተጨማሪ ከዚህ ያገኛሉ።
[45] ደጃዝማች ይፍሩ በአገሩ ባላባትና የተከበሩ ሰው ነበሩ።

ብለህ።....'' እንድትሰጠው ከሚፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ አንደኛው ይኸ ነው። ሌላው ምን ብሎ ሊገልጸው የማይችለው ብቻ ሲረካ የሚሰማው እሱዋነቱዋ ነው። አጥብቆ ያዛት። የማይጠግባት፣ የማይሰለቻት አንድ ነገር ናት። በቸርነቱዋ ታቀፈችለት። ተሰጠችው። ረካ።

''ዳኘው፣'' አለ። ዝምበል ለማለት ቆንጠጥ አደረገችው። በጭለማው ውስጥ የሠራቸው ሁሉ ይፋ እንደወጣ ያህል ፈርታ። ከዚያም አፉን ሊይዝ የሚሄደው እጁዋን ያዝ አድርጎ ''ፋናዬ ስለ አስካለ ስታወሩልኝ እደሩ ነው የምትል፣'' አለ።

''አስካለ አልከሳም?'' አለች ሐፍረቱዋ እንዳይታወቅ ጠንቀቅ ብላ። አንድ ጊዜ ከተናገረች በኋላ ተዝናናች።

''ምን ሆና ትከሳለች። ጥንት ነበር እንጂ አረሙ፣ አጨዳው፣ የማድቤት ሥራው፣ ውሀ መቅዳቱ የሚያጉላላት። ዛሬማ እንደ እመቤት በቅሎ ጭና፣ ቁጭ ብላ እየበላች፣ ሁሉ ነገር ሞልቶ ተርፎ፣ ምን ሆና ትከሳለች፣'' አለ ታደሰ በቀልድ እያሸመረ። ለፋናዬ አስካለ ድሮ እንደምታውቂያት አይደለችም። ከስታለች፣ ገርጥታለች ብሎ ለማለት ስላልደፈረ ''በጣም ጠንካራ ሆናለች፣'' ብሎ ነበር ቀደም ሲል የነገራት።

''ምን ታሾፋለህ?'' አለች ፋናዬ። ስለ ሃብታም ዘርነቱዋ በተዘዋዋሪ መንገድ በጨዋታ ሲያነሱላት ደስ ይላታል።

''ምን አሾፈ ብለሽ ነው ፋና፣'' አለ ዳኘው እሱም ለመቀለድ ፈልጎ። እስካሁን ድረስ የከፈለውንና የራስን ጠብ ሲያስብ ቆይቶ አሁን ተወት አድርጎታል። ''ዛሬማ አንችም ታደሰን የመሰለ የሃብታም ዘር፣ ሃብታም፣ አግብተሽ፣'' አለና ሳቀ። ታደሰ በአርበኝነቱ ዘመን በጎበዝ እልቅናው የተፈራ፣ በሕብረተሰቡ ክብሩ ከፍ ያለ እንጂ የሃብታም ዘር አልነበርም።[46] እንደ ድሮው ቢሆን ፋናዬን ለማግባት ቀርቶ አያልመውም ነበር። ሁሉም ሳቁ። ''አንድ ጊዜ የሆንኩትን ላጫውታችሁ፣'' አለ ዳኘው ያን ያለፈ ትዕይንት በጨለማው ውስጥ ዓይኑን ከጣራው ተክሎ ሲመለከተው ይበልጥ ጎልቶ እየተመለከተው። ''እንዳሁኑ ዘመን ሳይሆን የዚያን ጊዜ አንድ ቀን ወደ ሰላድንጋይ ለመውጣት በንብዋሻ በኩል ሳልፍ ፋናዬና አስካለ በበቅሎ ላይ ሆነው እየተምነሸነሹ ከፊለፊቴ ሲመጡ አየሁና የቀኛዝማችን የልጅ ልጆች እጅ ብነሳ አስካለ ለትህትናው ሰላም ስትለኝ ወይዘሮ ፋናዬ ዝም ብለውኝ አለፉ፣'' አለና ፋናዬ

[46] በአርበኝነቱ ዘመን የተደረገውን የመደብ መሸጋሸግ ቀኛዝማች ኃይሌ ባልቻ ለልጅ ከፈለው ግንቦት 13 ቀን 1930 ዓም በጻፉት ደብዳቤ ይታያል። ''አርጋው .... ጥንት ኮርተኸብኛል ብሎ እከፍተኛ ደረጃ ላይ የነበሩትን ባላባቶች ሁሉ ለጊዜው ሐይለኛ ሰለሆነ በስቃይ ብድር መመለስ አልነበረም። ይኸን ሁሉ ያልተማረ ሰው አያውቀውምና ስለዚህ ይሆናል። በጊዜው መዘዋወር ማዘኑን ትቶ የግፍ ግፍ መሥራቱና ራሱ የሠራ አንሶት ደህና ሰው መስሎ ወደ አንተ ዘንድ መጥቶ በደለኛ መምሰሉና አንተን ወንድማችንን ብዙ የምታውቀውን እኛን ሕብር አርገህ አንድነትን ሃይል አድርገን እርስ በርሳችን እየተጣላን ለጠላት ደስ ማሰኘትን ትተን እጥቂ ጠላታችንን እኛው እየተማከርን እንድንሠራ ግን ይህን ሁሉ መጻፈነገሩን ተረድተህ እንድታመዛዝነውና እንደተጻጻትህ በጻፍክልኝ ድብዳቤ ላይ ተረዳሁት። አንተም ነገሩን አሻሽለህ በጣሙን እንድትረዳው በማክበር እለምንሃለሁ።.......''

ሁሉንም ወንድ ስታይ ፍዝዝ ብላ የምትመለከተውን ለማውራት ዳድቶ አፍሮ፣ ጉዳዩም በመጥፎ እንዳይተረጎምበት ሰግቶ፣ ትንሽ ሲያስብ ዝም ብሎ ቆየና "ይኸውልህ ዛሬ እኔና ፋና በአንድ ቤት ውስጥ እኩል ተቀምጠን ታደሰም የፋናን ወገብ ለማቀፍ በቃህ አለ፣" አለ።

"ውሸቱን ነው ዳኘው፣" አለች ፋናዬ። "በመንገድም ተያይተን አናውቅም።"

"ድሮስ ሃብታም መቸ ሁሉ ሰው በዓይኑ ሞልቶ ይታየዋል። መርሳት የጌትነት ነው፣" አለ ዳኘው እየሳቀ።

"በሉ ትንሽ አረፍ እንበልና እነተኛ። በሌሊት ተጓዥ ነን፣" አለ ታደሰ የነገው ጉዞዋቸው ትዝ ብሎት። "ከራስ ጋር ያለን ጉዳይ እንዴት ያልቅ ይመስልሃል?" አለ። ዳኘው እስካሁን ዝም ያለው ከከፈለው ጋር አብሮ ለመሄድ በመወሰኑ ነው ብሎ በማመን። ሁሉም ሰው በተገኝ ቡሴይራና በደጃዝማቹ ጉዳይ አብሮ የመከረና የተሳተፈ ነው።

"እኛን ሲከተሉ አይኖሩም። ትንሽ ቆይተው ወደ ቡልጋቸው ይመለሳሉ፣" አለና ዳኘው አንድ ጊዜ አዛግቶ ወደ እንቅልፍ ዓለም ተሻገረ። የከፈለው አዝማሚያ ደስ ባይለውም፣ ከከፈለው ቢለየው ከፈለው ሳይወድ ጦርነት ይከፍታል ብሎ ፈርቱዋል። ስለዚህ አብሮት ለመሄድ ወስኑዋል። ታደሰም፣ "ይሁን እስቲ፣" ብሎ ተገላበጠና እንቅልፍ እንዲወስደው ራሱን ማባበል ያዘ።

በማግስቱ እነከፈለው ቋች ደርሰው እረፍት እንዳደርጉ የመንዝ ሌሎች አርበኞችና ዋናው አስተባባሪ ግዛቸው ኃይሌ ከራስ አበበ ጋር ተገናኙ። ራስም እንግዶቹን ሲቀበሉ በዓይናቸው ቢቃኙ ከፈለውን ስላጡት በመጠራጠር "ልጅ ከፈለውስ? አልመጣም? እመጣለሁ ብሎ አልነበር?" አሉ ወደ ጋሻጃግሬአቸው ዘወር ብለው።

"አይ ጌታዬ የምትፈራውን ነገር እነዳያነሱብህ ከፈለግህ ሲመሻሽ ሄደህ ነገ እመጣለሁ ብለህ ተመለስ እንደሚባለው ሆኖ ነው፣" አለ ጋሻጃግሬው አንድ የሚያውቀውና ያልተናገረው ነገር መኖሩ ከድምጹና ከፊቱ ግልጽ ሆኖ እየታየ።

"ምነው ምን እንዲህ አሳሰበህ?" አሉ ራስ ጋሻጃግሬው ለአቤቱታ ለመጡት ዘመዱና ለተገኝ ቡሴይራ ጥብቅና ልቁም በማለት ሥልጣናቸውን እንዳይጋፋ ኮስተር ብለው፣ በተጨማሪ ግን ሊናገረው የሚፈልገው ነገር ካለ እንዲናገረው ለማድረግ።

"ልጅ ከፈለው ወደ ቋች ቆላው ሌሊቱን ወርደዋል አሉ፣" አለ ራስ እንደሚናደዱ በማወቁ ደስ ብሎት ደስታው እንዳይታይበት ፊቱን እያቀረቀረ።

"ለምን?" አሉ ራስ በመገረምና የነገሩን ሁኔታ ለማጤን ግምባራቸውን ኮስተር አድርገው ራሳቸው በራሳቸው መልስ ለማግኘት እየተጣጣሩ። "ወይ ከፈለው፣" ሲሉ አሰቡ። "ምን ልሁን ነው የሚለው?" አሉና ሁሉም ነገር ተምታቶባቸው ሃሳባቸው ባዶ ሆነ። ከዚያም ከከፈለው ጋር በተገናኙባቸው ቀናት ሁሉ ከከፈለው ግንባርና አነጋገር ላይ የንቀት ነገር ተመለከቱ። "የዚያን እለትም ተሳስቼ ተደስትኩለት እንጂ ወደ ግንደበረት

ከመውረዳችን በፊት ግዳዩን ሲጥል፣ ከፊቴ ሲፎክር፣ አክብሮኝ ሳይሆን ለማሾፍ ነበር፣” ሲሉ አሰቡና የከፈለው አሽሟጣጭ ፊትና የቆከራው እያነዳነዳቸው ቃላት አሽሙር ሆነው ታዩዋቸው። ወዲያው ደግሞ አንድ ቀን አግኝተውት የነበረው ጊዜ ትዝ አላቸው። በእርግጥም ልባዊ ፍቅርና አክብሮት አዩ። ወዲያው ግን ይኸኛውም ንቀትና አሽሙር ሆኖ ታያቸው። “ለመሆኑ እሱ ከማን ይበልጣል? ሌሎች የመንዝ አርበኞች፣ ሌላው ቀርቶ ግዛቸው ኃይሌ፣ ከፊቴ አለ አይደለሞይ? ....ይህን ያህል የምናቅ ነኝ?” ሲሉ አሰቡና ከፈለውን ምን እንደበደሉት ቢያወጡ ቢያወርዱ አንድም ምክንያት አጡለት። “ሰው ከሶሃል፣ መልስ ስጥ ማለትስ እንዲህ ያደርጋል?.......ሰው መናቁ ነው፣” አሉ። “ጥንትስ በነፃነት ጊዜም ቢሆን የበላይ ነኝ። በስሬ ወታደር ባይሆንም ያው የበላዩ ነኝ። .... በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ሆነን የዚህ ዓይነት ነገር የሚፈጽም አይረባም። ....... አሳየዋለሁ፣” ሲሉ ደመደሙና በረጅሙ ተነፈሱ።

“አሁንም በዝምታ ካለፍነው ምሳሌነቱ መጥፎ ነው፣” አለ ጋሻጃግሬው ከራስ ግንባር ላይ ስለከፈለው የደረሱበትን ውሣኔ አንብቦ። አብሮ መኖር የሰውን ፍላጎትና ስሜት ሳይናገር በፊት ለመለካት ያስችላል። በጭንቀትና ጥበት ጊዜ የስሜት ማንበብ ኃይል በጣም ይዳብራል።

“ይሁን። ጌታዬ ብዙ አታስብ። እሱ ካልመጣ እኛ ሄደን እንገናኘዋለን፣” አሉ ራስ ትህትናቸው ንዴታቸውን አልብሶት የታመቀው እልህ ግን ሰውነታቸውን ዛል አድርጎት።

⅄ ⅄ ⅄

# ይህንንስ ጠላት አይስማው

የራስ አበበ ጦር የከፈለውን ጦር ለመውጋት ማሰቡ ቋቾ ቆላው እንደተሰማ ከሁሉ ይበልጥ የተሸበረውና የተጨነቀው ዳኘው ነበር። ለከፈለው ግን የሚያስጨንቅ አልሆነበትም። “የአበበ ጦር ከጣሊያን ጦር አይበልጥም። ትዕቢት ነው። ምን አጠፋሁ። እርስ በርሳችን ከምንዋጋ ብዬ ሸሸሁ፣” አለ ከፈለው ወሬውን ማታውኑ ሰምቶት በበነገታው ጡዋት።

ከፈለው ወሬውን ከሰማ በኋላ ሌሊቱን ሙሉ ሲናደድ ነበር ያደረው። ንዴቱ በረድ ሲል ስለ ጉዳዩ ሲያስብበት የሱ ሥራ ትክክል፣ የአበበ ሥራ ግን ለጣሊያን ባንዳዎች መደገፍ እንደሆነ አመነበት። “የማንም ባንዳ የጠላትን ጦር ሲመግብ ዝም ብዬ አላይም። ደግሞም ከባንዳና ከባንዳ ቀላቢ ጋር ጎን ለጎን ቆሜ አልሟገትም፣” ሲል አሰበ። ደጃዝማቹ ለራስ አበበ ያቀረቡት አቤቱታ ትዝ ብሎት። “ተገኝ ቡሴይራም ቢሆን ባንዳ ነው። መትረየስ ይዞ

የተቀመጠው ለጣሊያን ሊያስረክበው ካልሆነ አይዋጋበትም፣” አለ ነገሩን ይበልጥ በቁጭት ሲያብሰለስለው ይበልጥ የሱን ሃሳብ የሚያጠናክሩ ብዙ የመከራከሪያ ነጥቦች እያገኘ ሄደ። “አበበ የሚለው፣” ሲል አሰበ አንቱታውን ትቶት “ሰውዬው የኔ የውስጥ አርበኛ መሆኑን እየነገረህ፣ ደግሞም ከሱ ጋር መጣላት የአገሩን ሰው ማስቀየም ነው። ዘመደ ብዙ ነው። ነው የሚል የኛ ዘመደ ብዙ ፈሪ የታባቱ፣” አለ በሃሳቡ ተገኝ ቡሴይራ እየታየው። “ምናባቱ እሱ ንጉሥ መሆኑ ነው። መንግሥት ፈርሷል፣ ያለው የጣሊያን መንግሥት ነው። እሱን በየፊናችን እንዋጋለን። አሳየዋለሁ፣” እያለ አሰበና መች እንደሆን ሳያውቀው እንቅልፍ ይዞት ሄደ።

ጡዋት ከዳኘው ጋር ሲገናኝ ከፈለው የተናገረው ይህንኑ ነበር።

“ጠላት እርስ በርሳችን መጣላታችንን ካወቀ ያጠቃናል። ለአገራችን፣ ለነፃነታችን የምናፈሰውን ደም በከንቱ ለጣሊያን መንግሥት እንደማፍሰስ ያህል ነው፣” አለ ዳኘው በአንድ በኩል ከፈለው ተናድዶ በኋላ ለምክርም እንዳያስቸግር በመፍራት፣ በሌላ በኩል በሃሳቡ እንዲገፋበት ላለማደፋፈር በታሰበ የጥንቃቄ አባባል።

“ዳኘው አንተ አብረኸኝ ለመሆን ካልፈለግህ ሰዎችህን ይዘህ ለመሄድ ትችላለህ፣ እኔ እወጣዋለሁ፣” አለ ከፈለው ቆራጥነት በተመላበት ሁኔታ።

“እንደዚያ ማለቴ አይደለም። ሁሉንም እርምጃዎች የወሰድነው ወንድም አርበኞቻችን ጋር አብረን ተወያይተንበት፣ ተስማምተንበት ነው። ነገሩ እኛ ጥፋተኞች ነን ለማለት ሳይሆን በስምምነት የሚያልቅበትን መንገድ መፈለግ አለብን ማለቴ ነው።”

“ለክፋት ሲያስቡን እንጂ እኔ ጦሩን ወክዬ ከነዚያ ሰዎች ጋር ጎን ለጎን ቆሜ እንድፋረድ ከማድረግ ይልቅ በግል ልንነጋገርበት እንችል ነበር።” አለ ከፈለው ራስ አበበ ሰውን ለማዋረድ የታጠቁ ናቸው የሚለው እምነቱ ጎልቶ እየታዬ።

ዳኘው፣ የራስ አበበ አሠራር ተበዳይ ነን የሚሉትን ሰዎች ለማረጋጋትና ስልፋቸውን ከጣሊያን ጋር እንዳያደርጉ ለማግባባት በሚል ዘይቤ መሆኑ ተሰምቶት እንዴት ሊያስቀምጠው እንደሚችል ሲያስብ፣ ከሩቅ የልጅ ግዛቸው ኃይሌ ባልደረባ ሲመጣ አንድ ተስፋ ታይቶት፣ “የልጅ ግዛቸው ሰው መጣ፣” አለ፣ ደስታው ከፊቱ ላይ እየተነበበ።

“ምን ሊሉ ይሆን?” አለ ከፈለው “እኔ እርዱኝ አላልኩ። ሰው ምን አስጨነቀው።” አለ ቅር ብሎት።[47]

---

[47] በዚህ ወቅት ጉዳዩ ወደ ግጭት እንዳያመራ ከልጅ ግዛቸው ሌላ ደብዳቤ የጻፉ ደጃዝማች አውራሪስ ናቸው። ደብዳቤያቸው ስለ አገር ፍቅር፣ ተስማምቶ የመሥራትን ጥቅም በሰፊው የሚያትትና አስተማሪነት ያለው ነው።

ከመልዕክተኛው ደብዳቤውን ተቀብሎ ሲያነበው በውስጡ ስለ ጠቡ በቀጥታ ባያወራም ሁለቱ እንዲገናኙ የሚጠይቀውና ከፈለው ግዛቸው ካለበት ሰጋጥ ድረስ መጥቶ ሰለ ሁኔታው እንዲወያዩ የሚጠይቅ ሲሆን በተዘዋዋሪም በልጅ ግዛቸው በመንዝ፣ ይፋትና ተጉለት አርበኞች አስተባባሪ በኩል ከፈለውን በማያስከፋ መንገድ መፍትሄ ሊገኝለት እንደሚችል የሚጠቁም ነው። ሆኖም ግን ልጅ ግዛቸው ዘንድ ከሄደ በኋላ ልጅ ግዛቸው ባለበትም ከራስ አበበ ጋር ሲገናኝ፣ ከሳሾቹም እዚያው እንደሚኖሩ በማወቁ፣ ለመልዕክተኛው ሰላምታውን ለልጅ ግዛቸውና ለሌሎች ወንድሞቹ እንዲያቀርብለት ጠይቆ እሱ ግን ሌላ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር አሁን እነደማይመጣ ገለጸ።

“ባይሆን እኔ ልሂድና ልጅ ግዛቸው በወረቀቱ ላይ ያልገለጹትን ሃሳብ ልስማውና በኋላ እንወያይበታለን። ልጅ ግዛቸው የኛን ክብር የሚነካ አያደርጉም፣ ለራሳቸውም ቢሆን ውርደት ነው፣” አለ ዳኘው።

“ትችላለህ ለመሄድ፣” አለ ከፈለው “ተነሱ ተከተሉት!” አለ የዳኘውን ወታደሮች እየተመለከተ።

“አይደለም። ሦስት ሰዎች ይበቁኛል። ሌሎቹ እዚሁ ይቆዩ። በዛሬው አዳር እመለሳለሁ፣” አለ ዳኘው ወታደሮቹን ጥሎ ከሄደ ከፈለው ጥርጣሬ አድሮበት ሳይመለስ በፊት ጠብ ከማንሳት ይቆጠባል ብሎ በማሰብ።

“እንደ ፈለግህ፣” አለ ከፈለው ለጦርነት የተነሳሳው ስሜቱ ከፊቱ እየተነበበ።

ዳኘው ሦስት ሰዎች ይዞ ተጣድፎ ተዘጋጅቶ ጉዞውን ቀጠለ። የልጅ

ግዛቸው መልዕክተኛ ግን እረፍት ለማድረግ ከዚያው ቆየ።

ዳኘው ወደ ተራራው አፋፍ የምታመራዋን መንገድ እንደያዘ እረጅም ቤልጅግ ጠበንጃውን ከእቅፉ ወደ ትከሻው አወጣና በማጅራቱ በኩል አሳልፎ በቀኝ እጁ ከሰደፉ በኩል፣ በግራ እጁ ከአፈ ሙዙ በኩል፣ ይዞ መራመድ ቀጠለ።

በሜዳ ላይ ሲሆን ወይም አቀበት ሲወጣ ጠመንጃውን እንደዚህ ይዞ መሄድ ይወዳል። ድሮም ዱላ በሚይዝበት ጊዜ እንደዚሁ ነበር። ይህ ዓይነቱ የዱላ ወይም የጠመንጃ አያያዝ ከወገቡ ወደ ኋላ ሰበቅ፣ አንገቱን ቀና አድርጎ ሩቁን አድማስ እያየ እንዲሄድ ያደርገዋል። እንደ አድማሱ ጥልቀት ሁሉ የሱም ዓይን ጠልቆ የማይጨርሰው አድማስ ውስጥ ይወረወርና ሃሳቡ ሁሉ ይረጋጋል። ብስጭትም፣ ሃሳብም ይጠፉና ባዶነት ሳይሆን ተመስጦ ልቡን ይሰልበዋል። ይኸኛው ተመስጦ ግን ሙሉነት፣ ከዓለሙ ጋር አንድ መሆን ነው።

ዳኘው እንደዚህ ተመስጦ ሲሄድ ከኋላው በኩል የሚነፍሰው ነፋስ የሎሚ ፀጉር ጐፈሬውን ከኋላው ገፍቶ በግንባሩ ላይ ጣለውና ዓይኑን ሲሸፍነው ከተመስጦው ቀሰቀሰው።

“አዬ የጋሼ ጐፈሬ፣” አሉ ሦስቱም አብረውት የሚሄዱት ሰዎች የነሱን የከረደደ ፀጉር ጐፈሬ ለነፋሱ የቋቋሚነት ለማሳየት ራሳቸውን እየዳበሱ።

“ሹርባ እሠራዋለሁ እንደ አይሌ፣” አለ ዳኘው።

“እንደ ሴት?” አለ አንደኛው በቀልድ፣ አክብሮት ግን ከድምጹ እየተነበበ።

“አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ ሹርባ ነበሩ። ጐፈሬ ለአንት ዓይነቱ ችፍርግ ፀጉር ነው። ዞማ ፀጉር አርበኛ ባለሹርባ ነው።” አለ ቀደም ሲል ለብቻው የምር ያሰበበትን ሁኔታ አሁን እንደ ቀልድ አምጥቶት። አርበኞች በሙሉ ፀጉራቸውን ስለሚያጐፍሩ ሉጫ ፀጉር ያላቸው በተኩስ ላይ ከፊታቸው እየተደፋ ስላስቸገራቸው አንዳንዶቹ ሹሩባ መሠራት ጀምረዋል። ዳኘው መሃከለኛ ቁመቱ ላይ የተጨማደደ ካኪ ሱሪውና ቀጭን ጠንካራ

የሆኑት እግሮቹ ላይ ያሰረው ጥቁር ገንባሌ የሚስማማው ሲሆን ሉጫ ጐፈሬ ፀጉሩ ግን በግራም፣ በቀኝም፣ በኋላም ተዘናፍሎ ወድቆ ጃንጥላ ያያዘ ያስመስለዋል። ትከሻው ሰፊ ባይሆን ኑሮ ልዩ መልክ ይሰጠው ነበር። ሰፊና ጐበጥ ያለ ትከሻው ግን ዋጥ አድርጐ ይይዘዋል።

“ስለ ፀጉራችን እንተወውና ይልቁንስ የምንሄድበት ጉዳይ ይቅናን እንበል፣” አለ ዳኘው ፀጉሩን ወደ ኋላው መልሶ ቁልቁለቱን ሲያያዝ ጠመንጃውውን ከትከሻው አውርዶ በማንገቻው አፈሙዙን ወደ ላይ አድርጐ በቀኝ ትከሻው አንጠልጥሎ።

“ምን ይቀናናል ብለህ ጋሼ፣” አለ ጋሻጃግሬው። “ፈርተነዎታል ብለን ብንሸሻቸው ተከትለውን እየመጡ። ሰው ፈራሁህ ሲሉት ይበቃኛል ብሎ ካልተመለሰ ሰው አይደለም። ” አለ።

“አስተዳደር፣ ፖለቲካ የሚሉት ነገር አለ፣” አለ ዳኘው ጥንት ክብር ዘበኛ ሳለ በቤተ መንግሥት አካባቢ የሚሰማውን ቃል ሲናገረው ቃሉ ከባድ መሆኑን ለማሳየት የቀኝ እጁን ወደ ላይ አጥፎ በእጁ አንድ ነገር እንደሚመዝን ላይና ታች እያደረገ።

“ራስ አበበ ነጋሪት ተመትቶ በአገራችን ላይ የሁላችን አስተዳዳሪ አልተባሉ።” አለ ሌላው።

“ንጉሥ በአገራችን ሳይኖር በአርበኝነት ስንሠማራ እንደ ኃይላችን መጠን በመፈቃቀድ መሿሿማችን ነው።” አለ ዳኘው የነፃነቱ ተጋድሎ ክብደት ተሰምቶት ሃዘን ድምጹን ሰብሮት። ሁሉም ሁኔታው ተሰምቶአቸው ዝም አሉ። “ደግሞም ራስ ብለው መልአከ ፀሐይ ሾመዋቸዋል፣” አለ ሰሞኑን ሰው ሁሉ በንዴት ማንነታቸውን መርሳቱ እያስገረመው።

ዳኘው ከግዛቸው ኃይሌ ዘንድ እንደቀረበ ስለሁኔታው አስረዳ። ልጅ ግዛቸውም ሁኔታውን ካዳመጠ በኋላ “ለከፈለው ደብዳቤ እጽፍለታለሁ። አንተ በቃልህ አስረዳው። ጦርነት ቢነሳ ሰው የሚፈርደው በሱ ነው። እኔም እቀየመዋለሁ። ቢሆን ይምጣና አብረን ራስ ዘንድ እንቀርባለን። ካለዚያ ጦርነት ከመከፈት አሁንም ያፈግፍግ። በመሃከሉ መፍትሄ እንፈልግለታለን። ይህንን ማለቴን አስረዳው። አንተም አግባባው።” አለ።

“ይህንንስ ጠላት አይስማው።” ሲል ቀስ ብሎ ተናገረ። ዳኘው ትንሽ አርፎ ምሳ ከበላ በኋላ ተመልሶ ወደ ከፈለው ዘንደ አመራ። ከፈለው የልጅ ግዛቸውን ደብዳቤ ሲያነብ “ባንተ የምለውጠው ሰው እንደሌለ እግዚአብሔርና እኔ ነን የምናውቀው።”[48] የሚለው ዓረፍተ ነገር ልቡን በላው። ከግዛቸው ጋር በተሰለፈባቸው ጦር ሜዳዎች ግድያውን ጥሎ በግዛቸው ፊት ሲፎክር ግዛቸው የሚሰማው ደስታ፣ ግዛቸው ከሁሉም ሰው ይበልጥ ጀግንነቱን እንደሚያደንቅለት ሲሰማው ልቡ ተለሳለሰ። “አንተ

የማትመጣ ከሆነ ግን ለኔ ቦታ ቆርጠህ ንገረኝና መጥቼ አገኝሃለሁ፣” ብሎ ለጻፈለት ግን መልስ ለመስጠት አልፈለገም። ግዛቸው ጋር ፊት ለፊት ቁጭ ብለው እንደ ወንድም የሚለምነውን ነገር እንቢ ለማለት አይችልም። ዳኘው በከፈለው ሆድ ውስጥ የሚብላላው ነገር ተሰማውና “በደብዳቤ ሁሉንም ነገር ለመግለጽ አልቻሉም። በቶሎ የማንገናኝ ከሆነ ሌላው ቢቀር አፈግፍጉ ብለዋል። አደራ ብለዋል፣” አለ።

“ብናፈገፍግ አይከተሉንም?” አለ ከፈለው። ጥያቄና አውቀህ ትቀልዳለህ ወይ የሚል አባባል ነበር።

“አፈግፍገን ከሰላድንጋይ ባሻገር እንሄዳለን። ካስፈለገ ሰላድንጋይ ወጥተን ጣሊያንን እንወጋለን። ከፈለጉ ጣሊያንን ስንወጋ መጥተው ይውጉን። ሰው በኛ አይፈርድም፣” አለ ዳኘው። ይህ ከችግሩ መውጫ መንገድ ይከፍታል ብሎ በማሰብ።

“ይሁን፣” አለ ከፈለው ተከትለውት ሲመጡ መዋጋቱ ካልቀረ በሰው አስፈርዶ ለመዋጋት። “ተነሱ ወደ ሞፈር ውሀ እንውረድ፣” አለ ከፈለው በመነጽር የራስ አበበን ጦር እያየ። ጦሩ ለዕረፍት ሰፈራ አድርጓል። ለጠበንጃ ተኩስ ግን ሁለቱም ጦሮች የተራራቁ ናቸው።

የራስ አበበ ጦር የከፈለው ጦር መንቃነቁን ሲያይ በፍጥነት ተሰባስቦ መከተሉን ያዘ። የከፈለው ጦር ቆላውን ወጥቶ ከተራራው አገር ወደ ሞፈር ውሀ ሲወርድ ባሻገሩ ተራራ ላይ ካለው ከሰላድንጋይ ከተማ የመሸገው የጣሊያን ጦር ቃፊር በመነጽር ተመልክቶት ማስጠንቀቂያ ሰጠ።

ከጣሊያን ካምፕ ውስጥ የጦርነት ዝግጅት ጥድፊያ መደረግ ተጀመረ። ኢጣሊያዊ አዛዥ ከበቅሎ ላይ ወጥቶ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ትዕዛዝ መስጠቱን ቀጠለ። በካምፑ ውስጥ ያሉ መድፎች አፈሙዛቸውን በሙሉ ወደ ሞፈር ውሀ መውጫ ጐዳና አቀኑ። እግረኛው ጦር በየክፍሉ እየተሰለፈ ጥይት እየተቀበለ ነው።

[48] የልጅ ግዛቸው ኃይሌ የታህሣስ 27 ቀን 1931 ዓም ለልጅ ከፈለው የተጻፈ ደብዳቤ።

ከብዙ ትርምስ፣ ከሁለት ሰዓት በኋላ፣ የጣሊያን ጦር ከካምፑ ተሰልፎ ሲወጣ ወደ ወንዙ ከገባው ጦር ሌላ ብዛቱ ከፍ ያለ ጦር ከተራራው ላይ ታየ። የዚያን ጊዜ ኢጣሊያዊው አዛዥ በቅሎውን ወደ ኋላ መልሶ የዕርዳታ ጥያቄ ቴሌግራም ለማስተላለፍ ወደ ቢሮው ተመለሰ።

# እንዴ!

ራስ አበበ የከፈለውን ጦር እንቅስቃሴ በመነጽራቸው እየተመለከቱ ብዙ ሀሳብ በአእምሮአቸው ተተራመሰና በመገረም «እንዴ! እንዴ! ከፈለው ከጣሊያን ሊደባለቅ ነው? » አሉ። ለማንም መናገራቸው ሳይሆን ያላሰቡትና ያላለሙት ጉዳይ አጋጥሞአቸው በመደነቅ።

«ጌታዬ፣ ከሰላድንጋይ የኢጣሊያ ጦር ወደ ከፈለው እየተጠጋ ነው። ሊቀበሉት ወዲያም ከኛ ሊከላከሉለት ነው።» አለ አንድ የጦር አዛዥ በመነጽሩ አሻግሮ እየተመለከተ። ራስ ይህን ተመልክተዋል ብሎ አላሰበም።

ራስ አበበ መልስ አልሰጡም ። ከፈለው አፈንጋጭነቱን እንዲተው ለማድረግ እንጂ ከጠላት ወገን ገብቶ ጠላትን እንዲያጠናክር ለመግፋት ሃሳብ አልነበራቸውም ። ከፈለው ግን ጠላት ጋር ከሚደባለቅ ከዚሁ በአስቸኳይ ፍፃሜውን ማሳየቱ ይመረጣል። በምንም ሁኔታ ቆላውን አልፎ ወደ ግምጫ ማስጫ መውጣትና ከዚያም አቆልቁሎ ወርዶ የራስን ጦር ለኢጣሊያ መድፍ መዳረግ የለበትም። «እነ ደምሴ ወልደ አማኑኤል ከኔ ጋር አብራችሁ ትወርዳላችሁ፣ ሌሎቻችሁ በሩጫም ቢሆን ድረሱበት!" አሉ ራስ አበበ ሰው ሲናደዱና እልህ ሲይዛቸው አይቶት በማያውቀው ቅላፄና ገጽታ።

የራስ አበበ የጦር አዛገች ከነጭፍሮቻቸው በመንደርደር ከአፋፉ ወደ ታች መውረድ ያዙ። ሁሉም እልህ ይዙዋቸዋል። ጠላትን እስካሁን በአከባቢው ገትሮ የያዘውና ተሸንፎ የማያውቀው የከፈለው ኃይል ወደ ጠላት መግባት፣ የአርበኞችን እንቅስቃሴና የመንዝን መውጫና መግቢያ የሚያውቀው የትላንት አጋራቸው መከዳት፣ በነሱ ላይ የሚያስከትለው አደጋ በግልፅ ታይቶአቸዋል። ቀደም ሲልም ከሁለት ዓመታት በፊት ጣሊያን ሞፈር ውሃን ተሻግሮ መንዝን ያቃጠለው በአንዳንድ የአገር ተወላጅ ከሃዲዎች መንገድ መሪነትና ሰላይነት ነው። ከጠላት ጋር መዋጋት መጀመሪያ ከመሃል ያለን አሾህ መንጥሮ ነው። ከፈለውም በመነጽር የራስ አበበ ጦር ወደሱ ሲያመራ ያየው ይህንኑ ነበር።

ጦራቸው በአፋጣኝ ቁልቁል እየተንደረደረ ሲወርድ ራስ አበበ ተክዘው ሲመለከቱ ደምሴ ወልዴ አማኑኤል ሃሳቡን ለማቅረብ አመቺ ወቅት በመጠበቅ ከጎናቸው ቁሞአል።

አላዩትም። በራስ አበበ ሥር ካሉት በነፃነት ዘመን ወደ ፈረንጅ አገር ሄደው ተምረው ወይም በአዲስ አበባ ዘመናዊ ት/ቤቶች ገብተው ተምረው የነበሩ፣ ከመላው የኢትዮጵ ክፍሎች የተሰባሰቡ ምሁራን፣ ጠላት አዲስ አበባ ከመግባቱ በፊት ከራስ አበበ ጋር ወደ ገጠር የገቡት ምሁራን፣ ስለተፈጠረው ችግር ሲወያዩበት ነበር ። በዚህ ጨለማ ወቅት ድርጅት የመፍጠሩ ጉዳይና መሪ የማፍለቁ ነገር አዳጋች እንደሚሆን ከብደቱ ሁልጊዜም ይሰማቸዋል ። ቡልጋ ላይ መልአከ ፀሐይ እያሱንና ራስ አበበን ከፍ ሲያደርጉ ሁሉ በመካከላቸው ትልቅ ንትርክ የፈጠረው ጉዳይ ይኸው መሪ የማፍለቁ ጉዳይ ከባድነት ነበር።

“ባላምባራስ አበበን ጠቅላይ አዛዥ አድርገን ይፋ ቢወጣ፣ ሌሎች የአርበኞች መሪዎች ይቀበላሉ? በፈረንሳይ ሪቮሊሲዮን፣ በሌሎችም ሪቮሊሲዮኖች እንደታየው ተፎካካሪ ቡድኖች እስካሉ ድረስ አንደኛው ሰው አሸንፎ መሪ እስኪሆን ድረስ ብዙ የርስ በርስ መተላለቅ ይሆናል ። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ባገራችን ቢፈጠር ደግሞ ለጣሊያኖች በጣም ይረዳቸዋል። ይልቁንስ እንደ አሁኑ ዝም ብሎ ካለ ድርጅት በመተሳሰብ መረዳዳቱ ይሻላል። ” የሚሉ ብዙ ምሁራን ነበሩ።

“አይደለም።” ይል ነበር ሌላው ክፍል “በአሁኑ ጊዜ እንደ እኛ ጦር፣ እንደ ባላምባራስ አበበ አረጋይ ኃይለኛ የለም ። አንዳንዶች ቢያፈነግጡም መቆጣጠር ይቻላል። ጦርነት አይገጥሙንም ። ከዚያም በዚሁ አከባቢ ያሉት በሙሉ ከተባረሩ የጎጃም፣ የወሎ፣ የትግሬ፣ የወለጋ፣ የጂማ በአጠቃላይ የሌሎችንም ቀስ በቀስ ማስተባበር ይቻላል ። በዚህ ላይ መልአከ ፀሐይ እያሱን ማንገሱ ወሎን ሲያስተባብር፣ ባላምባራስ አበበም በትውልዳቸው ከአማራውም ከኦሮሞውም[49] ድጋፍ የሚያስገኙ ናቸው ።” በመሃከላቸው ማንም ሰው ጉዳዩ ቀላል ነው ብሎ የገመተ አልነበረም ። ሁሉም የተጨነቁት ይህንን ዓላማ ለማሳካት በሚጠየቀው፣ በሚከፈለው መስዋዕትነት ነበር። ሌሊቱን ሙሉ ተከራክረውበት ሊነጋጋ ሲል ነበር ከስምምነት የደረሱት። እያንዳንዱን የአርበኛ መሪ በተናጠል ለዚህ ዓይነቱ ሃሳብ የሚኖረው ተቀባይነትና ተቃውሞን ተንትነው፣ አብዛኛው ደጋፊ እንደሚሆን ከተማመኑ በኋላ ነበር ስምምነት ላይ የደረሱት። ስለ ከፈለው ወልደ ፃዲቅ በሚወያዩበት ወቅት ከፈለው በጥንቃቄ ከተያዘ፣ ግዛቸው ኃይሌን ስለሚያከብርና ግዛቸው ኃይሌም አገሩን የሚጠቅም ጉዳይ እስከሆነ ስለ ግል ሥልጣኑ የማይጨነቅ ከመሆኑም ሌላ የሀሳቡ ተባባሪ እንደሚሆን፣ ከፈለውም ከግዛቸው ቃል እንደማይወጣ፣ በተረፈም መንዝ በተቃጠለች ወደ ግንደበረት አብረው የመጡት የይፋት፣ የመንዝና የተጉለት አርበኞች በአካባቢው ሃሳቡ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ እንደሚችሉ ከተነተኑ በኋላ ነበር።

ከዚያም ሃሳቡን ራስ አበበ ተቀብለውት መልአከ ፀሐይ እያሱ ነግሠው ባላምባራስ አበበም ራስ ተብለው ሥራው እንደተጀመረ ልጅ ኃይለማሪያም ማሞ በአሠራሩ

[49] በፊተኞቹ ምዕራፎች በተጠቀሰው ዓይነት ለማድረግ

አለመስማማታቸውና በዚሁም ምክንያት የተፈጠረው ችግር ለወጣቶቹ የራስ ምታት ሆኖ ከመቆየቱ በቀር ከሌሎች አካባቢዎች ግልፅ የሆነ ተቃውሞ አልደረሳቸውም ነበር።

አሁን ግን ባላሰቡት መንገድ አንድ ችግር ተፈጥሩዋል። በተገኝ ቡሴይራ ምክንያት ከፈለው ይህን ያህል ያደርጋል፣ ራስ አበበም እንደዚህ ይሆናሉ ብለው አላሰቡበትም ነበር ። ይህ የተፈጠረው ችግር ግን በሌላ ጊዜም እንዳይደገም አንድ አጠቃላይ የሆነ መፍትሔ መፈለግ እንደሚጠይቅ ስላነሳሳቸው ችግሩ ከተፈጠረ ጀምሮ ሲወያዩበት ቆይተዋል። ተወያይተውበትም አንድ ውሳኔ ላይ በመድረሳቸውና መፍትሔ ብለው ያሰቡትም ነገር የሚያጎመራ ፍሬ እንደሚያፈራ በማመን ደምሴ ወልደ አማኑኤል ለራስ አበበ እንዲያቀርበው ተስማምተው ደምሴም ከራስ ጎን ቆሞ ወቅት ይጠባበቃል። ከፍለው በመነጽሩ ሲመለከት የራስ አበበ ጦር እየተንደረደረ ወደ እሱ ሲጎርፍ ሲያስተውል ከአሰበው በላይ ሁኔታው እየተለወጠ መሆኑ ታይቶት በመገረም “እንዴ! እንዴ! ጣሊያን ከፊታችን ሊወጋን ሲዘጋጅ እነሱም ሊወጉን ነው!” ሲል ጮሆ ተናገረ። ጣሊያን ስለመዘጋጀቱ ባያይም፣ መዘጋጀቱ አይቀርም ብሎ፣ ወዲያውም ራስን ለማሳጣት።

ዳኘውም እንደ ሬዲዮ አንቴና እየተሳበ የሚመዘዝ መነጽሩን አውጥቶ ተመለከተና ገረመው። እስካሁን አተኩሮ የሚያስበው ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ያደርጋሉ ብሎ ስለሚጠብቀው ጉዳይ ነበር። አሁን ግን የጉዳዩን አሳሳቢነት በማየት ከፈለውንም ሳያማክር በደመ ነፍስ ከችግሩ መውጫ ነው ብሎ ያሰበውን ነገር “አቀበቱን ወጥተን ግምጫ ማስጫ ላይ እንድረስ።” አለ። ከፈለውም አሁን ያሉበት ቦታ ለወታደራዊ እንቅስቃሴ አመች አለመሆኑን በማሰብ ተስማማበት።

የከፈለውና የዳኘው ጦር ከግምጫ ማስጫ ደርሶ ከፈለው በመነጽሩ የራስ አበበን ጦር ሲፈልግ ባሻገሩ የመንዝ አፋፍ ላይ ጦሩ ጋብ ብሎ ተመለከተና ለዳኘው ሊነግረው መለስ ቢል ዳኘው ባሻገሩ ከሰላድንጋይ ከተማ ላይ መነጽሩን ተክሎ በተመስጦ ሲመለከት ተመለከተና “ምነው ዳኘው? ምን አየህ?” አለ። የዳኘው ትከሻ የሚቀፍ ነገር ሲያይ ጎበጥ ማለት አንደኛው እግሩ ላይ ክብደቱን ጣል አድርጎ መቆም የተመለደ ስለሆነ ይህንኑ ተመልክቶ ። ዳኘው ግን መልስ ሳይሰጠው ከፈለው የራሱን መነጽር ወደዚያ አነጣጠረ። የጣሊያን መድፎች አፈሙዞች ከፊቱ ተጋረጡ። የኢጣሊያ ወታደሮች ከአፋፉ ላይ ጠበንጃዎቻቸውን ይዘው ዝም ብለው ቆመዋል። አንዳንዶቹ ወደ ኋላ አንገታቸውን ዘወር እያደረጉ ይመለከታሉ። ተኩሱ የሚል ትዕዛዝ ይጠባበቃሉ ሲል አሰበ።

ሁለቱም የተመካከሩ ያህል መነጽሮቻቸውን አውርደው ዝም ብለው ተያዩ ። አልተነጋገሩም ። በመሀከላቸው አንድም ቃል ሳያልፍ ብዙ ተወያዩ። ዳኘው ዓይኑን ወደ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ትንሹዋ ባንዲራ ተመለከተና ከዚያም መነጽሩን አንስቶ ወደ ራስ አበበ ጦር ተመለከተ። ከዚያም አሻገረና መነጽሩን ከፍ አድርጎ ጥቂት ሰዎች ቁመው ድብዝብዝ ያለ ስዕል ታየው። “ራስ አበበ ከጥቂት ሰዎች ጋር” ሲል አሰበ።

የኢጣሊያኑ ጦር አዛዥ እርዳታ ለመጠየቅ ወደ ቢሮው ተመልሶ ገብቶ ወደ ደብረብርሃን ለጀነራል ናዚ ስለሁኔታው ሲያስረዳ ጀነራል ናዚ በስድብ መለሰለት ። "ከፊት ያለው የቱ ጦር ነው? ከኋላ ብዙ ደጀን የምትለው የማን ጦር ነው? የሽፍቶቹ መሪዎች እነማን ናቸው?"

ለዚህ መልስ ለመስጠት ሻለቃው ተቸግሮ ራሱን በጡጫ እየደበደበ ትንሽ አሰበና ቀና ሲል እረዳቱን መቶ አለቃ ከፊቱ ተገትሮ አየውና ታዲያስ ለማለት የግንባሩን ቆዳ ወደ ላይ ሸፍሽፎ አትኩሮ ተመለከተው።

"ሻለቃዬ አሁን በደረሰን ሪፖርት መሠረት ሽፍቶቹ እርስ በርሳቸው ተጣልተው ራሱን ራስ ብሎ የሰየመው አበበ ያን እርኩስ ሽፍታ ከፈለውን ሊወጋው እያባረረ ነው።" አለ። ከፊቱ ላይ እፎይታና ደስታ እየተነበበ።

"ምን ያህል የታመነ ወሬ ነው?" አለ ሻለቃው አርበኞች ብዙ ጊዜ በማስመሰል እርምጃ እያታለሉ ስለሚያጠቁት የማይረባ ወሬ ይዘህ አተትምጣብኝ ለማለት ግንባሩን አኮሳትሮ መቶ አለቃውን እየተመለከተ። ለእሱ አርበኞች የሚሠሩት፣ የሚሉት ሁሉ የማይታመን ነው ። ሌላው ቀርቶ ችግር ሲያጋጥማቸው ችግራቸው እስኪያልፍ ድረስ "ላንተ እንገባለን፣" እያሉ ተስፋ ሰጥተውት አታለውታል ። በስም እንጂ ተግባራቸው የአረመኔ ካልሆነ የክርስቲያን አይደለም ብሎ ደምድሞአል። አማካሪዎቹ፣ ኢትዮጵያውያን ሃይማኖተኛ ስለሆኑ ዳዊት ይዘው ከማሉ ቃላቸውን አያጥፉም ሲሉት በሞኝነታቸው ሰፊ አፉን ከፍቶ ተንከትክቶ ይስቅባቸዋል። መቶ አለቃው ግን ወሬው እርግጠኛ መሆኑን እንደነገረው ለጀነራል ናዚ መልስ የሚሰጠው ስላገኘ ተደስቶ ሁኔታውን አስረድቶ ወደፊት ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ቃል ገብቶ ተሰናበተ ። ወዲያው ግን ወደ መቶ አለቃው ዘወር ብሎ "በሁለቱም ላይ መድፎች ይነጣጠሩ፣ እስከዚያ እኔ እመጣለሁ።" በማለት አሰናበተውና ከመቀመጫው ላይ እንዳለ ፈዞ ቀረ።

ከዚያም አንድ ነገር እንደወጋው ከመቀመጫው ብድግ ብሎ አንድ የሚያጣድፍ ጉዳይ እንደደረሰ በችኮላ በራፉን ሲከፍት የወህኒ አዛዡን መቶ አለቃ ጣሊያን፣ አገኘውና "እንዚያን ሦስት ሴቶች እየገረፍክ አዘጋጅልኝ። ያቺን ወፍራሙዋን ግን የሰለጠነ የፍቅር ጨዋታ እንድታሳየኝ በደንብ አግባባት፣" ሲል ትዕዛዝ ሰጠውና ወደፊቱ ገሠገሠ።

መቶ አለቃው ኢጣሊያዊ ወህኒ አዛዥ በዚህ ሥራው ላይ ከተመደበ ጀምሮ ቆነጃጅት ሴቶችን ካለምንም ምክንያት እያሰረ፣ ህሊናቸውን እስኪስቱ እያስቀጠቀጠ፣ የሚያስቅቁ ነገሮችን እንዲመለከቱ እያደረገ፣ በጎን ደግሞ የሱን ፍላጎት ቢፈፅሙ እንደሚፈቱ እያሰበከ ፍላጎቱን የሚያረካና ለአለቃውም በአንድ ቀን ሁለት ሦስት ሴቶች የሚያቀርብለትና ሴቶችን በመጠጥና በስልጣኔ ስም ሞራል ነክ የሆኑ ፍትዎቶች በማስገደድ ጭምር የሚያስተምር ነው ። ሻለቃው ወደ ጦርነት ሲሄድና ሲመለስ ብዙ ሴቶችን ማስቃየት ደስ የሚለው ነው። ዛሬም ይህ ጠባዩ ተነስቶበታል። ለእሱ ሴቶች በአርበኞች የሚደርስበት ጥቃት የሚፈጥረው እልህ

መውጫ ናቸው ። አርበኞችም የሁለቱን ሰዎች እርኩስ አድራጎት ስለሚያውቁ አንድ ቀን ይዘው ተገቢ ቅጣቱን ለመስጠት እንደተመኙ፣ እንዳደቡ ነው።

ሻለቃው ከአፋፉ ላይ የሚጠብቀው ጦር ዘንድ እንደ ደረሰ በመነጽሩ የራስ አበበንና የከፈለውን ጦር በየተራ ተመለከተና ወደ ፊት ግፉ እንባላለን ብለው በመረበሽ ወደሚጠብቁት የኢጣሊያንና የባንዳ ወታደሮች ፊቱን አዞረ። መንዝ ከተቃጠለች በኋላ በአንድ ዓመት ውስጥ አርበኞች አገግመው በተወሰኑ ካምፖች ብቻ የኢጣሊያ ጦር እንዲገታ ያደረጉ ሲሆን ጣሊያኖችም ከካንፓቸው እየወጡ መዋጋት ለሞት እራስን አሳልፎ መስጠት መሆኑን አውቀውታል። ሻለቃውም የወታደሮቹን የልባቸውን ስሜት ስለሚያውቅ ሁሉንም ገርመም አድርጎ ተመልከቶ "እኛ አሁን አንደኛቸው ወይም ሁለቱም የሽፍታ ቡድኖች ላይ ብንተኩስ እናስተባብራቸዋለን። ስለዚህ መድፎቹን አነጣጥራችሁ ጠብቁ። እግረኛው ጦርም በተጠንቀቅ ይጠብቅ ። ማንም ግን ካለኔ ትዕዛዝ ተኩስ እንዳይከፍት። "ሲል አዘዘ።

"ሽፍታ እርስ በርሱ ይተላለቅ!" ሲሉ ብዙ ድምፆች በደስታ ጮሁ። የተረበሸው ሆዳቸው፣ የተረበሸው መንፈሳቸው፣ ጦርነት ባለመኖሩ ተደስቶ ሲረጋጋ የሁሉም ፊት መጨማደዱ ቀርቶለት መዝናናት ሰፈነበት።

ራስ አበበ የኢጣሊያን ጦር መዝናናትን በመነጽር ውስጥ አይተው የከፈለውም ጦር እንቅስቃሴ መቆሙን ተመልከተው ግራ ገብቶአቸው አይናቸውን ከመነጽሩ ሽሽት አድርገው አንገታቸውን ዘወር አድርገው በመገረም ደምሴን ተመለከቱት ።

"ምነው ጌታዬ?" አለ ደምሴ አመለካከታቸው ለምን ፈለግከኝ ሳይሆን ነገሩ ሁሉ ምንድነው የሚል ጥያቄ ያዘለ መሆኑን አስተውሎ።

"የከፈለውም ጦር፣ የኢጣሊያንም ጦር መንቀሳቀሱን አቆመ። ከፈለውም ወደ ጣሊያን አይሄድም ። የተደናገረው ይመስላል።" አሉ በቀድሞ ሃሳባቸው ጥርጣሬ አድሮባቸው።

"ልጅ ግዛቸው ኃይሌም መጥቱዋል ። ግንባር የቀደመው ጦር ጦርነት እንዴት ሊጀምር ነው?" አለ ደምሴ በተዘዋዋሪ መንገድ ሊያስታውሳቸው።

"ምን?" አሉ ራስ ደንግጠው። በየትኛውም ደቂቃ ከከፈለው ጋር ጦራቸው ተኩስ ሊከፍት ይችላል። የከፈለው ጦር በሆነው ሁኔታ እንዲደመሰስ ትዕዛዝ ሰጥተዋል ። ሁለቱ ጦሮች ለጥይት ምት ያህል ተቀራርበዋል።

⅄ ⅄ ⅄

# ጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች ማኅበር

"ጌታዬ የአሁኑን ችግር ያመጣው የመተዳደሪ ደንብ ተቋቁሞ የአርበኛ መሪዎች እንዲፈርሙበት ተደርጎ የዚህንም ጠቃሚነት ማስረዳት ስላልተደረገ ነው፣" አለ ደምሴ ወልደ አማኑኤል[50]። ይህንን ሃሳብ ብዙ ምሳሌዎችን ጠቅሶ ጠቃሚነቱን በሰፊው አብራርቶ ለማቅረብና ተቀባይነት እንዲያገኝ ሲያስብበት የቆየ ቢሆንም በጊዜው ሁኔታ መንፈሱ ተረብሾ ጉዳዩን በግርድፉ በአጭሩ ተናግሮት።

"ምን አልክ ጌታዬ?" አሉ ራስ አበበ ደምሴ የሚለውን ነገር ሙሉ በሙሉ ስላልሰሙት።

"የመንዝና የተጉለት የይፋት አርበኞች ከፈለው ፈራሁ ብሎ ከሸሸ አክብሮቱን መግለጹ ስለሆነ ጦርነቱ አስፈላጊ አይደለም የሚል ቅሬታ አላቸው።" ራስ ዝም ብለው ማዳመጣቸውን ቀጠሉ ። ጆሮአቸውን፣ ልባቸውን በሙሉ እንደሰጡት ከሁኔታቸው ተመለከተ። "ጌታዬ ሁሉም የአርበኛ መሪዎች፣ ሕብረት ጠቃሚ እንደሆነ ያምናሉ።" ሲል ቀጠለ። ዝምታቸው ጨዋታህን ቀጥል ማለታቸው እንደሆነ ገብቶት። "እንግዲህ እንደዚህ ከሆነ ስብሰባ ተደርጎ ደንብ ይቁምና በዚያ ደንብ ላይ ሁሉም እንዲፈርሙ ይደረግ። ያንን ደንብ የጣሰ በደንቡ መሠረት መቅጣቱ የሁሉም ፈንታ ይሆናል ። ከፈለውም መጥቶ ከፈረመ ጥሩ፣ እምቢም ካለ ከሁሉም ይነጠላል።" አለ አሁንም በቃል ያስቀመጠው ነገር በሆዱ ያለውን ሃሳብ ሁሉ ስላልገለጠለት በራሱ ቅሬታ እየተሰማው። "በአገራችን ታሪክ ውስጥ ነገሥታቱ ይፈርዱ የነበረው በፍትሐ ነገሥት ነበር። ያ ፍትሐ ነገሥት በፈራጁም በፍርድ ተቀባዩም ዘንድ ተቀባይነት ስላለው ግላዊ ጥላቻን አያስከትልም።" አለ። ፈራጁና ፍርድ ተቀባይ በድምጽ ብልጫ ባያፀድቁትም በተለምዶ መቀበላቸው ልዩነት የለውም ብሎ አሰቦ። "እኛም አሁን ደምብ አቁመን፣ ሁሉም የአርበኛ መሪ በሚወክላቸው አርበኞች ስም ቢፈርም፣ የማህበሩ ደንብ አስፈፃሚዎችና ፍርድ ተቀባዮች በተስማሙበት መሠረት ስለሚሆን ቅሬታ ሳይፈጥር ማስተዳደር ይቻላል። እንዲህ ዓይነት ደንብ ሳይኖር የሚሠራ ሥራ ሁሉ ውጤቱ ጥሩ አይሆንም ። የመንግሥት አስተዳደር በገዥውና በተገዥው መሀከል በማህበራዊ ኮንትራት ወይም ውል የሚካሄድ ነው።" አለ የፈረንሳይ ሪቮሊሲዮን ውጤት እየታየው።

ራስ አበበም ትንሽ እንደማሰብ አሉና "ጥሩ ነው ። ምከሩና አዘጋጁት።" አሉ። የሚያምኑዋቸው፣ የሚመኩባቸው፣ ወጣቶች ናቸው። ከዚህ ቀደምም ገንዘብም ሆነ ስንቅ ለማግኘት ማኅበር መስርቶ መዋጮ ስለመክፈልና በዚያም መዋጮ የነፃነቱን ተጋድሎ

[50] ደምሴ ወልደ አማኑኤል በኋላ ደጃዝማች።

ለማፋፋም እንደሚቻል መክረዋቸው ነበር። “ደምሴ፣ የከፈለው የአሁኑ ጉዳይስ?” አሉ። ለራሳቸውም ጭምር ያቀረቡት ጥያቄ ነበር።

ግዛቸው ኃይሌ ራስ አበበን እጅ ነስቶ ተጠጋ። ጨዋታቸውን እስኪጨርሱ እንኳን ጊዜ የሚሰጥ ጉዳይ አይደለም ።” ጌታዬ ከከፈለው ጋር የሚደረገው ጦርነት ይቋረጥ። ለጠላት የሚያመች ሁኔታ ይፈጥራል። እሱም ፈርቶ ከሸሸ አላሸሽም ማለቱ አይጠቅምም።” አለ። ራስ አበበም እንደከፈለው እልህ የያዛቸው አድርጎ ወስዶ በመበሳጨት።

“ምን ይሁን ነው የምትለው? እንደ ሽፍታ እንደፈለገው ይሁን ነው የምትለው?”

“አይደለም ።” አለ ግዛቸው ሃሳቡን በንጹህ ልቦና ያላዳመጡት መስሎት እንደማዘን ብሎ።

“ምን አድርግ ነው የምትለኝ?” አሉ እንዲከፋ ስለማይፈልጉ መከፋቱ አበሳጭቷቸው።

“ጉዳዩ በደንብ እስኪመከርበት ድረስ ጦርነቱ እንዳይጀመር ትዕዛዝ ያስተላልፉ።”

“ከፈለው ከጣሊያ ሊገባ አይደለም? ዝም ብሎ ይግባ ወይ?” አሉ ቀድሞ ሊገባ ነው ብለው ቢያስቡም በኋላ ሃሳባቸው ዋልሎ ነበር። የአሁኑ ክርክር ግን የቀድሞውን ሀሳባቸውን አጠናከረው።

“አይገባም! ከፈለው በዚህ የሚጠረጠር አይደለም። ከዳኘው ጋር በተወያየንበት መሠረት እየሸሹ ነው። ላዩም ከጣሊያን ጋር ስዋጋ ከኋላየ ይውጉኝ ነው የሚል ። ለርስዎም ስም ይህ ጥሩ አይደለም ።”

የግዛቸውን ቃል ሊጠራጠሩት አይችሉም ። እሳቸው እስከሚያውቁት፣ ማንም ሰው እንደሚያውቀው፣ ግዛቸው ሃይማኖተ ብርቱ፣ ለነፃነቱ ለመሞት ትንሽ እንኳ ማመንታት የሌለው ጀግና ነው። “ይሁን።” አሉና ራስ ወዲያው ጋሻጃግሬያቸውን በጥሪ ተኩስ እንዳይጀመር ፊት ለቀደመው ጦራቸው እንዲነግር አዘዙ። አገሩ የሰንሰለት ተራራ ስለሆነ ከአንዱ አፋፍ ወደ ሌላው አፋፍ የሚደረገው ጥሪ ይሰማል። በድምጽ ጥሪ ግን መልእክቱ እንዴት እደንደሚተላለፍ ተጨንቀው አላሰቡበትም።

ጥሪው ራስ አበበ ካሉበት ተራራ ባሻገር ላለው አፋፍ ተነግሮ ከዚያ ቀጥሎ ካለው አፋፍ መልዕክቱ ደርሶ ጦሩ ካለበት ሳይደርስ በከፈለውና በራስ ጦር መሃከል ተኩስ የተከፈተ መሰለ። ራስ አበበ፣ ግዛቸው ኃይሌ፣ ደምሴ ወልደ አማኑኤል አንገታቸውን ደፉ። “አንድ መሪ ለማስገኘት፣ ለማግኘት፣ በአንድ እንደ አንድ ሰው ለመራመድ፣ አንድ ሕዝብ የሚከፍለው መስዋዕትነት።” ሲል ደምሴ አሰበ።

ኢጣሊያዊው ሻለቃ በአርበኞቹ መሃከል ጦርነት መከፈቱን በመነጽሩ ሲመለከት በጣም ደስ አለው ። መላው ሠራዊቱም በግብታዊነት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ በደስታ ጮኸ።

የነገሩ ሁኔታ ራስን እንዳበሳጫቸው ያወቀው ጋሻ ጃግሬአቸው ጠቡን ማፋፋሙ እንደማያገለግለው ብቻ ሳይሆን ለደረሰው ጥፋት ተጠያቂም እንዳይሆን ፈርቶ መትረየሱን ወደ ከፈለው አቅጣጫ አደረገና ቃታውን ያዝ ለቀቅ እያደረገ ታታታታ....... ታታ .... ታታታታ ማድረግ ያዘ።

ዳኘው ጦርነቱ እንደተከፈተ መነጽሩን ወደ ሰላድንጋይ አቅንቶ ነበርና ጣሊያኖች ሆ ብለው ሲነሱ ሲያይ መከበብ አድርጎ ስለወሰደው "ጣሊያኖችም በዚህ በኩል ሊከቡን ነው። ወደ ግራ ወደ አቅሬ እንውረድ" አለ። ወዲያው የከፈለው ጦር ወደ ታች ወረደ። ዳኘው ራስ አበበ ካሉበት ቦታ የተከፈተው የመትረየስ ተኩስ እነሱ ዘንድ ሊደርስ የማይችል ስለሆነ የመትየረስ የተኩስ መልእክት እንደሆነ ገብቶታል ። ምን መልእክት እንደሆነ አላወቀም።

የተስፋ ጭላንጭል ታየው ። እነ ዳኘው ወደ አቅሬ ሲወርዱ ከኢጣሊያም፣ ከራስ አበበም ጦር እየተሰወሩ ስለሆነ ተኩሱ ይቆማል ። ወርደው ሳይጨርሱ ግን ተኩሱ ቆመ።

የኢጣሊያ ጦር ከመንዝ መቃጠል በኋላ አርበኞች ካፈገፈጉበት ቆላው ተመልሰው እንደገና ብዙ ክልሎችን አስለቅቀው ከካምፑ ውጪ እንዳይነቃነቅ ካደረጉት ወዲህ፣ የዘመቻ እርምጃዎችን ከደብረብርሃን ጠቅላይ ሠፈር የወታደር ክምችትና የአይሮፕላን ድጋፍ ካልተሰጠ ስለማይነቃነቅ፣ ይህ አጋጣሚ ከውርደት ስላዳነው፣ ጣሊያኑ አዛዥ ጦሩን ወደ ሁዋላ መለሰ። ራስ አበበም ድርጊቱን ሲመለከቱ ከፈለው ኢጣሊያኖች እንዲረዱት ተላልኮ ያላደረገው መሆኑን ሲገነዘቡ በከፈለው ላይ ያላቸው ቅሬታ ቀነሰ። ይህም ሁኔታ ጉዳዩን በጥሞና ለማሰብ ጊዜ ሰጣቸው ። "ደምሴ ቅድም ያማከራችሁኝን ቶሎ ፈጽሙት።" አሉ ደምሴ ብቻውን ያማከራቸው ቢሆንም የመሰሎቹ ሁሉ ሀሳብ አንድ መሆኑን አውቀው። "ጉዳዩን ግን ከዚህ ሆነን ልናከናውነው ስለማንችል ወደ አንቀላፊኝ እናምራ። መጠርጠር ጥሩ ነውና ወደፊትም የሃሣባችሁ ተቀባይ እንዲሆን የከፈለውን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር ክፍል ግን እዚሁ ይቆይ" አሉ። ራስ አንቀላፊኝ አገሩ ሜዳና እርሻውም አጥጋቢ ስለሆነ በሠፈርነቱ በኩል ያለው አመችነትና ከፈለውንም ዝም ብሎ መተውም በጠባዩ እንዲገፉ ያበረታታዋል ብለው በማሰብ ። ራስ ትዕዛዛቸው ወዲያውኑ ተፈፃሚነት እንደሚያገኝ ስለሚያውቁ ጉዞ ለመጀመር ተነሱ።

የዚያን ሰሞን በአንቀላፊኝ የራስ አበበ የጦር አዝማቾች ከምሁራን ባልደረቦቻቸው ጋር ባደረጉት ውይይት የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኛን ማኅበርን አቋቁመው ፈረሙ።

"ለምንድነው ጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ስንል ጀግኖች የሚለውን ቃል የጨመርነው?" አለ ወለደ ኪሮ አሰያየሙ ገርሞት። በሌላ በኩል ግን መተዳደሪ ደንቡ ሙሉ በሙሉ አርክቶታል ። ማኅበሩን የሚመለከቱ ጉዳዮች ውሣኔ የሚያገኙት በድምጽ ብልጫ ሲሆን ሥራ አስኪያጆችም የሚመረጡት በድምፅ ብልጫ ነው። እያንዳንዱ አርበኛ ከሚያገኘው አስር በመቶ ለማኅበሩ ይከፍላል። በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያው ዲሞክራሲዊ በሆነ መንገድ የሚመረጥና የሚሠራ ፖለቲካዊ የሆነ ማኅበር ነው። ጀግኖች የሚለው ማንገቻ አስፈላጊነት ብቻ አልገባውም።

"ጀግኖች" የሚለው ቃል ከባንዳዎች፣ ከፈሪዎቹ የምንለይበት፣ ፍራቻቸውን የምናስታውስበት ቃል ነው።" አለ ደምሴ ጉዳዩን ሲያብራራ። "ወልደ ኪሮስ አንተ የማህበሩ ፀሐፊ ነህ፣ እነዚህን ነገሮች በደንብ ማስረዳት መቻል አለብህ።" አለ ወልደ ኪሮስ በጠባዩ ብዙም ስለማያስደተው። ማህበሩ በዚያው ስብሰባው ራስ አበበን የበላይ ጠባቂው አድርጎ መረጠ። ራስ አበበም በሥነ ሥርዓት ተለምነው ፈቃደኛ ሆኑ። ከዚህ በኋላ ለመንዝና ለተጉለት አርበኞች ለከፈለው ወልደ ፃዲቅ ጭምር በየግል ደብዳቤ ሲፃፍላቸው ይኸው መደረጉ ተገልፆ ለአስተባባሪው ለግዛቸው ኃይሌ ሰፊ ማብራሪያ የያዘ ደብዳቤ ተፃፈ።

ከፈለው ደብዳቤውን መጀመሪያ በሆዱ አነበበና ከዚያም ዙሪያውን ከበው ደብዳቤው እንዲነበብ የሚጠይቁትን ሰዎች ተመለከተና ደብዳቤውን በቀጥታ በማንበብ ፈንታ በቃሉ ማብራራት ያዘ። "ንጉሥ በሌለበት ሁኔታ አገራችን በፋሺስት ኢጣሊያ ስትወረር ሁላችንም በየፊናችን ጫካ ገብተን የምንጋደል ሲሆን ይህ ግን ከመሃከላችን በሰማዕትነት ለሚያልፉት ወንድሞቻችን ታሪካቸው እንዳይጠፉ ለማድረግ፣ ቋሚዎቹ ተበታትነን እንዳንቀር ለማስባሰብና ለመረዳዳት ደንብ እንዲቆም፣ የኛም ክፍል ተሳታፊ እንዲሆን የሚጠይቅ ነው።" አለ ሁሉንም ተራ በተራ

እየተመለከተ።

"ይነበብልን ።" አለ ዳኘው ይህን የተቀደሰ ነገር በሰፊው ለመስማት ቸኩሎ። ሌሎቹም "አዎን!" ሲሉ አስተጋቡ።

"እሺ "አለና ከፈለው ደብዳቤውን ማንበብ ያዘ። ደብዳቤውን አንብቦ እንደጨረሰም "ታዲያ ምን ይመስላችኋላ?" አለ የስብሰባውን በአጠቃላይ እንጂ በዝርዝር ለመስማት እንዳልፈለገ አብረውት ብዙ ጊዜ በመቆየት የሚያውቁት ሰዎች መሃል በግልጽ እየታየ።

"ጥሩ ነው!" .... አሉ ሁሉም ባንድ ድምጽ

"ሰምተኸዋል አንተም።" አለ ደብዳቤውን ይዞ የመጣውን ሰው በተለመደው ንቀት በሚመስል ፈገግታው እየተመለከተ። "እኔም እስማማበታለሁ። ይህንኑ ንገራቸው።" አለ ። ቀደም ሲል የግዛቸው ኃይሌ መልእክተኛ መጥቶ ስለ ጉዳዩ ማብራሪያ የሰጠው ሲሆን ግዛቸው ኃይሌ በምንም ሁኔታ ከራስ ጋር እንዳይካረር፣ ይህን ካደረገ ግን ፋሺስት ጣሊያን ጠላታችን እንደሚያስደስት፣ ይህንንም በሰሞኑ ሁኔታ ከፈለው ሳይረዳው እንዳልቀረ ጽፎለት ነበር። ከፈለውም ቢሆን አቅሬን በምታክል ቦታ ጦሩን መግቦ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት እንደማይችልና ከዚህ ሁኔታ ክብር ባለው መልክ ለመውጣት ፈልጉዋል ። አሁንም ሆዱን የሚበላው ጉዳይ ግን ከራስ ጋር ፊት ለፊት የመተያየቱ ጉዳይ ነው። ከፈለው በሃሳብ ተመስጦ ትንሽ ቆየና የራስን መልእክተኛ አሰናብቶ ስብሰባውን መምራቱን ቀጠለ።

"የማህበሩን ደንብ ለመስማማት ስብሰባው የሚደረገው ይህን ሦስት ቀን ነው። በነዚህ ሦስት ቀናት ሁሉም ሰው አንቀላፊኝ ላይ ይገኛል። ልጅ ግዛቸው ከዚያን እንድትገኝ

ብለውኛል። እኔ በበኬሌ ግን አልሄድም ። ዳኘው ቀድሞም ከራስ አበበ ጋር ስለሚተዋወቅ ወኪላችን ሆኖ ይሄድ ዘንድ ከፈለጋችሁ ልንመርጠው እንችላለን።" አለ ከፈለው ሰዎቹንም ግራ በማጋባቱ ቅሬታ እየተሰማው።

"እርስዎ መቅረትዎን እንደ ንቀት ቆጥረው እንዳይተናኮሉን እንጂ፣" አለ የከፈለው ጋሻ ጃግሬ የጀመረውን ሃሳብ እንዴት ብሎ እንደሚጨርሰው ተቸግሮ።

"አዎን ልክ ነው።" አሉ ብዙ ድምጾች።

"እኔ በድንገት ታምሜ እንደቀረሁ ደብዳቤ እጽፋለሁ።" አለ ከፈለው ቁርጥ ባለ አነጋገር። "ጭራሽኑ ከመቅረት ተወካይ መላኩ ይሻላል።" አለ ቀጠል አድርጎ።

"ይሁን፣ "አሉ በቅሬታ ብዙ ድምጾች።

"ዳኘው ምርጫችሁ ነው?" አለ ከፈለው ሁሉንም በየተራ እየቃኘ። "ይሁን "አሉ በቅሬታ ብዙ ድምጾች። ዳኘው ከአቅሬ ማታውኑ ተነስቶ ሊነጋጋ ሲል አንቀላፊኝ ራስ አበበ ጦር ሠፈር ደረሰ ። ከብዙ ሰዎች ጋር ሰላምታ ከተሰጣጠ በኋላ ራስ አበበ ዘንድ ቀርቦ እጅ ነሣ።

"ዳኘው መጣህ? አንተ ብዙ ተቸገርክ ። ከፈለው ቀረ?" አሉት። ጥያቄ ሳይሆን መደነቅ ነበር።

"አሙዋቸው ቀርተዋል። ተወካይ እኔን ልከዋል ። ደብዳቤም ጽፈዋል።" አለና ዳኘው ደብዳቤውን ለራስ አበበ ሰጠ። ራስም ደብዳቤውን በጽሞና ደጋግመው አነበቡት።

"ዳኘው የራሱን ክፍል ወክሎ በራሱ ስም ይፈርም። ከፈለው ስለራሱ መጥቶ ይፈርም። እስኪድን እንጠብቀዋለን።" አሉ ራስ ስብሰባውን እየተመለከቱ።

ዳኘው በማግሥቱ ወደ አቅሬ ተመልሶ ይህንኑ ጉዳይ አስረዳ። ከፈለው በጣም ተበሳጨ። አሁንም የራስ አበበ አንድ የጦር ክፍል ከፈለውን ይጠብቃል።

ይህ በሆነ በሳምንቱ አንድ ጡዋት ከፈለውን የሚጠብቀው ጦር አሻግሮ ወደነከፈለው ካምፕ ሲመለከት ሰፈሩ ባዶ ሆኖ አገኘው። የከፈለው ጦር ምድር ተሰንጥቃ ትዋጠው ወይም እንደ ጭስ በኖ ይጥፋ የት እንደደረሰ ማወቅ አልተቻለም። ራስ አበበ ጉዳዩን ሲሰሙ በጣም ተበሳጭተው ከፈለው ሌሊቱን ካመለጠ ከመንዝ አይወጣም ብለው መንዝ በሙሉ ቢያሳስሱ ከፈለውና ጦሩ ከዳኘው ጭምር አልተገኙም። ጠላት ጋር ተደባልቆ ይሆናል ተብሎ ቢሰለልም ስለከፈለውና ጦሩ የሚያውቅ ሰው ጠፋ።

⅄ ⅄ ⅄

# ችግርና ጦር ጠብቁኝ ብሎ አይመጣም

"ጌቶች የይፋት የኢጣሊያ ምሽግ ትልቅ ጥፋት ደረሰበት አሉ። "አሉ የራስ አበበ ነፍስ አባት የማይመስል ወሬ መናገሩ አደናግሯቸው ግን እውነት መሆኑን ከሚያምኑት ሰው ሰምተውት ዝም ማለቱም አስጨንቋቸው።

"ማን ጥፋት አደረሰበት አባቴ? "አሉ ራስ በዚያ በኩል የአርበኛ ኃይል ለጊዜው እንደሌለ ስለሚያውቁ ። የይፋትና የተጉለት አርበኞች ሰላድንጋይ ከተማ በኢጣሊያ ከተያዘችና ከመንዝ መቃጠል በኋላ ከሳቸው ጋር ወደ ግንደበረት ወርደው አሁንም አብረዋቸው መሆናቸውን ስለሚያውቁ፣ ለትህትናው ያህል ብቻ ጥያቄአቸውን በቻልተኝነት አቅርበው።

"እነማን እንደወጉት በውል አልታወቀም እንጂ፣ ትልቅ ጉዳት እንደደረሰበት ከሚታመን ሰው ነው የሰማሁት።" አሉ ራስ ጨዋታቸውን እንደአሉባልታ እንደወሰዱባቸው ገብቱዋቸው። "ነገሩን ማመን ያስቸግራል፣ ግን እግዚአብሔር ታምር ሊሠራ ይችላል።" አሉ የተለመደ አፍ ማሲያዣቸውን አምጥተው።

ራስ ነፍስ አባታቸው እንደዚህ አምርረው ሲናገሩ ነገሩ የቀልድ እንዳልሆነ ገብቶአቸው ብቻ ሳይሆን፣ ነፍስ አባታቸው ከሳቸው ፊት አሉባልታ ይዞ መቅረብ ልምድ እንደሌላቸው አስታውሰው "እስቲ በሰፊው ያጫውቱኝ አባቴ፣" አሉ። ነፍስ አባታቸውን ያከብሩአቸዋል፣ ይወዱዋቸዋል። ሰው እናቱን እንደሚወደውና እንደሚያፈቅረው ዓይነት ግምት አላቸው። ንስሀ አባታቸው ምስጢር ጠባቂያቸው፣ ምድራዊ ፉክክር የሚያስከትለው መናናቅ የሚያመጣው ነገር እንዳይደርስ ሳይጠነቀቁ ተዝናንተው የሚጫወቱአቸው ሰው ናቸው። ነፍስ አባታቸውም ይህን መቀራረብ ምክንያት አድርገው በሸንጎ ፊትና ከሌላ ሰው ፊት ራስን አንድም ቀን ተቃርነዋቸው አያውቁም።

"ሳይታሰብ በሌሊት ብዙ አርበኞች ከካምፑ ደርሰው ቃፊሮቹን ገድለው፣ሰፈሩን አተራምሰው፣ ዘርፈው፣ ተመለሱ ነው የሚባለው።" አሉ አባ ራስ ሊያዳምጡአቸው እንደፈለጉ አውቀው ደስ ብሎአቸው።

"እነዚህ ጀግኖች እነማን ይባላሉ አሉ?" ሲሉ ራስ ጠየቁ። ስማቸውን ቢነግሩአቸው ምናልባት ሊያውቁአቸው ይችላሉ። ካለዘዚያም እከሌ ማነው ብለው ይጠይቃሉ።

"ባውቀውማ እነግርዎት አልነበረም። እከሌ እንዴት ጀግና ነው። እንዲህ አድርጎ እል ነበር እንጂ የሰው ሙያ መቸ እደብቅ ነበር።" አሉ አባ።

"እስቲ እናጠያይቃለን፣" አሉ ራስ ነገሩ ግራ ገብቶአቸው። "ለመሆኑ መቸ ነው ይኸ የሆነው?" አሉ ይፋት ያለው የውስጥ አርበኞች ድርጅት እስካሁን ይህን ባለማስታወቁ ጥርጣሬአቸው ከፍ ብሎ።

“ከአራት ቀን በፊት ነው አሉ።” አሉ አባ ራስ ጥያቄውን ለምን እንዳቀረቡ ገብቶአቸው፣ እሳቸውም ስለሰሙት ወሬ ጥርጣሬ አድሮባቸው አፋቸውን ያዝ እያደረጋቸው።

“ይሁን “አሉ ራስ አባን ከአፋቸው ያዝ ሲያደርጋቸው አይተው ነገሩን አቃለውት። ከዚያም ዘወር ቢሉ ጋሻ ጃግሬቸው ጎን ቃፊራቸው ቆሞ ለመናገር ቸኩሎ አዩትና “እንደምን አደርክ፣”አሉት ሃሳባቸውን እየሰጡት።

እጅ ነሳና “ጌታዬ እጅግ ብዙ የሆነ ጦር ከሣሢት ካለው ጦር ጋር ማታውን ተደባልቆ ኑሮ ወደዚህ በማምራት ላይ ነው።” አለ ተልዕኮውን በማሰማቱ አንድ ነገረ ከትከሻው እደንደወረደለት ያህል እፎይታ ተሰምቶት። አባና ራስ የያዙትን ጨዋታ አቋርጦ ለመናገር እየዳዳው፣ ብልግና ይሆናል ብሎ ፈርቶ ዝም በማለቱ መንፈሱ ተረብሾበት ነበር።

“የጦር አለቆች ሰምተውት የለ?” አሉ ራስ የጦር አለቆች ከሰሙ እስካሁን ዝግጅቱን እንደሚያጣድፉ በማመን።

“አዎን ጌታዬ ።”

“ጥሩ።” አሉና ከድንኳናቸው ወጣ አሉ። ከበራፉ የይፋቱን የውስጥ አርበኛቸውን አዩትና መጀመሪያ ገረማቸው። በኋላም ቅሬታ ተሰማቸውና እጅ ለነሳቸው “እንደምን አለህ። ምነው ጠፋህ?” አሉት መቆየቱ አሁን ከተፈጠረው ሁኔታ ጋር ሳይዛመድ አይቀርም ብለው ጠርጥረው።

“ችግር አጋጠመኝ እንጂ አልቆይም ነበር። ሁኔታው እንደ ተፈጠረ ነበር ጉዞ የጀመርኩት ታሥሬ ቆየሁ እንጂ፣” አለ ለዚህ አደጋ መድረስ አስተዋጽኦ ያደረገ መስሎት ወንጀለኝነት ተሰምቶት።

“ምን ተፈጥሮ ነበር?” አሉት ከአባ የሰሙት ነገር እውነት መሆኑ ተሰምቶአቸው ለመስማት ቸኩለው።

“ልጅ ከፈለውና ዳኘው የይፋቱን የኢጣሊያ ምሽጋ መትተው ከፍተኛ አደጋ እንዳደረሱበት ወሬው እስካሁን ከዚህ ሳይሰማ አይቀርም።” አለ ምናልባት ሰምተውት ከሆነ ዝርዝሩን መድገሙ፣ አሁን የመጣበትን ጉዳይ አፈፃፀም እንዳያዘገየው ለመቀጠል ወይም ላለመቀጠል ፈቃድ እስኪያገኝ ጥቂት ዝም ብሎ።

“አልሰማነውም።” አሉ ራስ። ከፈለው ከአቅሬ ከጠፋ በኋላ ወደዚያ ይሄዳል የሚል ጥርጣሬ የላቸውም ነበር። “በዝርዝር የሆነውን ነገር ሁሉ ንገረኝ፣” አሉና ወደ ጋሻጃግሬአቸው ዘወር ብለው “አንተ ዝግጅቱን እንዲያጣድፉ ዕቃዎች ወደ ንብዋሻ ጥግ እንዲወርዱ፣ ንገር፣” አሉና ፊታቸውን ወደ ውስጥ አርበኛቸው መለሱ።

“እነ ልጅ ከፈለው ሳይታሰብ ካምፑን ሰብረው፣ የአዲስ አበባ ደሴ መንገድን ዘግተው፣ ብዙ ጠላት ፈጅተው፣ ዘርፈው፣ ሌሊቱን በአዳል በረሃ በኩል ዞሩ። የዚህን ጊዜ ጠላት በኃይል ከመደናገጡም ሌላ አገሩን በሙሉ አሰሰው።” አለና በዚህን ጊዜ የሱን መታሰር ማውራት ፈልጎ ወቅቱ አይደለም በማለት ትንሽ አሰበና “ከዚያም የደብረሲናውም፣ የደብረ ብርሃኑም ጦር በአንድ ላይ ከትት ብሎ የመንዝ አርበኞች ናቸው ይህን ያደረጉት ስለተባለ ወደዚህ ዘመተ።” ሲል አጠቃለለና ዝም አለ። ዘመቻው ከራስ ዘንድ ደርሱዋል። በተግባሩ መሠረት ወሬውን ከዘመቻው አስቀድሞ ስላላደረሰም በሃፍረት አቀረቀረ።

“እህ..፣” አሉ ራስ በረጅሙ ተንፍሰው፣ ከፈለው የሠራው ሥራ እስከ ሙሉ ክብደቱ እየታያቸው ። ከዚያም ወደ ጦሩ ለመቀላቀል ሲሄዱ ግፍጥጫ ላይ የቃፊሩ ጦር ከጣሊያኑ ጦር ጋር ተኩስ ጀመረ። ከተሰበሰበው ጦር ዘንድ እንደደረሱ “ግንባር የቀደሙትን ለመርዳት አንድ ሦስት አዛገች፣” አሉ። ጥያቄ ነበር። ብዙዎቹ ተነሱ። እጃቸው የመራቸውን ሦስት ሰዎች አመለከቱና ከዚያም እንዚህ ሦስት ሰዎች እስከሰዎቻቸው በአፋጣኝ ሲሄዱ ተመልከተው ለተረፉት ደግሞ መመሪያ ሰጡ። ጠላት ያው እንደተለመደው በግራና በቀኝ ለጥ ካለው ሜዳ ጥገት ጥገቱን ባሉት ተራራዎች ሥራ እየተሸለከለከ መምጣቱ አይቀርም።

የተወሰኑ የጦር አዛገች አመለከቱና “እናንተ ግራውን እናንተ ደግሞ ቀኙን በጥገቱ በኩል ውረዱ። በምንም ሁኔታ ወደፊት ጠላት መግፋት የለበትም ። ከሜዳው መሃል ከግፍጥጫ ኮረብታ ያሉት ወንድሞቻችን እንዳይከበቡ ተጠንቀቁ።” አሉና ጨረሱ።

ማናኛውም አቅጣጫ የሌለውን አቅጣጫ ሁኔታ ያወቀ የለም። ብቻ ቀኑ መሽቶ ለዓይን እስኪይዝ ድረስ ተኩስ ቀጠለ። የኢጣሊን ጦር በተደጋጋሚ ወደፊት ለመግፋት ባደረጋቸው ሙከራዎች ብዙ ሰዎች አለቁበት። ከአርበኞችም በኩል ሃያ የሚሆኑ ቆስለው አምስት ሞተው በቃሬዛ ወደኋላ እንዲመለሱ ተደረገ። ሴቶች እነዚህን ቁስለኞችና ሙታን እየተሸከሙ መውሰዱና ማስታመሙ አዝሎአቸው ደክመዋል ። አስካለ ከሁለት ባልደረባዎቹዋ ጋር ሦስት ቁስለኞችን ተሸክማ ካጉዋጉዋዘች በኋላ እግሩዋ መነቃነቅ አቃተው። “አይ አሹዋፊ!” አለችው እግሩዋን እየተመለከተችው፣ “ቁስለኛው ሁሉ ተጉዞ ማለቁን ስታውቅ፣ ቢቀጡኝም አይጨክኑብኝ ብለህ፣ አልነቃነቅ አልክ።”

ከአጠገቡዋ የነበረች ሴት ሳቀች። “አስካልዬ የምትለውን ስሙ” ብላ አንዱዋ ለሴቶቹ ደገመችላቸው። ሁሉም ሳቁ። ብዙዎቹ በጭኖቻቸው ላይ የአንዳንድ ቁስለኛ ጭንቅላት አንተርሰው፣ በጨርቅ ውሃ እየነከሩ ያንጠባጥባሉ።

ምሽቱን የአርበኛው ጦር ከያለበት አዳባይ በርሃ ገብቶ ወንዝ ወንዙን መሄድ ቀጠለ። የኢጣሊያም ጦር መተኮስም ባይችል፣ ወንዙን ተከትሎ ማባረሩን ያዘ ። የራስም ጦር እያፈገፈገ አንኮበር ድረስ ተጉዋዘ። ጣሊያንም ከዚህ ወዲያ ማባረሩ ከንቱ ልፋት መሆኑ ገብቶት አቅጣጫውን ቀይሮ ከፈለው ወዳለበት ቦታ ፊቱን አዞረ።

ራስ አበበ ቡልጋ እንደገቡ እሳቸውን ያባረረው ጦር፣ በከፈለው[51] ላይ ዘምቶ የከፈለው ጦር ድል እንዳደረገው ሰሙ። ወሬውን እንደሰሙም አካባቢቸው ላሉት ሰዎች ዘወር ብለው "ከፈለው እኮ ያንን ጦር ድል አደረገው።" አሉ ። ታምናላችሁ የሚል ዘይቤ ነበረው።

"ምናሉ ጌታዬ?" አሉ አባ ራስ የተናገሩትን ሳይሰሙት ቀርተው ሳይሆን በደንብ አጣርተው ለማስማት ፈልገው ።

"ከፈለው ዛሬ ይህን ባያደርግ ኑሮ አልምረውም ነበር። አሁን ግን የመጣውን ጠላት ራሱ ከመለሰው፣ ድል ከነሳው፣ ጀግና ነውና ወዳጄ ነው ።" አሉ ራስ ለከፈለው ያላቸው አድናቆት ከፊታቸው ላይ በግልጽ እየታየ።

"ጀግንነትማ ከማን አለ። ጠባይ የለውም እንጂ።" አሉ ደጃዝማች ዘውዱም[52] ለከፈለው የልብ ምስክርነት እየሰጡ።

"እኛ እንኳን የት እንደገባ ማወቅ አቅቶን የነበረ እንዴት ብሎ ጣሊያን ከፈለው በየት በኩል እንደሚመጣ ይወቅ።" አሉ አባ የራስ መንፈስ መለሳለሱን ካረጋገጡ በኋላ ። ከይፋቱ የውስጥ አርበኛ የአዲስ አበባ ደሴን መንገድ ለሦስት ቀን ዘግቶ የይፋትን ምሽግ የመታው ከፈለው መሆኑን ካወቁ በኋላ ከፈለውን በጀግንነቱ ያደነቁት ሲሆን፣ ከአሁን በፊት ግን ቢናገሩት እሱን ማገዝና፣ ያደረሰውን ጥፋት ትክክል አስመስሎ ማቅረብ፣ ተብሎ እንዳይተረጎምባቸው ፈርተው በሆዳቸው አምቀው ይዘውት ነበር።

"ጀግና ነው።" እሉ ራስ ከፈለውን ከማድነቅ አልፈው ተደስተውበት። የከፈለውና የዳኘው ጦር በአቅሬ ውስጥ በአንድ በኩል ከሰላድንጋይ የኢጣሊያ ጦር ጋር ተፋጦ፣ ወደኋላ አፈግፍጎም መንዝ ውስጥ እንዳይላወስ የራስ አበበ ጦር ተወካይ ተኩስም መከፈት፣ የእርስ በርስ ጦርነት ለማስነሳት ኃላፊ መሆን ከመሆኑም በላይ የዳኘው ለዘብተኛ አቋም ግራ አጋብቶት ብዙ እንደቆየ ለስብሰባ ንብዋሻ ጥሪ በተደረገ ጊዜ እንደገና ከዚህ ማጥ የመውጫ መንገድ የተገኘ መስሎ ሁሉም ተደሰተ። ዳኘው ወኪል ሆኖ ሲሄድ ግን ራስ ከፈለው ካልመጣ በማለታቸው ራስም ከፈለው እሳቸው ጋ እንዲመጣ ማስገደጃ አድርገውት እገዳውን ስላጠነከሩ፣ በየጊዜው ጦሩ መፈናፈኛ ማጣት ብቻ ሳይሆን በጠባብ አካባቢ በመታፈኑም፣ ረሃብ ገባበት።

"ዳኘው አሁንስ ምንድነው የምትለው?" አለ ከፈለው አንድ ቀን ምሽት ላይ።

---

[51] ከፈለው ወልደፃዲቅ በኋላ ደጃዝማች

[52] ከራስ አበበ ጋር የነበሩ የታወቁ አርበኛ

ዳኘው ከፈለው ከፊታቸው ሲቀርብ ክፉ ይናገሩኝና መልስ ስሰጥ ያስሩኛል ብሎ እንጂ የአርበኞችን ማኅበርን ላለመቀበል ሃሳብ እንደሌለው ስለሚያውቅና እሱ ራሱም ተወካይ ሆኖ በሄደ ጊዜ በዚህ ክፍል ስም ሊፈርምና ከፈለውም ጉዳዩ ሲረጋጋ ከራስ ዘንድ ሽማግሌ ተልኮ ይቅራረብ እንደነበር አሰበና "እንግዲህስ አንድ ነገር ማድረግ አለብን "አለ።

"እንዋጋ?" አለ ከፈለው። ምንድነው ሃሳብህ የሚል ዘይቤ የያዘ አባባል ነበር።

"አንዋጋም ። በመሀከላቸው ሰንጥቀን አልፈን፣ ይፋት ሂደን፣ የጣሊያንን ምሽግ ሰብረን፣ ከዚያ ዘርፈን እንበላለን።" አለ ዳኘው።

"አርፎ የተቀመጠ ንብ ቆስቁሳችሁ አስነደፋችሁን ቢሉንስ?" አለ ከፈለው የነገሩ ውጤት ምን እንደሚሆን ታይቶት።

"ድሮውንስ አርበኛ የሆነ ሰው አርፎ ለመቀመጥ አልተፈጠረ። ማን እንዲህ ይላል?" አለ ዳኘው ቀንም ሌትም ጠላትን ማስጨነቅ መነቃነቅ ያርበኛ ተፈጥሮ ነው ብሎ ስለሚያምን። "ይልቁንስ አሁን ተነስተን ለምን እብስ አንልም?" አለ።

ያ ምሽት አልፎ ጠዋት ሲነጋ ከፈለውና ዳኘው ከነጦራቸው ከዚያ አለመኖራቸው የታወቀው፣ እነሱም እንደ ጭስ በነው የጠፉ እስኪመስል ጥያቄ ያስነሱት፣ በዚህ መንገድ ነበር።

ራስ አበበ ስለከፈለው ባልደረቦቻቸው ያወሩትን ካዳመጡ በኋላ ጉዞአቸውን ወደ ቡልጋ ለመቀጠል ስብሰባ ጠርተው ውይይት ተደርጎበት በአጭር ጊዜ ተወሰነ።

"ባላምባራስ በሻህ" አሉ ራስ አበበ የአስካለን አጎት በሻህ ኃይሌን ራስ ከተባሉ በኋላ ባላምባራስ ብለው ሹመውታል። "ሰሞኑን ከፈለው ያደረገው ሥራ በተጉለትና በይፋት እየተዘዋዘዋሩ እንደ 1929 መሥራት መቻሉን ነው። ስለዚህ አንተ ከዚህ ለመቅረት ቀደም ብለህ የጠየቅከኝን ተስማምቻለሁ።"

"እሺ ጌታዬ" አለ ባላምባራስ በሻህ ተጉለት ገብቶ እንደ ጥንቱ ሥራውን ለመቀጠል እንደሚችል ታይቶት ፊቱ ፈክቶ። ወዲው ግን ከመንዝ ቡልጋ፣ ከቡልጋ መንዝ፣ ዝውውር ወቅት አዲስ ካፈራቸው ጓደኞች መለያየቱ መሆኑ ተሰምቶት ተከዘ። በእንዲህ ዓይነት ዘመን ጠላትነትም ወዳጅነትም በአጭር ጊዜ ይፈጠራል። ይህም ጓደኝነት ልቡን አባባው።

⅄ ⅄ ⅄

# የጀግና ቀብሩ በፉካሮ በቀረርቶ በሆታ ነው

አስካለና ለገሠ በጨዋታ ብቻ ሳሆን በአርበኝነት ሥራቸው ላይ ስለሚደጋገፉ አስካለም ይበልጥ ጀግናና የሰው ባሕሪ አዋቂ እየሆነች፣ ለገሠም የተዋጣለት የጦር መሪ እየሆኑ ሄዱ።

ሴቶች በአርበኝነት ዘመን የተለያዩ ወቅቶች ውስጥ፣ የተለያየ ሚና ነበራቸው። የትውልድ መንደራቸው በጣሊያን ሳይያዝ በፊት፣ በድንበሮች ላይና ሌሎች አርበኞችን ለመርዳት በሚደረጉ ውጊያዎች፣ ስንቅ ለማዘጋጀትና ቁስለኛ ለማንሳት የተወሰኑ ሴቶች ብቻ ከወንዶች ጋር ይጉዋዛሉ። ይህ ሁኔታ በመንዝ በ1929 አከተመ። ጣሊያኖች ሰላድንጋይን ይዘው መንዝንም ሲወሩ ሴቶች ከባሎቻቸውና ከወንድሞቻቸው ጋር ጫካ ገቡ።

ከየትኛውም ወቅት ግን ሴቶች ያላቋረጠ ተመሳሳይ የሆነ፣ አንድ ወጥ ወቅት የማይለውጠው፣ ተግባር ነበራቸው። ሴቶች ለወንዶቹ የእርማቸውን ሥጋ የለበሱ ማስታወሻ ምስሎቻቸው ነበሩ። በጦርነት ውስጥ ወይም ከውጊያ በኋላ ወንዶቹ እልህና ወኔ ሲተናነቃቸው መከረው፣ ዘከረው፣ ወደፊት እንዲገፉ የሚያስፈልጋቸውን የፀጥታ አካባቢና የስንቅ ጉዳይ የሚያሟሉላቸውና በመሀከላቸው ወንድማዊ ስሜት እንዲቀጥል የሚያደርጉላቸው ነበሩ።

አስካለ ባሉዋ ለገሠ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወደ ሰፈር ሲመለስ ለሱ ብቻ ሳይሆን ለተከታዮቹ ጭምር ከሌሎች ጋር በቂ ድግስ ደግሳ መቀመጫና መተኛውን አዘጋጅታ ትጠብቀዋለች። ከጦር ሜዳ ሲመለሱ በሳቅ በፈገግታ ትቀበለዋለች። እንደ ሌላው ቀን አብራው መብላቱዋን ትታ ቆማ እሱና ጓደኞቹን ታስተናግዳለች። ለገሠ ለእከሌ ይህን ስጡት፣ ይህ ጎደለበት፣ ብሎ እንኳን ለማሰብ ፋታ አትሰጠውም።

በጨዋታ ወቅት ለገሠ ከተከታዮቹ አንዳንድ መስማት የሚፈልጋቸውን እሱ ግን ሊያነሳቸው ያልደፈራቸውን ታነሳቸዋለች። ተከታዮቹ ከአለቃቸው ስለነሱ ጀግንነት እንዲያወሳላቸው የሚፈልጉትን ሁሉም ለምን እንዴት እንደሆነ እንኳን በማይጠረጥሩት መንገድ እንደ ጨዋታ አድርጋ ለገሠ እንዲናገረው ታደርጋለች።

ከሁሉም በላይ እልህ፣ ወኔ፣ ወንድማዊ ስሜት ስታይ ትደሰታለች። ሴቶች ሁሉ በወንዶቻቸው ደስ ይላቸዋል። የወንድ ልጅ እልህና ቁጣ ተስፋ አለመቁረጡን፣ ልበ ሙሉነቱን፣ ያሳያል። የወንዶቻቸው ልበ ሙሉነት በተረጋገጠበት ወቅት ሴቶች ወንዶቻቸው ምግብና መጠጣቸው እንዳይጎድልባቸው ብቻ እየተጠነቀቁ ለብቻቸው ተወት አድርገዋቸው እርስ በርሳቸው ከልጆቻቸው ጋር ይጫወታሉ። ወንዶቹም ተጨቃጭቀውም ሆነ ተፋጠው፣ ተወጋግዘው፣ ፎክረው ጠላታቸውን የሚያጠቁበትን እቅድ ያወጣሉ።

በዚህ ዓይነደት ወቅቶች እስካለ ለቤተሰቡ ልክ እንደ እንግዳ እያበላች፣ እያጠጣች፣ ልጆችን እያጎራረሰች፣ ከመሐል ተቀምጣ ተዝናንታ ትጫወታለች። ወደ ወንዶቹ ዘንድ እርሱዋ ከምትልካቸው ሌላ ሰዎች እንዳይገቡ ልጆችንና ሴቶችን "ዋ! ለገሠ ይቆጣችኋል!"፣

“ወለተ ፃዲቅ አርፈሽ ተቀመጭ ምን ታደርጊያለሽ? ጠላ ሲያልቅ ትወስጅላቸዋለሽ ነይ ይችን ጠጪ።” እያለች ትቆጣጠራለች።

በመጥፎ ቀውጢ ቀናት ከጦርነት በኋላ ወንዶች ማቅርቀር፣ ዝም ማለት፣ መዛል፣ እሺታ ሲሰፍንባቸው ሴቶቻቸው ይህን ሁኔታ መለወጥ እንዳለባቸው ይረዱታል። በዚህ ዓይነት ቀናት አስካለ ሙሉውን ቀን ወንዶች ዘንድ ስለምታተኩር ልጆችና ሴቶች የምሳ ሰዓታቸው ይተላለፋል። የወንዶቻቸውን ዝምታ፣ ማቅርቀርና ወኔ ማጣት ለመለወጥ፣ ሴቶች ከዳር ጀምረው እያለሳለሱ፣ ተጫውተው፣ ጨዋታው ሲደራም ፎክረው፣ የወንዶቻቸውን ወኔ ይቀሰቅሱታል። በጦርነት ወቅት ደግሞ ፈንጠዝያና ልብ መሰበር ቶሎ ቶሎ የሚፈራረቁ ናቸው። አስካለ መፎከር ባትችልም ሁኔታውን ታመቻቻለች። በመጨረሻም ተራ በተራ ወንዶቹ ያገግማሉ። የድሮው መንፈስ ይመለሳል። ሴቶች በወንዶቻቸው እንደገና ይረካሉ። በዚህ ተልእኮአቸው የወደቁ ሴቶች በመንፈስም በስጋም ይወድቃሉ።

ሁሉም አርበኛ ግን የትዳር ጓደኛው የተዋጣችለት አልነበረም። ተፈጥሮ ግን ሁሉም የሚሆነውን፣ የሚበጀውን እንዲመርጥ የምታደርግበት ዘዴ አላት። ካለዚያም እያንዳንዱ ብቁ ሆኖ ባለመገኘቱ ከመንገድ ይወድቃል። አብዛኛው አርበኛ ተስማሚ የሆነችውን የትዳር ጓደኛ ሳያውቀው ያገኛል። በሰላሙ ጊዜ፣ በዱሮው አኑዋኑዋር፣ ትስማማኛለች ያላትን አሁን ይፈታል። ዘመኑ እንደመለወጡ የሰዎች ባህሪም ይሽጋሽጋል። አስካለና ለገሠ ደስተኛ ነበሩ። ለገሠ በመሪነቱ ያሰባሰባቸው ተከታዮቹ አስካለን እንደ እናት ሲቆጥሩዋት እሱ ደግሞ እናቱም፣ እህቱም፣ ሚስቱም፣ ገረዱም፣ እመቤቱም መሆኑዋን ይቀበላል። አፄ ቴዎድሮስ ለሚስታቸው የገጠሙትን ግጥም አንድ ቄስ አንድ ቀን ቢያጫውቱት ወዲያው ከራሱ ተቀርፆበት ዘለዓለም ይደግመዋል። የሱንም ሕይወት ያንፀባርቅበታል። እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ስትሄድ

እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ

ሰው የልቡን እምነት በሌላ ሰው ሃሳብ ሲቀርብለት እንዴት ቶሎ ይቀበላዋል!

የትኛውም ጦር ሜዳ ብቻውን ይዋል፣ አስካለ አንዳንድ ጊዜ ከጦር ሜዳ ትቀራለች፣ ከቤት ውስጥ ምንም ያህል ችግር ይኑር፣ አስካለ መስተንግዶውን ታውቅበታለች። እሱም የሆነው ጠላት ቢመጣ አስተናግዶ መመለሱን ያውቅበታል። እሱ ጦር ሜዳ ሲውል አስካለ ከፉ እንዳይደርስበት እንደትምጨነቀው ሁሉ እሱም ከቤትም ሆነ ከውጭ ደፋ ቀና ስትል ትጎዳለች እያለ ያስብላታል። ካለ እሱዋ የሚሆን ነገር እንደሌለ ቢያውቅም፣ ደፋ ቀና እያለች ከጦርነት መልስ እንዳትሠራ አምርሮ ይቆጣት ነበር። እሱዋ ሰምታው አታውቅም።

ጳጉሜ 3 ቀን 1931 የመንዝ የይፋትና የተጉለት አርበኞች አስተባባሪ የነበረው ግዛቸው ኃይሌ ከአገር አገር ሲዘዋወር በአልባሌ ባንዳዎች በመገደሉ የሰው ልብ ሁሉ ከባድ ሀዘን ተጫነው፡፡[53]

አገሩ በሙሉ ግዛቸው ኃይሌን የተስፋቸው፣ የወኔያቸው ምስል አድርገው ወስደውት ስለነበር መርዶው ልብ የሚሰብር ነበር። እንደማንኛውም ልብ ሰብራት ግን እየዳነ ሄደ። እንደማንኛውም ቁስል ግን ጠባሳ ሳይተው አላለፈም። በግዛቸው ኃይሌ አስተባባሪነት ባንድነት ይሠሩ የነበሩት ውስጥ ከፈለው ወልደፃዲቅ እንደግዛቸው ኃይሌ ብዙ ሰዎች በሥሩ ቢያስተባብርም ጥቂቶቹ በሱ ሥራ ከመሆን ይልቅ ወደ ራስ አበበ ዘንድ ሄዱ። በሻህ ኃይሌ ለተጉለት ጠባቂነት ለገሠን እስከ አርበኞቹ ትቶ እሱ ብዙ ተከታዮቹን ይዞ ወደ ራስ አበበ ሄደ። እርስ በርሳቸው ምን ያህል ባይስማሙም ግዛቸው ኃይሌ ከመቃብር አፋፍ ሆኖ ስለኢትዮጵያ ነፃነት ያላቸውን አልረሱም ።

ለለገሥና ለአስካለ ይህንን ሀዘን የከፈለላቸው ወንድ ልጅ መውለዳቸው ነበር። ለአለፉት ዘጠኝ ወራት በተለይም ስድስት ወራት አስካለ በጦርነት ሜዳ ላይ ጉዳት ይደርስበታል እያለ ይጨነቅ የነበረው ዛሬ ተቃልሎለታል። የልጁንም ክርስትና በተቻለ መጠን ድግስ እንዲኖረው ስለቆረጠ በሰልቻ ድፍድፍ ተደፍድፎ፣ በአህያ ከዕቃ ጋር እየተጓጓዘ፣ ድፍድፉም በድል ጊዜ እረፍት እያደረገ፣ በሽሽት ጊዜ ወንዝ እያቋረጠ፣ ተጉዞዋል። ድግሱም በሽሽት ላይ አንድ ቀን ማታ ተደርጉዋል።

ዛሬ ልጁ ከተወለደ ስድስት ወር ቢሆነውም ለገሠ ትላንት የተወለደ ያህል ይብጠለጠልለታል። ሕይወቱ ሁሉ በልጁ ዙሪያ የሚሽከረከር ሆኑዋል። አርበኞች ወንድሞቹም ስለ ልጁ የሚሰማውን ደስታ እያስተዋሉ እነሱም ደስ ይላቸዋል። ለገሠ ልጁ በሕይወት አስከኖረለት ድረስ እሱ ቢሞት ከእንግዲህ ግዴለውም። ለአገሩ የሚከፍለው መስዋዕት አሁን ቀሎ ይታየዋል። ዘር አፍርቱዋል። ይህንን አዲስ ተስፋውን ጠላት ለማጨለም የቆረጠ ይመስል ደግሞ ጦርነቱ ከቀን ቀን አያቋርጥም ። ለዚህ ነበር ለገሠ ዛሬ የመጣውን ጠላት በኃይል መልሶ ትንሽ ቀን እረፍት ለማድረግ፣ ካለዚያም ከበባውን ጥሶ አገር ለመቀየር የቆረጠው። አገር ከቀየረ ደግሞ ከነ በሻህ ኃይሌ ዘንድ ይደባለቃል። ከዚያም ሰላም ነው ሲሉ ሰምቱዋል። ለገሠ ከበባውን ለመሰበር በሚሞክርበት አቅጣጫ ጣሊያኖች የመትረየስና የመድፉን ተኩስ አበርትተውታል። የኢጣሊያ አይሮፕላኖች የሚወረውሩዋቸው ቦንቦች ግን ሁልጊዜም ጉዳት ስለማያስከትሉ የተጨነቀባቸው አልነበረም። ሰዓቱም እየመሻሸ ሲሄድ አይሮፕላኖቹ ተሰናብተዋል። ለገሥም ቦታ ቀይሮ መስኩን ከያዘ በጨለማ አሳብሮ ወደ በሻህ ኃይሌ ይደርሳል።

[53] ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ከተገደለ በኋላ ከፈለው ወልደ ፃዲቅ አፈንጋጮችን ቀጥቶ አገሩን እስኪያረጋጋው የተፈጠረው ችግር ከፍተኛ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ለገሥ ቦታ ለመቀየር በመፈለግ ቁልቁል ተራራውን፣ ሽቅብ ዳገቱን ተመለከተና ከጎኑ የነበረችውን ባለቤቱን ልጁን ይዘሽ በዚህ በኩል ውጭ የሚል ትእዛዝ ሰጣት። አስካለም ልጁን በጨርቅ አዝላ በጢሻ መሀል ዳገቱን ስትወጣ ልጁ ከጀርባዋ ተንሸራትቶ ወደቀ። አስካለ ጮሀ ወደ ኋላዋ ስትመለስ ለገሥ የሚያለቅሰውን ልጅ በእቅፎቹ ይዞ የደነገጡ ዓይኖቹን እያየ "አይዞሽ! ደህና ነው" አላት። አስካለም በድንጋጤ ምርር ብሎ የሚያለቅሰውን ልጅዋን ተቀብላ ስታባብለው ቆይታ ወደ ለገሥ መለስ አለች። በቆመበት ዙሪያ የመትረየስ ጥይት ሳር ቅጠሉን ያርገበግበዋል። "እጄን ያዝና ወደዚህ ውጣ!" ብላ ጮሀ እጁዋን ሰደደችለት። እሱ ግን ፊቱን መልሶ መትረየሱን መተኮስ ቀጠለ። ጥይት ሲመታው እንዳታይ እጁዋን ሰዳለት አቀርቅራ "ያዘኝና ውጣ!" እያለች መጮሁዋን ቀጠለች። "ይኸኛውን መትረየስ ፀጥ ማሰኘት ከተቻለ ለገሥ ወሳኝ ወደ ሆነ ምዕራፍ እንደሚሸጋገር፣ ቆሞ አካባቢውን ሲቃኝ ተገንዝቦታል። በዚያ በኩል ሰብሮ ለመውጣትና ወደ አባቱ አገር ለመሄድ ይችላል። ልጁም አደጋ አይደርስበትም።

አስካለ ዓይኑዋን ካቀረቀረችበት ቀና አድርጋ የተመለከተችው የባሉዋ መትረየስ ዝምታ አጠራጥሩዋት ነበር። ከወዲያም ወገን የመትረየስ ተኩስ አይሰማም። ብዙ ጥይቶች ዘንበውበት ለገሥ ወድቋል። አስካለ ልጅዋን እንዳዘለች ዘላ ከጎኑ አርፋ አንገቱን ቀና አድርጋ ያዘችው። ነፍሱ አለች። ዓይኑን ገለጥ አድርጎ ተመልክቱዋት መልሶ ዘጋቸው። ቀስ ብላ አስተኝታው እጆቹዋን አወጣችና የባሉዋን መትረየስ አነሳች። እሱ ሲያደርግ እንደምታየው መትረየሱን እየተኮሰች ዘወር ብላ ለወታደሮቹ ትእዛዝ ሰጠች።

"አዝብጤና ሞገስ ለገሥን በቃሬዛ አንስታችሁ እለፉ። ሌሎቻችሁ በርትታችሁ ጠላት እንዳይሰባሰብ ተከላከሉ።" አለች አስካለ፣ አመራሩን በራሱዋ እጅ አግብታ።

አርበኞቹም አንዳች ነገር እንደቀሰቀሳቸው፣ እንደነዘራቸው ያህል ከቀድሞው ሁኔታ ከመደናገጡ ወጥተው፣ ጠበንጃዎቻቸውን ይበልጥ ያዙአቸው ጀመር። ከፀሐይዋ መጥለቅ ጋር ተኩሱም እረጭ እያለ ሄደ። በቀጭኑዋ የእግር መንገድ ለገሥ በጣለው መትረየስ ተኳሽ በኩል ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ብዙ ወርደው ከወንዙ ሲደርሱ ሁሉም በውሀው ውስጥ ቆሙ።

አስካለ ከአንድ ገሎ ላይ ቆማ ንፋሱ ከፊትዋ በኩል ሲመታት የለበሰችው ጋቢ በንፋሱ ተወጥሮ በኃይል ይሰባታል። ከሥር ረጂሙ ቀሚስዋ ይርገበገባል። ንፋሱ የሚስብባትን ጋቢ ነጥቃ በሰውነትዋ ላይ ለመለጠፍ አንዱን ጫፍ ልትይዝ ስትል ስላመለጣት ያንን ለመያዝ መለስ አለች።

አዝብጤ መልኩዋን አስተዋለ። በቅርብ ጊዜ ካያት ይበልጥ አርጅታለች። የግንባሩዋ ላይ መስመሮች በእጥፍ ጨምረዋል። ከሌላ ዓለም የመጣች ስቃይተኛ መሰለችው። እራሱዋን ከገሎው ላይ ወደ ታች ወደ ወንዙ የምትወረውር መሰለው። ሊጠራት ሞከረ። አፉ ግን ታሰረ። ሮጦ ቢጠጋት እራሱዋን የምትወረውር ይመስል ቀስ ብሎ ወደ አሱዋ ተጉዋዘ። ከአጠገቡዋ ደርሶ ልጅ ሳለች እንደሚያደርገው አንገቱዋን አቀፍ አድርጎ

"እቴ አስካለ" አላት። ከፊቱ ላይ ምን እንዳየች ባይገባውም ትኩር ብላ ተመልክታው "ጋሼ አመመህ? "አለችው።

"ምንም አልሆንኩ "ብሎዋት ሳያስበው የሱዋ ዓይን ያረፈበትን ፊቱን ዳበሰው ። እጁ እርሶ ተመለሰ።

ከዚያ ጎን ለጎን ቁጭ ብለው ቁልቁል ወንዙ ወደሚወርድበት መመልከት ቀጠሉ። እሱም የሚያውቀውን ለመግለጽ ግራ ገብቶት እሱዋም የሚለውን አየጠበቀች ለብዙ ጊዜ እንዲህ ቆዩ። አዝብጤ ያጎቱዋ ልጅ ነው።

በለገሥ ላይ ከደረሰውም ሌላ በእሱዋ ላይ የደረሰውም አስጨንቆታል። ከዚህ ሁኔታ ያላቀቃቸው ጉዞዋቸውን እንደገና ሲጀምሩ ነው።

አፋፉን ወጥተው ከለገሥ አባት ቤት ገቡ። ክብ ጥሰው የመጡት አርበኞች ማረፊያቸው ከለገሥ አባት ቤት እንዲሆን በግልፅ አልተመካከሩም። ለገሥ በከፈተላቸው መንገድ ወጥተው፣ አቅጣጫው በመራቸው ከመምጣታው ሌላ፣ ለአባቱ ልጃቸውን መስጠት ስለነበረባቸው ከዚያ ገቡ።

ለሊቱ ሊነጋጋ ሲልም አስካለ ከለገሥ መደብ ሥር ቁጭ ብላ ዓይን ዓይኑን ትመለከተው ነበር። ፊቱ እየተለዋወጠ እንደመወራጨትም ይላል ። ቅዠትም ይሁን ሲቃ ይተራመሱበታል። "ልጁስ" ብሎ አንዳንድየ ይጠይቃል።

አንዳንድ ጊዜ ህሊናውን ይስታል። ባዶ እንደሆነ ይሰማዋል። የስሜት ሕዋሳቶቹ ለውጭውም ሆነ ለውስጣዊ ሰውነቱ አዳማጭነታቸው ያቆማል። እንደገና ተመልሰው ማዳመጥ ማስተዋል ሲጀምሩ ለመናገር የፈለገውን ለማስተላለፍ ይቸኩልና ፊቱ ላይ መንቀጥቀጥ፣ በግንባሩ ላይ ላቡ ቸፈፍ ማለት ይጀምራል። እንደዚህ ብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ ዓይኑን ሳይገልጥ በደከመ ድምጽ "አስካለ፣" አለ።

"የኔ ጌታ ምን ላርግልህ? "አለችው በመናገሩ እንደሚድን አዲስ ተስፋ ልቡዋን አሙቆት ቶሎ እንዲድን፣ መዳንና መሞት በሱ ሥልጣን ሥር እንደሆኑ ሁሉ እየተለማመጠችው። እሱም ፈቃዱዋን ለመፈፀም የተዘጋጀ ይመስል ኃይሉን ሁሉ አሰባስቦ ዓይኑን ገለጠ።

"አይዞህ፣" አለችው ። ጥረቱ ሁሉ በትክክለኛው አቅጣጫ መምራቱን ዓይታ ስታደፋፍረው ። እንዳይቀየም ብዙ እየተጠነቀቀች።

"አስካለ" አላት አሁንም ብዙ መንገድ እሮጦ ደክሞት መተንፈስ እንኳን እንዳቃተው መልዕክተኛ። "አርበኞቹ አይለዩሽም አ-ው-ቀዋለሁ። አንቺም እንዳይበተኑ........" ከዚህ ላይ ሲደርስ ደክሞት አቋረጠ።

"ዝም በል የኔታ ጌታ፣" አለችው። ደክሞት፣ ሀሳቡን ቀይሮ ወደ ሙታን ዓለም እንዳያመራ ፈርታ። ትንሽ ቆይቶ ግን ቀጠለ።

"ባል ማግባት ካስፈለገሽም አግቢ። ዋናው ነፃነታችንን ማስመለስ ነው። …… ልጄን አደራ …. አርበኛ መሆን፣ ተዋጊ መሆን ችግር ነው ። ብዙ መከራ አለው። ባሪያም ከመሆን የበለጠ ነው……. ብቻ ብዙ ጊዜ አይቆይም።" ከዚያ ፀጥ አለ። እስካለም መተንፈስ የለ፣ መናገር የለ፣ ማየት የለ፣ ፀጥ አለች።

ፀሐይ ብልጭ ከማለቱዋ በፊት ወገግታዋ ዓለሙን ባለበሰው ሰዓት ከለገሠ እናት አገር፣ ከአባቱ አገር ወዲያ ማዶ፣ ከወንዙ ባሻገር ካለው አገር ከአፋፉ ብዙ ሰዎች ችምችም ብለው ቆመዋል።

በደንብ የማይሰማውን የጥሪ ድምጽ ለመጥለፍ ከየቤቱ ሰዎች ወጥተው ከጓሮአቸው ካለው አፋፍ በፀጥታ ቆመው ጆሮአቸውን አቅንተዋል። ከባድ ችግር ካልተፈጠረ ሰው አገር ከአገር አይጠራራም።

ምንም እንኳን ጥሪው ለሌላም ነገር ሊሆን ቢችል እያንዳንዱ ሰው የየራሱን መርዶ እየተጠባበቀ ለራሱ ተጨንቁዋል። ሴቶች እንኳን ሳይተጣጠቡ ሥራቸውን ትተው ወጥተው ጥሪውን ለማዳመጥ ፀጥ ብለው በጭንቀት ቆመዋል። ልጆችም ጫዋታቸውንና ጫጫታቸውን አቁመው በተጋባባቸው ፍራት የወላጆቻቸውን ሁኔታ እየሠረቁ እየተመለከቱ፣ በትናንሽ ዱላዎቻቸው ጫፍ መሬቱን ይጫጭራሉ።

ጥሪውን ለማዳመጥ ከተሰበሰቡት ሰዎች መሐል አንደኛው "አልሰማሁም" እያለ ይመልሳል። በአካባቢው ያሉት ሰዎች ሁሉ የወዲያኛውን ጎራ ተጣሪ መልስ ለመስማት ትንፋሻቸውን ይውጣሉ። ይህ ሁኔታ ለብዙ ጊዜ ከተደጋገመ በኋላ በቦታው አቀማመጥ፣ በነፋሱ አመጣጥ፣ ጥሪው የተሰማው መርዶውን ተቀበለ። "አርበኛው ለገሠ ሞቱዋል አቃብሩን ነው የሚሉት፣" ሲል ፊቱን ወደ ፀዳለ አዙሮ ተናገረ።

ፀዳለ የለገሠ እህቱ ናት። አሳዛኙን ወሬ ወዲያው እንደሰማች እየጮኸች ማልቀስ ጀመረች። ቤተሰቡዋም ተከተላት። ብዙ ቆይተው ሰዎች አባብለዋት ዝም አለች። ወዲያው ግን የለገሠ ነገር ትዝ ሲላት የዋለላት ውለታ፣ አብረው የተጫወቱት ጨዋታ ሲደቀንባት፣ እየጮኸች ብቻ ሳይሆን ፊቱዋን እየነጨች ታለቅሳለች።

መርዶው ከዋሲያ ተራራ ወደ የከሴ መጠራቱ ነበር ። ከየከሴ ወደ ግምጫ ማስጫ፣ ያም አሻገሩን መንዝ በመጥራት ዘመድ ያለበት አገር ሁሉ ተዳረሰ።

ተራራማው አገር የአንዱን አገር ከሌላው አገር እርቀት በመሬቱ ውጣ ውረድ ለእግር ጉዞ አስቸጋሪና ረጅም አድርጎታል። ሰዎች እንደልባቸው ተነቃንቀው፣ ተገናኝተው፣ በየጊዜው የሃሳብ ልውውጥ ለማድረግ ያስቸግራል። ተፈጥሮ ግን ይህን እንቅፋት የመውጫውንም ዘዴ አልነፈገችም። በሜዳውማ አገር የማይቻለውን ከዚህ የሚቻል ያደረገችው የጥሪ ግንኙነት አለ። በአንድ በኩል ረጅምና አስቸጋሪ የሆነው በሌላ በኩል ቅርብና አመች ነው። አገሩ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው በወፍ በረር እርቀት ቅርብ ነው። ወንዞች መልካ ምድሩን ሸነታትረው ተራራ ያደረጉት አገር ባሻገራቸው ተነፃፃሪ ሆኖ ይታያል። በእግር ጉዞ እያንዳንዱን መንደር ስንጥቀው የሚያልፉት ሸለቆዎች፣ ተራራ ወጥቶ

ተራራ መውረድ ስለሆነ፣ ብዙ ሰዓት ይፈጃሉ። ከአንዱ አገር ወደ ሌላው ሀገር በማለዳና በምሽት የሚደረገው ጥሪ ግን ይሰማል።

ከያለበት ያሉት አርበኞች፣ ለገሥን በግል የሚጠሉት ሳይቀሩ ቃፈሮቻቸውን እየተው ለለቅሶ ወንዝ እየተሸገሩ መጡ። ዘመድ አዝማድም ለልቅሶኛ የሚሆን ንፍሮ እየያዘ ከየአገሩ መጣ። ከሁሉም አቅጣጫ የሚመጣው ለቅሶኛ ከሃዘኑ ቦታ ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ይሰባሰብና "ጆሎ ናመገን-ጃሎ!" ማለት ይጀምራል።

እነ ፀዳለም ከቦታው እንደተቃረቡ ትንሽ ሰዎች ከተጠቃቀሱ በኋላ አንድ ድምጸ መልካም በዝግታ "ጆሎ ና-መገን-ጃሎ!" አለ።

"አሆ! "ሲሉ በዝግታ አንዳንድ ሰዎች ተቀበሉት። የመሰብሰቢያ፣ የማዳመቂያ ሆታ ነው። በኋላ ግን ከግጥም ጋር እያደባለቀ "ጆሎ ና-መገንጃሎ!" ሲል አካባቢው የነበሩት ሃሳባቸውን ሰጡት። ወንዶቹ አውራጁን እየተቀበሉ፣ ይመረኮዙት የነበረውን ዱላ፣ አንግተውት የነበረውን ጠበንጃ፣ ወደ ትከሻቸው አወጡ። አንዳንዶቹ አለባበሳቸው፣ ነጠላ አጠፋፋቸው ወቅቱን መከተሉን አስተዋሉ። ከሩቅም ከቅርብም ዱላዎች ከሰዎች በላይ መነቃነቅ ጀመሩ ። ድምጽ ከፍ እያለ ሆታው እየበረታ ሄደ።

"ሽቦው! ሎጋው ሽቦ!" አለ አውራጁ ድምፁን ፈጠንና ከፍ አድርጎ። ተቀባዮቹም ሞቅ ባለ ድምጽ፣ ጠንከር ባለ ውዝዋዜ "ሃይ! ሃይ! ሎጋው ሽቦ!" እያሉ ተቀበሉት።

አውራጁ ሙዋቹን እያሞጋገሰ፣ ተቀባዩም ሆታውን እያለ ሁሉም ወደ አስከሬኑ ተጠጉ። በዚህ ሁኔታ የአራቱም ማዕዘን ለቅሶኞች አስከሬኑ ወደ አረፈበት ቦታ ቀረቡ።

ዙሪያውን ፀጉራቸውን ሹሩባ የተሠሩና ወይም ያጎፈሩ አርበኞች ተገጥግጠዋል። መንዝና አካባቢዋ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ከመሃሉ ፈልቀው ተላምዱአቸዋል። የኢትዮጵያ ነፃነት ካልተመለሰ ፀጉራቸውን ምላጭ አይነካውም። አንዲት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራ አንድ ባለ ጎፈሬ አርበኛ ከፍ አድርጎ ይዞዋት ተውለበለባለች። እንዳንድ ጊዜ በመቋሚያዋ ላይ ዘንፈል ትላለች። እንደገና ንፋሱ ቀጥ ያደርጋታል።

ጡቶቻቸውን ወደ ታች ላግ አድርገው በነጠላቸው ያሥሩ፣ ደረታቸውን የጣሉ፣ ሴቶች በተርታ ቁመው ከጉልበታቸው አጠፍ እያሉ እንደገና ቀጥ በማለት ከአንገታቸውና ከራሳቸው ወደፊት በመሳብ ሌጣ ደረታቸውን በሁለት እጃቸው ይመታሉ። ስሜታቸው በኃይል የተነካው ከእግራቸው መሬቱን በመልቀቅ እየዘለሉ፣ እንደ ሌሎቹ እየተወዛወዙ፣ ደረታቸውን በኃይል ይጠልዙታል። ደረታቸውን በሚመቱበት ወቅት የሚያሰሙት "እንዴህ! እንዴህ!" የሚለው ድምጽ እየተቋራረጠና የብዙዎቹ በአንድ ላይ እየተነባበረ በደንብ አይሰማም።

ኣቅራሪው ስለ ለገሥ ጀግንነት ትዝታ የሚቀሰቅሱ ግጥሞችን በረጅሙ በሚውረገረግ ድምጽ ማሰማት ሲጀምር ሴቶቹ ዝላዩን፣ ደረት መምታቱን አቁመው ፀጥ ይላሉ። በቀረርቶው የተነሸጠ አንዱ ተነስቶ የሙዋቹን ጀግንነት በማውሳት ሲፎክር ሴቶቹ ካዳመጡ

በኋላ፣ በነገሩ መስማማታቸውን ለመግለጽ፣ እርማቸውንም ለማውጣት፣ "እንዴህ! እንዴህ!" በማለት ደረት መምታቱን የሐዘን ውዝዋዜውን ይቀጥላሉ። የጀግና ቀብሩ በፉካሮ፣ በቀረርቶ፣ በሆታ ነው። አስከሬኑ በድንክ የጠፍር አልጋ ላይ ሆኖ በቁመቱ ከአልጋው ሥር ሁለት ሞፈሮች ጎን ለጎን ተጋድመዋል። የቅርብ ቤተ ዘመዶቹ ዙሪያውን ከበዋል። አስካለ ተዳክማለች። የሟች አባት ፊታቸውን እርጅና በሸነታተረው እጃቸው እያሻሹ ወዲያና ወዲህ እየተንጎራደዱ ያለቅሳሉ። የጀግናም ይሁን የአልባሌ ሰው ሞት ለቅርቡ ሰው ሀዘኑ አንድ ነው።

ከሩቅ የመጣው ለቅሶኛ ሆታውን በመቀጠል ከሬሳው እንደተጠጋ ሎጋው ሸበ የሚለውን ሆታ "ዓለም ወላዋይ! "በሚለው ተከቶ አስከሬኑን መዞር ቀጠለ። አውራጁ በጎረነነ ድምጽ "አበባዬ አንቺ አበባዬ! "ሲል "ዓለም ወላዋይ! "ሲሉ ይቀበሉታል። ከተቀባዮቹ መሀል አብዛኞቹ ድምፃቸው ጎርድፉዋል። ብዙ ሰዎች ወደ አስከሬኑ በተጠጉ ቁጥር ስለ መሞቱ በይበልጥ እርግጠኛ የሆኑ ይመስል እንባ ያንቃቸዋል። አውራጁ ስለ ለገሠ፣ ስለ አርበኞቹ እያነሳሳ፣ ተቀባዮቹ በምሬት "ዓለም ወላዋይ!" እያሉ አስከሬኑን በሆታ ሦስት ጊዜ ዞረው ክብ ሰርተው ቆሙ። ከየአቅጣቻውም የመጡት ሴቶች፣ ከመንደሩ ሴቶች ተደባልቀው፣ በክቡ መሐል ሆነው ደረታቸውን እየመቱ ማልቀስ ቀጠሉ።

ሦስት ባለ ሹርባ አርበኞችና አንድ ባለ ጎፈሬ አርበኛ የሬሳውን አልጋ በሁለት ሞፈሮች አንስተው በትከሻቸው ተሸከሙ። በዙሪያቸው የተረፈው አርበኛ ሊያግዝ ተሰበሰበ።

ከተራራው በታች ወደ አለች ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ቀድመው፣ ወንዶች አስከሬኑን ተከትለው ጉዞ ተጀመረ ። ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደተደረሰ አስከሬኑ አርፎ ከአገሩ የሚብለጨለጭ ልብስ ተከህኖአቸውንና ጃንጥላቸውን ይዘው የመጡት ቀሳውስት ቅዳሴ ለማድረግ በአስከሬኑ ዙሪያ ተሰበሰቡ። ከመሃከላቸው አንደኛው ጥና ያወዛውዛል። የጥናው ሰንሰለቶችና ዘለበቶች ሲጋጩና ሲተሻሹ ከሚሰማው ድምጽ ጋር የእጣኑ ጢስም ቡልቅ እያለ በአከባቢው ይበተናል። አንድ ጊዜ ብቻ የእጣኑ ጢስ ከአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲረዋ ላይ እንዳረፈ ባንዲራዋ ተወለበለበችና ጭሱ ጠፋ።

ከቄሶቹ ግራና ቀኝ፣ ሴቶቹ በአንድ ወገን፣ ወንዶቹ በአንድ ወገን፣ ሆነው አንድ ትልቅ ክብ ሠርተው ይላቀሳሉ። ከክቡ መሃል ከራሱ ላይ ነጭ ሻሽ ያሠረ፣ ጣምራ ጦር በእጁ የያዘ፣ በወገቡ ሽጉጥ ያነገበ፣ አርበኛ እየተንጎራደደ ሲፎክር ሌሎች ሁለት አርበኞች የሱን መንጎራደድ ከኋላው እየተከተሉ በመድገም ያጅቡታል። የለገሥን ጀግንነት በማውሳት ከፎከረ በኋላ ተደጋግሞ ጥይት ተተኮሰ። ሴቶችም "እንዴህ! እንዴህ! "በማለት ደረት የመምታቱን ውዝዋዜ ቀጠሉ። ፎካሪው እየተወዛወዘ፣ ደረት መችዎችን ትንሽ መርቶ ተመለሰ። አንድ ጠበንጃ ያነገበ ጋሜ ሁለት ጆሮዎቹን ይዞ ማቅራራት ሲጀምር፣ ደረት መምታቱ ይቆማል። አስከሬኑ ቤተ ክርስቲያኑ እድሞ ካረፈ በኋላና ቤተ ክርስቲያኑን ተሳልሞ አፈር አስከቀመሰ ድረስ ይህ መላቀስ አላቋረጠም። የቤተ ክርስቲያኑ ደውል ተደወለ።

በክቡ በስተምስራቅ በኩል አራት አርበኞች የአንደኛቸውን ጋቢ አራቱን ጫፎች ከራሳቸው በላይ በመያዝ ዳስ ሠሩ። ከኋላ በኩል ያሉት ሁለቱ በርከክ ሲሉ የፊተኞቹ እንደቆሙ በመቅረታቸው ጋቢው ድንኳን መሰለ። የዚህን ጊዜ ሁለት አርበኞች ጠበንጃቸውን በእጃቸው ይዘው "ከድንኳኑ" በግራና በቀኝ ቁጢጥ ብለው ሲቀመጡ፣ አንድ ግርማው የሚያስፈራ አርበኛ ከድንኳኑ በር ላይ ጠበንጃውን በተጠንቀቅ አድርጎ፣ በርከክ ብሎ ተቀመጠ።

ለቅሶኞች በየቦታው ለመፎከሪያ ይዘዋቸው የነበሩት ረጃጅም መቃዎች ተሰብሰበው፣ ሻሽ ያሠረው ፎካሪ አርበኛ ጭብጥ ጭብጡን መቃ በእጁ እየያዘ ከፎከረ በኋላ፣ "ከድንኳኑ" ፊት መወርወር ቀጠለ። "ከድንኳኑ" በራፍ የተቀመጠው እንደ ማባረር ብሎ ይመለሳል። ወዳጅ ዘመድ አርበኛ ሁሉ ወደ ሰማይ ይተኩሳል ። በሦስተኛው ዙር መቃዎቹን ብቻ ሳይሆን የመፎከሪያውንም ጦር ከድንኳኑ ጥሎ ተመለሰ። ሻሽ ያሠረው ፎካሪ ፉከራውን እንደጨረሰ፣ ሴቶች ደረት መምታታቸውን፣ ጀግኖች ወደ ሰማይ መተኮሳቸውን ከመጀመራቸው በፊት፣ ድምፁን ከፍ አድርጎ "ለገሠ ከእዚህኛው ዓለም ወደ ወዲያኛው፣ ወደ ሰማዕታት አርበኞች ዘንድ፣ ሄጃለሁ። ለኢትዮጵያ ነፃነት ተጋደሉ። ሚስትና ልጄን አደራ ብሎዋቸኋል! ደህና ሁኑ ብሎዋችኋል!" በማለት ተናገረ።

አርበኞች ወንድሞቹ ወደ ሰማይ ተኩሱን አከታትለው እየተኮሱ ወደ ባንዲራቸው አይናቸውን አቀኑ። ሌላውም ሰው፣ ወንዱም ሴቱም፣ ተደበላለቀና አልቃሹዋ "ሆ! ሆ! ኢይይይይ "ስትል "ሆ! ሆ! "እለ እንደ ደስታው ቀን ጭፋሮ "እሽ! እሽ!" በማለት እስክስታ እየወረደ፣ እንባ ተራጨ። ተንሰቅስቆ የሚለቅስ እስክስታ የሚወርድ ይመስላል።[54]

ወዲያው ግን ቃፊሩ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ወደሚላቀሰው ሰው ተጠጋ።

⅄ ⅄ ⅄

[54] ገጸ ባሕሪይ ለገሠ የተዋቀረው በአሥር አለቃ ለገሠ የቀድሞ ክብር ዘበኛ የነበር ሰው ታሪክ ላይ ሲሆን ንጉሡ ለዓለም መንግሥታት ለማመልከት ከመሄዳቸው በፊት የክብር ዘበኞችን፣ ጥቁር አንበሳ ብለው ሰይመው፣ ለአርበኝነቱ ዉጊያ መሪዎች ሲደለድሉ፣ አሥር አለቃ ለገሠ ለባላምባራስ በሻህ የተመደበ ነበር። አገሩም በአንቀላፊኝ ጥገት እንቆያ ነው።

# ችግር ብቻውን አይመጣም

ቃሬሩ ይዞ የመጣው ወሬ ያው የተለመደው የጣሊያኖች መምጣት ነበር። ማንም እንግዳ የሆነበት የለም ። አስካለም ቀስ ብላ ከባሉዋ መቃብር ተነሳች። ከመቃብሩ ጎን ካለው ትልቅ የዋርካ ዛፍ ላይ ብዙ ወፎች ቤታቸውን ሰርተው ይዘፍናሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከአሁን ጀምሮ ወደ ለገሥ መቃብር ስትመጣ የሚቀበሉዋትን፣ እነዚህን የሰማይ ፍጡሮች፣ ለትንሽ ቅጽበት አዳመጠቻቸው። ሁልጊዜም በየትም ቦታ ቢሆን ስታልፍ እንደዚያ ዓይነት ወፎች ሲዘምሩ ከሰማች፣ ለገሥን ያስታውሱዋታል። አስካለ ከመቃብሩ ቦታ ተነስታ ስትወርድ፣ የለገሥ ተባባሪዎች የነበሩት አርበኞች፣ ከሌሎች የጦር መሪዎች ጋር ለመደባለቅ ለቅሶ ለመድረስ ከመጡት ሰዎች ጋር ይወያያሉ ብላ ስላሰበች፣ ሰው የተከተላት አልመሰላትም ነበር። ሩቅ ከሄደች በኋላ መለስ ስትል ግን እንደ ትላንትናው ዛሬም ተከትለዋታል። ማንም ከሌላ ክፍል አርበኛ ጋር የተደባለቀ የለም። አስካለ ወደ ዘመዶቹዋ ለመሄድ የነበራት ሃሳብ ተገታ።

ከቀብሩ ሥነ ሥርዓት በኋላና ከዚያም በኋላ በተከተለው ውጊያ የለገሥ ወታደሮች፣ አሽከሮች፣ አስካለን እንደ አዲሱዋ አዛዣቸው፣ እንደ እናታቸው ተከተሉዋት። ብዙውን ጊዜ ተግባሮቻቸውን የሚያከናውኑት እርስ በርሳቸው እየተመካከሩ፣ እሱዋን ለማስደሰት በመሽቀዳደም እንጂ የሱዋን ትዕዛዝ በመጠበቅ አልነበረም። እሱዋም እናትነቱዋን የማትነፍጋቸው ቢሆንም፣ አንድ ወንድ አዛዥ እንደሚያስፈልጋቸው ገባት። በምታውቀው፣ በሰማችው ታሪክ ውስጥ የሴት አዝማች አታውቅም።

ለገሥና አስካለ አንድ ላይ የተዋጣላቸው መሪዎች ነበሩ። ለገሥን ተክታ ግን አስካለ ለማስተዳደር ችሎታ ይኖረኛል የሚለው ሃሳብ በልቡዋ አልሠረፀም። ለገሥ የጐደለውን አስካለ ታሙዋላለች። አስካለ የሚጎድላትን የሚያሙዋለው ለገሥ የለም። ለስንቅም፣ ለትጥቅም በቆራጥነት (ወይም የሚጠሉት እንደሚሉት በጨካኝነት) የመዝረፍ፣ አጥፊን (ወይም የሚጠሉት እንደሚሉት ንጹሀንን) ለመቅጣት የሚያስፈልገው ቆራጥነት ይሁን ጭካኔ እሱዋ የላትም። ለገሥ ይህንንም ሆነ ሌላ ሲያደርግ፣ እሱዋ በፀጥታና በዓይኖቹዋ ሕይወትን ወደ ኋላ በፀፀት እንዳይመለከት በማድረግ ሞራሉ እንዳይወድቅ ኃይል የምሰጠው እንጂ፣ ይኸኛውን ለማድረግ ችሎታ የላትም። ማንም ሰው አድራጎቱን የሚያደርግ ባልደረባና ግማሽ አካሉ የሆነች፣ በመግባባት የምታስተውለው ሴት ካገኘ ደስተኛ ነው። ለገሥ ቆራጥነቱም ቢሆን ከመጠን እንዳያልፍ የምታግደው እንጂ እሱዋ ብቻዋን የምትፈጽመው አይደለም። ለገሥ ብቻውን አውሬ ይሆናል። ሁለቱ ሲዋሀዱ በማኅበራቸው ውስጥ ቆራጥ ይሆናሉ። ካለዚያ በአንድ እጅ ማጨብጨብ ነው።

ለጊዜው ግን አርበኛው እንዳይበተን ተልዕኮ አለባት። ቁጭ ብላ ለረጅም ጊዜ አብጠለጠለችው። እስካሁን ድረስ አርበኞች ባልደረቦቹዋ በሙሉ ከለገሥ ይበልጥ ይታዘዙዋታል። በውጊያም ላይ አሳፍረዋት አያውቁም። ከመሀከላቸው እንኳ ሳትኖር፣ በደጀንነት ከምትጠብቃቸው ቦታ ስለ ድላቸው ሊያወሩዋት እንደ ሕፃናት ልጆች

ይሽቀዳደማሉ። ለለገሥ እንደዚህ አድርገው አያውቁም። ቀደም ሲል ከለገሥ ጋር በተጣላ ቁጥር አስካለ ዘንድ እየመጣ “ይኸ ጋሼ እንደዚህ አደረገኝ፣ እንደዚያ አድርጎኝ……” እያለ የሚነጫነጨው ዛሬ ደግሞ አንድ ጀብዱ ሠርቶ ለአስካለ ለማውራት ይመጣል። እሱዋም ዝም ብላ ታዳምጠውና ፈገግ ትላለች። “እትዬ ጀግና አይደለሁም?”

“በጣም ጀግና ነህ፣” ትለዋለች ፈገግ ብላ።

“ውነትሽን ነው እትዬ?”

“አዎን።”

ደስ ብሎት ደረቱን ነፍቶ ይወጣል።

አስካለ ለረጅም ጊዜ በዚህ ለመቀጠል እንደማትችል ልቦናዋ ነግሩዋታል። በአለፉት ወራት አርበኞቹ በጥንት ዘይቤአቸው ለምግባቸውና በአካባቢው ተፈሪነትን ለማግኘት፣ የሚያደርጉት ሁሉ ቀን በቀን እየተከታተለች ስትሰማው ሩህሩህ አንጀቱዋ አልችል ብሏታል። “ጦርነት ባይኖር ጥሩ ነበር።” ብላ አሰበች። “ሴት ልጅ ጦረኛ አይደለችም። እንደምንም ሳሲትን አቁዋርጬ ይፋት ከደረስኩ፣ ለአብዬ በሻህ አርበኞቹን አስረክብና እኔ እንደ ዱሮዬ እቀጥላለሁ።” አለች።

በቅርቡዋ ያሉት የከፈለው የጦር አዝማቾችና ራሱ ከፈለው ትዝ አላሉዋትም። አርበኞቹዋ ከከፈለው ጋር ቢደባለቁ አጎቱዋ በሻህ ኃይሌ ቅር ይለዋል ብላ አስባለች።

በማግስቱ አርበኞች ወንድሞቹዋን ይዛ ወደ በሻህ ኃይሌ ለመሄድ ተነሳች። አልፈው አልፈው የተሠሩትን የጣሊያን ምሽጎች ወደ ጎን እየተወች፣ በሌሊት እያሳበረች፣ ብዙ ተጓዘች።

በሁለተኛው ቀን ላይ፣ ወደ አረፉበት ቦታ፣ አንድ ባላገር መሳይ ሲመጣ በሩቅ ተመልከተች። ገና ስታየው ደስ አላላትም። ብዙ ሰዎች አንድን ሰው አይተው በመልኩ ብቻ ይጠሉታል። ከሚጠሉት ሰው ጋር የአፍንጫው፣ ወይ የአፉ አቀዳደድ ወይ አረማመድ ከተመሳሰለ ስሜታቸውን የሚዘጋው አንዳች ነገር አለ። አስካለ ይህ ዓይነት ስሜት ተሰምቱዋት አታውቅም። ያውም ሰውየውን ገና በሩቅ መልኩን ልትለየው አትችልም። አካሄዱም የተለየ አይደለም።

ሰውዬው ቀረብ እያለ ሲመጣ አጎቱዋ ነጋሽ መሆኑን አወቀችና ቀደም ሲል በተሰማት መጥፎ ስሜት ራሱዋን ወቀሰች። ነጋሽን ስትቀበለው፣ የዚያን ዕለት ተሰምቱዋት የነበረው ሃፍረት፣ ከዚህ የመነጨ ነበር። እሱም ቢሆን ሙሉ ዓይኑዋን ለማየት ፈርቶ ዓይኖቹ ይንከራተታሉ።

“አብዬ ከሩቅ ሳይህ ሌላ ሰው መስለኸኝ ነበር፣” አለች ሳታስበው። ከዚያም የመጣባትን ሃሳብ ዋጥ አድርጋ እየሳቀች ልታጫውተው ሞከረች። ከሱ በኩል እፊቱ ላይ ባነበበችውም ይሁን በሌላ ባልገባት ምክንያት ስሜቱዋ ታፈነ። እሱም ተጠራጥራለች ሲል

አሰበ። ተኮራርፈው ኑረው ከታረቁ በኋላ ተጫወቱ ሲልዋቸው ሰዎች የሚሰማቸው ዓይነት ስሜት በሁለቱም ላይ ሰፈነባቸው።

“አስካልዬ ... መቸስ ....... የሰላም ዘመን ቢሆን ኑሮ፣ የነፃነት ዘመን ቢሆን ኑሮ፣ ለሁሉም ሥነ ሥርዓት ነበርው። እኔንም እንደዚህ ምንም እንዳልሆንኩ ሆኘ አታይኝም ነበር።....... ወግ ነበረው ለሁሉም። ....... ምን ያደርጋል?” አለ እርዳታ እንደሚፈልግ አካባቢውን እየተመለከተ። “ባላምባራስ በሻህ ኃይሌ ተማርከው ተወስደዋል። ባለቤታቸው ሞተዋል።” ብሎ ዝም አለና አቀረቀረ።

አስካለም ብዙ አልቅሳ ቀና አለችና “እንዴት ነው የተፈፀመው?” አለች።

“ባለቤትየዋ በርኖስ ለብሰው በበቅሎ ተቀምጠው፣ ባላምባራስን ቀድመው፣ ፊት ፊት ይሄዱ ነበር። ታዲያ ባላምባራስ መስለዋቸው ተኩሰው ጣሉአቸው።”

“ወይ የኔ እናት እኔ ልደፋ፣” ብላ አስካለ ተንሰቅስቃ ማልቀስ ጀመረች። ከዚያም አፍንጫዋን ጠራርጋ “የት ተቀበሩ?” አለች።

“ምን ቀብር አለ፣” አለ ነጋሽ ተከዞ። አስካለም እንዳላጣችው አውቆ ቀጠለ። “ከዚያም ባላምባራስ በሻህ የት እንዳሉ ከሜይቴ ገረድ ሰምተው ከዋሻ እንዳሉ ከበቡዋቸው፣” አለ ነጋሽ። “ገረዲቱ እንኳን ወድዳ አይደለም። በኃይል ደበደቡዋት። የሞቱ ሰዎች ሬሳ አሳዩዋት አሉ። ጨንቋት ነው።” አለ ከአስካለ ፊት ላይ ሳይሆን ሌሎቹ አርበኞች ገረዲቱን መግደል ነበር ብለው ሲቆጩ ሰምቶ። “ከዚያ ብዙ ቀን አልፎ ከዋሻው ጥሰን እንወጣለን ብለወ ሲንደረደሩ ቆስለው ተማርከው ደብረብርሃን ወሰዱአቸው።’’ ሲል ነጋሽ ገድሉን አበቃ።

ከትንሽ ለቅሶና ሃዘን በኋላ የመልስ ጉዞ ተጀመረ። ማታውን ግን አስካለ በጠና ታመመች። ኃይለኛ ትኩሳት፣ ላብ የሚያሰምጥ ትኩሳት፣ እንደያዛት ሁሉም በጃቸው እየደባበሱ አወቁ።

ጨረቃ በጠፋችበት በዚያ ምሽት ከተኛችበት ሜዳ ላይ ሽለብ ሲያደርጋት፣ ቅዠት የተመላበት እንቅልፍ ይወስዳትና ወዲያው ስትነቃና ዓይኑዋን ስትገልጥ፣ ዲያብሎስን በእጥፍ ይበልጣል ብላ ያሰበችውን ትልቅ አጋንንት፣ ቁመቱ ከባሕር ዛፍ የበለጠ፣ ከፊቱዋ ተደንቅሮ ታያለች። በፍራት ዓይኖቹዋን ትከደናቸዋለች። እንደገና አላስችል ብሎዋት ቀስ ብላ ዓይኖቹዋን ትገልጣቸዋለች። “በስመ አብ ወልድ፣’’ ብላ አትኩራ ትመለከተዋለች። “ዛፍ ነው?’’ ብላ ትጠራጠራለች። እንደገና “በስመ አብ ወልድ፣’’ ትላለች።

‘’እትዬ ሻል አለሽ?” በአካባቢዋ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን ታረጋግጣለች። ከፊቱዋ የተገተረው ሰይጣን የመሰላት ዛፍ እንደሆነ ታረጋግጣለች። “ሲያቃዠት ነበር። ነብሩ በላኝ ስትል ነበር። አሁን ሊሻላት ነው መሰል።” ሲሉ ትሰማለች። እንደገና መልሶ ሽለብ ያደርጋታል። ቅዠት።

አርበኞች ወንድሞቹዋ አለቃቸውን በቃሬዛ ይዘው የተጉለትንና የመንዝን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሽለቆዎች እየወጡ፣ እየወረዱ፣ ከአዳባይ ቆላው ይዘዋት ገቡ። አስካለ እንዴት እንደተጉዋዙ፣ ከስንት የጠላት ከበባዎች እንዳለፉ አላስተዋለችም።

ከአሥራ ሁለተ ቀናት በኋላ ትንሽ እንደመሻል ሲላት፣ አብሮ አደጉዋን ሳቆቴን ከአጠገቡዋ አየቻት። እንደተለመደው ቅዠት መስሎዋት ዓይኑዋን አላመነችውም። አፍጥጣ አየቻት።

“አስካልዬ ሻል አለሽ? ትንሽ የምተቀምሽው ላምጣልሽ።” ብላት “እሰይ አስካልዬ ዳነች።” እያለች ወደ ዋሻው ጥግ ስታመራም አስካለ ሕልም መስሎዋት መልስ ሳትሰጣት በዓይኑዋ ብቻ ትከተላታለች። ከዚያም ተመልሳ አጠገቡዋ ቁጭ ስትል አስካለ በእጁዋ ዳሰስ አርጋ፣ “ሳቆቴ ከዬት መጣሽ?” አለቻት።

ሳቆቴ አመልካች ጣቱዋን ከሙቅ ውስጥ ነክራ ጣቱዋን አስካለ አፍ ውስጥ ከታ ዝም ብላ አየቻት። አስካለም ሙቁን ስታጣጥም ቆየችና ይህ ብቻ ምክንያት፣ ነገሩ ሁሉ ህልም እንዳልሆነ እንደሚያረጋግጥ አምና፣ ደስ ብሎዋት ፈገግ አለች። ሳቆቴም ግንባሩዋን ዝቅ ብላ ሳመቻት።

“ከዬት መጣሽ? እንዴት መጣሽ?” አለች ቀስ ብላ በመገረምም፣ በመደሰትም፣ የደስታዋ ብዛት ልቡዋን አለሳልሶት፣ እንባዋን እየዋጠች።

“ባንዳዎች ከጦርነት ሲመለሱ ያንቺንም መታመም እርስ በርሳቸው ሲያወሩ ሰምቼ፣ ቢገድሉኝም ይግደሉኝ ብዬ፣ አምልጬ መጣሁ።”

አሁን ሳቆቴን በአጠገቡዋ በማግኘቱዋም ይሁን ወይም የበሽታው ጊዜ አደገኛነት ወቅቱ በማለፉ ወይም ሁለቱም ተጣምረው፣ አስካለ እየተሻላት ሄደ።

አስካለ ከአልጋ ተነስታ ገላዋን እንዳያማታት ተጣጥባ፣ ከዋሻው በራፍ ፀሐይ መውጣት ስትጀምር፣ ወጥታ፣ ወታደሮቹዋ በምን ሁኔታ ላይ እንደሆኑ አስተዋለች። እሱዋ ነፍሱዋን በሳተችበት ወቅት፣ የባንዳ አካባቢ ከሚሉት እንደልባቸው ቢዘርፉም አሁን አስካለ ነፍስ ከዘራች በኋላ ይህን ሲያደርጉ ብታይ ትበሳጫለች ብለው ከአድራጎታቸው በመቆጠባቸው፣ ትልቅ ራብ ውስጥ ናቸው።

ዝረፉና ብሉ ለማለት አንጀቱዋ ቆራጥነቱን አጣ። ዝም ብላችሁ ሙቱ ለማለት ያው አንጀቱዋ አልችል አለ። በዚህ ሃሳብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ሲያቅታት፣ አጐቱዋን አዝብጤን በጣም ሳትጨክኑ እህል የሚያበድሩአችሁን ሰዎች አጠያይቁ አለችው።

“መች እንከፍላቸዋለን?’’ አለ እየሳቀ። ወዲያው ደግሞ ሃሳቡዋን እንዳትቀይር ፈርቶ “እሺ” ብሎ ቶሎ ወጣ። አዝብጤ እንደወጣ ግን የሳቆቴን አንገት አቅፋ አለቀሰች። አበዳሪው ፈርቶ እንጂ ወዶ፣ ተቸገሮ እንጂ ተርፎት፣ እንደማያበድር ታውቃለች።

"አርበኞቹዋ አንድ ላምና አምስት ስልቻ እህል ይዘው ሲመጡ ግን አብረው ለአስካለም ጥሩ ወሬ ይዘውላት መጡ። "ራስ አበበ ሳሲት መጥተዋል አሉ!"

አስካለም ከመቅጽበት ውሳኔ ላይ ደረሰች። ቀድማ በንቃት ይህ መፍትሔ ይሆናል ብላ አላሰበችበትም። የራስ አበበ ስም ሲጠራ ግን በሻህ ኃይሌ ለራስ ያለው ታማኝነት ትዝ አላትና የባሉዋ ባልደረቦች የሆኑትን አርበኞች፣ ለራስ አበበ ለማስረከብ ወሰነች። እራት እየተበላ ጨዋታው ሲሞቅ አስካለ እየተዘዋወረች ወጥ ስትጨልፍላቸው ቆይታ ይህንኑ ሃሳብ ለሁሉም አቀረበችላቸው።

ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አብዛኛው ከራስ አበበ ጋር ለመደባለቅ ሲስማማ፣ አስራ አምስት ሰዎች ግን በምንም ሁኔታ ከአንቺ አንለይም አሉ። ሆኖም ግን ከራስ አበበ ዘንድ ለመደባለቅ የወሰኑት አስካለ አብራቸው ሄዳ እንድታስተዋውቃቸው ጠየቁ። አስካለም ተስማማች።

አስካለ ወታደሮቹዋን አስከትላ ራስ አበበ ዘንድ ስትደርስ ብዙ ለውጦች ተመለከተች። ራስ አበበ ራስ ለሚለው ክብራቸውና ለአዲሱ ሹመታቸው የሚመጥን የክብር አስተነጋገድ እንደሚደረግላቸው ሁሉ፣ ራስም አካባቢያቸውን የሚመለከቱት ከፍ ብለው ነው። ሁሉም ሰው "ራስ" ብሎ ይጠራቸዋል። ራስ መጡ! ራስ እንዲህ አሉ፣ ራስ ወዲያ ሄዱ ይባላል። እናት አባታቸው ያወጡላቸው ስም ብዙ አይጠቀስም። አስካለም "ራስ" ዘንድ የቀረበችው ቀጠሮ ተይዞላት ብዙ ዘቦችን አልፋ ነው። "ራስ" አስካለን የተቀበሉአት በታላቅ ክብር ነበር። አስካለ ታሪኩዋን ስታጫውታቸው ራስ አዘኑ። ግን ሴቱዋን ጀግና አደነቁዋት። በመጨረሻም የባሉዋን ተከታዮች ከሳቸው ጋር ለማደባለቅ እንደመጣች ስትነግራቸው ደስ አላቸው።

"አንቺስ? አስካለ?" አሉ ራስ።

"እኔ ከአሥሩ ወንድሞቼ ጋር አገሬ እመለሳለሁ።" አለች። ከአሥራ አምስቱ አምስቱ ሳሲት ከደረሱ በኋላ ከራስ ጦር ለመደባለቅ ወስነዋል።

"እዚያ ይሻልሻል?" አሉ ራስ መንዝ ስትመለስ ምናልባት ተከታዮቹዋን ለራስ አበበ በማስረከቡዋ ከፈለው ቅር ብሎት እንዳይተናኮላት በመስጋት።

"እዚያው ይሻለኛል።" አለች አስካለ። "ራስ" ቁርጥ ያለ ነገር ከድምጹዋ አንብበው ክርክሩን አቁዋረጡ።

አስካለ ወደ መንዝ እንደተመለሰች ጣሊያኖች ለገሥ ሲሞት አውቆ ይበተናል ብለው ያሰቡትን ሠራዊት እንዳለ ከራስ አበበ ጦር ጋር መዋሃዱን ሲሰሙ፣ በገባች፣ በወጣችበት፣ እየተከታተሉ መድረሻ አሳጡዋት። አሥር ወታደሮቹዋን ይዛ ለመከላከል የምታደርጋቸው ሙከራዎች ሁሉ

እየከሸፉባት ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ መሰደድ፣ መሸሸ ሆነ።

አዳባይና ዙሪያው አገር ግን የራሱን ሴት ጀግና አገኘ። ስለ ሴቱዋ አዝማች፣ ስለ ጀግንነቱዋ፣ የተጋነኑ ወሬዎች መንፈስ ጀመሩ። የአርበኞችና የደጋፊዎቻቸው መንፈስ ታደሰ።

ከፈለውና ዳኘውም የአስካለን ታሪክ ሲሰሙ ደስ አላቸው። በጀግንነቱዋ አደነቁዋት። ብዙም ሳይቆይ ግን በችግር ላይ መሆኑዋን ሲሰሙ አዘኑ። በተለይ ዳኘው ስለ አርበኞች ማኅበር ምስረታ በተደረገ ስብሰባ ላይ የሰማው ነገር ትዝ እያለው በችግሩዋ ሊደርስላት ስሜቱ ተነሳሳ።

ጣሊያኖች በእልህና በንዴት የሚፈልጉዋት አስካለ ግን፣ ከአደጋ ለማምለጥ ከቦታ ቦታ ስለምትዘዋወር፣ አድራሻዋንም ሆነ ነፍሱዋ መኖሩን በእርግጡ የሚያውቅ አልተገኘም።

⅄ ⅄ ⅄

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ክፍል ሦስት

## ዝንጀሮና አርበኛ ገደሉን አይለቅም

የከፈለው ጦር ከአቅሬ ሌሊቱን ተጉዞ፣ በይፋት ማቋዋረጫ ላይ የነበረችውን ትንሽ የኢጣሊያ ምሽግ ከመታ በኋላ፣ በምሽጉ የነበሩት የኢጣሊያ ግብር አበሮች ወደ ካራቆሬ ትልቁ የኢጣሊያ ምሽግ ሲደባለቁ፣ የከፈለውና የዳኘው ጦር የአዲስ አበባ ደሴ መንገድን ለሦስት ቀናት ዘግቶ፣ አጥቂ ቡድኖችን እየሰደደ አካባቢውን፣ ጣሊያን ያረጋጋውን አገር፣ መውጋት ያዘ። የኢጣሊያም መንግሥት የአዲስ አበባ ደሴ መንገድ መዘጋቱ በፖለቲካው አንፃር ከፍተኛ ተፅእኖ እንደሚኖረው በማወቁ ያለ የሌለውን ጦር ከየአቅጣጫው አሰባስቦ ሲመጣ፣ የከፈለውና የዳኘው ጦር በሰላድንጋይ ዙሪያ አድርጎ በእመወታ በኩል አልፎ፣ አቅሬ ተመለሰ። በደብረብርሃን በኩል የሚመጣው የኢጣሊያ ጦር፣ ከሌላው ኃይል ጋር ተዳብሎ አንቀላፊኝ ላይ የራስ አበበን ጦር አግኝቶ፣ አንኮበር ድረስ ከሸኘ በኋላ፣ ወደ ከፈለው ፊቱን አዙሮ አቅሬ ላይ መጣ። የነከፈለው ጦር አቅሬ ላይ ተዋግቶ፣ ጠላት ላይ ብዙ ጉዳት አድርሶ ከመለሰው በኋላ፣ የራስ አበበን መሄድ እንደሰማ ወደ ቋች አመራ። ከቋች አፋፍ ላይ እረፍት አደረገ።

"እንውረድ እንጂ፣" አለ ዳኘው ቆላውን ቋች እየተመለከተ። ከሥሩ የአዳባይ ወንዝ በጥቅጥቅ ጫካው ውስጥ እየተጠማዘዘ ይፈሳል። ልቡ ወደ ወንዙ በረረ። ከሕፃንነቱ ጀምሮ አዳባይ ፍራቻም፣ አድናቆትም፣ ፍቅርም አሳድሮበት ከተራራዎች ላይ ሆኖ ባየው ቁጥር ናፍቆቱ ይቀሰፈዋል።

"የኢጣሊያ እንቅስቃሴ አቁሟዋል። ከዚህ ትንሽ ልንቆይ እንችላለን፣" አለ አንተ ባይደክምህም ሰው አይደክመውም ወይ በሚል ቅላጼ። አብሮ አደጉ ጓደኛው ነበር የተናገረው። ደክሞት ከዚህ ማረፍ ፈልጓል።

"ጠላት ቢኖርም ባይኖርም ዝንጀሮና አርበኛ ገደሉን አይለቅም።" አለ ዳኘው። በልጅነት አባቱ ዝንጀሮና ሽፍታ ገደሉን አይለቅም የሚሉት አባባል ትዝ ብሎት፣ ትንሽ አስተካክሎ እየተናገር። የኢጣሊያ መንግሥት አርበኞቹን እንደ ተራ ሽፍታ ስለሚቆጥራቸው፣ ሽፍታ የሚለውን ቃል ሊጠቀምበት አልፈለገም። "ከአፋፍ ላይ የሚቀመጥ ቃፊር ብቻ ነው።

የአርበኛመልካ እየተመለከተ። ማረፊያው፣ የአርበኛ ከተማው ቆላ ነው።" አለ አሁንም የአዳባይን መልካ እየተመለከተ።

አርበኞች ከቆላው ቋች እንደወረዱ፣ በክፍል በክፍል አዛዦቻቸው አንዳንድ መንደር ተመሩ። እያንዳንዱ አዛዥ፣ ከነወታደሮቹ በአንድ መንደር ውስጥ ቤት ተደልድሎ

ይቀመጣል። በእንግድነት ባረፈበት ቤት ውስጥ ሚስትና ጓዝ ያለው ከሆነ፣ መጠለያውን ብቻ እያገኘ፣ ምግቡን የራሱ ቤተሰብ እያዘጋጀለት ይበላል። ችግር ሆኖ ለምግብ የሚሆን እህል ከሌለው፣ ከአስተናጋጁ ቤተሰብ ጋር ይበላል። በዚህ ሁኔታ ግን አርበኞች ብዙ ጊዜ ሰው እያስቸገሩ መኖርን ይጠላሉ። ስለዚህም ለኢጣሊያ ካደረው አገር ወይም ከኢጣሊያኖች ካምፕ አሳሽ ወታደሮች በመላክ አስዘርፈው አምጥተው ያከፋፍላሉ።

አንዳንድ ጊዜ ግን አማኞቸው አገር የፈጸመውን በጎ አድራጎት፣ የባንዳው አገር ሰዎች ይጠቁሙና፣ ጣሊያን አርበኛውን ያመነውን አገር ቤቱን አቃጥሎ፣ ከብቱን ነድቶ፣ እህሉን ጭኖ ይወስድበታል። የዚህን ጊዜ አርበኞች ካፈገፈጉበት ቦታ ተመልሰው፣ ለኢጣሊያ ካደረው አገር ሄደው ከብቱን ነድተው፣ እህሉን ጭነው መጥተው፣ ለአማኞቻቸው ያካፍላሉ። ጦርነት ጋብ ባለበት ጊዜ አርበኞቹ ገበሬውን በእርሻ ሥራው ያግዛሉ።

ዳኘው የከፈለውን ጦር ከተደባለቀ በኋላ፣ በአገሬው ሰው በኩል የሚመጣውን አቤቱታ በዳኝነት ማየትና በከፈለው ሥር ያሉ ጦር አዛዦች የሠፈረ አመዳደብ ሥራን እንዲያከናውን ስለተመረጠ፣ በሰፈረ አመዳደብ በኩል ትልቅ ጥንቃቄ ያደርጋል። እያንዳንዱ የጦር አዛዥ ከተመደበበት መንደር ውጭ እስከነጦሩ ከመንደር መንደርም እንዳይዘዋወር ይቆጣጠራል። ምንም እንኳን ይህ አድራጎቱ ከአርበኞች ወንድሞቹ ጋር ቅሬታ ቢፈጥርበትም፣ “ሁሉም እንደፈለገ በየመንደሩ እየዞረ በአክብሮት ወይም በፍራት የሚቀርብለትን እየበላና እየጠጣ ሕዝቡን ካስጨነቀው ነፃነታችንን የማስመለሱ ተጋድሎ አይሳካም፣” ስለሚል ከውሳኔው ንቅንቅ አይልም። የዚህን ሃሳብ ጠቃሚነት የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር አባልነትን ሲፈርም ደጋግሞ ሰምቶት አምኖበታል። ቋችም እንደደረሱ ድልድሉና ሥነ ሥርዓቱን የመራው በዚሁ መንገድ ነበር።

በአንዱ አካባቢ ያለው የአርበኛ ኃይል፣ ወደ ሌላ አካባቢ ሲመጣ፣ ከዚያ ቦታ መድረሱን ለዚያ አካባቢ አስተዳዳሪ አርበኛ ያስታውቅና ከዚያ በሚቆይባቸው ጊዜያት የሚያርፍበት መንደር ተሰጥቶት፣ ተልዕኮውን ካከናወነ በኋላ በሰላም ወደ ራሱ ክልል መመለሱ በመላው አገርም እየተለመደ ሄዱዋል።

ዳኘው በቋች ውስጥ የሠፈር ድልድል ሲያደርግ፣ ለራሱ ጦር ሰፈር ግን ባሮ ሁዳድን መረጠ። ከቅድም አያቱ ጀምሮ የዘር እርስታችን ይመለስልን እያለ የተከራከረበት ቦታ ላይ ዳኘው ከነጦሩ ሰፈረ።

አርበኞች ቋች ላይ ግን ለረዥም ጊዜ እረፍት አላደረጉም። ሞላሌ ላይ ያለው የኢጣሊያ ጦር ቋች ላይ ተደላድለው መቀመጣቸውን እንደሰማ መጣ። ከአፋፉ ላይ የነበሩት ቃፊሮች ይህንኑ አስታወቁ። ጦርነት ሲመጣ ሁሉም ሰው ይባባል። ተጋዳይ ግን ዓላማውን አይስትም። የኢጣሊያ ጦር አመጣጥ እንደታወቀ አርበኞች ከቆላው መንደር ወደ ባሻገሩ አፋፍ ወጡ።

“በአሁኑ አመጣጡ ልናጠቃውና ልንመልሰው እንችላለን።” አለ ዳኘው ያደገበትን አገር መውጫ መግቢያውን፣ አቀበት፣ ቁልቁለቱን ስለሚያውቀው። ሁሉም የጦር አዛዦች ይኸው መሆኑ ተሰምቶአቸው ጆሮአቸውን ሰጡት።

“እንዴት ዳኜ?” አለ ከፈለው በዳኘው ላይ ያለው እምነቱ ጎልቶ እየታየ።

“አሁን ካለንበት አፋፍ ለመድረስ የሚችለው፣ በዚህ በአንድ ሰርጥ ብቻ ነው።” አለ ስርጡዋን እያመለከተ። “ሌላው ሁሉ ጥርብ ያለ ገደል ስለሆነ እንኳን ሰው ዝንጀሮም አይወጣው። ስለዚህ ከስርጡ በላይ ትንሽ ሰው ተሰውሮ ይቀመጥና እኛ ከወዲያ በኩል ሆነን እንታየው። ጣሊያን በስርጡዋ በኩል ለመውጣት መጀመሪያ አሳሽ ጦር ይልካል። ዋናው ጦርም አሳሹን በርቀት ለመከተል ከመንደሩ ይደርሳል። በዚህን ጊዜ ከሥርጡ ግንባር ቀደም ሆኖ የሚመጣውን ዓይን ለዓይን ሲተያዩ መምታት ነው።” አለ ስርጡ ጠመዝማዛ ስለሆነ ከአፋፉ፣ ከበራፉ ከሆኑ ከታች የሚመጣ እስከመውጫው እስኪቀርብ፣ ከመውጫው በራፍ ምን እንዳለ ለማየት እንደማይችል እየታየው። “የዚህን ጊዜ ከመንደሩ የገባውን ጠላት እኛ ዝቅ ብለን እንቆላዋለን።” አለ።

“ይሳካል ብለህ ነው?” አለ ከፈለው። ከዚህም፣ ከበፊት ልምዱም፣ የዳኘውን ሃሳብ ጠቃሚነት አይቶ በተባሉት ቦታዎች ሰው ደለደለ። የኢጣሊያ ጦር እንደታሰበው ትንሽ ሰዎች መንገድ አሳሽ አድርጎ በስርጡ ሲልክ ዋናው ጦር ግን ከአፋፉ ወደ ወንዙ ወረደ። መንገድ አሳሹ ጦር በስርጡ አጋማሽ ላይ ሲደርስ ከስርጡ መውጫ በር ላይ ላሉት አርበኞች በግልጥ ታያቸው። ከተራራው የወረደው የኢጣሊያ ጦር ከወንዙ መውጣት ጀመረ። “ዳኘው ያሰብከው ሁሉ እየሆነ ነው።” አለ ከፈለው ጠላት የሸሹ እንዲመስለው ብዙውን ሰው ከኋላ ካለው ጉድባ ስላስቀመጠ ከዳኘው ጋር ሆኖ ተደብቆ እየተመለከተ። ከፈለው ሰውን ማሞገስ፣ ወደ አፉ የቀረበውን እህል እንኳን ለሰው ማጉረስ ይወዳል።

“ተበላሸ፣” ሲል ዳኘው ጮኸ። የስርጡን በር የሚጠብቁት አርበኞች መንገድ አሳሹ ጦር ከመውጫው ሳይደርስ መሃል መንገድ ላይ ተኮሱበት። ጥቂት የኢጣሊያ ወታደሮች ሞቱ። ከወንዙ ወደ መንደሩ ያመራው የኢጣሊያ ጦር እንቅስቃሴውን አቆመ። ዳኘው እጆቹን መትረየሱ ላይ አድርጎ በእጆቹ ላይ ጭንቅላቱን ጣል አድርጎ ተከዘ። የትውልድ መንደሩ፣ የአዳባይ መልካ፣ ከእንግዲህ በኢጣሊያኖች ይታመሳል። ጥንት የሚያውቃቸው መንደሮች ተቃጥለው ወና ይሆናሉ። አብሮአቸው ያደጋቸው ሰዎች፣ እስካሁን አርበኞችን ሲያስተናግዱ የነበሩት ሰዎች፣ ከብቶቻቸው ተነድተው፣ እህላቸው ተዘርፎ ባዶ እጃቸውን ይቀራሉ።

“ሁሉም ነገር ተበላሽቷል። ወደ ሌላ አገር ቦታ እንቀይር።” አለ ከፈለው ተክዞ። አርበኞችን ያቀፉ መንደሮች የሚጠብቃቸውን ስቃይ ያውቀዋል።

“አይ እኔ የትም አልሄድም።” አለ ዳኘው አንገቱን እንዳቀረቀረ።

“ምን ሊደረግ ይችላል?” አለ ከፈለው። ዳኘው ለትውልድ መንደሩ ያደረበትን ሃዘን አውቆት ለማጽናናት ጭምር።

“በዚያ በኩል፣ ወንዙ በሚጠማዘዝበት ገደል፣ የዝንጀሮ መንገድ አለ። በዚያ ወርጄ ጠላትን ከወንዙ ውስጥ ቀስቅሼ ከዚያ የስንዴ ቅብቅብ አወጣዋለሁ።” አለ ዳኘው አዲስ የመጣለት ሃሳብ ሃዘኑን አስረስቶት ከአቀረቀረበት ቀና ብሎ።

“የዝንጀሮ መንገድ ሰው አያስኬድም። ምን ያደርጋል?” አለ ከፈለው ዳኘው በንዴት፣ በእልህ፣ የማይረባ ሃሳብ ያቀረበ መስሎት።

“ድሮ እረኛ ሆኜ መንገዱን እወጣና እወርድበት ነበር። አያቅተኝም። ከሥርጡ ያሉት አርበኞች ከዚያ በታች ብቅ ስል ጠላት መስያቸው እንዳይተኩሱብኝ እኔ ከወረድሁ በኋላ ይነገሩ። እናንተ ከስንዴው ቅብቅብ ላይ ለማጥቃት እንዲመቻችሁ፣ ይህን ቦታ ለቃችሁ ቦታ ቀይሩ።” አለ ዳኘው ከከፈለው የሚጠይቀውን ፈቃድ እንደ ትዕዛዝ አቅርቦት።

“ይሁንልህ፣” አለ ከፈለው። ዳኘው አስር ሰዎች ይዞ ወደ ሁዋላ ካፈገፈገ በኋላ፣ ጠላት እንዳያየው በገደል ውስጥ አልፎ፣ ዝንጀሮው መንገድ ሲገባ ፀሐይ እያቀለቀለች ነበር። ከፈለው፣ ዳኘው ከተራራ ወጭዎች ምርጥ ሰዎች ጋር፣ በዝንጀሮው መንገድ ወርዶ ብቅ ሲል ሲያየው፣ ቁልቁል ወርዶ በዙሪያው መንገድ ስርጡ ጋ ከደረሰ በኋላ፣ የዳኘውን ቦታ እያሳየ። “ዳኘው ከዚያ ወርዱዋል፣ ጠላት መስሏችሁ እንዳትመቱት።” አለ በሩን ለሚጠብቁት ሰዎች። “መነጽር ያላችሁ በመነጽር ተመልከቱ።” አለ የማይታመን ነገር በታአምር የተሠራ ያህል። መነጽር ያለቸው በመነጽራቸው ተመልከተው ገረማቸው።

ዳኘው በዝንጀሮ መንገድ በጭንቀት ከነሰዎቹ ወርዶ፣ ወንዙ አፋፍ ላይ ከደረሰ በኋላ ሁኔታውን ገመገመው። የጣሊያን ጦር፣ የከፈለውን ጦር እንቅስቃሴ እየተመለከተ ሲያወካ እየና አሁን ካለበት ቦታ ከወንዙ ጥግ ካለው ቋጥኝ በቦንብ የሚደበድብበትን መንገድ ቀየሰ። ትንሽ እረፍት ተደርጎ፣ ዳኘው አራት ሰዎች ይዞ ከቋጥኙ ወጣና፣ ወደ ታች ከኢጣሊያ ጦር መሃል፣ አራቱም ሰዎች እየደጋገሙ በእጅ ቦንብ አደበላለቁት። ዳኘው ከነሰዎቹ ወደ ኋላ ተመለሰና በሸንበቆ መሃል ተሽሎክልኮ፣ ከስንዴው ቅብቅብ ብቅ አለ። የጣሊያን ጦር ከድንጋጤው ነፍሱ ሲመለስ፣ ዳኘውን ለማባረር ወደ ስንዴው ቅብቅብ አመራ። ዳኘው ከስንዴው ቅብቅብ ወጥቶ ወደ ገደሉ ወጣ። ተኩስ ተከፈተ።

ዋናው የአርበኛ ጦር ድንገት ሳይታሰብ በሌላ አፋፍ ብቅ ብሎ፣ ከስንዴው ቅብቅብ ውስጥ ጠላትን ፈጀው። ጠላት የሚያደርገው ጠፋው። በየድንጋዩ ሥር ተወሽቆ ጠላት መታኮስ ያዘ። ከዚያም እያፈገፈገ ወደ ወንዙ ተመለሰ። ፀሐይ ከአድማሱ አቀለቀለች። ሁሉም ነገር ፀጥ አለ።

“ጋሼ ጠበንጃውን ልማርክ።” አለ የዳኘው ሻንጣ ተሸካሚ። ወጣት ልጅ ነው። ጠበንጃ ስለሌለው ጥይት የሞላውን ሻንጣ ተሸክሞ ዳኘውን ይከተላል። ዳኘው መትረየሱን ሲተኩስ እሱ እመትረየሱ ዝናር ውስጥ ጥይት ይከታል። መሣሪያ ከማረከ፣ ወይም ትርፍ

ጠበንጃ ከተገኘ ግን ከሻንጣ ተሸካሚነት ወታደር ይሆናል። ባሻገሩ የሞተ ጠላት አይቶ፣ ተኩስም ፀጥ ከማለቱ ጋር ተደፋፍሮ፣ "ጋሼ ጠበንጃ ልማርክ?" አለ ሎጋው የ16 ዓመት ወጣት።

"ይቅርብህ፣ አልሞተ እንደሆነ ያበላሽሃል!" አለ ዳኘው።

"ግዴለህም ጋሼ ሞቱዋል፣" አለ ወጣቱ ቸኩሎ፣ ጉዋጉቶ።

"ዳኘው ምን ቸገረህ። ሁልጊዜም ያንተ ሻንጣ ተሸካሚ ሁኖ ይቅር ነው የምትል?" አለ የዳኘው አብሮ አደጉ የሆነ ወታደር። "እኔ ለዚህ አይደለም። እንደፈለገ።" አለ ዳኘው ቅር ብሎት። ወጣቱ እየተንደረደረ ሄዶ ከጠላት ሬሳ ደረሰ። በትልቅ ደስታ ጠበንጃውን አነሳና ከፍ አድርጎ ለወገኖቹ አሳያቸው። ሁሉም በደስታ ፈገግ አሉ።

ወዲያው ብዙም ሳይቆይ፣ ካሻገሩ ካሉት ሬሳዎች መሃል፣ አንድ የወደቀ ጠላት ሽጉጡን አነጣጥሮ ተኮሰ። ወጣቱን ልጅ በአንገቱ ሥር የገባችው ጥይት ጣለችው። ወገኖቹ ሁሉ አንገታቸውን ደፉ። "አስገደልከው።" አለ ዳኘው አብሮ አደጉን ወታደር በምሬት እየተመለከተው።

"አዎን እኔ ነኝ ጥፋተኛው። እኔ ልደፋ!" አለና ወታደሩ አለቀሰ።

"ደለለኝ በደረትህ እየተሳብክ ሄደህ እግሩን አስረህ እየጎተትህ አምጣው፣" አለ ዳኘው ለሚወደው፣ ለሚመካበት፣ ለጀግናው ጋሻጃግሬው። ሁልጊዜም ቢሆን ከዳኘው ሻንጣ ገመድ አይለይም። ገደል ለመውረጃ፣ ዕቃ ለማሰሪያ ገመድ ያለውን ጥቅም በደንብ ያውቃል።

"እሱም እንዳይሞት።" አለ ሌላው ሀዘን በሠበረው ድምጽ።

"ወንድማችንን ሳንቀብረው አንሄድም። ተደርጎም አይታወቅ።" አለ ዳኘው። ይህን ለማሙዋላት ሁላችንም እናልቅ ይሆናል በሚል ዘይቤ።

ደለለኝ እየተሳበ ወርዶ ከሙዋቹ ባልደረባቸው እግር ላይ ገመድ አስሮ ወደ ኋላ እየሳበ ሲያመጣው ከጉድጓድ ገባበት። ከዚያም ሌሎች ሰዎች ተጨምረው ተጋግዘው አመጡት።

"ጉድጓድ ከዚህ ቆፍሩ።" አለ ዳኘው ቤተ ክርስቲያን ሊቀበር ያልቻለውን አርበኛ በልብ ስብራት እየተመለከተ።

"የእህል ጉድጓድ!" ሲል ከቆፋሪዎቹ መሃል አንዱ ተናገረ።

"የምን እህል?" አለ ሌላው።

"ባዶ የእህል ጉድጓድ!" አለ ወደ ውስጥ ሲገባ በቁመቱ ልክ እየሆነ።

"ሕዝቡ እንዴት ተሰቃየ፣" አለና ዳኘው "ከጎንና ከጎን ደርምሱት፣" አለ። ፀሐይ እየጠለቀች ነው።

አርበኞች ጉድጓዱን ካዘጋጁ በኋላ ወጣቱ ወንድማቸውን በአንገቱ ላይ ጠምጥሞት በነበረውና ለምርኮ ሲነሳ ከዚያው ጥሎት የነበረውን ጋቢ አንስተው በዚያ ገንዘው ቀበሩት። ሁሉም አንገታቸውን ደፍተው በመስዋዕትነት የቀደማቸውን አርበኛ በተመስጦ ተሰናበቱት።

"በዚህ በጨለማ ተመልሰን በዝንጀሮ መንገድ አንሄድም። ይችን ቁልቁለቱዋን እንደ ምንም እየቡዋጠጥን ወርደን፣ በመንደሩ ባሻገር እናልፋለን።" አለ ዳኘው። ሁሉም በድፍረት የማይቻል ችግር እንዲጋፈጡ የሚያደርጋቸውን፣ በውጤቱ ግን ትልቅ ኩራት የሚያስገኝላቸውን መሪ በፀጥታ ተመለከቱት። በደስታ ሰክሮ የነበረው ልባቸው በከፈሉት መስዋዕትነት ተከዙዋል። ከመንደሩ ወርደው፣ ሰው ሁሉ ካርበኞቹ ጋር ሸሽቶ ስለሄደ ባዶ በሆነው መንደር፣ በትካዜ አለፉ። ከመንደሩ ወጥተው ወደ ስርጡ ሲያመሩ ግን አካባቢው በብርሃን ተሸፈነ።

ስርጡን ይጠብቅ የነበረው ክፍል በነዳኘው በኩል የተገኘው ድል አነሳስቶትና ቀደም ሲል ያጠፋውን ጥፋት ለማካካስ፣ በተራው ጀብዱ ለመሥራት፣ ከስርጡ ወደ መንደሩ አልፎ ወደ ወንዙ ተሻግሮ ቦንብ ሲወረውር በዚያ አካባቢ አንዲት ብቻዋን የቆመች አሮጌ ጎጆ ስለነበረች ተቀጣጠለች። በዚህ ብርሃን በመጠቀም የኢጣሊያ ጦር አምስት አርበኞች ጣለ። ሁሉም አርበኞች ከመሬት ወድቀው ፀጥ አሉ። እነ ዳኘውና ከስርጡ የወረደው ጦር መሬት ከመያዛቸው በፊት፣ ቅርብ ለቅርብ ሆነው ብርሃኑ ውስጥ ተያዩ። ዳኘው በደረቱ እየተሳበ ወደ እነሱ ሄደና "ምነው ምን ነካችሁ?" አለ። ወዲያውም መልስ እንደማይጠብቅ ሰው ፊቱን አዞረ።

"የሆነው ጥፋት ሁኑዋል። አሁን ሬሳ ማንሳት ነው ያለብን፣" አለ ሌላው።

"ቃጠሎው እስኪያበቃ ዝም ብሎ መጠበቅ ነው።" አለ ዳኘው አሁንም እንደከፋው።

ቃጠሎው ሲያበቃ አርበኞች ሙታኖቻቸውን አንስተው ወደ ተራራውወጡ። ጓደኞቻቸውን ቀብረው ትንሽ ቆይቶ ነጋ። ከፈለው በመነጽሩ ሲመለከት፣ የኢጣሊያ ጦር ከወንዙ ተመልሶ ወደ ሞላሌ ያመራል። ሌሎችም መነጽር ያላቸው ተመለከቱ። ሁሉም በአንድ ላይ ተንደርድረው የጦርነት ቦታ ከነበረው ወረዱ። አምስት መትረየሶች፣ ብዙ ጠበምጃዎች፣ ብዙ ጥይቶች አገኙ። የከፈለው ሠራዊት ባለሰባት መትረየስ ሆነ።

"ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠላት ድል አደረገን።" አለ ዳኘው መሬት መሬቱን እያየ። ሹርባ የተሠራው ረጅም ሉጫ ፀጉሩ ከተከሻው ዘንፈል ብሎ ወድቁዋል። "እስከ ዛሬ ጠላት ከአገር አገር አሳዶ፣ ከቦ የዱር ፍሬ እንድንበላ፣ ውሀ አጥተን ሽንት እንድንጠጣ ያደረገበት ጊዜ አለ። እንደ ዛሬ ግን በራሳችን ስህተት ስድስት ሰው ገድሎብን አያውቅም።"

⅄ ⅄ ⅄

# አስካለ መጣች

አስካለ ወደ ላሎምድር መምጣቱዋ በሰፊው ይወራል። በሁሉም ቦታ አለች እየተባለ ይወራል። አስካለ መጣች እየተባለ ከሚነፍሰው ወሬ ጋር አስካለ አትታይም። እንደ ወንድ ጣሊያኖች የሚያሳድዱዋትን ጀግና ለመርዳት ሁሉም ልቡ ተነሳስቱዋል። እስካሁን ግን ለዚህ እድል የበቃ የለም።

ለገሠ በሞተ በስድስተኛው ወር፣ ለራስ ጦሩን ባስረከበች በሁለት ወሩዋ፣ አስካለ ንብዋሻ መግባቱዋን ዳኘው ሰማ። ወዲያው በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን አርበኞች አስተባብሮ በአርበኞቹ ስም ለጀግናው ለገሠ ልጅ ማሳደጊያ አንዲት ላም ተዋጥታ፣ እሱ ከጥቂት ሰዎች ጋር በአርበኞቹ ስም ለቅሶ ሊደርስ እንዲወሰን አሳስቦ ሃሳቡ ድጋፍ አገኘ።

ለቅሶና ሠርግ የሚደርሰው ለስንፉ ነው ይባላል። ለሠርገኛው ወይ ለሃዘንተኛው ያለን ፍቅር ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን፣ ሰውየው በዘመድ ወዳጁ ብዛት ልቡ እንዲሞላ፣ እከሌ እንዲህ ነው እንዲባል ነው። በጥንታዊ ኅብረተሰብ ሰዎች በቤተ ዘመድ በሚመደቡበትና ዘመድ ቡድን ሳይሆን መመኪያ ከነበረበት ዘመን ሳይጠፋ የቆየ ባሕል ነው።

ዳኘው የአሁኑ ልቅሶ የመድረስ ጉዞ በዚህ መልኩና በአርበኞች ማኅበር ቅርጽ አዋህዶ ስላየው፣ ልቡ በጣም ተነክቱዋል።

የሰርግና የልቅሶ ስንፉ የምኞት ዝክር ነው። የቤተ ዘመድ ወግ ማጥበቂያ ነው። ሰው ለዘመዱ እንባውን ሳያፈስ፣ ዘመዱን ሳይቀብር እህል ውሃ የማይቀምሰው፣ ከቤተ ዘመድ ሥርዓተ ማኅበር የተላለፈ ወግ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ አንድ ሰው የዘመድ እትብቱን እንዳይበጠስ ለመሳቢያም እንዲያገለግል፣ ይህን አለማድረግ በሰማይም በመሬትም የሚያስቀጣ ነው ተብሎ ይወሰዳል። አንድ ሰው የሞተበትን ዘመድ ሳይረዳ ቀርቶ እንባውን ሳያፈስ ቢቀር እስከ እርሙ በላ ይባላል።

አንድም ሰው ቃል ገብቶ ቃሉን ካፈረሰ እርሙን በላ ይባላል። በቃሉም ከፀና ሰው በሃሳብ ጽኑነቱ በመደሰት እርመኛ ነው ይለዋል። ዳኘውም እርመኛንና አርበኛን እንደ አንድ ነገር እንደሚመለከታቸው ሁሉ ሌላ የተቸገረ አርበኛ ለቅሶ አለመድረስም እርም መብላት ብሎ ይወስደዋል።

አስካለ ከነወታደሮቹዋ ብትራብም፣ ብትታረዝም፣ ብትንከራተትም፣ የተቻላትን ያህል እየተከላከለች ቆይታለች። አስካለ ከለገሠ ለቅሶ በኋላ ወደ ይፋት ለማምራት ስትነሳ የለገሠ እህት አማላጅ ቄስ ይዘው መጥተው፣ ወንድሜ ሌላ ዘር ስለሌለው ልጁን ስጪኝ ብለው ወጥረው ይዘዋት፣ እነሱም በዚህ ኑሮዋ ታስገድለዋለች ብለው መፍራታቸው ትክክለኛ መሆናቸውን አምና፣ ለልጁም ደህንነት ይህ እንደሚበጀው አውቃ፣ አልቅሳ፣ ስማ ሰጥታቸዋለች።

“ጦርነት ከሁሉ በላይ የሚያሰቃየው፣ የሚያዳሽቀው፣ ልብ የሚሠብረው እኛን ሴቶችን ነው።” ብላ አሰበች አስካለ። “እኛ ከልጆቻችን ጋር አብረን በሃሳብ ስንወድቅ፣

ስንሞት፣ ልጆቻችን ምንም ባይሆኑም መጥፎ ነገር ደርሶባቸዋል ብለን ስንጨነቅ፣ ከነሱ ይበልጥ እንሞታለን። ብቻ መሞት ምናለበት። ወንዶች ብቻቸውን ነው የሚሞቱት። እኛ ከመሞታችን በፊት በጭንቀት ልዩ ልዩ ዓይነት ሞቶችን እንሞታለን።" ብላ ተከዘች። አስካለ ከዚያ በኋላ በመታመሙዋ ህሊናዋን ብትስትም ወዲያው እንደዳነች የልጇዋ ሃሳብ መጥቶባት ሳትጨነቅ ያሳለፈችው ቀን አልነበረም።

አሁን ንብዋሻ የዘመድ አገር ስለሆነ ከዚያ ትንሽ ለማረፍ የምትችል ቢሆንም፣ ከሰው ቤት መግባቱ ግን እሱዋ ስትሄድ አስተናጋጆቹዋን እንዳያጠቁባት በመፍራት፣ ዋሻ ገብታለች። የትም ቦታ ይሁን ግን ሁልጊዜም በተጠንቀቅ መጠበቅ አለባት። በዚህ ዘመን ላይ፣ አብዛኛው የጣሊያን ጦር የአገር ተወላጅ ባንዳ እየሆነ በመሄዱ፣ ጥንት አብዛኛውን ኢጣሊያዊ ከነበረበት ዘመን ይልቅ በጥቆማ በኩል የተሳካለት እየሆነ መጥቱዋል። ከዚህም በላይ አስካለ በሴትነቱዋ የተነሳ ዝርፊያን፣ ቅሚያን ስለምትከለክል ከደረሰባት ችግርም ሌላ አውቆ የሚሰጣት እምብዛም የለም።

ለገሥ ቢሰጡት ይቀበላል፣ ባይሰጡት አስፈላጊ ከሆነ ያስገድዳል። ደግሞም ሲጠይቅ ስለሚፈሩት በእሺታ ሰጥተው ምስጋናቸውንና ለኢትዮጵያ፣ ለሃይማኖታቸው፣ ለነፃነታቸው ያለባቸውን ግዴታ አዳምጠው ይሰነባበታሉ። አስካለ ይህ አይሆንላትም። አብረዋት ያሉት አርበኞች ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም የዕለት በዕለት ችግሩዋ ግን ብዙ ሳሉም ከነበረው እየባሰ ሄዱዋል።

"አስካልዬ......." ይላታል አዝብጤ ብቻቸውን የሆኑ ጊዜ፣ "ሴት ልጅ ብቻዋን መሪ ሆና አትዘልቅም። ወታደሮችሽ ደግሞ ምን ቢመጣ ካንቺ ለመለየት አይፈልጉም።"

ድንግርግር የሚለው ፊቱን ታይና እያዘነችለትም፣ "ምን ለማለት ፈልገህ ነው? አንተ እኮ ይሉኝታ የለህም።" ትለዋለች።

"አስካልዬ አትቀየሚኝ። አድምጭኝ። በጦርነት ጊዜ የምናደርጋቸውን በሰላሙ ጊዜ እናደርጋቸው ነበር? ነጥቀን እንበላ ነበር? የማናውቀውን፣ አይተነው የማናውቀውን ሰው እንገድል ነበር? ደግሞስ እንደዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ እናይ፣ እንሰማ፣ እናረጅ ነበር?"

"ታዲያስ?"

"ተይው አስካልዬ።" ይልና ጨዋታውን ይቀይራል።

በዚህ ዓይነት ስቃይ ኑሮ አንድ ቀን ከዋሻዋ ውስጥ ሆና ከወታደሮቹዋ ጋር ስትጫወት ሳቆቴ እየሮጠች መጥታ "ተከበናል አስካልዬ!" አለቻት። ከዚያም ሳቆቴ ራሱዋን በሁለት እጆቹዋ ይዛ ቁጢጥ ብላ ተቀምጣ ምጥ እንደያዛት ሴት እየተወራጨች "አስካልዬ!" ትል ጀመር። ለአስካለ እንደተጨነቀች ግልጽ ነበር።

አስካለም ፈርታለች። ግን ፍራቱዋን እንደሱዋ ማሳየት አትችልም። ፍራቱዋን ዋጥ አድርጋ፣ እንደ ድንጋይ በደነዘዙ እግሮቹዋ እየተራመደች፣ የሙዋች ባሉዋ ጠበንጃ

የተሰቀለበት ግድግዳ ዘንድ ተጠጋች። ወንዶቹም ከተቀመጡበት ቦታ እየተነሱ ጠበንጃዎቻቸውን አቀባበሉ። የዋሻው በራፎች በጠበንጃ አፈሙዝ ተዘጉ።

“እንደምን ዋሉ ወይዘሮ አስካለ። ወገኖች ነን።” አለ ዳኘው ቶሎ መናገር እንዳለበት አንድ ነገር ተሰምቶት። የአስካለ ቃፊር የነበረውም ተክለወልድ ከውጭ ወደ ዋሻው እየገባ “እትዬ፣ አቶ ዳኘው ናቸው። ለቅሶ ለመድረስ መጥተው ነው።” አለ።

“ታዲያ ሰው ያስባል፣ ይደነግጣል ብለህ አታስብም? ማስጠንቀቂያ ቀድመህ ብትሰጠን ምን አለ?” አለች።

ተክለወልድም በሁኔታውም፣ በአረፉበት ብዙ ዓይኖችም ጭምር ጥፋተኛነቱ እንደተሰማው በሚያሳይ ገጽታ አቀርቅሮ “ላስገባቸው?” ሲል ጠየቀ፣ እኔው ያመጣሁትን እኔው እመልሰዋለሁ የሚል ቁርጠኝነትም እየተነበበበት።

ዳኘው ከጥቂት ሰዎች ጋር ወደ ዋሻው ውስጥ ገብቶ ከሰላምታ መለዋወጥ በኋላ ተቀመጠ። ዙሪያ ከቡን አስተውሎ ዓይኑ ከአስካለ ላይ አረፈ። ለመስተንግዶ ቦታው ስለአለመመቸቱ አስካለ የተሰማትን ጭንቀት ተመልክቶ ፈጠን በማለት “የደረሰበዎትን አደጋ ሰምተን ሁላችንም አዘን።.... እኛ ሞተን በቁማችን ተዝካራችንን ያወጣን ስለሆነ ብዙም ማዘን አይገባም። አቶ ለገሠን የመሠለ ጀግና ማጣት እጦቱ የሚሰማው ሰመላው አገሪቱ ነው።” አለ።

“እሱማ ነው። ....... . እኔ አንጀቴ አልችል አለ እንጂ።” አለች እንባ ያቀረሩ ዓይኖቹዋን ወደ መሬት ደፍታ።

“አቶ ለገሥ ከሞቱ ዓመት ሆናቸው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ለቅሶ ለመድረስ ሁሉም አርበኛ አልቻለም። በተለይ ወደዚህ መምጣትዎን ስንሰማ አርበኞች በሙሉ ደስ ነው ያለን። ”

“አዎን እርግጥ ነው፣” አለ ሌላው ከዳኘው ጋር የመጣ አርበኛ። “እርሰዎን የመሰለ ጀግና በሚቸገርበት ጊዜ ሁላችንም ከጐንዎ ብንገኝ ክብር አድርገን ነው የምንቆጥረው።”

ከትንሽ ጊዜ ማስተዛዘን በኋላ ዳኘው ከሱ የአርበኞች ክፍል ለጀግናው ልጅ ማሳደጊያ በስጦታ የተበረከተች ላም ይዞ መምጣቱን፣ እሱም አንድ ዳውላ እህል ስላመጣ ተቀባይ እንዲደረግለት ጠየቀ።

አስካለ ስሜቱዋ ተነክቶ አይኖቹዋ እንባ አቀረሩ። ከአርበኝነት ዘመኑዋ በፊት እንዲህ ዓይነት መተሳሰብ በማይተዋወቁ ሰዎች መሃል ያለ አይመስላትም ነበር። አስካለ አፍንጫዋን ጠረገችና፣” አመሰግናለሁ። እግዜር ይስጥልኝ።” አለች።

አስካለ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቡና እያፈላች ነበር። ሳቆቴ ደክሞኛል ስላለች አስካለ ቡናውን ታፈላ ነበር። ከሳሲት አንድ ዘመዱዋ አምጥቶ ስጥቱዋት ይዛው ከአገር አገር ስትዞር ነበር።

ቡናው እንዳይገነፍል መክለሊቱን ገርበብ ስታደርግ ዳኘው ተመለከታት። ሁልጊዜም ሲያስደንቀው የሚኖረውን ባሕሪዋን ከዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ አየው። በጦርነት ቦታ እንደ ወንድ ፍራት አይሰማትም፣ ጠንካራ ስለሆነች የሴት የጦር አዝማች ናት የሚባልላት አስካለ፣ በቤት ውስጥ አንገቱዋን የደፋችና ዘገምተኛ ስለሆነች ወድቃ የምትነሳ አትመስልም። በሕይወቱዋ ውስጥ የሚያልፉት የወኔ ወቅቶች በባሕሪዋ ላይ ማኅተም ትተው አያልፉም። በመልኩዋና በጨዋታዋ የጦርነት ሰው መሆኑዋ፣ ብዙ የጦር ሜዳ ማወቁዋ አይታይም። እሱዋም ስለዚህ ማውራት ቀርቶ ልዩ በሆነ ባሕሪ ይህ ዓይነቱ ጨዋታ በፊቱዋ እንዳይነሳ ለማድረግ ትችላለች።

ዳኘው አንጀቱ ተንሰፈሰፈ። በጣም አዘነላትና ችግርና መከራ በእርሱዋ ላይ መድረስ እንደሌለባቸው በመመራመር ከእግዚአብሔር ጋር ከመጋፋቱም ሌላ ችግርና መከራ ያመጣባትን የጋራ ጠላታቸውን ይበልጥ ጠላው።

"የገጠ ጦርነት ጊዜ ተገናኝተን ነበር። ታደሰ አስተዋውቆን ነበር።" አለ።

አስካለም ከራስ አበበ ጋር ከሰላሌ መልስ መጀመሪያ መንዝ ሲደርሱ ስንቅ ይዞ መጥቶ ያስተናገደችው መሆኑ ትዝ አላት። ከራስ አበበም ጋር ጥሩ መግባባት እንዳለቸው የሰማችው ትዝ አላት። አንድ ትንሽ ነገር ብዙ ነገሮችን አስታወሳት። "አዎን እኔም ስለርሰዎ ብዙ ሰምቻለሁ። የዚያን ዕለትም ለገሥ ብዙ ስለርሰዎ አጫውቶኛል፣" አለች። ለገሥ ጭብጦውን ያመጣውን ሰው እያሳያት ጥሩ መትረየስ ተኳሽ ነው ይባላል። ክብር ዘበኛ ነበር ያላት ትዝ ብሎዋት።

ቡናው ደርሶ ዳኘው ቢቸሪውን እየተመለከተ ፉት ሲል፣ አስካለም በተራዋ ተመለከተችው። እግሮቹ ብቻ ሳይሆኑ ፊቱም ቀጭን ረጅም ሆኖ፣ ያፍንጫው ጫፍ ወደላይ ነሳ ያለ ነው። ይህ የአፍንጫው ቅርጽ በቀላሉ በደል የሚረሳና ሊታለል የሚችል ሰው ያስመስለዋል። የዋህ ዓይነት መልክ ሰጥቶታል። በሽፋሎቹ መሃል የተኮሳተረው ግንባሩ ካፍንጫው ጋር ሲተያይ ጭካኔው እራሱ ለራሱ የሰጠው ሽፋን ይመስላል። የገበሬና የድሀ አስተዳደጉ አሁንም ካለቦታው ተዝናንቶ መደባለቅ አለመቻልን ትቶበታል። ዓይኖቹ በርበሬ ስለሚመስሉ ለአጠቃላይ ሰውነቱ ግርማ ሞገስ ሰጥተውታል። አስካለ ሰው ሁሉ ከሚያወራውና በወሬ ከሰማቸው በላይ የዳኘውን ጠባይ ገመተችው።

ዳኘውን ስትሰናበተው አስካለ "ለጦር ጓደኞችዎ እግዜር ይስጥልኝ። ምን አሳሰባችሁ። የኢትዮጵያ አምላክ ብድራችሁን ይክፈልልኝ።

እርሰዎንም አመስግናለሁ።" አለች በሀዘን ፈገግ ብላ።

"እግዚአብሔር ያጽናዎት! ይበርቱ!" ሲል በጎረደፈ ድምጹ ዓይኑን ሰበር አድርጎ ተናገራት። ለገሥ ከሞተ ሦስት ቀን የሆነው ያህል ሁኔታውን አቅርቦ። ከዚያም "ታደሰና ፋናዬ ሰላምታ አቅርብልን። መጥተው ይጠይቁን በልልን ብለውኛል።" አለ።

"ፋናዬ ተሻላት? አቶ ታደሰ ደህና ነው? ለሁለቱም ሰላምታዬን ያቅርቡልኝ።" አለች አስካለ ተከዝ ብላ።

"መቼ መጥተው ይጠይቁአቸዋል?" አለ ዳኘው።

"እመጣለሁ።" አለች አስካለ በደፈናው ከሩቅ እንደሚናገር ሰው። ዳኘው መንገዱን ከጓደኞቹ ጋር ሳያወራ በሃሳብ ተውጦ ሳያውቀው አጋመሰው።

አስካለ ወደ ዋሻው እንደተመለሰች ሳቆቴ በፈገግታ ተቀበለቻት። "አስካልዬ ይህን ሰው አግቢው። ጎበዝ ነው። መልከ ቀና ነው። ጀግና ነው።"

"ለምን ትቀባጥሪያለሽ? አማላጅ የተላክሽ አትመስይም?"

"አትቆጭ አስካልዬ። አክስቶችሽም፣ ዘመዶችሽም የተዳሩት የቤተ ዘመድ ማጠናከሪያ ሆነው እንጂ ወደው አይደለም። አንቺም ለአርበኞችሽ ስትይ ለገሡ ያለሽን ጠብቀሽ አግቢ። "

ከመቅጽበት የአዝብጤ፣ የሳቆቴ ንግግርና ዳኘው ዘንድ ያሉት የፋናዬና የታደሰ ሁኔታዎች ከፊቱዋ ተደቀኑ።

ወደ ምድጃው ተመልሳ አመዱን በስንጥር እየጫጫረች አስካለ ተከዘች።

⅄ ⅄ ⅄

# የጠላት ዕርቅ

የኢጣሊያ መንግሥት አርበኞችን ለመደምሰስ ባለመቻሉ ብቻ ሳይሆን፣ የዓለም ጦርነት ሂደት ባስከተለው ለውጥ፣ ለጊዜው ለአርበኞች ብዙ ነገር ለቆ፣ ከስምምነት ለመድረስ ፖለቲካዊ ውሳኔ አደረገ። አርበኞች እጃቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ የማይቻል መሆኑ ተደጋግመው በተደረጉት ሙከራዎች ታውቂዋል። ከዚህ ቀደምም ለእያንዳንዱ የአርበኞች መሪ ከጣሊያን ዘንድ እንዲገቡ፣ ወደሱም ቢገቡ ምንም ጉዳት እንደማይደርስባቸው፣ ደጋግሞ ደብዳቤ ጽፎ ጥሩ መልስ አላገኘም። አርበኞቹ ምናልባት እጃቸንን ብንሰጥ ጉዳት ይደርስብናል ብለው ቃሉን ሳያምኑት ቀርተው ነው ብሎ፣ በእግዚአብሔር ስም እየተገዘተ፣ ለእሱ ያደሩ ጳጳሳትን ፊርማና ማረጋገጫ እያከለም ጽፉዋል። ጣሊያን ከአርበኞች ያገኘው ምላሽ ግን ትንሽ አዘናግተውት ከዚያም ጥቃትና ውርደት ነው።

ጣሊያን ከራስ አበበ አረጋይ ጋር እርቅ ለማድረግ ሲነሳ ብዙ የሚያጉዋጉ ነገሮችን መስጠት እንዳለበት ተረድቱዋል። ስለዚህም የሸዋው ዋና አስተዳዳሪ ጄነራል ናዚ አርበኞች ጦርነትን ቢያቆሙ፣ አሁን ከያዙት ክልል ሌላ፣ በአካባቢያቸው ያሉ የኢጣሊያ ምሽጎች ሁሉ ለነሱ እንደሚለቀቁ፣ በውስጥ አስተዳደራቸውም ጣልቃ እንደማይገባ፣ በመግለጽ የእርቅ ድርድር ጠየቀ። አርበኞችም ይህን እንዲቀበሉ ለማድረግ በየጊዜው ትላልቅ የማስፈራሪያ ዘመቻዎችን ቀጠለ።

አርበኞችም ተደጋግሞ በደረሰባቸው ጦርነት፣ በረሃብና በበሽታ ተጉላልተው ስለነበር ይህን ሁኔታ እስኪወጡት ድረስና የጣሊያንን ምሽጎች ከተረከቡና ሰፋፊ ግዛቶች ከያዙም ለወደፊቱ ትግላቸው የሚኖረውን ጥቅም በማሰብ ፈቃደኛ ሆኑ። ራስ አበበ ሰሞኑን ጅቡቲ ከሚገኘው የውስጥ አርበኛቸው የዓለም ጦርነቱ ሚዛን ወደ እንግሊዝና አጋሮቹዋ እያደላ ስለመሆኑ፣ ወደፊትም የውጭ አገር ዕርዳታ ለማግኘት ተስፋ እንዳለ ገልጾ ጽፎላቸው ነበር።

"የኢጣሊያ መንግሥት ይህን ያህል ሞኝ አይደለም። በዙሪያችን ያለውን ምሽጉን ሰጥቶን ፋታ የሚሰጠን ወዶ አይደለም። ተቸግሮ ነው። ነገር ግን በዚያው መጠን ያጠመደልን ወጥመድ ይኖራል። መጀመሪያ እሱ ያሰበልን ወጥመድ ምን እንደሆነ እንወያይ።" አሉ ራስ የጦር አዛዦች ስብሰባን ሲያኪያሂዱ።

"ከውስጥ አርበኞች በተገኘው ወሬ መሠረት፣ የኢጣሊያ መንግሥትን የእንግሊዝ መንግሥት ሊወጋው ስለሆነ፣ የወታደር ኃይሉን ወደዚያ ግንባር ለማዞር ይፈልጋል። በዚህን ጊዜ እኛ ሰላም ከሰጠነው እንግሊዝን ካሸነፈ ፊቱን እንደገና ወደ እኛ ያዞራል።" አሉ ደኛዝማች ዘውዴ አፋቸውን ያዝ እያደረጋቸው።

"ይህማ ከሆነ ለምን ፋታ እንሰጠዋለን። አስጨንቀን መያዝ ነው እንጂ።" አለ ሌላ የጦር አዛዥ።

"ጣሊያን የእንግሊዝን መንግሥት አያሸንፍም። የእንግሊዝን መንግሥት አሸናፊነት ካመንን፣ ማድረግ የሚገባን፣ በአሁኑ ሁኔታ ተጠቅመን ኃይላችንን አጠናክረን መገኘትና ጣሊያን በእንግሊዝ ድል በሚሆንበት ጊዜ ነፃነታችንን ማስመለስ ነው።" አለ ወጣቱ ቀኛዝማች ደምሴ ወልደ አማኑኤል። ራስ አበበ ለተከታዮቻቸው ሹመት ሲሰጡ እሱንም ቀኛዝማች ብለውታል።

"ጣሊያንስ ካሸነፈ?" አለ ሌላ የጦር አዛዥ። ነገሩ ለውሳኔ አስቸጋሪ መሆኑ የገባው ስለሆነ ጥያቄውን ያቀረበው የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቶ ማብራሪያ ለማግኘት ነው።

"ጣሊያንማ ይህን ዓይነት የመደራደሪያ ሃሳብ ያቀረበልን አሸነፋለሁ ብሎ በማሰብ ነው። የጀርመን ጦር ሰሜን አፍሪካን እያጥለቀለቀ ስለሆነ፣ ይህ የልብ ልብ ሰጥቶት ነው። በታሪክ እንደታየው ግን እንግሊዝ መጀመሪያ የተሸነፈች ብትመስልም የኋላ ኋላ ግን አሸናፊ ትሆናለች።" አለ ቀኛዝማች ደምሴ። "ከእንግሊዝ ጋር አብረው የተሰለፉት ፈረንሳይና

ሩሲያም ቢሆኑ ቀላል መንግሥታት አይደሉም። ወደፊት ደግሞ አሜሪካንም እንግሊዝን መደገፉዋ አይቀርም። እንግሊዝና አሜሪካ በቋንቋና በባሕል አንድ ናቸው።"

ራስ አበበ ከየጦር አዛዦቹ የሚሰነዘረውን ሃሳብ ካዳመጡ በኋላ "ለጊዜው በቅድሚያ ምሽጎቹን ተረክበን ድርድሩን ብንጀምርና ከዚያም በየጊዜው የጣሊያንን ሴራ እየተከታተልን ብናከሽፍ የሚሻል ይመስለኛል።" አሉ።

"አይሆንም ጌታዬ። በኛ በኩል ሃሳባችን ለአገራችን ነፃነት የማያወላውል ቢሆንም፣ በባላገሩ ሕዝብ ዘንድና በሩቅ በሚገኙ አርበኞች ዘንድ የእርቅ ነገር መነሳቱ፣ ልባቸው እንዲዋልል፣ ተስፋ እንዲቆርጡ፣ ካለዚያም እኛን እንዲያወግዙ ያደርጋቸዋል።" አለ ሌላ የጦር አዛዥ።

"ልክ ነህ ጌታዬ። ይህ አይደርስም አይባልም። እኛ ግን ቀኛዝማች ደምሴን ጣሊያን ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር እንዲፈቅድ ግዴታ አስገብተን ለጦር አዛዦች በምስጢር ስለ ሁኔታው እንዲነግራቸው ልናደርግ እንችላለን። ትንሽ ቅሬታ ቢፈጥርም በጊዜ ውስጥ ሊፈታ ይችላል።" አሉ ራስ ነገሩ እየከነከናቸው፣ እያስጨነቃቸው።

"ጣሊያን ይህንን ይፈቅዳል?" አሉ ደጃዝማች።

"የቸገረው ሃሳቡ እንዲሟላለት የማያደርገው የለም።" አለ ቀኛዝማች ደምሴ።

የዚያን ሰሞን፣ አከታትሎ በተደረጉ ስብሰባዎች፣ አርበኞች የኢጣሊያ ምሽጎችን ተረክበው፣ ድርድር ለመጀመር ፈቃደኛ ሆነው፣ የእርቅ ድርድርና የተኩስ አቁም ስምምነት ጀመረ። ጄነራል ናዚም ምሽጎችን ለማስረከብ የተኩስ አቁሙን ስምምነት በትክክል ለማክበር እንዲቻል፣ በራስ ማኅበር ሥር በየቦታው ያሉ አርበኞች ዝርዝር እንዲሰጠው በመልዕክተኛው በሜጀር ሎኮቲ በኩል ጠየቀ። ጄነራል ናዚ ከፈለው ወልደፃዲቅ ከራስ ማኅበር ውስጥ እንደሌለ ስለሚያውቅ፣ የከፈለው ስም ዝርዝሩ ውስጥ እንደማይኖር ገብቶታል። ይህንን ግን በግልጽ በማንሳት ፈንታ በሌላ አቅጣጫ አደረገው። የራስም ጦር፣ የናዚን ተንኮል ሳያውቅ፣ የማኅበርተኞቹን ስም ሰጠ። የራስ አበበ ተወካይ በመሆንም ወጣቱ ቀኛዝማች ደምሴ ወልደ አማኑኤል ወደ ደብረ ብርሃን ወጣ። ጀነራል ናዚም በዝርዝሩ ውስጥ የከፈለው ስም አለመኖሩ በጣም ደስ አለው። ከራስ አበበ ደብዳቤ ዝርዝር ውስጥ የዳኘው ቢኖርም ይህ ለሥራውና ለዓላማው እንቅፋት አይሆንበትም። እንግዲህ መላ ኃይሉን በከፈለው ላይ አድርጎ ይደመስሰዋል። ከዚያም የኢጣሊያ ጦር ፊቱን ወደ ዓለም ጦርነት ሲያዞር የተዳከመ የአርበኛ ኃይል ከሁዋላው ጥሎ ይሄዳል። ጀነራል ናዚ ይህን ደስታውን በሚያከብርበት ጊዜ የራስ አበበን ጦር ገለልተኝነት ለማረጋገጥ፣ በአካባቢው ከነበሩት ምሽጎች ውስጥ የነበሩትን ወታደሮቹን ከሞላሌና ከደብረ ብርሃን ምሽግ ጋር አዳበላቸው። ሃሰቡንም ለጀነራል ግራዚያኒ አማክሮ በከፈለው ላይ ለሚደረገው ዘመቻ የሰላሌና የወረኢሉ ጦር አብሮ እንዲዘምት አስፈቀደ።

የኢጣሊያ ጦር በአምስት አቅጣጫ ወደ ቋች ተነቃነቀ። ከሞላሌ የተነሳው በላሎ ምድር በኩል፣ ከወረኢሉ የተነሳው በቃያ ገብርኤል፣ ከሰላሌ የተነሳው አዳባይ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ወንዝ ወንዙን ወደ ላይ ሲያቀና ከአዲስ አበባ የተነሳው በጅሩ በኩል፣ የደብረ ብርሃኑ በወግዳ አድርጎ ተጉዋዘ። በትንሽ ቀናት ውስጥ ቋች አካባቢ በሁሉም አቅጣጫ ታጠረ።

ራስ አበበ፣ በከፈለው ላይ የተቃጣውን ወረራ እንደሰሙ፣ ቀኛዝማች ደምሴ ወልደ አማኑኤል ከፈለውንና የጦር አዛዦቹን በማነጋገር፣ እነሱም እርቁን እንዲቀበሉና ለጊዜው እረፍት እንዲያደርጉ እንዲያግባባ መልዕክተኛቸውን ላኩ። ቀኛዝማች ደምሴም ይህንኑ ለማድረግ ከደብረ ብርሃን ወደ ሰላድንጋይ ገሠገሠ።

የከፈለውና የጦር አዛዦቹ በዚህን ጊዜ በከበባ ውስጥ መሆናቸውን ከአዲስ አበባ የውስጥ አርበኞች ከዳኘው ጓደኛ፣ ከተክለሃይማኖት፣ ሰምተው፣ የሠፈሩበትን አገር ሕዝብ ሰብስበው በአጣዳፊ መመሪያ እየሰጡ ነበር። ዳኘው የሰበሰባቸውን ሰዎች በቅሬታ ፈገግታ ትንሽ ተመለከታቸውና ከዚያም እስካሁን ድረስ ለአርበኞች ያደረጉትን ውለታ ታየውና ተከዘ። በመጨረሻም የትውልድ መንደሩን ሽማግሌና ሕፃናት የፈዘዙ ዓይኖች ተመለከተና እንባው መጣ። እንባውን ግን ዋጥ አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ። “እስካሁን ለእኛና ለአገራችሁ ብዙ መስዋዕትነት ከፈላችሁ። ዛሬ ደግሞ በትልቅ ችግር ውስጥ አብራችሁን ወድቃችኋል። ” አለ። ለእነሱ በግል ያደርጉትና ለአገራቸው የከፈሉት መስዋዕትነት ሁሉ ለግል ለራሱ የተደረገ ያህል ከብዶት። “ችግርን ግን ከተባበርን እናልፈዋለን። የኢጣሊያ ጦር ከዚች አገር ውስጥ ሲገባ፣ ከዚያም ከመሃከላችሁ ብዙዎቻችሁን አስሮ ሲመረምር፣ በአንድ ቃል እንደ አንድ ሰው ከተናገራችሁ አትጎዱም። ስለ እኛ ሲጠይቁዋችሁ ሳትወዱ፣ አስገድደናችሁ፣ በሬአችሁን እያረድን፣ እህላችሁን እየቀማን፣ ሚስቶቻችሁን እየደፈርን፣ ሳትወዱ በግድ እንዳኖራችሁን በአንድ ቃል ተናገሩ። አሁን ግን ሃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ነፃ እንዳወጣችሁ አድርጋችሁ ይህንኑ አስጠኑዋቸው። ከዚህ ውጭ ማድረግ ግን በአገራችን ነፃነት ተጋድሎ ላይ ማመጽ ስለሆነ ተመልሰን ስንመጣ አጥፊውን አይቀጡ ቅጣት እንቀጣለን።” አለና ዝም፣ ፀጥ አለ።

የዚህን ሃሳብ ጠቃሚነት ሽማግሌዎች እየተነሱ ከምስጋና ጋር አቀረቡ። ሕዝቡም በደስታ ተቀበለው። በሁሉም ስብሰባ ቦታዎች ይህ ከተከናወነ በኋላ የጦር አዘዦች ስብሰባ ተደረገ።

“እስቲ አንዳንድ ሃሳብ ሠንዝሩ።” አለ ከፈለው ፊቱም፣ ፈገግታውም፣ መላ ሰውነቱ ሞትን መናቁን እየተናገረ።

“ከገደሉ ላይ ካለው ዋሻ ውስጥ ገብተን በሩን አጥረን ይዘን ጠላት እስኪሰለቸው ብንዋጋ ይሻላል እላለሁ።” አለ አንድ የጦር አዘዥ የጦርነት ሽታው እያቅበጠበጠው።

“አይሆንም፣” አለ ዳኘው። “ከአንድ ዋሻ ውስጥ ታጉረን፣ ተዋግተን ሳይሆን በራብና በውሃ ጥም እንሞታለን። ይልቁንስ በወረኢሉው ጦርና በሞላሌው ጦር መሃከል ያለው በጠላት ወታደሮች የታጠረ ቢሆንም የቦታው አቀማመጥ በኃይል ወጣ ገባ የበዛበት ስለሆነ

በድንገት ሳይታሰብ ደርሰን በተኩስ አደባልቀነው፣ የሞተው ሞቶ፣ ጢሻ ለጢሻ አፍቀራ እንገባለን። አፍቀራ ከገባን ከበባው መጣሱ ብቻ ሳይሆን ያለችውን መግቢያ በር ቀድመን ከያዝን እንኳን ጣሊያን ሰይጣንም አያጠቃን።”

“ከበባውን ስንጥስ ምን ያህል ሰዎች እንተርፋለን?” አለ አንዱ በማሾፍ መልክ። ሞትን ብዙ ጊዜ ስለተፋጠጡት ይቀልዱበታል።

“ተጋድሎውን ለመቀጠል እምንችል ያህል።” አለ ሌላው ጥቂትም ቢሆኑ እያደር እንደሚበዙ ከቀደምት ልምዱ አውቆት።

“ውሳኔ ላይ መድረስ አለብን።” አለ ከፈለው ጊዜው ለቀልድ ፋታ የሚሰጥ አለመሆኑን ለመጠቆም።

“የዚህን አገር መውጫ መግቢያ ቀዳዳውን የሚያቅ ዳኘው ነው። እሱ ነበር ከዚህ እረኛ ሆኖም፣ ገበሬ ሆኖም ይኖር የነበረ። እኛ የምናውቀው አካባቢ ሌላ ሌላውን ያደግንበትን ነው።” አለ ሌላው።

“ልክ ነው፣” አሉ ብዙ ድምጾች ይህንን በሚመለከት ዳኘው ያለውን ችሎታ ብዙ ጊዜ አስመስክሩዋል።

በአምስቱም አቅጣጫ የኢጣሊያ ጦር ቋችን በዓይን ለማየት በደረሰበት ጊዜ አርበኞቹ አይታዩም ነበር። ብዙው ሕዝብ ግን የኢጣሊያ መንግሥትን ገናናነት በማውካት ወደ ኢጣሊያ ጦር እየተጠጋ ነበር። ሌሊቱን ሙሉ የጭንቀትና የጥበት ወቅት ነበር። የኢጣሊያ ጦር የያዛቸውን ሰላማዊ ሰዎች በመግረፍ ቢመረምርም ከሁሉም ያገኘው ቃል አርበኞቹን የሚያወግዝ ግን ወዴት እንደሄዱ የማያውቅ ነበር።

በበነገታው ላይ ሊነጋጋ ሲል ባልታሰበ ጊዜ የአርበኞች ኃይል ሙሉ በሙሉ በታሰበው ቦታ ላይ በድንገት ደርሶ በዚያ የነበረውን የጠላት ኃይል በቦንብና በጥይት አተራምሶ አልፎ አፍቀራ ገባ። ከአርበኞች መሃል የሞተ ሰው አልነበረም። የአርበኛው ጦር በድንገት ብቅ ብሎ፣ እንደ አጥር የሆነውን ጦር አተራምሶ፣ ከዚያም ከትንሽ ዥረት፣ ከዚያም ከሩቅ ተራራ፣ ከዚያም ከአፍቀራ ሲገባ ብቻ ታየ።

ጀነራል ናዚም ይህን ሲሰማ በጣም ተበሳጨ። አብዛኛው ጦሩ አንድም ጥይት አልተኮሰ። አንዱም ክፍለ ጦር ጦርነት አላደረገም። አንድም የተደመሰሰ ሽፍታ የለም። ቀኛዝማች ደምሴም በመጣደፍ ሰላድንጋይ እንደደረሰ ከኢጣሊያ ባለ ሥልጣኖች የሰማው ይህንኑ ነበር።

“አይ ከፈለው!” አለ ደምሴ የራሱን ተከታዮች በፈገግታ እየተመለከተ።

“ምን አለ? ምን አለ?” ሲል ኢጣሊያዊው አዛዥ አስተርጎሚውን ጠቀው።

“ሾላካ ነው!” አለ የቀኛዝማች ደምሴ ተከታይ። በእነዚህ ቃላት ደምሴና እሱ ጠላት የሚሉትን ሳይሰማ ከፈለውን እያደነቁት ነበር።

ኢጣሊያዊው ከአስተርጓሚው እነ ቀኛዝማች ደምሴ ያሉትን በቅኔው ሳይሆን፣ በግርድፉ ሰምቶት፣ ሊያጽናናቸው እንደሚፈልግ ሰው "የትም አያመልጥም፣ ይደመሰሳል። " አለ።

"እኔ የመጣሁት ከፈለው እርቁን እንዲቀበል ለማድረግ ለማግባባት ነበር። አሁንም ቢሆን መልዕክተኛ ልኬበት መጥቶ ቢያነጋግረን ይሻላል።" አለ ወጣቱ ቀኛዝማች።

"ጥሩ! ጥሩ!" አለ ጣሊያኑ። እንደመስሰዋለን ፕሮፓጋንዳ እንጂ ፖለቲካ እንዳልሆነ ይገባዋል። ቀኛዝማች ደምሴም ለከፈለው ደብዳቤ ጽፎ፣ በቃል የሚነገረውን ለመልዕክተኛው አስጠንቶ፣ መልዕክተኛውን ላከ።

የከፈለው ጦር ራስ አበበ የእርቅ ድርድር ከጀመሩ ጀምሮ ተደጋጋሚ ጥቃት የደረሰበት ሲሆን፣ ይኸኛው ግን ለህልውናውም በጣም አስጊ ስለነበር በራስ አበበ ላይ ያለውን ቅሬታ አባባሰበት። በተለይ እነከፈለው የእርቁን ድርድር ዓላማ ምን እንደሆነ በግልጽ ስለማያቁት፣ ለጣሊያን ባንዳነት አድርገው ወስደውታል። ከፈለውም ጭራሹንም ለራስ አበበ የዚያን ጊዜ መሸሹ ትክክል አለመሆኑ ተሰምቶታል። 1932 ከፈለው በሥልጣኑ ከፍ እያለ፣ እየተደላደለ የሄደበት ወቅት ነው። ግዛቸው ኃይሌ ከሞተ በኋላ እሱ የመንዝ አርበኞች ተጠሪ ሁኑዋል። ይህ ጦርነት ሳይመጣ በፊት የመንዝ አስተዳዳሪነት ሊያገኝ ቀርቶ ሊያልመውም አይደፍር ነበር። ተራ ገበሬ ሆኖ ይቀር ነበር። ዛሬ ግን ንጉሥ ባይሾመውም ገዥነቱ ተረጋግጡዋል። የንጉሥ አገረ ገዥ የሱን ያህል ባይወደድም፣ ይከበር ይፈራ እንደነበረው ሁሉ ከፈለውም ይከበራል፣ ይፈራል። ጌታዬ ብሎ እጅ የማይነሳው የለም። በሱም ገጽታ ላይ አካባቢን በንቀት መመልከት የሚያመጣው የሹም ግርማ ሞገስ ሰፍኖበታል። እሱም ጣሊያኖችን ከምሽጋቸው እንዳይወጡ አድርጎ ይዞ ነበር። ዛሬ ግን በአካባቢው ያሉት አርበኞች ከጣሊያን ጋር ተስማምተው ምሽግ ሲረከቡ በሱ ጦር ላይ የተደረገው ከበባ አስከፍቶታል። ራስ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ ናቸው።

አዝማሪው መስንቆውን ቃኘና፣ የአካባቢው ሰው ጆሮውን እንዲሰጠው ጭራውን እየከረከረ፣ በዓይኑና በአፉ ፈገግ ብሎ፣ ተራ በተራ ሰዎቹን ተመለከተና። ታረቁ ይላሉ አበበ አረጋው፣ እርቁን የሚያፈሰው ማን ይሆን ዳኛው። አለ ራስ የሚለውን የክብር ስማቸውን ገፉአቸው።

ከፈለው ሳቅ አለና አፉን ወደ ጎን ጠመም አድርጎ ትንሽ ቆየና "ጣሊያንና ኢትዮጵያ ሲታረቁ በገለልተኝነት ዳኝነቱን ጀነራል ናዚ ያያላ!" አለ። መጀመሪያ አንዳንዶቹ ከዚያ ሁሉም ሳቁ።

"ብድር መመለሳቸው ይሆናል! እሚያደርጉት ቢያጡ ከጠላት ተዋውለው ሊያስጠፉን አስበው ነው!" አለ ሌላው፣ የራስ አበበን ሁኔታ በዚህም በዚያም ቢያዞረው አልገባ ብሎት።

ምንም እንኳን የራስ አበበ የእርቅ ድርድር፣ ሰዎች አሁን ከዚህ

እንደሚያወሩት፣ ባንዳነት እንዳልሆነ፣ ቢጠረጥርም፣ ዳኘው ጥርጣሬውን ይፋ አውጥቶ ሊያወራ አይችልም። እሱ ቢናገር አያምርበትም። አርበኞቹ ስለዚህ ሁኔታ ሲወያዩ ከቃፊሮች መሃል አንዱ ከአንድ ሰው ጋር መጣ። በእድሜያቸው ሸምገል ያሉ ሰው ናቸው። “የቀኛዝማች ደምሴ መልዕክተኛ፣” ሲል ቃፊሩ አስተዋወቀ።

መልዕክተኛው እጅ ነሱና የመጡበትን ጉዳይ ከተናገሩ በኋላ ለልጅ ከፈለው ደብዳቤውን ሰጡና “ለጦር አዛዦች የሚነገር የቃል መልዕክትም አለኝ።” አሉ።

“እሺ አረፍ ይበሉ።” አለ ከፈለው ደብዳቤውን እየዘረጋ። ደብዳቤው ላይ የተፃፈው ቃል ከኢጣሊያ ጋር እርቅ ማድረጉ ጠቃሚ ስለመሆኑና የኢጣሊያ መንግሥት ሊፈጽማቸው ቃል ስለተገባላቸው ጉዳዮች የሚያብራራ ነበር። የጦር አዛዦች ስብሰባ ተደርጎ መልዕክተኛው በቃል እንዳስረዱት ደግሞ የደከሙት ከብቶች እስኪያገግሙ፣ አርበኛው በስንቅና በትጥቁ እስኪጠናከር፣ እረፍት ለማግኘትና በድርድር ጊዜ ሰፋፊ ክልሎችን በቁጥጥር ሥር ማዋሉ ለወደፊቱ ተጋድሎ ጠቃሚነት ስላለው ከኢጣሊያ እርቅ የፈለጉ መስሎ የመጠቀም ዘዴ ነበር።

የጦር አዛዦች ስብሰባም፣ ስለ ጉዳዩ በሰፊው ውይይት አደረገበት። ከዚያም ከቀኛዝማች ደምሴ ጋር ሰላድንጋይ ወጥቶ ከመወያየቱ፣ ለራስ አበበ በቀጥታ ጽፎ ስለ ሁኔታው ከራሳቸው መስማትና የመተዳደሪያ ደንቡንም እንዲልኩ ማድረጉ ተመረጠ። ከፈለውም በደስታ ተስማማበት። ይፋትን በመታ ጊዜና ከዚያም ፊቱን ከአንቀላፊኝ ወደ ቡልጋ የዞራቸውን የጠላት ኃይል ከፈለው በመልሱ ላይ ድል እንዳደረገው ሰምተው፣ ከፈለውን ከፊቴ ማንም በክፉ እንዳያነሳ፣ ማለታቸውን ሰምቶ ስለነበር፣ የዛሬው መልዕክት ክፋት እንደሌለበት ገብቶታል።

ለመልዕክተኛው የማያስከፋ መልስ ከተሰጠ በኋላ፣ ለራስ አበበ አድራሻው የሆነ ደብዳቤ ተፃፈ። ደብዳቤውም ቀኛዝማች ደምሴ የላኩትን መልዕክት የሚጠቅስና ያም ሃሳብ የራስ ሃሳብ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠይቅና የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ደብዳቤውን ይዞ ለመጣው ሰው ቢላክ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበርን በመንዝ ውስጥ ለማስፋፋት እንደሚቻል የሚያትት ነበር። ደብዳቤው ተጽፎ ካለቀ በኋላ ከፈለው ዳኘውና ሌሎቹም የጦር አለቆች ፈረሙበት።

“ዳኘው ደብዳቤውን ለማን እንስደደው?” አለ ከፈለው ስብሰባው ካለቀ በኋላ ቀጣዩ ችግር ትዝ ብሎት።

“ተክለሃይማኖት ሰሞኑን ተመላሽ ነው። እሱ በቡልጋ በኩል ቢያልፍስ?” አለ ዳኘው። ከኢጣሊያ ወረራ በፊት አብሮት ከአገሩ ወታደርነት ለመቀጠር አዲስ አበባ የወጣው ጓደኛው ጋር፣ ጣሊያን አዲስ አበባ ከገባ በኋላ ተለያይተው፣ ከዚያም ተክለሃይማኖት ከመንዝ ታዋቂ ሰላይ የውስጥ አርበኞች አንዱ ሆኑዋል። ተክለሃይማኖት ስለ ኢጣሊያ ጦር እንቅስቃሴ ከቤተ መንግሥቱ አካባቢ ጭምር ዜና የሚያገኝና ከፈለውና ሌሎች የመንዝ አርበኞች እንደ ዓይንና ጆሮአቸው የሚቆጥሩት ሰው ነው። ተክለሃይማኖት በሌሎች

የውስጥ አርበኞች አማካይነት የጣሊያን የንግድ ፈቃድ፣ ሊቼንሳ፣ ስላለው እንደፈለገው ከቦታ ቦታ ይዘዋወራል። በስለላ ሥራውም ይበልጥ እንዲቀለጥፍበት በአርበኞቹ ፈቃድ ለጣሊያንም ሰላይ ሆኖ ይሠራል። በአዲስ አበባ ውስጥ የከፈለውን ጦር በአምስት አቅጣጫ ወሮ ለማጥፋት ስለሚደረገው ዝግጅት ሰምቶ ይህንኑ ለማስጠንቀቅ እየተጣደፈ ቢመጣም፣ ጊዜው ካለፈ በኋላ ደርሱዋል። ከዚያም ወደ አፍቀራ ተሻግሩዋል።

“ዳኜ እግዜር ይስጥህ አንድ ችግር ተቃለለ።” አለ ከፈለው። ዳኘው ራሴው ይዤልህ ልሂድ ያለው ያህል።

በማግስቱ ተክለሃይማኖት ደብዳቤውን በጨርቅ ውስጥ ሰፍቶ፣ ለንግድ አስመስሎ ወደ ቡልጋ ዞረ። ከአዲስ አበባ ይዞት ያመጣውን ሸቀጥ በየመንገድ እየሸጠ ራስ ዘንድ ደርሶ፣ በአስረኛው ቀን ወደነከፈለው ደብዳቤ ይዞ መጣ። የራስ አበበ ደብዳቤ ከፈለውንና ሌላውንም ሰው በጣም አስደሰተ። ራስ አበበ ከውጭ አገር ካሉ ኢትዮጵያውያን በተጻጻፉት መሠረት የአውሮፓ ጦርነት መልኩን እየለወጠ በመሆኑ፣ ይህንን ሁኔታ በመጠቀም በተጠናከረ ሁኔታ ላይ ለመገኘት የሚያደርጉት የፖለቲካ ትግል እንጂ፣ እውነተኛ እርቅ አለመሆኑን ከመግለጻቸውም በቀር ከቀድሞ አቋማቸው ተለሳልሰዋል። እንደ ቀድሞው ከፈለው እራሱ እንዲመጣ በግድ የሚጠይቁ ሳይሆን፣ ቢቻል ከፈለው፣ ካለዚያም የጦር አዛዥ የሆነ ሰው ቢላክ የመተዳደሪያ ደንቡ እንደሚላክ ሲገልጡ በአሁኑ መልዕክተኛ በኩል መተዳደሪያ ደንቡን ያላኩት፣ በውስጥ ደንባቸው መሠረት የመተዳደሪያ ደንብ የሚሰጠው ለጦር አዛዥ ስለሆነ መሆኑን ጽፈዋል።

ተክለሃይማኖት እነከፈለው ዘንድ በደረሰበት ቀን ከሮም አንድ ትልቅ ባለሥልጣን አዲስ አበባ ገብቱዋል። ከአርበኞች ጋር የሚደረገው ድርድር በአውሮፓ ውስጥ የጣሊያንን ፖለቲካ ስላበላሸ፣ እርቁ ቆሞ፣ አርበኞች በአስቸኳይ እንዲደመሰሱ፣ ሙሶሎኒ አዞዋል።

ከፈለው የራስ ደብዳቤ ደስ ቢለውም እሱና ዳኘው እንዲሄዱ አልፈለገም። ከራስ ጋር በዘዴ ከታረቀ በኋላ በሩቅ ለመቀመጥ ፈልጉዋል። ዳኘው ከራስ ዘንድ ቢሄድ ጥሩ መሆኑን ቢያውቅም ተክለሃይማኖት ወደ ቡልጋ ሲሄድ አርበኞቹ እንደገና ወደ ቋች ስለተመለሱ ሌላ ጦርነት ቢነሳ የዳኘው አስፈላጊነት ተተኪ የማይገኝለት መሆኑን አውቁዋል። የአርበኛው የአጠቃላይ ስብሰባ ተጠርቶ በሰፊው ውይይት ተካሄደ።

ሁሉም አርበኛ በአንድ ድምፅ የራስን መልዕክት ደግፎ ተናገረ።

“ወይ ጉድ ራስን በከንቱ ስናማቸው ከረምን።” አለ አንዱ አርበኛ። ተወካይ ሆኖ የሚሄድ የጦር መሪ ለመምረጥ ሰው በየፊናው እንዲወያይበት ዕረፍት ተሰጥቶ ነበር። ከፈለው በበኩሉ እሱ እንደማይሄድ ገልጿል።

ሰው እርስ በርሱ መወያየቱን አቁሞ እንደገና ወደ ስብሰባው ቦታ ተመለሰ።

ከፈለው ከቦታው እንደተቀመጠ፣ “ወንድሞቼ እንግዲህ ማንን ተወካይ እንምረጥ ትላላችሁ?” አለ።

"ዳኘው ይሁን። ቀድሞም የላከነው እሱን ነበር።" የሚል ድምጽ አስተጋባ። ሌሊቱን ሙሉ ሁሉም በየቤቱ መክሮበት ወስኑዋል። ዳኘው ከራስ ጋር ስምም ከመሆኑም በላይ ስለ ማኅበሩ ፍቅር ያለው፣ ለጓደኞቹም ታማኝ ነው።

የዳኘው ልብ ተደበላለቀ። ለአደጋ የሚጠራና ለሹመት የሚጠራ ይደነግጣል።

"አይሆንም!" አለ አንድ አርበኛ። "ዳኘው አዋጊያችን ነው። ምናልባት አደጋ ቢደርስበት በኃይል ያጎድለናል። "የለም እሱ መሄድ አለበት።" የሚል ድምጽ እንደገና አስተጋባ።

ከፈለው ትንሽ እንደማሰብ አለና ዳኘውን ቀስ ብሎ "ሌላ ይመረጥ እኔ አልሄድም በል።" ሲል መከረው። ከፈለው ዳኘው ላይ አደጋ ይደርስበታል ከሚለው ሃሳብ ሌላ ዳኘው እንዲለየው አልፈለገም።

"አይሆንልኝም።" አለ ዳኘው። "መቸም ሁልጊዜ እንደዚህ ተንከራተን አንቀርም። አንድ ቀን ባንዲራችን ከወደቀችበት ብትነሳ ኃላፊነት ቢሰጠው እንቢ ብሎ ነበር ተብዬ እወቀስበታለሁ።"

"ይሁን።" አለ ከፈለው፣ ላዩም የዳኘው መሄድ ለጉዳዩ መሳካት እንደሚበጅ አምኖ።

ከዚያ ብዙ መጨቃጨቆች፣ የጦር አለቆች ለየት ለየት ብሎ እርስ በርስ መወያየት፣ ቀጠለ።

እንደገና በአጠቃላይ ስብሰባ ጉዳዩን መመካከር የጀመሩት ፀሐይ

ከአናት በላይ ወጥታ ሰማዩን ስታጋምስ ነበር።

"በምን ቆረጣችሁ?" አለ ከፈለው።

"በዳኘው ተስማምተናል።"

"ይሁን እንግዲያው በዚህ ከተቆረጠ ዳኘው መንገዱን ስለማያውቀው ተክለሃይማኖት እየመራው፣ ትንሽ ሰው ይዞ፣ በጠላት ክልል ሳያልፍ አቆራርጦ፣ ከራስ አበበ ዘንድ ይድረስ። ምንም እንኳን ጣሊያኖች ከራስ ጋር ለሚወያይ የይለፍ ይሰጣሉ ቢባልም ጣሊያኖች ብዙ ምሽጎችን ለአርበኞች የለቀቁ ቢሆንም፣ የአይጥና የድመት ጨዋታ አያስተማምንምና ዳር ዳሩን መሄድ ይመረጣል።"

"እርግጥ ነው።" አለ ዳኘው። በተለይ ከተክለሃይማኖት ከአብሮ አደጉ ጋር መጓዙ ደስ አለው። ተክለሃይማኖትን እንዳገኘው፣ "ተክሌ እንደገና አዳባይን ልናቁዋረጥ ነው። ጠንቋይ እንጠይቅ ብለን አንመለስም።" አለ እየሳቀ። የልጅነት መኮብለላቸው ሁኔታ ትዝ ብሎት።

"የጠንቋዩን ተወውና ጥሩ ወርቅ ከሲዳሞ መጥታ አዲስ አበባ አገኘሁዋት።" አለ ተክለሃይማኖት ፈገግ ብሎ።

“ደህና ናት? እንዴት ናት?” አለ ዳኘው ስለሱዋ ለመስማት ብዙ ቸኩሎ።

“ባል አግብታ ሁለት ወልዳለች።” አለ ተክለሃይማኖት የዳኘውን ስሜት በማንጠልጠሉ ቅር ብሎት።

“አሁንም አዲስ አበባ ናት?” አለ ዳኘው አዲስ አበባ ሄዶ ይጠይቃት ይመስል።

“ተመልሳለች።” አለ ተክለሃይማኖት። ወሬውን ለመቀየር ፈልጎ “እንግዲህ ራስ ዘንድ እስክንደርስ ስለ አዲስ አበባ ብዙ አጫውትሃለሁ። አዲስ አበባ የጥንቱ አይምሰልህ።”

ዳኘው የራሱን ጦር ከዋናው ከከፈለው ጦር ጋር ትቶ፣ እሱ ራሱ 13 ወታደሮችን ይዞ መልዕክተኛነቱን ለማሙዋላት መጋቢት 1 ቀን 1932 ማኅበረ በከረ ማርያም ከራስ የጦር ሠፈር ደረሰ።

የራስ የጦር ሠፈር ለመግባት ለውይይት የመጡት ጣሊያኖች የመጀመሪያውን የፍተሻ በር ሲያልፉ ደርሶ እሱም ከመጀመሪያው ኬላ ጉዳዩን ነግሮ ካለምንም ችግር አለፈ። ከፍተሻዎቹ ሰባት ኬላዎች ላይ የጣሊያን መኮንኖች የሚደረግባቸውን ከባድ ፍተሻ ሲመለከት፣ ጣሊያኖችም ይህን ሁሉ ፍተሻ በትእግሥት መቀበላቸውን ሲያይ፣ ዳኘው ለእርቅ ምን ያህል ፍላጎት እንዳላቸው አወቀ።

መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ሰባት ፈታሽ ዘበኞችን ማለፍ ይገባል አሉ። ራስም ዘንድ ለመድረስ ጣሊያኖች ሰባት ዘበኞች ያልፋሉ አሉ። ይህም የነፍስ ጉዞ ሰባቱም ቦታ ላይ መራመድ መንቀጥቀጥን ያስከትላል። ራስም ሰባቱም የፍተሻ ቦታዎች የሚያስፈሩ፣ ዓይናቸው የሚጉረጠረጥ ሰዎች በማስቀመጥ የጣሊያኖቹን ሞራል ለመስበር አስበውበታል።

የጣሊያን ተወካዮች ራስ ዘንድ ሲቀርቡ ራስና የጦር አዝማቾቻቸው ከኋላቸው የኢትዮጵያን ባንዲራ ከፍ አድርገው ሰቅለው ይቀበሉአቸዋል። በራስ ዙሪያ ያሉት ባልደረባዎቻቸው ጣሊያኖችን አትኩረው በጥላቻ ይመለከቱዋቸዋል። ይገላምጡአቸዋል። ለጣሊያኖች ሁሉም ነገር አእምሮአቸውን ለማሰባሰብ የሚያስናቸው ነው። ጣሊያኖች በየጊዜው አንድ የተጨበጠ ነገር ለማግኘት ቢመጡም፣ አንዱንም ቀን ተጨባጭ መልስ አግኝተው አያውቁም።

ዳኘው በሰባቱ ኬላዎች ሲያልፍ ሰላምታ እየተለዋወጠ፣ በሳቅ በጨዋታ ከዋናው ክልል ገብቶ ቀጠሮ ተያዘለት።

ከራስ ዘንድ እንደቀረበ “እኛ ከናዚ ጋር እርቅ ለማድረግ አስበናል። እናንተስ ምን አስባችኋል?” አሉ ራስ። ምናልባት ከፈለው በእርግጥ እርቅ ያደርጋሉ ብሎ አምኖ እንደሆነ ለመፈተሽ። “ዳኘው ከፈለው ሃሳቡ እንዴት ነው?”

ዳኘው በጣም ደነገጠ። የይለፍ ወረቀት ተጽፎለህ፣ በደብረ ብርሃን በኩል እለፍ ብለው አንድ የጦር አዛዥ መክረውት እንቢ ብሎ በሌሊት አቋዋርጬ አልፋለሁ እንጂ

በጠላት ክልል ውስጥ አላልፍም ብሎ ስንት የኳተነው ያ የሚጠረጥረው ነገር ከዚህ አገኘው። “እኔ ለዚህ ጉዳይ አልተላኩም። የተላኩት የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ ይዤ ተመልሼ በመንዝ ውስጥ ማኅበሩን ለማቋቋም ነው።” ሲል በድንጋጤና በእልህ ተናገረ።

“አይደለም ጌታዬ።” አሉ ራስ በተለመደው ዘይቤአቸው፣ “እርቅ ብንልህ እርቅ አይደለም። (ስንፈትንህ ነበር የሚል ፈገግታ እያሳዩት) ። ናዚ እርቅ አደርጋለሁ ብሎ የተቃጠርንበት ቦታ ሲመጣ፣ አደጋ ጥለን፣ ቢቻለን ማርከነው ወደ ጫካ ለመውሰድ፣ ካለዚያም ለመግደል ነው።” ዳኘው የፊቱ ፀዳል አብርቶ አንድ ነገር ከላዩ ላይ እንደወረደ ያህል ቀሎት ትከሻውን አነቃንቆ ራስን በድሮው የፍቅር ዓይን መመልከት ጀመረ። “አንተ ከመጣህልን፣” አሉ ራስ ቀጥለው። የጥንት ክብር ዘበኛ በመሆኑ ለሥራቸው እንደሚያስፈልጋቸው አምነው። “ላዩም አንተ ከመጣህልን አንተ ያደጋው ጣይ መሪ ትሆንልናለህ።”

ራስ ለዳኘው የጀነራል ናዚን የመግደል ወይ የመማረክ እቅድ አስረዱት። “እኔ ከጥቂት ባልደረቦቼ ጋር ናዚ ጋር በምንጨባበጥበት ወቅት ናዚን ይዘን ለመማረክ እንሞክራለን። ያቃተን እንደሆነ ግን አንተ ከቡድንህ ጋር ከምትጠባበቅበት፣ ከዚህ ከአፋፉዋ፣ ቢቻል ናዚን ነጥለህ ትመታዋለህ። ጓደኞችህም ለሎቹን ይገድላሉ። ናዚን ነጥለህ መምታት ካልቻልክ እኔንም አብረህ ምታኝ። ለአገራችን ይህ መስዋዕትነት ትልቅ የፖለቲካ ድል ነው። በተለይ በአሁኑ ወቅት! ።”[55] ዳኘው በራስ አበበ ቆራጥነት ልቡ ተነከቶ አቀረቀረ። ምንም መናገር አልቻለም። ያዘዙትን ግን ለመፈጸም ዝግጁ ነው።

ጀነራል ናዚ ከቀጠሮው ለሚገኝበት ለመጋቢት 4 ቀን ዝግጅቶች መጣደፍ ያዙ። ዳኘውም የተሰጠውን ሥራ ሙሉ መንፈሱን ስለሰጠው በህልሙም በእውኑም በሃሳብ ያከናውነው ጀመር።

ዳኘው መትረየሱን አምስት እርምጃ ያህል ብቻ እርቆ በጀነራል ናዚ ደረት ላይ ጥይቱን ያዘንባል። ከራሱ ጀምሮ እስከ እግር ጥፍሩ ያንጣጣበታል። ጀነራል ናዚ ምንም ሳይሆን ከት ብሎ እየሳቀ ከራስ ኋላ ይደበቃል። ዳኘው የሚያረገው ይጠፋዋል። ደርበህ ምታን ይሉታል። ዳኘው ከዚህ ይልቅ በእጄ ባንቀው ብሎ ከራስ ዘንድ ሲጠጋ ናዚ ወደ አፋፉ ይሮጥበታል። ዳኘው ናዚን ተከትሎ ለመያዝ ሲሮጥ ሳያስበው ከአንድ አፋፍ ላይ ደርሶ ዥው ብሎ ሲወድቅ፣ ከአፋፉ መሃል ላይ እንዳለ፣ ከእንቅልፉ ደንግጦ ነቃ።

[55] ራስ አበበ ሞትን ለመጋፈጥ ያላቸውን ቁመና በታኅሣሥ ግርግር ወቅትም ደግመውታል። መሣሪያ ተደቅኖባቸው፣ ደረታቸውን ሰጥተው ወደ ተኳሹ ሲሄዱ፣ ጀነራል ናዚ በቆሰለበት ቤተመንግሥት፣ ከሌሎች የአርበኞች መሪዎች ጋር ሆነው መስዋዕትነት ከፈሉ።

በበነገታው ስለሕልሙ ለተከለሃይማኖት ሲነግረው ተከለሃይማኖት ለመሆኑ ናዚን አይተኸው አታውቅ ምንን ተመስሎ ታየህ ብሎ አሾፈበት። ዳኘው እንደ ሰሞኑ ጠበንጃውንና ሽጉጡን ወልውሎአቸው አያውቅም።

ለአንድ ታሪካዊ ሥራ እድል የመረጠችው አድርጎ ራሱን ቆጥሩዋል።

⅄ ⅄ ⅄

# ጌታዬ ሰው ውሃ ይጠጣ እኛ በዚህ በኩል እንለፍ

መጋቢት አራት ቀን ጀነራል ናዚ ከቀጠሮው ቦታ አልመጣም። የሮም መንግሥት፣ የአውሮፓን ጦርነት አዲስ ሁኔታ ከመጋፈጡ በፊት አርበኞችን መደምሰሱ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑን በመግለጽ፣ የእርቁ ድርድር እንዲቆም ባዘዘው መሠረት፣ የእርቁን ድርድር አፈረሰ። የራስ አበበ ተወካይ ወጣቱ ቀኛዝማች ደምሴ መታሠሩ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፀሐፊ የነበረው ወልደ ኮሮስ ከድቶ ለኢጣሊያ ማደሩ ተሰማ።

“ደምሴ ነው አንጀቴን የበላኝ።” አሉ ራስ ተክዘው። ከዚህም ቀደም የእርቁ ድርድር ከተጀመረና ጣሊያኖችም ብዙ ምሽጎቻቸውን ካስረከቡ ወዲያ፣ ጀግናው አርበኛ አድማሴ ማገኛ ከ27 ሌሎች አርበኞች ጋር በጣሊያኖች ተገድሉዋል። አድማሴ ግን ሞቶም ጠላትን ተዋግቱዋል። የእርቁን ድርድር በአጭር ጊዜ ለመፈፀም ኢጣሊያ የኦርቶዶክስ ጳጳሳትን ግዝት እንዲያደርጉና እንዲያማምሉ አዘጋጅቶ፣ ቀነ ቀጠሮ ሲወስን ያ ቀን የተራዘመው፣ ለአድማሴ መገደል ጣሊያን በገንዘብ ልካስ ያለው፣ በሕዝቡ ዘንድ የወንድም ደም እንዴት በገንዘብ ይካሳል ብሎ ቅሬታ ስለፈጠረ፣ ይህን ሁኔታ ለማረጋጋት የጊዜ ማራዘም እንዲሰጥ በመጠየቅ ነበር። አርበኞች መስቀል ይዘው የውሸት እርቅ ለመፈጸም አልፈለጉም ነበር። አሁን ደግሞ የደምሴ መታሰር ራስን አንገበገባቸው። “ወልደ ኪሮስ ይካድ፣ ሁሉም ወቅት ፈሪና ከነፃነቱ ይልቅ ለእለት ጥቅም ሲል ባርነትን የሚመርጥ ሰው ሞልቶታል።” አሉ።

“ወልደ ኪሮስ ስለከዳ ጣሊያንም አያርፍም፣ እኛም አናልቅም። የሚያሳዝነው ምስጢራችንን ሁሉ ይዞ መሄዱ ነው።” አሉ የራስ ነፍስ አባት። “ይሁዳ ነውና ፍጻሜው አያምርም።”

የጣሊያን አውሮፕላኖች እየተመላለሱ እያንዳንዱ አርበኛ የምህረቱን አዋጅ ተጠቅሞ አቅራቢያው ላሉ ባለሥልጣኖችና ሬዘዳንቶች እጁን እንዲሰጥ ወረቀት ይበትናሉ። በአርበኛው መሃከል የጦርነት ዝግኝት ይጣደፋል። ጣሊያኖች የሚበትኑአቸውን ወረቀቶች አርበኞች እየተሽቀዳደሙ ይለቅሙአቸዋል። ደብዳቤዎች የሚጻጻፉት በእንደዚህ ዓይነት ወረቀቶች ጀርባና በጥንት የማዘዣ ወረቀቶችና ካርኔዎች ላይ እየጻፉ ነው። ብዙው አርበኛ

እንዲህ ዓይነት ደብዳቤዎች በግል በስሙ እየተጻፉ በአማላጅ በኩል ባለፉት ዓመታት ሲደርሰው የቆየ ስለሆነ የተደነቀባቸው ሰው የለም።

ማኅበረ በኩር በአንድ በኩልዋ ሁለት መቶ ሺ የኢጣሊያ ወታደር ተሰልፎባታል። በሌላ ጎኑዋ ቁልቁል ወርዶ የአዳል በረሃ ተነጥፎአል። አርበኞች ከመሃል ዝግጅቶቻቸውን ያጣድፋሉ። ከመንደሪቱ መውረጃዎች የአርበኞች ግንባር ቀደም ጦር በተጠንቀቅ ይጠብቃል። የደጀኑ ጦር ሜዳውን ለቆ በጫካው ውስጥ ዝግጅት ያደርጋል።

ጡዋት ላይ ግንባር ቀደሙ ጦር በሩን ዘግቶ ከኢጣሊያኖች ተኩስ እንደ ጀመረ አምስት የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ሲመጡ ከሩቅ ታዩ። ራስ አበበ ወዲያውኑ "የሠፈሩ ጦር በሙሉ ከጫካው ወጥቶ ከሜዳው ላይ ካሉት ድንጋዮችና ዛፎች ስር ሳይነቃነቅ ሳይተኩስ ቁጭ ቁጭ ይበል።" ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ። አካባቢያቸው የነበሩት ሰዎች በሙሉ ወደ ጫካው ገብተው "ከሜዳው ወጥታችሁ በየዛፉ ሥር ሳትነቃነቁ ቁሙ። በየድንጋዩ ሥር ተቀመጡ። ማንም እንዳይተኩስ!" እያሉ ትዕዛዝ ሰጡ።[56]

በጫካው ውስጥ የነበረው ሰው እየሮጠ ወጥቶ በየድንጋዩ ሥር ተቀመጠ። ግማሹ በየዛፉ ሥር ተገትሮ ቆመ። በሜዳው ላይ ካሉት ነጭ ድንጋዮች ጎን የተቀመጠው ሰው ራሱ ድንጋይ መሰለ። ዳኘው ከአንድ ዛፍ ሥር ቆሞ ዙሪያውን ሲመለከት ጣሊያኖች ከአውሮፕላን ላይ ሆነው ምን እንደሚያዩ ገረመው።

የጣሊያን አይሮፕላኖች ከጫካው ውስጥ አለ ብለው ያሰቡትን የአርበኞች ኃይል እስከጫካው አብረው ለማንደድ እየደጋገሙ በቦንብ በመደብደብ በመትረየስ ጥይት ጨፈጨፉት።

ራስ አበበ ከአንድ ዛፍ ሥር ቆመው፣ ካኪ ቀለም ካባቸውን ከአንድ ወገን ከትከሻቸው አጥፈው፣ ቀኝ እጃቸውን አጥፈው መዳፋቸውን ወደታችና ላይ እያነቃነቁ ፀጥ ብላችሁ ቁሙ በማለት፣ አካባቢው ያሉትን ሰዎች ይቃኛሉ። ዳኘው በአድናቆት ተመለከታቸው። በጦርነት ጊዜ ካባቸውን ወደ ሁዋላ አድርገው መትረየሳቸው ላይ ከተቀመጡ ተከታዮቻቸው መጥተው ጥይት አልቆብናል እናፈግፍግ ብለው በግድ ካላስነሱዋቸው አይነሱም። ውሳኔ በሚያስፈልግበት ጊዜ ደግሞ ካለምንም መረበሽ የሰከነ ትዕዛዝ ይሰጣሉ።

ዳኘው ከቆመበት ቦታ ሆኖ እግሩ ሲደነዝዝ ተሰማው። ከመቆም ይልቅ

መቀመጥ የተሻለ ነው። ለካስ ቆሞ እንደመዋል ትልቅ ቅጣት የለም?" ሲል አሰበ። ከሱ ፈንጠር ብሎ ከድንጋይ ሥር የተቀመጠው ሰው ሳይነቃነቁ እንደመቀመጥ ትልቅ ቅጣት የለም ብሎ ያሰበው ከዳኘው ቀድሞ ነበር። ሁለቱም ግን አንዳቸው በሌላቸው አእምሮ

[56] አርበኞች ከፎሰጂንና መስታርድ ጋዝ ሌላ አካባቢውን የሚያነድ ኬሚካል ሲረጭ ከጫካዎች ወደ ነጭ አፈርና ድንጋይ ስር ማድፈጥን ለምደዋል።

ውስጥ የሚብላላውን አላወቁም። ሁለቱም ተያዩና እርስ በርሳቸው ተቀናኑ። ዳኘው እድለኛ ነህ ለማለት ፈገግ አለ። ያኛውም ሰው ነገሩ ገብቶት ፈገግ አለ።

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን እየተመላለሱ ይደበድቡ የነበሩት አውሮፕላኖች ከሰማዩ ላይ ጠፉ። እነሱ ያን ያህል ሲተኩሱ፣ ያን ያህል ቦንብ ሲጥሉ የተኮሰባቸው ወይም ከጫካው እየሮጠ የወጣ ሰው የለም። ከፓይለቶቹ መሃከል ሁለቱ የዚያን ለት ማታ ተገርመው ሲከራከሩ የነበረውም ስለዚህ ነበር። ሃበሻ አውሮፕላን ሲያይ ሲሮጥ፣ በምንሽር አውሮፕላን ይጥል ይመስል ጥይቱን ሲያባክን ነው የሚያውቁት። በዚህ ምክንያት ነበር አንደኛው በዚያው አካባቢ ሰው ባይኖር ነው ሲል ሌላኛውም ታዲያ ሽፍቶቹ የት ገቡ ብሎ መልስ የጠየቀው።

አውሮፕላኖቹ እንደተመለሱ ራስ ጓዝና ደጀኑ ጦር ወደ አዳል በረሃ አቅጣጫ እንዲነቃነቅ፣ ግንባር ቀደሙ ጦር ግን እስኪመሽ ተዋግቶ ከሚያርፉበት ቦታ ድረስ እንዲመጣ ትዕዛዝ ሰጡ። ደጀኑ ጦርና ጓዝ በየክፍል አለቃው አማካይነት ተነቃነቀ። ዳኘውም ምድብ ክፍል የሌለው እንግዳ ስለሆነ ከራስ ጋር መጉዋዝ ቀጠለ። ባሩድ የጨሰበት አርበኛ በውሃ ጥም ተቃጥሎዋል። ዳኘው ከራስ በቅሎ አጠገብ እየተራመደ እያጫወታቸው አንድ ሦስት ኪሎሜትር እንደተጉዋዙ የቀበና ወንዝ አፋፍ ደረሱ። ከፊት የቀደመው ጦር ከወንዙ ዳርና ወንዙ ውስጥ ተገጥግጦ ቆሙዋል። ራስ ጦርአቸው ለምን እንደማይሄድ ገርሙዋቸው "ወደ ፊት ሂዱ ብለህ ንገር።" እያሉ ለጋሻጃግሬያቸው ደጋግመው ይናገራሉ። ትእዛዝ ቢተላለፍም የሚነቃነቅ ሰው የለም። ዳኘው ከወንዙ ዳርና ወንዙ ውስጥ ተገትሮ የቀረውን ጦር ዝም ብሎ መመልከቱን ቀጠለ። ከወንዙ ካሉት ሰዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ይጠቅሱታል። ምን እንደሆነ አልገባውም። አትኩሮ መመልከቱን ቀጠለ። አሁን ገባው።

"ገታዬ ሰው ውሀ ይጠጣበት። በዚች በኩል እንለፍ።" አለ ዳኘው አቁዋራጭ መንገድ በጣቱ እያመለከታቸው። ከዚያም የበቅሎዋን ልጉዋም ይዞ ወደዚያ መራት። ወንዙን ተሻገሩና አንድ ከወደቀ ዛፍ አጠገብ ሲደርሱ ራስ ነገሩ ከንከኖአቸው "አንተ መንዜ ምንድነው የምትለው! እኔ ውሀ አትጠጡ ብዬ እከለክላለሁ?" አሉ ዳኘውን ትኩር ብለው እየተመለከቱ።

"ጌታዬ በስም አጥረውት እንዴት ከርስዎ ፊት ይጠጣ?" አለ ዳኘው ትህትናውን ለማሳየት ድምጹን ለስለስ አድርጎ።

"አይሄሄ፣" አሉና ራስ ዳኘው የሚናገረው እውነቱን እንደሆነ ለማወቅ ከወደቀው ዛፍ ላይ ወጡና ወደ ወንዙ ተመለከቱ። ጦሩ በሙሉ፣ ፊታውራሪ ቀኛዝማቹም፣ ከወንዙ ላይ ተደፍቱዋል። "ደጃዝማች ዘውዴ! ደጃዝማች ዘውዴ!" ብለው ራስ ተጣሩ።

"ምነው ፈለጉኝ?" አሉ ደጃዝማች ዘውዴ። ሲናገሩ ኮልታፋ ስለሆኑ አፋቸው ደስ ይላል።

“አዩ ደጃዝማች ይኸ መንዜ ጉድ ሠራኝ። ሰውን ሁሉ በስም አጥረኸው ውሀ አላስጠጣ አልክ አለኝ።” አሉ ራስ እየሳቁ።

“ድሮም እኔ ነግሬሃለሁ። እነዚህ መንዞች ቂል መስለው ተንኮለኞች ናቸው። ከእነሱ ጋር አይዋሉ ብያለሁ።” አሉ እያንዳንዱን ፊደል አፋቸውን እየያዛቸው፣ በዚህ ላይ እየሳቁ። በራስ አበበ ሥር ያሉት አርበኞች ከአማራው፣ ከኦሮሞው፣ ከትግሬው፣ ከወላይታው ወዘተ የተውጣጡና የሚፈቃቀሩ ስለሆነ እርስ በርሳቸው ይቀላለዳሉ።

“አንተንም ቀኛዝማች ብለን ልንሾምህ ወስነን ምናልባት አትቀበልም ብለን ነው ያቆየነው። ባይሆን አገርህ ስትደርስ በደብዳቤ እናስታውቅህ ብለን ወስነን ነው።” አሉ ራስ ለዳኘው። ራስ ለተከታዮቻቸው ሹመት ሰጥተዋል። ሸዋ የማታውቃቸው የነበሩ ገበሬዎች አሁን ፊታውራሪ፣ ቀኛዝማች፣ ግራዝማች፣ ባላምባራስ ተብለዋል።

“ጌታዬ ደግሞ በአገሬም እንጨት ሰብሬ፣ ውሀ ቀድቼ እንዳልበላ ቀኛዝማች ብለውኝ በራብ ሊጨርሱኝ ነው?” አለ ዳኘው ደረጃ ክብሩን ጠብቆ ለመኖር አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ከፈለው የሚሰማው ቅሬታ ታይቶት።

“አየህልኝ ይህን መንዜ፣ ከፈለውን አስቀይመዋለሁ ብሎ ነው። ውነቱን ነው። ከተሾሙ ሁለቱም ነው።” አሉ ደጃዝማች።

“ባይሆን ይህ ቃልዎ ወደፊት ነፃነታችን ተመልሶ አዲስ አበባ ከገባን እንዳይረሱብኝ። የዚያን ጊዜ በደስታ እቀበላለሁ።” አለ ዳኘው የምሩን፣ ራስን በአክብሮት እየተመለከተና ሹመቱ ስላስደሰተው እጅ እየነሳ። ራስም አስተዋይነቱ ደስ ብሎአቸው ፈገግ ብለው ተመለከቱት።

ጦሩ ከወንዙ እየወጣ ነበር። በስንት ድካም አመሌ ገማኝ ከሚባል ቦታ ተደረሶ እረፍት ሲደረግ የጣሊያን ጦር በድንገት ደርሶ ተኩስ ከፈተ። ጦሩ እየተታኮሰ አመች ቦታ ለመያዝ በየቦታው ተበታተነ። ያልታሰበ አደጋ ስለነበር መቋቋም አልተቻለም። ዳኘው ከጉዋዝ ጋር የነበሩት የራስ አበበ እናት ላይ የተጫነውን ጦር ለመበተን በቤልጅግ ጠበንጃው እየተታኮሰ በአካባቢው የሚሆነውን ሁኔታ አላወቀም። “ተማረኩ! ተማረኩ! እመቤቴ እመቤቴ!” ሲል ዳኘው ጮኸ። የራስ አበበን እናት ሁለት የኢጣሊያ ወታደሮች እያዳፉ ወደ ደጀናቸው ጦር ወሰዱዋቸው።

ዳኘው አካባቢውን ተመለከተ። የአርበኛው ጦር ተበትኖአል። እልህ፣ ንዴት ጉሮሮውን አንቆ ትንፋሹን ዘግቶት በግድ ይተነፍስ ጀመረ። ከተኛበት ብድግ ብሎ አሻገሩን ተመለከተ። ራስ ያሉበትን ቦታ ለማየት አልቻለም። ፊቱን አዙሮ አሥራ ሦስት ወታደሮቹን ተመለከተና “ቁልቁል እንውረድ!” አለ። የጣሊያን ወታደሮች ተኩስ ግራና ቀኙን ያዋከበው ጀመር። ዳኘው ከመሬት ወድቆ እየተንከባለለ ወደ ታች ወረደ። ከዚያም እስከ ሰዎቹ ከጫካ ውስጥ ገብቶ እየተጣደፈ ጉዞ ቀጠሉ። “ራስ አበበ በየት በኩል ሄዱ?” አለ ዳኘው ወደ ሰዎቹ ዘወር ብሎ።

“ብቻቸውን ጥቂት ሰዎች አስከትለው በወዲያ በኩል አለፈዋል።” አለ ጋሻጃግሬው። የልጅነት ዓይኑ የአካባቢ ሁኔታዎችን ማተኮር ይወዳል።

“በዬት?” አለ ዳኘው። ነፍሳቸው መትረፉ ላይ ብቻ ሃሳቡ ተንጠልጥሎ ጋሻጃግሬው የተናገረውን ሙሉ በሙሉ አልሰማውም ነበር።

“ወደ ራስ ከመሄድ ፊታውራሪ አየለ ኃይሌ በዚህ በኩል ስለሚገኙ ወደ እነሱ እንሂድ። አገሩን በደንብ ስለማናውቀው የማይሆን እርምጃ መውሰድ የለብንም፣” አለ ተክለሃይማኖት። ልጅ አየለ ሃይሌም ፊታውራሪ ተብለው በራስ ተሹመዋል።

“ውነትህን ነው ተክሌ፣” አለ ዳኘው ረጅሙን ጓደኛውን አንጋጦ እየተመለከተው።

“ዳኜ እኔን ተከተሉ። ከናንተ እኔ እሻላለሁ።” አለ ተክለሃይማኖት መንገዱን እየመራ። ቡልጋን ብዙ ጊዜ ተመላልሶበታል።

ከፊታውራሪ ኃይሌ ጋር እነዳኘው ሲገናኙ ጥሩ ወሬ አልጠበቃቸውም። ራስ አበበ ከጥቂት ተከታዮች ጋር አዳል በረሃ ከመግባታቸው በቀር ሌላው ጦር በየአቅጣጫው ተበትኖ ያለበት ቦታ አይታወቅም። እንዳኘው የደረሱ ሌሊቱን ስለነበር ይህንኑ እያወሩ አነጉ። ጡዋት ሲነጋጋ ከዚያ ያለው አርበኛ በሙሉ ተሰብስቦ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበርን መዝሙር እየዘመረ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራቸውን አነሱ።

ኢትዮጵያ ሆይ ሀገራችን እናታችን

ለጥንታዊት ክብርሽ ይፈሳል ደማችን።

በትጋት ዘርጊ እጆችሽን

አይነፍግም አምላክ ልመናሽን።

ብርቱ ምሽግ ናቸውና በርሃዎች ወንዞች ተራሮችሽ

የተባበሩት አርበኞችሽ ምንም አይሰጉ ከጠላትሽ።

ኢትዮጵያ ሆይ ሀገራችን እናታችን

ለጥንታዊት ክብርሽ ይፈሳል ደማችን።

የዳኘው ሰዎች መዝሙሩን በደንብ ባያውቁትም በተመስጦ ቆመዋል። ከዛሬ ወዲያ ይህን መዝሙር አይረሱትም። “ሁለተኛው መዝሙር ይቀጥል!” አሉ ፊታውራሪ ኃይሌ። የዳኘው ሰዎች ከተዝናኑበት ሁኔታ እንደገና ጠበንጃቸውን ደረታቸው ላይ አድርገው ቆሙ። ያደፈ ልብሳቸው ቢጨማደድም፣ ሰውነታቸው ቢዝልም፣ ቢቆሽሹም፣ ቢያድፉም ከባንዲራቸው ፊት ግን ሳይነቃነቁ በጥንካሬ ቆሙ።

ጥንታዊት ኢትዮጵያ እናታችን ሆይ

አርበኛሽ ጽኑ ነው ቆራጥ ተጋዳይ

የደሙ ምልክት ያው በልብሱ ላይ።

ጥንታዊት ኢትዮጵያ አትደፈሪቱ

ጠላትሽ ግፈኛ አረመኔ ከንቱ።

ጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች ማኅበር

ጠላትሽ ተዋርዶ ስምሽ እንዲከበር

እንሽከማለን የመከራ ቀንበር።

የባንዲራ ማንሳቱ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል። አርበኞቹ ግን አሁንም በዝምታ በተጠንቀቅ ቆመዋል።

"እሺ ወንድሞቼ?" አሉ ፊታውራሪ አየለ። ምን እናድርግ ብሎ ለመጠየቅ።

"ባዶ እጃችንን ወደ መንዝ አንመለስም።" አለ ዳኘው ለፊታውራሪ እየተናገረ የሱን ሰዎች እየተመለከተ።

"አዎን እርግጥ ነው።" አሉ ሰዎቹ። ከመንዝ ሲወጡ በስምንት ቀን ውስጥ እንመለሳለን ብለው ነበር። ዛሬ ወራቸውን አከብረዋል። ዓመትም ቢፈጅ ግን የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይዘው ሄደው ባገራቸው ይህንኑ ደንብ በሰፊው ማቆም አለባቸው።

"እኛም አንቀር። አብረን እንሄዳለን።" አሉ ፊታውራሪ አየለ። ራስ አበበ በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ሆነው አርፈው ሊቀመጡ አይችሉም። ራስ አበበን ከአዳል በርሃ ሲያገኙዋቸው ከብዙ ሰው ጋር ነበር። በየቦታው ተበታትኖ የነበረው አርበኛ እያፈላለገ አግኝቱአቸዋል። ከአምስት ሰዎች ጋር ብቻ በበረሃ ውስጥ ቀርተው የነበሩት ራስ ቀስ በቀስ ጦራቸው በዝቶአል። "ዳኘው መጣህ? ቁምነገረኛ ነህ። ደህና መውጣትህን አይቼአለሁ። በዚያው ወደ አገርህ የምትሄድ መስሎኝ ነበር።" አሉ ራስ በደስታ ዳኘውን እየተመለከቱት።

"ምን ይገፍ አገሬ እገባለሁ። የመተዳደሪያ ደንቡ አልተሰጠኝም።" አለ ዳኘው።

"ሳትሰማው አትቀርም። የመተዳደሪያ ደንቡን ሌሎችንም ወረቀቶች ወልደ ኪሮስ ከጣሊያን ዘንድ ይዞዋቸው ገብቱዋል። ከምን ላይ ተገልብጦ ይሰጥሃል። ቢሆንም ለከፈለው ደብዳቤ እጽፍለታለሁ። አንተም አንቀላፊኝ ላይ የመተዳደሪያ ደንቡን ስትፈርም ስለምታውቀው ጽሁፍም ባይኖር በቃልህ ሥራውን አከናውን።" አሉ ራስ ተከዘው።

ጦርነቱ አሁንም አልቆመም። ጣሊያን እንደገና እየመጣ ነው። ሰሞኑን እያከታተለ እየወጋ፣ እያባረራቸው ነበር። ራስ አበበ በአዳል በርሃ ዘልቀው ለመግባት ሲነሱ ዳኘው ተሰነባብቶ ወደ መንዝ አመራ።

ዳኘው ጠላት በሌለበት ክልል በኩል እያቋረጠ መሄድ እንደጀመረ ከመሃከላቸው አንዱ ሰው ታመመ። ራብ የጎዳው፣ መንገድ ያጠቃው አርበኛ በሽታውን ሊቋቋመው ስላልቻለ በማግስቱ ሞተ። ጓደኛቸውን በአዳል በርሃ ውስጥ ቀብረው ጉዞ ቀጠሉ። የጠላት

ጦር ግን ከመንገድ ስላገኛቸው አስራ ሁለቱ ሰዎች እየተዋጉ ተመልሰው ወደ አዳል በርሃ ወረዱ። በአጋጣሚም እንደገና ከራስ ጋር ተገናኙ።

የአዳል ሕዝብ አርበኞቹን በወንድምነት ተቀብሎ ከጎናቸው ቆሞ ይዋጋል፣ ያስተናግዳቸዋል። ዳኘው በጣም ደስ አለው። በሰላሙ ዘመን ከአዳሎች ጋር ይህን ያህል መቀራረብ አልነበረም። ዛሬ ችግር እንደ እናት ልጅ አፋቅሮአቸዋል።

የኢጣሊያ ጦር በመሰልቸት ወደየምሽጉ መመለስ ያዘ። ራስም ወደ ደጋው ለመውጣት ሲነሱ ዳኘው በረሃውን አቋርጦ በተጉለት ወንዝ በጋዶ ጅረት አድርጎ ከአስራ ሁለት ሰዎች ጋር ከመንዝ በወጣ በሦስት ወሩ አዳባይ መልካ ገባ። ከዚህም ግን የሚያስደስት ነገር የለም።

⅄ ⅄ ⅄

# የዱር ፍሬ የሚበላው ጦር[57]

ዳኘው ስለነከፈለው ወሬ ሰምቶ አያውቅም። በዚህ ዘመን ደግሞ ሦስት ወር እንደ ሰላሳ ዓመት ነው። በመልስ ጉዞው ላይ ወደ መንዝ እየተቃረበ ሲሄድ ይበልጥ ስለነሱ ማሰብ ያዘ። እስካሁን በረሃ ለበረሃ ስለሚሄድ በደጋዎቹ አገሮች ምን እንደደረሰ አያውቅም። ሁሉም መንደሮችና ሰዎች በዓይነ ሕሊናው የሚታዩት ቀድሞ ሲለያቸው እንደነበሩት ሆነው ነው። ተጉለት ደርሶ ወደ መንዝ ሲገሰግስ ግን በሕዝቡም፣ በአገሩም፣ ላይ ትልቅ ለውጥ ማየት ጀመረ። የሰዎች ዓይን፣ ደስታና ሃዘን ሳይሆን ባዶነት ሰፍኖባቸዋል። ራብ የጠናበት ሰውነታቸው ተዳክሙዋል። ሰው በሩቅ ይሸሻሉ። ወደ ትውልድ መንደሩ ለመድረስ የነበረው ጉጉትና ደስታ ገና ከመንገድ እያከተመ ሄደ። ቀስ በቀስ ጭራሹንም የሚያስበው የአገር ሰው ሞትና የቤተ ዘመድ ሞት ሆነ። “ወይ እናቴ፣ ወይ ወንድሞቼ፣ ሁለም አልቀዋል፣ ” ሲል ገመገመና እንባው መጣ። ይህን ስሜቱን ግን ለማንም አልገለፀም። አብረውት ያሉት አሥራ ሁለቱ ሰዎችም የሚያስቡት እንደሱ ቢሆንም የሆዳቸውን ምስጢር አውጥተው እርስ በርሳቸው አልተወያዩበትም።

“አገሩ ደህና አይመስልም።” አለ ተክለሃይማኖት። የየአንዳንዱን ሰው ችግር ሳይሆን ስለ አጠቃላይ ሁኔታ መናገሩን ግልጽ እያደረገ።

[57] ጦሩ የሚለው የጦር ሠራዊት የሚለውን ቃል ለመግለጽ በሕብረተሰቡ ዘንድ በጥቅም ይውል እንደነበር ማስታወስ ይጠቅማል

"ነፃነት፣ አገር፣ የሌለው ሕዝብ ምን ደህንነት አለው።" አለ ዳኘው ጨዋታው ስለ አጠቃላይ ሁኔታ እንደሆነ እንዲቀጥል በማሰብ። ቋቾ የደረሱት በማታ ላይ ነበር። መጀመሪያ ያዩዋቸው ሰዎች የጠላት ወገኖች መስለዋቸው ተሸማቀቁ። ከዚያም እነሱ መሆናቸውን ሲያውቁ በደስታ አለቀሱ። "አገር ደህና ነው?" አለ ዳኘው በአካባቢው ከሚያያቸው ሰዎች ሌላ ሌሎቹን በዓይኑ እየፈለገ።

"ምን ደህንነት አለ። እነ ልጅ ከፈለው ዙሪያ ምሁይ ምልጫ ዋሻ ተደብቀዋል። በአገራችን ብዙ ሰው ሞቱዋል።" አለች እህቱ ካብታሙዋ እንባዋ አቅርሮ። ለወንድሙዋ መመለስ ተደስታ የዘራችውን እንባ ደግሞ አሁን ለሙታኑ ልታንቆረቁረው የእንባ እጢዎቹዋ እያበጡ።

"በዚህም በኩል ጦርነት ነበር?" አለ ዳኘው ሆዱ የሚያውቀውን ከሰው አፍ ማወቅ ጓጉቶ።

"ኃይለኛ ተደርገው የማያውቁ ጦርነቶች፣ የጠላት ግፍ እንደ ፀጉር በዝቶ እንደ አዳባይ ሞልቶ ፈሰሰ።" አለች ካብታሙዋ በዓይነ ሕሊናዋ መከራው፣ ሞቱ፣ ግፉ እያለፈ። በሳንጃ እየተወጉ ከሳት የተጨመሩት ልጆች፣ ቤት ተዘግቶባቸው የተቃጠሉት አርበኞች፣ አዛውንት፣ ወጣቶች ትዝታ ምራቁዋን አድርቆት፣ ሆዱዋን አገላብጦት፣ ጉልበቱዋን አርዶት እየተዝለፈለፈች።

"አመመሽ ካብታሙዋ?" አለ ዳኘው እንዳትወድቅ እየደገፋት። ከዚያም ወሬውን ለመቀየር ፈልጎ የሚለው ጠፋውና እሱዋኑ ዓይን ዓይኑዋን እያየ "አንቺስ ደህና ነሽ?" አላት። እስካሁን አምቃ የያዘችው ከፌቱዋ ሁሉ እጥለቀለቃትና በእቅፉ ውስጥ እንዳለች አምርራ ማልቀስ ያዘች።

በየመንደሩ ለቅሶ ዋይታ በረከተ። ከሦስት ወር በኋላ የተመለሱት መንገደኞች እንሱ በሌሉበት ጊዜ የሞቱትን ዘመዶቻቸውን እርም እንዳይበሉ መርዶው ተነግሮአቸዋል። በመንደሩ ቀርተው ሙታኑን የቀበሩትም እንደገና ከነዚሁ ዘመዶቻቸው ጋር ማልቀስ ያዙ።

"አሁን ጣሊያኖች የት ነው ያሉት?" አለ ዳኘው ከመሃከላቸው የሚያውቅ ይኖር ይሆን በማለት በዓይኑ እየቃኘ።

"ጥንት ከነበሩት ምሽጎች ሌላ ብዙ ምሽጎች አቋቁመዋል። አሁን በየምሽጐቻቸው ነው ያሉት።" አለ አንድ ወጣት።

ዳኘው ከዚህ መቆየቱ በዚህ ግፍ በቀመሰ ሕዝብ ላይ ሌላ ግፍ ማስከተል መሆኑ ገባው። ስለዚህም ሌሊቱን አስራ አንዱን ሰዎች ይዞ እነከፈለው ወደሚገኙበት ቦታ ሄደ። ተክለሃይማኖት ግን መደበኛ ሥራውን ለማከናወን ወደ አዲስ አበባ ተነሳ።

"ምን ትሠራላችሁ እዚህ?" አለ ዳኘው የዱር ፍራፍሬና ስር እየበሉ ለወር በዋሻ ውስጥ የተቀመጡ ጓደኞቹን ደስ የሚያሰኝ መፍትሔ እንደያዘ ሰው በፈገግታ

እየተመለከታቸው። ሁሉም ተነስተው አዲስ ከመጡት ሰዎች ጋር መሳሳም፣ መጎሻሸም፣ እንደገና መሳሳም፣ መተያየት ቀጠለ።

“ምን እንደምንሠራ በኋላ እንነግራችኋለን። ብዙውን እስካሁን ሳትሰሙት አትቀሩም። ስለ እናንተ አጫውቱን፣” አለ ከፈለው ዳኘው ያለው ነገር ትዝ ብሎት። ዳኘው ከአገራቸው ከወጡ ጀምሮ ያጋጠማቸውን ሁኔታና በመጨረሻም ጦርነቱ እንዴት እንደተፈጸመ በዝርዝር አጫወታቸው።

“አሁን ራስ አበበ እንዴት ናቸው?” አለ ከፈለው። ራስ ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱ በአጠቃላይ በአርበኛው ንቅናቄ ላይ ያለውን ክብደት በማስተዋል።

“አሁን ችግሩ ሁሉ አልፉዋል።” አለ ዳኘው ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር እንደሌለ ለማሳየት ፊቱን በፈገግታ አጅቦ። “እናንተም ከኛ የተሻለ እንዳላጋጠማችሁ አየነው።” አለ ቀጥሎ ለእራት ያዘጋጁትን የዱር ፍሬና ቅጠላ ቅጠል እየተመለከተ። ከፈለው ደጋግሞ ስለቆሰለ ድካም

እንደሚሰማው አይቶ ልቡ በሃዘን እየተነካ።

“ጦርነት እንኳን ከአንድ ወር ወዲህ አልገጠምንም። ጣሊያን በየካምፑ ተመልሱዋል። ሄደን ብንገጥመው ወይም ብንተነኩሰው ያው መከራ ይመጣል ብለን ጊዜ እየተጠባበቅን ነው።” አለ ከፈለው ጦርነት ሳይደረግ ወር ማለፉ እስከ ሙሉ ክብደቱ ለዳኘው ሲናገረው እየተሰማው።

“ባለፍንባቸው ቦታዎች ሁሉ ሁኔታውን ተመልክተናል። ስለዚህ ሰዎቹን መልሱልኝና ከናንተም ሰው አዋጥታችሁ ብትሰጡኝ ሌላው ቢቀር ለምግብ አንቸገርም።” አለ ዳኘው ሊያጠቃው የሚችለውን ቦታ እያመዛዘነ። ከፈለው በሽታ ባይዘው ምን ሊያደርግ እንደሚችል ይገባዋል።

“እሱ ነገ ተነገወዲያ ይደርሳል። ሌላ ሌላውን አጫውተን። የማኅበሩ ጉዳይ እንዴት ሆነ?” አለ ከፈለው ዳኘው ከመንገድ እንደገባ ለመዝመት የተነሳው የከፈለው ችግር አሳስቦት እንደሆነ በማወቅ።

“የእርቁ ድርድር ስለፈረሰ እርቅ የለም። በተረፈ ግን ራስም ደብዳቤ ጽፈዋል።” አለና ዳኘው የደረቱን ኪስ የቆለፈበትን መርፌ ቁልፍ ፈቶ ደብዳቤውን አውጥቶ ሰጠ።

ከፈለው ደብዳቤውን በተመስጦ አነበበና “ዳኘው እንግዲህ የማኅበሩን

ማስፋፋት ቀጥልበት። ሁላችንም እንተባበርሃለን።” አለ።

በተከታዮቹ ቀናት የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ሥራ መጣደፍ ብቻ ሳይሆን አርበኞች በድል አድራጊነት ተመልሰው ቋቻ ገቡ። ከዚያም አዳባይን ተሻግረው በአንቀላፊኝ በኩል አልፈው ሳሲትን አጠቁ።

“ዳኘው ግንባርህ ጥሩ ነው አንተ ስለመጣህ ቀናን።” አለ ከፈለው ዳኘውን ለማሞገስ ፈልጎ።

“የአውሮፓ ጦርነት ነው የረዳን።” አለ ዳኘው ምስጋናው ደስ ቢለውም ስለበዛበት። ከኢጣሊያ ምሽጎች ወታደሮች እየተቀነሱ ወደ አዲስ አበባ መሄዳቸው ብቻ ሳይሆን አዳዲሶቹ ምሽጎች እየታጠፉ ነበር።

⅄ ⅄ ⅄

# አንድ ሌሊት በሁለት ሰዎች ሕይወት ውስጥ

ራስ አበበ፣ በማኀበረ በኩር ከጣሊያኖች ጋር ድርድር በጀመሩበት ወቅት፣ የተኩስ አቁም ስምምነትና ጣሊያኖች በአካባቢው የያዙትን ምሽግ ለአርበኞች ማስረከቡን ይጠይቅ ስለነበር፣ በአስካለ ላይም ጣሊያኖች የሚያደርጉት ክትትል እንዲቆም በመጠየቁ ጭምር፣ አስካለ ንብዋሻ ተዝናንታ ለመቀመጥ ቻለች።

አስካለ ይህ ሁኔታ እርሻ ለማረስና ሳይዘርፉ እራስን ለመመገብ በሚያስችል ሁኔታ ለመኖር ያስችላል ብላ ስላሰበች የአያቱዋን መሬት በወታደሮቹዋ ካሳረሰች በኋላ፣ የዘር እህል ግን ስለሌላት፣ የዘር እህል ፈልጋ ከንብዋሻ የአንድ ቀን የእግር ጉዞ ወደሚርቀው የአክስቱዋ አገር፣ የከሴ፣ እንዳትታወቅ ራሱዋን ሸፋፍና ሄደች።

ዳኘው በዚህ ቀን ከሚስቱ ከሸዋንግዥው ጋር ስለተጣላና ከአንድ ዓመት በፊት የወለደችለትን ሁሉም ይፈርን ትታለት ስለሄደች ስለኑሮው ሲያሰላስል ነበር። ዳኘው የተጉለትን በር ይዞ አዳባይን መልካውን እያስተዳደረ እንዲቀመጥ ሲወሰን ሸዋንግዥው አጀብ አጀብ የሚለው ሕይወቱ ጭራሹኑ ስለሰለቻት ወታደሮቹም በጥሩ ዓይን ሳይሆን በክፉ ዓይን ስለሚመለከቱዋት ጥላው ሄደች።

ሁሉም ይፈር በትናንሽ እጆቹ ዳኘውን አቅፎት ጢሙን በጉንጩ እያሻሸ ። “ጢምህ ይዋጋል!” እያለ እየሳቀ ይንፈራፈራል። ዳኘው እያንጎላጀ “ተኛ! ተኛ!” ይለዋል። ከዚያም ዳኘው ከአንድ አፋፍ ላይ ቆሞ ራሱን ያገኛል። ከዚያ ቦታ እንዴት እንደመጣ አያውቅም። ቤቱን ከአፋፉ ወዲያ ሜፍ ያየዋል። ሁሉም ይፈር ሲያለቅስ የሰማ ይመስለዋል። ቶሎ ቁልቁለቱን ለመውረድ ብሎ በሃረግ ላይ ተንጠልጥሎ ሲወርድ ከመሃል ገደል ላይ ሃረጉ ይበጠሳል።

ደንግጦ ተንስቶ ሕልም መሆኑን ሲያውቅ እንደገና ተመልሶ ተኛ። በጎኑ ተኝቶ ስለሕይወቱ ማሰላሰል ያዘ። ሁሉም ይፈር ከጎኑ ድብን አድርጎ እንቅልፍ ወስዶታል። ሌላ ሴት ባገባ ብሎ ማሰብ እንደጀመረ ሳይቀጥልበት እንቅልፍ እንደማሸለብ አደረገው። ከዚያም

ወደ ቅዠት ዓለም ሊገባ ሲል ባነነና በጨለማው ውስጥ አትኩሮ አስተዋለ። ከእግሩ ሥር አንድ የሚሄድ ነገር አየ። ደንገጥ ብሎ በደንብ አስተዋለ። ውሮ ነች።

“ምን ዓይነት የሚያቀባዥር ሌሊት ነው።” አለ ጮክ ብሎ። ምናልባት እንደ እሱ እንቅልፍ ያልወሰደው ሰው ካለ ለመጫወት በመፈለግ። መልስ ግን አጣ። ስለዚህ ተመልሶ እንቅልፍ እንዲወስደው እራሱን ማባበል ቀጠለ። ከዚያ በኋላ የሚያስደነግጥ ትዕይንት የሌለበት አንድ ሕልም አየ። ለሱ ሌሊቱን ሙሉ ሲያልመው ያደረ መስሎታል። ወፍ ሲንጫጫ ከጐኑ ያሉት ሰዎች በሕልሙ ጦርና ጋሻ እንደያዘ ሳያውቅ ነካ አድርገው አስነሱት።

“ታደሰ ከምን ዓይነት ሕልም ቀሰቀስከኝ መሰለህ?” አለ ዳኘው ጓደኛውን ታደሰን በፈገግታ እየተመለከተው። “ጥሩ ሕልም አየሁልህ።”

ታደሰም የታየለት ጥሩ ሕልም እንዲነገረው ቸኩሎ “ምን አለምክልኝ ዳኜ?” አለ።

“ያንን ቆንጆውን የቀኛዝማች እርገጤ የነበረውን ነጩን ፈረስ ታስታውሰዋለህ?” አለ ዳኘው የሚስቱ የፋናዬን አያት ፈረስ በዓይነ ሕሊናው እያስተዋለ። “በዚያ ነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጠህ የሽምጥ ትጋልባለህ። በእጅችህ የቀኛዝማች እርገጤን ጦርና ጋሻ ይዘህ ነበር። በአውድማው ላይ ስታልፍ ጦርና ጋሻውን ጣልከው። እኔም ጦርና ጋሻውን ጣልከው እያልኩ ስጠራህ ሳትሰማኝ ሽምጥ ግልቢያህን ቀጠልክ። እኔም የት እንደደረስክ ጠፋህብኝ። ጦርና ጋሻውን አንስቼ በእጄ እንደያዝኩ ባነንኩ።”

“ጥሩ አልመሃል።” አለ ታደሰ እንደመተከዝ ብሎ። “አንተ ከቀኛዝማች እርገጤ ዘር ልጆች ትወልዳለህ። ጦርና ጋሻ ዘር ነው። እኔ ግን ዘር የለኝም።”

ዳኘው የሕልሙ አተረጓጎም ባላሰበው መንገድ በመሄዱ ደንግጦ “ለምን? አንተ ነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጠህ ነው ያየሁት። ነጭ ፈረስ ደግሞ ጥሩ ነው። ለምን ዘር የለኝም ትላለህ። ፋናዬ ትወልድልሃለች።” አለ ጓደኛውን በቅሬታ እየተመለከተው።

“የለም ዳኜ። ነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጬ አየህ እንጂ የት እንደደረስኩ እንኳን አላየህም። ” አለና ታደሰ አቀረቀረ። ታደሰ ሕልም በጣም ያምናል። ዳኘው ለጓደኛው በጡዋት መጥፎ ነገር በመናገሩ አዝኖ ስሕተቱን ለማረም ሕልም አተረጓጐምም እንደ ታደሰ እንዳልሆነ ለማስረዳት ብሎ “ቀኛዝማች እርገጤ ሴት ልጅ የላቸው። እኔስ ከየት እወልዳለሁ ብለህ ነው። እንዲያው ቅዠት ነው።” አለ።

“የኔን ሚስት እህት አስካለን፣ አርበኛዋን አስካለን፣ ለምን አታገባትም?” አለ ታደሰ። ጓደኛ ለጓደኛው ሲያወራ ብዙም ሳይጨነቅ እቅጩን ተናግሮ ነው።

ዳኘው ስለ ሕልሙ ፍች ትቶ “እኔ ብጤየን የድሃ ልጅ አገባለሁ እንጂ ለምን ብየ የሃብታም ልጅ አገባለሁ።” አለ።

"አንተ ዛሬ ባሮ ሁዳድን የራስህ ያደረግህ ሀብታም። አስካለ ምን አላት።" አለ ታደሰ ስለ ጌትነትና ድህነት ካለ ዘመኑና ካለቦታው ሲወራ ገርሞት። "ደግሞም የህልሙም ፍች ይኸው ነው።" አለ።

ዳኘው ጨዋታውን ለመለወጥ ፈልጎ "ለመሆኑ ከዚህ ከነፃነት ማጣት በኋላ ብዙ ጊዜ ሕልም የምናልመው ለምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀና ሁሉም ሰው አያልም እንደሆነ ተጠራጥሮ "ሁላችሁም እንደኔ ሳታልሙና ሳትቃዡ አታድሩም?" አለ።

"እውነትህን እኮ ነው። ህልምና ቅዠት አይለየንም።" አለ ታደሰ ሕይወቱን በተመስጦ እየመረመረ። "ነገር ግን በነፃነቱም ዘመን ቢሆን ሌሊት ቁንጫውንና ትኋኑን ለመሸሽ እንደሆነ እንጂ ገና በሌሊት ተነስቶ ሰው ሁሉ ሕልሙን ሲናገር ሕልም ሲፈታ ነበር የሚያነጋው። ከሀብታሞች ቤት እንጂ። ፋናዬን መጠየቅ ነው።" አለ ፈገግ ብሎ።

"ቢሆንም እንደ አሁኑ አይሆንም። ዛሬ ዛሬ ብዙ ስለምንመኝ፣ ብዙ ስለምንጨነቅ፣ ብዙ ስለምናይ፣ በሞትና ሕይወት መሃል በየቀኑ ስለምናልፍ ይሆናል።" አለ ዳኘው ፍዝዝ ብሎ ግድግዳውን እየተመለከተ።

ዳኘውና ታደሰ ይህን በሚጫወቱበት ወቅት አስካለ የከሴ ላይ ሌሊቱን ያየችውን ሕልም ለአክስቱዋ ለወይዘሮ ላቀች እየነገረች ነበር።

"እነዚህ ጉዶች ከበውኝ ይመስለኛል።" አለች አስካለ ምናልባት ጀሮ ጠቢዎች የጣሊያንን መንግሥት የምትቃወም ሴት አለች ብለው እንዳያውቁባት ጣሊያኖችን "እነዚያ ጉዶች፣ እነዚያ ሰዎች ወዘተ፣" በማለት ትጠራቸዋለች። ሁለቱም ወደፊት መከራው ላይቀርላቸው መከራን በዚህ ሊያራዝሙት የሚችሉ እየመሰላቸው ብልሃት ይቀይሳሉ። "ንብዋሻ ወደ ገረገራ መውረጃው ገደል ላይ ይመስለኛል።" ስትል ቀጠለች አስካለ። "ከወንድሞቼ (ወታደሮቹዋን ነው) ጋር ተቀምጠን እሳት የምናነድ ይመስለኛል። እኔ ቡና አፈላ ነበር። መሰለኝ። አዎን ቡና ጥጄ ነበር። ቡናው ገንፍሎብኝ ውሃ በሸክና ልቀዳ ወደ እንስራው ዘወር ስል ስፍር ቁጥር የሌለው (ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ) ጣሊያን ከንብዋሻ አፋፍ ላይ ሲወርድ ተመለከትኩ። ቤታችንን ሊዘርፉት ነው። የአያቴን ጠበንጃዎች ይወስዱአቸዋል። ቶሎ ሮጬ ማውጣት አለብኝ ብዬ ስሮጥ ወንድሞቼ ተመልክተው ሮጠው ይዘው ከድንጋይ ሥር ያስተኙኛል። ወዲያው ተኩስ ይከፈታል። በሩቅ ቤታችንን ሳየው ባንዳዎች እየተሹለከለኩ ይመዘብሩታል። ምርር ብዬ አልቅሼ ቀና ስል ዳኘው፣ ከልጅ ከፈለው ጋር ያለውን ያውቁታል አይደለም? ካጠገቤ ሆኖ መትረየስ ሲተኩስ አየዋለሁ። "ከየት መጡ? እዚህ ነበሩ? እለዋለሁ። "የአያትዎን ቤት ሲያቃጥሉት ሊዘርፉት እንደሆነ በሩቅ በመነጽር አይቼ (ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ) ከጣሊያኖች በፊት ከቤቱ ውስጥ እነዚህን ጠበንጃዎች ይዤ መጣሁ ብሎ ጠበንጃዎቹን ሲሰጠኝ ባነንኩ።"

“ጥሩ ህልም ነው።” አሉ ወይዘሮ ላቀች ሕልሙዋን አውርታ ስትጨርስ እንዲተረጐሙላት የሚጠባበቁ ዓይኖቹዋን አትኩረው እያዩ። “ደግሞስ ጦርነት ከሆነ ከቅርብሽ ያለው ዳኘው አይደል?” አሉ እየሳቁ።

“ጠበንጃ ምንድነው?” አለች አስካለ።

“ጥሩ ነው። እረፈደ እንነሳ። ለመሆኑ ባል ለማግባት ታስቢያለሽ?” አሉ እንደዋዛ አድርገው።

“አላስብም።” አለች አስካለ ቅር በሉዋት።

“አስካለ፣” አሉ ወይዘሮ ላቀች ረጋ ብለው። “እኛ ሴቶች ከሰው ጋር ተዋውቆ መቀራረብና ማፍቀር መሃከል እምብዛም ለውጥ አናውቅ። የሚሆንሽን መርጠሽ ማግባት ነው። ዛሬ ጥንቱ አይደለም።”

አስካለ ዝም ብላ ወደ ውጭ ወጣች። ከእድሞው ቆም ብላ የከሴ አካባቢውን ተመለከተች። የእነ ዳኘውን በአገሩ መኖር ሳትናገሩ አደጋ አስደርሳችሁብናል በማለት ጣሊያኖች ከዓመት በፊት አገሩን በሙሉ አቃጥለውታል። የጥንቱና የዛሬው ትዕይንት አንድ አይደለም።

የየቤተሰቡ መኖሪያዎች ውስጥ ካሉት ቤቶች በቁልቋል እንጨት፣ በሸንበቆና በሰንበሌጥ የተሠራው ጣሪያቸው ተቃጥሎ የድንጋይ ክብ ግድግዳዎቻቸው እንደተከፈተ ጎተራ ቆመዋል። ዙሪያቸው በቃጠሎው በጥላሸት ጠቁሮ የሐዘን ልብስ የለበሱ ይመስላሉ። ከየአጥር ግቢው ጎን ጎተራዎች የነበሩባቸው ቦታዎች በከሰለ እንጨትና አመድ ተሸፍነው የቆሻሻ ማፍሰሻ መስለዋል። የድንጋይ ካብ አጥሮች ከላያቸው ያለው ሽምጣቸው ሲቃጠል በረገፈባቸው ከሰል ጠቁረዋል።

ጥንት በየእድሞአቸው በራፍ ተኮልኩለው ይስቁ ይሳለቁ የነበሩት ሰዎች አሁን ከቤት መዋል እንደጀመሩ ያህል አይታዩም። “አይ የከሴ ያ ሁሉ የደስ ደስሽ የለም!” ስትል አስካለ ብቻዋን ተናገረች። ተክዛ ቀና ብላ ሩቁን ተመለከተች።

ጎርጎው ዛፍ፣ እንቧጮው፣ ቁልቋሉ አብቦ መሬት ቀይ ለብሳለች። ድሮ ሞቅ የሚል ስሜት የሚፈጥርባት ይህ ትዕይንት ዛሬ የደም መፍሰስን አስታወሳት። መሬትም ቆስላ ደሙዋ የሚፈስ መሰላት። “ሰዎች ብቻ ሳንሆን አገራችንም፣ ምድሪቱም ቆስላለች።” አለች።

“አስካለ!” አሉዋት አክስቱዋ ላቀች ሳታስበው ደርሰውባት እጃቸውን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርገው። የአንገት ማስገቢያና ሰፊ የእጀች ቀዳዳ ያለው ሰፊው ቀሚሳቸው በመቀነት አሰር አድርገውት ሲቆሙ እጃቸውንም የሚሸፍን ሲሆን እጃቸውን ሲያነሱት ግን እስከብብታቸው ባዶ ሆኖ ሞቃቱ ክንዳቸው በአንገቱዋ ላይ የደስ ደስ ስሜት ነዛበት። “አስካለ ምነው ብቻሽን ቆምሽ?” አሉዋት ትኩር ብለው እየተመለከቱዋት በነዚያ ዓይኖቻቸው ውስጣዊ ስሜቱዋን ለማንበብ እየተጣጣሩ። “ፀጉርሽንም አበጥሪው።

እራስሽን አትጣይ ……” አሉና እጆቹዋን ጨበጥ አድርገው “እጆችሽ እንዴት ከስተዋል። ” ብለው ሲሉዋት ቀና ስትል እንባ ያዘሉትን ዓይኖቻቸውን አየቻቸው።

ጉንጮቻቸው ጐድጉደው ፀጉራቸው ሽበት አልብሱዋቸዋል። ባላቸው አቶ መርን ታስረው ከሄዱ በኋላ ሰውነታቸው እያለቀ ነው። አስካለ ግን ይህንን ለማንሳት አልደፈረችም። ልትጠይቃቸው የመጣችውንም ጉዳይ ትታዋለች። የነሱም ሁኔታ ከሱዋ ምንም ያህል አይሻልም።

“እትዬ እንግዲህ ነገ ወደ አገሬ ልመለስ።” አለቻቸው።

“ይሁን አስካለ …. እኔ ዘንድ ብትከርሚ ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን እሺ እንደማትይ አውቀዋለሁ። ….. ብቻ ተጠንቅቀሽ ኑሪ። አደራሽን። …. ራስ አበበ ወታደሮቹን ሲረከቡሽ ጥቂትም እርዳታ አላደረጉልሽ?” አሉ ከሳቸው እነሱ እንደሚሻሉ ገምተው።

“እንሱስ ምን አላቸው። ሁላችንም አንድ ነን።” አለችና አስካለ ይህን በመናገሩዋ ስጡኝ ብላ የጠየቀች ያህል አፈረችና “ደህና ነው ችግር ያልፋል።” ብላ ልታርመው ሞከራ አቅቱዋት ተደናገራት። “ይሁን አስካለ።” አሉ አክስቱዋ ጭንቀቱዋ ገብቷቸው።

ወደ ቤት ሲመለሱ ፀሐይ በማዶው ተራራ ስታቆለቁል ነበር። ከተራራው በላይ ሰማዩ ቀይ ቀለም ለብሶ ከመሃሉ ላይ ጥቁር ጉም የደረቀ ደም መስሎ ተለጥፎበታል። ይህንን አስተውላ ዘወር ስትል ወይዘሮ ላቀች ዐይናቸውን ጠበብ አድርገው እሱዋን ሲያዩ ደረሰች። “ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆኑ አመለካከታችንም ተለውጡዋል። ጦርነት ምን ጊዜም ባይኖር መልካም ነው፣” የሚል ሃሳብ ሽው አላት።

በበነገታው ለጉዞ ስትነሳ አክስቱዋ በግድ አንድ ቁና እህል ይዛ እንድትሄድ ሰጡዋት። “አስካለ ደብቄ ያስቀመጥኩት አስር ቁና እህል አለኝ። ሌላውን ዘርፈውታል። ይችን ግን በግድ መውሰድ አለብሽ።” ሲሉ በስልቻ የተቋጠረውን እህል አሳዩዋት።

አስካለም አያስፈለገኝም ስትል ብዙ ተከራከረች። በመጨረሻ ግን ተቀበለች። እየራቀች ወደ አገሩዋ ስትሄድ ይህን ያህል ብዙ እህል ማግኘቱዋ ደስ አላት። ንብዋሻ ስትደርስ ግን የእርቁ ድርድር ከፈረሰ መቆየቱንና ረግቶ መቀመጥም እንደማይቻል አወቀች። ከምሥሩ ላይ ግን ተቆንጥሮ ተንገርግቦ ከወታደሮቹዋ ጋር እየተጫወተች ስትቅም ከየከሴ ሮጦ የመጣ ገብረፃዲቅ ቁና ቁና እየተነፈሰ ገብቶ አክስቱዋ በጣሊያኖች ታስረው መሄዳቸውን አረዳት።

አፉዋ ውስጥ ያለውን ምሥር ተፍታ የሞቱ ያህል እየየ ብላ እያለቀሰች ከቤቱዋ በራፍ ወጣች። “ምነው ቅዠት በሆነ!” ስትል ተመኘች።

⅄ ⅄ ⅄

# ጋብቻ

አስካለ የወይዘሮ ላቀች መታሠር ሲያብከነክናት ቆየ። ጣሊያኖች እስረኞችን በምን ሁኔታ እንደሚይዙ ስትጠይቅ በጣም አሰቃቂ የሆኑ ወሬዎች እየሰማች ቀን ከሌት ማልቀስ ሆነ። ሳቆቴም ይህንን ሁኔታ በማወቁዋ ወደ ዋሻቸው እንግዳ ሲመጣ ቀደም ብላ አስካለ ስለ እስረኞች የሚያውቀውን ስትጠይቀው አለሳልሶ እንዲነግራት ማስጠንቀቅ ያዘች። አስካለም መጥፎ መጥፎውን ወሬ እያመነች ቆይታ አንድ ቀን ጣሊያኖች ከሜዳው አንቀላፊኝ ወደ ንብዋሻ እየመጡ መሆናቸውን ሰማች። የወይዘሮ ላቀችን ደም ለመበቀል ቆርጣ ከዋሻዋ ወጥታ ከንብዋሻ ጥገቱ እስከወታደሮቹዋ ብዙ ጉዳት ካደረሰች በኋላ ከአዳባይ መልካ ባሻገር ካለው አገር ዘመዱዋ የሆነ ሰው ስለነበር ወደዚያ ለመሄድ አፈገፈገች።

መንገዱዋ በነዳኘው መንደር በኩል ስለሚያልፍ፣ የአክስቱዋን ልጅ ፋናዬንና ባሉዋን ታደሰን በዚያው ጠይቃ ለማለፍ ወሰነች። ታደሰ በልጅነቱም ቢሆን ታታሪ፣ ጎበዝ ነበር። ፋናዬ ከአንድ አመሉዋ በቀር በጣም ደግና ተጫዋች ነች። ወንድ ከአየች ግን ልቡዋ ይሰለባል። ሰው ሁሉ ፋናዬን በመንገድ ሲያያት፣ ከቤት ሲያጫውታት ውሎ ከጓደኞቹ ጋር የሚላት ትዝ አላትና ከፋት። "ዓይኖቹዋ ወንድ ሲያዩ "እኔ እወድሃለሁ አንተ ትወደኛለህ?" የሚሉ ይመስላሉ።" እያሉ ፋናዬን ያሙዋታል። ፋናዬም ብትሆን ብቻዋን ካለወንድ ለማደር ደስ እንደማይላትና ያየችው ወንድ ሁሉ በፍትወት እንደሚያሰኛት ትናገራለች። በመንዝና አካባቢዋ ስለ ፋናዬ ውበት የማይናገር የለም። እጅግ በጣም ውብ የሆነ ቀለም፣ ዞማ ፀጉር፣ ትላልቅ ዐይኖች፣ ለግላጋ ቁመት፣ ሸንቃጣ ወገብ አላት። አዝማሪው፣ ድሃው፣ ጌታው ሁሉ ፋናዬን ያልጠየቀ፣ በፍቅሩዋ ያልተያዘ የለም። በአገሩ በሙሉ ሰው ሁሉ ስሙዋን የሚያነሳው፣ የሚዘፍንላት ካለምክንያት አልነበረም። የአገሩ ሴቶች በሙሉ በሴሰኝነቱዋ ቢሸረድዱዋትም፣ ቢጠሉዋትም፣ የሚገርማቸው ግን ይችን የመሰለች ሴሰኛ፣ ወንዱ ሁሉ ለምን እንደሚወዳት ነው። የሰው ማፍቀር አላት ይላሉ። በዚህም ይቀኑባታል።

"ፋና አሁን ይህን ጠባዩን ቢተው ምናለ? አረጀ ከእንግዲህ።" አለች አስካለ። በቤተ ዘመዳቸው ደንብ አንተ ብላ። አያታቸው ድንቅነሽ ብዙ ልጅ ስለሞተባቸው ልጆቻቸውን የሚነጥቃቸውን መጥፎ መንፈስ ለማሳሳት ወንዱን በሴት፣ ሴቱን በወንድ ስለሚጠሩ ቤተሰብ ይህን ፈሊጥ ተከትሎ አድጐበታል። "ታደሰን ካገባ ግን ተሸሎታል አሉ።" አለች አስካለ ስለፋናዬ ከሰዎች የሰማችውን እያስታወሰች። "ታደሰ ጎበዝ ሰው ነው። ፋና ደግሞ ጠንካራ ሰው ይፈራል።" ስትል አሰበችና የፋናዬ ፍራት ትዝ ብሎዋት ፈገግ አለች። "ፋና በድግነቱ ላይ ጨዋነት ቢያክል ግሩም ሰው ነበር፣" ብላ ደመደመችና ቀና ብላ ከሩቅ የሚመጡ ሁለት ሰዎች አስተዋለች።

ዓይኑዋን ጠበብ አድርጋ አትኩራ ስትመለከት ፋናዬና ታደሰ ወደ እርሱዋ ሲመጡ አስተዋለች። "አስካለ ዛሬ ተገኘህ። ከእኛ ጋር ብዙ ትቆያለህ፣" አለች ፋናዬ አስካለን አገላብጣ እየሳመች።

"ፋና ደህና ነህ? አልከሳህም። ተስማምቶሃል፣" አለች አስካለ የልጅነት ዘመን ሕይወታቸው እየተፈራረቀ በዓይነ ሕሊናዋ እያለፈ። "ታደሰ ደህና ነህ? ቤተሰብ ደህና? አገር ደህና?" አለች፣ ፋናዬን ስማ ታደሰን ስትስመው።

"ዛሬ ከኛ ጋር ሳታድር የምትሄድ አይምሰልህ!" አለች ፋናዬ አስካለን ከርሱዋ ጋር እንድትከርም ለጠየቀቻች ጥያቄ ያለመመለሱዋ ትዝ ብሎዋት።

"ጉዳይ አለብኝ። አላድርም።" አለች አስካለ ከፊቱዋ ላይ ውሳኔዋ እየተነበበ።

"አስካለ ይህ የማይሆን ነገር ነው። እንጣላለን። እሱን በኋላ እንመካከርበታለን። አሁን ወደ ቤት እንሂድ፣" አለ ታደሰ ቅር ብሎት። አስካለም ታደሰ ቅር መሰኘቱን አይታ የምታደርገው ጠፍቱዋት "ለማደር እንኳን አላድርም። ቤታችሁ ሳልገባ ግን እንዴት እሄዳለሁ።" አለች ፈገግ ብላ። ፋናዬም ታደሰም ደስ አላቸው።

ከቤት እንደገቡ ለአስካለና ለወታደሮቹዋ ንፍሮ ቀርቦላቸው ሲበሉ ታደሰ "አስካለ ዳኘው ቀድሞ ወርዱዋል። እንግዶች መጥተውብናል።" አለ እንዴት እንደሚያስቀምጠው እየተደናገረው። ጣሊያኖችን እንግዶች ይላቸዋል። "እኔም ያንቺን መምጣት ሰምቼ ነው የዘገየሁት። አንቺ ከፋናዬ ጋር ስትጫወቺ ጠብቂኝ። ትሄጂና እንጣላለን። ሙች ሁለተኛ አንነጋገርም፣" አለ።

"እኛው ነን ይዘንባችሁ የመጣንና እናግዛችኋለን፣" አለች አስካለ ጣሊያኖች ተከትለዋት የመጡ መስሎዋት።

"እኛ እንበቃለን። ብቻ አንቺ አታስቸግሪን። ከዚህ ስንጫወት ማደር አለብሽ። እኛ እንመልሰዋለን፣" አለ ታደሰ ከጠላት መምጣት እኩል የአስካለ መስተንግዶ እየጨነቀው።

"አስካለ ከዚህ ትቆይ። ላዩም አመም አድርጉዋታል። እኛ ከእናንተ ጋር እንውረድ፣" አለ የአስካለ የብቻ አጎቱዋ በአስካለ ወታደሮች ስም እየተናገረ።

"ይህ እንኳን ይሁን፣" አለ ታደሰ አስካለን ከቤት ለማቆያ ዘዴ አድርጎ ወስዶት።

"እኔም እወርዳለሁ፣" አለች አስካለ ቆጣ ብላ።

"አንተ ከዚህ ከኔ ጋር ቆይ አስካልዬ ስሞትልህ። ሥራ ታግዘኛለህ። ወንዶቹ ይውረዱ። በድንቅነሽ ሞት፣" አለች ፋናዬ ማሸነፊያዋን ግዝት አስቀድማ። አስካለ የምታደርገው ጠፍቱዋት ዝም አለች።

ዳኘው ታደሰ ከብዙ ሰዎች ጋር ሲመጣ አይቶት ግራ ገብቶት ቆሞ ይመለከት ጀመር። ታደሰ፣ የዳኘው ግራ መጋባት ምክንያት ገብቶት ጮክ ብሎ "የአስካለ ሰዎች ጋር ነኝ!" ሲል ተናገረ። ዳኘው አሁንም አላመነም። በክብ ውስጥ የገባ መሰለው። መነጽሩን አውጥቶ ተመለከተ። አስካለ ጋር ከዚህ ቀደም በእርግጥ ያየሁዋቸው ናቸው፣" አለና ተዝናና።

አስካለ ከፋናዬ ጋር ስትጫወት ትንሽ ከቆየች በኋላ “በል ወደ ማድቤት እንግባ። አመች ቦታ ይዘው ስለሚጠብቁ ቶሎ ድል አድርገው መመለሳቸው አይቀርም፣” አለች አስካለ ቀደም ብላ አወራረዳቸውን በሩቅ ስላስተዋለች። ማድ ቤት እንደገቡ አስካለ ዞሪያውን ቃኘችና “ምን ምን አለህ ፋና?” ብላ ጠየቀች።

“ሽንብራ ክክ ለወጥ አለን። እንጀራ እየተጋገረ ነው፣” አለች ፋናዬ ምኑ ከምን እንደሚሆን እየተጨነቀች።

“ከክክ ወጥ ሌላ ሽንብራ አሳ ወጥ፣ የሽንብራ ዳቦ ሊሠራ ይችላል። ግማሹ ክክ ይፈጭና እንየው። ተልባ የለህም?” አለች አስካለ ሽንብራውን በዓይኑዋ እየመዘነች። እነ ዳኘው ክልላቸውን ከጣሊያን ለማስከበር ከቻሉ ወዲህ በእህል በኩል ችግራቸውን እንዳስወገዱ ሰምታ ነበር።

“አለ፣” አለች ፋናዬ ደስ ብሎዋት። መሥራቱን እየሰነፈች እንጂ እሱዋም ጥሩ ጥሩ መብላት ትወዳለች።

“ከመንገዱ ስንመጣ ያለፍነው ጐመን የማነው?” አለች አስካለ የነሱ ሳይሆን እንደማይቀር ጠርጥራ። “ሳቆቴ ጐመን መቀቀል ታውቃለች፣” አለች ቀልደ አስመስላ። ካለፍላጎታቸው በአንድ ቀን ድግስ እንዳታከስራቸው አስባ ሃሳቡዋን ለመለወጥ መንገድ እየፈለገች።

“የኛ ነው። ጠላትን ገትረው መያዝ ከጀመሩ በኋላ እርሻውን እየሞካከሩት ነው፣” አለችና ወዲያው ዘወር ብላ “አበበች ጎመን ቀጥፈሽ ነይ፣” ብላ ተናገረች።

ዳኘው ታደሰ ይዞዋቸው የሚመጣውን የአስካለ ወታደሮች እንዳየ አንድ ሃሳብ ብልጭ አለበት። “አሥሩ ሰዎች በትንሹዋ ወንዝ መልካ ውስጥ ሳይታዩ ሂደው ከጠላት ጎን ተኩስ ቢከፍቱ፣ ጠላትም በሰላዮቹ በኩል የኛን ኃይል ስለሚያውቅ ሙሉ በሙሉ ከአፋፉ ላይ ካየን፣ ሳያስበው ጥቃት ልናደርስበት እንችላለን፣” አለ። በዚሁ መሠረት ጉዳዩ ተፈጽሞ ጣሊያንን ሞፈር ውሃ ወንዝ ላይ ሲዋጉ ጠላት ሳያስበው የአስካለ ወታደሮች በአዝብጤ አዝማችነት በጎን በኩል መጥተው ተኩስ ሲከፍቱበት የሞተበትን እሬሳ ሳያነሳ እግሬ አውጭኝ ብሎ እየተግተለተለ በመጣበት ጎዳና ተመለሰ። ከክብ ውስጥ የገባ መስሎት ስለነበር ሙያ የሠራ ይህል ሽንፈትን በፀጋ ተቀበለው።

ጀግኖቹ ወደ ሰፈር ሲመለሱ አይተውት የማያውቁት መስተንግዶ ቀረበላቸው። የአስካለ ወታደሮች አህል ካለ መስተንግዶው እንግዳ ባይሆንባቸውም የዳኘው ወታደሮች ግን የአስካለን ዝና ብዙ የሰሙ ቢሆንም በዓይናቸው ሲያዩት በጣም ገረማቸው። ታደሰ አስካለንና ዳኘውን ለማጋባት ሃሳብ እንዳለው ያውቁ ስለነበር ሁሉም ከታደሰ ጎን ተሰለፉ።

ታደሰ ዳኘውንና አስካለን ለማጋባት ያሰበው በአርበኞች ጋብቻ ሥነ ሥርዓት ነው። ሰው የዕለት በዕለት ተግባሩን እንደ እምነቱ ርዕዮት ያካሂዳል። እምነቱን ደግሞ ዘመን ይወስነዋል። ያወጣዋል። ከዚያ በዚያ ይራምዳል። ለመጥፎም ይሁን ለጥሩ ተግባር

የተሰባሰቡ ሰዎች በዚያ ዕምነታቸው ራሳቸውን ያስተዳድራሉ። ቀውጢ ቀኖችም እንደ ዱሮው መኖር ስለማይቻልባቸው አዲስ ፈሊጥ ይፈጥራሉ። የአርበኝነት ዘመንም የራሱ ፈሊጥና ዘይቤ ነበረው። ጋብቻም፣ ድግስም አጠር መጠን ባለ ዘዴ በጫካም በዱሩም ይካሄዳል። አስካለና ፋናዬ ወደ ውጭ ወጣ እንዳሉ ዳኘውን "አስካለ እንድታገባህ ዛሬ እንጠይቅልሃለን፣" አሉት። የታደሰ ወታደሮችና የራሱ ወታደሮች አንድ ላይ ሆነው።

"እኔ ብጤዬን የድሃ ልጅ ......" በማለት ዳኘው መናገር ጀመረ። "ዝም በል እባክህ!" ሲሉ ብዙ ድምጾች ጮሁ።

አስካለ ወደ ቤት ተመልሳ እንደመጣች ሁሉም ቆሙ። በእግዜር፣ በእግዜር ብላ ቶሎ አልፋ ተቀመጠችና ብትመለከት ሰው ሁሉ አልተቀመጠም። "ተቀመጡ እንጂ ምን ሆናችሁዋል?" አለች በመገረም።

"እሺ እስክትይን አንቀመጥም፣" አሉ ሁሉም።

"እሺ በያቸው አስካልዬ፣" አለች ሳቆቴ አስካለ እንዳትቆጣት በዓይኑዋ እያባበለች። አስካለም ወዲያው ጉዳዩን አወቀችው። ከዋናዎቹ ሽማግሌዎች መሃል አዝብጤ ቆሙዋል።

ዳኘው ከሰዎቹ መሃል አንገቱን ደፍቶ ቆሙዋል። በሕይወቱ ውስጥ ወሳኝ የሆነ አንድ ምዕራፍ ተዘርግቶዋል። አስካለን ማግባቱ ደስ የሚለውም ቢሆን እንቢ መባልን ደግሞ ከሁሉ ይጠላዋል። አስካለ እሺ የምትል ስላልመሰለው ጓደኞቹ ከእንዲህ ዓይነት ሀፍረት ሊከቱት መስሎት ጠላቸው። ወዲያው ደግሞ ለእሱም፣ ለራሳቸውም ሲሉ ያደረጉት መሆኑን አሰላስሎ፣ ሰው ምኞቱ ሊሳካለት ሲሞክሩለት አለመሳካቱን በማወቁ ሊረዱት የሚሞክሩትን ይጠላል?" ሲል አሰበ።

"አይዞህ እሺ ትላለች። በጣም ስለወደድካት ነው የፈራኸው። የሚወዱት ሰው እሩቅ የማይደረስበት መስሎ ነው የሚታየው፣" አለ ታደሰ ሃሳቡን እንዳነበበ ሰው እያፌዘበት። "ዘወር በል ብየሃለሁ፣" አለ ዳኘው ተቆጥቶ ግን ቀስ ብሎ። አስካለ ዳኘውን ጠልታው ሳይሆን ከለገሠ በኋላ ባል ላለማግባት በመወሰኑዋ እንቢተኛ ሆና አስቸገረች። በመጨረሻ ግን ሰው ሁሉ ከብዱዋት እሺ አለች።

በማግስቱ አስካለና ዳኘው ጎን ለጎን እንደተኙ ዳኘውን "ዓይንህ ለምንድነው ቀይ የሆነው?" ብላ ጠየቀችው። ቁመቱ አጭር፣ ዓይኑ ቀይ፣ ከወገቡ ጎንበስ ያለ ነው።

"የጎበዝ ዓይን ቀይ ነው፣" አለ እሱዋን ለሱ የትዳር ጓደኝነት የሚያበቃው ጀግንነቱ ይመስል። ከዚያም አፈር ብሎ ዓይኑን ሰበር አደረገ። ወዲያው በራፉ ተቆረቆረና "እህ ዳኘው?" ሲል ታደሰ ሳቀ።

ዳኘውም ካቀረቀረበት ቀና ብሎ "ጥርስህ ይርገፍ፣" ብሎ በፍቅር ዓይን እያየው ሳቀ።

"አሁን የመጣሁት እንግዶች ስለመጡብን ያንተንም፣ የአስካለንም ወታደሮች ይዤ መውረዴን ልነግራችሁ ነው። እናንተ ተከትላችሁን ድረሱ፣" አለና ወጣ። ጣሊያኖች የትላንትናውን ብድር ለመመለስ መጥተዋል።

⅄ ⅄ ⅄

# ጣሊያንና ሥልጣኔ

ለአርበኞችና ለጣሊያኖች የጦርነት መረማመጃ ለሆኑት ገጠሮች ሕይወት መራራ የነበረችውን ያህል በአዲስ አበባ የመሸታ ቤት ለከፈቱት ሴቶችና ወንዶች ደግሞ ገባያቸው እንደዚያን ጊዜ ደርቶላቸው አያውቅም።

ቀደም ሲል ከጋለሞታና ከመጠጥ የተቆጠቡት ወንዶች አሁን የሚያመሹት በየቡና ቤቱ ከጋለሞታዎች ጋር ነው። ከጦርነት የሚመለሱት ጣሊያኖችና ባንዳዎች ከመጠጥና ከጋለሞታ በቀር የሚታያቸው የለም። ተፈላጊዎቹ ጋለሞታዎችና መጠጦችም በብዛት ወደ መሸታ ቤት ይጎርፋሉ።

አዲስ አበባ በመሸታ ቤቶች ተጥለቀለቀች። ሲኒማ፣ ቲያትር ቤቶች ተስፋፉ። ሁሉም ሰው እውነታውን ለመርሳት የሚፈልግ ይመስል ሃሳቡን የሚካፈሉት እነዚህን ቦታዎች አዘወተረ። ግማሹ ነፃነት በማጣቱ፣ የተዋረደ አገዛዝ ለህሊናው ስለከበደው፣ ስለተረበሸ፣ ወደነዚህ ቦታዎች በመሄድ ከህሊናው ይርቃል። ሌላው እለት በእለት የአርበኞች ጥይት ነፍሱን የምትወስድ እየመሰለው በረጅም ዘመን ሊቀጭ ያሰበውን ደስታ በአጭር ጊዜ ሊወጣው ይፈልጋል። ዓላማ ባይኖረውም የወቅቱ ሁኔታ ሽብር የፈጠረበት ከእውነታ ለመራቅ ወደነዚህ ቦታዎች ይመጣል።

ለጦርነት ማጓጓዣ አዳዲስ መንገዶች ሲከፈቱ፣ የማምረቻ መሣሪያዎች ሲቋቋሙ፣ እነዚህ ሁሉ የሰው `ይል ስለሚፈልጉ ከአፄ ሚኒሊክ ጀምሮ ባሪያ መፈንገል የተከለከለ ቢሆንም፣ ገና በእርግጥ ነፃ ያልወጡት ወይም ሁኔታው ከባሪያ ያልተሻለ ሁኔታ ላይ ያስቀመጣቸው የድሮ ጌቶቻቸውን ከጣሊያን ወይ ከአርበኛ ጋር ሆነው ለመዋጋት ወይም አርበኛ ለመሆን ያልቻሉት ሴቶችና ወንዶች በነዚህ ሥራዎች ተሠማሩ። ለግማሾቹ ሴቶች በከተማዎች ውስጥ የመሸታ ቤቶች ክፍት የሥራ ቦታ አስገኙላቸው። መንደሮች በጣሊያን መድፍ ሲታረሱ፣ በአውሮፕላን ቦንብ ሲቃጠሉ፣ አመድ ሲሆኑ፣ ቤተሰብ ሲበተን፣ ግማሹ ወደ ዱር፣ ሌላውም ወደ ከተማ ሲወጣ፣ ለቆነጃጅት ሴቶች መሸታ ቤቶች የአዲስ ሕይወት መጀመሪያ ሆኑ።

ከተማዎች በጥንት መልካቸው አልቆዩም። የቅኝ ግዛት ምዝበራ ምሽግ ሆነው አዲስ ወግና ፈሊጥ ያዙ። ከተማዎች እንዴት እንደተለወጡም አርበኞች ሁልጊዜም ይሰማሉ።

በውጭ አገር፣ በፈረንጅ አገር፣ ጥንት ትምህርት የተከታተሉት አርበኞች እንግዳ ባይሆንባቸውም ለአገሬው አርበኞች አዲስ አበባን ብቻ ለሚያውቁት ግን ግራ ነበር። ከመንዝ የውስጥ አርበኞች ተክለሃይማኖት በዓመት አራት አምስት ጊዜ ወደ አገር ቤት ይመጣል።

"እንዴት ነው አዲስ አበባ?" ብለው ይጠይቁታል።

"መንገዱ በሙሉ ዳር ዳሩ መሸታ ቤት ሆኑዋል።" ይላል ስለ ጣሊያን ቪላዎችና አዲስ ሕንፃዎች ይልቅ የሞራል ዝቅጠቱ ስለሚያስገርመው።

"የኛም ሰፈር?" ሲል ድሮ አዲስ አበባ የነበረ አርበኛ ይጠይቃል። የሱ ሰፈር የነበረው ከዚህ ዓይነቱ ወራዳ ተግባር የራቀ እንደነበር እያስታወሰ።

"የአቶ ዘነበ ቤት፣ የአቶ ፈለቀ፣ የወይዘሮ ዘርትሁን ቤቶች በሙሉ ጠጅ ቤት ሆነዋል። የባላምባራስ ለጥይበሉ ቤት ትልቅ ቡና ቤት፣ ትልቅ ቆንጆ መጠጥ ቤት ሆኑዋል። አዳዲስ ቤቶች ተሠርተው እንደዚሁ ሆነዋል። መንገድ ዳር ያሉ ብዙ ቤቶች ወይ ልኳንዳ፣ ወይ የአረብ ቤት፣ ሱቅ ሆነዋል። ጣሊያኖችም ብዙ ሰቀላ ቤቶች ሠርተዋል። ሁሉም ተለውጡዋል። ብትመለስና ብትመጣ ሳይጠፋህ አይቀርም።

"እዚህ ሁሉ መሸታ ቤት ማን ይጠጣል?"

"ሁሉም ሰው ይጠጣል። ወታደሩም፣ ነጋዴውም፣ የቢሮ ሠራተኛውም፣ ጣሊያኑም ይጠጣል። ሁሉም ጣሊያን ከዚህ በተረፈ ድግስ እየደገሠ ከቤቱም ያጠጣል ይጠጣል። ሁሉም መሸታ ቤቶች ገባያ ለመሳቢያ ብዙ ሴቶች አሉዋቸው።" ይላል ተክለሃይማኖት በሰሚዎቹ ላይ የሚፈጥረው ስሜት እየታየው ፈገግ ብሎ።

"ሴቶች እንዴት ገበያ ያመጣሉ?" ይላል አንዱ በመደነቅ።

"ከሴቱዋ ጋር ለማደር የመጣው ሁሉ ይጠጣል። ጣሊያኖች ለአንዲት ሻንቅላ ለአንድ ቀን አዳር ብዙ ሰዎልዲ ይከፍላሉ። ከዚህ የነበረችውን የወለቱን ልጅ አሁን ብታዩዋት ይገርማችኋል፣ ወርቅ በወርቅ ሆናለች። ትባልግ እንጂ ጨዋ ናት። ጠባዩዋ አልተለወጠም። ከአገራችንም የስንቱ ጨዋ ልጅ በዚህ ሥራ ተሠማርቱዋል መሰላችሁ! ከራስ አበበ ጋር ያለ አንድ አርበኛ ሚስት የአንድ ጣሊያን ቅምጥ ሆና አይቻት እንዴት አዘንኩ መሰላችሁ?"

"ከጣሊያኖች ጋር የአገራችን ሴቶች ያድራሉ? ስትቀልድ ነው?"

"የምሬን ነው።"

"ከካቶሊክ ጋር፣ ከፈረንጅ ጋር?! ሊጥ ከሚመስል ሰው ጋር፣ ከእስላም ጋር ያድራሉ?"

"አዎን።"

“የታባታቸው። መስቀል ማረድ ነበር!”

“ጣሊያን ከአገራችን የሚፈልገው ሴቶቻችንንና ስንዴ ነው!” አለ ተክለሃይማኖት ተከዝ ብሎ።

“እንዴት? ሴቶቹንስ እንዳልከን ይሁን። ስንዴው እንዴት ነው። ምን ይተርፈዋል ብለህ ነው።”

“እኛ የምንበላውንና የምንጠጣውን የምንወደውን ሳይሆን እሱ ለፓስታ ለፉርኖ የሚፈልገውን ገበሬው እንዲዘራ እያስገደደ ነው።”

“እኔም ዳቦ እወዳለሁ። ግን ሁለተኛ ስንዴ አልዘራም።” ይላል አንዱ አርበኛ በእልህ።

ተክለሃይማኖት ለአርበኞች ያመጣላቸውን ጨርቅ ይሰጣቸዋል። ከከተማ ባላገር የሚመላለሰው በነጋዴ ስም ነው። የጣሊያን ሠራዊት ውስጥ ሥልጣን ያለው የውስጥ አርበኛ ተክለሃይማኖት ጥሩ ሰላይ ስለሆነ ለጣሊያን አርበኞችን ይከታተላልና ሊቸንሳ ይሰጠው ብሎ ለኢጣሊያዊው አዛዥ አቅርቦት ሊቸንሳ ተሰጥቶታል።

ወደ አገር ቤት በመጣ ቁጥር ሁሉም ከበው ስለከተማው ወሬ እንዲያወራላቸው ይገፋፉታል። ይደከመውና ሰበብ ፈልጎ ጨዋታውን ይቀይራል።

ተክለሃይማኖት ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ ለጣሊያኖች ምን እንደሚነግራቸው ከከፈለው ዘንድ መመሪያ ይቀበላል። ሁልጊዜም ቢሆን ንግግራቸው የሚከተለውን ይመስላል።

“ስለ ጣሊያን የጦር እንቅስቃሴ አቀረብኩ። ለጣሊያኖች ምን ልበላቸው?”

“አንተ አርበኞች ያሉት ከዚህ አሁን ካለንበት ቦታ ነው ብለህ ንገረው። ቁጥራችንን ሲጠይቅህ አምስት መቶ ይሆናሉ በለው።”

“ይኸማ እውነቱን መናገር ነው። የመጣስ እንደሆን?”

“መምጣቱም እኛን ማግኘቱም ያስፈልጋል። እኛም ጠብቀነው ድንገት እንደደረሰብን አድርገን እናፈገፍጋለን። ይህ ካልሆነማ አያምንህም።”

“የተጠቃችሁስ እንደሆነ?!” ይላል ተክለሃይማኖት በመገረም።

“በምናውቀው አገር፣ በጥሪ በምንረዳዳበት አገር፣ አውቀን በምንጠብቀው ጊዜ እናጠቃዋለን እንጂ አያጠቃንም።”

በዛሬው አመጣጡ ግን ተክለሃይማኖት የተሰጠው መመሪያ የዚህ ዓይነት አልነበረም። በአርበኛው መሃል ከፍተኛ የተስቦ በሽታ ገብቶ ረፍርፎታል። ለመዋጋት ቀርቶ ለማፈግፈግ እንኳን የሚችል ሠራዊት አይደለም። ስለዚህ ከፈለው ዘንድ ለመሰናበት እንደቀረበ “መቸም እንደምታየው ተስቦ ገብቶ ሁሉም ወድቋል። ስለዚህ ለጣሊያኑ ከዚህ ቦታ የሉም ብለህ

ንገረው። ወደ ደንገዜ በርሃ ወርደዋል ሲባል ሰምቻለሁ በለው። የዚህን ጊዜ አልፎን ሄዶ ተንከራቶ ይመለሳል። እኛም ተኩሰ አንከፍትም።

ይህ በሆነ በሁለት ሳምነቱ ጣሊያን አርበኞች ወርደዋል ወደተባለበት ቦታ ሲጉዋዝ በአርበኞች ሠፈር ግን አርበኞች የሉም ተብሎ ስለተነገረው ተዝናንቶ ይራመድ ነበር። በዚህን ጊዜ የጣሊያን ጦር አዛዥ እንደ ቀኝ እጁ የሚመካበት የውስጥ አርበኛው መምሬ ወልደሃኔ ዙሪያውን ለመቃኘት በሚል ሰበብ ወደ ግራ ካለው ተራራ ወጣ። ብዙም ሳይቆይ የከፈለው ባልደረባ የሆነ ከከፈለው ሰፈር ራቅ ብሎ በዋሻ ውስጥ ከነወታደሮቹ የመሸገው ዘውዴ ጉልች [58] እየተዝናና በሚሄደው በጣሊያን ጦር ላይ የመትረየስ ተኩስ ከፍቶ እረፈረፈው። የጣሊያን ጦር ሰልፍ ተሰባብሮ ብትርምስምሱ መሃል የጫነውን መድፍ ሁሉ ጥሎ ወደ ኋላ ፈረጠጠ።

መምሬ ወልደሃኔ የተኩስ ድምጽ ከመስማቱ በቀር ምን እንደሆነ አልገባውም። ብቻ ቶሎ ብሎ አቆራርጦ ከዋናው የጣሊያን ጦር ለመድረስ ሲያመራ ድንገት ከሚያፈገፍገው፣ አሁን ከተሰበሰበው የጣሊያን ጦር ጋር ተገናኘ። ጣሊያኑ ጦር አዛዥ መምሬ ወልደሃኔ ከነወታደሮችህ ተሰለፍ ብሎ አዘዘ።

መምሬ ወልደሃኔም እስከነወታደሮቹ ምንም ሳያወላውል ተሰለፈ። ጉዳዩ ሁሉ አልገባውም። ከዚያም የጣሊያኑ ጦር አዛዥ ከመምሬ ወልደሃኔ ጎን እነደማለፍ ብሎ ግንባሩን በሽጉጥ መትቶ ጣለው። አብረውት የነበሩትም የአገር ተወላጅ ወታደሮች በጥይት ተደበደቡ። “ከዳተኛ ምሱ ይህ ነው። ተክለሃይማኖትስ የታል?” ሲል ጣሊያኑ አዛዥ ተናገረ።

ብዙም ሳይቆይ የጣሊያን ጦር ውርደቱን ተከናንቦ ከምሽጉ ገባ። ፀሐይ ከአድማሱ ልትጠልቅ ደም በለበሰችበት ሰማይ ሥር ከሁለት ከተራራቁ ቦታዎች የመምሬ ወልደሃኔና የወታደሮቹን ሬሳ፣ በአሻገሩ የጣሊያንና የባንዳዎቹን ሬሳ፣ እየተመለከተች ብዙም ሳትቆይ ጠለቀች።

በማግስቱ አርበኞች ምርኮአቸውን ካነሱ በኋላ የውስጥ አርበኛቸውን ሬሳ ለማንሳት ወደ መምሬ ወልደሃኔ ሄዱ። እሬሳውንም ሲያነሱ ከኪሱ ከከፈለው የተጻፈለትን ደብዳቤ አገኙ። ጣሊያኑ የገደለው በተኩሱ ሰዓት ከዚያ ባለመኖሩ ተጠራጥሮ ሁለተኛም ድክመቱን በሱ ለመለጠፍ እንጂ በእውነት ሰላይነቱን አምኖ እንዳልሆነ አወቁ። አርበኞቹ ግን ሁሉም አለቀሱለት።

“ዘውዴ ምነው እንዲህ አደረግህ?” አለ ከፈለው።

[58] ዘውዴ ጉልች ከነፃነት በኋላም መንዝ ውስጥ በመንግሥት ላይ ሸፍተው ዋሻቸው ከገቡ በኋላ ታስረው በምህረት ተፈቱ።

"እኔ መቸ ምክሩን ሰማሁ። ጣሊያን ያለንበትን አውቆ የመጣ መሰለኝ እንጂ።" አለ ዘውዴ ጉልች በአንድ በኩል ያገኘው ድል ቢያስደስተውም የውስጥ አርበኞቹ ሞት አስተከዞት።

"እሱስ ውነትህን ነው። ብዙ ሰው በተስቦ ወድቆብን መልእክተኛም ቸገረን፣" አለ ከፈለው በተራው ተክዞ።

ወዲያው አንድ ባላገር እየሮጠ መጥቶ የዚያን እለት ተክለሃይማኖትም

መገደሉን ነገራቸው።

"እንዴት ሞተ?" አለ ከፈለው ሬሳውን ከነመምሬ ወልደሃኔ ጋር ባለማግኘቱ ተደንቆ።

"ማገሩ ከፊቱ አቅርቦ ግንባሩን በጥይት መታው።" አለ ትዕይንቱ እየሰቀጠጠው።

"ማን ነገረህ?" አለ ከፈለው ከሰው የሰማውን የሚነግረው መስሎት።

"በዓይኔ ነው ያየሁት።" አለ ባላገሩ ዱላውን ሞርከዝ ብሎ ያን ትዕይንት እንደገና በዓይነ ሕሊናው አምጥቶ ለማየት እየሞከረ።

ለሁሉም አርበኞች ውሎ ተዋለላቸው። አርበኞች ቃሬዛ አዘጋጅተው፣ ቃሬዛውን ጨርቅ አልብሰው ከመሃከላቸው አስቀምጠው፣ መላቀሻ እንዲሆናቸው መስቀለኛ እንጨቶች ሠርተው እንጨቶቹን ኮት አልብሰው፣ የመጀመሪያውን የመሞቱ ማስታወሻ ሁለተኛውን በቁሙ ሳለ እንዴት እንደነበር ለማስታወሻ አድርገው አለቀሱ። በጀግና ቀብርም መሥረት እየተፎከረ፣ እየተሸለለ፣ ሥራው እየተወሳለት ለሁሉም ውሎ ተዋለ።

ከውሎው በኋላ ዳኘውና አስካለ ጎን ለጎን እንደተቀመጡ "ልጄ

ተክለሃይማኖት የሞቱ አይመስለኝም።" አለች አስካለ።

"መሰለሽ፣ አልመሰለሽ ምን ያደርጋል። እሱ እንደሆነ ሞቷል።" አለ ዳኘው የልጅነት ጓደኛው ትዝታ ይዞት ሄዶ። ወታደርነት ለመቀጠር አዳባይን ሲሻገሩ ታየው። ጣሊያኖች አዲስ አበባን እንደያዙ ጉለሌ ሲሰነባበቱ ዳኘው ተክለሃይማኖት ታየው። ብዙም ሳይቆይ ተክለሃይማኖት በውስጥ አርበኝነት መንዝ መጥቶ ሲገናኙ የነበረው ደስታ ታየው። ዳኘው ከሃሳቡ ሲነቃ ተክለሃይማኖት አለመኖሩ ታይቶት ዓይኖቹ እንባ አቀረሩ።

ሁሉም ሰው ከተክለሃይማኖት የተሠራለትን ውለታ የዚያን ዕለት በህሊናው ሲቆጥር በልብስ መግዛትም ሆነ በምክር በመልዕክተኛነት አላገለገለኝም የሚል አልነበረም።

አርበኞች ስለከተማው ወሬ የሚነግራቸው እምብዛም አላጡም። ስለጣሊያን ወታደራዊ ንቅናቄ ግን የሚያገኙት ወሬ እንደሚቀዘቅዝ አውቀዋል።

በአዲስ አበባ ውስጥ ኑሮ እንደበፊቱ ቀጥሉዋል። አዲስ አበባ ከምን ጊዜውም ይበልጥ ብዙ ሰዎች ታስተናግዳለች። የኢጣሊያ ወታደሮች ከሰሜን አፍሪካ ጭምር እያቋረጡዋት ወደ ደቡብ ይጓዛሉ። በየመንገዱ ዳር የሸማው፣ የኮንትሮባንዱ፣ የፍራፍሬው፣ የዳቦ፣

የቆሎው፣ ንግድ ተስፋፍቶዋል። የጨርቃጨርቅ ንግድ ከመሸታው መስፋፋት ጋር አብሮ አድጉዋል። አዳዲስ ሕንጻዎች ለጣሊያኖች መኖሪያና ለመሥሪያ ቤትነት ተሠርተዋል። ለጣሊያኖች የሚያገለግሉ ትላልቅ መደብሮች ተከፍተዋል። በግ በረት ለጣሊያኖች ብቻ መኖሪያነት ስለተከለለ ብዙ ቪላ ቤቶች ፈሰውበታል። ወታደራዊ ንቅናቄ ግን ከተማዋን በወሬ ያውዳታል።

"ምን ተፈጥሮአል? ብዙ ወታደር ወደ ታች ወረደ እባክህ።" ይላል አንዱ ሰው።

"አርበኛው በደቡብ በኩል አይሏል። የኦሮሞው፣ የወላሞው፣ የጉራጌው አርበኛ አላነቃንቅ ብሎ ነው።" ይላል የአገር ፍቅር ያለው ሌላ ሰው፣ ሁሉን እንደምኞቱ ተርጉሞ።

"አይደለም ጀርመኖች ጣሊያኖችን በሱማሌ በኩል ስለወረሩ ነው።" ይላል ሌላው በፈረንጆች መሀከል በመልካቸው ልዩነት እንደማያይ ሁሉ የተለያየ መጠሪያቸው እየተደናገረው።

"እንግሊዝ ጣሊያንን ከሱማሌ አስወጥቶ ወደ ኢትዮጵያ እየገሠገሠ ነው።"

መሸታ ቤቶችና የመዝናኛ ቦታዎች በወቅቱ ሁኔታ ሰውን ሁሉ ወደ እነሱ እንደመሰብሰባቸው ያህል ወሬም ከአፍ አፍ በአፋጣኝ እንዲተላለፍ አስችለዋል። በሦስት ሰዓት የተሰማው ወሬ ከተማውን ሲያዳርስ ቆይቶ በአራት ሰዓት በሌላ ተተክቶ መልሶ ከዚያው ቦታ ይደርሳል። ብዙም ሳይቆይ የመጀመሪያው እንደገና ተጠናክሮ ይቀርባል። ሰው እንደ ወገን እንደወገኑ፣ እንደፍላጐቱ የራሱ ወገን ያደረገውን ጀብዱ ሲያወራ ለድል የተቃረበ ይመስላል።

እንደወሬው ዓይነት የሰውም መንፈስ ይለወጣል። የአርበኞች ማየል፣ የእርዳታ መምጣት፣ የንጉሡ መመለስ ሲወራ በጣሊያች አገዛዝ የተንገፈገፈው በቅኔ ጣሊያኖችን መተረብ፣ የጣሊያን ባንዳዎችን መገላመጥ ይጀምራል። ወሬው ተቀይሮ የጣሊያኖች ማየል ሲሰማ ነገሩ የተገላቢጦሹን ይይዝና ቀድሞ ተገላማጭ ገላማጭ፣ በፊት አቀርቃሪው ዓይን አሰባሪ ይሆናል።

አዲስ አበባ እንደ ጥንቱ ብዙ ልውላንና ራሶች የሉዋትም። በነሱ ምትክ አስተዳዳሪዎች የሚባሉ ሰዎች ተተክተዋል። ጥንት ለንጉሡ ነገሥቱ ታማኝነቱን አረጋግጦ የራሱ የወታደር ኃይልና የፍርድ ችሎት ኑሮት ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ይገዛ የነበረው ሁሉ ዛሬ ዘመናዊ አስተዳደር በሚል የራሱ የወታደር ኃይል ሳይኖረው፣ ራስ ደጃዝማች ሳይሆን የጣሊያን ሹም ያስተዳድራል። በአጼ ሚኒሊክ የተመሠረተው ዘመነ መሳፍንትን የሚያከትመው፣የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን ከፍ የሚያደርገው፣ የማዕከላዊውን መንግሥት ሥልጣን ከፍ በማድረግ ወደ ከፍተኛ ሥልጣኔ ድልድይ የሆነው የማዕከላዊ የፖለቲካ፣ የአስተዳደርና የሶሻል አውታሮች እያንዳንዱ መስፍን፣ ንጉስ፣ ቋሮ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ መሆኑ ሆኖ በውስጥ አስተዳደሩ ግን ፈላጭ ቆራጭ የነበረው አሠራር በኢጣሊያኖች የማዕከላዊ የአስተዳደርና የዕዝ ውጣ ውረድ ፍርክስክሱ ወጥቱዋል። ጣሊያኖች የየአገሩን ንጉሦች፣ መሳፍንቶችና ቆሮዎች እየገደሉም፣ እየነቀሉም የራሳቸውን አስተዳዳሪዎች ሾሙባቸው። የባላባቱን ጠርም

በራሳቸው መደበኛ ሠራዊት ተኩት። እየተንገዳገደ የነበረው ዘመነ መሳፍንት አከተመ። አንዳንድ ባንዳ ንጉሶችን፣ መሳፍንትን እንኳ ከጣሊያኖች ጋር እንዲሠሩ ቢደረግም የጣሊያን ቡርጅዋ አስተዳደር መዋቅር ተቀጥላ እንጂ የጥንቱ ፈላጭ ቆራጭ አልነበሩም።[59]

ከዚህ ለውጥ ጋር ግን በከተማዎች ውስጥ የአዲስ ዘመን ብሩህ ተስፋ የለም። ገጠሩ እንደጨለመበት ከተማዎችም ደንዝዘው ነፍስ አጥተዋል። ሁሉም ይደበታል። ትናንሽ ከተማዎች እንኳን ከዚህ በሽታ አላመለጡም። አዝማሪው የሰውን ልቦና ያንፀባርቃል።

ከነገሥታቱ አገር ዴይሴ ላይ ነው ማደር

በማታው ጠጥቶ በነጋው ለመስከር።

ሌሊቱን ሙሉ በውሀ ጥም እንዳረረ ወይም ነገ የሚጠጣ ነገር ይጠፋል እንዳሉት ሲጠጣ፣ ሲዘላብድ ያመሸው በበነገታው ወደ አዳባባይ ሲወጣ ተንዠባርሮ ነው። አንዳንዱ "ለዚች አላፊ ሕይወት መጨነቅ አያስፈልግም።" ይላል ከጎኑ የረገፉ ዘመድ፣ ባልደረባና ባዕዳንን በዓይነ ሕሊናው እየቆጠረ። ሌላው "እስረኛና አዲስ ወግ፣ አዲስ ባሕል ጠራቂ ባዶነት የሚሰማው፣ የሚፈልገውን ስለማያውቅ ነው። ስለዚህ ይጠጣል አይረካም፣ ይበላል አይረካም። መፍትሔ ይሆነኛል ያለው መፍትሔ እንዳልሆነው በተግባር እያየው ራሱን ይስታል። ያጣው ነፃነት ሲሆን ነፃነት ደግሞ በምግብና በመጠጥ አይካካስም።" ይላል። ሦስተኛው ጉድ ዘመን መጣ ይላል። ሌላው መኪናውን የሚያነቃንቀው ሰይጣን ሰውን ሁሉ ለከፈው ብሎ ይከራከራል።

አርበኞች በሠፈሩባቸውና በሚያስተዳድሩዋቸው ገጠሮች የጥንቱ ሹማምንት የሉም። አርበኞች ራሳቸው አስተዳዳሪ ሆነዋል። በሚያውቁትና በለመዱት ወግ ያስተዳድራሉ። አንዳንዱ ዘመን ያነሳቸው ይላቸዋል። ሌላው ጀግና ይፈጠራል እንጂ አይወለድም ይልላቸዋል።[60] ባሕላቸውን፣ ወግ ፈሊጣቸውን፣ የሚያውቁትን መንገድ መጠበቃቸው ነፃነታቸው ነው። የጣሊያኖችን የአስተዳደር ዘይቤን ስላልቀመሱት ወይም ስላላዩት አይጨነቁበትም። ከጣሊያን የሚያውቁት አረመኔነቱን ነው። ውጭ አገር ተምረው የነበሩ አርበኞችም በቅኝ ግዛታዊ ካፒታሊዝምና በአገር ቤት ካፒታሊዝም መሃከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ። ለአገሬው አርበኛ ከጣሊያን ጥሩ ነገር ቢያውቅ የመንገድ ሥራውና ፉርኖው ነው። የደብረሲናን ዋሻ ቀዶ ሲሠራው አድንቀውታል። ሃበሻን አስገድዶ ኩሉ በማድረጉ ሸንቁጠውታል። ከፉርኖው ዘርፈው ቀምሰውለታል። የፓስታ ሹታ ነገር ግን ያስቃቸዋል።

[59] አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ በትዝታ መጽሐፋቸው ንጉሥ ነገሥቱ ከኢጣሊያ ወረራ በፊት በደቡብ የአካባቢውን ባላባቶች በተሿሚዎች ተክተው ስለነበር፣ ጣሊያን ካሸነፈ በኋላ ባላባቶቹ ከጣሊያኖች ጋር ስለመቆማቸው የሚያነሱት ነጥብ አለ።

[60] ልጅ ኃይሌ ባልቻ ግንቦት 10 ቀን 1930 ለልጅ ከፈለው ወልደ ፃዲቅ በጻፉት ደብዳቤ፣ አርጋው የሚባል አርበኛ፣ ጊዜ የጣላቸውን የቀድሞ ባላባቶችና ሹሞች ድሮ ገላምጠውኛል ብሎ አሁን በጉልበቱ ባገኘው ሥልጣን ግፍ እየሠራ መሆኑን በመግለጽ፣ ልጅ ከፈለው ተሳስቶ እንዳይደግፈው ጽፈዋል።

አንድ ጊዜ ከተጉለት አርበኞች በቀለ ደነገጤ [61] ከነባልደረቦቹ ከማረካቸው እቃዎች ውስጥ እረገኘሁም ሰንበሌጥ የሚመስል ነገር አገኘ። "ምንድንው ይኼ?" አለ።

"ምኑ እባክህ? እስቲ! እስቲ ልየው። ሰንበሌጥ አይደለም?" አለ ጋሻጃግሬው በወረቀት የተጠቀለለ ሰንበሌጥ መሳይ ነገር እያገላበጠ እያየ።

"የፈረንጅ ሰንበሌጥ ነው። ዳቦአቸው የኛን ዳቦ እንደማይመስል ሁሉ ሰንበሌጣቸውም አይመስልም።" አለ ለእንቆቅልሹ መልስ ያገኘ መስሎት ደስ ብሎት።

"ሰንበሌጥ ምን ሊያረግለት በወረቀት ጠቅልሎ ይዞ ያመጣል?" አለ በቀለ፣ ሰንበሌጥ ነው ብሎ ቀደም ሲል ቢያምንም እንደገና ተጠራጥሮ።

"ኢጋሰሱን፣ በቅሎውን ሊያበላው ነዋ! ኢጋሰሱና በቅሎው ወድሎ አላየኸውም ጋሼ?" አለ የበቀለ ባልደረባ እርግጠኛ ሆኖ።

እነሱም ለከብቶቻቸው "አዲሱን ሰንበሌጥ" ሰጡ። ከብቶቻቸው ግን ያልለመዱት ስለሆነ አልደፈሩትም።

በቀለና ጓደኞቹ ስለ ፓስታ ካወቁ በኋላ ፓስታ ባዩ ቁጥር ይስቃሉ።

ዳኘው የአርበኞችን አስተዳደር ዘይቤ ሲያስታውስ ይገርመዋል። ከተራ ገበሬነት አስተዳዳሪ መሆኑ፣ አባቶቹ ለስንት ትውልድ ተከራክረው ያላስመለሱትን ባሮ፣ አስካልና ጆርን በእጁ ማድረጉ ታምር ይመስለዋል። በጀግንነት የንጉሡን ልጅ ያገባው ድሃ ተረት በሰላሙ ጊዜ ሊደረስበት የማይቻለው በቀውጢ ቀን ቀረብ ይላል። ዳኘው የአዳባይ መልካ አስተዳዳሪ፣ የተጉለት በር ጠባቂ ሆኖ ግዛቱን እያሰፋ ወደ ተጉለትም ያመራል። ደንገዜ አብዛኛው ከተለቀቀ በኋላ ከፈለው ወልደ ፃዲቅ የዳኘውን ወንድም ወልደሰማዕትን[62] ገዥ አድርጎ ሾሞታል።

ወልደሰማዕት ከዳኘው ጋር ወደ ከተማ ኮብልሎ ወታደርነት ለመቀጠር ፈቃደኛ ያልነበረ፣ ወታደርነትን የማይወድ ቢሆንም በዚህ ቀውጢ ወቅት ግን ታላቅ አዋጊና ተዋጊ ወጥቶታል። አሁንም ምኞቱ ግን ጦርነቱ ቶሎ አልቆ፣ ነፃነት ሲመለስ ከትውልድ መንደሩ ተመልሶ ግብርናውን መቀጠል ነው።

ዳኘው ጋደም ብሎ ይህንን እያሰበ በሃሳብ ሲዋልል ሚቹ ተክለሃይማኖት በራፉን እየቆረቆረ እየጠራው ነው። ኢጋንንት ማለት ነው። ኢጋንንት ሲጣራ ደግሞ ወይ አይባልም። መናገር መንቀሳቀስ ቢፈልግም ደግሞ አይችልም። መጣራቱን አቁሞ ይቆረቁራል። አስካለ ድንገት ነቃችና "ማነው?" አለች። በራፉ ተከፍቶ ተክለሃይማኖት ረጅም ቁመቱ ከእድሞው

61 ቀኛዝማች በቀለ ደነገጤ በኋላ ደጃዝማች።

62 ወልደሰማዕት ዘለልክ በኋላ ግራዝማች።

እንዳይጋጭ ጎንበስ ብሎ ገባ። "ሞቱዋል ብላችሁ ውሎ ዋላችሁልኝ አሉ። ውሸታም ሰው ነው ያወራችሁ።" አለ እየሳቀ።

ዓመታት የሚመስሉ ትንሽ ቅጽበቶች አለፉ። ልባቸው እየተንደፋደፈባቸው ሁሉም ሳሙት። እሳት እንደገና ነዶ ራት ቀርቦ እየበሉ በኋላም ጋደም ብለው ስለዚህ ታምር የሚመስል ነገር እያወሩ ብዙ ቆዩ። "ለመሆኑ እንዴት ተረፍክ?" አለ ዳኘው ድንጋጤ፣ ደስታ የሰወረው ልቡ ሲረጋጋ።

"ያኛው የኛ ደጋፊ ካራሜሪ በወልደሃኔ ላይ የደረሰውን ሲያይ ልብስህን ለውጥ ብሎ የወጥ ቤት ልብስ አልብሶ ሸፋፍኖ አዲስ አበባ አደረሰኝ። ያቺ ክፉ ቀን እንዲህ አለፈች።" አለ ተክለሃይማኖት ተናግሮ፣ አውርቶ የማይጨርሰው የመሰለውን ነገር መናገር ሲጀምር ቶሎ ተጠቃሎበት።

"እግዜር ትረፊ ያላት ነፍስ። ለእግዚአብሔር ምን ተስኖት። አላወቁብህም?" አለ ዳኘው። ሌሎቹም ብዙ ጥያቄዎች ደረደሩለት። ያን ሁሉ ጥያቄ ሲመልስ ታሪኩን በሙሉ ለማጫወት ብዙ ሰዓት ፈጀበት። ስለነመምሬ ወልደሃኔም እየደጋገሙ ጠየቁት። ወዳጅ ዘመድ የሞተበት ሁኔታ እንዴት እንደነበር ደጋግመው ቢያወሩት፣ ቢሰሙት አይሰለችም። እያንዳንዱ ወሬ ከሙዋች ልብ የሚያደርስ ይመስላል። በታምር የሞተውን ሰው እንዳልሞተ ማረጋገጫ የሚያስገኝ ይመስላል።

በመጨረሻም "አዲስ አበባ እንዴት ነው?" የሚለው የተለመደው ጥያቄ ቀረበ። እንዴት ብሎ ማስረዳት እንደሚችል አያውቅም። እነሱም የተለወጠውን ነገር በልቦናቸው ለመገመት እንኳን መሰሉን ወይም ቀረቡን አይተው አያውቁም። ዝም አለ።

⅄ ⅄ ⅄

# እንቁላል የምትወደው ጣሊያን

ሰኔ 1932 የጣሊያን ሠራዊት ከሞላሌ ምሽጉ ወጥቶ ከከፈለው ቤት ከእመወታ አርበኞችን ለመያዝ መጣ።

እመወታ ማርያም በሰኔ ትነግሳለች። የዚህን እለት ከአካባቢው አገሮች ሕዝቡ በሙሉ ወደዚህ ይመጣል። ባሻገሩ የግምጫ ማስጫ ኪዳነ ምህረት በየካቲት ስትነግስ ደግሞ የአካባቢው አገሮች ሕዝብ ወደዚያ ያመራል። የከሴ አቦ በመጋቢት አምስት ሲነግሱ ደግሞ ከመንዝም ከተጉለትም አካባቢዎች ሕዝቡ ወደዚያ ይሄዳል። አንድ የመልከኛ አገር ታቦት በሚነግስበት ጊዜ (ሁሉም አገር የራሱ ታቦት አለው) ሁሉም ሰው ጠላ ጠምቆ፣ ዳቦ ጋግሮ፣ ቆሎ ቆልቶ፣ እንጀራ ወጥ አዘጋጅቶ ይደግሳል። መንደሩ በሙሉ ደጋሽ ይሆናል። ስለዚህ

ወንዝ እያቋረጠ የሦስትና የአራት ሰዓት መንገድ ተጉዞ የሚመጣው እንግዳ መስተንግዶ አያጣም። ሌላው አገር ድግስ ሲኖር ንቅል ብሎ የሚጉዋዘው ሕዝብ በየአገሩ አስር ጊዜ በልቶ ሌላው አገር በሙሉ ነቅሎ ሲመጣበት ከየአገሩ የመጡ አስር ሰዎችን ማስተናገድ ብድር መመለስ ነው። ያለው ሀብታም ግን በየሄደባቸው አገሮች ካስተናገዱትም ሌላ ከቻለ እልፍ ሊያበላ ሊያጠጣ፣ ሃብቱን ሊያሳይ፣ ሰውም ሊያከብረው ይችላል።

ከፈለው የእመወታን በዓል በአገሩ፣ በቤቱ ለማሳለፍ ባደረገው ድግስ እመወታ ለተጉለት አዋሳኝ የሆነች የመንዝ አገር ስለሆነች ከአካባቢው የመንዝና የተጉለት መንደሮች ብቻ ሳይሆን ከሩቅም ቦታ አርበኞችን ግብዣ ጠርቶ ነበር። በር ለመጠበቅ ጥቂት ሰዎች ከመተዋቸው በቀር እነዳኘውም ከአዳባይ መልካ ሙልጭ ብለው መጥተዋል።

ጨዋታው እየደራ ሄዱዋል። ከምግብ በኋላ መጠጡ በገፍ ቀርቡዋል።

እቴ ሙኒት ሙኒት……እቴ ሙኒት ሙኒት

እቴ ሙኒት ሙኒት እቴ……ሙኒት ሙኒት

አይ! ይይ!..........ኤይ……አይ……አይ!

"እንካ ነጠላ፣" አለች አስካለ። ዳኘው ትንሽ ሞቅ ብሎት ካለ ነጠላ መሬቱን በእግሮቹ በፈረቃ እየመታ ሲጨፍር። ዳኘው መጠጥ በጠጣና ሞቅ ባለው ጊዜ ጎባጣ ወገቡ ቀጥ ይልና ዝምተኛ አፉ ተከፍቶ የታፈነ መንፈሱ ተፈቶ መጨፈር ይወዳል። ዳኘው ነጠላውን ተቀብሎ እያጣፋ መጨፈሩን አላቋረጠም። አስካለ ወደ ቦታዋ ስትመለስ ከኋላዋ እየተከተለ እየጨፈረ ሸኝቱዋት ተመለሰ። ዳኘው ትከሻውን ሲያርገበግብ ወደ ሰማይ በኃይል ሲዘል ሰው ሁሉ በደስታ ሲመለከተው አስካለም እየሳቀች ትንሽ ተመለከተችውና ወጣ አለች።

"እትዬ እነጋሼስ? …..ደርሰውብናል፣" አላት ከቃፊሮቹ የተላከው መልዕክተኛ።

ሰውን በታላቅ ደስታው ጊዜ መርዶ ማርዳት፣ ለመርዶው ተቀምጦ ደስታ መንገር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ አስካለ ታውቃለች። "ቆይ እኔ እነግርልሃለሁ። አንተ ከማድ ቤቱ ገባ በልና በቁምህም ቢሆን አንድ ሽክና ጠላ ተጎንጭ።" አለችው።

"ሰውና ግንድ አንድ ነው፣" ስትል አሰበች። "አንድ ግንድ ከውሃ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቢያስቀምጡት አይበሰብስም። በፀሐይ ላይ ለረጅም ጊዜ ቢያስቀምጡት አይበሰብስም። አሁን ከውሃ ውስጥ ወዲያው አውጥቶ ከፀሐይ እንደገና ውሃ እያሉ ቶሎ ቶሎ ካፈራረቁበት ግን በቶሎ ይበሰብስና ይንኮታኮታል። በደስታ መሃል ችግር ማውራት የሚከብደውም እንደዚህ በመሆኑ ነው። ጦርነትም ቶሎ የሚያስረጀን ለዚህ ነው።" ስትል እራሱዋ በራሱዋ ደመደመች።

ወደ ቤት እንደገባች ለማንም በተናጠል ሳይሆን በደፈናው ለሁሉም "ምነው እናንተ ጨዋታ አበዛችሁ። አደጋስ ቢደርስ። ባይሆን ጠበንጃችሁን ይዛችሁ አትጠጡም።" አለች። ከመቅጽበት ሁሉም አንድ ነገር ነካቸው። ቢደርስ ብሎ ነገር ……………አስካለ ቀስ ብላ

ለዳኘው ስለጣሊያኖች መምጣት ነገረችው። ዳኘውም ሞቅታው ሁሉ በነነና ከአፋም ከአረማመዱም ቆጠብ ብሎ ጉዳዩን ለከፈለው ነገረና ወታደሮቹን አሰባሰቡ።

ወታደሮቹ ከቤት ወደ ጦር ሜዳ ሲወጡ አስካለ በገንቦ ጠላ ይዛ እየሳቀች "ውሃ እንዳይጠማህ" እያለች ትቀዳለቸዋለች። በፊቱዋ ላይ የሚያዩት መዝናናትና የጨዋታው ግዴለሽነት እየተጋባባቸው እነሱም ይቀልዳሉ።

"እትዬ ባንዳ ሳይሆን ዛሬ ጣሊያን ገድዬ ስፎክር የምጠጣው ከዚህ ጠላ አቆይኝ።" አለ ቀድሞ የለገሥ ጋሻጃግሬ የነበረው ወጣት አስካለን እንደ እናቱ በፍቅር እየተመለከታት።

"እሺ! እንዲያውም ያልተከፈተ እንሥራ ካለበት ቤት ሄጄ አስመጣልሃለሁ።" አለችና አስካለ አደጋ እንዳይደርስበት ሰግታ "ጠንቀቅ እያልክ የኔ ልጅ።" አለችው ፍራቱዋ ከፊቱዋ እንዳይነበብ አቀርቅራ። ወታደሮቹ ወደ አፋፉ ሲወርዱ ከፈለው ዘወር ብሎ ለሚከተለው ሕዝብ "እናንተ ተጫወቱ። ድግሱ ይቀጥል። እኛም ከዚሁ ያለን ይምሰለው። በአሳቻ መንገድ ወርደን ተራራውን ወርዶ ከወንዙ ሲገባ ጉድ እንሠራዋለን፣" አለ።

ጣሊያኖች የአገሪቱን ባሕል እየተላመዱት ስለሄዱ በእመወታ ድግስ በተደረገ ጊዜ ሳይታሰብ ደርሰው ከፈለውንና ለድግሱ የመጡትን አርበኞችን ለመያዝ አቅደው ስለነበር ከሞላሌ ምሽግ ሆኖ መንዝን አስተዳድራለሁ የሚለው ጣሊያን ወታደሩን አግተልትሎ መጥቱዋል።

"ዳኘው አንተ የቱን ቦታ ትይዛለህ?" አለ ከፈለው።

"ግራውን እይዛለሁ።"

"ሁልጊዜም ከባዱን ነው የምትመርጠው።" አለ። ይህ ግን ለማንም የተናገረው አልነበረም።

አዘናግቶ ለመድረስ ሲክለፈለፍ የጣሊያን ጦር ሳያስበው ከተራራ ወርዶ ወንዙ ገብቶ ተራራውን ለመውጣት ሳይችል፣ ከወንዙ ሊደርስ ሲል፣ ወደ ኋላና ወደ ፊት ከማይልበት ቦታ ላይ ተኩስ ተከፈተበት። በዚህን ጊዜ ጦሩን ይመራ የነበረው ቲሊንቲ ማርኩኝ በማለት እጆቹን ወደ ላይ አወጣ። አርበኞችም ቲሊንቲንና አልጋ አንጣፊዎቹንና ወጥ ቤቶቹን አምስት ባንዳዎች ማረኩ።

ከድሉ በኋላ አርበኞች ባደረጉት ስብሰባ ስለ ምርኮኞቹ ውይይት ቀጠለ።

ግማሹ ጣሊያኑንም ባንዳዎቹንም መግደል ነው አለ።

"የለም።" አለ ዳኘው። "በጦር ደንብ መሠረት ምርኮኛ አይገደልም።"

"አገሩን የወጋ ባንዳ ምርኮኛ አይደለም። ጣሊያኑ እንደፈለገው ምርኮኛ ቢባልም ዋናው ጠላታችን ባንዳ ነው።" አለ አንደኛው አርበኛ።

“ልጅ ግዛቸው ያደርጉት እንደነበረው እነዚህ ባንዳዎች ወደ እኛ እንዲመለሱ አድርገን ከኛ ጋር ጠበንጃ ይዘው ለአገራቸው ይዋጉ። ካልሆነም ወደ ሰፈራቸው ተመለሰው ስለ እኛ መልካም ነገር መናገራቸው ጥሩ ነው።” አለ ከፈለው።

ብዙ ክርክር ተደረገ። በመጨረሻ ግን ቲሊንቲን ዳኘው እንዲጠብቀው ተሰጠ። የዚህን ጣሊያን ስም ያወቀው የለም። ብቻ ባንዳዎቹ ክቡር ቲሊንቲ ስለሚሉት አርበኞቹ “ቲሊንቲ” አሉት።

አስካለ ቲሊንቲ እንደመጣ በሩቅ ሆና ብዙ አጠናችው። ስለ እሱ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ይገድሉኛል ብሎ በማሰብ ዓይኑ ክርትት ይላል። “መልኩ ያልበሰለ ሊጥ ይመስላል። ቅርጹ እንደ እኛው ነው። ዓይኖቹ የድመት ይመስላሉ። የሚያዩ ሳይሆን እንደመስተዋት ዓይነት ናቸው።” ስትል አስካለ አሰበች።

ዳኘው ወደ ቤት ይዞት እንደመጣ አስካለ “ቲሊንቲ እርቦሻል?” አለችው በአማርኛ ቋንቋዋ። በጣምልስልስ የሆነ ያልጠነከረ ትንሽ ነገርን በሴት ጾታ እንደምትጠራ ሁሉ ቲሊነቲኒም አንቺ እንጂ አንተ ብላው አታውቅም። እያደር ግን ወንድሞቹዋን አንቺ እንደምትለው ያህል ተሰማት። “ቲሊንቲ እርቦሻል?” ብላ የጠየቀችውን ባለመመለሱ አማርኛ እንደማያውቅ ትዝ ብሎዋት በምታውቀው በወላይትኛ ቋንቋ ጠየቀችው።

አሁንም ቀና ብሎ ከማየት በቀር አልገባኝም ለማለት ያህል ብቻ አንድ ነገር እየተንተባተበ እራሱን ነቀነቀ። ዓይኖቹ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ተስፋና ደስታ ተነበቡ። አስካለ ክፉ እንዳልሆነች አወቀ።

አስካለ እንጀራ በበርበሬ ወጥ አቀረበችለት። የሚበላ ነገር በማግኘቱ ተደስቶ ቆርሶ ሲቀምሰው አቃጠለውና ተወው። “በርበሬ መብላት አትችልም ይች ቲሊንቲ!” አለች አስካለ። ደረቁንም እንጀራ ለመብላት ሞክሮ ሲያቅተው አየች።

አስካለ አንድ ሃሳበ መጣላት። ጣሊያኖች ይበላሉ እየተባለ የሰማችው ብዙ ነገር አለ። እንቁራሪት፣ ትል፣ ፈረስ፣ ውሻ ይበላሉ ይባላል። ከሁሉ በላይ ግን እንቁራሪትና እንቁላል ይወዳሉ እየተባለ ይወራል።

ሃሳቡዋን አሙዋልታ የተመለሰችው ከግማሽ ሰዓት በኋላ ነበር። ከመንደር መንደር ዞራ አራት እንቁላሎች ይዛ መጥታ በድስታ አድርጋ ጣደቻቸው። ከበሰሉ በኋላ አውጥታ ውሃውን አፍስሳ በረድ እስኪሉ ድረስ አንዲቱዋን እንቁላል ላጠችና “እንቁላል ሃም! ሃም!” አለችው እንደ መብላት እያደረገች እንቁላሊቱዋን በእጁዋ ይዛ።

አሁንም እየተንተባተበ አዎን ለማለት ራሱን ቀና ቀና እያደረገ ፈገግ አለ። እወዳለሁ ማለቱ እንደሆነ ከቋንቋው ሳይሆን ሁሉም ሰው ሲጉዋጉዋ በሚታይበት ጠባይ አወቀችው። የቲሊንቲ ሊጥ የሚመስል እጅ እንዳይነካት እየተጠነቀቀች ሰጠችው። ባንድ ጊዜ አልጎምጉሞ ዋጣት። ሁለተኛውን፣ አራተኛውን እንቁላል ሰጠችው። ሁሉንም በላቸው።

አስካለ ደስ ብሎዋት ስቃ አካባቢው ለነበሩት ሰዎች እነሱ እንዳላዩት ሁሉ "ቲሊንቲ እንቁላል ትወዳለች!" ብላ ተናገረች።

ቀስ በቀስ ቲሊንቲ አስካለ እንደ እናቱ ያህል እንደምታስብለት አወቀ። ከዚያም ዳኘው ከተንጨባረረው ፀጉሩ፣ ከኮስትራ ግንባሩ ሥር አዛኝ መሆኑን ተረዳ።

አስካለ ወደ ሥራ ወይ ወደ ጦርነት ስትሄድ "ደህና ሁኝ ቲሊንቲ!" ትለዋለች። ቲሊንቲም "ደህና ሁኚ" ማለትን ለመደ። ወንዱንም ሴቱንም 'ደህና ሁኚ!' ይላል። አስካለ ያስተማረችው ፈሊጥ ብለው ሁሉም አርበኞች ፈገግ ይላሉ።

እሱን ለማስደሰት ሲሉ እነሱ በስንት መከራ የሚያገኙትን እንቁላል ከየቦታው እየፈለጉ ሲያቀርቡለት ውለታቸው ከበደው። ዳኘው ለወታደሩ ስጋ በታረደ ጊዜ ጥሬውን ሲበሉ እንዳይጓጓ ቀደም ብሎ እንዲጠብሱለት ስለሚያስልክለት እሱም በወቅቱ ይበላል። አበሻ ጥሬ ስጋ ሲበላ ሲያይ መጀመሪያ የሚያስደነግጠው ዛሬ ተላምዶታል። "ጥሬ ስጋ ቢበሉም ከፍተኛ ሥነ ምግባር ያላቸው ናቸው።" እያለ ያስባል።

ሁልጊዜም ግን ምን ቢወዱት ከሱ ራቅ ማለትን እንደሚፈልጉ ያውቃል። አስካለ እንኳን እጁ እንዲነካት እንደማትፈልግ ያውቃል። ይከነከነዋል። የክፋት እንዳልሆነ ግን ያውቃል። ይህንን እንቆቅልሽ ለመፍታት ብዙ አሰቦበታል። አስካለ ግን ያልበሰለ ሊጥ አድርጋ ወስዳው እንደሆነ እስከ መጨረሻው አላወቀም።

⅄ ⅄ ⅄

# ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ

ቲሊንቲ አርበኞች የሱ ወገኖች እንደሚያደርጉት በአንድ እስር ቤት የመታሠርና በየጊዜው ለምርመራ እየተጠራ መጉላላት ባይደርስበትም፣ አብዛኛውን ጊዜውን ከዳኘው መኖሪያ ቤት እንዳይወጣ ስለሚከለከል፣ ከሰዎች ጋር እንደፈለገው እንዲደባለቅ ስለማይፈቀድለት እሥረኛ መሆኑ ይሰማዋል። ሌሎች የአገሩ ሰዎች የሆኑ እስረኞች ጓደኞች ስለሌሉት ደግሞ ጠባቡን የእስር ዓለም ለመፍጠር አልቻለም። እስረኞች እርስ በርስ ጓደኛ ሆነው ትንሽ ተስፋ ሲሰሙ የሚፈነድቁበት፣ ትንሽ ሲከፋቸው እንደ ሕፃን ልጅ የሚነጫነጩበት፣ በጠባቡ ዓለማቸው ውስጥ ማህበራዊ አኑዋኑዋር የሚመሠርቱበት፣ የራሳቸው የሆነች ክልልና ሕዝብ ቲሊንቲ የለውም። አማርኛ ባለማወቁ ደግሞ ከማራኪዎቹ ጋር ለመጫወት አልቻለም። የሱን ሁኔታ ከሁሉ በላይ የሚያስከፋ አድርጐ ወሰደው።

አርበኞችም ጠባዩን ገምግመው ከሌሎች ሰዎች ጋር እንደፈለገው እየተደባለቀ ከመንደሩ ሳይወጣ በአይን ቁራኛ እየተጠበቀ እንዲኖር ፈቅደውለት እንኳን ደስተኛ አልሆነም።[63]

አንዳንድ ጊዜ ስለ አርበኞች ሁኔታ ሲያስብ ውለታቸው በጣም ይከብደውና ለምን ቀደም ሲል አረመኔ አድርጐ ይገምታቸው እንደነበር ይገርመዋል። አርበኞች ጣሊያኖችን ይዘው አንገታቸውን ቆርጠው ገበያ ላይ የሚሰቅሉበት የነበረውም ሁኔታ ይታወሰዋል። እያደር ሲያስበው ግን በእርሱ አካባቢ አርበኞች ይህን ማድረግ የጀመሩት ጣሊያኖች የአርበኞችን ራስ እየቆረጡ በአካባቢው መስቀል ከጀመሩ በኋላ እንደነበር ትዝ አለው። እሱስ ራሱ ቢሆን ይህን ሲያደርግ አልነበረም? አሁን አርበኞች ይህን ቢያውቁ የሚሰቅሉት ስለሚመስለው ይፈራል። እያደር ግን እነዚህ መልካቸው አውሬ የሚመስል አርበኞች ስሜታቸው፣ ፍርዳቸው፣ የእስረኛ

አያያዛቸው የሰለጠነው ዓለም ከሚለው በላይ ሆኖ በማግኘቱ እያከበራቸው ሄደ። ይህን የልቡን ስሜትም በቋንቋ ሊገልጽላቸው ስላልቻለ በእንጨት ፈለጣ፣ በቤት ሥራ በኩል ሳይጠይቁት ተሽቀዳድሞ በመሥራት የሆዱን መልዕክት ለማስተላለፍ መሞከር ያዘ።

ቲሊንቲ አርበኞች እንደማይገድሉት እርግጠኛ ከሆነ በኋላ ሳያውቀው ቀኑንም ሌሊቱንም ሃሣቡ ሴት ሆነ። ፍትወት። ዓይኑ እንደተገለጠ ከዚህ ቀደም የሚያውቃቸው ሴቶች ጋር የፈጸመው ፍትወት ሁሉ እንደዚያን ጊዜው ሆኖ ይታየዋል። ሌሊት፣ ዓይነ ሕሊናውን ጨለማው ስለሚያበረታው ይሁን በሌላ ምክንያት ሁልጊዜም ሴሰኛ ውሽሞቹ ይበልጥ ግልጽ ሆነው ይታዩታል።

ከጊዜ በኋላ ግን በአፉ ተናግሮ የማይገልጸው ሃሣቡ እየታፈነበት፣ ይበልጥ ከራሱ ጋር መጫወት፣ በአካባቢው የሚያያቸው ሴቶች ሁሉ በፍትወት የሚስቡት ሆነ። ሴቶቹን ግን ተዳፍሮ መጐተት፣ አርበኞቹን ማስቀየም ስለመሰለውና አበሻ በሴቱ ቀናተኛ ነው የሚለውን ወሬ ጥንት ሰምቶ ስለነበር እየሠረቀ እየተመለከተ ልቡ መቃጠል ያዘ። በተለይ ሳቆቴ ከሁሉም ጋር መጫወት፣ መቀለድ ስለምትወድ እሱንም አንዳንድ ጊዜ በንግግር ልትቀልደው ባትችልም በመጐነታተል ስለምትቀልደው ወደዳት።

የሳቆቴ ትልቅ ዳሌ፣ ወፍራም ባት፣ ትላልቅ ጡቶች የፍትወት ርሃቡን ለማስታገስ የሚያስፈልገው መሰለው። ከቀን ወደ ቀንም የሚዳራቸው ሴቶች ከማጣቱና መንፈሱም ወደ ራሱ ልብ እየተመለሰ በሄደ ቁጥር እያንዳንዱ የሳቆቴ ነገር ልዩ እየሆነበት ሄደ። የቀሚሱዋ ንቅናቄ፣ የእግር ኮቴዋ ድምጽ፣ የዳሌዋ ንቅናቄ፣ የጡቶቹዋ ወደ ላይና ወደ ታች ማለት፣ የወገቡዋ ስጋ መተጣጠፍ ሁሉ ልቡን ስውር ከሚያደርገው በላይ ልዩ ዓይነት እየሆነበትና የደሙ መሞቅ ዓይኑን እያደበዘዘው የምኞቱ ሁሉ ውበት ሆነች።

[63] በኢትዮጵያ ውስጥ ግዞትና እሥራት በአንድ ክፍል ውስጥ ታጉሮ መታሠር የተጀመረው በዘመናዊ ሥርዓት እንጂ ቀድሞ እስር ቲሊንቲ እንደታሰረው ነበር።

አንድ ቀን አስካለ፣ ሳቆቴና ቲሊንቲ ከቤት ውስጥ ብቻቸውን ነበሩ። ቲሊንቲ ከአዳራሹ ዙሪያውን ከተሠራው መደብ ባሻገራቸው ጋደም ብሎ መሬቱን ይጭራል። አስካለ ከምድጃው ወጥ ትሠራለች። ሳቆቴ ከመደቡ ላይ ቁጭ ብላ ጥጥ መፍተያ እንዝርቱዋን ስታስተካክል ቆየችና ከዚያም ከቀኝ ባትዋ ላይ የነበረውን ቀሚሱዋን ወደ ላይ ሰብስባ ጭኑዋን ገለጠችና የእንዝርቱዋን እጀታ ከጭኑዋ ላይ እያሾረች መፍተል ያዘች። የቲሊንቲ ዓይኑ በጭኖቹዋ ላይ ተተክሎ ፊቱ ሳንባ መሰለ።

"ቲሊንቲ አመማት መሰለኝ። ፊቱን እይው አስካልዬ፣" አለች ሳቆቴ። ፊቱ እንደዚያ ተለዋውጦ አይታው አታውቅም። በድንገት ደግሞ የዚህ ዓይነት ለውጥ ማሳየቱ በጤና አይሆንም። ተከፍቱዋል ብለው እንዳያስቡ ከትንሽ ጊዜ በፊት ደህና ነበር። እነሱም ቢሆኑ የአረጉት ነገር የለም። ጥጥ ሲፈትሉ፣ ወጥ ሲሰሩ ከሱ ጋር አልተነጋገሩም። ሁለቱም ከተለመደ ባሕሪያቸው ውጭ ያደረጉት ነገር የለም።

"አሞታል መሰለኝ፣ አዎን አሞታል፣" አለች አስካለ ቀይ የሆነ ፊቱን እየተመለከተች። ማጅራቱ አብሶ ደም መስሏል። ሳቆቴ ውሀ ስጭው እስቲ እኔ ዳኘውን ልንገረው፣" ብላ አስካለ ወጣች።

ሳቆቴ ለቲሊንቲ በሽክና ወሀ ቀድታ ይዛለት ሄደች። ውሀውን ተቀብሎዋት ወደ አፉ ሳይወስደው በእጁ ይዞት ዓይን ዓይኑዋን መመልከት ያዘ። "ውይ የኔ ዓይን ይንከራተት፣ ምንድነው ቲሊንቲ። እንቁላል?" አለች ሳቆቴ።

ራሱን ነቀነቀ። እንቁላል የሚለውን ቃል ያውቀዋል። እጁዋን ያዘና ደረቱ ላይ አደረገው።

"ልብህን አመመህ? አይዞህ።" አለች ሳቆቴ ለልብ ህመም መድኃኒቱ ምን እንደነበር ለማስታወስ እየሞከረች ፈዛ። ቲሊንቲ ከጣቱ ላይ የነበረውን የወርቅ ቀለበት አውጥቶ የቀለበት ጣቱዋ ስለአነሰበት መሃል ጣቱዋ ላይ ሲያደርገው ሁሉ በሃሳብ ተውጣ አልሰማችውም። ከዚያም እጁዋን ሲስመው ወደሱ ዘወር አለች።ቲሊንቲ ደስ ብሎት ፈገግ ብሏል። "ሻል አለህ?" አለችው ፈገግታውን ተመልክታ። በሁለት እጆቹ ጣቶቹዋን አቅፎ ፊቱን በጉልበትዋ ላይ ደፋ።

"ቲሊንቲ አይዞህ! አመመህ?" አለች ሳቆቴ የምትይዘው የምትለቀው ነገር ጠፍቷት። "ውይ ቲሊንቲ እንደ ህፃን ልጅ ድፍት አለ። አይ ፈረንጅ።" አለች ሳቆቴ ፈረንጅ በሽታና ችግር አይችልም ሲሉ የሰማችው ትዝ ብሏት።

ባትዋን እየሳማት ሲያሻሻት አንድ ነገር ጠርጥራ አንገቱን ቀና አድርጋ ተመለከተችው። የማይገባት ነገር እየተኮለተፈ በትንሽ ጣቱ ላይ የነበረውን ወርቅ አውጥቶ እጁዋን ይዞ ከቀለበት ጣቱዋ ላይ ሊሰካ ሲል ከመሃል ጣቱዋ ላይ ቀለበት አይታ ሁሉም ነገር ገባት። ገፍትራ ጣለችውና የመሃል ጣቱዋ ላይ ያለውን ወርቅ አውጥታ ልትወርውርለት ስትል

ከመቅጽበት ተነስቶ ወገቡዋን አቅፎ ጭንቅላቱን በጡቶቹዋ መሃከል ደፋ። ሳቆቴ እየተሳደበች ጀርባውን የመታችው ሁሉ ምንም አልተሰማውም።

ከዚያም ፀጉሩን ጐትታ ከደረቱዋ ስታስነሳው ቀና ብሎ አፉዋን ሲስማት ዘወር ብላ ተፋችና ቲሊንቲ ማበዱን እርግጠኛ ሆነች። ፍቅር የመሰላትም እንዳይደለ አወቀች። ገፍትራው ከእቅፉ ወጣችና እየሮጠች ከቤት ወጣች።

አስካለ ለዳኘው ስለቲሊንቲ በድንገት መታመም ስትነግረው በጣም አዘነ። ወዲያውም የድንገተኛና የምች መድኃኒት የሚባሉትን የአገር ባሕል መድኃኒቶች ቆፍሮና ቀንጥቦ ከአስካለ ጋር ወደ ቤት ሲመለስ ሳቆቴን ከውጭ አስካለ አይታት "ባሰበት?" ስትል ጠየቀቻት። ሳቆቴ ዝም አለች።

ዳኘው ወደ ቤት እንደገባ ሽክና አምጡ ብሎ የቆረጠና የቆፈረውን መድሃኒት በውሀ በጥብጦ ወደ ቲሊንቲ ቀረበና ጠጣው ሲል በምልክት ተናግሮ ሰጠው።

ቲሊነቲም ለጥፋቱ መርዝ አጠጥተው የሚገድሉት መስሎት እጆቹን እያወዛወዘ ብዙ እየቀባጠረ እራሱን ሲነቀንቅ ዳኘው ባይገባውም የሀበሻ መድኃኒት ይገላል ብሎ ፈርቶ ይሆናል ብሎ ስለጠረጠረ መድኃኒቱን ቀመሰለትና ወደ እሱ ዘረጋው።

ቲሊንቲም የሚገድል ነገር እንዳልሆነ ገብቶት ምክንያታቸው ምን እንደሆነ ባያውቀውም ተቀብሎ ዥው አድርጎ ጠጣውና ቀና ብሎ ዳኘውን ሲመለከት ዳኘው በፈገግታ ሲመለከተው አይቶ እሱም ፈገግ አለ። ዳኘውም "ይሻልሃል አይዞህ፣" ብሎት ከመደቡ ላይ ተቀመጠ። አስካለም ምድጃ አጠገብ ስትቀመጥ ሳቆቴም ከመደቡ ቁጭ ብላ ቀሚሱዋን ሰብሰብ አድረጋ ፈተሉዋን ቀጠለች። ቲሊንቲም ከቆመበት ሳይቀመጥ የሳቆቴን የተገለጠ ባት እየተመለከተ ፊቱ ሳንባ መሰለ። ዳኘው ቲሊንቲን ሲያስታውስ ነበርና የቲሊንቲ ዓይን ከሳቆቴ የተገለጠ ጭን ላይ ተተክሎ ፊቱ ደም ሲመስል ተመልክቶ እየተንደፋደፈ ይስቅ ጀመር።

"ምን ያስቅሃል?" አለች አስካለ። ዳኘው ሳቁን ሳይጨርስ እንደገና ሳቅ ይዞት ጭልጥ አለ።

ዳኘው የሳቀበትን ምክንያት ለመናገር የቻለው ከብዙ ሳቅ በኋላ ነበር። "አመመው የምትሉት ይህንን ነው …… ሃ! ሃ! ሃ! ተክሌ ነግሮኝ ነበር ……ሃሃሃ ፈረንጅ ጡት፣ ባት፣ ዳሌ ሲያይ ልቡ የሠወራል ሃሃሃ …" ዳኘው እንደገና እንደ መጀመሪያው መሳቅ ያዘ።

"የምን ባት የምን ጡት ነው?" አለች አስካለም የሚያስቀው ነገር ባይገባትም እሱዋም በዳኘው ሥራ እየሳቀች።

"የሳቆቴ ባት፣ …." አለ ዳኘው እንባውን እየጠረገ እንደገና ሳቅ እያፈነው። "ስትፈትል …. ዓይኑን አላያችሁትም?" አለ።

“የሳቆቴ ባት ምን አለው?” አለ ተክለወልድ የለገሥ ጋሻጃግሬ የነበረው በኋላም ከዳኘው የተደባለቀው የአስካለ ወታደር።

“እኔም ተክለሃይማኖት ስለ አዲስ አበባ ሲያወራልኝ ፈረንጆች ጡት፣ ባት ካዩ ልክ እንደ አህያ ስሪያ ሴቱዋ እንኳ ብትረግጣቸው አይመለሱም ብሎኝ ነበር። ውሸቱን መስሎኝ ነበር።” አለ ዳኘው እንደገና ሳቁ እየመጣበት።

“ምን አለ?” አለ ተክለወልደ ፊቱ ጠቁሮ። አስካለን “እትዬ ሳቆቴ እንድታገባኝ አማልጅኝ” እያለ ሰሞኑን ሲለምን ነበር። ዛሬ እሱ የሚወዳትን ይህ ጣሊያን እንደሚያስባት ሲያውቅ ንዴቱ ገንፍሎበት ሊገለው ወሰነ።

“ተክለወልድ። አርፈህ ተቀመጥ።” አለች አስካለ ከፊቱ ያነበበችው ነገር ቲሊንቲን ለመግደል እንደቆረጠ ነግሩዋት። አስካለ ሳቆቴን ተክለወልድን አግቢው እያለች ብዙ ጊዜ ጠይቃለች። ሳቆቴ ግን ተክለወልድ አብረው ባይተኙም በቃል ንግግር ስምምነት ከደረሱ በኋላ በሱዋ ላይ ሌላ ሴት መያዙን ካወቀች በኋላ ባታኮርፈውም የራቀችው ሲሆን እንድታገባው የላከባትን አማላጅ ሁሉ አሻፈረኝ ብላለች።

“ተክለወልድ ልጅ አትሁን። ከአገራችን ሰዎች አንዳቸው እንደዚህ ቢሉ ብትቀየም አይከፋም። ግን ይህ ፈረንጅ የፈለገውን ቢል ሳቆቴ እሽ እንደማትለው እያወቅህ ምን አናደደህ። አሁን አንድ ሕፃን ልጅ ሳቆቴ ውሽማዬ ናት ቢል ትናደዳለህ?” አለ ዳኘው።

“እኔ ምኑ ነኝ? ምን ማለቱ ነው።” አለች ሳቆቴ ደሙዋ ፈልቶ። “ባሌ ነው፣ ምኔ ነው? ሂደህ ያችኑ ሚስትህን ተቆጣጠር፣” አለች ሳቆቴ ውሽማውን ሚስት ብላ።

ተክለወልድ ከቤት ወጥቶ ሄደ። ዳኘውም ተክለወልድ ሲወጣ ወደ በራፉ እያመለከተ “ቲሊንቲ ዋ ዱዋ፣” አለ ጥይት እንደመተኮስ እያሳየው። ከዳኘው ፊት ላይ ባነበበው መልዕክትና ዱዋ! ከሚለው ድምጽ ቲሊንቲ ምን ዓይነት አደጋ ውስጥ እንደሆነ ገባው።

“እሺ እሺ፣” አለ ቲሊንቲ። መዳፉን ወደ ውጭ አድርጎ ከፊለፊቱ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ።

አስካለም ለመጀመሪያ ጊዜ ቲሊንቲን በክፉ ዓይን አየችው። እንዲህ ዓይነት ሽረኛ አይመስላትም ነበር። ቲሊንቲም ከዚያ ቀን በኋላ ሴቶችን በእጁ መንካት ቀርቶ በዓይኑ መከተሉም ቀረ።

የዚያን ሰሞን የዳኘው የገብርኤል ድግስ የሚደረግ ስለሆነ ከቤት ብዙ ሥራም ቢኖር እነዳኘው ለዘመቻ ሲነሱ ተክለወልድን ከኔ ጎን እንዳትለይ ብላ አስካለ አብራቸው ወደ ጦር ሜዳው ወረደች። ተክለወልድ በደረሰበት ንዴት የማይሆን ሥራ ሠርቶ እንዳይሞት ስለፈራች ልትለየው አልፈለገችም። ተክለወልድም የአስካለን ጭንቀት በመረዳት ለሱም ስትል በምታደርገው ሥራ ውለታዋ ከብዶት “እትዬ ሙች ትቸዋለሁ። አንቺ ሳቆቴን የምታግባቢልኝ ከሆነ ግዴለም፣” አለ።

አስካለም “እሱን በኔ ጣለው። አንድ ምርኮኛ መግደል ስም ያጠፋል።” አለች።

ለገብርኤል ፀበል ከተደገሰው ውስጥ ተቆንጥሮ ሳቆቴና ተክለወልድ ተጋቡ። ማታውኑ መብራቱ እንደጠፋ ሳቆቴ ልብስዋን እንደለበሰች ከመደቡ ላይ ጋደም አለች። ተክለወልድ ሱሪውን አውልቆ ከጋቢዋ ገልጦ ሲገባ ዝም አለች። አንገቱዋን አቀፈና “ልብስሽን አታወጭውም። ይቆሽሽብሻል፣” አለ።

“ግዴለሽም አውጭው፣” አላት ከአንገትዋ ቀና እያደረጋት። ሳቆቴም በጭለማው ውስጥ ልብሱዋን አውልቃ ጉልበቱዋን አጥፋ ተኛች። ተክለወልድም እንግዲህ ታርቀናል ምንድነው የምትይው ብሎ ጉንዋን ሲኮረኩራት ሳቆቴ ስቃ እግሩዋን ስትዘረጋ አቀፋት።

አርበኞች አንዳንድ ቀን ቲሊንቲ ያደረገው ትዝ ሲላቸው የሚስቁ ቢሆንም ቲሊንቲ ጨዋ እየሆነ ስለሄደ ቂም አልያዙበትም። ቲሊንቲም እራሱን ወቅሶ ጠባዩን አስተካከለ። ሁሉም እንደ ጓደኛ ወሰዱት። ተክለወልድ ሳቆቴን ካገባ በኋላ ይቅርታ አድርጎለት አንዳንድ ቀን ጀርባውን መታ እያደረገ ይስቅለታል። ቲሊንቲም ከአርበኞች ጋር ሆኖ የሙሶሎኒ አገዛዝ ለመዋጋት በምልክት የጠየቀ ቢሆንም አርበኞች ስላላመኑት አልፈቀዱለትም። በተረፈ ግን ተለይተውት በልተው አያውቁም።

⅄ ⅄ ⅄

# የዳኘው ማኅበር

ዳኘው አስካለን የትዳር ጓደኛው ካደረገ በኋላ የሱዋን ሙያ የአካባቢው ሕዝብ ያደነቀው ቢሆንም፣ የሩቅም አርበኞች ጀግናም፣ ባለሙያም እንደሆነች በግብርም በዝናም ቢያውቁም፣ ሰው የሚያውቀው ስላልመሰለው ግብዣ አድርጎ መላ አገሩን ለማስደነቅ ፈልጎ አጋጣሚ ይጠባበቅ ነበር። አንድ መልካም ነገር ሲገኝ ስለዚያ ቢያወሩ አይጠገብም። ሁሉም ቢያደንቀው ደስ ይላል። በተለይ ያን ዓይነት መልካም እድል ለመጀመሪያ ጊዜ ላገኘ ብዙ አድናቂና ተመልካች ያሻዋል። ዳኘው ሲናፍቀው የነበረው ጊዜ ጥቅምት ላይ ደረሰ። ዳኘው ጥንትም የገብርኤልን ጽዋ ስለሚጠጣ ለገብርኤል ድግስ በሰፊው እንዲዘጋጅ ካደረገ በሁዋላ ከየአገሩ ያሉትን አርበኞች ከመንዝም ከተጉለትም ጋበዘ።

ያ ሁሉ አርበኛ በአንድ ቦታ በሚገኝበት ሁኔታ ደግሞ ጣሊያኖች አደጋ መጣላቸው የተለመደ ስለሆነ ዳኘው የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ሁሉ አዘጋጀ።

ጣሊያኖች ባሻገሩ ሳሲት ላይ መሽገዋል። ከዚያ ምሽግ ወጥተው ወደ መንዝ ለመሻገር ሁልጊዜም ይሞክራሉ።

ሳሲት ኮረብታውን ትንሽ ወረድ ብሎ አገሩ ለጥ ያለ ሜዳ ነው። ቢሄዱት የማያልቅ የሚመስል፣ ተለዋዋጭ ነገር የማይታይበት፣ ለተጉዋዥ የሚሰለች አገር ለዓይን ቅርብ፣ ለእግር ሩቅ የሆነ፣ ሰዎችም አንቀላፊኝ ብለው የሰየሙት ነው። በተራራማው አገር እያንዳንዱ እርምጃ አዲስ ትእይንት በሚያቀርብበት ቦታ መጓዝ የለመዱ ከዚህ መረሬ አፈርና ለጥ ያለ ሜዳ ጉዞ እያሰለቸ እንቅልፍ ያመጣባቸዋል።

ከሳሲት ሆኖ በመነጽር ሁለት የዋርካ ዛፎች ጎን ለጎን ቆመው ይታያሉ። ከዚያ መሬቱ በአንድ ነገር እንደተዋጠ ይጠፋና ባሻገሩ እንደሰንሰለት፣ ግዴለሽ እንደወረወረው ድንጋይ በየቦታው ያፈጠጡ ተራራዎች ይታያሉ።

በአንቀላፊኝ ሜዳ ውስጥ አንዲት ትንሽ ጉርባ ብቻ ትታያለች። በሜዳው መሃል ይችን ጉርባ ምን እንዳመጣት የተመራመሩት ያገሬው ሰዎች አፈታሪክ ፈጥረዋል። “ግራኝ ሙሐመድ በአንቀላፊኝ በኩል ሲያልፍ የወታደሩን ስፍር ቁጥር ለማወቅ ፈልጎ ጉዋልም ይሁን ድንጋይ ወታደሮቹ አንዳንድ እንዲይዙ አዘዛቸው። ከዚያም ከዚያች ቦታ ሲደርሱ የያዛችሁትን ከዚህ ወርውሩት አላቸው። የግራኝ ወታደረም እልፍ አእላፍ ስለነበር የያዘው ድንጋይና አፈር ባንድ ላይ ሲከመር ኮረብታ ወጣው። ይችን ጉርባ የአገሬው ሰዎች ግፍጥጫ ይሉዋታል። ቁመትዋ አጭር ስለሆነች ከሩቅ ሆኖ አሻገሩን ለማየት አታስቸግርም።

ከሜዳው መጨረሻ፣ ከሁለት ዋርካዎች ሥር፣ ከአዳባይ መልካ ተነስቶ

እንደ ደረጃ እየሆነ ወደ ላይ ከሚወጣው ተራራ ጫፍ ግርጌ፣ ንብዋሻ፣ ከአስካለ የትውልድ መንደር፣ ዳኘው ቋሚ ቃፊሮች አሉት። ከንብዋሻ ለጥቂት ደቂቃ በሰው ሠራሽ ደረጃ ጥርቡን ገደል እየወጡ እየወረዱ ባለማቋረጥ ከመስኩ ጫፍ ይሆኑና አንቀላፊኝ ሜዳውን ያማትሩታል። በመነጽር ሳሲትን ይቃኙታል።

ዛሬ ግን ጉዳዩ አሳሳቢ ስለሆነ በታላቅ ጥንቃቄና ምሰጢር የጣሊያን ምሽግ ካለበት ሳሲት ወሰን ላይ ሁለት ቃፊሮች፣ ከዚያም ከንብዋሻ አፋፍ ላይ ሁለት ቃፊሮች፣ ከዚያም ዝቅ ብሎ ሌላ ቃፊር መደበ። የመጀመሪያው ቃፊር የወታደር እንቅስቃሴ ሲያይ በፍጥነት ሄዶ ለሁለተኛው ቡድን ያስታውቃል። ሁለተኛው በተኩስ ድምጽ በጥንቃቄ ለሚጠባበቀው ለሦስተኛው ቡድን ያስተላልፍና ወደ ቆላው ይወርዳል። ሦስተኛውም በተኩስ ድምጽ መልዕክቱን ለእነዳኘው ያደርስና ወደ ቆላው ይወርዳል። አገሩን ለማያውቀው ሰው ከየት ቦታ የተተኮሰ የት እንደሚደርስ ለማወቅ ቢቸግርም እነ ዳኘው በረጅም ጊዜ ልምድ ያውቁታል። በድምጽ ከመጠራራት ይልቅ በጠበንጃ ተኩስ ሩቅ ከሩቅ ሆኖ ለመደማመጥ ያስችላል።

በጦርነት ጊዜ በአፍ ትእዛዝ ከመስጠት በመትረየስ ተኩስ መነጋገርንም አርበኞች ተምረው ነበር። ሂድ፣ ግፋ፣ በቀኝ በኩል፣ በግራ በኩል፣ ሰው ወደቀ፣ አፈግፍጉ፣ ወዘተ ለሚሉ ቃላት የመትረየስ ተኩስ ድምጾች ተመድበውላቸው ነበር። የመትረየሱን ቃታ በማዘዝ የተተኮሰውንም ጥይት በጠላት ላይ አነጣጥሮ በአንድ ጊዜ ሁለት ሥራ መሥራት የተለመደ ነበር። ከያለበት የተጠራቀሙት እነዚህ ባላገሮች የፈጠራ ችሎታቸው ጣሊያንንም ያስደንቀዋል።

ዳኘው በቃሬሮቹ በመተማመን፣ እንግዶቹም ዳኘው ጥንቃቄ እንደሚያደርግ በማመን፣ ተዝናንተው መደሰት ቀጠሉ። ሁሉም ሲደሰት አመሸ። ከቃሬሮቹ በቀር ያልፈነጠዘ አልነበረም።

ፀሐይ ስትጠልቅ የሳሲት ብርድ የመጀመሪያዎቹን ቃሬሮች ቆፈን አኮማተራቸው። እስካሁን ድረስ የወታደር ንቅናቄ አልተመለከቱም። የጣሊያን ካምፕ ምንም አዲስ ነገር አይታይበትም። እነሱም ከድንጋይ ሥር በልባቸው ተኝተው መመልከት አላቋዋረጡም። ሥራቸው ክቡር ቢሆንም ፍሬ በማጣቱ ቅር ብሎአቸው ሳለ አንድ የመንደሩ ሰው ወደ እነሱ ሲመጣ ተመለከቱና ጠንቀቅ አሉ። እነሱ እዚያ እንዳሉ የሚያውቅ ማነው?

"እንደምን አመሻችሁ?" አለ አዲሱ መጭ። ከአርበኞች ጋር ተባባሪ ስለመሆኑ የሚያውቁት ሰው ነው። ሰላምታ ከተለዋወጡና ብዙ ከተጫወቱ በኋላ ስለ ሳሲት አጫወታቸው። በመጨረሻም "እባካችሁ ከኔ ቤት እንሂድና ጠላ አለና ጠጡ። ይህን ብርድ አትችሉትም። ደግሞም በምሽቱ ውስጥ ምንም እንቅስቃሴ የለም።" ሲል በአሳማኝ ሁኔታ አስረዳቸው።

ሳያመነቱ እሺ አሉት። ተግባር ግዴታ እየሆነ እንጂ አንዳንድ ነገር በአዘቦቱ ቀን ከዚያ ለመገላገል የአጭር ጊዜ ጥቅም የሚመረጥበት ነው። ራብን ቆንጠጥ አድርጎ የሚያስችለው የነፃነት ተጋድሎ እንጅ አንዳንድ ጊዜ አሸከርም ሆኖ ፍርፋሪን መብላት ያስመርጣል። ዔሳው [64] ብክሩናውን ለወንድሙ ለምስር ወጥ የሸጠው ወዶ አይደለም። እነዚህ ቃሬሮች ግን አደጋ በሌለበት ሁኔታ ከግዳጃቸው ፈቀቅ ቢሉ ነውሩ አልታያቸውም። ስለዚህ ጆሮአቸውን ወደ ከተማው አቅነተው ከአስተናጋጃቸው ቤት ቁጭ ብለው ጠላውን፣ አረቄውን ተጋተሩት። ሌሊቱም ከነጋ በኋላ ቃሬሮቹ የወታደር ንቅናቄ ከውጭ ወጥተው ቢያዩ ሳላላዩ ደስ አላቸው። "እኛም ግብዣ አላጣን፣" ሲሉ ተሳለቁ።

ሊነጋጋ ሲል ግን ዳኘው ግብዣ ከሚያደርግበት ከቃያ ገብርኤል አፋፍ ላይ ስፍር ቁጥር የሌለው የጣሊያን ሠራዊት ሠፍሮ ታየ። ከፈለው ወልደ ፃዲቅ ብልጭ ብሎበት ወደ ዳኘው ዞር ብሎ "ቃሬር እንኳን ሳታደርግ ከዚህ ያስቀመጥከን ስንሰክር ለማስያዝ ኑሮዋል?" አለ። የተጋባዡን አርበኛ የልብ ትርታ ነው የተናገረው።

ዳኘው ቃሬሮች ሦስት ቦታ በምን ዓይነት ሁኔታ እንዳስቀመጠ ሲናገርና ወታደሮቹም ሲያስተማምኑ የተጋባዡ አርበኛ ልብ ቢለሳለስም አላመኑትም። ዳኘው ግን "እኔው ያመጣሁትን እኔው እመልሰዋለሁ።" ብሎ ሲነሳ መጨረሻውን ለማየት ተወት አድርገውት ከአዳባይ መልካ ወጥተው ወደ ሞፈር ውሀ መልካ ገቡ። ዳኘው የሱን ክፍል ጦር ይዞ ዳገቱን ወደ ላይ፣ ወደ ጣሊያን ሠፈር ወጣ።

---

[64] ቀድሞ በስሕተት ያዕቆብ የተባለው ታርሞ ነው።

የጣሊያን ጦር የተመለከተው ወደ ሞፈር ውሀ ጅረት መልካ የገባውን አርበኛ እንጂ ዳኘውን ስላልሆነ ወደዚያ ለመድረስ በሩቅ እየደበደበ ወረደ። ዳኘውም የጣሊያን ጦር በአንዲቱዋና በብቸኛዋ በር ወደ ቆላው በመውረድ ላይ መሆኑን ከተኩስ አወቀ።

ዳኘው ከነጦሩ ከበሩዋ በታች ሲደርስ ቦታ ቦታ እንዲይዙ አዘዘና እሱ ከአንድ ገሎ ስር መትረየሱን ጠምዶ አደፈጠ። ከገሎው አናት የበቀለው ሳር በጥቅምት ፀሐይ ቢጫ ሆኖ አጎንብሱዋል። ዛፎች አፍርተው በወርዳቸው ሰፍተው ቅጠላቸው ችምችም ብሏል። ባሻገሩ አንዲት እርሾ የምትመስል ትንሽ ጅረት ትወርዳለች። ለቅጽበት ያህል ሁሉንም ቃኛቸው። ከፊለፊቱ ያለውን ሳር ገለጥ አድርጎ ድንጋዩን በእጆቹ ይዞ ተመለከተ። ከጣሊያን ጦር ጋር ተያየ።

የዳኘው ጦር በሩ ላይ የሚደርሰውን ጠላት ሲያጭደው እየተምዘገዘገ ገደል ይወርዳል። ከኋላ ያለው ይተካና እንዲሁ ታጭዶ ይወርዳል።

ሞፈር ውሀ ጅረት ገብቶ የመድፍ ተኩስ የሚወርድበት አርበኛም በመነጽር ከዳኘው ጋር የሚደረገውን ጦርነት ተመልክቶ ተደነቀ። ዳኘውን በመጠርጠራቸው አዘኑ። አሁን ጦርነቱ በዳኘው ላይ አተኮረ። ዳኘው ግን አመች ቦታ ስለያዘ መርዳቱ አስፈላጊ እንዳልሆነ አውቀው ከሞፈር ውሀ ጅረት ወደ ዳኘው ግብዣ ቦታ ተመለሱ።

ጀምበር ልትጠልቅ ስትል ሽፈራው እርገጤ[65] ዳኘውን እተካዋለሁ ሲል ከግብዣው ቦታ ወታደሮቹን ይዞ ተነሳ። ሽፈራው ጀግንነቱ የታወቀ ከልጅ ግዛቸው ኃይሌ ጋር ሰሜን [66] ዘምቶ በኋላም በአርበኝነት ሙያውን ያስመሰከረ ነው። ሽፈራው ሌሊቱን ሲዋጋ ሲያድር ዳኘው ከግብዣው ቦታ ተመልሶ ይቅርታ ተጠይቆ ሊነጋጋ ሲል ለተዋጊው ምግብ ይዞ ጦርነቱ ቦታ ተመለሰ።

ቦጋለ አቦዬ የሚባለው አንድ አርበኛ ከዳኘውና ከሽፈራው ጎን በጣም እየጮኸ "እነ ወልዴ ፈለቀ! እንደተነጋገርነው እንጠብቃችኋለን። በቶሎ ፈጽማችሁ እንድትመጡ!" እያለ ደጋግሞ ይጣራ ጀመር።

"ምን ማለትህ ነው። አብደሃል?" አለ ሽፈራው እርገጤ ከጠላት ሰፈር አርበኞችን እነ ወልዴ ፈለቀን በመጥራቱ ተገርሞ። ቦጋለ አቦዬም ምክንያቱን ሲነግረው ሽፈራው በጣም ሳቀ።

[65] ፊታውራሪ ሽፈራው እርገጤ በኋላ ደጃዝማች። ፋሽስቶች ከነፃነት በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩትን በመመልከት ጦርነቱ አላበቃም በማለት ትጥቃቸውን ሳይፈቱ ኖረው አረፉ።

[66] በትክክለኛው አባባል የታሪክ እውነታን እንዲያንጸባርቅ ከማይጨው የተለወጠ።

ብዙም ሳይቆይ በጠላት ሠፈር ከፍተኛ ተኩስ ተሰማ። አርበኞች ድምጻቸውን አጥፍተው ዝም አሉ። ጠላት እርስ በርሱ ይታኮስ ጀመር እንዴ? ሲሉ አሰቡ። ብዙም ሳይቆይ ደግሞ የጠላት ጦር ፊቱን አዙሮ ወደ ሳሲት አመራ።

አርበኞቹ የሆነውን ሁሉ አይተው የተገረሙት የጣሊያን ጦር ወደ ሳሲት ማምራቱን ከአረጋገጡ በኋላ ከአፋፉ ሲወጡ ነበር። እነ ፈለቀ ወልዴ በጣሊያን ጥይት ተደብድበው ተረፍርፈዋል። ያ ሁሉ ተኩስ ለካስ ለዚህ ኑሮዋል! ።

እነ ወልዴ ፈለቀ ከልባቸው ከድተው ለጣሊያን ካደሩ በኋላ የትላንት ጓደኞቻቸውን አርበኞችን በጣሊያኖች ለማስያዝ የዳኘውን ማኅበር ድግስ ይጠቀሙበታል። ዳኘው የመደባቸውን ቃፊሮች አርበኞች በመሆናቸው ስለሚያቁ ሳሲት ካሉ ሰዎች ጋር ተስማምተው የመጀመሪያዎቹን ቃፊሮች ከሥራቸው ካዘናጉ በኋላ እነሱ ከጣሊያን ጋር ተሰልፈው ይመጣሉ። ሁለተኛውና ሦስተኛው የቃፊሮች ቡድን ጠላት በድንገት እየደረሰበት ተግባሩን ባለማከናወኑ አርበኞች ካሉበት በድንገት ለመድረስ ይችላሉ። ጣሊያኑም አዛዥ ይደሰታል። ነገር ግን ሳይታሰብ የዳኘው ጦር ከዋናው ጦር ተገንጥሎ ያልታሰበ ጥቃት ሲያደርስ ጣሊያኑ አዛዥ እነ ወልዴ ፈለቀ ተማከረው ያስጠቁት መስሎት ጥርጣሬ ይገባበታል። በመጨረሻም ቦጋለ "እንደተማከርነው አድርጋችሁ ኑ!" እያለ እነ ወልዴ ፈለቀን ሲጣራ ጥርጣሬው እውነት ይመስለውና ወልዴ ፈለቀንና ጓደኞቹን አሰልፎ ይረሽናቸዋል።

የዚያን ሰሞን ዳኘው ቦጋለን ባየው ቁጥር ሳቁ ይመጣበት የነበረው ለዚህ ነበር። ታስቦ የተደረገ የጦርነት ሥልት በውጤቱ አያስደንቀም። አጋጣሚ ስልቱን የቀየሰችለት ጦርነት ትዝታ ግን የወታደራዊ ጠበብትን በማሳፈሩ ብቻ ሳይሆን በየአቅጣጫው ብዙ የፈጠራ ታሪኮችን ስለሚፈጥር ትዝታው ረጅምና የሚያስቅ ነው።

የጣሊያን ጦር ወደ ሳሲት በሚያመራበት ጊዜ አርበኞች እየተከታተሉ አደጋ ጣሉበት። ጣሊያንም ይህን ብድር ለመመለስ ቆረጠ። ዳኘው ግን የሳሲትን ምሽግ ለማስለቀቅ እንደ አሁኑ ጊዜ የተመቸ ጊዜ እንደማይኖር አመነ። ይህንን ሃሳቡን ለማሙዋላት ለኢጣሊያ ያደሩ ብዙ ባንዳዎችን ለማስከዳት እንደሚችል ተረዳው።

ዳኘው ይህን እቅዱን ከሥራ ላይ ለማዋል በቤቱ በኩል ምንም ችግር እንደማይገጥመው ያውቃል። ከዚህ ቀደም ከጠላት ከድተው የመጡት ወታደሮችና አለቆች ቅሬታ እንዳይሰማቸው አስካለ የምትጨነቅ ናት። እነሱን የሚነኩ ያልታሰቡ ጨዋታዎችን እንኳ ሳይታሰብ አቅጣጫቸውን ቀይራ ሁሉም በወንድማማችነት እንዲጫወቱ ታደርጋለች። በጦርነት ወቅት ግንባር ለግንባር ጠላት ጋር ተፋጥጦ አንዱ አንዱን ስለማይተርብ ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ ባያስፈልግም፣ በጨዋታ ላይ ግን ይህ እንዳይፈጠር ባላት ቁጥጥር የትኛውም ጨዋታና ቀልድ፣ ቅናትና አሽሙር በዚህ አቅጣጫ እንዳይሆን ታደርጋለች።

በአስካለ ዙሪያ “ምልስ አፈሮች” የሚለው ቃል ተነስቶ አያውቅም። የሚኩራሩ አርበኞች ከጠላት ከድተው የሚመጡትን “ምልስ አፈሮች” ይሉዋቸዋል። በዚህ ቃል የተነሳ በሌላ ቦታዎች ብዙ ሰዎች ተመልሰው ለጣሊያን አድረዋል።

አቶ ደቦጭና 35 ወታደሮቹ የዳኘውና የአስካለ መልዕክት ሲደርሳቸው በደስታ የተቀበሉት ለዚህ ነበር። ዳኘውም እነዚህን ሰዎች ካስከዳ በኋላ የሳሲትን ምሽግ አስጨንቆ ወግቶ አስለቀቀ። ዳኘው ተጉለት ዘለቀ።

የዚያን ዕለት ዳኘው ሳሲት ላይ ቆሞ ፀሐይ ከአድማሱ ስታቆለቁል ከሕፃንነቱ ጀምሮ እንደሚያደርገው አትኩሮ እየተመለከታት ልቡ ተሰለበ። በአለፉት ዓመታት የዋለባቸውን የጦር ሜዳዎች ቆጠራቸው። የዓለም ፓለቲካ ይዘት ትልቅ ለውጥ እያመጣ ነው። እንግሊዝ በኢጣሊያ ላይ ጦርነት ልታውጅ ነው። ጣሊያኖችም ከእንግሊዝ ጋር ለሚያደርጉት ግጥሚያ ለመዘጋጀት በቅድሚያ አርበኞችን ለመደምሰስ ያደረጉት ሙከራ በኩረ ማርያም ላይ ከሽፉዋል።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ክፍል አራት

## ውሃ ዋናም ቸር ወሬ ያሰማል

ጃንሆይ፣ ከእንግሊዝ አገር መኖሪያቸው የውሀ ዋና ባሕር፣ ቀስ እያሉ ገብተው አንድ ጊዜ በወርዱ አቋረጡትና ተመልሰው በመሰላሉ ላይ ወደ ላይ ወጣ አሉና የመሰላሉን መደገፊያዎች ይዘው ተከዙ። መንግሥቴ ይመለስልኝ ብለው ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይ ካጣ በኋላ የዓለምም ፖለቲካ እንደ አገር ቤቱ ፖለቲካ የእሰጥ አገባ የእከከኝ ልከክህ ጨዋታ እንደሆነ ገብቷቸዋል።

በስደት ላይ ያሉት ቤተሰቦቻቸውና ሹማምንትም ሕይወት እንደ ኢትዮጵያ ባለመሆኑ ኑሮአቸው ደስተኛ አይደለም። ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ ከመሆንም በላይ ብዙ መቶ አሽከር አጀብ አጀብ የሚያደርግበት የሚያቅፍ የሚደግፍ ሰው የበዛባትን ኢትዮጵያን የሚመስል የለም። አግኝቶ ያጣ ደግሞ ድህነትን በቀላሉ አይለምድም።

የስደተኛ ኑሮ መራራ ነው። ሰው ከአገሩ ተሰዶ ነፍሱን ያድን እንደሁ እንጂ ደስተኛ አይሆንም። ዛሬ ግን ንጉሡን ይበልጥ ያስተከዛቸው የሌሊቱ ሕልማቸው ነው። አሁንም ሆዳቸውን ባር ባር እያለው ነው።

ትላንት ማታ የእንግሊዝ መንግሥት በጣሊያን ላይ ጦርነት ማወጁን ሰምተው እንደተኙ በሕልማቸው አገራቸው ገብተው እንደ ዱሮው ለማስተዳደር ሲሞክሩ ወዲያው ሕልሙ በዚህ ይቋረጥና አንድ ሌላ በውል የማያውቁትን ሰው ሌሎች መሳፍንቶች ከበውት ከዙፋኑ ተቀምጦ አይተው ለመሸሽ ሲሞክሩ አዲሱ ሰው እሳት ይተፋባቸውና እጆቹ እየረዘሙ ሄደው ይቀድሙአቸዋል። …. ስንትና ስንት ሲያቀባዥራቸው አድሩዋል።

በተቻለ መጠን ግን የእንግሊዝ ሹማምንትን ለማግባባት እስከ ዛሬ ያላደረጉት የለም። በእንግሊዝ አገርም ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ የሆኑ፣ ለፀረ ቅኝ ግዛት ትግል ኃይላቸውን ለማስተባበር ወደ ሁዋላ የማይሉ፣ እነ ሲልቪያ ፓንክረስትን የመሰሉ ጎበዝ ሶሻሊስት አጋሮች አሉዋቸው። ቢሆንም ግን ጣሊያንም እንግሊዝም ከሳቸው የተሻለ ሰው ፈልገው ሊያገኙ ይችላሉ።

ሃሳባቸ የሚከፈልላቸው ከውሀው ውስጥ ሲሆኑ መሆኑን አምነው እንደገና ባሕሩን ለማቋረጥ ራሳቸውን ወርውረው ጠልቀው ዋኙና ብቅ ሲሉ ስማቸው የተጠራውስጥ የሚያውቁትመሰላቸውና ጉዳይመለስ አሉ።አስፈጻሚ በእንግሊዝ በእርግጥም የውጭ ከባሕሩ ጉዳይ ዳርሚኒስቴር ቆሞ ይጠቅሳቸዋል። ወዲያውኑ ወደ ባሕሩ ዳር ተመልሰው ሰላምታ እየሰጡት መሰላሉን ይዘው ብቅ አሉ። የሚነግራቸው ጉዳይ ከባድ እንደሚሆን ጠርጥረው ልባቸው ይንደፋደፋል። “ወደ ኢትዮጵያ ጦር ልናዘምት እንፈልጋለን። አብረውን ለመሄድ ይፈልጋሉ?” ሲል ጠየቀ።

አጠያየቁ ብዙም ተስፋ የማይሰጥ፣ ስለወደፊቱ የኢትዮጵያ እድል የማያብራራ ቢሆንም፣ "በእርግጥ እንጂ ምን ያጠረጠራል፣" አሉና ጃንሆይ ከውሀው ውስጥ ወጥተው ልብሳቸውን ሲለብሱ ሰውነታቸው ይንቀጠቀጣል። የጠበቁት ወሬ ሲደርስ ደስታው ልብ ያሸብራል።

በዚያው ሰሞን በስደት ላይ ይገኙ ለነበሩት ሹማምንት ደብዳቤዎችን ጽፈው፣ ወደ ሱዳን ለመሄድ ተዘጋጁ። ከዚያም ዝርዝር ዝግጅቱን ሲያውቁት የእንግሊዙ ተወካይ ከሳቸው በላይ ሥልጣን እንዳለው አወቁ። የእንግሊዝ ዋናው ጦር በሶማሌ በኩል ገብቶ አዲስ አበባን ሲይዝ በሱዳን በኩል ንጉሡን አርበኞች ተቀብለው፣ በእንግሊዝ ወኪል ትዕዛዝ የሚነቃነቁ ማድረግ ነው። ሆኖም መቀበሉ ይጠቅማል ብለው ተስማምተውበት ሱዳን ገቡ።

ከሱዳን ወሰን አልፈው ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት መልዕክቱ የደረሰውና ስለሁኔታው ገለጻ የተደረገለት የጎጃም አርበኛ ተቀበላቸው። እንግሊዞች የአርበኞችን ኃይል ይህን ያህል ስላልገመቱት አዲሱ ሁኔታ እቅዳቸውን ሊያከሽፍ የሚችል መሆኑን የተጠራጠሩት ከዚህ ጊዜ በኋላ ነበር።

የንጉሡን መምጣት የመንዝ አርበኞች የሰሙት ከዚህ በኋላ ወር ቆይቶ ነበር። በመጀመሪያ ጊዜ ያው እንደተለመደው የባላገርን ልብ ለማጽናኛ መስሎ ነበር። በተለይ መልአከ ፀሐይ እያሱ ከሞቱ በኋላ ይህን ወሬ ማናፈስ ተለምዶ ነበር። እያደር ግን እውን መሆኑ ታወቀ። ደጃዝማች ከበደ ወደ መሃል አገር እየገቡ፣ ደብዳቤም እየጻፉ ያስታውቁት ሁሉ አመነ።

የጃንሆይ መምጣት በአርበኞች መሪዎች ዘንድ የተለያየ ሁኔታ ፈጠረ። ጃንሆይን በኃይል የሚወዱት እነ ሻለቃ መስፍን ስለሺ[67] የመመለሳቸውን ወሬ ሲሰሙ ጎጃም እስከነወታደሮቻቸው ተሻግረው ተቀበሉአቸው። ራስ አበበም የጦር ሰው ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ሰውም ስለሆኑ፣ ኃይላቸውን ማጠናከር ለሁሉም እንደሚበጅ አምነው፣ ጣሊያኖች በሽሽት በለቀቁዋቸውና የራስ አበበ ጦር ባስለቀቃቸው የሸዋ አውራጃዎችና ወረዳዎች የራሳቸውን ሹማምንት ሾመው አዲስ አበባ የገባውን የእንግሊዝ ጦር ዙሪያውን አጥረው፣ እሳቸው ፍቼ ድረስ በመሄድ ንጉሡን ተቀበሉ። እንግሊዞች በራስ አበበ ኃይል ተደናግጠው የነበሩ ቢሆንም ንጉሡን በመቀበላቸው ደስ ሲላቸው ሁኔታዎች ግን ያልታሰበ አቅጣጫ እየያዙ መሆናቸውን በደንብ ተረዱት።

ከሁሉም ቦት ወሬው ዘግይቶ የደረሰው ከከፈለው ወልደ ፃዲቅ ሰፈር ነበር። ለአስካለ መጀመሪያ ወሬውን የነገረቻት ሳቆቴ ስትሆን ሁለተኛው ዳኘው ነበር። "እናቴ ጃንሆይ መጡ አሉ።" አለ ዳኘው።

---

[67] በኋላ ራስ መስፍን ስለሺ የታወቁ አርበኛ ነበሩ።

“ዛሬ አገር ተቀብሎዋችኋል። አላስቸገራችሁ። ይህ ዓይነት ወሬ ምን ያደርግላችኋል። መዋሸት እኮ ሲገደዱ ነው እንጂ ሥራ ሲፈቱ አይደልም።” አለች አስካለ ተቆጥታ። ዳኘው ሳይነግራት በፊት ሳቆቴ “አስካልዬ ጃንሆይ መጡ እየተባለ ይወራል። ሰው ሁሉ ያወራዋል። ለምን ይሆን? ምን ታስቦ ነው?” ብላ ጠይቃት ነበር።

“ስቀልደ አይደለም። እውነት ነው።” አለና እንደመከፋት አለ። ሁልጊዜም የምሩን ተናግሮ ቀልድ ሲያስመስሉበት ይከፋዋል።

“እንዳፍህ ያድርገው።” አለች አስካለ አዲሱ ሁኔታ ሊፈጥር የሚችለውን ነገር በቅድሚያ ለማወቅ አእምሮዋን እየጨመቀች።

“እነሻለቃ መስፍን ጃንሆይን ሊቀበሉ ሄደዋል አሉ። እኔም ብሄድ ደስ ይለኝ ነበር።”

“ልጅ ከፈለውም ያስባሉ?”

“ማሰብማ መች ይቀራል። ማን አሳልፎ እንጂ። ንጉሡ ከመጡ ደግሞ በጉልበት ተዋግቶ ጥሶ ማለፍ አይገባም። ሕገ ወጥ መሆን ነው።” አለ ዳኘው ንጉሡ ከመጡ ከዙፋናቸው ለመቀመጥ የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለ አምኖ።

“ምኑ ነው የሚጣሰው?” አለች አስካለ ንግግሩ አልገባ ብሎአት።

“ራስ እኛ በያዝነው ክልል ዙሪያ በሙሉ ያለውን አገር ለራሳቸው ሰዎች ሾመው፣ በወታደር ኃይል አጠናክረው፣ ከፈለውንና ወታደሮቹን አታሳልፉ የሚል ትዕዛዝ ሰጥተዋል። ” አለ ተክዞ። ነፃነት ከተመለሰ በሁዋላ ረጅም ዕረፍት ለማድረግ ያቀደው እቅድ ካሁኑ እየተበላሸ መሆኑ ታየው።

በራስ አበበ ሥራ አስካለም ተከዘች። ወዲያው ግን ሌላ ነገር ትዝ አላት። “ዳኘው” አለችው። “ንጉሡ የነጠካቸውን መሬት እንድትመልስ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ይቀጡሃል!”

“ምን መሬት ነጠኩዋቸው እማማ?” አለ የምትቀልድ መስሎት።

“ባሮ ሁዳድ፣ አስኳል፣ ጆር ቤተ ርስት እንደነበሩ አትርሳ።”

“ጣሊያን ከሚወስደው እኔ ወሰድኩት፣ ቢፈልጉ መልሰው ውሰዱት። እላቸዋለሁ።” ብሎ ባፉ ቢናገርም በሆዱ ግን ደነገጠ። ይህ ይኖራል ብሎ እስካሁን አላሰበም ነበር።

“ለመሆኑ፣” አለች አስካለ በትካዜ፣ “አገሩን በሙሉ እናንተ ተሿሹማችሁበታል። ንጉሡ አብረዋቸው ለሚመጡትስ ምን ይሰጣሉ?” አለች እስከዛሬ ሴት ተሹዋሚ ስለሌለ እናንተ ብላ።

በተለይ ለዳኘው የተናገረችው አልነበረም። ዳኘውም አልመሰለም።

⅄⅄⅄

# ደህና ሰንብች ዳኘው

ሰኔ 13 ቀን 1933 ለዳኘው የማይረሳ ትዝታ አለው። ሞገስ ያገኘበት ቀን ስለሆነ አይደለም። ችግር ስለገጠመውም አይደለም። አንዳንድ ቀን የማይረሳ ትዝታ ጥሎ የሚያልፈው በውንም በሕልምም ያልጠበቁትን ነገር በማሰማቱ ነው።

ንጉሡ ደብረብርሃን ላይ መጥተው አርበኞችን ይቀበላሉ ተብሎ ሲወራ የነበረው በሰኔ 12 እና 13 እውን ሆኖ ደብረብርሃን በአርበኞች ተጥለቀለቀች። ንጉሡ የእንግሊዝ መንግሥት ተወካይን ይዘው ቀደም ሲል አዲስ አበባ ሄደው በነበሩት አርበኞች ታጅበው በስደተኞች ታቅፈው ደብረብርሃን ደረሱ። ባሕል ነውና ደንብ ነውና ነፃነት መመለሱ ነውና ሴቱ በእልልታ፣ አርበኛው በፉከራ፣ ተቀብሎአቸው ቤተ መንግሥቱ ገብተው ትላንት የኢጣሊያ አስተዳዳሪ ይገዛበት ከነበረው ሡገነት ላይ ቆሙ። ከንጉሡ በስተግራ በኩል ራስ አበበ በስተቀኝ የእንግሊዝ መንግሥት ተወካይ ቆመዋል። እነሻለቃ መስፍን ስለሺ ዙሪያውን አጀብ አጀብ ያደርጋሉ። ትላንት ከሌላው አርበኛ ጋር አብረው የነበሩ ሳይሆን እነሱም እንግዳ ይመስላሉ። ወይ ሁለት ወር።

ከፈለው ወልደፃዲቅ ወታደሮቹን ይዞ በሌሊት አቋራርጦ ደብረ ብርሃን ስለገባ ከሰልፉ ተካፋይ ሆኑዋል። ራስ አበበ ከዚያው ሊያቆዩት የነበረውን ሙከራ በእልህ፣ በጉልበት ሳይሆን ዳኘው ባፈለቀው መንገድ በብልሃት ሰብሮታል። ከፈለው ጠበንጃውን ይዞ እየተንጓማለለ ሲፎክር "ጠበንጃህን ስጥተህ አንተ ና!" የሚል መልዕክት ከንጉሡ መጣበት። ጠበንጃውን ከእጁ ማውጣቱ ደስ ሳይለው ለተከታዩ ሰጥቶ ከንጉሡ ፊት ቀረበና ስለ ሕይወት ታሪኩ ተጠየቀ።

"ከአገር ቤት ተማሪ ቤት ግቡ እየተባለ ሲጠራ ሰምቼ እስከ አራተኛ ክፍል በዳግማዊ ሚኒሊክ ትምህርት ቤት ከተማርኩ በኋላ አባቴ ሙግት ስለተነሳባቸው ትምህርቱን አቋዋርጬ አገሬ ገባሁ።"

"እና ምን አድርገንልህ እናውቃለን?" አሉ ንጉሡ።

"ተማሪ ሳለሁ አንድ መጽሐፍ ከእጅዎ ተሸልሜአለሁ።"

"ሹመት ነበረህ?"

"የለኝም ነበር ጃንሆይ!"

"መሬት ሰጥተንህ ነበር?"

"የለም ጃንሆይ።"

"ጋሻ መሬት ነበረህ?" "የለኝም።"

ከስደት መልስ አዲስ አበባ ሲገቡ የሰማይ መላዕክት የምድር ሠራዊት ሊያስቡትና ሊገምቱት በማይችሉት በዚች ቀን ….” ብለው ንግግር ያደረጉት ንጉሥ “ታዲያ ምን አድርገንልህ ነው እንዲህ በጀግንነት የተዋጋህልን?” ሲሉ ጠየቁት።

ከፈለው ያሰበው፣ ያለመው ጥያቄ አልነበረም። በአርበኝነት ሕይወቱ ውስጥ ደጋግሞ የሰማው “የደማችንን ዋጋ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማየት ያብቃን።” የሚለውን እንጂ ጃንሆይ መጡ የሚባለው የወላዋይን ልብ ለማረጋጋት እንጂ በእርግጥ ተመልሰው ይመጣሉ ብሎ ያሰበ የለም። ንጉሡ በስደት ለአርበኞች ደብዳቤ ቢጽፉም የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ከጥንካሬ የመነጨ አልነበረም። ባላምባራስ አበበ ራስ ሲባሉ እሳቸውም ራስ ብለው ጽፈዋል። በዓለም መንግሥታት ዘንድ የአርበኞቹን ተጋድሎ ለማስተዋወቅ እንዲቻል ስለ አርበኝነቱ ተጋድሎ ደብዳቤ አንዳንድ ጊዜ ቢጻፍላቸውም ተመልሰው የመምጣታቸው ጉዳይ ግን እየተረሳ ሄዶ ነበር። ከፈለው አሁን ከንጉሡ ፊት ቆሞ ሲያስበው ከንጉሡ ጎን ከቆሙት ከራስ አበበ ጋር ባለው መቃቃር የተነሳ “ጃንሆይ ውሸት ነው እኔ ለኢትዮጵያ ነፃነት ነው የተዋጋሁት።” ሊል አይችልም። ዝም አለ።

ዳኘው ቲሊንቲን ይዞ መትረየሶች እየጠበቀ ራቅ ብሎ ቆሙዋል። ከፈለውና ንጉሡ የሚነጋገሩት ትንሽ ትንሽ ይሰማዋል። ከፈለውም ትንሽ ዝም ብሎ ቆየና የሚለው ነገር ሲጠፋው “ከኔ ይልቅ ለዚህ የተዋጋው ዳኘው ነው።” አለ። ዳኘው ጥንት ክብር ዘበኛ ስለነበር ዳኘው ለንጉሡ ጥያቄ መልስ አያጣም ብሎ የተናገረው ነበር። ከፈለው በየትኛውም አቅጣጫ ለእገሌ አሽከር ሆኘ ተዋጋሁን አይቀበልም።

ራስ አበበ ከፈለውን የማቃለያ ዘዴ ከራሱ ከከፈለው ትህትና በማግኘታቸው ደስ አላቸው። ራስ አበበ ከፈለው ጀግና እንደሆነ ያውቃሉ። በጀግንነት በኩል የሚያደንቁት ሰው ቢኖር ከፈለው ቅድሚያ አለው። ወቅቱ ግን እጅግ አሳሳቢና የአርበኝነቱ ተጋድሎ ከጠየቀው እኩል የአርበኞችን አንድነት ይጠይቃል። ንጉሡን ያመጡዋቸው እንግሊዞች በጣሊያኖች እግር ተተክተው ኢትዮጵያን ጥገኛቸው ለማድረግ ፍላጎት አላቸው። ሰሞኑን በተመለከቱት ሁኔታ ደግሞ እንግሊዞች ንጉሡን ይዘው በንጉሡ በኩል ፍላጎታቸውን ለማርካት አርበኞችን ለማዳከም እየሞከሩ ነው። ንጉሡም የእንግሊዞችን ሴራ ቢያውቁም እንግሊዞችን ለመቋቋም አቅም እንደሌላቸው ራስ ገብቱዋቸዋል። በአርበኛው መሃከል መከፋፈል ካለና ይህ ከታወቀ ንጉሡም ለግል ሥልጣናቸው እንግሊዞችም ለራሳቸው ዓላማ ያራግቡትና የኢትዮጵያ ነፃነት ከአደጋ ሊወድቅ ይችላል።

ስለዚህ ራስ አበበ ባለሰቡት መንገድ ከፈለው ከንጉሡ ጋር በመገናኘቱ ፕላናቸው ሊበላሽ ይችላል። ይህ ሁኔታ ግን እንደገና የሚታረምበት ዘዴ ከራሱ ከከፈለው አነጋገር ተገኘ።

ከፈለው ለዓላማቸው እንቅፋት የሚሆንባቸው አሁንም ከሌሎቹ አርበኞች ያነሰ የአገር መውደድ ስላለው እንዳልሆነ ያውቃሉ። ንገሡን በመውደድ ሳይሆን በእልሁና በንዴቱ የተነሳ እንቅፋት እንደሚሆንባቸው አመኑ። ራስ የሚፈልጉት በአርበኞች መሃከል መከፋፈል

ሳይኖር ሁሉም አርበኛ እሳቸው እንደሚሉት ሆኖ መልአከ ፀሐይን እንዳደረጉት ንጉሡን በቁጥጥር ስር አድርጎ፣ ለስሙ ያህል ብቻ አስቀምጦ መምራት ነው። ከፈለውና አበበ ያላቸውን ጠብ ንጉሡ ካወቁ እንደሚጠቀሙበት አልጠረጠሩም። ምንም እንኳን በእልኸኛነቱ የተነሳ ከፈለው ለንጉሡ ታዛዥ እንደማይሆን ቢያውቁም ራስ የንጉሡን ብልጠት ያውቃሉ። ስለዚህ ከፈለው ከንጉሡ ጋር እንዳይገናኝ በማለት ዙሪያውን ባሉት አገሮች በመጋቢት 1933 ላይ ራስ የራሳቸውን ሹማምንት ሹመው ከፈለውን እንዳያስተላልፉት ከለከሉ።

ዛሬ ሰኔ 13 ቀን ከፈለው ይህን ሁሉ ጥሶ ከንጉሡ ጋር ተገናኝቱዋል። ስለዳኘው ከፈለው የሚሰጠውን ምስክርነት ሲሰሙ ራስ ዳኘውን አስተዋሉና አሰቡ። "ዳኘው ጥሩ ሰው ነው። አንቀላፊኝ ላይም ሆነ በኩረ ማርያም ስንገናኝ አስተሳሰቡ እንደ ከፈለው አይደለም። ስለ አርበኞች አንድነት የሚቆረቆር ነው። ደግሞም ትሁት ነው። ታዛዥ ነው።" አሉና ከፈለውን ዝቅ አድርገው ዳኘውን ለማንሳት ቆረጡ። "ዳኘው የቱ ነው?" አሉ ንጉሡ። አባ ሃና ደብረክ ደብረክ ሲሉ ወደ ዳኘው መጥተው "አንተ ነህ ዳኘው? ትጠራለህ። " አሉ። ለምን አውቀህ አትመጣም ታለፋኛለህ በሚል መሰልቸት። ዳኘው የሰለለው ድምፃቸው ገረመው። ዳኘው ቲሊንቲን፣ መትረየስና ዕቃዎችን እያመለከተ "ምርኮኛና እቃ እጠብቃለሁ። የት አድርጌ ነው የምመጣው?" አለ።

የእንግሊዝ መንግሥት ተወካይ ጭውውታቸውን ይመለከት ነበርና አንድ ነጭ በማየቱ ተደስቶ ቲሊንቲን እያመለከተ ይናገር ጀመር። ወዲያው ቲሊንቲን ተረካቢዎች መጡና ከዳኘው ዘንድ ወሰዱት።

ዳኘው ቲሊንቲን ካስረከበ በኋላ እቃውን ጠባቂ አድርጎ ወደ ንጉሡ

ቀረበ። "ምን አድርገንልህ ነው እንደዚህ የተዋጋህልን?" አሉት ንጉሡ።

"ከጣሊያን በፊት ክብር ዘበኛ ነበርኩ። …… "

"ምን አደረግንልህ ታዲያ?"

ዳኘው በክብር ዘበኝነት ዘመኑ የበላውን ሥጋ የጠጣውን ጠጅ መቁጠርያዘ።

ራስ አበበ በሆዳቸው ሲያብላሉት የነበረው ነገር ብልጭ አለባቸው። የራሳቸውን ምስክርነት ለመስጠት ዘውዴ ጉልችንና ዳኘውን በግራና በቀኝ እጆቻቸው ይዘው ከንጉሡ ፊለፊት ቆሙና ምስክርነታቸውን ሰጡ። ዳኘውን በሚመለከት የአርበኞች ማኅበር ሲመሠረት በምክርም እየረዳ ማገልገሉን ከአዲስ አበባ ወደ አገሩ በ1928 ስለ አደረገው ውጊያ ከፍ አድርገው ተናገሩ።

ንጉሡም በበኩላቸው ዳኘውን ማስጠጋቱ የሚጠቅም መሆኑን አሰቡ። ራስ አበበ ይህን አላወቁም። ንጉሡ ግን ዳኘውን በመያዝ የመከፋፈል ተግባሩን ለመቀጠል

እንደሚችሉ አወቁ። ከፈለውን ቢያቀርቡት ራስ አበበ ይቀየማሉ። ዳኘውን ግን የሚቃወሙ አይመስሉም። ዳኘው ደግሞ ለከፈለው ታማኝ ባይሆን ኑሮ ከከፈለው ጋር አይኖርም ነበር።

ዳኘው ውለታ ቆጣሪ መሆኑን አስተውለው ብቻ ሳይሆን ተደርጎለት የሚያውቀው ቋሚ ነገር እንደሌላ ስላወቁ፣ ሁለተኛም አከታትለው ባለጋሻ መሬቶችና ሹሞች ያልነበሩ የጦር መሪዎች ብቻ በማግኘታቸው የአጠያየቅ ዘይቤአቸውን ቀይረው "ምን እንድናደርግልህ ትፈልጋለህ?" አሉት።

"በቅድም አያቴ ጊዜ የነበረው የቤተሰብ እርስት ተወስዶ መተዳደሪያ ሳይኖረን ስንከራከር እስከ ጣሊያን መምጣት ተጋዥ ሆነን ኖረናል። አሁንም ይኸው ባሮ ሁዳድ እንዲመለስልኝ ግርማዊነትዎ ቢፈቅድልኝ።" አለ ዳኘው በቁጥጥሬ ስር መሬቱን አድርጌ በአለፉት ዓመታት ተጠቅሜበታለሁ ማለትን አፍሮ።

"የማን ይዞታ ነው?" አሉ ንጉሡ ከሰው ጋር እንዳይጋጩ በማሰብ። በዚህ ዓይነት ወቅት መጠንቀቅ ያሻል።

"የቤተ ርስት ነው ጃንሆይ።"

"ሰጥተንሃል።" አሉ ንጉሡ ለዚህ ነው ችግሩ ለማለት ጣቶቻቸውን እርስ በርሳቸው እያፋተጉ።

ዳኘው ለጥ ብሎ እጅ ነሳ። የንጉሡን መመለስ ሲሰማ በጉልበቱ በቁጥጥር ስር ያደረገው ባሮ ሁዳድ ከይዞታው ወጥቶ ወደ ቤተ ርስትነት ይመለሳል ብሎ ፈርቶ ነበር። ፍራቱ ሳይዝ በመቅረቱ የሌለውን ነገር ያገኘ ያህል ተደሰተ።

ንጉሡ ባላሰቡት መንገድ ዳኘውን ማስደሰት መቻላቸው አስደስቱዋቸው "አንተ ከኛ ጋር በተከታይ መኪና አዲስ አበባ ትሄዳልህ።" አሉት።

"ግርማዊ ጃንሆይ ጦሩን ለማን ትቼ?"

"ጦር አለህ?" አሉ እንዳላወቁ መስለው። ራስ በዳኘው ሁኔታ ቅር እንዳለቸው አይተው ስለነበር።

"ጥሩ ነው ጦሩ ከከፈለው ጋር ይቆይ። አንተ ተከትለኸን ትሄዳለህ። ከቤተሰባችን አንለይህም።" ዳኘው ካሰበው በላይ ቀናው። ከፈለው የነገሩ አጀማመር ብቻ ሳይሆን

አጨራረሱም ደነቀው።

ዳኘው ስለ አዲሱ ሁኔታ እያሰላሰለ መሬት መሬት እያየ ሲያስብ "ደህና

ሁኝ ዳኘው!" የሚል የተኮላተፈ ድምፅ ሰማና ቀና አለ።

በአርበኞች ተማርከው የነበሩ የጣሊያን ወታደሮች እንግሊዞች ባቀረቡት ካሚዎን ተጭነው ይጓዛሉ። ከመሃከላቸው አንድ እጅ ይውለበለባል።

“ደህና ሰን……ቢቹ….ዳኘው……! ደ….ህና…….” የቲሊንቲ ድምፅ። ዳኘው ሮጦ ቲሊንቲን ስሞ ሊሰናበተው ፈልጎ የቲሊንቲን እጅ በፍቅር ዓይን እያየ ለመሮጥም ሆነ እንደ ቲሊንቲ እጁን ለማወዛወዝ አቅቶት ተገትሮ ቀረ። ልቡና ሰውነቱ ተለያዩ። እንደ ጫካው ኑሮ ትክክል የመሰለውን ከመሥራት የሚቆጥበው ተመልካች የሚሉዋቸው የንጉሡ ጆሮ ጠቢዎች ይኖራሉ የሚለው ፍራት ሰረፀበት። ጆሮ ጠቢ ስለመኖር አለመኖሩ የሚያውቀው ወይም እከሌ ነው ብሎ የሚጠረጥረው የለም። ብቻ ፈራ። “ከሌላ ሰው ይበልጥ የምፈራው ጥንት ክብር ዘበኛ ስለነበርኩ ይሆናል።” ሲል አሰበ። “የጫካ ሥነ ሥርዓትና የነፃነት ሥነ ሥርዓት በማለት ከፋፍሎ ሁለት ሥነ ሥርዓቶች ታዩት። ሰው ነፃነቱን ሌላ ሰው ከሚገፈው በላይ ከነገሮች ጋር ሳይቃረን ለመዋሃድ ሲጠነቀቅም ያጣዋል።

“ዳኘው ቀናህ አይደለም? ጥሩ አደረኩልህ። መሄድህ ነው? አይደለም?” አለ ከፈለው ተደናግሮትና ትንሽ ተከዞ።

“መሄዴ ነው። እግዜር ይስጥልኝ። ውለታዎን አልረሳም።” አለ ዳኘው ከፈለው ስለ እሱ የተናገረውን ሲያስታውስ ደስታ ልቡን አለሳልሶት።

“የሚገባህን ነው የተናገርኩት።” አለ ከፈለው ዳኘው ውለታውን ባለመርሳቱ ደስ ብሎት። “ይልቁንስ አዲስ አበባ ስመጣ የማርፍበት ቤት ተከራይተህ ጠብቀኝ።” አለ።

ዳኘው ወደ አዲስ አበባ ሲጉዋዝ የቲሊንቲ ድምፅ በሕሊናው ይደውላል። የቲሊንቲ እጅ በዓይነ ሕሊናው ይውለበለባል። “ደህና ሁኚ ቲሊንቲ!” ሲል በሆዱ ጮኸ። ከዚያም ሳያውቅ አውጥቶ በአፉ ተናግሮት እንደሆነ ፈርቶ ዙሪያውን ቃኘ።

⅄⅄⅄

# ጀግና ፀጉሩን ሲላጭ

ዳኘው አዲስ አበባን እንደ ቀድሞው ሆና አለማግኘቱ ብቻ ሳይሆን ጥንት በሚያውቃት ከተማ እንደ እንግዳ፣ እንደ ፀጉረ ልውጥ መታየቱም አስገረመው። አዲስ አበባ እንደ ደረሰ ተክለሃይማኖት ይነግረው የነበረውን ለውጥ ሲመለከተው፣ ከሰማው በላይ ሆኖ አገኘው። “ከመስማት ማየት ያስደንቃል።” አለ ዳኘው ፒያሳን እየተዘዋወረ ሲመለከት።

ንጉሡን ተከትለው የመጡት ስደተኞች፣ በከተማው ውስጥ አምስቱን ዓመት ያሳለፉ ያገር ተወላጆች፣ የጣሊያን ባለሙዋል የነበሩ ባንዳዎች፣ አለባበሳቸው፣ አወራራቸው እንደ ፈረንጅ ሆኑዋል። ግማሹ በንግግሩ መሃል ፈረንሳይኛ ደብለቅ ሲያደርግ፣ ሌላው ጣሊያንኛ ወይም እንግሊዘኛ ያክልበታል። የፈረንጅ ቋንቋ ማወቅ፣ እንደ ፈረንጅ መሆን፣ ትልቅ ሙያ ሆኖ በመቆጠሩ፣ ጦርነቱ ከማለቁ ጋር አርበኝነት ቸል በመባሉ፣ ዳኘውና ጓደኞቹን

እንዳልሠለጠነ ሰው እንዲሚቆጥሯቸው፣ የፈረንጅ ባለሙዋል በሕዝብ ዓይን ከፍተኛ ግምት እንዳለው ማየቱም፣ አስደነቀው። ባለውለታ አድርጎ የቆጠረው ሰውም የሚኖር አልመስል አለው።

ዳኘው አምስት ዓመት ያሳደገው ፀጉሩን ሹርባ ተሠርቶት ከትከሻው ላይ ዘፍ ብሎ፣ በዘመናት ውስጥ ጠንካራ ሆነው እንደ ገመድ የሚወጠሩት ጡንቻዎቹን፣ ቀጫጭን ቅልጥሞቹን፣ ቁምጣው ሳይሸፍነው መራመዱ ብቻ ሳይሆን፣ ችግር አርሶት የሸነታተረው ግንባሩና ብዙ የተኮሰው ጠበንጃው ከእጁ ጋር ተስማምቶ፣ አውሬ እያስመሰለው፣ ብቸኝነት ተሰማው። ካንድ ጠረንገሎ ወፍራም ማጅራት መች ይልቅ የዳኘው ቁመና በሰዎች ልብ የሚፈጥረው ፍርሃት፣ ብቸኝነት እንዲሰማው አደረገው። ብዙ እሱን የመሰሉ አርበኞች አሉ። አዲስ አበባ ግን መጭውን ትለውጣለች እንጂ አትለወጥም።

አርበኞቹን አዲስ አበባዎች እንደ ልዩ ፍጡር ያዩዋቸዋል። ከጣሊያን በፊት በአዲስ አበባ ውስጥ ፀጉራቸውን በኃይል ያጎፈሩ ወይም እንደ ሴት ልጅ ሹሩባ የተሠሩ ሰዎች አልነበሩም። የእነ አጼ ቴዎድሮስ ትዝታ ለአብዛኛው ሕዝብ የሹርባ አልነበረም። እንደ አርበኞች ደግሞ ትግል ግርማ ሞገስ የሰጠው ፊት ያ ትውልድ አይቶ አያውቅም።

ሰው እንደ ጉድ እንደሚያያቸው ሁሉ አርበኞችም አዲስ አበባን ለመላመድ አልቻሉም። ከመሰሎቻቸው ተለይተው ብቻቸውን ሲሆኑ ባእድ አገር የገቡ ይመስላቸዋል። ስለዚህም መሸታ ቤት ሲገቡም ሆነ መንገድ ሲሄዱ አብረው እጅብ ብለው አሥር ሃያ ሆነው ነው። መንገድ ላይ የሚያጋጥማቸው ሰው ዘወር ብሎ ያሳልፋቸዋል። መሸታ ቤት ሲገቡ ቀድሞ ይጠጣ የነበረው ሰው ሹልክ እያለ ይወጣል። አርበኞችና ነዋሪው ተቻችሎ መኖር አልቻሉም። በአርበኞቹ ላይ የሰው ዓይን ያሳደረባቸው ስሜት መጥፎ ስለሆነ አርበኞች በቀላሉ ጠብ የሚያነሱና የሚተጋገዙ ናቸው። በአርበኞች መሃከል የተፈጠረው ይህ ስሜት እርስ በርሳቸው አፋቀራቸው። በጫካ በነበሩበት ጊዜ ነፍስ ለመዋደቅ ይፈላለጉ የነበሩ አርበኞች አዲስ አበባ ውስጥ እንደ እናት ልጆች ይተሳሰቡ ጀመር።

ስለ ጎፈሬ በተነሳ ጊዜ የአዲስ አበባ ነዋሪ ጎፈሬ የጀግና ምልክት አይደለም፣ ራስ አበበ አያጎፍሩም፣ ከፈለው ወልደ ፃዲቅ አያጎፍርም አሉ፣ ሌሎችም ቢላጩት ይሻላል ይላል። አርበኞች ፊት ግን ይህን የሚያነሳ የለም። ራስ አበበ በአርበኝነት ጎፈሬያቸውን በአጭሩ ስለሚከረክሙት በኃይል አድጎ አያውቅም። ከፈለው ግን ሊያጎፍር እየሞከረ ቅጫም እየያዘ አስቸግሮት እርግፍ አድርጎ ትቶታል። ሌላው አርበኛ ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሳምሶን ሳይላጭ ስለተወው በኃይል አድጎ በተኩስ ጊዜ ከፊቱ ላይ እየተደፋ ያስቸገረው ባለሉጫ ፀጉር ሹርባ መሠራት ጀመረ። ከዚያም ጎፈሬና ሹርባ የአርበኞች የተለየ መታወቂያቸው ሆነ። በጣሊያን የባንዳ ሠራዊት ውስጥ ጎፈሬና ሹርባ ክልክል ሲሆን አንዳንድ በጦሊዮን እንዲያጎፍር የተፈቀደለት እንደ አርበኛው ግርማ ሞገስ ለመስጠት ነበር።

ከጎፈሬና ሹርባ ሌላ፣ አርበኞች የከተሜውን ሰው ፈሪ ብለው እንደሚንቁት ሁሉ፣ የከተሜው ሰው ያልሠለጠነ፣ አውሬ፣ እያለ ያማቸዋል። በሁሉቱም በኩል የቀድሞ

ዘያቸውን እንደያዙ የሚቆዩ መስለው ታዩ። ለዓመት ያህል፣ አርበኞች በጎፈሬና ሹርባቸው ኮርተው፣ ከተሜውም ፀጉሩን አሳጥሮ፣ ለማጎፈር ሳይሞክር ቀረ።

ይህ ግን ለሁልጊዜውም የሚዘልቅ አልነበረም። ከማኅበራዊ ግንኙነት ውጥረቱ ሌላ የአርበኞች እርስ በርሳቸው መስማማትና ራሳቸውን ነጥለው ማየት፣ በፖለቲካ አንፃሩም ለንጉሡ አሳሳቢ እየሆነ ሄደ። ስለዚህም መደበኛ ጦር ሠራዊት ሲቋቋም አርበኞችንም እንዲመለምል ተደርጎ፣ አርበኞች ፀጉራቸውን እየተሸለቱ፣ ቆብ እንዲጭኑ ተደረገ። የዚያን ሰሞን አርበኞች እርስ በርሳቸው ስለ ሹርባና ጎፈሬያቸው መቀለድ ያዙ።

“ወየው ጉድ። እንዴት ቅልል አልክ?” ይላል ጎፈሬውን ወይም ሹርባውን ያልተሸለተው አርበኛ የተሸለተውን አርበኛ ሲያይ። “ታሾፋለህ። አንተም ነገ ይደርስሃል።” ይላል መልስ ሰጭ።

የከተሜው ሰው ደግሞ ፀጉሩን ተላጭቶ ቆብ የደፋውን አርበኛ አሁን በጣም አማረብህ ይለዋል።

ከቀልዱና አሽሙሩ ባሻገር ግን በእርግጥም አርበኞች ከፀጉራቸው ጋር እየገፈፉ የሚጥሉት ነገር ነበር። የጫካ ባህልና ዘይቤአቸውን፣ የባላገር ዘይቤአቸውን ትተው የከተማውን እየተቀበሉ ነበር። መለያቸውን ጎፈሬና ሹርባቸውን ሲላጩ በመሃከላቸው ያለውን አንድነት ጥለው በአዲሱ ጦር ሠራዊት ውስጥና በሰፊ ክልሎች ውስጥ ተበተኑ።

መንፈሳቸው ከመላላቱ ጋር ልብሶቻቸውንም በከተማው ሞድ ማስቀደድ ያዙ። በአውሮፓ የልብስ ቅድ የራሱ የሆነ ይዘትና ትርጉም አለው። ወፍራሙን ሰው ቀጭን ለማስመሰል፣ ዳሌን ወጣ ለማድረግ ወይም ዳሌን ዋጥ ለማድረግ የሚያገለግል የልብስ ቅድ አለ። የበጋ ልብስ፣ የክረምት ልብስ የሚባልም የአየሩን ወቅት ተከትሎ የሚለዋወጥ አለባበስ ይገኛል። በሽግግር ሕብረተሰብ፣ በጣልቃ ገብ እድገት ግን ሰው ለገላው የሚስማማውን ሳይሆን ለመምሰል ብቻ ቀለሙንና ቅዱን በሌላ ሰው ዓይነት ስለሚያሰፋው በልኩ የተሰፋ ሳይሆን የተውሶ ይመስላል። ከሆዱ ዘርጣጣ ከቂጡ ወደ ኋላ የገፋ ጣሊያን ይህንን ቅርጽን ለማቅለል የሚያሰፋቸው ልብሶች እንደ ጌጥ በቀጫጭን አበሾች ሲለበሱ ቀጭኑ ወፍራም ለምምሰል የሚያስቀድደው ቅድ በወፍራሞች በመለበሱ የወፍራሙ በቀጭን በመለበሱ፣ ቀለም አመራረጡ ባለመስተካከሉ ሃበሻ ጥራዝ ነጠቅ ሆነ። እስካለ ዳኘውን በዚህ ዓይነት ልብስ መጀመሪያ ያየችው በጣም ገርሙዋት “ድሮ እንደ ጣሊያን ሁኑ ቢሉን ውርደት፣ ስድብ ይመስለን ነበር። ዛሬ ድል አድርገነው እንደሱ ለመሆን እንጣጣር ጀመር።” ብላ ሳቀች። እስካለም ግን የፈረንጅ ቀሚስ ብዙም ሳይቆይ አሰፋች።

ከፈለው ወደ አዲስ አበባ እንደመጣ ዳኘው ተቀብሎ ተከራይቶለት ከነበረው ቤት አስገብቶ አስተናግዶት ሌሊቱን ሙሉ ሲጫወቱ አደሩ። “ዳኜ ጃንሆይ ምን ምን ጠየቁህ? ምንስ ምንስ አልካቸው?” አለ ከፈለው ብቻቸውን የሆኑበትን ጊዜ መርጦ።

“እኔ ወታደሮቼን ይገፔ ክብር ዘበኝነት እንድመለስ ተፈቅዶልኛል። እርሰዎም ቢጠይቁ ወደ ጦር ሠራዊቱ ለመግባት ካለዚያም አገረ ገዥነት አያጡም። የራስ አበበን ራስነት እንዳፀደቁላቸው የመንዝ ገዥነትን ማን ይከለክለዎታል።”

“እኔን በሚመለከት ጥይቀውህ፣ አነጋግረውህ ነበር?” አለ ከፈለው።

“ክፉ ነገር የለበትም።” አለ ዳኘው በአጋጣሚ በሚመስል አከኋን ስለከፈለው ብዙ ሰው የጠየቀውን እያስታወሰ።

“እንዴት ነው ሁኔታው ሁሉ?” አለ ከፈለው። በአለፉት ጥቂት ቀናት አዲሱን ሁኔታ ለማወቅ ራሱን ቢጨምቅም የሚከሰትለት ተጨባጭ ነገር አጥቶ ተቸግሮአል።

“በጣም ጥሩ ነው። አርበኛው ሁሉ እርስት የሚፈልግ እርስት፣ ሹመት የሚፈልግ ሹመት እየጠየቀ ያገኛል።”

በእርግጥም ንጉሡ በፈረሰው የኢጣሊያ የአስተዳድር መዋቅር ምትክ

ጥንት በሚያውቁት መንገድ ሌላ መዋቅር ለመመሥረት አርበኞችንና ሌሎችን ክፍሎች እየተጠቀሙ ነው። ባንዳውና የከተማው ሰውም በሃሰት አርበኛ ነኝ እያለ ሲያስመሰክር ንጉሡ የአርበኞችን ቁጣ ሳያስነሱ በአርበኛው ስም ሌላውን ለመሾም እንዳለየ ያልፋሉ። ወሎን ለአልጋ ወራሹ፣ ሐረርን ለልዑል መኮንን ............ ወዘተ ሰጥተው ከዚያም በኢጣሊያ ጊዜ ያልሞቱትን መሳፍንት እነ ራስ ኃይሉና ራስ ስዩምን[68] በጎጃምና በትግራይ ከሾሙ በኋላ ቁልፍ የአስተዳደር ቦታዎችን ለስደተኞች ሰጥተው የተረፈውን ለኃይለኞቹ አርበኞች እየሰጡ ነው።

ትልቁ ችግር ግን በጣሊያን አስተዳደር መዋቅር መልክ በደመወዝ የሚተዳደር ጦርና የሲቪል አውታር መዘርጋቱ ነው። ይህም የማይቻል በመሆኑ ወታደሩና አስተዳዳሪው በማደሪያ መሬትነት በሚሾምበት አገር ላይ በመመራት እንዲተዳደር ተወሰነ። አብዛኛውን ሰው ለማስደሰት በሚደረግ ጥረትና፣ ከጦርነት በኋላ የሚፈጠረውን አለመረጋጋት ለመቆጣጠር በሚያስፈልገው የጦር ኃይል ብዛት የተነሳ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ወደ ጭሰኝነት ተወረወሩ። በዚህ ሁሉ መሃል ለንጉሡ የቀን በቀን ችግራቸው በአርበኞች፣ በስደተኞች፣ በባንዳዎች መሃከል ያለውን ልዩነት እየተጠቀሙ፣ ከሁሉም አስተዋጽኦ እየተቀበሉ ሥልጣንን ማደላደል ነው።

ከፈለው ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንደቀረበ “ልጃችንን አልጋወራሽን ይዘህ ወደ ወሎ ሂድልን። ይህን ትልቅ አደራ ካንተ በቀር ለማንም ልንሰጠው አንችልም።” አሉት።

---

[68] በጃንሆይ “ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ” ውስጥ የማይጨው ጦርነት እንደ ነገ ሊደረግ ትግራይ በመነሳቀሉ ራስ ስዩም ለጣሊያን የገቡ መስለው አርበኝነቱን እንዲያግዙ እንደዚሁም ከአዲስ አበባ ወደ ስደት ሲሄዱ ራስ ኃይሉን ከስር ቤት አውጥተው እስከ ድሬዳዋ ድረስ ይዘዋቸው ሲሄዱ አርበኞችን እንዲረዱ አስምለው እንደለቀቋቸው ጽፈዋል።

ከፈለው ከአዲስ አበባ፣ ከመንዝ እርቆ የሚሄድበት ምክንያት ስላልታየው "ጃንሆይ! ዳኘው ክብር ዘበኝነት ተፈቅዶልኛል ብሏል። ወታደሮቹንም ይዞ ክብር ዘበኛ ሊገባ ነው። ስለዚህ የኔ ጦር እየተሸረሸረ ነው። እኔ ብቻየን ምን ጦር እሆናለሁ። ከዚህም በላይ እኔ ሕመምተኛ ነኝ። ዳኘው ቢሄድ ይሻላል።" አለ።

ንጉሡ ስለከፈለው ባሕሪ አጥንተዋል። እልህ አያዋጣም። ለጊዜው መሄድ አልፈለገም። በሥሩ ያለውን ሠራዊት ግን ከዳኘው ጋር አቀላቅሎ መስደድን አይቃወምም። ንጉሡ ትንሽ እንደማሰብ አሉና በፈገግታ እየተመለከቱት "አንተ ትንሽ ጊዜ ውጭ ቆየን ዳኘው ይምጣ።" አሉ።

ዳኘው እንደገባ "ምን የገባንልህ ቃል ነበር?" አሉት ምስጢር

ባለመጠበቁ ብቻ ሳይሆን በየዋህነቱም ተገረመው።

"ክብር ዘበኝነት ከነባልደረቦቼ እንድመለስ ፈቅደውልኝ ነበር ጃንሆይ።" አለ ዳኘው በመርሳታቸው በመገረምና ከፈለው ዳኘው እንዲህ አለ ብሎ በመናገሩ እንደ ስህተት ሳይቆጠር እንደማይቀር ጠርጥሮ።

"እ.... እ........አዎን።" አሉትና በእርግጥ ድሮ ክብር ዘበኛ ከነበረ በቤተ መንግሥት ውስጥ የሚነገር ነገር ሁሉ በይፋ ከመገለጹ በፊት ምሥጢር መሆኑን ባለማወቁ ውሸታም መስላቸውና አንዲት ደወል ደወሉ። ደወሉ እንደተደወለም ሦስቱም ልጆቻቸው ከመጋረጃ ውስጥ ብቅ አሉ።

"ከነዚህ ከሦስቱ ልጃችን ማነው?" አሉት።

"መች አጣኋቸው ጃንሆይ። ሁሉም ልጆችዎ ናቸው። ከነዚህም ሌላ መጨረሻ የተወለዱት አሉ። ....." አለ።

"ባለቤታችን አገሩዋ የት ነው?"

"ወሎ ነው። እንዴት አጣዋለሁ ግርማዊ ሆይ። የሠርጉ ጊዜ ......"

"አሁን የፈለግንህ፣" አሉት ንጉሡ አቋርጠውት "ልጃችንን አልጋወራሽን ይዘህ የመንዝን ጦር ይዘህ ወሎ እንድትሄድ ነው።"

"ጃንሆይ እኔ አልሄድም።" ይህ መልሱ አላስከፋቸውም። ሸርና ጥበብ የማያውቅ የዋህ ባላገር ለጊዜው ባደረበት ፍቅር ከአጠገብ ላለመራቅ የሚያደርገው የዋህነት ጠባይ ነው። "እኛ በሌለንበት ለመንግሥታችን መዋጋት፣ ስንመጣ ትዕዛዝ አልቀበልም ማለት ምንድነው?" አሉ እንደመከፋት ብለው።

"ለዚህ አይደለም ጃንሆይ። ማይጨው ሲዘመት ጭፍራ ከአለቃው አይለይም ተብዬ ሳልዘምት ቀረሁ። አሁን ደግሞ ገና ጠላት ሙሉ በሙሉ ከአገራችን ሳይወጣ ከአጠገብዎ አልለይም ብዬ ነው።"

"ይሁን። ልጃችንስ ያው እኛ ማለት አይደለም?"

"እሺ ጃንሆይ። ትዕዛዝ ይጸፍልኝ። የይለፍ ይታዘዝልኝ።"

"አይዞህ። ከጓደኞችህ አናሳንስህም። ውለታህ ይከፈልሃል።" አሉት። እሱ ግን ሞገስ ማገኘቱን እንጂ ከዚህ ወዲያ ዓለም ስለመኖሩ ጥልቀቱ ገና አልሠፋም።

ከፈለው የመንዝ ገዥ ሆኖ ተሾመ። የከፈለውም ጥልቀት ከዚህ አይበልጥም። ዳኘው አልጋ ወራሹን አጅቦ ወደ ወሎ ሄደ። መሬት ያልነበራቸው አርሶ አደር አርበኞች ባለ ጋሻ መሬት፣ ሹመት ያልነበራቸው ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ቀኛዝማች፣ ግራዝማች ተባሉ። ከግብርና ወደ ገዥነት።

ዳኘው ፀጉሩን ከተቆረጠ በኋላ ፊቱን በመስተዋት ሲያይ ግርማ ሞገሱ ተገፎ ታየው። "አይ ሳምሶን" ብሎ በራሱ ቀለደ። ወዲያው ግን ፊታውራሪ የሚለውን ስምና መሬቱን አስታውሶ ልቡ ሞላና በመስተዋት ውስጥ ያለውን ዳኘውን አገላብጦ በፍቅርና በኩራት ተመለከተው።

⅄ ⅄ ⅄

# አይጣልን ነው ማውራት

ኃይለ መስቀል የአስካለ የአክስቱዋ ልጅ ነው። አስካለን በጣም ስለሚወዳት አስካልዬ እንጂ በሌላ ስም ጠርቱዋት አያውቅም። ቤተሰቦቹም በሙሉ የሱን ፈሊጥ በመከተል አዋቂውም ልጁም አስካልዬ ይላታል። አሰካለም ከሁሉ ሰው ይበልጥ ትወደዋለች። ሕይወት የምትቀይሰው ጐዳና ጠመዝማዛ ቢሆንም አስካለ የትኛውንም አቅጣጫ በትእግሥት ትቀበለዋለች። የማይሆን ነገር ስታገኝ አስካለ "ወደው አይስቁ" ትላለች።

በሕይወት ውስጥ ሦስት ዓይነት ማኅበራዊ አኑዋኑዋሮች አሉ። ሁሉም ሥርዓተ ማኅበር እነዚህን ሦስት አኑዋኑዋሮች እስካሁን ያቀፈ ነው። አንዱ ሌላውን በደንብ ላያውቀው ይችላል። አንደኛው ዓይነት፣ ሀብታምም ሆነ ድሃ ቤተሰብ፣ የተደላደሉ ሰዎች፣ አብዛኛው ሕዝብ በሚያውቀው ፈሊጥና ዘዬ ሕይወታቸውንና ጨዋታቸውን የሚመሩበት ነው። ሁለተኛው ዓይነት፣ በተወገዘው፣ በተከለለው ሽፍን ክፍል፣ ሕብረተሰቡ የተፋቸው እሥረኞች፣ ሴተኛ አዳሪዎች፣ እናት አባት ጠለላ የሌላቸው ልጆችና ኑሮ ያዳሽቃቸው አዋቂዎች በፈጠሩት ዓለም ውስጥ ያለው ዘይቤ ፈሊጥ ነው። ሦስተኛውና ብዙ ሰዎች ያላተኮሩበት ተጠላን፣ ተረሳን፣ የሚሉ ሰዎች የሚፈጥሩት የደነዘዘ ዓለም ነው። አስካለ የኋለኞቹ ሁለት ዓለማት ሰዎችን ስለማታገላቸው ይወዱዋታል። የአርበኝነትን ልዩ ክብር ከፊታቸው በማሞገስ እንደ ኤሊ ከድንጋይ ሽፋናቸው እንዲደበቁ አታደርጋቸውም።

ይልቁንስ የታፈኑ ስሜታቸውን በጥሞናና በተቆርቋሪነት በማዳመጥ ወደተሻለው ዓለም እንዲሻገሩ ታግዛቸዋለች።

ኃይለ መስቀል የባንዳነቱን ነገር፣ ከኢጣሊያ ጎን የመሰለፉን ነገር፣ ሲያነሱበት ግንፍል የሚል ነበር። ሰዎች ይህንን ያነሱብኛል ወይም ያለማወቅ በሰው ፊት ባንዳነቱን ያጋልጡብኛል ብሎ በመፍራት ዘወትር እንዴት ጀግና አርበኛ እንደነበር ያወራል። በተለይም በሃሰት የአምስት ዓመት አርበኛ ነኝ ብሎ ካስመሰከረ በኋላ ይህ ጠባዩ ብሶበታል። በኢጣሊያ ሠራዊት ውስጥ የነበሩ ሌሎች ሰዎች የርስ በርስ ግኑኙነታቸውን አጠናከረው፣ በአርበኞች እያሾፉ፣ ስለግል ጀግንነታቸው እርስ በርሳቸው እያወሩ በሚዝናኑበት ቦታ እሱ በጭንቀት ይኖራል።

ዛሬ አቶ ኃይሉ የሚባሉ የእነአስካለ አገርን ሰው ፈንክቶ ከአስካለ ጋር ጭቅጭቅ ገጥሙዋል። "ለመሆኑ በውሀ ቀጠነ እየተነሳህ ሰው መደብደብ አለብህ?" አለችው አስካለ ንዴት በፈጠረው ምሬት ጥላቻ ከፊቱዋ ላይ እየተነበበ።

"አስካልዬ በሰው ፊት አዋርዶኝ ነው የመታሁት። በአገራችን ልጆች ፊት ብቻ አይምሰልሽ። ከዚህ ከአገሬው ሰዎች ብዙ ነበሩ።" አለ አስካለ እንደምትቆረቆርለት አስተውሎ ልቡዋን ለማለስለስ በፈጠረው ዘዴ።

"ምን አለህ?" አለች አስካለ አሁንም እንደተናደደች ነገር ግን ምክንያቱን እንዲሰጥ በመፍቀድ።

"በነገር ሲነካኩኝ አርበኛ ነኝ ባይ ሁሉ ጀግና ላይሆን ይችላል። አሉ። እኔን ሲነኩኝ ነው። አሽሙር ነው።" አለ እልህና ምሬት እየተናነቀው።

"አይጣልን ነው ማውራት።" አለች አስካለ ተከዛ። የምትለው የምተናገረው ጠፍቱዋት።

"አስካልዬ አይጣልን ነው ማውራት ያልሽው ልክ ነው።" አለ ሳያስፈልግ እንድትናደድ በማድረጉ ተጸጽቶ። "ከጣለብንስ ወዲያ አስካልዬ?" አለ በማሳዘን ዓይን እየተመለከታት።

"ምንም አልጣለብህ። አንተው እራስህ ነህ ራስህን የምታስጨንቅ።" አለች። "አይደለሁም።"

አስካለ ግንፍል ብሎባት ተናግራው በማታውቀው ምሬት "ታዲያ አርበኝነት እንደዚህ የምትኮራበት ከሆነ ከጣሊያኖች ጋር ለምን ተደባለቅህ?" አለችው።

"አስካልዬ" አለ መሬት መሬት እያየ ተከዞ "ጨንቆኝ ነው! ወድጄው ነው፣ ጠልቼው ነው ማለት አይገልፀውም። ……… ደብረብርሃን የወጣሁ ጊዜ ታስታውሻለሽ? ያችን እርኩስ አክስቴን ነፍሱዋ መኖሩን ለመጠየቅ የወጣሁ ጊዜ? …… ከተማው እንደገባሁ ብዙ ወታደር ነበር። ቅዳሜ እለት ነበር። ቶሎ ቶሎ ሂዱ እያሉ ሲያመናጭቁን እኔም የጣሊያን ወታደሮችን ላለመጠጋት ከሚነዳው ሕዝብ መሃል መሃሉን እየሆንኩ በፍራት

ተውጨ ከገበያው ደረስኩ። አንገታቸው ተቆርጦ ጭንቅላታቸው ካብ ላይ የተደረደሩ ሰዎች ጋር ተፋጠጥሁ። ልቤ ፍስስ አለ። ......... ለማልቀስም ፈልጌ ለምን አለቀስክ ተብዬ የምገደል መሰለኝ። ምን እንዳሰኘኝ፣ ለምን እንዳልኩት አላውቀውም እንጂ በቁጣ የሚመለከተኝን የጣሊያን ወታደር ዓይኖች እየሸሸሁ "የታባታቸው! ይገባቸዋል!" ብዬ ተናግሬ ያንን ወታደር ቀና ብዬ ተመለከትኩት። እሱ ግን መረበሼንና መደንገጤን ብቻ የሚፈልግ እንጂ የኔን ድጋፍ የማይፈልግ ኑሮ፣ ወይም ቋንቋ ለቋንቋ አልተግባባን ይሆናል በካልቾ ዝቆ አባረረኝ። እኔም እሺ ጌታዬ እያልኩ፣ ምኑን እሺ እንደምለው እንጃ፣ አስር አስር ጊዜ እጅ እየነሳሁ ትንሽ ሄጄ ከዚያም ከገበያው ወጣ ብዬ ላይና ታች አለኝ።"

"ውይ ወንድሜ! ውይ ወንድሜን! ተወው። ይህን ዓይነቱን መርሳት ነው ቆንጆው። ከፉ ከፉውን ቢያስታውሱት ራስ ያዞራል።" አለች አስካለ ዓይኖቹዋ እንባ አቅርረው።

"የለም ለጠየቅሽኝ ነው መመለስ የጀመርኩት። ደግሞም እመልስልሻለሁ። ....... . ከዚያ ቦታ ሆኘ ከገበያተኛው መሃል አንዳንዱ እየተለቀመ እዚያው ሲረሸን ተመለከትኩ። ድንጋጤየ አፍኖኝ እንጂ "እኔ ከናንተ ጋር ነኝ። ከነሱ አይደለሁም። የጣሊያን መንግሥት ለዘለዓለም ይኑር።" ብዬ ለመጮህ ፈልጌ ነበር። ቃሌ ተዋጠ። የአብዬ አዝብጤን ልጅ፣ አብረን ሄደን የነበረውን ሲሰቅሉት በኔና በእሱ መሃል ልዩነት እንደሌለ ባውቅም "ይገባዋል! የታባቱ!" እያልኩ ዙሪያየ ላለው ሰው ሁሉ እየጮኩ አወራ ነበር። ከዚያ በኋላ አላስታውስም። ሲነጋ ከአንድ ዛፍ ሥር ላብ አስምጦኝ እየተንቀጠቀጥሁ ነቃሁ። ሊጥ እንደሰረቀች ውሻ ሹልክ ብዬ መቆም የማይችሉት እግሮቼ እየተርበተበቱ አገሬ ገባሁ። ብዙ ወር ታምሜ ዳንኩ። አስካልዬ ይህንን ዓይነት ፍራትና ሽብር ያልደረሰበት ቢነግሩት አይገባውም። ልቦለድ ይመስለዋል።

"ይህን ሁኔታ እየረሳሁት ቆይቼ በ1930 ላይ ጣሊያኖች አግረመርፊያ ሲመጡ ተረበሽኩ። ቀደም ሲል ራስ አበበ ሚስታቸውንና ሌሎች ቁስለኞች ይዘው መጥተው ለዳኘው አንተ ደብቀህ አስቀምጥልን ብለውት ወደ ቡልጋ ሲሻገሩ ጣሊያኖች ከነሱ የባሰ ኃይለኞች መሆናቸው ተሰምቶኝ ነበር። ጣሊያኖቹ የመጡ እለት ዳኘው ባንዲራ እያውለበለበ አገሩ ሰላም ነው። ታማኞች ነን። አታጥፉን በማለት ወደ ጣሊያኑ ሠፈር ሲያመራ እኔ እንደ መጥፎ ቅዠት ብቻ ሳይሆን እንደ ተስፋም አየው ነበር። ከዚያም ከጣሊያኖች መንደር ውስጥ ሲገባ አየሁት። ትንሽ ቆይቶ የኛን መንደር ጣሊያኖች በመድፍ መደብደብ ያዙ። ወዲያው ግን አቆሙ። ዳኘው እንደገና ወደ እኛ ሲመለስ ተመለከትኩ። አሽናፊዎቹ ኢጣሊያኖቹ ከመንደራችን ሲገቡ ተደግሶላቸው ሲበሉ እኔ በመርበትበት ቀባጠርኩ።"

"ምኑን?" አለች አስካለ በሃዘን ፈገግ ብላ።

"የራስ አበበን ባለቤትና ቁሰለኞቹን ከዋሻ ደብቆአቸው ሲመለስ ዳኘው ሰብስቦን ጣሊያን ሲመጣ ስለ ቁስለኞቹ ብትናገሩ ራስ አበበ ተመልሰው ይፈጁዋችኋል። እኔ አገሩ

ታማኝ መሆኑን ጣሊያኖቹን ሰብኬ እንዳይጎዱን አግባባለሁ። ማንም ሰው በምንም ሁኔታ ከዚህ ዝንፍ ቢል ወዮላችሁ፣'' ብሎን ነበር። "ስለ አገር ስለ ነፃነት ብዙ አውርቶ ነበር። አላስታውሰውም።''

"ታዲያ ምን ምስጢር አባከንክ።''

"በጣም ፈርቼ ስለነበር ስለ ጣሊያን ታላቅነት ብዙ እቀባጥር ነበር። በዚህን ጊዜ አንዱ ሹምባሽ ተነስቶ መፎከር ጀመረ። ግጥሙ ሁሉ እኔን የሚመለከት መሰለኝ። በጣም ፈራሁ ከዚያም አንዱ አበሻ የጣሊያን ወታደር ተነስቶ "በመሃከላችሁ የተደበቀ አርበኛ ቢኖር ለሚጠቁመው ኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ሽልማት ይሰጣል። አውቆ ሳይናገር የቀረ፣ የደበቀ ግን አይቀጡ ቅጣት ይቀጣል።'' ብሎ ተናገረ። በዓይነ ሕሊናዬ ላይ ደብረብርሃን ያየሁት በኔ ላይ ሲፈጸም ታየኝ። ስለዚህ አጠገቤ ላለው ሹም ባሽ እኔ አውቃለሁ። እናገራለሁ አልኩት።''

"ምነው በኃይል ይጨንቅሃል? አመመህ እንዴ?''

"አላመመኝም፣ ያለፈው እንደዚያን ጊዜ እየተፋጠጠኝ ነው። ሁልጊዜም እንደተፋጠጠኝ ነው። እኔም ሁልጊዜ ልሸፍነው እንደሞከርኩ ነው። ለዚህ ነው ስለ አርበኝነት ዘመን ከአርበኞች ይበልጥ የማወራው። ወሬየን አቋረጥሽኝ። አጠገቤ ላለው ሹምባሽ እኔ እናገራለሁ ስለው በማላውቀው ቋንቋ ተናግሮ ገፈተረኝ። የዚህን ጊዜ የዳኘው ወንድም ወልደሰማዕት ወደ ጎን ሳብ አድርጎ አጽናናኝ። ድፍረት ሰጠኝ። ግን በዚህ አላቆመም።'' አለ ከአስካለ ፊት ታዲያ ምን አጠፋህ የሚል ነገር ያነበበ መስሎት።

"ታዲያ ምን ሆነ?'' አለችው።

"ጣሊያኖች ከመሃከላችን ወታደርነት ለመቀጠር የሚፈልግ እንዳለ ሲጠይቁ እኔ ፈታደኛ ሆኘ ቀረብኩ። ፈቃደኛ የሆንኩት ግን መርበትበቴን ያዩት የአገሬ ሰዎች ይስቁብኛል ብዬ ሳይሆን ፈቃደኛ ሆኖ ቶሎ ያልወጣ የሚረሸን መስሎኝ ነበር። የዚያን ጊዜ ዳኘው በትዝብት ተመለከተኝ። ጣሊያኖችም ጥድፊያ ላይ ስለነበሩ አግረመርፊያ ብዙ ሰዓት አልቆዩም። እኔም ከኢጣሊያኖች ጋር ወደ ወረኢሉ ሄድኩ። የራስ አበበ ባለቤትና ሌሎች አርበኞች የተደበቁበትን ዋሻ ባለመናገሬ አደጋ ይደርስብኛል ብዬ ብፈራም ከአገሬ እየራቅሁ ስሄድ እየረሳሁት መጣሁ።''

"ስንተ ስቃይ አይተሃል! ወይ ወንድሜን!'' አለች አስካለ ልቡዋ በሃዘን ተሰብሮ።

"ምን ማለትሽ ነው? ከአንቺ ይበልጥ ተሰቃይቻለሁ?'' አለ በአነጋገሩዋ ደስ አለመሰኘቱ ከፊቱ ላይ እየተነበበ።

"አዎን። እኔ ከመሰሎቼ ጋር ሆኜ ጠላትን አድፍጦ የመጠበቅና የማጥቃት፣ የመጠቃት፣ የመባረር፣ የመራብ፣ የመሳሰሉትን ስቃዮች ነው የማውቀው። ሞትም ቢሆን ለጓደኞቼ በጦርነተ መሃል የሚመጣ አብዛኛውን አፋጣኝ ነው። ቁስለኞችም ከኛው ጋር

ራቡን ይቅመሱ እንጂ፣ እንደ አውሬ በዋሻ ውስጥ ያገግሙ እንጂ በጠላት እጅ አልተሰቃዩም። ያንተና የእትዬ ላቀች ሁኔታ ነው የሚያሳዝነኝ።" አለች ዓይኖቿዋ በአለፈ ትዝታ ፍዝዝ ብለው።

ወልደ መስቀል ጨዋታውን ከራሱ ወደ ሌላ ማዛወሩ ደስ ብሎት "የኔ እንዲያው ነው። የወይዘሮ ላቀች በእርግጥ ያሳዝናል። እሳቸውንም ባላያቸው በጦርነቱ ጊዜ ብዙ እስረኞችን አይቻለሁ። በአንደ ተራ ባለጌና ዱርየ እጅ በጅራፍ ሲተለተሉ እሱ ምህረት ይሰጥ ይመስል ጌታዬ ስሞትልህ የፈለግከውን አደርጋለሁ፣ በአርባ አራቱ ታቦት እያሉ መለመኑና፣ ሲበሻቀጡ እንደ ውሻ መሆን፣ እሱን ለማስደሰት በብልግናው መሳቅ፣ በስድቡ ፈገግ ማለት .......... ያ ተወዳዳሪ የሌለው ስቃይ ነው። በጠላት እጅ ከመውደቅ መሞት ይሻላል ይባልስ የለ? የጠላቱን አውሬነት በመመልከት ሰው እኮ፣ ጀግና እኮ በሰባራ እግሩ ሲቆም፣ በተቆራረጠ እግሩ በፍራት ሲራመድ አይቻለሁ። ......... ለዚህማ ማዘን ይገባል። እኔ ይህን መሰሉን ያየሁት ከምርኮ በኋላ ነው።" አለ ጨዋታውን እንደገና ወደ ራሱ ሳያውቀው መልሶ።

"የምን ምርኮ አመጣህ?" አለች ስቃይ መስማቱ አደንዝዙዋት።

"በ1933 ጣሊያኖች ጎንደር ወስደውን ስንዋጋ ቆይተን በትግራይ ወሰን በኩል እንግሊዞች ማረኩን። ከዚያም የምርኮኛ ቁጥር በጀርባችን ላይ ተለጥፎ ወደ ደሴ አምጥተው ጣሉን። ቁጥሩን እንኳን አልረሳውም። 5840 ነበር። ...... ጣሊያኖች ተሸንፈው ወጥተው የእኛ መንግሥት ተቋቁሞ ስለነበር ድሮ የሚገለፍጡልን ሰዎች እንደ ውሻ ተመለከቱን። ሌላው ሰው ግዴለውም። እኔ ግን ውሎዬ ከናነተ ጋርም እንደሆነ እንጃ የምገባበት ቀዳዳ አጣሁ። ....... .መሞት ስንት ጣሙ። ....... ፈሪ ሺ ጊዜ ይሞታል ይላሉ። ......... ማን የማይፈራ አለ። የእግዜር ጥለት ነው። ...... የዚያን ሁሉ ሰው ዓይን ለመሸሽና መጥፎ ነገር እንዳይናገር መለማመጡ አንዳንድ ጊዜ ከበው ማመናጨቅ ብቻ ሳይሆን የሚደባደቡትን መለመኑ እንዴት የሚያሰቅቅ መሰለሽ።"

"ምነው ጦርነት ባልኖረ።" አለች አስካለ። "በቃኝ አታጫውተኝ። ደግ ደጉን ነው ጨዋታ። ..... ይልቁንስ ጠላ ላምጣልህ።" ብላ ወደ ጉዋዳ ገባች።

"እሺ አስካልዬ" አለና የመጣበትን ምሬት ለመዋጥና እስካሁን ያለፈውን ለመርሳት ያህል ፀጉሩንና ማጅራቱን አሻሽቶ በኃይል አዛጋና ጣራ ጣራውን እያየ "አስካልዬ ቶሎ በይ። የምሄድበት አለኝ። አሰለቸሁሽ!" ብሎ ሳቀ። መገረምም ያስቃል። አስካለ ከነፃነትም በኋላ ፀጥታ ማረጋጋቱ ብቻ ሳይሆን የሰው መንፈስም መታደስ እንዳለበት እስከ ሙሉ ክብደቱ ተሰምቱዋት ተከዘች።

⅄⅄⅄

# የመጀመሪያው መጨረሻ

## የሁለተኛው መጀመሪያ ነው

ዳኘው አልጋ ወራሹን ይዞ ወደ ወሎ ለመሄድ ዝግጅት ባለበት ወቅት አስካለ ደግሞ ይዞት የሚሄደውን ስንቅ ለማዘጋጀት ከላይ ታች ስለምትል ብዙ ጊዜ አይገናኙም። ዳኘውም ወደ ቤቱ እንደመጣ የሚያጫውተው ሰው ስላጣ መቀመጫ ይዞ ወደ መስኮቱ ሄደና ተቀመጠ።

መስኮቱ አጠገብ ቁጭ ብሎ ከዛፎቹ ባሻገር ሰማዩን ተመለከተ። በውሀ መሳዩ ሰማይ ላይ የተዘረጋው ልቃቂት ደመና ዓይኑን ሳበው። ልቃቂቱ ደመና የቆንጆ ልጅ ፊት ቅርጽ ይዞ ወጣ። "ነፍስ ያለው ልጅ ይመስላል። ከፎቶግራፍም ይበልጣል።" ሲል አሰበና ከጎኑ ካለው ልቃቂት ደመና ላይ አተኮረ። የሚንጠራራ ግመል የመሰለ ስዕል አየና ሁለቱን ለማወዳደር ወደ ልጁ ምስል ዘወር አለ። በምትኩ ያገጠጠ አፉን የከፈተ ጭራቅ የሚመስል ስዕል አይቶ ተከዘ። ጥቁር ደመና መጥቶ ሲሸፍነው ደስ አለው። ከልቃቂቶቹ ደመናዎች አቅራቢያ የነበረው ጥቁር ደመና እየተነቃነቀ እንደነበር አላስታወሰም። ጥቁሩ ደመና በላያቸው ላይ ሲያልፍ ልቃቂት ደመናዎችም ወደ እሱ ውስጥ የሚሰጥሙ መሰለው። "አልፈውት ብቅ ባሉ፣" ሲል ተመኘ። ጥቁሩ ደመና በላያቸው ላይ ተደርቦ ዋጣቸው። ጥቁሩ ደመና ለቆት የሄደው ሰማይ ኩል መስሎ ታየው። አሁን የሚነቃነቅ ጉም የለም። አንዲት አሞራ ብቻ ብቅ ብላ በዛፎቹ ላይ አንዣባ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከበስተጀርባቸው ጠፋች።

ትንሽ ወደ ቤቱ ውስጥ ሲመለከት ቆይቶ እንደገና በመስኮቱ ሲመለከት ጥቁሩ ዳመና አልፎ ልቃቂቶቹ ደመናዎች ብቻ ቀርተዋል። አሁን ሁሉ ፀጥ ብሏል። "አንድ ነገር የሚነቃነቅ የሚመስለው ከሌላ ነገር ጋር ሲነፃፀር ነው ለካስ?" ሲል ትልቅ ነገር ያወቀ ያህል ተሰማው። "ቋሚ ነገር የለም። ጥቁሩን ደመና አሳልፎ የማይነቃነቅ የሚመስለው ይህም ልቃቂት ደመና ከትንሽ ጊዜ በኋላ ይበተናል ወይም ይጠቁራል።" አለ። እንደ በፊቱ ጥሩ ጥሩ ቅርጾችን መሥራት አቁሙዋል። አስቀያሚ ምስሎች እንኳን አይታዩበትም። ከሙት ፊት ዓይኑን እንደሚያዞር ተጠይፎት ተመለሰ።

ዳኘው ነፃነት ከተመለሰ፣ ባንዲራ ከቆመች በኋላ ስለሚያደርጋቸው ነገሮች ብዙ እቅድ አውጥቶ ነበር። በአርበኝነት ዘመን ከጠላት ጋር ፊለፊት እየገጠመ የጠላት ሰው ደም ማፍሰስ ብቻ ሳይሆን ለጣሊያን ያደረውን ሰፈር ለወታደር ስንቅ ሲዘርፈው በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳስከተለ ይገባው ነበር። እንደ ጊዜ በተመስጦ ራሱን በራሱ ሲመረምረው ጥንት ያልነበረበት ጭካኔ እየተጠናወተው መሆኑን ጦርነትም በግድ የሰው ልጅን ስቃይ የሚያስከትል፣ ወታደር ሲቪል የማይል መሆኑን ተገንዝቦ "ነፃነት አንድ ጊዜ ከተመለሰ፣

ባንዲራችን ተመልሳ ብትቆም ይህ ዓይነቱ የጦር ሕይወትን እርግፍ አድርጌ ትቼ እርስቴን ባሮ ሁዳድን እያረስኩ እኖራለሁ።'' ብሎ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ገባ።

ዛሬ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ ግን የማረጋጋት ሥራ የሚል ተተካ። ነፃ አውጭ ነን ብለው ከንጉሡ ጋር የመጡት እንግሊዞች ኢትዮጵያን በሞግዚትነት ለማስተዳደር ያላቸውን ፍላጎት ለማክሸፍ አርበኞች ከእንግሊዞች እየቀደሙ ርዝራዡን የኢጣሊያ ጦር ማንበርከክና መሣሪያውን መማረክ፣ ሰፊ ግዛቶቹን በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ አለባቸው። በዚህም የተነሳ እስካሁን ድረስ ከቦታ ቦታ፣ ከአገር አገር የመንከራተቱ፣ የመድከሙ፣ የመታኮሱ፣ በአጠቃላይ የጦርነት ወቅት ኑሮ አለቀቀውም። ከዚህ ከእንግሊዞች ጋር በሚደረግ ፉክክር ሌላ ደግሞ አገር የማረጋጋት ሥራ የሚሉት የንጉሡ ነገሥቱን ሥልጣን በአገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ማስገኘቱና ፖለቲካዊ አንድነቱን ማስገኘቱ፣ ያው የጦርነት ወቅት ነሮ ነው። ስለዚህ ዳኘው አስካለን አዲስ አበባ አስቀምጦ እሱ አልጋወራሹን ይዞ ወደ ወሎ ሄደ። ደሴ ከደረሰ በኋላ እንኳን አላረፈም። በየቦታው አፈንጋጮችን ለመቆጣጠር ጦር ይዞ መዞር አለበት። በአምስቱ ዓመት የአርበኝነት ዘመን ውስጥ ሳያልቁ የቀሩት መሳፍንትና ባላባቶች በጊዜው የማዕከላዊ ኃይል አለመኖር የተነሳ የራሳቸውን ግዛት የማቋቋም ፍላጎታቸው እያንሠራራ ነው።

በ1935 መንገሻ ስዩም[69] የወያኔ አመጽን በማስነሳቱ የመንዝን ጦር ይዞ ወደ ትግራይ እንዲሄድ ታዘዘ። ወደ ትግራይ ጉዞው ግን ገና ከመጀመሪያው ችግር ነበረበት። በከፈለው ሥር ከነበሩት የጦር አዛዦች ዘውዴ ጉልች[70] ከፈለው አያዘኝም በማለት እራሱን ገንጥሎ አውጥቶ ከእንደራሴው ከዳኘው ጦር ተነጠለ። አልጋወራሹም ከፈለውን እንደተቀናቃኝ ስለሚወስደው ዘውዴ ጉልችን ስለደገፈ የከፈለው ጦር ለወያኔ ጦርነት ወደ ሰሜን ሲያቀና የዘውዴ ጉልች ጦር ደሴ ላይ ቀረ።

አባቱ ራስ ስዩም[71] ቢመክሩት እንኳን አሻፈረኝ ብሎ ዘመነ መሳፍንትን እንደገና ለመመሥረት ሸፍቱዋል የተባለውን መንገሻ ስዩምን ለመያዝ ብዙ ጦር ወደ ሰሜን ተንቃነቀ። መንገሻ ስዩምም ብዙ ሰዎች ለማሰለፍ ችሎ ስለነበር የአገሩ ጀግኖች ከባድ ጦርነት አደረጉ። በመጨረሻ ግን አፈግፍጎ ከበረሃው ከጨው መቁረጫ ስለወረደ ዳኘው የሚያዘው ጦር ወደዚያ አመራ። ብዙም ሳይቆይ ግን መንገሻ ስዩም እጁን ሰጥቶ ወደ ንጉሡ ሊላክ ነው የሚል ወሬ ተሰማ። ንጉሡ ምህረት በማድረግ የወያኔን ጦርነት ምሳሌነት እንዳይኖረው ለማድረግ ያላቸው እቅድ በደፈናው ምህረት ሊያደርጉለት ነው ተብሎ ሲወራ በጦሩ መሃል

---

[69] በኋላ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም። በወቅቀቱ በሸዋ ውስጥ የወያኔን ንቅናቄ ያቀጣጠሉ ተብሎ ይታመን ነበር። በፍርዱ ወቅት ግን ነፃ ወጡ።

[70] ልጅ ዘውዴ ጉልች በሸዋ የታወቁ አርበኛና በዚህ ዘመን መንዝ ውስጥ ሸፍተው ከታሠሩ በኋላ በምህረት ተለቀቁ።

[71] ልዑል ራስ ስዩም ታዋቂ አርበኛና በታህሣሱ ግርግር ጊዜ መስዋዕት የሆኑ።

ቅሬታን ፈጠረ። ዘመነ መሳፍንትን ለማምጣት፣ ስንት ደም ያፈሰሰና ያፋሰሰ ሰው እንዴት ጥሩ ነገር እንደሠራ ሞገስ ያገኛል የሚል ማጉረምረም ተነሳ።

የዳኘውም ጦር ከጨው መቁረጫ እንደተመለሰ ይህን ወሬ ሲሰማ ተናደደ። ስለዚህም መንገሻ ያልፍበታል የምትባለውን መኪና አድፍጠው መጠበቅ ያዙ። መንገሻ ግን በአሳቻ መንገድ እንዲያልፍ ተደርጎ አዲስ አበባ ገባ። ብዙም ሳይቆይ ለትምህርት ተብሎ ወደ እንግሊዝ አገር መላኩን እነዳኘው ሲሰሙ ገረማቸው። የንጉሥ ደም ያለው እንደ ተራ ሰው እንደማይዳኝ፣ ቢታሠርም በወርቅ ሠንሠለት እንጂ በብረት እንዳልሆነ ታሪክ እየጠቃቀሱ ሁሉም አውርተው ረሱት። የወያኔ ጦርነት ግን የጦርነት ሕይወት አመራር ማብቂያ አልነበረም።

ዘውዴ ጉልች ወደ መንዝ ተመልሶ ሸፍቱዋል ስለተባለ ያንን ለማብረድ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ዳኘው ታዘዘ። ዘውዴ ጉልችና ዳኘው ጓደኛሞች ብቻ ሳይሆኑ ዘመዳሞች መሆናቸውን ንጉሡ ስለሚያውቁ ነገሩን በብልሃት ይዘውታል። ዳኘው ስለ ዘውዴ አሸፋፈት ታሪክ ትግራይ ሰምቶታል።

ለወያኔ ጦርነት ሳይዘምት የቀረው ዘውዴ ጉልች ወሎ፣ ለገሂዳ፣ አካባቢ አገሩ ሸፍቱዋል ስለተባለ ከአንድ ደጃዝማች ጦር ጋር ተዳብሎ ይዘምታል። ከዚያም ከባድ ጦርነት ይሆንና ደጃዝማቹ ሲሞቱ ዘውዴ ጉልች ግን ከበባውን ጥሶ ወደ አገሩ መንዝ ይመለሳል። "ይኸማ ያው እንደድሮው ጦርነት ተነሳ አይደለሞይ" በሚል መንደርደሪያ ዘውዴ ጉልች መንዝ ገብቶ እንደ ቀድሞው የአርበኝነት ዘመኑ ዋሻ ገብቶ እምቢ ያለውንም በመግደል ደም ይቃባል። በመንግሥት በኩልም ሌላው ቢቀር በወንጀል እንደሚፈለግ ስለጠረጠረ ሽፍትነቱን ይቀጥልበታል።

ዳኘው አዲስ አበባ መጥቶ ከንጉሡ ፊት ሲቀርብ በመልካም አቀራረባቸው መንዝ እንዲሄድና አገሩን እንዲያረጋጋ አዘዙት። "ዘውዴ እንዴት እንደሸፈተ ሰምተናል።" አሉት። "መንግሥት የፈረሰ መስሎት ለኛ የተጋደለ መስሎት ነው የሸፈተው። በዚህም ስሕተት ብዙ ደም አፍስሱዋል። አሁን አንተ ሄደህ ከደመኞቹ እንዲታረቅ፣ ካሣውን ግን እኛ እንደምንከፍልለት አሳምነኸው፣ ምንም እንደማይደርስበት አስረድተኸው ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲመለስ አድርግ። እንቢ ካለ ምን ይደረጋል።" አሉና ካባቸውን አጣፉ። ዳኘው ንጉሡ የሚሉትን ብቻ ሳይሆን መልካም ሃሳባቸውን፣ እሳቸው ለዘውዴ ካሣ ከፋይ መሆናቸው ታይቶት ሳይቅማማ እሺ አለ።

ዘውዴ ጉልች ጋር ብዙ ጦር ሜዳዎች አብረው መዋላቸው ብቻ ሳይሆን የሚወደው ዘመዱ ስለሆነ ከስሕተት ላይ በወደቀበት ጊዜ ደርሶ መጥፎ እንዳልታሰበበት አስረድቶ ከክፉ ነገረ ሊያድነው እድል በማግኘቱ ደስ አለው።

ወደ መንዝ ጦሩን ይዞ ሲሄድ የሚያሰላስለው የነበረው ዘውዴን በወንድምነቱ እንዴት እንደሚገስፀው ነበር። ዘውዴ ጉልች ከመሸገበት ቦታ እንደደረሰ መልዕክተኛ ሲልክበት

ወዲያው እንደሚመጣ አምኖ ነበር። “ለበደልካቸው ጃንሆይ ካሣውን ይከፍሉልሃል። አንተ ከደመኞችህ ታረቅ.......” ብሎ ላከበት።

ዘውዴ ይህ የማይሆን ነገር ነው ብሎ መልስ ሲሰጥ ዳኘው በጣም ከፋው። ከዘውዴ ጋር ደግሞ ጦርነት ሊገጥም አይችልም። ዘመዱ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ዘውዴ ከዋሻው ውስጥ ሆኖ የተጠጋውን ጦር ለመረፍረፍ እንደሚችል ያውቃል። ዳኘው አካባቢውን ስለሚያውቀው ዘውዴ በአርበኝነት ከዚያች ዋሻ እየወጣ ጣሊያንን የሚያጠቃበትን ማለፊያ መንገድ ስለሚያውቅ ከበራፎቹ ላይ ወታደሮቹን እርሻ እያረሱ ዘብ እየጠበቁ እንዲቀመጡ አደረገ። ብዙ ወራት አለፉ። ዘውዴ ጉልችም በሩ ስለተያዘበት ዘውዴም ከዋሻው ውስጥና አካባቢ ስለሆነ አልተደፋፈሩም። በየጊዜው ግን በሰው በኩል ሰላምታ ይለዋወጣሉ።

አንድ ቀን ዘውዴ ጉልች ዳኘውን ብቻህን መጥተህ ተጋበዝ ብሎ ላከበት። ዘውዴ በዋሻው ውስጥ ጠላ አስጠምቆ ነበር። ዳኘውም ሰው ሳያስከትል ሄደ።

“እኔ ወንድሜ ነህ አልወጋህም። ከእንግዲህ ተለዋጭ ጦር ይመጣልሃል። ከዚያ ጋር ትዋጋለህ። ለመሆኑ የእርቁን ጃንሆይ ከከፈሉልህ አንተ ከባላጋራዎችህ የማትታረቀው ለምንድነው? ጃንሆይን ጠርጥረሃቸው እንደሆነ በኔ ይሁንብህ ክፋት የለውም።”

“ምን አሉ?” አለ ዘውዴ በዝርዝር ሊሰማው ፈልጎ።

“ከአገርህ የገባኸው፣ የሸፈትከው፣ መንግሥት የፈረሰና የጣሊያን ዘመን ዓይነት የመጣ መስሎህ እንደሆነ ያውቃሉ። ለኛ የተዋጋ መስሎት ነው ብለውኛል።”

“ያልሆነስ እንደሆነ? እያወቁ ሊያታልሉኝ እንደሆነስ?”

“አይደለም። አገልግሎትህን አይተው ነው ካሣውን እኔ እከፍላለሁ ያሉት። ተው አይበጅም።” አለ ዳኘው።

መጠጥ እየጠጡ ሲጫወቱ ዘውዴ ስሜቱ ተለሳልሶ በዳኘው ውስጥ ያሉ የድሮ ጓደኞቹን አንድ ባንድ እየጠራ ይጋብዝ ጀመር። ዋሻው በዘውዴና በዳኘው ሰዎች እኩል ለእኩል ተሞላ። በመጨረሻም ዘውዴ ከደመኞቹ ለመታረቅ ፈቃደኛ መሆኑን ገለፀና ዳኘው ወደ ራሱ ሠፈር ብቻውን ተመለሰ።

በማግስቱ ዳኘው ዘውዴ አባቴን ገድሎብኛል ከሚል ሰው ጋር ሆኖ ሲጠብቀው ዘውዴ ከዳኘውና ከራሱ ሰዎች ጋር መጣ። ዘውዴ ግን የሙዋቹን ልጅ ሲያየው ደሙ ፈልቶ እርቁንም፣ ይቅርታ መጠየቁንም ረስቶት “ምን ዓይንህን ታጉረጠርጥብኛለህ?” አለ።

ዳኘው እንደገና ደም ከመፍሰሱና ነገሩ ይበልጥ ከመበላሸቱ በፊት እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ተገነዘበ። ዘውዴ ጠበንጃ በትከሻው፣ ቦንብና ሽጉጥ በወገቡ ያነገበው ለቀልደ አይደለም። ከተናደደ እንኳን ለአንድ ሰው ሺም ሰው ቢሆን መሣሪያዎቹን ያሠራቸዋል። ዳኘው “መሣሪያውን ግፈፉት!” ሲል ትዕዛዝ ሰጠና ዘውዴ ሳያስበው በርብርብ መሣሪያዎቹን ተገፈፈ። የዘውዴ ሰዎችም ወደ ሰላማዊ ኑሮ ለመመለስ ባላቸው ፍላጎትና

አደጋ እንደማይደርስበት ባላቸው እምነት አላንገራገሩም። ዘውዴ ይህን ሁኔታ ሊቀበለው ስለማይችል፣ ከተለቀቀም ሰው ይጨርሳል ተብሎ ስለተፈራ ንጉሡ የገቡለትን ቃል እስኪፈጽሙ ድረስ ወደ እሥር ቤት ተዛወረ።

“ከአገሬ ሰዎች ጋር ቂም አተረፍኩ። ደጃዝማች ከፈለው አልዘምትም ያሉት ይህን ፈርተው ኑሮዋል። እኔ ዛፍ ብሆን ሥሮቼን አውቄ እንደቆረጥኩ ይቆጠራል።” ሲል ዳኘው አሰበ። ቢሆንም ግን አሁን ተግባሩን ስለፈጸመ ከንጉሡ ስንብት ተቀብሎ ወደ አገሩ ተመልሶ በእርሻ ለመተዳደር አዲስ አበባ ሄደ።

ዳኘው አዲስ አበባ ደርሶ ከንጉሡ ፊት እንደቀረበ ግን ወደ አዶላ የወርቅ ማዕድን ለሥራ እንዲሄድ ታዘዘ። ዛሬ ግን ለሌላ ሳይሆን ለቤተሰቡ በማሰብ መልስ ሰጠ። “ጃንሆይ!” አለ። “እኔ ደካማ ወላጆቼን፣ ልጆቼን ትቼ በጠላት የፈረሰ ንብረቴን ሳላቋቁም እስካሁን በመንከራተት ላይ ነኝ። አሁን አገሬ ተመልሼ ትዳሬን ለማቃናት፣ ጃንሆይ በመለሱልኝ እርስት እየረዳሁ ለመኖር እፈልጋለሁ። ቤተሰቤን እስካሁን ያጉላላሁት አንሶ ከእንግዲህ አልቀጥልበትም። የወታደርነት አግልግሎቴ ከተፈጸመ ወደ ግብርና ለመመለስ ፈልጌአለሁ። የአስተዳደር ሥራ ችሎታ የለኝም። መልካም ፈቃድዎን ይስጡኝ።” አለ በልመና።

“ስንት ልጆች አሉህ?” አሉት ንጉሡ ስለቤተሰቡ ተጨንቆ እንደሆነ መፍቻ መንገድ እየፈለጉ።

“ሦስት ልጆች አሉኝ ጃንሆይ። አንደኛው ትንሽ ነው።” አለ በቤተሰቡ ላይ ያለውን ችግር የትንሽ ልጅ መኖር ክብደት እንደሚሰጠው በማመን እና ነገሩ ማጠያየቅ በማስነሳቱ ቅር ብሎት።

ከዘውዴ ጉልች አመጽ ማብቃት በኋላ ዳኘው በአርበኝነት ዘመኑ ከነፃነት በኋላ ይመኘው የነበረው ኑሮ መሳኪያው እንደ ደረሰ ተሰምቶት ደስ ብሎት ነበር። እንግሊዞች ኢትዮጵያን በሞግዚትነት የማስተዳደር ፍላጎታቸውን የተው ሲሆን አጋዴንን ግን በጦርነት ሳይሆን በሌላ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ዘዴ የፈጠሩ ይመስል ሹማምንቱ ስለተውት ዳኘውም ትቶታል። አጋዴን ካልተዘመተ ደግሞ ጦርነት አበቃ ማለት ነው። ጦርነት ካበቃ እሱ እንደፍላጎቱ ግብርናውን ይቀጥላል። በዚህ ሃሳብ ልቡ ሞልቶ የመጣው ዳኘው አሁን ደግሞ ለአስተዳደር ሥራ ሲፈለግ አበሳጨው።

ንጉሡ ከልጆቹ በቀር ሌላ ችግር እንዳልነገራቸው ወይም እንዳልሰሙ ያህል “አንተ ወደታዘዝክበት ሂድ። ታማኝ ሰው ስለፈለግን ነው ያዘዝንህ፣ እኛ ልጆችህን ትልልቆቹን በትምህርት ቤት ትንሹን በሞግዚት እናሳድግልሃለን። ከፈለው ልጆቹን አምጥቶ ያስረክበናል።” አሉ።

ዳኘው ዙሪያውን ያሉት ሰዎች “እጅ ንሳ! እጅ ንሳ! ቶንጆ ሆኖልሃል!” ሲሉት ሳያውቀው ለጥ ብሎ እጅ ነሣ። ንጉሡም የሥራ ሰዓታቸውን ጨርሰው ተነሱ።

"አስካለ፣" አለ ዳኘው እቃውን ለማንሳት ወደ አገሩ ሲመለስ። "ቶሎ ብለሽ ለመንገድ ተዘጋጂ። ጃንሆይ ወደ አዶላ ለአስተዳደር ሥራ እንድንሄድ አዘዋል።"

"የአስተዳደር ሥራ ትፈልግ ኑሮዋል?" አለች በመገረም። "እኛስ ይሁን ልጆቹን ከአገር አገር ይዘን ልንዞር ነው?" አለች።

የሆነውን ሁሉ በልበ ሙሉነት ነገራት። አስካለ ግን ትምህርት ቤቱም ሞግዚቱም ደስ አላላት።

"ልጆቹን ጃንሆይ ያሳድጉአቸዋል። ደጃዝማች ከፈለው እንዲያስረክቡ ታዘዋል። እኔም አደራ ብያቸዋለሁ። ከንጉሥ ቤት ከማደግ በቀር ለልጆቹ ምን ትመኝላቸዋለሽ? እኔና አንቺ አዶላ ሄደን ፈቃዳቸውን መፈፀም ነው። ልጆቹ ከዚያ እስኪሄዱ እማማ የኔ እናት አለችላቸው። ከዚያም ከቀናን ቶሎ ሥራችንን ጨርሰን ተመልሰን ከዚሁ ከባሮ ሁዳድ የሰለም ኑሮ እንኖራለን።" አለ ዳኘው ጎረቤት ሁሉ አስካለ ወደ አዶላ እንድትሄድ ሲያግባቡዋት አቋዋርጦ።

"የመጀመሪያው መጨረሻ የሁለተኛው መጀመሪያ ነው።" አለች አስካለ ከጦርነት በኋላ ሁለተኛ ሆኖ መምጣት ያለበት ግብርናው መሆኑ ታይቱዋት። ዳኘው ምን ማለቱዋ እንደሆነ አልገባውም። ነገር ግን አዶላ አብራው ለመሄድ ማቅማማቱዋን ከፊቱዋና ከአነጋገሩዋ አንብቦ ደስ አለው።

⅄ ⅄ ⅄

# ሁለት ያጣ

ዳኘው አዶላ እንደደረሰ ያስተዳደር ሥራውን ጀመረ። በአዶላ የወርቅ ማዕድን ሥራው ለሕሊናው እርካታ የማይሰጠው ሆኖ አገኘው። ሠራተኞቹ ወርቅ እንዳይሰርቁ አንዱ ሌላውን እንዲሰልል ማድረግ ስለነበረበት በአርበኝነት ዘመን ሰዎች እርስ በርሳቸው እንደ ወንድም እንዲተያዩ ከሚያደርገው የተቀደሰ ሥራ ተቃራኒ በመሆኑ ከበደው። በአዶላ የወርቅ ማዕድን የሚሠሩ ሰዎች ለእረፍት ወደ አገራቸው ሲሄዱ ወርቅ ውጠዋል ተብሎ ከታሰበ ኮሶ እንዲጠጡ ስለሚደረግ ዳኘው በቀጥታ ባያደርገውም ኃላፊነት እንዳለበት በመገንዘቡ በሥራው ላይ እርካታ አጣበት። ይህንንም ፍተሻ አልፈው ወደ አገራቸው የሚመለሱ ሰዎችን ለመቆጣጠር ደግሞ መንግሥት ለደራሳና ጉጂ ጎሳዎች ወርቅ ይዞ ያገኙትን ሰው በሚመለከት "ከብቱን ለራስህ እጁን ለእኔ!" የሚል አዋጅ በማወጁና ትንሽ ቅሪት ለማግኘት ሞክረው በዚህ ዓይነት መንገድ የተያዙ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ከባድ ቅጣት አንገፈገፈው።

ዳኘው ከቤቱ ወጥቶ መሥሪያ ቤት ሲገባ ብዙ ስቃዮችን ስለሚመለከትና ለአሁኑ ሥራው የሕሊና ማጽናኛም ስላጣለት ብስጩ ሆነ። በጦርነቱ ዘመን ሰው ቢገድል ለነፃነቱ ተጋድሎ ነው። አሁን ግን ለብልጽግና በሚደረገው ሩጫ የሰው ማሰቅየት ጉዳይ ከባድ ሆነበት። ከዚህም ሌላ ሥራውን ሊተወው ባለመቻሉ ቅብጥብጥ ሆነ። ሕሊናው ተረበሸ። ከመሥሪያ ቤት ወደ ቤት ሲመለስ ሳያስበው ትልልቆችን ከማመናጨቁም ሌላ ትንንሽ ልጆችን መቆጣት ጀመረ። ከተቆጣ በኋላ ይፀፀታል። ሁለተኛ ከቤቱ ውስጥ እንደዚህ ላለማድረግ ቃል ይገባል። በማግስቱ ግን ያው ነው።

ዳኘውና አስካለ በዚህ ኑሮ ውስጥ ትንሽ ደስታ የሚሰጣቸው የነበረው ስለ ልጆቻቸው ሲያስቡ ነበር። አስካለ የንጉሥ ቃል አይታጠፍምና ልጆቹዋ እስካሁን ቤተ መንግሥት ገብተው ሲያድጉ ይታያታል። ንጉሥ ቤት ሁሉ ሞልቱዋል። “መቸም እናቴ የሚለኝ አይኖር …. ግን ትላልቅ መኳንንት ይሆናሉ። ……… እነሱ እድላቸው ይቃና እንጂ እኔ እንደ እድሌ እኖራለሁ” እያለች ታስባለች። ዳኘውም ከዚህ የተለየ ሃሳብ አልነበረውም። ብቻ ልጆቹን በሱ ጥረት እረኛ ሆኖ ከመቅረት የቤተ መንግሥት ቅምጥሎችና ወደፊትም ሹሞች በማድረጉ ወዲፊት ውለታውን ከፍለው እንደማይጨርሱት እየተሰማው አድገው የሚሉትን ሲያልመው ፈገግ ፈገግ ይላል። የሱን አባት አባቱ ጡዋሪው አገልጋዩ አድርጎ ነበር የሚየስበው። የሱ አባት እሱን እረኛ፣ ገበሬ፣ ጡዋሪ አድርገው ያስቡት ነበር። እሱ ግን ልጆቹን ታደጋቸው እንጂ አልተጠቀመባቸውም።

ዳኘውና አስካለ ይችም ተስፋቸው የደበዘዘችባቸው የዳኘው እናት ስለሞቱ መርዶ የመጣ ጊዜ ነበር። ዳኘው በእናት ሞት ሀዘን ልቡ ተሰብሮ ለቅሶ ለመድረስ፣ ከዘመዶቹ ጋር ለመላቀስ፣ ወደ አዲስ አበባ ተነሳ። አስካለም ተከተለችው። አዲስ አበባ እንደ ደረሱ ልጆቻቸውን ለማየት ጉዋጉተው ሲያጠያይቁ ልጆቹ ከአገር ቤት ገና እንዳልመጡ ነገሩዋቸው።

ዳኘው ከንጉሡ ፊት እንደቀረበ ለእናቱ ለቅሶ መንዝ ለመሄድ እንደመጣ ከተናገረ በኋላ እሳቸው ባሉት መሠረት ልጆቹን ከሜዳ አፍስሶ ሄዶ ቃል እንዳልተጠበቀለትና ከሥራው ስንብት ተሰጥቶት በግብርና እንዲተዳደር ጠየቀ።

“ከፈለውን አምጣ ብለነው ይኸው እስካሁን አላመጣልንም። በዚህ ነው እንጂ ረስተነው አይደለም። ለመሆኑ ስንት ናቸው ልጆችህ?” አሉት ንጉሡ ቀደም ሲል የነገራቸውን የዘነጉ በሚመስል ገጽታ። “ሦስት።” አለ ዳኘው መከፋቱ እንዳይታወቅበት እየተጠነቀቀ።

ንጉሡ በቀላሉ ሊሸነግሉት እንደሚችሉ አስተውለው የመንግሥት አዳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪ እንዳነሳቸው ትዝ ብሎዋቸው “እስከ አርባ እንቀበልሃለን። ከአገርህ የቻልከውን ያህል ይዘህ ና። ለቅሶህን ደርሰህ ልጆቹን ይዘህ ና። በትንሹ መከፋት አያስፈልግም።” አሉ በትክክለኛው መንገድ በለመታየታቸው የከፋቸው በመምሰል።

ዳኘው ጥፋቱን የደጃዝማች ከፈለው አድርጎ ተመለከተና የጃንሆይን ደግነት አስተዋለ። ዘውዴ ጉልች እንኳን ያን ያህል አስቸግሮ የደም ካሣውን እሳቸው ከፍለውለት ከእስር ቤት ወጥቶ አገሩ ገብቱዋል። ቃላቸውን ይጠብቃሉ ሲል አሰበ። ወዲያውም ዘውዴ ጉልች ባይፈታ ኑሮ ለልቅሶ እንኳን አገሩ ለመግባት እንደሚያዳግተውና እሱም ቂም ይዞ ምን ይሠራ እንደነበር ሲያስበው ዘገነነው። ደግሞም ወደ አስተዳደር ሥራ ሲመደብ ወታደሮቹ ወደ ጦር ሠራዊትነት ስለተዛወሩ አጃቢም የለው።

ሃሰቡ ወደ አርባዎቹ ልጆች ተመለሰና ያን ሁሉ ልጅ ከአገር ቤት አግተልትሎ ሲመጣ ታየው። ዘመድ ወዳጁንም ሊታደግ ነው!! ዳኘው አግረመርፊያ እንደደረሰ ለቅሶ ሊደርስ የመጣውን ሰው ሁሉ ልጆቻችሁን ስጡኝ። ጃንሆይ ያስተምሩላችኋል። እያለ ይሰብክ ጀመር። ሰው ግን ይህንን ሰበካውን የተለያየ ትርጉም ይሰጠው ጀመር።

ግማሹ ፈረንጅ አገር በጦርነቱ ምክንያት ወንዱ አልቆ ባሕር ማዶ ልጆቻችንን ሊልኩ ሲያታልሉን ነው አለ።

ሌላው ልጆቻችንን ካቶሊክ ሊያደርጉዋቸው ነው አለ። ሁሉም ሰው ግን እረኛ ልጁን ሰጥቶ ከብት ማን ሊጠብቅለት እንደሆነ አሰላስሎ በዚህ ደመደመ።

ዳኘውን የአገሩ ሰዎች አዲስ ባገኘው ክብርና ሹመት መሠረት ከፍ አድርገው እንጂ የነሱ የነበረ የጥንት ተራ ሰው አሁንም የነሱ የሆነ አድርገው አይቆጥሩትም። ስለዚህ ለሰበካው ጆሮዋቸውን አልሰጡትም። ታዳጊያቸው አድርገው አልወሰዱትም። ሌላው ቀርቶ የአስካለን የብቻ ልጆች ዘመዶቹዋ አንሰጥም አሉ። ተታኩሼ እወስዳለሁ ቢልም አስካለ ከለከለችው። ዳኘው በንዴት ሰውን ሁሉ በክፉ ይመለከት ጀመር። ባለውለታው የከዳው ሰው ንዴት ገነፈለበት።

ምን ቢናደድ ግን ወደ አዲስ አበባ ይዟቸው የመጣው ልጆች አርባ ሳይሆኑ ሦስት የራሱና ስድስት ሌሎች ብቻ ነበር። ሁሉም አዳሪ ትምህርት ቤት ገቡ። ዳኘው ወደ አዶላ ሲመለስ አስካለ ከልጆቹዋ ላለመራቅ አዲስ አበባ ተቀመጠች። ዳኘውም የቀድሞ ስሕተቱ ስለከነከነው አብራው እንድትሄድ አልገፋፋትም።

አስካለ ሁልጊዜም ከልጆቹዋ አዳሪ ትምህርት ቤት እየሄደች ለስድስት ወር ያህል ሳያዩዋት በአጥር እያሾለከች ሁኔታቸውን ታያለች። ዳኘው ከሸዋንግዥው የወለዳቸው ሁለቱ ልጆች ትልቅ ሲሆኑ ከሱዋ የተወለደው ግን ገና ልጅ ነው። አሁን ሃሳቡዋ ቤት መናፈቃቸውን ትተው ከዚያ እንዲለምዱ ነው። በምንም ሁኔታ ዳኘውን ትምህርት ቤቱ እንዲቀር ልታሳምነው አትችልም። በነዚህ እረጅም ጊዜያት አስካለ ከሃሳቡዋ ጋር ተሙዋገተች። አጥሩን ተደግፋ ከሩቅ ድምጽ እንደሌለው ሲኒማ እንቅስቃሴያቸውን እየተመለከተች በጥሩና በመጥፎ እየተረጎመች ከሩቅ በስሜቱዋ እንቅስቃሴያቸውን ለመምራት እየታገለች ቆየች። መንፈሱዋ የሚያርፈው ቅዳሜና እሁድ ለእረፍት ከቤቱዋ ስትወስዳቸው ነበር።

ዳኘው በዚህን ጊዜ ውስጥ ከአዶላ የወርቅ ማዕድን ሥራ ቦታው ንጉሡን ሳያስፈቅድ ወሎ አልጋ ወራሹ ዘንድ ተመለሰ። በአዶላ የወርቅ ማዕድን ውስጥ ከመሥራት አልጋ ወራሹ ዘንድ ሄዶ አሁን ካለው ደመወዝም ቀንሶ ወረዳ አስተዳዳሪ መሆንን የተሻለ አድርጎ ቆጠረው። ከአዶላ የአስተዳደር ሥራ ወደ ወረዳ አስተዳዳሪነት ሥራ ሲኮበልል ግን በእርሻ ለመተዳደር የነበረውን የረጅም ጊዜ እቅድ እርግፍ አድርጎ መተዉ ነበር። በአስተዳደር ሥራ ውስጥ የተሻለ ቦታ መምረጡ ለአስተዳደር ሥራ ፍላጎት እንዳደረበት ከማይመለሱበት ነጥብ መድረሱን የሚያሳይ ነበር። እስካለም ይህን ስትሰማ ደነገጠች። ወቅት፣ ሁኔታ ገፋፍተው በራሳቸው ባሕር ውስጥ እንዳሰመጡት አወቀች። ነገር ግን ምንም አልተናገረች። ዳኘው በዚያ በአዶላ ሲኦል ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ ያደረገውን ውሳኔ ለመውቀስ አልደፈረችም።

ለዳኘው አዲሱ ሥራው በጣም ተስማማው። በዳኝነት ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ ጉቦ ሳይበላ በመሰለው በመፍረድ፣ በአስተዳደር ላይ በሕዝቡ ላይ ጭንቀት ባለመፍጠሩ የመንፈስ ደስታ አገኘ። እያንዳንዱዋን ቀን ባከናወነው ሥራ ስለሚደሰት ከሥራ ቦታ ወደ ቤት ሲመለስ እንኳን ደስተኛ ነበር። በዚህ ሁኔታ ለስድስት ወር ያህል እንደቆየ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ከጽሕፈት ሚኒስቴር ትዕዛዝ ደረሰው። አዲስ አበባ የገባ ዕለት ዳኘው አዲስ ልጅ ተወለደለት። በጣም ደስ አለው።

ጽሕፈት ሚኒስቴር እንደደረሰ የጠበቀው ሌላም ቢሆን ውለታህ እንዲከፈልህ ማመልከቻ ጻፍ ተባለ። ከአዶላ ወርቅ ማዕድን ደህና ደመወዝ ከሚያገኝበት ቦታ ጠፍቶ መሄዱ እንደተሰማ ሁኔታው አሳሳቢ ሆኖ ነበር። በኋላ ግን የሄደው አልጋ ወራሹ ዘንድ መሆኑ ሲሰማ ከፍቶት ሊሸፍት ሳይሆን ውለታው እንዲከፈለው ማንገራበዱ ነው ተብሎ ተተረጎመ። ስለዚህ ነበር ጽሕፈት ሚኒስቴር አስጠርቶ ውለታህ እንዲከፈልህ ማመልከቻ ጻፍ ያለው። ይህ አቀራረብ ለዳኘው እንግዳ እንደሆነበት ሁሉ ለጽሕፈት ሚኒስትሩም የዳኘው መልስ ግራ ሆነባቸው። "እኔ ውለታዬ አልተከፈለኝም፣ ተበደልኩ አላልኩም። ስለዚህ የምጽፈው ማመልከቻ የለኝም።" አለ ዳኘው የተጠየቀው ጥያቄ ቀልድ ይሁን የምር ማወቅ ተስኖት።

"ፊታውራሪ ትልቅ ሰው ነዎት። አያስቸግሩ። ጃንሆይ ውለታዎን ይከፍሉዎታል። መቀየም አያስፈልግም።" አሉ የጽሕፈት ሚኒስትሩ የዳኘው መልስ ከኩርፊያ፣ ከንዴት የመነጨ መስሎዋቸው።

"እኔ አልጽፍም። አልጋ ወራሽ በቂየን ሰጥተውኛል። ምን አሳጡኝና ነው የማሳጣቸው።" አለ ዳኘው ለአልጋ ወራሹ ያለው ታማኝነት ከፀዳሉ እያበራ። "ይልቁንስ ከአዶላ ሥራዬ ስንብት ቢሰጠኝ ደስ ይለኛል።"

ጽሕፈት ሚኒስትሩ ይህን ሲሰሙ ፈገግ አሉ። ትልቅ ችግር እፈታለሁ ብለው የተጠበቡት ሰው፣ ከፊለፊታቸው የዋህ ሰው በማየታቸው ገረማቸው። "ኀበዝ ወታደር ሁሉ የዋህ ይሆን?" ብለው አሰቡ። ከቢሮአቸው ዳኘውን እንዳሰናበቱ ለንጉሡ ማታውኑ ሄደው ከዳኘው ጋር ስላደረጉት ጭውውት እየሳቁ ነገሩዋቸው። ንጉሡ ግን ይህንን ማመን

አቃታቸው። ሌላው ቢቀር በዘውዴ ጉልች ጉዳይ ትልቅ ትዕግሥትና ጥበብ አሳይቱዋል። “እስቲ ይሁን እናየዋለን።” አሉ ንጉሡ።

አዲስ አበባ ውስጥ ዳኘው አሥራ አምሥት ቀን እንደተቀመጠ ከቤተ መንግሥት የግብዣ ወረቀት ደረሰው። ወደ ግብዣው አዳራሽም እንደደረሰ የሱ ቦታ ከንገሡ ፊለፊት ከብዙ መኳንንት ጋር ሆኖ አገኘው። ዳኘው በጣም ተገረመ። ጃንሆይ ምን አስበው ይሆን?” ሲል አሰበ። መልስ ግን አላገኘለትም።

በግብዣው ላይ ከጎኑ የተቀመጠ አንድ ሥልጡን ባንዳ ያጫውተዋል። ዳኘው ምንም ለመጫወት ፍላጎት የለውም። ለትህትናው ያህል ግን ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ይሰጣል። ባንዳው የሚበላው በማንኪያና ሹካ ሲሆን ዳኘው ግን ስጋውን በእጁ ይዞ በቢላዋ እየቆረጠ ነው። የበታችነትና ያለቦታው የተደነቀረ ሰው ስሜት ተሰማው። የአርበኛ አበላልና አቀማመጥ ልዩ ነው ብሎ እራሱን ለማኩራራት ሞከረ። የንጉሡ ዓይን እስካሁን ከሱ ላይ አልተነቀለም። ጎንበስ ሲል፣ ከባንዳው ጋር ዘወር ብሎ ሲጫወት ሁሉ የንጉሡ ዓይን እንደተተከለበት ይሰማዋል። “ጃንሆይ ጀግና ይወዳሉ። የጀግና አበላልም ደስ ይላቸዋል። ስለዚህ በኔ አበላል ደስ ሳይላቸው አይቀርም።” ሲል አሰበ።

ንጉሡ ሰሞኑን በሰሙት ወሬ አንፃር ሲገመግሙት ቆዩና “የወጣለት ባላገር ነው” ሲሉ ሃሳባቸውን ደመደሙ። ልዕልት፣ የንጉሡ ሴት ልጅ አባታቸውን ስለሚያውቁ ደስ ብሎአቸው ፈገግ አሉ። ደኘው በጠባዩ ሳይሆን የሚፈልጉትን ነገር በእጁ ውስጥ እንዳደረገ ስለሚያውቁና አባታቸወም በዚያ በኩል እስካሁን ማሳመን ስላቃታቸው ይበሳጫሉ።

ዳኘው በማግስቱ ጽሕፈት ሚኒስቴር ሲሄድ ንጉሡ ከፈለገ ወሎ ይመለስ። ሁለቱም ቤታችን ነው ብለዋል የሚል ውሳኔ ተሰጠውና በጣም ደስ አለው። ከዚህም ሌላ መቶ ብር መጉዋጉዋዣ እንደታዘዘለት ተነግሮት መቶው ብር ተሰጠው። ከአስካለ የተወለደለት ሁለተኛው ልጅ ክርስትና ደርሶ ስለነበር በአስሩ ብር ደርዘን አረቄ ገዝቶ ከቤቱ ተመለሰ። ከደርዘኑ አረቄም ላይ ሁለቱን አንስቶ ትልቅ ፈንጠዝያ አደረገ። አስካለም ደስታው ተጋብቶባት ደስ አላት። ስለዚህም ወደ ወሎ አብረው እንዲሄዱ ሲጠይቃት እንቢ አላለችም።

ወሎ ውስጥ ዳኘውና አስካለ ለሦስት ዓመታት ደስ ብሎዋቸው ኖሩ። ይህ ደስታ ግን አልዘለቀም። ጉቦ አለመብላቱ ብቻ ሳይሆን በልቶ አለማብላቱ ከአልጋ ወራሹ ጀምሮ እስከ ስር ሹማምንት ቅሬታ ፈጠረ። ሹማምንቱ በመገባበዝ፣ ስጦታ በመለዋወጥ፣ በፌዝና በቀልድ፣ በተጫዋችነት እርስ በርሳቸው በሚተሻሹበት ወቅት ዳኘው የውጭ ተመልካች በመሆኑ እየተገለለ ሄደ። አንዳንድ ሹማምንት እንዳጋጣሚ ሲያገኙት እንደ ማሞገስ እያሉ ስለ ጉቦ አለመብላቱ ሲያነሱበት “በአርበኝነት ጊዜ አንድ ቀን ነፃነት ከተመለሰ በሰው ላይ መጥፎ ነገር ላላደርግ ለእግዚአብሔር ቃል ገብቼ ነበር።” ሲል ይመልሳል።

“ወሎ ጉቦ የማይበላ ሹም አይወድም።” ይሉታል።

ይህ ክርክር ከልቡ ጠብ አይልም። የሚያውቃቸው፣ የሚያስተዳድራቸው ሰዎች በጉቦ ባለመፍረዱ፣ በጉቦ ባለማስተዳደሩ እንደሚወዱት ያውቃል። አልጋ ወራሹም ጉቦ ባለመብላቱ ደስ ይላቸዋል ብሎ ያስባል። አንድ ቀን እሳቸው ይህንኑ አንስተው አሞግሰውታል። ለዚህ ነበር አስተዳደር አይችልም ተብሎ ከሥራው ሲታገድ በጣም እንግዳ የሆነበት።

አልጋ ወራሹ ዘንድ ቀርቦ ሥራውን የታገደው ያላግባብ መሆኑን ያስረዳ

ጊዜ ለጊዜው ደመወዝህን እየበላህ ተቀመጥ ሥራው ግን እንዴት እንደሚሆን እናስብበታለን ብለው መልስ ሰጡት። ዳኘውም ነገሩ ሁሉ ግራ አጋብቶት ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ።

የእንግሊዝ ንግሥት ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ይመጣሉ ከተባለበት ቀን አንድ ቀን ቀደም ብሎ ንጉሡ ባሮ ሁዳድን ከሱ ወስደው ለሴት ልጃቸው እንደሰጡ ሰማ። ይህም በጣም ከማስደንገጥ አልፎ የሚሠራውን አሳጣው። ወደ አገር ቤት ተመለሶ በግብርና ለመተዳደር ሲያስብ ስለነበር በጣም ከፋው።

ግብርናም አስተዳደርም እንደቀሩ አወቀ። ወደ ቤቱ ተመልሶ ሲገባ አስካለ ከምድጃው ዳር ተከዛ መቀመጡዋን እንኳን ዓይኑ ቢያይም ልቡ ያላስተዋለው በዚህ ብስጭት የተነሳ ነበር።

ዳኘው ለአስካለ የሆነውን ነገር ካጫወታት በኋላ በመጨረሻ የአስካለ ትካዜ ወደ ንዴት ተለወጠና "ሁለት ያጣ" ብላ በረጅሙ ተንፍሳ ከምድጃው ዳር ተነሳች። አንድ መንገድ ሊኖር እንደሚችል ተሰምቱዋታል። ምን እንደሆነ አላወቀችም። ዳኘው ቅድም ሽማግሌ ነው ወደ ሁዋላ እየተመለከተ ያለፈ ሕይወቱን የሚያሰላስል ያለው ትዝ አላት። "መበሳጨት አያስፈልግም። አምላክ ያውቃል።" አለች። ዳኘውም ፈገግ በሎ ተመልክቱዋት ከመቀመጫው ተነሳ።

የአርበኝነቱ ዘመን፣ የእነሱና የወላጆቻቸው ነበር። ያሁኑ ዘመን ደግሞ የእነሱና የልጆቻቸው ነው። "ከልጆቻችን ጋር የተሻለ ኑሮ ለመገንባት እንጥራለን።" አለ ዳኘው ከልጅነቱ መንደር አዳባይ በበልጉ ጎርፍ ሽሮ እየመሰለ፣ እየደፈረሰ፣ መልካዎቹን ለማልበስ እየገነፈለ፣ እየቀዘቀዘ ሲወርድ በዓይነ ሕሊናው እየታየው።

# ተፈጸመ

# የመጀመሪያው እትም መቅድም

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያን በአውሮፓና በአሜሪካ ከተሞች በጋዜጦች አማካይነት ስሙዋን በክብር ሲያስነሳ የቆየው አርበኞቹዋ የሚያደርጉት ተጋድሎ ነበር። በሩቅ ምሥራቅ የነፃነት ተጋዳዮች ዘንድ ደግሞ የአርበኞቹዋ የሽምቅ ውጊያ ጥበብ ምሳሌነቱና ጥልቀቱ ዝናዋ በቻይናና በቬትናም በረሃዎችና ጫካዎች እንዲወሳ፣ እንዲደነቅና እንዲተኮር አድርጉዋታል። ከዚያም የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲፈጸም ሰዎች በመልሶ ማቋዋቋዋም ተግባር ላይ በማተኮራቸው፣ በአገራችን ሥነ ጽሑፍ ባለመዳበሩ፣ አርበኞችም የራሳቸውን የተጋድሎ ታሪክ የመፃፍ ባሕሉም፣ ልምዱም፣ ችሎታውም ስለሌላቸው በአገራችን በአፈ ታሪክነት ብቻ ሲነገር ከምንጩ ማጠናከሪያ ያላገኘው ሌላው ዓለምም አየረሳው ሄደ። ዛሬ የዚያን ጊዜ ስለነበረው አብዛኛው ገበሬ የነበረ የአርበኛ ሠራዊት ማህበራዊ አኑዋኑዋር፣ ተጋድሎና ጥበብ በጥልቀት የሚታወቅ ነገር እምብዛም የለም። ራሳቸውን መስዋዕት ለማድረግ የቆረጡትና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው ሳምሶን ጥንካሬና ወኔያቸው ካለመላጨት የሚመነጭ ይመስላል ነፃነት ካልተመለሰ ፀጉራቸውን ምላጭ እንዳይነካው እርም ያሉት ተጋዳዮች ጥንካሬና ግስቁልናቸው የሚነበብበት ፎቶግራፍ አንዳንድ ጊዜ ብቅ ሲል ማህበራዊ አኑዋኗዋራቸውና የልብ ሥር ስሜታቸው ግን በየትኛውም ስዕል ወይም የታሪክ መጽሐፍ ሊታይ አይችልም።

እኔም ያገራችን የአርበኞች ተጋድሎ የሚያኮራና ትልቅ ትምህርትነት ያለው መሆኑ ቢሰማኝም ያንን ዘመንና እነዚያን ሰዎች በደንብ ለማወቅ ግን ቤተ መፃሕፍት ሊረዱኝ እንደማይችሉ በመረዳትና አርበኞችንም አዲስ አበባ ሆኖ ቢያነጋግሩዋቸው የቃለ መጠይቅ መልስ አሰጣጥ ችሎታቸው ለተነሳሁበት ዓላማ ማሙዋላት እነደማያጠግበኝ በመገንዘብ በቅርቡ በመንዝና ተጉለት ወሰን ላይ እየተዘዋወርኩ ጥናት ለማድረግ ተነሳሳሁ። የዚህ ዓይነት ጥናት ለሚጠይቀውም ሁኔታ እራሴን በማመቻቸት እንደ አገሬው በመኖርና የአገሬውን አስተሳሰብ ለመገንዘብ ከአካባቢው ጋር ራሴን ለማዛመድ ሞክሬያለሁ። ከሩቅና ከተገነጠለ ተመልካች ይልቅ የቅርብና የተዋሃደ ተሳታፊ የሆነ ልምድ አንድን ነገር ለማተኮር አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው። ምንም እንኳ ከዚያ ዘመን የራቅሁ በመሆኔ የሩቅ ተመልካች ብሆንም እነዚያ ሰዎች የኖሩትን ሕይወት ግማሹን ማለትም የዕለት በዕለት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮአቸውን ገበሬ በመሆን አይቸዋለሁ።

ለጠላት አንገዛም ብለው በዱርና በገደል ተሰደው የሽምቅ ዉጊያ ሲያካሂዱ የነበሩት የነዚህ ጀግኖች ታሪክ ዛሬም በየአጋጣሚው እየተነሳሣ እየተደነቀም እየተዋረደም የሚወራ ስለሆነ ስለነዚህ ሰዎች ታሪክ ብዙ በማዳመጤ ይበልጥ እንዳውቃቸው ጉጉት ስላደረብኝ የጽሑፍ ማስረጃዎችን መፈለግ ያዝኩ። የፈለግኩትን ያህል ባይሆንም አርበኞች እርስ በርሳቸው የተፃፃፉዋቸው አንዳንድ ደብዳቤዎችና ጣሊያኖች ለአርበኞች የበተኑአቸው ወይም የላኩዋቸው አንዳንድ ማግባቢያዎችን ለማግኘት ቻልኩ። በተለይም ከአገሬው ሕዝብ መሃል ለአርበኞች መሪዎች የቀረቡ የጽሑፍ አቤቱታዎችን በማግኘቴ የተነሣሁበት

ሥራዬ እንደሚሳካልኝ አመንኩ።[72] ከዚያም ይህን ጥናቴን ለመቀጠል ወደ አዲስ አበባ ከተመለስሁ በኋላ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የተጻፉ መጻሕፍትን በማንበብና ስለ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተደረሱ ታሪካዊ ልቦለዶችን በመመርመር የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን ሳውጠነጥን ቆይቻለሁ። ይህ ታሪክ ቀመስ ልቦለድ መጽሐፍ እንግዲህ የነዚህ ሙከራዎቼ ውጤት መሆኑ ነው።

አንዲት ባለሙያ ወይዘሮ በምትሠራው ወጥ ሽታና ቅመም ወስፋትዋ ከተዘጋ ጣዕሙን እነደማታውቀው ሁሉ ይህን ጽሑፍ ሳጠናቅቀው ምን ያህል የተዋጣለት መሆኑን አንባቢ እንዲገመግመው በመተው ስለዚህ ዓይነት ድርሰቶች ማብራሪያ መስጠት እወዳለሁ።

በአውሮፓና አሜሪካ ከሺ ዘመናት በፊት የነበሩ የታሪክ ሰዎችንና በቅርብ ጊዜም በታሪክ ውስጥ የታወቁ ባለሙያዎችን በመውሰድ የጊዜያቸውን አካባቢና ሁኔታ በሕብረተሰብ ሳይንስ፣ በማህበራዊ ሥነ ልቦና ሳይንስ ወዘተ በመረዳት መልሶ ለመፍጠር በሚደረጉ ሙከራዎች ረጃጅም ድርሰቶች እየቀረቡ ተወዳጅነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያለ መጥቱዋል። እንደዚህ ዓይነት ጽሑፎች ከምርምርና ከጥናት ከተቻለም ከሕይወት ልምድ የተገኙ ዉጤቶች ከሆኑ ከመደበኛው የታሪክ አጻጻፍም ይበልጥ አንድን ዘመን ቁልጭ አድርገው ከማሳየታቸውም በላይ ለአንባቢ የማይሰለቹ ናቸው።

በሀገራችን የግርማቸው ተ/ሃዋርያት "አርአያ" ፣ የአሰፋ ገብረ ማርያም "እንደ ወጣች ቀረች"[73] የመሳሰሉት ዝነኛ መጽሐፍት ከኢጣሊያ ወረራ ጋር ተዛምደው የቀረቡ ሲሆን አቶ ከበደ ሚካኤል ያቀረቡዋቸው የሃኒባል፣ የንጉሥ ካሌብ፣ የአክአብ ወዘተርፈ የቴአትር ድርሰቶች ከሥነ ምግባር ማስተማር ተልዕኮአቸው ሌላ አንድን የታሪክ ወቅት በይበልጥ ግልጽ አድርጐ ለማሳየት ይጠቅማሉ። ስለዚህ የዚህን ዓይነት የሥነ ጽሑፍ አቀራረብን ከሕዝብ ጋር ስላላመዱት የኔ አቀራረብ አዲስ ነገር አይደለም።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አብዛኛዎቹ ባለታሪኮች በእርግጥ የነበሩና ለነፃነቱና ለፀረ ኮሎኒያሊስቱ ተጋድሎ እዚህ ከተጠቀሰውም በላይ አስተዋጽኦ ያደረጉ እነጂ ያነሰ የሠሩ አይደሉም። በየወቅቱ ያደረጉት ጭውውት፣ የተሰማቸው ስሜት ወዘተርፈ ግን እንደተለመደው የግለሰባዊ ሥነ ልቦናና የማህበራዊ ሥነ ልቦና ሳይንስን በመጠቀም እንደገና የተዋቀሩ ናቸው። ይህም ቢሆን ግን በየጨዋታው ላይ የወቅቱን ስሜቶች ከሃሳባዊ መንደርደሪያዎች ጋር ለማገናዘብ የመስከ ላይ ጥናቴን ተገልግየበታለሁ።

---

[72] እነዚህ ደብዳቤዎች ከፊሎቹ አቶ ገበየሁ ጣሰው ዘንድ፣ ከፊሎቹ አቶ ሰለሞን ግርማ ዘንድ ጥቂቶቹ እኔ ዘንድ ይገኛሉ። በዚህ ሁለተኛው እትም ለናሙና ያህል ጥቂት ደብዳቤዎች በአባሪነት ተካተዋል።

[73] የቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው 'አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም" በታሪክ ቀመስ ልቦለድ መልክ ጣሊያኖች በኡጋዴን በመርዝ ጋዝ ሠራዊትና ሕዝብ የፈጁበት ታሪክን ዘግቦታል። ደራሲው በጦርነቱ ተካፋይ ስለነበሩ ዕይታቸው የተጠናከረ ነበር። አዳባይ ሲጻፍ ባልጠቅሳቸውም ለአንባቢው ማስታወስ በመፈለጌ ከዚህ ተጠቀሱ።

ባለፈ ትውልድ የተሠራን ታሪክ ሕያው አድርጐ ለማቅረብ ውጤቱ በሚቀዳባቸው ምንጮች ተሙዋልተው አይገኙም። በዚህም ምክንያት አነስተኛ ሚና ያላቸው አንዳንድ የፈጠራ ባለታሪኮች ማስገባት ግዴታ ይሆናል። ። አንዳንድ ሰዎች በዚህ መንገድ ቀርበዋል። ከዚህ በተረፈ ግን ታሪኩ እውነተኛ ነው።

የታሪኩ መድረክ መንዝና አካባቢዋ ሆኖ የተመረጠው በአጋጣሚ እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም። በኢጣሊያ ፋሽስት ወረራ ጊዜም ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ አርበኞች በመንዝና አካባቢዋ ዱርና ሸለቆዎች ይገኙ የነበሩት ለአዲስ አበባ ቅርብ በመሆንዋ አጋጣሚ ነበር። በአምስቱ ዓመት የአርበኝነት ዘመን እምቢ ላገሬ፣ እምቢ ለነጻነቴ ብሎ የተዋጋው አርበኛ ከኢትዮጵያ አጥናፍ እስከ አጥናፍ በየመንደሩ የነበረ ነው። የየአካባቢው አርበኞች ታሪክ በዚህ ባሁኑ መጽሐፍ መልክ ወይም በመደበኛ ታሪክ አቀራረብ ቢወጣ የሚደገፍ ከመሆኑም በላይ ገና በጠላት ዘመን በ1931 ዓ.ም. የተቋቋመው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ባሁኑ ጊዜ ይህንኑ ሥራ ትኩረት የሰጠው መሆኑን ስለሰማሁ በጣም ደስ ብሎኛል።

በሩሲያ፣ በአውሮፓና አሜሪካ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ላይ የተመሠረቱ ብዙ ሺ መጻሕፍት እየታተሙ ሲወጡ በኢትዮጵያ ይህ አለመሆኑ ከተጋድሎው ከፍተኛነት ጋር ተጨምሮ ከደራሲያን ገና ብዙ የሚጠበቅ እንዳለ ያመለክተናል። ስለዚህም ነገ፣ ተነገ ወዲያ በደቡብም በሰሜንም በምሥራቅም በምዕራብም ስለነበረው ያርበኝነት ተጋድሎ ብዙ ጽሑፎች እንደሚቀርቡ ጥርጥር የለውም። በጦርነት፣ በእርስ በርስ ግጭት ውስጥ የአብዮትን ያህል ባይሆንም የሰዎች ኑሮ ጠባይ የድሮውን ሳይሆን ለውጥ ያሳያል። የሰዎች ልቦና በእሳት እነደተፈተነ ሁሉ በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ በስሎ የጥንት ቅዠቱ፣ ምኞቱ፣ ጨቅላነቱ ረግፈውለት ገቢራዊ የሆነ እውነታ ይዞ ከመውጣቱም ሌላ በኢኮኖሚያዊ ኑሮውና በፖለቲካ ተቋሞች ውስጥም ሽግሽግ ያደርጋል። አጋጣሚና ሁኔታ ይበልጥ የሰው ልጆችን እድል ወሳኝ ይሆናሉ። ይህ መጽሐፍ ከታላቁ የነጻነት የሕዝቦች ተጋድሎ በተጨማሪ ይህን ሁኔታ ካንፀባረቀ በእኔ በኩል ዓላማየን አሙዋልቻለሁ እላለሁ።

ጥላሁን ጣሰው

# አባሪዎች ፣ የአርበኞች ደብዳቤዎችና ካርቱኖች

## አባሪ 1፣ የኢጣሊያ ኢትዮጵያን የመውረር እንደምታ



ከዚህ በላይ የተመለከተውን ካርቱን ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን የመውረር እንደምታን ለማሳየት ታዋቂውና የካርቱኒስቶች ንጉሥ ተብሎ የሚታወቀው ሰር ዴቪድ ሎው የዛሬ 79 ዓመት የሣለው ነው። ካርቱኑ የሙሶሊኒን ወረራ በግሪክ አፈታሪክ ከምትታወቀው ውብ እመቤት ፓንዶራ ድርጊት ጋር ያመሳስለዋል።

የሰዎችና የአማልክት አባት የሚባለው የጥንት ግሪኮች ዋነኛው አምላክ ዙስ፣ ለፈጠራት አማላይ ውብ ሴት ፓንዶራ፣ አንድ ሙዳይ እንዳትከፍተው አስጠንቅቆ ይሰጣታል። ፓንዶራ እንዳትከፍተው የተሰጣት ሙዳይ በውስጡ የያዘው ምን እንደሆነ ለማወቅ በመጓጓት፣ የዙስን ትዕዛዝ አፍርሳ፣ ሙዳዩን ስትከፍተው፣ በዓለም ላይ የምናውቃቸው በሽታዎችና ጭንቀቶች ከሙዳዩ ወጥተው ዓለምን ያጥለቀልቁታል። በዚህ ካርቱን የሙሶሊኒ ኢትዮጵያን የመውረር ድርጊት ከፓንዶራ አድራጎት ጋር ተመሳስሏል። ሙሶሎኒ በዓለም ሉል (ግሎብ) የተመሰለውን ሙዳይ ሲከፍት፣ ከሙዳዩ ውስጥ የሚወጣው ፍንዳታና እግሩን ሊያንቀው የተዘረጋ የልዩ ፍጡር እጅ ይታያል።

ሰር ዴቪድ ሎው እንደተነበየው በኢትዮጵያ መወረር ቅኝ ተገዥ ሕዝቦች

ከኢትዮጵያ ጋር እንዲያብሩና ለነፃነት እንዲነሳሱ አደረገ። በዚህ ወረራ የተነሳ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ተቀጣጠለ፣ የቅኝ ግዛት ተንኮታኮተ። የጦርነቶች ሁሉ ተፍጻሜት

ከተባለው የመጀመሪያው ዓለም ጦርነት በኋላ የተቋቋመው የዓለም መንግሥታት ማህበር ፈረሰ፣ የእንግሊዝ የበላይነት በአሜሪካ ተተካ። ሶቪዬት ሕብረት ሌላዋ ኃያል ሆና ወጣች። የቀዝቃዛው ጦርነት ተጀመረ።

**አባሪ 2፣** ኢጣሊያኖች የመርዝ ጦርነት ማድረጋቸውን ቢክዱትም በወቅቱ በእንግሊዝ ጋዜጣ ላይ ከወጡ ካርቱኖች





የመርዝ መከላከያ የለበሰውና መርዝ የታቀፈው ሙሶሎኒ፣ በአውሮፕላን በሚረጭ መርዝ የሞቱትን ሸማ የለበሱ ኢትዮጵያውያንን እያመለከተ "ሃይማኖት የሌላቸው አሕዛብ ናቸው።" ይላል። የሙሶሎኒን ትዕቢት ለማሳየት ሰር ዴቪድ ሎው በወቅቱ የሳለውና በወቅቱ የእንግሊዝ ጋዜጣ ላይ የወጣ ካርቱን።

ጣሊያን ተምቤን ላይ ካጋጠማት ሽንፈት በኋላ የተጠቀመችው መርዝ ከመስታርድና ፎሰጂን የተለየ ሲሆን የሰሜኑ ጦር አዝማች ከነበሩት በልዑል ራስ ካሣ እንደሚከተለው ተገልጿል። "ጥቅጥቅ ያለ የዝናብ ዓይነት ፍንጣቂ ሲዘንብብን አገሩ በሙሉ እሳት የተያያዘ ይመስል ነበር።.... ቡናማ ቀለም ያለው፣ የማይጨበጥ ቆዳን አቃጥሎ የሚበላ እንፋሎት ዓይነት የመርዝ ጋዝ ነበር በወታደሮቻችን ላይ የሚዘንብባቸው። በዚች ቀን ብቻ ቁጥሩን መናገር የሚያሰቅቅ ወታደሮቻችን አለቁ። ከሁለት ሺ ከብቶች በላይም በመርዙ አለቁ። በቅሎዎች፣ ላሞች፣ በጎችና የጫካው ዱር አራዊት ሁሉ እየሸሹ ወደ ሸለቆው እየሮጡ ገደል ገቡ። ለ ማርሴል ግሪዮል በወቅቱ ከሰጡት ቃለ መጠይቅ (ላቀች አክሊሉ ተርጉመው "የንጉሠ ነገሥቱ ትዝታዎች" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ ገጽ 66/68) ። ንጉሠ

ነገሥቱ "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" ላይ የመርዙ ዓይነት ቀደም ብሎ በየትኛውም ጦርነት ሥራ ላይ ያልዋለ እንደሆነ ገልጸዋል።


**አባሪ 3፣** ንጉሠ ነገሥቱ ባለመማረካቸው የጣሊያን አሸናፊነት እንደማይረጋገጥ




HITCH IN THE ROMAN TRIUMPH. (Copyright in All Cou

በዚህ "የሙሶሎኒ የድል አድራጊነት ሕጸጽ" በሚለው ካርቱን ሰር ዴቪድ ሎው የሙሶሎኒን የድል አድራጊነት ተጨባጭ አለመሆን ያሳያል። በጥንት ሮማውያን ባሕል፣ ድል አድራጊ ሠራዊት በጦርነት የሞቱ መሪዎችና የተማረኩ መሪዎች በጨፋሪው ድል አድራጊ ሕዝብ መሃከል በሠረገላ ይጎተታሉ። በዚህ ካርቱን ሰንሰለቱ ሰው ስላልታሰረበት፣ ሠረገላ ነጂው "ምርኮኞቹ ዘገዩ" ይላል። ንጉሠ

**አባሪ 4፣** ጣሊያኖችን ለምን ሁልጊዜም ከበባ ውስጥ እንደሚገቡ የሚያሳይ ከአንድ አርበኛ የተጻፈ ደብዳቤ



ከዚህ በላይ ባለው ደብዳቤ፣ ሃይሌ ባልቻ፣ ስለአርጋው ጉዳይ ከጻፈ በኋላ፣ ከራስ አበበ የተላከውን መልዕክት ለልጅ ከፈለውም ያካፍላል። "ራስ አበበ ደብረ ብርሃን ያለው የኢጣሊያ ወታደር በሙሉ ወደኛ ዘምቷልና እናንተም በምሽጉ አቅራቢያ እንድትሰሙት፣ ባቅራቢያህ ላለው በኔ ቃል ንገር። በያላችሁበት ጠንክሩ ብለው ስለጻፉልኝ፣ እንድትሰማው ብዬ ነው።" በማለት ግንቦት 17 ቀን 1930 ጻፈ።


የአርበኛው ጦር በሁሉም አካባቢ የሚገኝ ስለሆነ፣ በጽሑፍ ታዞም፣ በአጋጣሚም፣ በጩኸትም፣ በመሰባሰብ፣ የጣሊያንን ጦር ሁልጊዜም ክብ ውስጥ ያስገባዋል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ከበባዎች ሲጠቀሱ ልቦለድ ሳይሆን በእርግጠኛ የጦር ውሎ ታሪኮች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።


አባሪ 5፣ በራስ አበበና በልጅ ከፈለው መሃከል ስለተፈጠረው አለመግባባት ደጃዝማች አውራሪስ የጻፉት ደብዳቤ ትክክለኛ ግልባጭ

"ይድረስ ከልጅ ከፈለው። ወንድሜ እንደምን ሰንብተሃል። ለጤናህ አይደለህሞይ። የላከው ደብዳቤ ደረሰኝ። ሕመምህስ እንዴት ነው' እግዚዘአብሔር ይማርህ። ነገር ግን ከነራስ አበበ ጋር አንድነት ለጧት ለማታ እየተገናኘህ የምትቀመጥ መስሎኝ ነበር። በኋላ ግን ወደ ኋላህ እየራቅህ መሆንህን ብሰማ ወደነራስ አበበ ወረቀት ጽፈ ላክሁ። ለኢጣሊያ ዋና ረዳት የሆነው ግራዝማች መንገሻን የያዘ፣ ገድሌን ያጠፋ፣ ብላታ ተስፋዬን ከአገሩ ነቅሎ የሰደደ እሱ አይደለሞይ። ባንዲራችን በቆመ ጊዜ መዠመሪያ ዋና ክብረት የሚያገኝ አይደለሞይ። እሱን ማቅረብ ነው እንጂ ማራቅ አይገባም ብዬ ጽፌ ነበር። እነሱም መልሱን እኛ ምንም አላልነው። እሱ እንዲያው ወደ ኋላው ይርቅ ዠመር። እንጂ ብለው አስታወቁኝ። ምንም ቢሆን ያንድ ወንዝ ልጅ ወንድማማች የሆነ አንድነት መተባበር ቀርቶ በክፉ ቀን እኔ እናንተን ታጋለጥሁ እናንተ እኔን ታጋለጣችሁማ የት ይሆናል። አሁንም እኔ ሃሳቤ አንድነት የመተባበራችንን ብቻ ነውና የሥራችንን ሁሉ አንድነት ሆነን መምከር ነው። ዛሬማ ጠላታችንም ሌላ ባላጋራ የተነሳበትና በጣም የተጠጋ ይመስለኛል፣ እግዚአብሔር ወደ እኛ ሆኗል እርዳታው። እኔ ግን ወደ እነራስ አበበ የጻፍኩትም ቃል ፊታውራሪ ዳምጠው በድሎኛል የሚለው ይኽን ደም የተቃባበትን አገር አልወሰድሁ ብሎ ነው እንጂ ሌላ በደል የለውም። እኔ አውቃለሁ ብረቴንም ወሰደብኝ የሚለው ያልጋወራሽ አሽከሮች ከነወንዳፈረው ጋር አብረው በከበሬታ የተቀመጡ ነበሩ። እንሱን ነው። እነሱም ቢሆኑ እወደዱበት ቦታ የሚቀመጡ ናቸው እንጂ አሽከሮቹ አይደሉ። እውነት እኔ የማላውቀው የቀኛዝማች ተገኝን ብቻ ነው። የሱንም ቢሆን በደልና በደላቸውን አይተን ማስማማትና አንድነት መሥራት ነው ብዬ እንደዚህ ጻፍኩላቸው። እነሱም እኛ የምንፈልገው አንድነት ሆነን መሥራትን ነው እንጂ ሌላ ሃሳብ የለንም ብለው ደህና አድርገው ጽፈው አስታውቀውኛል። አሁንም አንድነት ሆነን መሥራት ብቻ ነው። ደግሞ አንድነት ሆኖ ለመሥራት ቅር የሚልህ የሚያውክህ ነገር እንዳለ እንደዚህ የሚቸግረኝ ነገር አለ ብለህ አስታውቀኝ። በዚህ ቢሆን እንደዚህ እናደርገዋለን ብለን አስበን እናደርገዋለን ምክር አድርገን።

*ታህሣስ 14 ቀን 1931 ዓም*


**አባሪ 6፣** በልጅ ከፈለውና በራስ አበበ መካከል ስለተፈጠረው አለመግባባት በትረካው ውስጥ የተጠቀሱት ልጅ ግዛቸው ኃይሌ የጻፋቸው ሁለት ደብዳቤዎች። ብዙዎቹ ትዕይንቶች ከዚህ ዓይነት ጥናትና ቃለ መጠይቆች ላይ የተመሠረቱ መሆኑን ለማሳዬት የቀረበ ናሙና።






ልጅ ግዛቸው ኃይሌ "አሁንም ማንም ሰው ቢሆን ባንተ የምለውጠው ሰው እንደሌለ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስወድህም በገሃድ ነው እንጂ የስውር ፍቅር አይደለም" ሲል ታሕሣስ 27 ቀን 1931 ለልጅ ከፈለው የጻፈውና በዚህ ትረካ የተጠቀሰው ደብዳቤ።


**አባሪ 7፣** ግዛቸው ኃይሌ፣ ባላምባራስ በሻህ ኃይሌ የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች። አሽከር የሚለው ቃል ወታደር የሚለውን ያመለክታል። በሌላ አገር አማርኛ ልጅ ማለትም ይሆናል።



**አባሪ 8፤** በአርበኞች የተያዙ ነጻ ክልሎች አስተዳደር ምሳሌ የሚሆኑ ደብዳቤዎች



በዚህ ሐምሌ 30 ቀን 1930 በተጻፈ ደብዳቤ ሥዩም ዋለሉ በዘመኑ አማርኛ አርበኛ መሆኑ እንደሚያኮራው ገልጾ ልጅ ከፈለው ለቅጣት እንዲወረስ ያደረገበት መሳሪያ እንዲመለስለት ደጅ ይጠናል።




በማናቸውም ምክንያት ለጩኸት የመጣ ሰው የሚቀበለው ቀላጤ ፡፡


ይድረስ ከ [illegible]

የከፈልው ገንዘብ [illegible] ሩብ ተቀብያለሁ ፡፡


ግዛቸው ኃይሌ ከሞተ በኋላ፣ ግዛቸው ሲያያስተዳድረው የነበረው ክልል ያገር ሌባና ያገር ወታደር እንዳይዘርፈው ልጅ ከፈለው ለጻፈው ደብዳቤ የተሰጠ መልስ ነው። ፀሐፊው በልጅ ግዛቸው እጅ በነበረው አገር እነሱም ችግሯቸው እህሉን እንዳነሱበትና የተውለትን ሌላ እንዳይዘርፈው ጠባቂ አድርገንበታል ብሎ በንቀት ይመልሳል።ከፈለው ታላቁ ጀግና፣ ሁሉንም አደላድሎ፣ ደጋፊዎቹ አርሰው በሰላም እንዲኖሩ ተንከባክቦ፣ ለጠላት ያደሩትን መሬታቸውን ነቅሎ፣ በጦርነት ድል አድርጎ፣ ነጻ ክልሉን አስፋፍቶ፣ በቀድሞ ሹማምንት፣ እንዲሁም 'በተራው ሕዝብ'፣ ተከብሮ፣ ተፈርቶ፣ የኖረ ጀግና ነበር።


ይድረስ ፡ ለ


በዚህ መስከረም 15 ቀን 1931 በተጻፈ ደብዳቤ ወይዘሮ ሙሉወርቅ ተስፋዬ የምትባል በነጻው ክልል እያሳረሰች እንድትኖር ተፈቅዶላት ከክልሉ ስለሄደች መሬቱም ንብረቱዋም ስለተወሰደባት እንዲመለስላት ሌላ አርበኛ ለልጅ ከፈለው የጻፈው አማላጅነት ነው።



በዚህ ግንቦት 13 ቀን 1930 በተጻፈ ደብዳቤ ቀኛዝማች ሃይሌ ባልቻ አርጋው በነበሩ በቀድሞ ሹማምንት ላይ ጊዜ ሰጠኝ ብሎ ግፍ ይፈጽማል ብለው የጻፉ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ልጅ ከፈለው በሚለው ከአርጋው ጋር ለመታረቅ ዝግጁ መሆናቸውን ይገልጻሉ። ቀኛዝማች ሃይሌ እንደ ደጃዝማች አውራሪስ ሁሉ በደብዳቤዎቻቸው ስለ አገር ፍቅርና ጠላትን ተባብሮ ስለማጥቃት አስፈላጊነት ይመክራሉ።




የመስከረም 30 ቀን 1930 የባላምባራስ በሻህ ኃይሌ ደብዳቤ ለልጅ መኩሪያ ። የልጅ ከፈለው አሽከሮች (ወታደሮች) ከድተው ባላምባራስ በሻህ ኃይሌ ዘንድ ገብተዋል ስለተባለ ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ባስተባባሪነቱ ለጻፈው ደብዳቤ በሻህ ኃይሌ ለልጅ መኩሪያ (ለከፈለው መልዕክተኛ) ከሱ ዘንድ እንደሌሉና "አንተስ እዚያ ሆነህ ከምትጠይቅ መጥተህ አታያቸውም ነበሮይ'' ብሎ የጻፈው።



በዚህ መጋቢት 1930 በአቶ ተፈራ ጠገናው በተጻፈ ደብዳቤ መሠረት ባላምባራስ አበበ አረጋይ ራስ አበበ አልተባሉም። በ1931 ጀምሮ በተጻፉ ደብዳቤዎች ራስ ተብለው ይጠራሉ። ደብዳቤው እንዲህ ይላል፤

“ይድረስ ለክቡር ጌታዬ ከልጅ ከፈለኝ። እንደምን ሰንብተዋል። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ክቡር ጌታዬ ሆይ የጌታዬ የባላምባራስ አበበ ቃል ስለመጣብኝና እንግዳ ለመቀበል ሄጄ እርሰዎም በዚህ በኩል ሲያልፉ ሳልገናኝዎ መቅረቴ በጣም ቅር አለኝ። አሁንም ጌታዬ ሆይ ፈረንጁ በቀደም ለታ ስላለቀው ሰው በጣም አድርጎ ደስ አለውና አጨበጨበ። አሁንም ነገሩ እርሶ እርቅ አድርገው ወንድሞቻችንም እንዲታረቁልን እጫማዎ ወድቀን እንለምንዎታለን። ከእርሰዎ



Mobali, 28 Febbraio 938
Il R. Residente

በዚህ ደብዳቤ ላይ ስምን ሳይጨምሩ በማዕረግ ስም ብቻ፣ ቲሊንቲ፣ ብሎ አጠቃቀስን ይመልከቱ። ትረካውም ላይ የምርኮኛው ስም ቲሊንቲ የተባለበት በዚህ ዓይነት መረጃዎች ምክንያት ነው።

**አባሪ 9፣ ንጉሠ ነገሥቱ በላመማረካቸው ወይም ባለመሞታቸው የሙሶሎኒ ድል ሕጸጽ መሆናቸውን የሚያሳዩ ካርቱኖች ከሰር ዴቪድ ሎው**




ይህ የሰር ዴቪድ ሎው ካርቱን ሙሶሎኒ እየጋለበ ከመጣው ፈረስ ላይ ሆኖ የዓለም መንግሥታት አባላት አገሮችን ለማግባባት የሚያደርገውን ሙከራ ለማሳዬት የተሳለ ነው። ሙሶሊኒ እንዲህ ይላል "ኢጣሊያ ፍትሕን ታውቃለች። እናንተ ኃይለ ሥላሴን ሸጡልኝ፣ እኔም ፍራንኮን (የስፔኑን) እሸጥላችሃለሁ።እሺ?"





የሙሶሎኒ ቅዠት ካርቱን። ሙሶሎኒ ተኝቶ ሲቃዥ ንጉሠ ነገሥቱ ብቅ ብለውበት ሲደነግጥ ይታያል።

**አባሪ 10፤** የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር የመጀመሪያ ስብሰባ የተደረገበት ሥፍራ



ፎቶ ግራፍ በዘነበች አየለ

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር የመጀመሪያው ስብሰባ የተደረገበት ዛፍ በአንቀላፊኝ። የወደቀው ዛፍና ሊሠራ የታቀደው ሃውልት መሠረት ይታያሉ። የማህበሩ ምሥረታ ሳሲት ከነበረው የኢጣሊያ ካምፕ በጣም ቅርብ በሆነ ቦታ መሆኑን አስተውሉ።



## ስለደራሲው በጥቂቱ

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. አዳባይ (**ልብወለድ**)
2. ፍትሕ እና ርትዕ (**ልብወለድ**)
3. Trying Times (**ልብወለድ**)
4. የመጭው ዘመን ቴክኖሎጂና ኑሮ (**ትምህርት**)
5. ኢፔሪያሊዝም (**ፖለቲካ**)
6. የኢትዮጵያና የጣልያን ሁለተኛው ጦርነት ታሪክ (**ታሪክ**)